IslamHouse.com | جمعية الدعوة وتوعية الجاليات بالربوة | جمعية خدمة المحتوى الإسلامي باللغات

# ሙንተቃ ከነቢያዊ ሓዲሦች ኢንሳይክሎፒዲያ የተውጣጣ ጥንቅር

## المنتقى من موسوعة الأحاديث النبوية

أمهري

አማርኛ




HadeethEnc.com

# المنتقى من موسوعة الأحاديث النبوية

اللغة الأمهرية

## إعداد القسم العلمي

جمعية خدمة المحتوى الإسلامي باللغات

جمعية الدعوة وتوعية الجاليات بالربوة

ح جمعية خدمة المحتوى الإسلامي باللغات ، ١٤٤٦ هـ

جمعية خدمة المحتوى الإسلامي

المنتقى من موسوعة الأحاديث النبوية - أمهري. / جمعية خدمة المحتوى الإسلامي - ط١ . .-الرياض ، ١٤٤٦هـ

٤٩١ ص ؛ ١٤ × ٢١ سم

ردمك: ٩٧٨-٦٠٣-٨٤٧٤-٣٣-٤

٦١٨٢ /١٤٤٦

شركاء التنفيذ :

دار الإسلام | بيان الإسلام | رواد التراجم | المحتوى الإسلامي

يتاح طباعة هذا الإصدار ونشره بأي وسيلة مع الالتزام بالإشارة إلى المصدر وعدم التغيير في النص

Tel : +966 50 244 7000
info@islamiccontent.org
Riyadh 13245-2836
www.islamiccontent.org

بسم الله الرحمن الرحيم

# በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በኾነው እጀምራለሁ

## መቅድም

ምስጋና ባጠቃላይ ለአለማት ጌታ ለአሏህ የተገባ ነው። የአሏህ ውዳሴና ሰላም በነቢያችን ሙሐመድ በቤተሰቦቻቸውና በባልደረቦቻቸው እንዲሁም እስከ እለተ ትንሳኤ ድረስ በተከተላቸው ላይ ሁሉ ይስፈን። በመቀጠል:

አንድ ሙስሊም ከቁርአን ቀጥሎ በማንበቡም፣ በመማሩም፣ በማስተንተኑ በኩልም፣ በመተግበሩ ረገድም ትልቁን ትኩረት ሊቸረው የሚገባው ጉዳይ ቢኖር የረሱል - ሶለሏሁ ዓለይሂ ወሰለም (የአሏህ ሶለዋትና ሰላም በሳቸው ላይ ይስፈንና) - ሱናቸውን ነው።

ነቢዩ (ሶለሏሁ ዓለይሂ ወሰለም) የአሏህ ውዳሴና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና እንዲህ ብለዋል:

«ሰዎች ሆይ! አጥብቃችሁ ብትይዙት መቼም የማትጠሙበት የሆነን ነገር በመካከላችሁ ትቼላችኋለሁ: ይኸውም የአሏህ ኪታብ እና የነቢዩ ሱና ነው።»

ኢማም ማሊክ ዘግበውታል።

የላቀው አሏህ እንዲህ ብሏል:

{መልክተኛውም የሰጣችሁን (ማንኛውንም) ነገር ያዙት። ከእርሱም የከለከላችሁን ነገር ተከልከሉ።} [አል-ሐሽር: 7]

ለዛም ሲባል የኢስላማዊ ይዘቶች በቋንቋዎች አግልግሎት ማህበር እና፣ በረብዋ የዳዕዋና ኮሚኒቲ ግንዛቤ ማስጨበጥ ማህበር  ነቢያዊ ሓዲሦችን በኢንሳይክሎፒዲያ መልክ አጠናቅሮ በተለያዩ ቋንቋዎች የመተርጎም እቅድን ሰነቁ።

የላቀው አላህ አግርቶት ሙስሊሙ በዲኑም በዱኒያውም ጉዳይ የሚያስፈልገውን የሓዲሦች ክምችት አጠር ካለ ማብራርያ፣ ሀሳብና ጥቆማዎች እንዲሁም በውስጡ የያዛቸውን ፍሬ ሀሳቦች ከመግለፅ ጋር ተጠናቅሯል። ተከታዩን ስያሜ በያዘ መጽሃፍ ተዘጋጅቶ ወጥቷል:

«ሙንተቃ (ከነቢያዊ ሓዲሦች ኢንሳይክሎፒዲያ የተውጣጣ ጥንቅር)»

መላው አለም በይዘቱ ተጠቃሚ ይሆን ዘንድ እና የአላህ መልክተኛ ሶለሏሁ ዓለይሂ ወሰለም ሱና በየቋንቋቸው ሊደርሳቸው ዘንድ ስራው በዓለም ታላላቅ የቋንቋዎች በመተርጎም ላይ ነው።

አላህን ይህንኑ መልካም ስራ እንዲቀበለን፣ ስራውንም የተባረከና ለርሱ ተብሎ የተሰራ እንዲያደርገው፤ በዝግጅቱም፣ በትርጉሙም ይሁን በስርጭቱም ላይ የተሳተፈውን ሁሉ መልካም ምንዳ ይመነዳው ዘንድ እንማፀነዋለን።

የአሏህ ውዳሴና ሰላም በነቢያችን ሙሐመድ ላይ ይስፈን

(١) - عن عمر بن الخطاب رضي الله عنه قال: قال رسول الله صلى الله عليه وسلم: «إِنَّمَا الْأَعْمَالُ بِالنِّيَّةِ، وَإِنَّمَا لِامْرِئٍ مَا نَوَى، فَمَنْ كَانَتْ هِجْرَتُهُ إِلَى اللهِ وَرَسُولِهِ، فَهِجْرَتُهُ إِلَى اللهِ وَرَسُولِهِ، وَمَنْ كَانَتْ هِجْرَتُهُ لِدُنْيَا يُصِيبُهَا أَوِ امْرَأَةٍ يَتَزَوَّجُهَا، فَهِجْرَتُهُ إِلَى مَا هَاجَرَ إِلَيْهِ».

وفي لفظ للبخاري: «إِنَّمَا الْأَعْمَالُ بِالنِّيَّاتِ، وَإِنَّمَا لِكُلِّ امْرِئٍ مَا نَوَى». [صحيح] - [متفق عليه]

(1) - ከዑመር ቢን አልኸጧብ -አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: የአላህ መልክተኛ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንዲህ ብለዋል፡- "ስራዎች የሚለኩት በኒያ (በሀሳብ) ብቻ ነው። ሰውየው የሚያገኘው ያሰበውን ነው። ስደቱ ወደ አላህና መልክተኛው የሆነ ሰው የስደቱ (ምንዳም) ወደ አላህና መልክተኛው ነው። ስደቱ ለዱንያ ጥቅማጥቅም ለማግኘት ወይም ሴትን ለማግባት የሆነ ሰው የስደቱ (ምንዳ) ወደ ተሰደደበት ነገር ወደዛው ነው። " በቡኻሪ ዘገባ ደግሞ፡- "ስራዎች የሚለኩት በኒያዎች (በሀሳብ) ብቻ ነው። ሁሉም ሰው የሚያገኘው ያሰበውን ነው።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ሁሉም ስራዎች ግምት የሚሰጣቸው በኒያ እንደሆነ አብራሩ። ይህ ብይን በአምልኳዊም ጉዳይ ሆነ ከሰው ጋር ባሉ መስተጋብሮች ሁሉንም ስራዎች የሚያጠቃልል ነው። በስራው የሆነን ጥቅም ያሰበ ሰው ከዛች ጥቅም በስተቀር ሌላ አያገኝም። ምንዳም የለውም። በስራው ወደ አላህ መቃረብን ያሰበ ሰው ደግሞ እንደ መብላትና መጠጣት የመሰሉ ተለምዷዊ ስራ ቢሆንም እንኳ ሰርቶ በስራው ምንዳና አጅርን ያገኛል።

ቀጥለውም ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ስራዎች በውጫዊ ይዘታቸው ሲታዩ ተመሳሳይ ከመሆናቸውም ጋር ኒያ በስራዎች ላይ የሚያሳድረውን ተፅእኖ ለማብራራት ምሳሌ ጠቀሱ። በስደቱና ሀገሩን በመተዉ የአላህን ውዴታ ማግኘትን ያሰበ ስደቱ ሸሪዐዊና ተቀባይነት ያለው ስደት ነው። ኒያው እውነተኛ ስለሆነም ይመነዳበታል። በስደቱ ግን እንደ ገንዘብ፣ ክብር፣ ንግድና ሚስት የመሳሰሉ ዓለማዊ ጥቅም የፈለገ ሰው ከስደቱ ይህችን ያሰባትን ጥቅም

በስተቀር ሌላ አያገኝም። ከምንዳና አጅርም ምንም እጣ ፈንታ እንደሌለው ገለፁ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. በኢኽላስ ላይ መበረታታቱ ፤ አላህ የሱ ፊት ተፈልጎበት የተሰራን ስራ ካልሆነ በስተቀር ምንም ስራ አይቀበልምና።
2. አንድ ሸሪዓዊ ብይኖች የሚመለከቱት ዕድሜ ክልል ላይ የደረሰ ሰው ወደ አላህ የሚቃረብበትን ስራ በተለምዷዊ እሳቤ ቢሰራው በስራው ወደ አላህ መቃረብን እስኪያስብ ድረስ በሷ አማካኝነት ምንም ምንዳ አይኖረውም።

(4560)

(٢) - عَنْ عَائِشَةَ رضي الله عنها قَالَتْ: قَالَ رَسُولُ اللهِ صلى الله عليه وسلم: «مَنْ أَحْدَثَ فِي أَمْرِنَا هَذَا مَا لَيْسَ فِيهِ فَهُوَ رَدٌّ» متفق عليه.

ولمسلم: «مَنْ عَمِلَ عَمَلًا لَيْسَ عَلَيْهِ أَمْرُنَا فَهُوَ رَدٌّ». [صحيح] - [متفق عليه]

(2) - ከእናታችን ዓኢሻ (ረዲየሏሁ ዐንሃ) - አላህ መልካም ሥራዋን ይውደድላትና - እንደተላለፈው እንዲህ ብላለች: "የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል: ‹በዚህ በመመሪያችን ውስጥ ከርሱ (ከትእዛዛችን) የሌለን አዲስ ነገር የፈጠረ ሰው እርሱ (የፈጠረው አዲስ ነገር) ተመላሽ ነው።›" ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል። በሙስሊም ዘገባ "ትእዛዛችን የሌለበትን ስራ የሰራ ሰው እርሱ (ሥራው) ተመላሽ ነው።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

በሃይማኖት ውስጥ አዲስ ነገር የፈጠረ ወይም ቁርአናዊና ሐዲሣዊ ማስረጃ ያልጠቆሙትን ስራ የሰራ ሰው በባለቤቱ ላይ ተመላሽ እንደሚሆንና አላህ ዘንድም ተቀባይነት እንደማይኖረው ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ገለፁ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. አምልኮ የተመሰረተው በቁርአንና ሐዲሥ ላይ በመጣው ላይ ስለሆነ አላህን የምናመልከው በደነገገው ድንጋጌ መሰረት እንጂ በተፈጠሩና በተፈበረኩ አምልኮዎች አይደለም።
2. የኢስላም ሃይማኖት ተግባራዊነት በግላዊ ምልከታና አንድን ነገር መልካም አድርጎ በማየት ሳይሆን መልክተኛውን (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) በመከተል ነው።
3. ይህ ሐዲሥ የኢስላምን ምሉእነት የሚጠቁም ነው።
4. ቢድዓ (መጤ) ማለት: በነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ዘመንና በሶሐቦች ዘመን ያልነበረ ሁሉም በሃይማኖት ውስጥ የተፈጠረ እምነታዊ ጉዳይ ወይም ንግግር ወይም ተግባር ነው።
5. ይህ ሐዲሥ ከኢስላም መሰረቶች መካከል አንድ መሰረት የሆነና ለተግባራቱም እንደሚዛን የሆነ ሐዲሥ ነው። የትኛውም የአላህ ፊት ያልተፈለገበት ስራ ባለቤቱ በስራው ምንዳ እንደማያገኝበት ሁሉ ልክ እንደዚሁ መልክተኛው (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ይዘው የመጡትን ያልገጠመ የትኛውም ስራም በባለቤቱ ላይ ተመላሽ ይሆናል።
6. የተከለከለው አዲስ ፈጠራ ሃይማኖታዊ ጉዳይ ላይ ነው እንጂ አለማዊ ጉዳይ ላይ አይደለም።

(4792)

(٣) - عن عمر بن الخطاب رضي الله عنه قال: بَيْنَمَا نَحْنُ عِنْدَ رَسُولِ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ ذَاتَ يَوْمٍ إِذْ طَلَعَ عَلَيْنَا رَجُلٌ شَدِيدُ بَيَاضِ الثِّيَابِ، شَدِيدُ سَوَادِ الشَّعَرِ، لَا يُرَى عَلَيْهِ أَثَرُ السَّفَرِ، وَلَا يَعْرِفُهُ مِنَّا أَحَدٌ، حَتَّى جَلَسَ إِلَى النَّبِيِّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ، فَأَسْنَدَ رُكْبَتَيْهِ إِلَى رُكْبَتَيْهِ، وَوَضَعَ كَفَّيْهِ عَلَى فَخِذَيْهِ، وَقَالَ: يَا مُحَمَّدُ، أَخْبِرْنِي عَنِ الْإِسْلَامِ، فَقَالَ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ: «الْإِسْلَامُ أَنْ تَشْهَدَ أَنْ لَا إِلَهَ إِلَّا اللهُ، وَأَنَّ مُحَمَّدًا رَسُولُ اللهِ، وَتُقِيمَ الصَّلَاةَ، وَتُؤْتِيَ الزَّكَاةَ، وَتَصُومَ رَمَضَانَ، وَتَحُجَّ الْبَيْتَ إِنِ اسْتَطَعْتَ إِلَيْهِ سَبِيلًا» قَالَ: صَدَقْتَ، قَالَ: فَعَجِبْنَا لَهُ، يَسْأَلُهُ وَيُصَدِّقُهُ، قَالَ: فَأَخْبِرْنِي عَنِ الْإِيمَانِ، قَالَ: «أَنْ تُؤْمِنَ بِاللهِ، وَمَلَائِكَتِهِ، وَكُتُبِهِ، وَرُسُلِهِ، وَالْيَوْمِ الْآخِرِ، وَتُؤْمِنَ بِالْقَدَرِ خَيْرِهِ وَشَرِّهِ» قَالَ: صَدَقْتَ، قَالَ: فَأَخْبِرْنِي عَنِ الْإِحْسَانِ، قَالَ: «أَنْ تَعْبُدَ اللهَ كَأَنَّكَ تَرَاهُ، فَإِنْ لَمْ تَكُنْ تَرَاهُ فَإِنَّهُ يَرَاكَ» قَالَ: فَأَخْبِرْنِي عَنِ السَّاعَةِ، قَالَ: «مَا الْمَسْؤُولُ عَنْهَا بِأَعْلَمَ مِنَ السَّائِلِ» قَالَ: فَأَخْبِرْنِي عَنْ أَمَارَتِهَا، قَالَ: «أَنْ تَلِدَ الْأَمَةُ رَبَّتَهَا، وَأَنْ تَرَى الْحُفَاةَ الْعُرَاةَ الْعَالَةَ رِعَاءَ الشَّاءِ يَتَطَاوَلُونَ فِي الْبُنْيَانِ» قَالَ: ثُمَّ انْطَلَقَ، فَلَبِثْتُ مَلِيًّا ثُمَّ قَالَ لِي: «يَا عُمَرُ، أَتَدْرِي مَنِ السَّائِلُ؟» قُلْتُ: اللهُ وَرَسُولُهُ أَعْلَمُ، قَالَ: «فَإِنَّهُ جِبْرِيلُ، أَتَاكُمْ يُعَلِّمُكُمْ دِينَكُمْ». [صحيح] - [رواه مسلم]

(3) - ከዑመር ቢን አልኸጧብ -አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ፦ ከዕለታት አንድ ቀን የአላህ መልክተኛ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ዘንድ ሳለን ድንገት ልብሱ እጅግ በጣም ነጭ የሆነ፤ ፀጉሩ ደግሞ እጅግ በጣም ጥቁር የሆነ ሰውዬ ብቅ አለ። በሱ ላይ የጉዞ ምልክት አይታይበትም፤ ከኛ ውስጥም አንድም የሚያውቀው ሰው የለም፤ ወደ ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ዘንድ መጥቶ ተቀመጠ። ጉልበቱን ወደ ጉልበታቸው አስጠጋ፤ መዳፎቹንም በታፋዎቹ ላይ አደረገና "ሙሐመድ ሆይ! ስለ ኢስላም ንገረኝ!" አላቸው። የአላህ መልዕክተኛም ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም "ኢስላም ማለት ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ አምላክ እንደሌለና ሙሐመድም የአላህ መልክተኛ መሆናቸውን ልትመሰክር፣ ሰላት ደንብና ስርዓቱን ጠብቀህ ልትሰግድ፣ ዘካን ልትሰጥ ፣ ረመዷንን ልትፆምና ወደርሱ መንገድን ከቻልክም የአላህን ቤት ልትጎበኝ ሐጅ ልታደርግ ነው።" አሉት። እሱም "እውነት አልክ!" አላቸው። "በሱ ተገረምን ይጠይቃቸዋልም (ጥያቄውን በትክክል እንደመለሱ)

ያረጋግጥላቸዋልም።" ከዚያም፦ "ስለኢማን ንገሩኝ!" አላቸው። እሳቸውም "በአላህ፣ በመላእክቱ፣ በመጻሕፍቱ፣ በመልክተኞቹ፣ በመጨረሻው ቀንና በጥሩውም ሆነ መጥፎ ውሳኔዎቹም ልታምን ነው።" አሉት። እሱም "እውነት አልክ!" አላቸው። "ስለኢሕሳን (በጎ መስራት) ንገሩኝ!" አላቸው። እሳቸውም "አላህን ልክ እንደምታየው ሆነህ ልትገዛው ነው። አንተ ባታየው እንኳ እርሱ ያይሀልና።" አሉት። "ስለ ሰዓቱ (ቂያማ) ንገረኝ!" አላቸው። እሳቸውም "ስለርሷ ተጠያቂው ከጠያቂው የበለጠ አዋቂ አይደለም።" አሉት። "ስለ ምልክቶቿ ይንገሩኝ!" አለ። እሳቸውም "ባሪያ ጌታዋን ልትወልድ ነው ፤ ያልተጫማ፣ የታረዘ፣ ድሃና የፍየል እረኛ የሆኑ ሰዎች ለህንፃዎች ሲሽቀዳደሙ ማየትህ ነው።" አሉት። ዑመር እንዲህ አለ "ከዚያም ሄደ። የተወሰነ ጊዜ ቆየሁ። ከዚያም ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም "ዑመር ሆይ! ጠያቂው ማን እንደነበር አውቀሀልን?" አሉኝ። እኔም "አላህና መልክተኛው ያውቃሉ።" አልኳቸው። እሳቸውም "እርሱ ጂብሪል ነው እምነታችሁን ሊያሳውቃችሁ መጥቷችሁ ነው። " አሉ። [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ዑመር ቢን አልኸጧብ -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- ከዕለታት አንድ ቀን ጂብሪል ዐለይሂ ሰላም በሶሐቦች መካከል አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና በማይታወቅ ሰው ተመስሎ እንደወጣ ይናገራሉ። ከዚህም ሰውዬ ባህሪ ልብሱ እጅግ የነጣ፣ ፀጉሩም እጅግ የጠቆረ ነበር። በሱ ላይም ድካም፣ አቧራ፣ የፀጉር መንጨባረርና የልብስ መቆሸሽ የመሰሉ የጉዞ ምልክት አይታይበትም። ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ዘንድ ተቀምጠው ከነበሩ ታዳሚዎች መካከልም አንድም ሰው አላወቀውም። ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ፊት እንደተማሪ አቀማመጥ ተቀመጠ። ስለ ኢስላምም ጠየቃቸው። እሳቸውም በሁለቱ የምስክር ቃላት ማረጋገጥን፣ አምስቱ ሶላቶች ላይ መጠባበቅን፣ ለሚገባው ሰው ዘካ መስጠትን፣ የረመዷን ወር መፃምን፣

በቻለ ላይ ግዴታ የሆነውን ሐጅ መፈፀምን ያካተተውን እነዚህን ማዕዘናት በመጥቀስ መለሱለት።

ጠያቂውም "እውነት አልክ!" አለ። ሶሐቦችም ከላይ ሲታይ አጠያየቁ አለማወቁን የሚጠቁም፤ ከዛ ደግሞ ትክክለኛ መልስ እንደተመለሰለት ማረጋገጡን በማስተዋላቸው ግራ ተጋቡ።

ከዚያም ስለ ኢማን ጠየቃቸው። እሳቸውም እነዚህን ስድስት ማዕዘናት ማመንን የሰበሰበ መልስ መለሱለት። እነሱም:-አላህ በመኖሩ፣ በባህሪያቶቹ፣ መፍጠርን በመሰሉ ድርጊቶቹና በአምልኮም ብቸኛ መሆኑን ማመን፤ አላህ ከብርሃን የፈጠራቸው መላእክቶች የተከበሩ ባሮቹ መሆናቸውን፣ አላህን የማያምፁና በትእዛዙ የሚተገብሩ መሆናቸውን ማመን፤ እንደ ቁርኣን፣ ተውራት፣ ኢንጂልና ሌሎችም ከአላህ ዘንድ በመልክተኞች ላይ በወረዱ መጽሐፍት ማመን፤ የአላህን ሃይማኖት የሚያደርሱ በሆኑ መልክተኞች ማመን ከነሱም መካከል ኑሕ፣ ኢብራሂም፣ ሙሳ፣ ዒሳና የመጨረሻቸው የሆኑት ሙሐመድ ሰለላሁ ዐለይሂም ወሰለምና ሌሎችም ነቢያቶችና መልክተኞች ይጠቀሳሉ። በመጨረሻው ቀን ማመን፤ እዚህ ምውስጥም ከሞት በኋላ ያሉ በቀብርና በበርዘኽ ህይወት እንዲሁም የሰው ልጅ ከሞት በኋላ የሚቀሰቀስና የሚተሳሰብ መመለሻውም ወይ ወደ ጀነት ወይ ወደ እሳት መሆኑን ማመንንም ያካትታል። አላህ በቀደመ ዕውቀቱ መሰረት፣ ጥበቡ ባስፈረደው መልኩ በፍላጎቱ መሰረት ነገሮችን እንደወሰነና በጽሑፍም እንዳሰፈረ ማመን፤ ምድር ላይ የሚከሰቱትም በወሰናትና በፈጠራት ልክ መሆኑንም ማመን ነው። ከዚያም ስለ ኢሕሳን (ስራን ማሳመር) ጠየቃቸው። ኢሕሳን ማለት ልክ አላህን እያዩ እንደሆነ እያሰቡ አላህን መገዛት ነው። እዚህ ደረጃ ላይ መድረስ ባይረጋገጥለት (ባይችል) እንኳ ልክ አላህ እርሱን እያየው እንደሆነ በማሰብ አላህን መገዛት ነው። የመጀመሪያው: የ "ሙሻሀዳህ" (አሏህን እያየህ እንደሆነ እያሰብክ የምታመልክበት) ደረጃ ነው እሱም የላቀ ደረጃ ነው። ሁለተኛው ደግሞ የ "ሙራቀባህ" (አሏህ እያየኝ ነው በሚል ሃሳብ የምታመልክበት) ደረጃ ነው።

ከዚያም ሰዓቲቱ መቼ እንደሆነች ጠየቃቸው። ነቢዩም ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም የሰዓቲቱ መከሰቻ ጊዜ አላህ በእውቀቱ ብቸኛ ከሆነበት ጉዳይ አንዱ በመሆኑ ተጠያቂውም ይሁን ጠያቂው ከፍጥረቱ መካከልም አንድም እንደማያውቀው ገለፁ።

ከዚያም ስለ ሰዓቲቱ ምልክቶች ጠየቃቸው። ከምልክቶቿ መካከል የጭን ገረዶችና ልጆቻቸው እንደሚበዙ ወይም የልጆች የእናቶቻቸውን ሐቅ አለመወጣታቸው እንደሚበዛ ይህም ከእናቶቻቸው ጋር ያላቸው መስተጋብር ልክ ከባሪያ ጋር እንዳላቸው አይነት መስተጋብር እንደሚሆን፤ ለበግ እረኞችና ለድሆች በመጨረሻው ዘመን ዱንያ ተዘርግታላቸው በህንፃ ውበትና አሰራር እንደሚፎካከሩ ገለፁ።

ከዚያም ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ጠያቂው ጂብሪል እንደነበረና የመጣውም ይህንኑ ቀጥተኛ እምነት ለሶሐቦች ሊያስተምር እንደሆነ ተናገሩ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. የነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ስነ ምግባር ማማር፤ ከባልደረቦቻቸው ጋር የሚቀመጡ መሆናቸውን እነሱም ከሳቸው ጋር እንደሚቀመጡ ፤
2. ለጠያቂ ገር መሆንና ማቅረብ የተደነገገ መሆኑን፤ ይህም ሳይጨናነቅና ሳይፈራ ለመጠየቅ እንዲመቻች ነው።
3. ልክ ጂብሪል እውቀት ሊቀስም ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ፊት ስርአት ያለውን አቀማመጥ በመቀመጥ እንደተገበረ ከአስተማሪ ጋር አደብ መያዝ እንደሚገባ ፤
4. የኢስላም ማዕዘናት አምስት የኢማን መሰረቶች ደግሞ ስድስት መሆናቸውን፤
5. "ኢስላም" የሚለው ቃልና "ኢማን" የሚለው ቃል አንድ ላይ ሲመጡ "ኢስላም" ውጫዊ በሆኑ ነገሮች ሲተረጎም "ኢማን" ደግሞ ውስጣዊ በሆኑ ነገሮች ይተረጎማል።

6. የኢስላም ሃይማኖት የሚበላለጡ ደረጃዎች እንዳሉት መገለፁ፤ የመጀመሪያው ደረጃ: ኢስላም ፣ ሁለተኛው: ኢማን ፣ ሶስተኛው: ኢሕሳን ነው። እርሱ (ኢሕሳን) ከፍተኛው ደረጃ ነው።
7. የጠያቂ መሰረቱ አለማወቅ ነው። አለማወቅ ነው ለጥያቄ የሚያነሳሳው። ለዚህም ነው ሶሐቦች እየጠየቀም የመልሱን እውነተኝነት ሲያረጋግጥ የተደነቁት።
8. እጅግ አንገብጋቢ ከሆነ ነጥብ መጀመር እንደሚገባ፤ እሳቸው ኢስላምን ሲያብራሩ በሁለቱ የምስክርነት ቃላት ነውና የጀመሩት፣ ኢማንን ሲያብራሩም በአላህ ከማመን ነውና የጀመሩት፤
9. ጠያቂው የሚያውቀውን ነገር ሌሎችን ለማሳወቅ ሲል የእውቀት ባለቤቶችን መጠየቅ እንደሚችል፤
10. የሰዓቲቱ እለት እውቀት አላህ በእውቀቱ ከተነጠለባቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ ነው።

(4563)

(٤) - عَنْ عَبْدِ اللهِ بنِ عُمَر رضي الله عنهما قال: قال رسولُ الله صلى الله عليه وسلم: «بُنِيَ الْإِسْلَامُ عَلَى خَمْسٍ: شَهَادَةِ أَنْ لَا إِلَهَ إِلَّا اللهُ، وَأَنَّ مُحَمَّدًا عَبْدُهُ وَرَسُولُهُ، وَإِقَامِ الصَّلَاةِ، وَإِيتَاءِ الزَّكَاةِ، وَحَجِّ الْبَيْتِ، وَصَوْمِ رَمَضَانَ». [صحيح] - [متفق عليه]

(4) - ከዐብደላህ ቢን ዑመር (ረዲየሏሁ ዐንሁማ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አለ: «የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል: «እስልምና በአምስት መሰረቶች ተገነባ እነርሱም: 'ላ ኢላሃ ኢለሏህ ወአንነ ሙሐመደን ዐብዱሁ ወረሱሉህ' (ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ የለም፤ ሙሐመድም የአላህ ባሪያና መልክተኛ ናቸው።) ብሎ መመስከር፣ ሶላትን ማቋቋም፣ ዘካ መስጠት፣ በተከበረው የአሏህ ቤት ሐጅ ማድረግ እና የረመዷንን ወር መፆም ናቸው።'»
[ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ኢስላምን አምስት አስተማማኝ ምሰሶዎች እንደተሸከሙት ቤት አድርገው መሰሉት። የተቀሩትን የኢስላም ጉዳዮች ደግሞ ቤቱን እንደሚያሟሉ ነገሮች ናቸው። ከእነዚህ ማእዘናት የመጀመሪያው: ሁለቱ የምስክርነት ቃላት ናቸው። እነርሱም: ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ እንደሌለና ሙሐመድም የአላህ መልክተኛ መሆናቸውን መመስከር ነው። እነዚህ ሁለቱ የምስክርነት ቃላት እንደ አንድ ማእዘን ናቸው። አንዱ ከሌላኛው ተለይቶ የሚታይ አይደለምና። የአላህን ብቸኛ መሆንና ከርሱ ውጪ ያለውን ትቶ በብቸኝነት ለአምልኮ የተገባው እርሱ ብቻ መሆኑን በማመን፣ የሚያስፈርዱትን በመተግበር፣ በሙሐመድ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) መልዕክተኝነታቸውን በማመንና እርሳቸውን በመከተል አንድ ባሪያ እነዚህን ሁለት የምስክርነት ቃላት ይናገራል። ሁለተኛው ማእዘን: በቀንና በምሽት የሚሰገዱ የሆኑት የፈጅር፣ የዙህር፣ የዐስር፣ የመግሪብ እና የዒሻእ ሶላቶችን መስፈርቶቹን፣ ማእዘናቶቹንና ግዴታዎቹን ጠብቆ ማቋቋም ነው። ሶስተኛው ማእዘን: ግዴታ የሆነውን ዘካ ማውጣት ነው። ይህም ገንዘቡ በሸሪዓ የተወሰነውን ያህል መጠን የደረሰ ባለገንዘብ በሙሉ፤ ለሚገባው አካል ሊሰጥ ግዴታ የተደረገበት ገንዘባዊ አምልኮ ነው። አራተኛው ማእዘን: ሐጅ ነው። እርሱም: አምልኳዊ በሆነ መልኩ የሐጅ ተግባራትን ለመፈፀም መካን ማሰብ ነው። አምስተኛው ማእዘን: ረመዷንን መፆም ነው። እርሱም: አላህን በማምለክ ኒያ ጎህ ከወጣችበት ሰአት ጀምሮ ፀሀይ እስከምትጠልቅ ድረስ ከመብላት፣ ከመጠጣትና ሌሎችም ፆምን ከሚያስፈጥሩ ነገሮች መቆጠብ ማለት ነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ሁለቱ የምስክርነት ቃላቶች ተያያዥ መሆናቸውን እንረዳለን። አንደኛዋ በሌላኛው ካልሆነ በቀር አትበቃምና። ስለዚህም ሸሪዓ እንደ አንድ ማእዘን አደረጋቸው።

2. የሃይማኖቱ መሰረቶች ሁለቱ የምስክርነት ቃላት ናቸው። ስለሆነም አንዷትም ንግግር ሆነች ተግባር ያለነርሱ ተቀባይነት የላትም።

(65000)

(٥) - عَنْ مُعَاذٍ رَضِيَ اللهُ عَنْهُ، قَالَ: كُنْتُ رِدْفَ النَّبِيِّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ عَلَى حِمَارٍ يُقَالُ لَهُ عُفَيْرٌ، فَقَالَ: «يَا مُعَاذُ، هَلْ تَدْرِي حَقَّ اللهِ عَلَى عِبَادِهِ، وَمَا حَقُّ العِبَادِ عَلَى اللهِ؟»، قُلْتُ: اللهُ وَرَسُولُهُ أَعْلَمُ، قَالَ: «فَإِنَّ حَقَّ اللهِ عَلَى العِبَادِ أَنْ يَعْبُدُوهُ وَلا يُشْرِكُوا بِهِ شَيْئًا، وَحَقَّ العِبَادِ عَلَى اللهِ أَنْ لا يُعَذِّبَ مَنْ لا يُشْرِكُ بِهِ شَيْئًا»، فَقُلْتُ: يَا رَسُولَ اللهِ أَفَلاَ أُبَشِّرُ بِهِ النَّاسَ؟ قَالَ: «لا تُبَشِّرْهُمْ، فَيَتَّكِلُوا». [صحيح] - [متفق عليه]

(5) - ሙዓዝ -አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና- እንዲህ አሉ : ከነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ኋላ ዑፈይር የሚባለው አህያ ላይ ተፈናጥጬ ሳለው "ሙዓዝ ሆይ አላህ በባሮቹ ላይ ያለውን ሐቅ፤ ባሮችስ አላህ ዘንድ ያላቸውን ሐቅ ታውቃለህን? " አሉ። "አላህና መልክተኛው ይወቁ !" አልኩኝ። እሳቸውም "አላህ በባሮቹ ላይ ያለው ሐቅ ሊገዙትና በሱ ላይም አንዳችንም ላያጋሩ ሲሆን፤ ባሮች በአላህ ዘንድ ያላቸው ሐቅ ደግሞ በሱ ላይ አንዳችንም ያላጋራን ላይቀጣ ነው።" አሉ። "የአላህ መልክተኛ ሆይ ይህን ሰዎችን ላበስራቸውን?" አልኳቸው። እሳቸውም "አታበስራቸው (በዚህ ስራ ብቻ) ይደገፋሉ (ይሳነፋሉ)። " አሉ። [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን አላህ በባሮቹ ላይ ያለውን ሐቅና ባሮች አላህ ዘንድ ያላቸውን ሐቅ አብራሩ። አላህ ባሮቹ ላይ ያለው ሐቅ እሱን ብቻ ሊያመልኩና በሱ ላይ አንዳችንም ላያጋሩ ነው። ባሮች በአላህ ላይ ያላቸው ሀቅ ደግሞ እነዚያ በሱ ላይ አንዳችንም ሳያጋሩ በብቸኝነት ያመለኩትን ላይቀጣ ነው። ቀጥሎ ሙዓዝ "የአላህ መልክተኛ ሆይ! ሰዎች በደስታ እንዲበሰሩ በዚህ የላቀ የአላህ ትሩፋት ላበስራቸውን?" አለ። ነቢዩም

የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን በሷ ላይ መደገፋቸውን ፈርተው እንዳያበስራቸው ከለከሉት።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. አላህ በባሮቹ ላይ ግዴታ ያደረገው ሐቅ መገለፁ፤ እሱም፥ ሊያመልኩትና በሱ ላይም ምንንም ላያጋሩ መሆኑ።
2. አላህ በችሮታውና በፀጋው በነፍሱ ላይ ግዴታ ያደረገው የባሮች አላህ ዘንድ ያላቸው ሐቅ መገለፁ፤ እሱም ጀነት ሊያስገባቸውና ላይቀጣቸው ነው።
3. እዚህ ሐዲሥ ውስጥ አላህ ላይ አንዳችንም የማያጋሩ የተውሒድ ሰዎች መመለሻቸው ጀነት መሆኑን የሚገልፅ ትልቅ ብስራት አለ።
4. ሙዓዝ ዕውቀት በመደበቃቸው ወንጀል ውስጥ እንዳይወድቁ ፈርተው፥ ይህን ሐዲሥ የተናገሩት ከመሞታቸው በፊት (ወደ ሞት አፋፍ ሲቃረቡ) ነው።
5. አንዳንድ ሐዲሦችን ከፊል ሰዎች ትርጉሙን በአግባቡ አይረዱትም ተብሎ ከተሰጋ አለመናገርን ያስገነዝበናል። ይህ የማንነግራቸው ግን በሐዲሡ ስር ተግባርን የሚያዝና ሸሪዐዊ የቅጣት ብይኖችን የሚያስቀምጥ ሐዲሥ ካልሆነ ነው።
6. ከተውሒድ ሰዎች መካከል ወንጀል የሰሩ በአላህ ፍላጎት ስር መሆናቸው። ከፈለገ የሚቀጣቸው፤ ከፈለገም የሚምራቸው እነደሆነ እና መመለሻቸው ወደ ጀነት መሆኑን።

(65007)

(٦) - عن أنس بن مالك رضي الله عنه: أَنَّ النَّبِيَّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ وَمُعَاذٌ رَدِيفُهُ عَلَى الرَّحْلِ قَالَ: «يَا مُعَاذُ بْنَ جَبَلٍ»، قَالَ: لَبَّيْكَ يَا رَسُولَ اللهِ وَسَعْدَيْكَ، قَالَ: «يَا مُعَاذُ»، قَالَ: لَبَّيْكَ يَا رَسُولَ اللهِ وَسَعْدَيْكَ، ثَلَاثًا، قَالَ: «مَا مِنْ أَحَدٍ يَشْهَدُ أَنْ لَا إِلَهَ إِلَّا اللهُ وَأَنَّ مُحَمَّدًا رَسُولُ اللهِ صِدْقًا مِنْ قَلْبِهِ إِلَّا حَرَّمَهُ اللهُ عَلَى النَّارِ»، قَالَ: يَا رَسُولَ اللهِ، أَفَلَا أُخْبِرُ بِهِ النَّاسَ فَيَسْتَبْشِرُوا؟ قَالَ: «إِذًا يَتَّكِلُوا». وَأَخْبَرَ بِهَا مُعَاذٌ عِنْدَ مَوْتِهِ تَأَثُّمًا. [صحيح] - [متفق عليه]

(6) - ከአነስ ቢን ማሊክ -አላህ መልካም ስራውን ይውደድለትና- እንደተላለፈው: "ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ግመል ላይ ሆነው ሙዓዝ ከኃላ ተፈናጦ ሳለ እንዲህ አሉ: 'አንተ ሙዓዝ ቢን ጀበል ሆይ' እርሱም ሶስቴ 'አቤት ብያለው በደስታ የአላህ መልክተኛ ሆይ!' አሁንም 'ሙዓዝ ሆይ!' አሉት: እሱም 'አቤት ብያለው በደስታ የአላህ መልክተኛ ሆይ!' አለ። ሶስት ጊዜ ደገሙትና ቀጥለውም ' አላህ በእርሱ ላይ እሳትን እርም ቢያደርግ እንጂ አንድም በእውነተኛ ልቡ ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ አምላክ እንደሌለ ሙሐመድም የአላህ መልክተኛ መሆናቸውን የሚመሰክር የለም።' አሉ። እርሱም 'የአላህ መልክተኛ ሆይ! ይህንን ለሰዎች ነገሬ ላበስራቸው እንዴ?' አለ። እሳቸውም 'ከነገርካቸውማ (በዚህ ሐዲሥ ላይ) ይደገፋሉ (ይሰንፋሉ)።' አሉ። ሙዓዝ ይህንን ሐዲስ የተናገረው ወንጀል ውስጥ ላለ መውደቅ ብሎ ሊሞት ሲል ነው።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ሙዓዝ ቢን ጀበል -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- ከነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም መጋጓዣ ኋላ ተፈናጦ ሳለ እሳቸው "ሙዓዝ ሆይ!" በማለት ጠሩት። ለርሱ የሚነግሩት ነገር አንገብጋቢ መሆኑን አፅንኦት ለመስጠትም ጥሪያቸውን ሶስት ጊዜ ደጋገሙት።

ሙዓዝም -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- በነዚህ ጥሪዎች ሁሉ "ለበይክ ያረሱለሏህ ወሰዕደይክ" ማለትም የአላህ መልክተኛ ሆይ!ደጋግሜ በደስታ አቤት ብያለሁ። እያለ ይመልስ ነበር።

ነቢዩም ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ እንደሌለና ሙሐመድም የአላህ መልክተኛ መሆናቸውን ሳይዋሽ በእውነተኛ ልቡ የሚመሰክር ሆኖ በዚህ ሁኔታው ላይ ከሞተ አላህ እሳትን በርሱ ላይ እርም እንደሚያደርግ ነገሩት።

ሙዓዝም -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- ሰዎች እንዲደሰቱና በመልካም እንዲበሰሩ ልንገራቸውን? በማለት ነቢዩን ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ጠየቀ።

ነቢዩም ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም በዚህች ንግግር ላይ በመደገፍ ስራዎቻቸው እንዳታንስ ፈሩ።

ሙዓዝም እውቀትን የመሸሸግ ወንጀል ውስጥ መውደቅን በመፍራት ከመሞታቸው በፊት ካልሆነ በቀር ከዛ በፊት ይህችን ሐዲሥ ለአንድም አልተናገረም።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ሙዓዝን ከመጓጓዣ እንስሳቸው ኋላ ማፈናጠጣቸው የሳቸውን መተናነስ ያስረዳናል።
2. ሙዓዝ እሳቸው ለሚናገሩት ንግግር ንቃቱ እንዲበረታ ሙዓዝን ደጋግመው መጥራታቸው የነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለምን የማስተማር ስልት እንረዳለን።
3. "ላኢላሃ ኢለሏህ እና ሙሐመድ ረሱሉሏህ" የሚሉት የምስክርነት ቃላት ካላቸው መስፈርቶች መካከል ተናጋሪው ሳይዋሽ ወይም ሳይጠራጠር እውነተኛና እርግጠኛ መሆኑ አንዱ ነው።
4. የተውሒድ ሰዎች በጀሀነም እሳት ውስጥ አይዘወትሩም። በወንጀሎቻቸው አማካኝነት ቢገቡ እንኳ ከፀዱ በኋላ ከርሷ ይወጣሉ።
5. ሁለቱ የምስክርነት ቃላቶችን በእውነት ለተናገረ ሰው ያላቸውን ትሩፋት እንረዳለን።
6. ሐዲሥን በመናገር ተከትሎ የሚመጣ ችግር (መፍሰዳህ) ካለ አንዳንድ ጊዜ ሐዲሡን ከመናገር መቆጠብ እንደሚፈቀድ እንረዳለን።

(10098)

(٧) - عن طارق بن أشيم الأشجعي رضي الله عنه قال: سمعت رسول الله صلى الله عليه وسلم يقول: «مَنْ قَالَ: لَا إِلَهَ إِلَّا اللهُ، وَكَفَرَ بِمَا يُعْبَدُ مِنْ دُونِ اللهِ حَرُمَ مَالُهُ وَدَمُهُ، وَحِسَابُهُ عَلَى اللهِ».
[صحيح] - [رواه مسلم]

(7) - ከጧሪቅ ቢን አሸየም አልአሸጀዒይ -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው እንዲህ ለዋሏል: "የአላህን መልክተኛ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንዲህ ሲሉ ሰምቻለሁ: 'ላኢላሃ ኢለሏህ ብሎ ከአላህ ውጪ በሚመለኩ ነገሮች የካደ ሰው ገንዘቡም ደሙም እርም ይሆናል። ሂሳቡ ያለው አላህ ላይ ነው።'" [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

በምላሱ "ላኢላሃ ኢለሏህ" ማለትም ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ የለም ያለና የመሰከረ ሰው ፤ ከአላህ ውጪ በሚመለኩ ነገሮች የካደና ከኢስላም ውጪ ካሉ ሁሉ እምነቶች የጠራ ሰው በሙስሊሞች ላይ ገንዘቡና ደሙ እርም ይሆናል። እኛ ውጫዊ ከሆኑ ስራዎቹ በስተቀር መፈላፈል አይፈቀድልንም። በኢስላማዊ ህግጋት ይህንን የሚያስገድድ አስገዳጅ ወንጀል እስካልፈፀመ ድረስ ገንዘቡም እንደማይነጠቅ ደሙም እንደማይፈስ ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ተናገሩ።

የትንሳኤ ቀን ሂሳቡን በበላይነት የሚመራው አሏህ ነው። እውነቱን ከሆነ ይመነዳዋል። ሙናፊቅ ከሆነ ደግሞ ይቀጣዋል።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. "ላኢላሃ ኢለሏህ" ብሎ መናገርና ከአላህ ውጪ በሚመለኩ ሁሉ መካድ ወደ ኢስላም ለመግባት መስፈርት ነው።
2. የ "ላኢላሃ ኢለሏህ" ትርጉም በጣኦታት፣ በመቃብሮችና በሌሎችም ከአላህ ውጪ በሚመለኩ ሁሉ መካድና በአምልኮ እሱን ብቻ መነጠል ነው።

3. ተውሒድን የተገበረና በውጫዊ ማንነቱ የአላህ ድንጋጌዎች ላይ የፀና ይህን የሚፃረር ነገር ከሱ ይፋ እስኪሆን ድረስ ከሱ መቆጠብ ግዴታ ነው።
4. የሙስሊም ገንዘብ፣ ደሙና ክብሩ በሸሪዓዊ ምክንያቶች ካልሆነ በስተቀር የተከበረ መሆኑን እንረዳለን።
5. በዱንያ ውስጥ ፍርድ የሚሰጠው በውጫዊ ማንነት ሲሆን በአኺራ ደግሞ ኒያዎችና አላማዎች ላይ በመንተራስ ነው።

(6765)

(٨) - عَنْ جَابِرٍ رضي الله عنه قَالَ: أَتَى النَّبِيَّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ رَجُلٌ فَقَالَ: يَا رَسُولَ اللهِ، مَا الْمُوجِبَتَانِ؟ فَقَالَ: «مَنْ مَاتَ لَا يُشْرِكُ بِاللهِ شَيْئًا دَخَلَ الْجَنَّةَ، وَمَنْ مَاتَ يُشْرِكُ بِاللهِ شَيْئًا دَخَلَ النَّارَ»

[صحيح] - [رواه مسلم]

(8) - ጃቢር - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንዲህ አሉ፦ ወደ ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ዘንድ አንድ ሰውዬ በመምጣት እንዲህ አለ፦ "የአላህ መልክተኛ ሆይ! ሁለቱ (ጀነትና እሳትን) የሚያስወስኑ ነገሮች ምንድናቸው?" እሳቸውም "በአላህ ላይ አንዳችንም ሳያጋራ የሞተ ሰው ጀነት ገባ፤ በአላህ ላይ አንዳችን እያጋራ የሞተ ሰው እሳት ገባ።" አሉ። [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

አንድ ሰውዬ ነቢዩን የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ጀነት መግባትን ስለሚያስወስን እና እሳት መግባትን ስለሚያወስን ሁለት ነገሮች ጠቃቸው። ነቢዩም የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን፦ ጀነትን የሚያስወስነው ነገር ሰውዬው አላህን በብቸኝነት እያመለከ በሱ አንዳችንም ሳያጋራ መሞቱ ነው ብለው መለሱለት። እሳትን የሚያስወስነው ነገር ደግሞ ሰውዬው ለአላህ በተመላኪነቱ ወይም በጌትነቱ ወይም በስሞቹና ባህሪያቶቹ መሳይ እና አቻ በማድረግ በአላህ ላይ አንዳችን ነገር እያጋራ መሞቱ ነው ብለው መለሱለት።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. የተውሒድ ትሩፋት መገለፁ። እሱም አማኝ ሆኖ በአላህ ላይ አንዳችንም ሳያጋራ የሞተ ሰው ጀነት የሚገባ መሆኑን።
2. የሺርክ አደገኝነትም መገለፁ። እሱም፥ በአላህ ላይ አንዳችን እያጋራ የሞተ ሰው እሳት የሚገባ መሆኑን።
3. ከተውሒድ ሰዎች መካከል፥ ወንጀል የሰሩ በአላህ ፍላጎት እና ውሳኔ ስር መሆናቸው፤ በመሆኑም ከፈለገ እንደሚቀጣቸው ከፈለገም የሚምራቸው እንድሆነ እና ከዚያም መመለሻቸው ወደ ጀነት መሆኑን።

(65008)

(٩) - عَنْ عَبْدِ اللهِ بنِ مَسْعُودٍ رضي الله عنه قال: قَالَ النَّبِيُّ صلى الله عليه وسلم كَلِمَةً وَقُلْتُ أُخْرَى، قَالَ النَّبِيُّ صلى الله عليه وسلم: «مَنْ مَاتَ وَهُوَ يَدْعُو مِنْ دُونِ اللهِ نِدًّا دَخَلَ النَّارَ» وَقُلْتُ أَنَا: مَنْ مَاتَ وَهُوَ لَا يَدْعُو لِلَّهِ نِدًّا دَخَلَ الْجَنَّةَ. [صحيح] - [متفق عليه]

(9) - ከዐብደላህ ቢን መስዑድ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: "ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) አንዷን ተናገሩ እኔ ደግሞ ሌላዋን ተናገርኩ። ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ አሉ: ‹ ከአላህ ውጪ ሌላን ቢጤን (ባላንጣን) እየተጣራ የሞተ ሰው እሳት ገባ።› እኔ ደግሞ: ‹ለአላህ ሌላን ቢጤን (ባላንጣን) ሳይጣራ የሞተ ሰው ጀነት ይገባል።› አልኩኝ።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ከአላህ ውጪ ያለን አካል መጣራትና ከአላህ ውጪ ካለ አካል እርዳታ መፈለግን የመሰለ ለአላህ ሊደረግ ግዴታ የሆነን አንዳች ነገር ለሌላ እየሰጠ የሞተ ሰው የእሳት ባለቤት መሆኑን ነገሩን። ኢብኑ መስዑድም (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም

ሥራቸውን ይውደድላቸውና - በአላህ አንዳችን ሳያጋራ የሞተ ሰው መመለሻው ወደ ጀነት ነው የሚለውን ጨመሩ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ዱዓእ ለአላህ ካልሆነ በስተቀር የማይሰጥ አምልኮ ነው።
2. በተውሒድ ላይ የሞተ ሰው በከፊል ወንጀሉ ቢቀጣም እንኳ ጀነት መግባቱ የተውሒድን ትሩፋት ያስረዳናል።
3. በሺርክ ላይ የሞተ ሰው እሳት መግባቱ የሺርክን አደገኝነት ይጠቁማል።

(3419)

(١٠) - عَنِ ابْنِ عَبَّاسٍ رَضِيَ اللهُ عَنْهُمَا قَالَ: قَالَ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ لِمُعَاذِ بْنِ جَبَلٍ، حِينَ بَعَثَهُ إِلَى الْيَمَنِ: «إِنَّكَ سَتَأْتِي قَوْمًا أَهْلَ كِتَابٍ، فَإِذَا جِئْتَهُمْ فَادْعُهُمْ إِلَى أَنْ يَشْهَدُوا أَنْ لَا إِلَهَ إِلَّا اللهُ، وَأَنَّ مُحَمَّدًا رَسُولُ اللهِ، فَإِنْ هُمْ أَطَاعُوا لَكَ بِذَلِكَ، فَأَخْبِرْهُمْ أَنَّ اللهَ قَدْ فَرَضَ عَلَيْهِمْ خَمْسَ صَلَوَاتٍ فِي كُلِّ يَوْمٍ وَلَيْلَةٍ، فَإِنْ هُمْ أَطَاعُوا لَكَ بِذَلِكَ، فَأَخْبِرْهُمْ أَنَّ اللهَ قَدْ فَرَضَ عَلَيْهِمْ صَدَقَةً تُؤْخَذُ مِنْ أَغْنِيَائِهِمْ فَتُرَدُّ عَلَى فُقَرَائِهِمْ، فَإِنْ هُمْ أَطَاعُوا لَكَ بِذَلِكَ، فَإِيَّاكَ وَكَرَائِمَ أَمْوَالِهِمْ، وَاتَّقِ دَعْوَةَ الْمَظْلُومِ، فَإِنَّهُ لَيْسَ بَيْنَهُ وَبَيْنَ اللهِ حِجَابٌ». [صحيح] - [متفق عليه]

(10) - ከኢብኑ ዐባስ ረዲየሏሁ ዐንሁማ እንደተላለፈው እንዲህ ብሏል: "የአላህ መልዕክተኛ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ሙዐዝ ቢን ጀበልን ወደ የመን በሚልኩበት ጊዜ እንዲህ አሉት: ' አንተ የመጽሐፍ ባለቤት ወደሆኑ ህዝቦች ትሄዳለህ። ስለዚህም እነርሱ ዘንድ ስትደርስ ከአሏህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ አምላክ እንደሌለና ሙሐመድም የአሏህ መልዕክተኛ መሆናቸውን ወደ መመስከር ጥሪ አድርግላቸው። እነሱ ለዚህ ጥሪህ ታዛዥ ከሆኑ አሏህ በነሱ ላይ በቀንና ምሽቱ ሁሉ አምስት ሰላቶችን ግዴታ እንዳደረገባቸው አሳውቃቸው። ለዚህ ጥሪህም ታዛዥ ከሆኑ አላህ በነሱ ላይ ከሀብታሞቻቸው ተይዞ ወደ ድሆቻቸው የምትሰጥ ምፅዋት ግዴታ እንዳደረገባቸው አሳውቃቸው። ለዚህ ጥሪህም ታዛዦች ከሆኑ አደራህን ውድ የሆኑ ንብረቶቻቸውን (ገንዘቦቻቸውን) ተጠንቀቅ! የተበዳይንም ልመና ተጠንቀቅ!

እነሆ በሷና በአላህ መሀል ግርዶሽ የለምና።'" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ሙዐዝ ቢን ጀበልን - ረዲየሏሁ ዐንሁ - ወደ አላህ መንገድ ተጣሪና አስተማሪ በማድረግ ወደ የመን በላኩበት ወቅት ከክርስቲያን የሆኑ ህዝቦችን ስለሚጋፈጥ እነርሱን በተመለከተ ዝግጁ እንዲሆን አሳሰቡት። ቀጥለውም ዳዕዋውን እጅግ አንገብጋቢ ከሆነው ነጥብ እንዲጀምር ነገሩት። መጀመርያ "ላ ኢላሃ ኢለሏህ ሙሐመዱን ረሱሉሏህ" ብለው በአሏህ አንድነትና በሙሐመድ መልዕክተኝነት በመመስከር እምነታቸውን እንዲያስተካክሉ ጥሪ እንዲያደርግ፤ ምክንያቱም ወደ እስልምና የሚገቡት በዚህ የምስክርነት ቃል ስለሆነ ነው። ይህንንም ተግባራዊ ካደረጉ ሶላትን እንዲሰግዱ ማዘዝ እንዳለበት ነገሩት። ምክንያቱም ከተውሒድ በኋላ ትልቁ ግዴታ ይህ በመሆኑ ነው። ሶላትንም ካስተካከሉ በኋላ ከመካከላቸው ያሉት ባለ ፀጋች በመካከላቸው ላሉት ድሆች ከገንዘባቸው ዘካን እንዲያወጡ ማዘዝ እንዳለበት ነገሩት። ከዚያም ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ለዘካ ብሎ ከውድ ንብረታቸው እንዳይወስድ አስጠነቀቁት። ምክንያቱም የመስጠት ግዴታቸው ከመካከለኛ ንብረታቸው ነውና። ከዚያም የተበዳይ ዱዓእ ተቀባይነቱ ከፍተኛ በመሆኑ ተበዳይ ዱዓእ እንዳያደርግበት ግፍን መጠንቀቅ እንዳለበት አሳሰቡት።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. በ "ላ ኢላሀ ኢለሏህ" የመመስከር ትርጉም አሏህን በአምልኮ መነጠልና ከአሏህ ውጪ ምንንም አለማምለክ እንደሆነ፤
2. ሙሐመድ የአሏህ መልዕክተኛ መሆናቸውን የመመስከር ትርጉሙ በሳቸውም ማመን፣ ይዘውት በመጡትም እውነትነቱን ማመን፤ እሳቸው ወደ ሰው ልጆች ከተላኩት የመጨረሻው መልዕክተኛ መሆናቸውንም ማመን መሆኑን፤

3. የእውቀት ባለቤት ወይም እርሱ ዘንድ ማምታቻ ያለውን ሰው ማናገር መሀይምን እንደማናገር አለመሆኑን፤ ስለዚህም ነው ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ሙዓዝን እንዲህ በማለት የጠቆሙት፡ "አንተ የመጽሐፍ ባለቤት ወደሆኑ ህዝቦች ትሄዳለህ።"
4. ሙስሊም በዲኑ ጉዳይ አወዛጋቢዎች ከሚያመጡት ማምታቻ መጥራት እንዲችል በእውቀት ላይ ሊሆን እንደሚገባው፤ ይህም ዒልም በመፈለግ የሚሆን ነገር ነው።
5. የአሏህ መልዕክተኛ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ከተላኩ በኋላ የአይሁዶችና የክርስያኖች ሃይማኖት ውድቅ መሆኑን፤ በነቢያችን የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን አምነው ወደ እስልምና እስካልገቡ ድረስም ከሚድኑት ጎራ አለመሆናቸውን እንረዳለን።

(3390)

(١١) - عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ رضي الله عنه أَنَّهُ قَالَ: قيل يا رسول الله من أسعد الناس بشفاعتك يوم القيامة؟ قال رسول الله صلى الله عليه وسلم: «لقد ظننت يا أبا هريرة ألا يسألني عن هذا الحديث أحد أول منك لما رأيت من حرصك على الحديث، أسعد الناس بشفاعتي يوم القيامة، من قال لا إله إلا الله، خالصًا من قلبه أو نفسه». [صحيح] - [رواه البخاري]

(11) - አቢ ሁረይራ ረዲየሏሁ ዐንሁ እንዲህ ማለታቸው ተላልፏል፡ "የአላህ መልእክተኛ ሆይ! የቂያማ ቀን በርሶ ምልጃ ከሰዎች ሁሉ ይበልጥ እድለኛው ማን ነው?" ተባሉ። የአላህ መልዕክተኛም የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ አሉ፡- 'አቡ ሁረይራ ሆይ! ባንተ ላይ ካየሁት የሐዲሥ ጉጉት አንፃር ይህንን ጥያቄ ለመጠየቅ የሚቀድምህ አይኖርም ብዬ አስቤ ነበር። የቂያማ ቀን በኔ አማላጅነት ከሰዎች ሁሉ ይበልጥ እድለኛ የሚሆኑት ጥርት ባለ መልኩ ከልባቸው ወይም ከነፍሳቸው 'ላ ኢላሃ ኢለሏህ' ያሉት ናቸው።'" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን የትንሳኤ ቀን በምልጃቸው ከሰዎች ሁሉ የበለጠ እድለኛ የሚሆኑት "ከልባቸው ወይም ከነፍሳቸው 'ላ ኢላሃ ኢለሏህ' ያሉት" ማለትም ከአሏህ በቀር በእውነት አምልኮ የሚገባው እንደሌለ አምነው ከሽርክ ይሁን ከይዩልኝና ይስሙልኝም ጥርት ያሉት መሆናቸውን እየነገሩን ነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ነብዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን አኼራ ላይ ሸፋዓ እንደሚያደርጉና ሸፋዓቸውም ተውሒድ ላላቸው ሰዎች መሆኑን ያፀድቃል፤
2. የነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ሸፋዓ ተውሒድ ላይ እያለ (በኃጢዓቱ ምክንያት) ጀሀነም የተፈረደበትን ወደ ጀሀነም እንዳይገባ፤ ከገባ ደግሞ እንዲወጣ የሚያደርጉት ምልጃ ነው፤
3. ለአላህ ጥርት ተደርጋ የተባለች የተውሒድ ቃል ያላት ትሩፋትና የምታሳድረው ከፍተኛ ፋና፤
4. የተውሒድ ቃል የሚረጋገጠው ትርጉሟን በማወቅና በምታስፈርደው ተግባራዊ በማድረግ ነው፤
5. አቢ ሁረይራ ያላቸውን ደረጃና በዕውቀት ላይ ያላቸውን ጉጉት እንረዳለን።

(3414)

(١٢) - عن أبي هريرة رضي الله عنه قال: قال رسول الله صلى الله عليه وسلم: «الْإِيمَانُ بِضْعٌ وَسَبْعُونَ -أَوْ بِضْعٌ وَسِتُّونَ- شُعْبَةً، فَأَفْضَلُهَا قَوْلُ لَا إِلَهَ إِلَّا اللهُ، وَأَدْنَاهَا إِمَاطَةُ الْأَذَى عَنِ الطَّرِيقِ، وَالْحَيَاءُ شُعْبَةٌ مِنَ الْإِيمَانِ». [صحيح] - [متفق عليه]

(12) - ከአቡ ሁረይራ -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ ብለዋል: "የአላህ መልዕክተኛ ሰለሏሁ ዓለይሂ ወስለም እንዲህ ብለዋል: 'ኢማን ሰባ ምናምን ወይም ስልሳ ምናምን ክፍሎች አሉት። በላጩ ክፍልም 'ላኢላሃ ኢለሏህ' ማለት ሲሆን ዝቅተኛው ክፍል መጥፎን ነገር ከመንገድ ላይ ማስወገድ ነው። ሓያእ (አይነ አፋርነትም) የኢማን አንዱ ክፍል ነው።'" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ኢማን ተግባሮችን፣ እምነቶችንና ንግግሮችን የጠቀለለ ብዙ ክፍሎች እንዳሉት ተናገሩ።

ከኢማን ክፍሎች ውስጥ በላጩና ከፍተኛው ትርጉሙን አውቆ ፣ የሚያስፈርደው በመተግበር "ላኢላሃ ኢለሏህ" ማለት ነው። አላህ አንድና ብቸኛ አምላክ መሆኑንና ለአምልኮ የተገባ ብቸኛ አምላክ መሆኑን ከርሱ ውጪ ያለ ማንም እንደማይገባውም ማመን ነው።

የኢማን ትንሹ ስራ ሰዎችን የሚያውክ የሆነን ነገር ሁሉ ከመንገዳቸው ላይ ማስወገድ ነው።

ቀጥለውም ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ሓያእ (አይነ አፋርነት) የኢማን አንድ ክፍል መሆኑን ተናገሩ። ይህም መልካም ለመስራትና ፀያፍ ለመተው የሚያነሳሳ ባህሪ ነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ኢማን ከፊሉ ከከፊሉ የሚበላለጡ ደረጃዎች አሉት።
2. ኢማን ንግግርም፣ ተግባርም እምነትም ነው።

3. አላህን ማፈር ሲባል: በከለከለህ ስፍራ አለማየቱና ባዘዘክ ስፍራ አለማጣቱን ያስፈርዳል።
4. ቁጥር መወሰቱ በርሱ ላይ ብቻ መገደቡን አያሲዝም። ይልቁንም የኢማን ተግባራት እንዲሁ መብዛታቸውን ይጠቁማል። ዓረቦች ከዛ ቁጥር በላይ ያለን ውድቅ ማድረግ ሳይፈልጉም አንዳንድ ነገሮችን በቁጥር ገድበው ያወሱታል።

(6468)

(١٣) - عَنْ عَبْدِ اللهِ بنِ مَسْعُودٍ رضي الله عنه قال: سَأَلْتُ النَّبِيَّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ: أَيُّ الذَّنْبِ أَعْظَمُ عِنْدَ اللهِ؟ قَالَ: «أَنْ تَجْعَلَ لِلَّهِ نِدًّا وَهُوَ خَلَقَكَ» قُلْتُ: إِنَّ ذَلِكَ لَعَظِيمٌ، قُلْتُ: ثُمَّ أَيُّ؟ قَالَ: «وَأَنْ تَقْتُلَ وَلَدَكَ؛ تَخَافُ أَنْ يَطْعَمَ مَعَكَ» قُلْتُ: ثُمَّ أَيُّ؟ قَالَ: «أَنْ تُزَانِيَ حَلِيلَةَ جَارِكَ».

[صحيح] - [متفق عليه]

(13) - ከዐብደላህ ቢን መስዑድ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ ብለዋል፦ "ነቢዩን (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) 'አላህ ዘንድ እጅግ ትልቁ ወንጀል ምንድነው?' ብዬ ጠየቅኩ። እርሳቸውም 'አላህ ፈጥሮህ ሳለ ለርሱ ቢጤን ማድረግክ ነው።' አሉ። እኔም 'ይህማ ትልቅ ነው።' አልኩኝ። 'ከዚያስ ቀጥሎ' አልኳቸው። እርሳቸውም 'ልጅህን ከአንተ ጋር መብላቱን ፈርተህ መግደልክ ነው።' አሉኝ። 'ከዚያስ ቀጥሎ' አልኳቸው። እርሳቸውም 'በጎረቤትህ ሚስት ላይ ዝሙት መስራትህ ነው።' አሉኝ።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ስለ እጅግ ትልቁ ወንጀል ተጠየቁ: እጅግ ትልቁ ወንጀል ትልቁ ሺርክ ነው። እርሱም ለአላህ በተመላኪነቱ ወይም በጌትነቱ ወይም በስሞቹና ባህሪያቶቹ ምሳሌ ወይም ቢጤን ማድረግክ ነው። ይህን ወንጀል አላህ ያለ ተውበት አይምረውም። ባለቤቱ በዚህ ወንጀል ላይ ሳለ ከሞተም በእሳት ውስጥ ዘውታሪ ነው።

ቀጥሎም ሰውዬው ልጁን ከርሱ ጋር መብላቱን ፈርቶ መግደሉ ነው። በመሰረቱ ነፍስን መግደል ክልክል ነው። ነገር ግን ተገዳዩ የገዳዩ ዘመድ ከሆነ ወንጀሉ የከፋ ይሆናል። አሁንም በድጋሚ ገዳዩ የመግደሉ አላማ ተገዳዩ በአላህ ሲሳይ ላይ እንዳይጋራው አስቦ ከሆነ ወንጀሉ እጅግ የከፋ ይሆናል። ቀጥሎ አንድ ሰው በጎረቤቱ ሚስት ላይ ዝሙት መስራቱ ነው። እርሷ ላይ ዝሙት እስኪሰራና ታዛዡ እስክትሆን ድረስ የጎረቤቱን ሚስት ለማታለል መሞከሩ ነው። በመሰረቱ ዚና ክልክል ነው። ነገር ግን ዝሙት የተሰራባት ሸሪዓ ለነርሱ መልካም እንድንውልላቸው፣ በጎ እንድናደርግላቸውና ጥሩ ወዳጅኝት እንዲኖረን ያዘዘን በሆነው የጎረቤት ሚስት ከሆነች ወንጀሉ የከፋ ይሆናል።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. መልካም ስራዎች በደረጃ እንደሚበላለጡት ሁሉ ወንጀሎችም በከባድነታቸው ይበላለጣሉ።
2. እጅግ ትልቁ ወንጀል በአላህ ማጋራት ነው። ቀጥሎ ከአንተ ጋር መብላቱን በመፍራት ልጅን መግደል ነው። ቀጥሎም በጎረቤት ሚስት ላይ ዝሙት መፈፀም ነው።
3. ሲሳይ በአላህ እጅ ነው። ጥራት የተገባው አላህ በፍጡራን ሲሳይ ላይ ኃላፊነቱን ወስዷል።
4. የጎረቤት ሐቅ ታላቅ መሆኑንና ጎረቤትን የማወክ ወንጀልነቱ ሌላን አካል ከማወክ የበለጠ እጅግ የከፋ ወንጀል መሆኑን እንረዳለን።
5. ፈጣሪ ብቸኛው ለአምልኮ የተገባና አጋር የሌለው ነው።

(5359)

(١٤) - عن أبي هريرة رضي الله عنه قال: قال رسول الله صلى الله عليه وسلم: «قال الله تبارك وتعالى: أنا أغنى الشركاء عن الشرك، من عمل عملًا أشرك فيه معي غيري، تركتُهُ وشركَهُ».
[صحيح] - [رواه مسلم]

(14) - አቡ ሁረይራ ረዲየሏሁ ዐንሁ እንዲህ ብለዋል፦ የአሏህ መልዕክተኛ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ ብለዋል፡ "የላቀው አሏህ እንዲህ ብሏል፡ 'እኔ በሽርክና ከመጋራት ከተብቃቁ ሁሉ እጅግ የተብቃቃሁ ነኝ። ከኔ ጋር ሌላን አጋርቶ ስራን የሰራ እሱንም ማጋራቱንም እተወዋለሁ።'" [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) አላህ ሱብሃነሁ ወተዓላ እንዲህ ማለቱን እየነገሩን ነው፦ አጋርን ከመፈለግ ከተብቃቁ ሁሉ እጅግ የተብቃቃው አሏህ ነው። እርሱም ከምንም የተብቃቃ ራሱን የቻለ ነው። አንድ ሰው መልካም ነገርን ሲያደርግ ለአላህም ለሌሎችም ብሎ ቢያደርገው አላህ ይህንን ስራውን ይተውለታል፤ አይቀበለውም፤ ወደራሱ ይመልስለታል። ስለዚህም ጥራት የተገባው አሏህ ጥርት ባለ መልኩ ለርሱ ተብሎ የተሰራውን መልካም ስራ ካልሆነ በቀር ሌላን ስራ ስለማይቀበል ኢኽላስን ለርሱ ማድረግ ግዴታ ነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ሽርክ መልካም ስራዎች ተቀባይነት እንዳያገኙ ግርዶ ስለሆነ በሁሉም መልኩ መጠንቀቅን፤
2. ስራን ለአሏህ ጥርት በማድረግ ላይ ስለሚያግዝ የአሏህን ሙሉ ተብቃቂነትና ታላቅነት ማስተዋል እንደሚያስፈልግ እንረዳለን።

(3342)

(١٥) - عن أبي هريرة رضي الله عنه أن رسول الله صلى الله عليه وسلم قال: «كُلُّ أُمَّتِي يَدْخُلُونَ الْجَنَّةَ إِلَّا مَنْ أَبَى»، قَالُوا: يَا رَسُولَ اللهِ، وَمَنْ يَأْبَى؟ قَالَ: «مَنْ أَطَاعَنِي دَخَلَ الْجَنَّةَ، وَمَنْ عَصَانِي فَقَدْ أَبَى». [صحيح] - [رواه البخاري]

(15) - ከአቡ ሁረይራ -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው የአላህ መልክተኛ ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም እንዲህ ብለዋል፡ "ሁሉም ህዝቦቼ ጀነት ይገባሉ እምቢ ያለ ሲቀር" ሶሐቦችም "የአላህ መልክተኛ ሆይ! ማን እምቢ ይላል?" አሉ። እሳቸውም "እኔን የታዘዘኝ ጀነት ገባ ፤ እኔን ያመፀኝ ደግሞ በርግጥም እምቢ ብሏል።" በማለት መለሱ።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ጀነት ከመግባት ራሱን ያቀበ ሰው ካልሆነ በስተቀር ሁሉም ህዝባቸው ጀነት እንደሚገቡ ተናገሩ።

ሰሐቦችም አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና "የአላህ መልክተኛ ሆይ! ማን ራሱን ከጀነት ያቅባል?" አሉ።

እሳቸውም ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም : "መልክተኛውን ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም የተከተለና የታዘዘ ጀነት ገባ። ያመፀና ለሸሪዐ ታዛዥ ያልሆነ ሰው ግን በርግጥም በመጥፎ ስራዎቹ ጀነት ከመግባት ራሱን አቅቧል።" በማለት መለሱላቸው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. መልክተኛውን ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም መታዘዝ አላህን ከመታዘዝ ይመደባል። እሳቸውን ማመፅም አላህን ከማመፅ ይመደባል።
2. ነቢዩን ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም መታዘዝ ጀነት መግባትን ስታስፈርድ እሳቸውን ማመፅ ደግሞ እሳት መግባትን የምታስፈርድ መሆኗ።
3. ከዚህ ኡማህ አላህና መልክተኛውን ያመፁ ሲቀሩ ነቢዩን ታዛዥ ለሆኑ ብስራት ነው፤ ሁሉም ጀነት ይገባሉና።

4. ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም በኡመታቸው ላይ ያላቸውን እዝነትና እንዲመሩ ያላቸውን ጥልቅ ጉጉት እንረዳለን።

(4947)

(١٦) - عَن عُمَرَ بنِ الخَطَّابِ رَضِيَ اللهُ عَنْهُ قال: سَمِعْتُ النَّبِيَّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ يَقُولُ: «لَا تُطْرُونِي كَمَا أَطْرَتِ النَّصَارَى ابْنَ مَرْيَمَ؛ فَإِنَّمَا أَنَا عَبْدُهُ، فَقُولُوا: عَبْدُ اللهِ وَرَسُولُهُ».

[صحيح] - [رواه البخاري]

(16) - ዑመር ኢብኑል ኸጧብ ረዲየሏሁ ዐንሁ እንዲህ ብለዋል፡ "የአሏህ መልዕክተኛ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ ሲሉ ሰምቻቸዋለሁ፡ "ክርስቲያኖች የመርየም ልጅን ሲያሞግሱ ወሰን እንዳለፉት እኔን ስታሞግሱ ወሰን አትለፉ። እኔ የአሏህ ባሪያ ብቻ ነኝ። ስለዚህም የአላህ ባሪያና መልክተኛው በሉኝ።"" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ክርስቲያኖች ዒሳ ዓለይሂ ሰላምን በተመለከተ ወሰን እንዳለፉት ሁሉ ነቢዩም የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ህዝባቸው እሳቸውን በማሞገስ በኩል፣ በአላህ ባህሪያትና ልዩ ድርጊቶቹ እሳቸውን በመግለፅ፣ የሩቅ እውቀትን እንደሚያውቁ በመሞገት፣ ወይም ከአሏህ ጋር እሳቸውን በመማፀንና በመሳሰሉት መልኩ ወሰን እንዳይታለፍባቸው አስጠነቀቁ። ከዚያም ከአሏህ ባርያዎች መካከል አንዱ መሆናቸውን ገልፀው፤ እሳቸውን "የአሏህ ባርያውና መልዕክተኛው" ብለን እንድንገልፃቸው አሳሰቡ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ወደ ሽርክ የሚያደርስ በመሆኑ በማላቅ እና በማወደስ ረገድ ሸሪዓ የደነገገውን ገደብ ከማለፍ መጠንቀቅ እንደሚገባ፤
2. ይህ ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ያስጠነቀቁት ነገር በእውነቱ በዚህ ኡማ ተከስቷል። ይህም የተወሰኑት ነብዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ላይ፣ ከፊሎች የነቢዩﷺ የአላህ ሰላትና ሰላም

በእርሳቸው ላይ ይስፈን ቤተሰቦች ላይ፣ ሌሎች ደግሞ ወልዮች ላይ ይህ ያስጠነቀቁትን ነገር በመፈፀም ሽርክ ላይ ወድቀዋል።

3. የአላህ መልእክተኛ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን የአሏህ ባሪያው ናቸው እንጂ ከአምላክ መለያዎች መካከል የትኛውም እንደማይገባቸው ለመጠቆም ራሳቸው የአላህ ባሪያ መሆናቸውን ገለፁ።
4. ረሱል የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ከአሏህ የተላኩ መልዕክተኛው በመሆናቸው ሊያምኗቸውና ሊከተሏቸው እንደሚገባ ለመጠቆም ራሳቸውን የአሏህ መልዕክተኛ መሆናቸውንም ገለፁ።

(3406)

(١٧) - عن أنس رضي الله عنه قال: قال النبي صلى الله عليه وسلم: «لَا يُؤْمِنُ أَحَدُكُمْ حَتَّى أَكُونَ أَحَبَّ إِلَيْهِ مِنْ وَالِدِهِ وَوَلَدِهِ وَالنَّاسِ أَجْمَعِينَ». [صحيح] - [متفق عليه]

(17) - ከአነስ -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው እንዲህ አለ: "ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንዲህ ብለዋል: "አንዳችሁ ከወላጆቹ ፣ ከልጁና ከሰዎች ባጠቃላይ እርሱ ዘንድ እጅግ ተወዳጁ እኔ እስክሆን ድረስ አላመነም።"" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

አንድ ሙስሊም ለአላህ መልክተኛ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ያለው ውዴታ ለእናቱ ፣ ለአባቱ ፣ ለወንድ ልጁ፣ ለሴት ልጁና ለሰዎችም ባጠቃላይ ካለው ውዴታ እስኪያስቀድም ድረስ ኢማኑ ምሉዕ አይሆንም በማለት የአላህ መልክተኛ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ተናገሩ። ይህ ውዴታም እሳቸውን መታዘዝን፣ መርዳትንና እሳቸውን ማመፅ መተውን ያስፈርዳል።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. መልክተኛውን ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም መውደድና ከሁሉም ፍጡራን ውዴታ ማስቀደም ግዴታ መሆኑን እንረዳለን።

2. የአላህን መልክተኛ ሱና መርዳትና በዚህ መንገድ ላይም ገንዘብና ነፍስን መለገስ ከተሟላ ውዴታ ምልክቶች መካከል አንዱ ነው።
3. መልክተኛውን ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም መውደድ ባዘዙት ነገር መታዘዝን፣ በተናገሩት ማመንን፣ ከከለከሉትና ካስጠነቀቁት ነገሮች መከልከልን፣ እሳቸውን መከተልንና ቢድዓን መተው ያስፈርዳል።
4. ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ከጥመት መንገድ (ወደ ቀናው) ለመመራታችን ፣ ከእሳት ለመዳናችን፣ ጀነትን ለመጎናፀፋችን ምክንያት ስለሆኑ የነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ሀቅ ከሁሉም ሰዎች ሀቅ የበለጠና የገዘፈ ነው።

(5953)

(١٨) - عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ رضي الله عنه عَنِ النَّبِيِّ صلى الله عليه وسلم قَالَ: «دَعُونِي مَا تَرَكْتُكُمْ، إِنَّمَا هَلَكَ مَنْ كَانَ قَبْلَكُمْ بِسُؤَالِهِمْ وَاخْتِلَافِهِمْ عَلَى أَنْبِيَائِهِمْ، فَإِذَا نَهَيْتُكُمْ عَنْ شَيْءٍ فَاجْتَنِبُوهُ، وَإِذَا أَمَرْتُكُمْ بِأَمْرٍ فَأْتُوا مِنْهُ مَا اسْتَطَعْتُمْ». [صحيح] - [متفق عليه]

(18) - ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው ነቢዩ ((የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል: "በተውኳችሁ ላይ ተዉኝ። ከናንተ በፊት የነበሩት ህዝቦች የጠፉት በመጠየቃቸውና ነቢያቶቻቸውን በመቃረናቸው ነው። ከአንዳች ነገር የከለከልኳችሁ ጊዜ ራቁት፤ በአንድ ትእዛዝ ያዘዝኳችሁ ጊዜ ደሞ የቻላችሁትን ያህል ከርሱ ፈፅሙ!" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## **ትንታኔ:**

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) የሸሪዓ ድንጋጌዎች ለሶስት እንደሚከፈሉ ገለፁ። እነሱም: ዝም የተባለ፣ ክልከላዎችና ትእዛዛት ናቸው።

የመጀመሪያው: አላህና ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ስለርሱ ዝም ያሉት ነው። ፍርድ ከሌለው የነገሮች መሰረቱ ግዴታ

አለመሆኑ ነው። በርሳቸው ዘመን ስለአንዳች ስላልተከሰተ ነገር መጠየቅን መተው ግዴታ ነበር። ይህም በርሳቸው ላይ ግዴታ የሚያደርግ ወይም ክልክል የሚያደርግ መመርያ እንዳይወርድ ነው። አላህ የተዋት ለባሮቹ በማዘኑ ነውና። እርሳቸው (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ከሞቱ በኋላ ግን ጥያቄው ፈታዋ በመጠየቅ መልኩ ወይም በሃይማኖቱ ጉዳይ የሚያስፈልገውን በመማር መልኩ የቀረበ ከሆነ ይህ የተፈቀደ ብቻ ሳይሆን የታዘዘበትም ጭምር ነው። ጥያቄን ተጨንቆ ፈጥሮና በግትርነት ከሆነ የጠየቀው ግን እዚህ ሐዲሥ ውስጥ መጠየቅን በመተው የተፈለገው ይህ አይነቱን ነው። ይህም በኒ ኢስራኤሎች ላይ የተከሰተው አምሳያ ወደመከሰት ስለሚያመራ ነው። ይህም ላም እንዲያርዱ በታዘዙ ወቅት ማንኛውንም የላም አይነት ቢያርዱ ትእዛዙን እንደፈፀሙ ይቆጠርላቸው ነበር። ነገር ግን እነሱ በመጠየቅ ሲያጠብቁት ትእዛዙም ጠበቀባቸው።

ሁለተኛው: ክልከላዎች ናቸው: ይህም መተዉ የሚያስመነዳ መተግበሩ የሚያስቀጣ ነው። ይህንንም ሙሉ ለሙሉ መራቅ ግዴታ ነው።

ሶስተኛው: ትእዛዝ ነው። እርሱም መስራቱ የሚያስመነዳ መተዉ የሚያስቀጣ ነው። በአቅም ልክ መተግበሩም ግዴታ ነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. አስፈላጊና አንገብጋቢ በሆነ ነገር ላይ መጠመድ ተገቢ ነው። ለጊዜው አስፈላጊ ያልሆነን ነገር መተውና ያልተከሰተን ነገር በመጠየቅ ከመጠመድ መታቀብም ተገቢ ነው።
2. ምናልባትም ጉዳዮችን ወደ መወሳሰብ የሚያደርስና ልዩነት እንዲበዛ መንስኤ የሚሆን የውዥንብርን በር የሚከፍት ጥያቄ መጠየቅ ክልክል ነው።
3. ሁሉንም ክልከላዎች በመተው መታዘዙ። ምክንያቱም መተዉ ምንም ስለማይከብድ ነው። ስለዚህም ነው ክልከላው አጠቃላይ የሆነው።
4. ትእዛዛትን መፈፀም ከአቅምና ችሎታ ጋር የተቆራኘ መሆኑን እንረዳለን። ይህም አንዳንዴ ትእዛዝን መፈፀም ሊከብድ ወይም አለመቻል ሊገጥም

ይሆናል። ስለዚህም ትእዛዝን መፈፀም የታዘዘው ከአቅም ጋር ተቆራኝቶ ሆነ።

5. ጥያቄን ማብዛት መከልከሉን እንረዳለን። ዑለማዎች መጠየቅን ለሁለት ከፍለውታል: አንደኛው: የሚያስፈልገውን ሃይማኖታዊ ጉዳይ በመማር መልኩ መጠየቅ ነው። በዚህ አላማ መጠየቅ ታዟል። የሶሐቦችም ጥያቄ በዚህ መልኩ ነበር። ሁለተኛው: ጥያቄን በመጨነቅና በግትርነት መልኩ መጠየቅ ሲሆን ይህኛው ግን የተከለከለው የመጠየቅ አይነት ነው።
6. ይህ ኡማ ከዚህ በፊት የነበሩት ህዝቦች ነቢያቸውን እንደተቃረኑት ነቢያቸውን ከመቃረን መከልከላቸውን እንረዳለን።
7. የማያስፈልግ ጥያቄ ማብዛትና ነቢያቶችን መቃረን የጥፋት ሰበብ ነው። በተለይ መልሱ የማይደረስበትን ጥያቄ መጠየቅ ለምሳሌ: ከአላህ በቀር ማንም የማያውቃቸውን የሩቅ እውቀት፣ የትንሳኤ ቀንን ሁኔታዎች መጠየቅ ይገኙበታል።
8. ከባባድ ርዕሶችን ከመጠየቅ መከልከሉ። አውዛዒ እንዲህ ብለዋል: "አላህ የእውቀትን በረከት ባሪያውን ሊነፍገው የፈለገ ጊዜ ምላሱ ላይ ጥያቄ ማብዛትን ይጥልበታል። እንደዚ አይነት ሰዎችን ትንሽ እውቀት ያላቸው ሆነው አግኝቻቸዋለሁ።" ኢብኑ ወህብ እንዲህ ብለዋል: ማሊክ እንዲህ ሲሉ ሰምቻቸዋለሁ: "እውቀትን መከራከር ከሰውዬው ቀልብ ውስጥ የእውቀትን ብርሀን ያስወግዳል።"

(4295)

(١٩) - عن عبد الله بن عمرو رضي الله عنهما أن النبي صلى الله عليه وسلم قال: «بَلِّغُوا عَنِّي وَلَوْ آيَةً، وَحَدِّثُوا عَنْ بَنِي إِسْرَائِيلَ وَلَا حَرَجَ، وَمَنْ كَذَبَ عَلَيَّ مُتَعَمِّدًا فَلْيَتَبَوَّأْ مَقْعَدَهُ مِنَ النَّارِ».
[صحيح] - [رواه البخاري]

(19) - ከዐብደሏህ ቢን ዐምር ረዲየሏሁ ዐንሁማ እንደተላለፈው ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ ብለዋል፡- "አንዷትም አንቀጽ ቢሆን ከኔ አስተላልፉ። ከቤተ እስራኤላውያንም አውሩ ችግር የለውም። ሆን ብሎ በኔ ላይ የዋሸ መቀመጫውን ከእሳት ያመቻች።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ከርሳቸው የተማርነውን ቁርአናዊም ይሁን ሐዲሣዊ እውቀት አንድ አንቀፅ ያህል ትንሽ እንኳ ቢሆን እንድናስተላልፈው አዘዙን፤ ይህም ግን የምንጣራበትንና የምናደርሰውን መልእክት ተረድተነው መሆኑ ቅድመ መስፈርቱ ነው። ከዚያም ሸሪዓችን ጋር እስካልተጋጨ ድረስ ከበኒ ኢስራኢሎች የተከሰተባቸውን ክስተትና መሰል ጉዳዮችን በተመለከተ ማውራታችንም ችግር እንደሌለው ገለፁ። ከዚያም በሳቸው ላይ መቅጠፍን አስጠነቀቁ፤ ሆን ብሎ በሳቸው ላይ የዋሸም ጀሀነም ውስጥ ማረፊያውን እንዲይዝ አሳሰቡ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. የአላህን ሸሪዓ ማስተላለፍ እንደሚበረታታና ማንኛውም ሰው የሸመደደውና የተረዳውን ትንሽም ቢሆን ማድረስ እንዳለበት፤
2. አሏህን በትክክል ለማምለክና መልዕክቱንም ለማድረስ እንዲያስችል ሸሪዓዊ እውቀትን መፈለግ ግዴታ መሆኑን፤
3. ይህ ከባድ ዛቻ ከሚመለከታቸው ሰዎች ላለመሆን ሲባል የትኛውንም ሐዲሥ ከማስተላለፋችንና ከማሰራጨታችን በፊት በትክክል ከሳቸው መሆኑን ማረጋገጥ ግዴታ እንደሆነ፤

4. ውሸት ላይ ላለመውደቅ ሲባል በተለይም በአኟህ ሸሪዓ ላይ በንግግራችን እውነተኞችና የምናወራውም የተሟላ መረጃው ያለንን ጉዳይ መሆኑ እንደሚበረታታ እንረዳለን።

(3686)

(٢٠) - عن المقدام بن معدِيْكَرِب رضي الله عنه قال: قال رسول الله صلى الله عليه وسلم: «أَلَا هَلْ عَسَى رَجُلٌ يَبْلُغُهُ الْحَدِيثُ عَنِّي وَهُوَ مُتَّكِئٌ عَلَى أَرِيكَتِهِ فَيَقُولُ: بَيْنَنَا وَبَيْنَكُمْ كِتَابُ اللهِ، فَمَا وَجَدْنَا فِيهِ حَلَالًا اسْتَحْلَلْنَاهُ، وَمَا وَجَدْنَا فِيهِ حَرَامًا حَرَّمْنَاهُ، وَإِنَّ مَا حَرَّمَ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ كَمَا حَرَّمَ اللهُ». [صحيح] - [رواه أبو داود والترمذي وابن ماجه]

(20) - አልሚቅዳም ቢን መዕዲከሪብ - አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና - እንዲህ አሉ፦ "የአላህ መልዕክተኛ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ ብለዋል፦ "አዋጅ! ከእኔ የሆነ ሐዲሥ ወደ አንዱ በአልጋው ላይ እንደተደገፈ ይደርሰውና፡ "በእኛና በእናንተ መካከል (የሚዳኘን) የአላህ መጽሐፍ ነው። በውስጡ የተፈቀደ ሆኖ ያገኘነውን (ብቻ) እንደ ሐላል እንቆጥረዋለን በውስጡም ሐራም ሆኖ ያገኘነውን (ብቻ) እንደ ሐራም እንቆጥረዋለን።" የሚልበት ወቅት ቅርብ ነው። በእርግጥ የአላህ መልክተኛ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ሐራም (እርም) ያደረጉት ማንኛውም ነገር አላህ ሐራም እንዳደረገው ነው።"" [ሶሒሕ ነው።] - [አቡዳውድ፣ ቲርሚዚና ኢብኑ ማጀህ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ከሰዎች መካከል የተወሰኑ ሰዎች አንድ ፍራሹ ላይ የተደገፈ ሰው፥ ከነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ሐዲሥ ሲደርሰው "በጉዳዮቻችን ላይ በእኛና በናንተ መካከል የሚዳኘን የተከበረው ቁርኣን ነው፤ እሱ በቂያችን ነው፤ በቁርኣን ውስጥ ያገኘነውን ሐላሎች (ፍቁድ) እንሰራበታለን፤ ቁርኣን ውስጥ ያገኘነውን ሐራሞች (እርሞች) እንርቀዋለን። " የሚልበት ዘመን እንደቀረበ ተናገሩ።

ቀጥለው ሁሉም በሱናቸው (ሀዲሳቸው) እርም ያደረጉት ወይም የከለከሉት ነገር ደረጃው ልክ አላህ በቁርኣኑ እንደከለከለው አምሳያ እንደሆነ ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን አብራሩ። ምክንያቱም እሳቸው የጌታቸውን መልዕክት አድራሽ ናቸውና።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ቁርኣን እንደሚከበረውና ከሱ ድንጋጌዎች እንደሚወሰደው ሁሉ ሱናንም ማላቅ እንደሚገባ።
2. መልክተኛውን መታዘዝ አላህን መታዘዝ ነው፤ እሳቸውንም አለመታዘዝ አላህን አለመታዘዝ ነው።
3. የሐዲሥ ማስረጃነት የፀና መሆኑና ሐዲሥን የማይቀበል ወይም የሚያወግዝ ሰው ላይ በቂ ምላሽ መሰጠቱ።
4. ከሐዲሥ በማፈንገጥ በቁርኣን ብቻ መብቃቃትን የሞገተ ሰው፥ በሁለቱም ላይ ያፈነገጠና ቁርኣንን እከተላለሁ የሚለው ሙግቱም ቅጥፈት እንደሆነ ያስረዳል።
5. የነቢዩን የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ነቢይነት ከሚጠቁሙ ነገሮች መካከል ለወደፊት ይከሰታል ብለው የተናገሩት ነገር እንደተናገሩት መከሰቱ ነው።

(65005)

(٢١) - عن عائشة وعبد الله بن عباس رضي الله عنهما قالا: لَمَّا نَزَلَ بِرَسُولِ اللَّهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ طَفِقَ يَطْرَحُ خَمِيصَةً لَهُ عَلَى وَجْهِهِ، فَإِذَا اغْتَمَّ بِهَا كَشَفَهَا عَنْ وَجْهِهِ، فَقَالَ وَهُوَ كَذَلِكَ: «لَعْنَةُ اللَّهِ عَلَى اليَهُودِ وَالنَّصَارَى، اتَّخَذُوا قُبُورَ أَنْبِيَائِهِمْ مَسَاجِدَ» يُحَذِّرُ مَا صَنَعُوا. [صحيح] - [متفق عليه]

(21) - ከእናትችን ዓኢሻና ዐብደላህ ቢን ዓባስ - (ረዲየሏሁ ዐንሁማ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ፦ "የሞት መልዐክ በአላህ መልዕክተኛ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ላይ የወረደ ጊዜ ፊታቸው ላይ ጨርቃቸውን ጣል ማድረግ ጀመሩ ፤ ሲያፍናቸው ደግሞ ይገልጧት ነበር ፤ በዚህ ሁኔታ ላይ እያሉ 'በአይሁድ እና ክርስቲያኖች ላይ የአላህ እርግማን ይውረድ ! የነቢያቶቻቸውን መቃብር መስገጃ አድርገው ያዙ።' አሉ፤ ከሰሩት ስራ እያስጠነቀቁ። '" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

እናታችን ዓኢሻና ኢብኑ ዓባስ (ረዲየሏሁ ዐንሁማ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - ነቢዩን (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ሞት የቀረባቸው ጊዜ የጨርቅ ቁራጭ ፊታቸው ላይ ጣል ያደርጉ እንደነበርና በሞት ስካር ሳቢያ ለመተንፈስ ያስቸገራቸው ጊዜም ከፊታቸው ያስወግዱት እንደነበር ነገሩን። በዚህ ከባድ ሁኔታ ላይ እያሉ አላህ አይሁድና ክርስቲያኖችን እንደረገመ፤ ከእዝነቱም እንዳራቀ፤ ይህም በነቢያቶቻቸው መቃብር ላይ መስገጃ በመገንባታቸው ምክንያት መሆኑን ነገሩን። የጉዳዩ አደገኛነት ከባድ ባልነበር በእንደዚ አይነት ሁኔታ ላይ ሆነው አይጠቅሱትም ነበር። ስለዚህም ይህ የአይሁዶችና ክርስቲያኖች ድርጊት እንዲሁም በአላህ ላይ ወደ ማጋራት የሚያዳርስ ነውና ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) በዚህ መሰል ድርጊቶች ላይ ከነርሱ ጋር መመሳሰልን ከለከሉ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. የነቢያቶችንና ደጋጎችን መቃብር ለአላህ የሚሰገድበት መስገጃ አድርጎ መያዝ ወደ ሺርክ የሚያዳርስ ስለሆነ መከልከሉን እንረዳለን።

2. የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) በተውሒድ ላይ ያላቸው ትኩረትና ጥንቃቄ የበረታ መሆኑንና መቃብርን ማላቅም ወደ ሺርክ ስለሚያዳርስ መስጋታቸውን እንረዳለን።
3. አይሁዶችንና ክርስቲያኖችን መርገም እንዲሁም ቀብር ላይ በመገንባትና መቃብርን መስገጃ አድርጎ በመያዝ የነርሱን ድርጊት አምሳያ የሰራን ሰውም መርገም እንደሚፈቀድ እንረዳለን።
4. በመቃብር ላይ መገንባት የአይሁዶችና ክርስቲያኖች ሱና መሆኑንና ሐዲሡ ከነርሱ ጋር መመሳሰልንም ይከለክላል።
5. መስገጃ ባይገነባበት እንኳ እርሱ ዘንድ መስገድና ወደርሱ ዙሮ መስገድ መቃብርን መስገጃ አድርጎ መያዝ ውስጥ ይካተታል።

(3330)

(٢٢) - عن أبي هريرة رضي الله عنه عن النبي صلى الله عليه وسلم: «اللَّهُمَّ لا تجعل قبري وثنًا، لعن الله قومًا اتخذوا قبور أنبيائهم مساجد». [صحيح] - [رواه أحمد]

(22) - አቢ ሁረይራ ረዲየሏሁ ዐንሁ ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ ማለታቸውን አስተላልፏል፡ "አሏህ ሆይ! ቀብሬን ጣኦት አታድርግብኝ፤ የነቢያቶቻቸውን መቃብር መስገጃ አድርገው በያዙ ህዝቦች ላይ የአሏህ እርግማን ሰፈነባቸው።" [ሶሒሕ ነው።] - [አሕመድ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ቀብራቸውን በማላቅና የሱጁድ አቅጣጫውን ወደዛው በማድረግ ሰዎች እንደሚያመልኩት ጣኦት እንዳያደርግባቸው አምላካቸውን ተማፀኑ፤ ከዚያም የነቢያቶችን መቃብር የአምልኮ ስፍራ አድርገው በሚይዙ ላይ የአሏህ እርግማን እንደሰፈነባቸውና ከእዝነቱም እንዳባረራቸው አሳወቁ። ምክንያቱም መቃብሩን የአምልኮ ስፍራ አድርጎ መያዝ የቀብሩን ባለቤት እንዲመለክ ለማድረግና በተቀበረበት አካል ዙርያ አጉል እምነት ለማሳደር መዳረሻ ነውና።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. የነብያትና የጻድቃን ሰዎች መቃብርን በተመለከተ ሸሪዓው ያስቀመጠውን ገደብ ማለፉ ከአላህ ሌላ የሚመለኩ ጣኦት እንዲሆኑ ስለሚያደርጋቸው ወደ ሽርክ (ሽርክ) ከሚመሩ መንገዶች መጠንቀቅ እንደሚገባ፤
2. የተቀበረበት አካል ወደ አሏህ ምንም አይነት ቅርበት ቢኖረውም ቀብሩን ለማላቅም ይሁን በመቃብሩ አሏህን ለማምለክ ማለም እንደማይፈቀድ፤
3. መስገጃን መቃብር ላይ መገንባት የተከለከለ መሆኑን፤
4. ሶላተል ጀናዛ ላልተሰገደበት ሰው ሊሰግዱበት ካልሆነ በቀር መስጂድ ባይገነቡም መቃብር ዘንድ መስገድ የተከለከለ መሆኑን እንረዳለን።

(3336)

(٢٣) - عن أبي هريرة رضي الله عنه قال: قال رسول الله صلى الله عليه وسلم: «لَا تَجْعَلُوا بُيُوتَكُمْ قُبُورًا، وَلَا تَجْعَلُوا قَبْرِي عِيدًا، وَصَلُّوا عَلَيَّ؛ فَإِنَّ صَلَاتَكُمْ تَبْلُغُنِي حَيْثُ كُنْتُمْ».

[حسن] - [رواه أبو داود]

(23) - አቡ ሁረይራ ረዲየሏሁ ዐንሁ እንዲህ ብለዋል: የአሏህ መልዕክተኛ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ ብለዋል፡ "ቤቶቻችሁን መቃብር አታድርጉ! ቀብሬንም የሚጎበኝ የበአል ስፍራ አታድርጉት! ይልቅ በኔ ላይ ሶለዋት አውርዱ! የትም ብትሆኑ ሶለዋታችሁ ትደርሰኛለችና።" [ሐሰን ነው።] - [አቡዳውድ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ቤቶችን እንደ መቃብር ከሶላት የተገለሉ እና ሶላት የማይሰገድባቸው ከማድረግ እየከለከሉ ነው። እንዲሁም ልማድ አድርጎ በመያዝ የሳቸውን ቀብር ደጋግሞ መጎብኘቱንም እዚያው መሰብሰቡም ወደ ሽርክ ስለሚያደርስ ከለከሉ። ከዛ ይልቅ ወደ ቀብራቸው መመላለስ ሳያስፈልግ ቅርብም ይሁን ሩቅ እኩል ለእርሳቸው

ስለሚደርሳቸው ከየትኛውም ቦታ ሆነን በሳቸው ላይ ሶለዋት እንድናወርድ አዘዙን።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ቤቶች አሏህን ከማምለክ መገለላቸው የተከለከለ መሆኑ፤
2. የነቢዩን የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ቀብር ለመዘየር አስቦ ጉዞ መውጣት መከልከሉን፤ ምክንያቱም ሶለዋት በሳቸው ላይ እንድናወርድና እንደሚደርሳቸውም ነግረውናልና። በአምልኮ መንፈስ ጉዞ የሚወጣው ወደ መስጂዱ ለመሄድና እዛው ለመስገድ ከሆነ ብቻ ነው።
3. በተለየ መልኩና በተለየ ጊዜ የርሳቸውን ቀብር ደጋግሞ መጎብኘትን ልምድ አድርጎ መያዝ መከልከሉ፤ የሌላን ቀብርም ቢሆን እንደዚሁ የተከለከለ ነው።
4. የላቀው አሏህ ከየትኛውም ቦታና በማንኛውም ጊዜ በሳቸው ላይ ሶለዋት ማውረድን መደንገጉ ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን አምላካቸው ዘንድ ያላቸውን ከፍተኛ ደረጃ ያሳያል።
5. መቃብር ዘንድ መስገድ መከልከሉ ሶሓቦች ዘንድ የፀና ጉዳይ በመሆኑ ነቢዩም የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ባልደረቦቻቸው ቤቶቻቸውንም እንደመቃብሩ የማይሰገድበት እንዳያደርጉ ከለከሏቸው።

(3350)

(٢٤) - عَنْ عَائِشَةَ أُمِّ المؤمنين رضي الله عنها: أَنَّ أُمَّ سَلَمَةَ ذَكَرَتْ لِرَسُولِ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ كَنِيسَةً رَأَتْهَا بِأَرْضِ الْحَبَشَةِ، يُقَالُ لَهَا مَارِيَةُ، فَذَكَرَتْ لَهُ مَا رَأَتْ فِيهَا مِنَ الصُّوَرِ، فَقَالَ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ: «أُولَئِكَ قَوْمٌ إِذَا مَاتَ فِيهِمُ الْعَبْدُ الصَّالِحُ، أَوِ الرَّجُلُ الصَّالِحُ، بَنَوْا عَلَى قَبْرِهِ مَسْجِدًا، وَصَوَّرُوا فِيهِ تِلْكَ الصُّوَرَ، أُولَئِكَ شِرَارُ الْخَلْقِ عِنْدَ اللهِ». [صحيح] - [متفق عليه]

(24) - የአማኞች እናት ከሆነችው ከዓኢሻ (ረዲየሏሁ ዐንሃ) - አላህ መልካም ሥራዋን ይውደድላትና - እንደተላለፈው፡- ኡሙ ሰላማ ለአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) በሀበሻ ምድር ማሪያህ በምትባል ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስላየቻቸው ምስሎች ነገረቻቸው። የአላህ መልዕክተኛም ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንዲህ አሉ፡- "እነዚህ ከመካከላቸው መልካም (ጻድቅ) ባርያ ወይም መልካም ሰው ሲሞት በመቃብሩ ላይ መስገጃን የሚገነቡ፤ በውስጡም (ምስሉን) ስእላ ስእል የሚቀርፁ ናቸው። እነዚህ ህዝቦች አላህ ዘንድ እጅግ ክፉ (መጥፎ) ፍጡራን ናቸው።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

የአማኞች እናት ኡሙ ሰለማ (ረዲየሏሁ ዐንሃ) - አላህ መልካም ሥራዋን ይውደድላትና - በሐበሻ ምድር ማሪያህ የምትባል ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስእሎች፣ ጌጦችና ቅርፆች ማየቷን በመደነቅ ለነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) አወሳች። ነቢዩም (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) የነዚህን ስእሎች መደረግ ምክንያት ገለፁ። "እነዚህ አሁን አንቺ የምታወሺያቸው በመካከላቸው ደግ ሰው የሞተ ጊዜ በቀብሩ ላይ መስጂድ ይገነቡና በውስጡ ይሰግዱበታልም እነዚህንም ስእሎች ይስላሉ።" አሉ። ይህንን የሚፈጽም ሰው አላህ ዘንድ ክፉ ፍጡር እንደሆነ ገለፁ፤ ምክንያቱም ይህ ድርጊቱ በአላህ ወደ ማጋራት ስለሚያዳርስ ነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ወደ ሺርክ የሚያደርስን መንገድ ለመዝጋት ሲባል በመቃብሮች ላይ መስጊዶች መገንባት ወይም እርሷ ዘንድ መስገድ ወይም መስጊድ ውስጥ ሟቾችን መቅበር ክልክል ነው።
2. መቃብሮች ላይ መስጇዶችን መገንባትና ስእሎችን መስጅድ ውስጥ መስቀል የአይሁድና ክርስቲያኖች ስራ መሆኑንና ይህንን የፈፀመም ከነርሱ ጋር መመሳሰሉን እንረዳለን።
3. ነፍስ ያላቸውን ነገሮች ስእል መያዝ ክልክል መሆኑ።
4. ቀብር ላይ መስጂድ የገነባ፣ መስጂድ ውስጥም (ነፍስ ያላቸው) ስእሎችን የሳለ ሰው ከክፉዎቹ የአላህ ፍጡሮች መካከል ነው።
5. ሸሪዓ ወደ ሺርክ የሚያደርሱ መንገዶችን ባጠቃላይ በመዝጋቱ ሸሪዓ የተውሒድን ዳር ድንበር ሙሉ ለሙሉ መጠበቁን እንረዳለን።
6. በደጋጎች ላይ ወሰን ማለፍ ሺርክ ላይ ለመውደቅ ምክንያት ስለሆነ ክልክል ነው።

(10887)

(٢٥) - عن جندب رضي الله عنه قال: سمعت النبي صلى الله عليه وسلم قبل أن يموت بخمسٍ وهو يقول: «إني أبرأ إلى الله أن يكون لي منكم خليلٌ، فإن الله تعالى قد اتخذني خليلًا، كما اتخذ إبراهيم خليلًا، ولو كنت متخذًا من أمتي خليلًا لاتخذت أبا بكر خليلًا، ألا وإن من كان قبلكم كانوا يتخذون قبور أنبيائهم وصالحيهم مساجد، ألا فلا تتخذوا القبور مساجد، إني أنهاكم عن ذلك». [صحيح] - [رواه مسلم]

(25) - ጁንዱብ ረዲየሏሁ ዐንሁ እንዲህ ብለዋል፡ "ነብዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) ከመሞታቸው አምስት (ሌሊቶች) በፊት እንዲህ ሲሉ ሰምቻቸዋለሁ፡- ' እኔ ከናንተ መካከል ፍፁም ወዳጅ ከመያዝ ወደ አላህ እጥራራለሁ። ምክንያቱም የላቀው አሏህ ኢብራሂምን ፍፁም ወዳጅ አድርጎ እንደያዘው ሁሉ እኔንም ፍፁም ወዳጅ አድርጎ ይዞኛልና። ከኡመቴ ፍፁም ወዳጅ አድርጌ የምይዝ ብሆን ኖሮ አቡበከርን ነበር ፍፁም ወዳጅ አድርጌ የምይዘው። አዋጅ! እነዚያ ከናንተ በፊት የነበሩት የነብያቶቻቸውንና የፃድቃኖቻቸውን መቃብር መስገጃ ስፍራ አድርገው ይይዙ ነበር። አዋጅ! መቃብርን መስገጃ ስፍራ አድርጋችሁ አትያዙ! እኔ እየከለከልኳችሁ ነው።'" [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን በአላህ ዘንድ ያላቸው ደረጃ አሳወቁ፤ ልክ እንደ ኢብራሂም ዐለይሂ ሰላም እሳቸውም ላእላይ እርከን የደረሰ ውዴታ መጎናፀፋቸውንም ተናገሩ። ከአሏህ ውጭ ፍፁም ወዳጅ ሊኖራቸው እንደማይችል ገለፁ። ምክንያቱም ልባቸው በአላህ ውዴታ፣ ማላቅና ማወቅ ተሞልቷልና ከአላህ ውጪ ለሳቸው ሌላ ፍፁም ወዳጅ ሊኖራቸው አይችልም። ከፍጡራን ፍፁም ወዳጅ የሚይዙ ቢሆኑ ኖሮ ያ ሰው አቡበከር አስሲዲቅ አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና ይሆን ነበር። ከዚያም አይሁዶችና ክርስቲያኖች የነቢያቶቻቸውና የፃድቃኖቻቸው መቃብር ከአላህ ውጪ ወደምትመለክ ጣኦታዊ የአምልኮ ስፍራ እስክትለወጥ እንዲሁም

መስገጃና ቤተ መቅደሶችን መቃብሮቻቸው ላይ በመገንባት የፈፀሙትን ልክ ያለፈ የውዴታ ድንበር ማለፍ  አስጠነቀቁ። አስከትለውም ኡመታቸውም የነሱን አይነት ድርጊት እንዳይፈፅሙ ከለከሉ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. አቡበክር ሲዲቅ ረዲየሏሁ ዐንሁ ያላቸውን በላጭነት፤ ከሶሓቦችም ሁሉ በላጩ እርሳቸው መሆናቸውን፤ ከረሱል ዐለይሂ ሶላቱ ወሰላም በኋላ በርሳቸው የመሪነት ቦታ ለመተካት ይበልጥ የተገቡትም እርሳቸው መሆናቸውን፤
2. በመቃብር ላይ መስገጃ መገንባት ያለፉት ህዝቦች ከሚፈፅሟቸው ውግዝ ተግባራት መካከል መሆኑ፤
3. ወደ ሽርክ ሊያደርስ ስለሚችል መቃብርን የአምልኮ ስፍራ አድርጎ መያዝ፣ በውስጧም ሆነ ወደሷ ዞሮ መስገድ፣ ወይም በላያቸው ላይ መስገጃ ወይም ጉልላት መስራት ክልክል መሆኑ፤
4. ወደ ሽርክ ሊያደርስ ስለሚችል በፃድቃን ላይ ድንበር ከማለፍ መጠንቀቅን፤
5. ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) ከመሞታቸው አምስት ቀናት ቀደም ብለው ማስጠንቀቃቸው ያስጠነቀቁት ጉዳይ ያለውን አሳሳቢነት እንደሚያሳይ እንረዳለን።

(3347)

(٢٦) - عن أبي الهيَّاج الأسدي قال: قَالَ لِي عَلِيُّ بْنُ أَبِي طَالِبٍ: أَلَا أَبْعَثُكَ عَلَى مَا بَعَثَنِي عَلَيْهِ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ؟ أَنْ لَا تَدَعَ تِمْثَالًا إِلَّا طَمَسْتَهُ، وَلَا قَبْرًا مُشْرِفًا إِلَّا سَوَّيْتَهُ.
[صحيح] - [رواه مسلم]

(26) - ከአቢል ሀያጅ አልአሰዲይ እንደተላለፈው እንዲህ አለ: "ዐሊይ ቢን አቢ ጧሊብ ለኔ እንዲህ አለኝ: 'የአላህ መልክተኛ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም በላኩኝ ነገር ላይ ልላክህን? ማንኛውም ምስልን (ስታገኝ) ያስወገድከው ቢሆን እንጂ ላትተወው ነው፤ ማንኛውም ከፍ ያለ ቀብርንም ያስተካከልከው ቢሆን እንጂ ላትተወው ነው።'" [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ሶሓቦቻቸውን "ምስልን" (እሱም አካል ይኑረውም አይኑረው የነፍስ ያለው ነገር ምስል ነው።) ያስወገዱት ወይም ያወደሙት ቢሆን እንጂ እንዳይተዉት ይልኩ ነበር።

ከፍ ያለ ቀብርንም ከምድር ጋር እኩል ያደረጉትና በላዩ ላይ የተገነባውንም ያወደሙ ወይም ከመሬት ብዙም ከፍ ሳይል አንድ ስንዝር ብቻ ከፍ በማድረግ ያስተካከሉት ቢሆን እንጂ እንዳይተዉት ይልኩ ነበር።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ነፍስ ያላቸው ነገራቶችን ምስል ማድረግ ወደ ሺርክ ስለሚያዳርስ ክልክል መሆኑን እንረዳለን።
2. ስልጣን ወይም አቅም ላለው ሰው መጥፎን ነገር በእጅ ማስወገዱ መደንገጉን ፤
3. ስዕላ ስእሎች፣ ቅርፃ ቅርፆችና ቀብር ላይ መገንባትን የመሳሰሉ ወደ ጃሂሊያ ዘመን ፈለጎች የሚጠቁሙ ነገሮችን ሁሉ በማስወገድ ላይ የነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለምን ጉጉት እንረዳለን።

(5934)

(٢٧) - عَنْ عَبْدِ اللهِ بْنِ مَسعودٍ رضي الله عنه عن رَسولِ اللهِ صلى الله عليه وسلم قال: «الطِّيَرَةُ شِرْكٌ، الطِّيَرَةُ شِرْكٌ، الطِّيَرَةُ شِرْكٌ، -ثلاثًا-»، وَمَا مِنَّا إِلَّا، وَلَـكِنَّ اللهَ عَزَّ وَجَلَّ يُذْهِبُهُ بِالتَّوَكُّلِ.
[صحيح] - [رواه أبو داود والترمذي وابن ماجه وأحمد]

(27) - ከዐብደላህ ቢን መስዑድ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል፡- "'የገድ እምነት ሺርክ ነው። የገድ እምነት ሺርክ ነው። የገድ እምነት ሺርክ ነው። (አሉ ሶስት ጊዜ)' ከኛ መካከል በልቡ የገድ እምነት የሚመጣበት እንጂ አንድም የለም። ነገር ግን አላህ በርሱ ላይ በመመካታችን ምክንያት ያስወግደዋል።" [ሶሒሕ ነው።] - [አቡዳውድ፣ ቲርሚዚ፣ ኢብኑማጀህና አሕመድ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ከገድ እምነት አስጠነቀቁ። እርሱም: በሚሰማም ይሁን በሚታይ ነገር፤ በበራሪም ሆነ በእንስሳም ሆነ በህመምተኞች (አካል ጉዳተኞች)፤ በቁጥሮችም ሆነ በቀናት ወይም ከነዚህ ውጪ ባሉ ማንኛውም ነገርም ቢሆን ገደ ቢስነትን ማመን ነው። ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) በራሪን የጠቀሱት ጃሂሊዮች ዘንድ የታወቀ ስለሆነ ነው። የዚህ ስራ መሰረቱም ጉዞ ወይም ንግድ ወይም ከዚህ ውጪ ያሉ ስራዎችን ለመጀመር ሲሉ በራሪን ይለቁና ወደ ቀኝ አቅጣጫ ከበረረ ገድ አለኝ ብሎ ወደ ፈለገበት ጉዳይ ይሄዳል። ወደ ግራ አቅጣጫ ከበረረ ደግሞ ገደ ቢስ ነኝ ብሎ ያሰበውን ጉዳይ ከመፈፀም ይቆጠባል። ይህ ነገር ሺርክ መሆኑንም ተናገሩ። ገደቢስነትን ማመን ሺርክ የሆነውም መልካምን ከአላህ በቀር የሚያመጣ ስለሌለና፤ መጥፎንም ብቸኛና አጋር ከሌለው አላህ በቀር የሚከላከል ስለሌለ ነው።

ኢብኑ መስዑድ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - በሙስሊም ቀልብ ውስጥ አንዳች ገደቢስ እምነት ሊከሰት

እንደሚችል፤ ነገር ግን ሰበቡን ከማድረስ ጋር በአላህ ላይ በመመካት ማስወገድ እንዳለበት ገለፀ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. የገድ እምነት ውስጥ ከአላህ ውጪ በሆነ አካል ላይ ልብን ማንጠልጠል ስላለ ሺርክ ነው።
2. አንገብጋቢ ጉዳዮች ልብ ውስጥ እንዲሸመደዱና እንዲፀኑ ሲባል መደጋገም ወሳኝ እንደሆነ እንረዳለን።
3. የገድ እምነትን በአላህ ላይ መመካት ያስወግደዋል።
4. ብቸኛ በሆነው አላህ ላይ መመካት መታዘዙንና ልብም በርሱ ላይ መንጠልጠል እንዳለበት እንረዳለን።

(3383)

(٢٨) - عن عمران بن حصين رضي الله عنه قال: قال رسول الله صلى الله عليه وسلم: «لَيْسَ مِنَّا مَنْ تَطَيَّرَ أَوْ تُطُيِّرَ لَهُ، أَوْ تَكَهَّنَ أَوْ تُكُهِّنَ لَهُ، أَوْ سَحَرَ أَوْ سُحِرَ لَهُ، وَمَنْ عَقَدَ عُقْدَةً، وَمَنْ أَتَى كَاهِنًا فَصَدَّقَهُ بِمَا يَقُولُ فَقَدْ كَفَرَ بِمَا أُنْزِلَ عَلَى مُحَمَّدٍ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ». [حسن] - [رواه البزار]

(28) - ከዒምራን ቢን ሑሰይን -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: "የአላህ መልክተኛ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንዲህ ብለዋል: 'የገድ ተግባርን የፈፀመ ወይም ለሱ የተፈፀመለት፣ ወይም የጠነቆለ ወይም ያስጠነቆለ፣ ወይም የደገመ ወይም ያስደገመ፣ ትብታብንም የተበተበ ከኛ አይደለም። ጠንቋይ ዘንድ የሄደና የሚናገረውን ነገር አምኖ የተቀበለ በሙሐመድ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ላይ በወረደው ነገር በእርግጥ ክዷል።'" [ሐሰን ነው።] - [በዛር ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም በኡመታቸው ውስጥ አንዳንድ ተግባራት የፈፀሙ ሰዎችን "ከኛ አይደሉም!" በማለት ዛቱ። ከተግባራቱም:-

የመጀመሪያው: "ገድ ተግባር የፈፀመ ወይም ለሱ የተፈፀመለት" የዚህ አመለካከት መሰረት:- ጉዞ ወይም ንግድ ወይም ከዚህ ውጪ ያለን ስራ ለመጀመር በራሪን ይለቃል፤ በራሪው ወደ ቀኝ አቅጣጫ ከበረረ ተስፋን በመሰነቅ ወደ ሚፈልገው አላማ ይሄዳል። ወደ ግራ አቅጣጫ ከበረረ ገደ ቢስነትን በማመን የሚፈልገውን አላማ ከመፈፀም ይቆጠባል። ይህን ተግባር ራሱም ይሁን ለርሱ የሚሰራለትን በመመደብም መፈፀም አይፈቀድም። በማንኛውም በራሪዎች ወይም እንስሳዎች ወይም በአካል ጉዳተኞች ወይም በቁጥሮች ወይም በቀናት ወይም ከዚህ ውጪ ባሉ በሚሰማም ይሁን በሚታይ በሆነ ነገር ገደ ቢስነትን ማመን እዚህ ውስጥ ይካተታል።

ሁለተኛው: "የጠነቆለ ወይም ያስጠነቆለ።" ከዋክብትንና ሌሎች ነገሮችን በመጠቀም የሩቅ እውቀትን የሞገተ ሰው ወይም እንደ ጠንቋይና የመሳሰሉት የሩቅን እውቀት ወደ ሚሞግቱ ሰዎች የሄደና የሩቅን እውቀት ሞግቶ በሚናገረው ያመነ በሙሐመድ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ላይ በወረደው በርግጥ ክዷል።

ሶስተኛ: "የደገመ ወይም የተደገመለት" እሱም አንድን ሰው ሊጠቅም ወይም ሊጎዳ የድግምትን ተግባር በራሱ የፈፀመ ወይም ለሱ ድግምት የሚሰራለትን የመደበ ሰው ወይም ትብታብን ተብትቦ የቋጠረና ክልክል የሆኑ መነባንቦችን በማነብነብና እርሱ ላይ በመትፋት የደገመበት ሰው ነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. በአላህ ላይ መመካትና በአላህ ውሳኔና ፍርድ ማመን ግዴታ መሆኑን፤ የገድ፣ የገደቢስነት፣ የጥንቆላ ፣ የድግምት እምነት ወይም ባለቤቶቹን ስለነዚህ ጉዳይ መጠየቅ ክልክል መሆኑን እንረዳለን።
2. የሩቅ እውቀትን መሞገት ተውሒድን የሚፃረር የሆነ ሺርክ ነው።
3. ጠንቋዮችን ማመንም ወደነርሱ መሄድም ክልክል ነው። እንዲሁ ለማወቅ በሚል ሰበብ ብቻ እንኳ መዳፍና ሲኒን ማንበብ፣ ኮኮብ ማየት ከጥንቆላ ውስጥ ይካተታል።

(5981)

(٢٩) - عَنْ أَنَسِ بْنِ مَالِكٍ رضي الله عنه عَنِ النَّبِيِّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ قَالَ: «لَا عَدْوَى، وَلَا طِيَرَةَ، وَيُعْجِبُنِي الْفَأْلُ» قَالَ قِيلَ: وَمَا الْفَأْلُ؟ قَالَ: «الْكَلِمَةُ الطَّيِّبَةُ». [صحيح] - [متفق عليه]

(29) - ከአነስ ቢን ማሊክ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል: "በራሱ የሚተላለፍ ተላላፊ በሽታ የለም፣ ገድም የለም ተስፈኘነት (በጎ ምኞት) ግን ያስደስተኛል።" "አልፈእል (በጎ ምኞት) ምንድነው?" ተባሉ። እርሳቸውም "መልካም ንግግር ነው።" አሉ። [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) በሽታ ከአንዱ ወደ ሌላው ያለ አላህ ውሳኔ በራሱ ይተላለፋል የሚለው የድንቁርና ዘመን ሰዎች ያምኑት የነበረው እምነት የተሳሳተ ከንቱ እምነት መሆኑን ተናገሩ። የገድ እምነትም ከንቱ አጉል እምነት ነው። እርሱም በማንኛውም የሚሰማ ወይም የሚታይ ወፍ ወይም እንስሳ ወይም አካል ጉዳተኞችን ወይም ቁጥሮች ወይም ቀናት ወይም ከዚህ ውጪ ባሉ ነገሮች ላይ ተመርኩዞ ገደቢስነትን ማመን ነው። ወፍን ያወሱት በድንቁርና ዘመን የታወቀው ገድ ማለት በርሱ ስለነበር ነው። መሰረቱም ስራ ወይም ጉዞ ወይም ንግድ ወይም ከዚህ ውጪ ያለ ጉዳይ ሊጀምሩ ሲፈልጉ ወፍን ይለቃል። ወፊቱ ወደ ቀኝ ከበረረች ጥሩ ገድ በማመን ወደፈለገው ይጓዛል። ወደ ግራ አቅጣጫ ከበረረች ደግሞ ገደቢስነትን በማመን ከፈለገው ጉዳይ ይቆጠባል። ቀጥለውም ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) "አልፈእል" (በጎ ምኞት) እንደሚያስደስታቸው ተናገሩ። እርሱም የሰው ልጅ ከሰማው መልካም ቃል አንፃር የሚያጋጥመው የደስታና ሀሴት ስሜት ነው። ይህም በጌታው ላይ መልካም እሳቤ እንዲኖረው ያደርጋልና።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ከአላህ በቀር መልካምን የሚያመጣና ከአላህ በቀርም መጥፎን የሚከላከል ስለሌለ በአላህ ላይ መመካት እንደሚገባ እንረዳለን።
2. የገድ እምነት መከልከሉን እንረዳለን። እርሱም ሰው ገድ የሚልበትና ከስራ የሚያቅበው ነገር ነው።
3. "አልፈእል" ከተከለከለው የገድ እምነት መካከል አይደለም። ይልቁንም ያ በአላህ ላይ መልካም እሳቤ ማሳደር ነው።
4. ሁሉም ነገር በብቸኛውና አጋር በሌለው በአላህ ውሳኔ ነው የሚከሰተው።

(3422)

(٣٠) - عَنْ زَيْدِ بْنِ خَالِدٍ الجُهَنِيِّ رضي الله عنه أَنَّهُ قَالَ: صَلَّى لَنَا رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ صَلَاةَ الصُّبْحِ بِالْحُدَيْبِيَةِ عَلَى إِثْرِ سَمَاءٍ كَانَتْ مِنَ اللَّيْلَةِ، فَلَمَّا انْصَرَفَ أَقْبَلَ عَلَى النَّاسِ، فَقَالَ: «هَلْ تَدْرُونَ مَاذَا قَالَ رَبُّكُمْ؟» قَالُوا: اللهُ وَرَسُولُهُ أَعْلَمُ، قَالَ: «أَصْبَحَ مِنْ عِبَادِي مُؤْمِنٌ بِي وَكَافِرٌ، فَأَمَّا مَنْ قَالَ: مُطِرْنَا بِفَضْلِ اللهِ وَرَحْمَتِهِ، فَذَلِكَ مُؤْمِنٌ بِي وَكَافِرٌ بِالْكَوْكَبِ، وَأَمَّا مَنْ قَالَ: بِنَوْءِ كَذَا وَكَذَا، فَذَلِكَ كَافِرٌ بِي وَمُؤْمِنٌ بِالْكَوْكَبِ». [صحيح] - [متفق عليه]

(30) - ዘይድ ቢን ኻሊድ አልጁሀኒይ -አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና- እንዲህ አሉ፦ የአላህ መልክተኛ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን በሑደይቢያ ምሽት የዘነበን ዝናብ አስከትለው የንጋትን ሰላት አሰገዱን። ሰላቱን ያጠናቀቁ ጊዜም ወደ ሰዎች በመዞር እንዲህ አሉ "ጌታችሁ ምን እንዳለ ታውቃላችሁን?" ሰሓቦችም "አላህና መልክተኛው ያውቃሉ" አሉ። እርሳቸውም አላህ እንዲህ አለ፦ "ከባሮቼ በኔ ያመነም የካደም ሆኖ ያነጋ አለ። በአላህ ችሮታና እዝነት ምክንያት ዘነበልን ያለ በኔ ያመነ በከዋክብት የካደ ነው። በእንዲህ እንዲህ የኮኮብ እንቅስቃሴ ምክንያት ዘነበልን ያለ ደግሞ በኔ የካደና በከዋክብት ያመነ ነው።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን በሑደይቢያ (መካ አቅራቢያ የምትገኝ መንደር ናት) የንጋት (የሱቢሕ) ሰላትን በዛ ምሽት ዝናብ ከዘነበ በኋላ አሰገዱ። ሰላቱን በማሰላመት ያጠናቀቁ ጊዜ ፊታቸውን ወደ ሰዎች በመዞር "የተከበረውና የላቀው ጌታቸሁ ምን እንዳለ ታውቃላችሁን?" በማለት ጠየቋቸው። ሰሓቦችም አላህና መልክተኛው ያውቃሉ በማለት መለሱላቸው። እርሳቸውም እንዲህ አሉ፦ " ከፍ ያለው አላህ ሰዎች ዝናብ በሚዘንብ ወቅት ለሁለት እንደሚከፈሉ ገለፁ። አንዱ ክፍል በአላህ አማኝ የሆነ ክፍል ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በአላህ ከሀዲ የሆነ ክፍል ነው።" በአላህ ችሮታና እዝነት ዘነበልን በማለት የዝናብን መውረድ ወደ አላህ ያስጠጋ ሰው ይህ ፈጣሪና የዩንቨርሱ አስተናባሪ በሆነው አላህ ያመነ በከዋክብት ደግሞ የካደ መሆኑን፤ በእንዲህ እንዲህ ኮኮብ ዘነበልን ያለ ደግሞ በአላህ የካደና በከዋክብት ያመነ መሆኑን ገለፀ። ይህ ክህደት የዝናብን መውረድ ወደ ከዋክብት ከማስጠጋቱ አንፃር ትንሹ ኩፍር ነው። ምክንያቱም አላህ በሸሪዐም ሆነ በውሳኔ ዝናብ ለመዝነብ ሰበብ አላደረገውምና ነው። የዝናብን መውረድና ሌሎች ምድራዊ ክስተቶችን ከዋክብት ለመውጣትና ለማረፍ (ለመውደቅ) ወደሚያደርጉት እንቅስቃሴ ያስጠጋና ከዋክብት ትክክለኛ አስተናባሪ መሆናቸውን ያመነ ትልቁን ክህደት የካደ ይሆናል።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ከዝናብ መውረድ በኋላ፦ በአላህ ችሮታና እዝነት ዘነበልን ማለት እንደሚወደድ።
2. የዝናብ መውረድና ሌሎችን ፀጋዎች መፍጠሩንም ሆነ ማስገኘቱን ወደ ከዋክብት ያስጠጋ ትልቁን ክህደት የካደ ሲሆን ወደ ከዋክብት በሰበብ ደረጃ ካስጠጋ ደግሞ ትንሹን ክህደት የካደ ይሆናል። ምክንያቱም ሸሪዐዊም ሆነ ህዋሳዊ ሰበብ አይደለምና።

3. አንድ ፀጋ በተካደ ጊዜ የክህደት ምክንያት ሲሆን፤ ተገቢ ምስጋና ከቀረበበት ደግሞ የኢማን ምክንያት ይሆናል።
4. የሽርክን መዳረሻ ለመዝጋት ሲባል ወቅቱን ለመግለፅ ተፈልጎበት ቢሆን እንኳን "በእንዲህ ኮኮብ እንቅስቃሴ ምክንያት ዘነበልን" ማለት መከልከሉ፤
5. ፀጋን በማምጣትና መአትን በመከላከል ረገድ ቀልብን በአላህ ላይ ማንጠልጠል ግዴታ መሆኑን ተረድተናል።

(65010)

(٣١) - عَنْ عُقْبَةَ بْنِ عَامِرٍ الْجُهَنِيِّ رضي الله عنه: أَنَّ رَسُولَ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ أَقْبَلَ إِلَيْهِ رَهْطٌ، فَبَايَعَ تِسْعَةً وَأَمْسَكَ عَنْ وَاحِدٍ، فَقَالُوا: يَا رَسُولَ اللهِ، بَايَعْتَ تِسْعَةً وَتَرَكْتَ هَذَا؟ قَالَ: «إِنَّ عَلَيْهِ تَمِيمَةً»، فَأَدْخَلَ يَدَهُ فَقَطَعَهَا، فَبَايَعَهُ، وَقَالَ: «مَنْ عَلَّقَ تَمِيمَةً فَقَدْ أَشْرَكَ».

[حسن] - [رواه أحمد]

(31) - ከዑቅባህ ቢን ዓሚር አልጁሀኒይ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) -አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው፦ "ወደ አላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) የተወሰኑ ሰዎች መጡ። ከዘጠኙ ጋር ቃልኪዳን ተጋቡና ከአንዱ ጋር ቃልኪዳን ከመጋባት ተቆጠቡ። ሶሐቦችም 'የአላህ መልክተኛ ሆይ! ከዘጠኙ ጋር ቃልኪዳን ተጋብተው ይህንን ለምን ተዉ?' አሉ። እርሳቸውም 'እርሱ ላይ ሒርዝ ስላለ ነው።' አሉ። (ይህንን ሲሰማ) እጁን አስገባና ቆረጠው። እርሳቸውም ቃልኪዳን ተጋቡትና 'ሒርዝ ያንጠለጠለ ሰው በርግጥም አጋርቷል!' አሉ።" [ሐሰን ነው።] - [አሕመድ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

የተወሰኑ ጭፍሮች ወደ ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) መጡ። ብዛታቸውም አስር ነበሩ። ከነርሱ መካከል ከዘጠኙ ጋር በኢስላም ላይና እርሳቸውን በመከተል ላይ ቃል ተጋቡና ከአስረኛው ጋር ቃልኪዳን ሳይጋቡ ቀሩ። የዚህን ምክንያት የተጠየቁ ጊዜም ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ አሉ: እርሱ ላይ ሒርዝ አለበት።

(ሒርዝ) ማለት፡- ዓይንን ወይም ጉዳትን ለመከላከል ከጨሌና ከሌላም ነገር የሚሰራ የሚታሰር ወይም የሚንጠለጠል ነው። ሰውዬውም ወደ ሒርዙ ስፍራ እጁን ከቶ በመቁረጥ ከሒርዙ ጠራ። ነቢዩም (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) የዚህ ጊዜ ቃልኪዳን ተጋቡት። ከሒርዝ ለማስጠንቀቅና ብይኗን ለመግለፅም እንዲህ አሉ: "ሒርዝ ያንጠለጠለ ሰው በርግጥም አጋርቷል።"

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ከአላህ ውጪ በሆነ ላይ የተመካን ሰው አላህ ጉዳዩን ካሰበው በተቃራኒ ያደርግበታል።
2. ጉዳትንና ዐይንን ለመከላከል ሒርዝ ማንጠልጠል ሰበብ ይሆናል ብሎ ማመን ትንሹ ሺርክ ነው። በራሷ ትጠቅማለች ብሎ ካመነ ግን ትልቁ ሺርክ ነው የሚሆነው።

(6762)

(٣٢) - عن عبد الله بن مسعود رضي الله عنه قال: سمعت رسول الله صلى الله عليه وسلم يقول:
«إنَّ الرُّقَى والتَمائِمَ والتِّوَلَةَ شِرْكٌ». [صحيح] - [رواه أبو داود وابن ماجه وأحمد]

(32) - ከዐብደላህ ቢን መስዑድ -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው እንዲህ አለ: የአላህን መልክተኛ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንዲህ ሲሉ ሰምቻቸዋለሁ: "ማነብነብ (ሩቃ) ፣ ሂርዝ ማንጠልጠልና መስተፋቅር ሽርክ ናቸው።" [ሶሒሕ ነው።] - [አቡዳውድ፣ ኢብኑ ማጀህና አሕመድ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ማድረጉ ሺርክ የሆኑ ሁኔታዎችን ገለፁ። ከነሱም መካከል: -

አንደኛ: ማነብነብ (ሩቃ) :- ይህም የጃሂሊያ ሰዎች ይታከሙበት የነበረውን ሽርክን የሰበሰበ ንግግር ነው።

ሁለተኛ: በጨሌና በመሳሰሉ የተሰሩ ሂርዞችን ማንጠልጠል: ይህም የሰው አይን እንዲከላከል በህፃናት፣ በእንስሶችና በሌሎችም ላይ የሚንጠለጠል ነው።

ሶስተኛ: መስተፋቅር: ይህም ከሁለቱ ጥንዶች መካከል አንዱ ሌላኛውን እንዲያፈቅር ተደርጎ የሚሰራ ነው።

እነዚህ ነገሮች ከሺርክ የሚመደቡ ናቸው። ምክንያቱም ይህ በማስረጃ የፀና ሸሪዓዊ ሰበብም ያልሆነን በተለምዶ የተረጋገጠ ህዋሳዊ ሰበብም ያልሆነን ሰበብ አድርጎ መያዝ ነውና። እንደ ቁርአን መቅራት የመሰለ ሸሪዐዊ ሰበቦችን መጠቀም ወይም በተለምዶ የተረጋገጡ መድሃኒቶችን የመሰለ ህዋሳዊ ሰበቦችን መጠቀም ግን መጥቀምና መጉዳት በአላህ እጅ መሆኑንና እነሱ ሰበብ ብቻ መሆናቸውን ከማመን ጋር እስከሆነ ድረስ መጠቀም ይፈቀዳል።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ተውሒድና ዐቂዳችንን ከሚያጎድላቸው ነገር መጠበቅ እንደሚገባ ፤
2. ሽርካዊ ማነብነቦችን፣ ሂርዝና መስተፋቅርን መጠቀም ክልክል መሆኑን ፤
3. እነዚህን ሶስት ነገሮች እንደ ሰበብ አድርጎ ማመን ትንሹ ሺርክ ነው። ምክንያቱም ሰበብ ያልሆነን ነገር ሰበብ ማድረግ ነውና። ነገር ግን (ከሰበብም በላይ) በራሷ ትጠቅማለችም ትጎዳለችም ብሎ ካመነ ትልቁ ሺርክ ነው።
4. ክልክል የሆኑ ሺርካዊ ሰበቦችን መፈፀም መከልከሉን ፤
5. ሸሪዐዊ ከሆነው ሩቃ በስተቀር ማነብነብ ሺርክ ስለሆነ መከልከሉን ፤
6. ቀልብ በአላህ ላይ ብቻ ነው ሊንጠለጠል የሚገባው ፤ ጉዳትም ይሁን ጥቅም የሚገኘው አጋር ከሌለው ከሱ ብቻ ነውና። ከአላህ ውጪ መልካምን የሚያመጣ የለም ፤ ከአላህ ውጪ መጥፎን የሚከላከልም የለም።
7. የሚፈቀደው ሩቃ ሶስት መስፈርቶችን ያካተተ መሆን ይገባዋል: 1- ሩቃው ሰበብ ብቻ እንደሆነና ከአላህ ፍቃድ ውጪ እንደማይጠቅም ማመን፤ 2 - ሩቃው በቁርአን፣ በአላህ ስሞችና ባህሪያት ፣ በነቢያዊ ዱዓዎች፣ ሸሪዐውን በጠበቁ ዱዓዎች ሊሆን ይገባዋል፤ 3 - ሩቃው በግልፅ ቋንቋ ሊሆን ይገባል።

የማይገቡ በሆኑ ቋንቋ የሚሰመሩ መስመሮችና ማታለያዎችን የራቀ ሊሆን ይገባል።

(5273)

(٣٣) - عن بعض أزواج النبي صلى الله عليه وسلم عن النبي صلى الله عليه وسلم قال: «مَنْ أَتَى عَرَّافًا فَسَأَلَهُ عَنْ شَيْءٍ لَمْ تُقْبَلْ لَهُ صَلَاةٌ أَرْبَعِينَ لَيْلَةً». [صحيح] - [رواه مسلم]

(33) - የነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ባለቤት ከሆኑት መካከል ከአንዷ እንደተላለፈው ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንዲህ ብለዋል፦ "ሩቅ አዋቂ ነኝ ባይ ጋር የሄደና ስለአንዳች ነገር የጠየቀው የአርባ ሌሊት ሶላቱ ተቀባይነት አይኖራትም።" [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ሩቅ አዋቂ ነኝ ባይ (ይህም ጠንቋይን፣ ኮኮብ እየተመለከቱ የሚተነብዩን፣ ጠጠርን ተንተርሰው የሚተነብዩንና የመሳሰሉትን የሩቅ እውቀትን ለመሞገት ለመነሻ ያህል የሚጠቀሙን የሚያጠቃልል የወል ስም ነው።) ጋር ከመሄድ አስጠነቀቁ። ሩቅ ከሆኑ ጉዳዮች መካከል አንዳችን መጠየቁ ብቻ በሱ ሳቢያ የአርባ ቀን የሶላቱን ምንዳ አላህ ይከለክለዋል። ይህም በዚህ ትልቅ ወንጀሉና ሀጢዐቱ ምክንያት መቀጣጫ እንዲሆነው ነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. የጥንቆላ ክልክልነትን ፣ ወደጠንቋዮች መሄድና ስለሩቅ ሚስጥር መጠየቅም ክልክል መሆኑን እንረዳለን።
2. ሰው ለወንጀሉ መቀጣጫ ይሆን ዘንድ የመልካም ስራውን ምንዳ ሊከለከል እንደሚችል እንረዳለን።
3. አስትሮኖሚ (ዞዲያክ/ኮከብ ቆጠራ) በመባል የሚጠራው እውቀትና ወደርሱ መመልከት ፣ መዳፍና ሲኒን ለማወቅ ያህል ብቻ እንኳ ቢሆን ማንበብ እዚህ ሐዲሥ ውስጥ ይካተታል። ምክንያቱም ይህ ሁሉ

ከጥንቆላና የሩቅ ምስጢር እውቀትን በመሞገት ውስጥ የሚመደብ ነውና።

4. ሩቅ ሚስጥር አዋቂ ነኝ ባይ ጋር የሄደ ሰው ምንዳው ይህ ከሆነ ራሱ ሩቅ ሚስጥር አዋቂ ነኝ ባዩ ምንዳው ምን ይሆን?
5. የአርባ ቀን ሶላቱ ስለምታብቃቃው ቀዳ የማውጣት ግዴታ አይኖርበትም። ነገር ግን በርሷ ምንም ምንዳ አያገኝም።

(5986)

(٣٤) - عن ابْنِ عُمَرَ رضي الله عنهما أنه سَمِعَ رَجُلًا يَقُولُ: لَا وَالْكَعْبَةِ، فَقَالَ ابْنُ عُمَرَ: لَا يُحْلَفُ بِغَيْرِ اللهِ فَإِنِّي سَمِعْتُ رَسُولَ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ يَقُولُ: «مَنْ حَلَفَ بِغَيْرِ اللهِ فَقَدْ كَفَرَ أَوْ أَشْرَكَ». [صحيح] - [رواه أبو داود والترمذي وأحمد]

(34) - ከኢብኑ ዑመር ረዲየሏሁ ዐንሁማ እንደተላለፈው የሆነ ሰው እንዲህ ሲል ሰሙ፦ "በካዕባ ይሁንብኝ በፍፁም!" ኢብኑ ዑመርም ረዲየሏሁ ዐንሁማ እንዲሁ አሉ፦ "ከአሏህ ውጭ ባለ አካል አይማልም! ምክንያቱም ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ ሲሉ ሰምቻቸዋለሁና 'ከአሏህ ውጭ ባለ አካል የማለ ከፍሯል ወይም አጋርቷል።'" [ሶሒሕ ነው።] - [አቡዳውድ፣ ቲርሚዚና አሕመድ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

በአሏህ ወይም በስምና ባህርያቱ ካልሆነ በቀር ከዛ ውጪ በሆነ መሀላ የማለ ሰው በአላህ ክዷል ወይም አጋርቷል እያሉን ነው። ምክንያቱም በአንድ አካል መማል እሱን ማላቃችንን ያስፈርዳል፤ በእውነቱ ልቅና ደግሞ የሚገባው ለአሏህ ብቻ ነው። ስለዚህም በሱ ወይም ከስምና ባህሪዎቹ መካከል በአንዱ ካልሆነ በስተቀር አይማልም። ይህ መሀላ ከትንሹ ሽርክ የሚመደብ ነው። ይሁን እንጂ የማለው ሰው የማለበትን አካል እንደ አሏህ ወይም ከዛም በላይ አልቆት ከሆነ ግን መሃላው ትልቁ ሽርክ ይሆናል።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. በመሀላ ማላቅ ጥራት የተገባው የአሏህ ሐቅ ነው። በመሆኑም በአላህ ፣ በስምና ባህርያቱ ካልሆነ በቀር በሌላ አይማልም።
2. ሰሓቦች በመልካም ለማዘዝ እና ከመጥፎ ለመከልከል የነበራቸውን ጉጉት ያሳያል፤ በተለይም ጥፋቱ ሽርክን ወይም ክህደትን የሚመለከት ሲሆን የበለጠ ጉጉት አላቸው።

(3359)

(٣٥) - عَنْ أَبِي مُوسَى الأَشْعَرِيِّ رضي الله عنه قَالَ: أَتَيْتُ رَسُولَ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ فِي رَهْطٍ مِنَ الأَشْعَرِيِّينَ أَسْتَحْمِلُهُ، فَقَالَ: «وَاللهِ لاَ أَحْمِلُكُمْ، مَا عِنْدِي مَا أَحْمِلُكُمْ» ثُمَّ لَبِثْنَا مَا شَاءَ اللهُ فَأُتِيَ بِإِبِلٍ، فَأَمَرَ لَنَا بِثَلاَثَةِ ذَوْدٍ، فَلَمَّا انْطَلَقْنَا قَالَ بَعْضُنَا لِبَعْضٍ: لاَ يُبَارِكُ اللهُ لَنَا، أَتَيْنَا رَسُولَ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ نَسْتَحْمِلُهُ فَحَلَفَ أَنْ لاَ يَحْمِلَنَا فَحَمَلَنَا، فَقَالَ أَبُو مُوسَى: فَأَتَيْنَا النَّبِيَّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ فَذَكَرْنَا ذَلِكَ لَهُ، فَقَالَ: «مَا أَنَا حَمَلْتُكُمْ، بَلِ اللهُ حَمَلَكُمْ، إِنِّي وَاللهِ -إِنْ شَاءَ اللهُ- لاَ أَحْلِفُ عَلَى يَمِينٍ، فَأَرَى غَيْرَهَا خَيْرًا مِنْهَا، إِلَّا كَفَّرْتُ عَنْ يَمِينِي، وَأَتَيْتُ الَّذِي هُوَ خَيْرٌ».

[صحيح] - [متفق عليه]

(35) - ከአቡ ሙሳ አልአሽዐሪይ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) -አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው እንዲህ አሉ፦ «የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ዘንድ ከተወሰኑ የአሽዐር ተወላጆች ጋር በመሆን ለጂሀድ መጓጓዣ እንዲሰጡን ለመጠየቅ መጣሁ። እርሳቸውም እንዲህ አሉ: "በአላህ እምላለሁ! መጓጓዣ አልሰጣችሁም። እኔ ዘንድ የምሰጣችሁ መጓጓዣ የለኝም።" ከዚያም አላህ የሻው ወቅት ያህል ቆየን። ግመል መጣላቸውና ለኛም ሶስት ግመል እንዲሰጠን አዘዙ። ግመሉን ይዘን ጉዞ የወጣን ጊዜ አንዳችን ለአንዳችን "አላህ በዚህ ግመል አይባርክልንና የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ዘንድ የጂሀድ መጓጓዣ ግመል ፈልገን መጣን። እርሳቸውም መጓጓዣ እንደማይሰጡን ማሉና ቀጥሎ ሰጡን! (ለመሀላቸው ብለን መቀበል አልነበረብንም።)" ተባባልን።» አቡ ሙሳ እንዲህ አለ: «ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ዘንድ በመምጣት ይህንን አወሳንላቸው። እርሳቸውም "እኔ አይደለሁም መጓጓዣ

የሰጠዋችሁ አላህ ነው የሰጣችሁ። እኔ ወላሂ አላህ ከሻ በአንድ ጉዳይ ከማልኩ በኋላ ተቃራኒው የተሻለ ሆኖ ከታየኝ የተሻለውን ፈፅሜ ለመሀላዬ ማካካሻ አደርጋለሁ እንጂ ከዚህ ውጪ ሌላ አላደርግም።" አሉን።» [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

አቡ ሙሳ አልአሽዐሪይ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - ከተወሰኑ የጎሳዎቹ ሰዎች ጋር በመሆን የአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ዘንድ እንደመጡ ተናገሩ። የመምጣታቸው አላማም በጂሀድ ለመካፈል እንዲመቻቸው የሚጋልቡትን ግመል ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና እንዲሰጧቸው ለመጠየቅ ነው። እርሳቸውም መጓጓዣ እንደማይሰጧቸውና የሚሰጧቸው መጓጓዣም እንደሌላቸው ምለው ነገሯቸው። ተመለሱና የተወሰነ ጊዜ እንደቆዩ ለነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ሶስት ግመል መጣላቸው። ግመሎቹም ወደነርሱ ተላኩ። ከፊሎቹ ለከፊሉ: "አላህ በነዚህ ግመሎች ለኛ አይባርክልንና ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና መጓጓዣ እንደማይሰጡን ምለው ሳለ እኛ እንዴት እንቀበላለን?" በመባባል መጥተው እርሳቸውን ጠየቁ። ነቢዩም (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና እንዲህ አሉ: ለናንተ መጓጓዣውን የሰጣችሁ አላህ ነው። እርሱ ነው የገጠማችሁና የለገሳችሁ። እኔማ በእጃችሁ እንዲደርስ አማካኝ የሆንኩ ሰበብ ብቻ ነኝ። ቀጥለውም ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና እንዲህ አሉ: እኔ ወላሂ አላህ ከሻ በአንዳች የምሰራው ወይም በምተወው ነገር ላይ ምዬ ከዚያም ከዛ ከተማለለት ነገር ተቃራኒው የተሻለና በላጭ መሆኑን ካየው የተሻለውን ነገር ፈፅሜ የማልኩበትን ነገር እተወዋለሁ። ለመሀላዬም ማካካሻ አወጣለሁ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ለወደፊት ለሚከሰት ነገር ቢሆንም እንኳ ንግግርን አፅንዖት ለመስጠት ሳያስምሉንም መማል እንደሚፈቀድ እንረዳለን።
2. ከመሀላ በኋላ "ኢን ሻአ አላህ" -በአላህ ፈቃድ- በሚል ቃል መሀላችንን የአላህ ፈቃድ ላይ ማንጠልጠል እንደሚፈቀድ፤ አላህ ከሻ የሚለውን ቃል ከመሀላው ጋር ነይቶ መሀላውን አስከትሎ የተናገረው መሀላውን ባፈረሰ ሰው ላይ ማካካሻ ግዴታ አይሆንም።
3. ከተማለበት ነገር ይልቅ ተቃራኒው የተሻለ ሆኖ ያገኘው ሰው መሀላውን ተቃርኖ ለመሀላው ማካካሻ በማውጣት ላይ መነሳሳቱን እንረዳለን።

(2961)

(٣٦) - عَنْ حُذَيْفَةَ رضي الله عنه أَنَّ رَسُولَ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ قَالَ: «لَا تَقُولُوا: مَا شَاءَ اللهُ وَشَاءَ فُلَانٌ، وَلَـكِنْ قُولُوا: مَا شَاءَ اللهُ ثُمَّ شَاءَ فُلَانٌ».

[صحيح بمجموع طرقه] - [رواه أبو داود والنسائي في الكبرى وأحمد]

(36) - ከሑዘይፋ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል፦ "አላህ ከሻ (ከፈለገ) እና እከሌ ከሻ (ከፈለገ)' አትበሉ። ይልቁንም 'አላህ ከሻ (ከፈለገ) ከዚያም እከሌ ከሻ (ከፈለገ)' በሉ።" [ከሁሉም ሰነዶቹ አንፃር ሶሒሕ ነው።] - [አቡዳውድ፣ ነሳኢ በኩብራ ውስጥ፣ አሕመድ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ማንኛውንም ሙስሊም በንግግሩ "አላህ ከሻ (ከፈለገ) እና እከሌ ከሻ (ከፈለገ)" ከማለት ከለከሉ። ወይም "አላህና እከሌ ሸተውት (ፈልገውት)" ከማለት ከለከሉ። ይህም የሆነው የአላህ መሻትና ፍላጎት ልቅ በመሆኑ አንድም የሚጋራው ስለሌለ ነው። "እና" የምትለውን ቃል በአጣማሪነት መጠቀማችን በመሻት በኩል ከአላህ ጋር

የሚጋራ ሌላ አካል እንዳለና በመካከላቸው ያለው መሻትም እኩል እንደሆነ ይጠቁማል። ነገር ግን "አላህ ሸቶት ከዚያም እከሌ ሸቶታል።" ይበል። "ከዚያም" የሚለውን ቃል "እና" በሚለው ተለዋጭ አድርጎ በመጠቀም የባሪያን መሻት የአላህን መሻት ተከትሎ የሚመጣ መሆኑን ግልፅ ያድርግ። ምክንያቱም "ከዚያም" የምትለው ቃል ቅደም ተከተልን ትጠቁማለችና።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. "አላህና አንተ ሸታቹሀል።" ማለትና ይህን የመሳሰሉ ቃላቶችን በ "እና" አጣምሮ አሏህ ጋር መጠቀም የቃላትና የንግግር ሺርክ ስለሆነ ክልክል መሆኑን እንረዳለን።
2. "አላህ ሸቶታል ከዚያም አንተ ሸተኸዋል" የሚለው ንግግርና ይህን የመሳሰሉ "ከዚያም" በሚለው መስተፃምር አሏህ ጋር መጠቀም የተከለከለው ነገር ስለሚወገድ ይፈቀዳል።
3. ለአላህ መሻት እንደምናፀድቅለት፣ ለባሪያም መሻት እንደምናፀድቅለት እና የባሪያ መሻት የአላህን መሻት ተከትሎ የሚመጣ መሆኑን እንረዳለን።
4. በቃል ደረጃ እንኳ ቢሆን በአላህ መሻት ላይ ፍጡራንን ማጋራት መከልከሉን እንረዳለን።
5. ተናጋሪው የባሪያ መሻት እንደ አላህ መሻት ነው፤ ከአላህ መሻት ጋር በአካታችነትም ይሁን በስፋት እኩል ነው ብሎ ካመነ ወይም ባሪያ ራሱን የቻለ (አላህ ባይሻለትም) የመሻት አቅም አለው ብሎ ካመነ ትልቁ ሺርክ ይሆናል። ከአላህ በታች የሆነ መሻት ነው ያለው ብሎ ካመነ ግን ትንሹ ሺርክ ይሆናል።

(3352)

(٣٧) - عَنْ مَحْمُودِ بْنِ لَبِيدٍ رضي الله عنه أَنَّ رَسُولَ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ قَالَ: «إِنَّ أَخْوَفَ مَا أَخَافُ عَلَيْكُمُ الشِّرْكُ الْأَصْغَرُ» قَالُوا: وَمَا الشِّرْكُ الْأَصْغَرُ يَا رَسُولَ اللهِ؟ قَالَ: «الرِّيَاءُ، يَقُولُ اللهُ عز وجل لَهُمْ يَوْمَ الْقِيَامَةِ إِذَا جُزِيَ النَّاسُ بِأَعْمَالِهِمْ: اذْهَبُوا إِلَى الَّذِينَ كُنْتُمْ تُرَاؤُونَ فِي الدُّنْيَا، فَانْظُرُوا هَلْ تَجِدُونَ عِنْدَهُمْ جَزَاءً؟». [حسن] - [رواه أحمد]

(37) - ከመሕሙድ ቢን ለቢድ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል: "በናንተ ላይ ከምፈራው ነገር እጅግ አስፈሪው ትንሹ ሺርክ ነው።" ሶሐቦችም "የአላህ መልክተኛ ሆይ! ትንሹ ሺርክ ምንድነው?" ብለው ጠየቁ። እሳቸውም "ይዩልኝ ነው። የትንሳኤ ቀን ሰዎች በስራዎቻቸው የተመነዱ ጊዜ ለነርሱ አሸናፊውና የላቀው አላህ እንዲህ ይላቸዋል፦ 'እነርሱ ዘንድ ምንዳን ታገኙ እንደሁ እስኪ በዱንያ ውስጥ ለይዩልኝ ወደምትሰሩላቸው ሂዱና ተመልከቱ?' " [ሐሰን ነው።] - [አሕመድ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) በኡመታቸው ላይ እጅግ የሚፈሩት ነገር ትንሹን ሺርክ እንደሆነ እሱም ይዩልኝ እንደሆነ ተናገሩ። ይህውም ለሰዎች ብሎ መስራቱ ነው። ቀጥለውም ለይዩልኝ የሚሰሩ ሰዎች የትንሳኤ ቀን የሚጠብቃቸውን ቅጣት ተናገሩ። ለነርሱ: "እነርሱ ዘንድ ምንዳን ታገኙ እንደሁ እስኪ በዱንያ ውስጥ ለይዩልኝ ወደምትሰሩላቸው ሂዱና ተመልከቱ? ለዚህ ስራችሁ ለናንተ መመንዳትና አጅር መስጠት ይችላሉን?" እንደሚባሉም ተናገሩ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ስራን ለአላህ ማጥራት ግዴታነቱንና ከይዩልኝም መጠንቀቅ እንዳለብን እንረዳለን።

2. ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ለኡመታቸው ያላቸውን ከባድ እዝነት፣ በመመራታቸው ላይ ያላቸውን ጉጉትና ለነርሱ ያላቸውን ተቆርቋሪነት እንረዳለን።
3. ሶሐቦች የደጋጎች አለቃ ከመሆናቸውም ጋር ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ሶሐቦችን ሲያናግሩ በዚህ ልክ የሚፈሩላቸው ከሆነ ከነርሱ በኋላ ባሉ ሰዎች ላይ ያላቸው ፍርሀት እጅግ የከበደ መሆኑን እንረዳለን።

(3381)

(٣٨) - عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ رضي الله عنه قَالَ: قَالَ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ: «اثْنَتَانِ فِي النَّاسِ هُمَا بِهِمْ كُفْرٌ: الطَّعْنُ فِي النَّسَبِ، وَالنِّيَاحَةُ عَلَى الْمَيِّتِ». [صحيح] - [رواه مسلم]

(38) - ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: «የአላህ መልክተኛ (ሶለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል: "በሰዎች ውስጥ ሁለት ነገሮች አሉ፤ ክህደት ናቸው። በዘር መተቸትና በሞተ ላይ ሙሾ ማውረድ ናቸው።"» [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና በሰዎች መካከል ስለሚገኙ ሁለት የከሃዲያን ስራዎችና የድንቁርና ዘመን ስነ ምግባሮች ተናገሩ። እነርሱም:

የመጀመሪያው: ሰዎችን በዘራቸው መተቸት፣ ማሳነስና በዘር እነርሱ ላይ መኩራራት ነው።

ሁለተኛው: በመከራ ወቅት የአላህን ውሳኔ በማማረር ድምፅን ከፍ ማድረግ ወይም ከትእግስት ማጣት ብዛት ልብስን መቅደድ ነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. በመተናነስ ላይና በሰዎች ላይ አለመኩራት መነሳሳቱን እንረዳለን።
2. በመከራ ላይ መታገስና አለመበሳጨት ግዴታ መሆኑን እንረዳለን።
3. እነዚህ ተግባራት ከትንሹ ክህደት ነው የሚመደቡት። ከትንሹ ክህደት ክፍሎች መካከል አንድ ስራን የሰራ ሰው ደሞ ትልቁን ክህደት እስኪሰራ ድረስ ከእስልምና የሚያስወጣ ክህደትን የካደ አይሆንም።
4. እስልምና ዘር መተቻቸትና የመሳሰሉትን በሙስሊሞች መካከል መከፋፈልን የሚፈጥሩ ነገሮችን ሁሉ ከልክሏል።

(6361)

(٣٩) - عن أبي مَرْثَدٍ الغَنَوِيّ رضي الله عنه قال: قال رسول الله صلى الله عليه وسلم: «لَا تَجْلِسُوا عَلَى الْقُبُورِ، وَلَا تُصَلُّوا إِلَيْهَا». [صحيح] - [رواه مسلم]

(39) - ከአቡ መርሠድ አልኘነዊይ -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: "የአላህ መልክተኛ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንዲህ ብለዋል: 'መቃብሮች ላይ አትቀመጡ! ወደርሷም አትስገዱ!'" [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም መቃብሮች ላይ ከመቀመጥ ከለከሉ።

ይህም ወደ መቃብሮች ከመስገድ እንደከለከሉት ነው። ቀብሩ ወደ ሰጋጁ ቂብላ አቅጣጫ መሆኑን ይመስል ማለት ነው። ይህም የተከለከለው ወደ ሺርክ ከሚያዳርሱ ምክንያቶች አንዱ ስለሆነ ነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. በሐዲስ እንደተረጋገጠው የጀናዛ ሶላት ካልሆነ በቀር በመቃብር ስፍራ ወይም በመቃብሮች መካከል ወይም ወደ መቃብር ዙሮ መስገድ ክልክል መሆኑን እንረዳለን።

2. ወደ መቃብር መስገድ የተከለከለው የሺርክን መዳረሻዎች ለመዝጋት ነው።
3. ኢስላም በመቃብር ወሰን ማለፍንም መቃብር ማዋረድንም ከልክሏል። ወሰን ማለፍም ማሳነስም የለምና።
4. ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም "የሙትን አጥንት መስበር በህይወት እንደመስበር ነው።" ስላሉ የሙስሊም ክብር ከሞተ በኋላም ዘላቂ ነው።

(10647)

(٤٠) - عَنْ أَبِي طَلْحَةَ رَضِيَ اللهُ عَنْهُ عَنِ النَّبِيِّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ قَالَ: «لاَ تَدْخُلُ المَلاَئِكَةُ بَيْتًا فِيهِ كَلْبٌ وَلاَ صُورَةٌ». [صحيح] - [متفق عليه]

(40) - ከአቡ ጦልሓ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል: "መላዕክቶች ውሻና ስዕል ወዳለበት ቤት አይገቡም።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

**ትንታኔ:**

ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) የእዝነት መላዕክቶች ውሻና ነፍስ ያላቸው የፍጡራን ስዕል ወዳለበት ቤት እንደማይገቡ ተናገሩ። ይህም ነፍስ ያለበት ምሥል አስከፊ ወንጀል ስለሆነ፤ ከአላህ አፈጣጠር ጋር መፎካከር ስለሆነ፤ የሽርክ መዳረሻም ስለሆነ፤ አንዳንዶቹ ምሥሎችም ከአላህ ውጪ የሚመለኩ ምሥሎች ስለሆኑ ነው። ውሻ ያለበት ቤት ከመግባት የመቆጠባቸው ምክንያት ደግሞ: በብዛት ነጃሳ ስለሚመገብ፤ አንዳንዶቹም ሸይጧን ተብለው ስለተጠሩ ነው። መላዕክት ደግሞ የሸይጧን ተቃራኒ ናቸው። በተጨማሪ የውሻ ሽታ አፀያፊ ስለሆነ ነው። መላዕክት ደሞ መጥፎ ሽታን ይጠላሉ። ስለዚህ ውሻን ማሳደግ ተከለከለ። የሚያሳድግ ሰውም የእዝነት መላዕክት ቤቱ ባለመግባታቸው፤ ለቤቱ ዱዓእ ባለማድረጋቸው፤ ለርሱ ምህረት ባለመጠየቃቸው፤ ለርሱና ለቤቱ በረከት ባለመጠየቃቸው፤ የሸይጧንን ጉዳት ከርሱ ላይ ባለመከላከላቸው ተቀጣ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. የአደን ውሻ ወይም የከብት ጠባቂ የሆነ ውሻ ወይም የአዝርዕት ጠባቂ የሆነ ውሻ ካልሆነ በቀር ውሻን ማሳደግ ክልክል መሆኑን እንረዳለን።
2. ስዕል ማስቀመጥ መላዕክት የሚሸሹት ከሆኑ ቆሻሻ ጉዳዮች አንዱ ነው። በአንድ ስፍራ ስዕል መኖሩ እዝነትን እንድንነፈግ ምክንያት ይሆነናል። ውሻም ልክ እንደዚሁ ነው።
3. ውሻ ወይም ስዕል ያለበት ቤት ውስጥ የማይገቡት መላዕክቶች የእዝነት መላዕክቶች ናቸው እንጂ ስራን የሚመዘግቡና ሌሎች እንደ መልዐከ ሞት የመሰሉ የስራ ድርሻ ያላቸው መላዕክቶች ግን ሁሉም ቤት ይገባሉ።
4. ግድግዳና ሌሎች ነገሮች ላይ ነፍስ ያላቸውን ፍጡራን ስዕላቸውን ማንጠልጠል ክልክል መሆኑን እንረዳለን።
5. ኸጧቢ እንዲህ ብለዋል: «መላዕክት ውሻ ወይም ስዕል ያለበት ቤት የማይገቡት ማስቀመጡ ክልክል የሆኑ ውሻዎችንና ስዕሎችን ነው። ክልክል ያልሆኑ የአደን ውሻ፣ የአዝርዕትና ከብቶች ጠባቂ የሆኑ ውሻዎችን እንዲሁም ምንጣፍ ላይ፣ ትራስ ላይና የመሳሰሉት ግን በነርሱ ምክንያት መላዕክት ከመግባት አይቆጠቡም።

(8950)

(٤١) - عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ رضي الله عنه أَنَّ رَسُولَ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ قَالَ: «لَا تَصْحَبُ الْمَلَائِكَةُ رُفْقَةً فِيهَا كَلْبٌ وَلَا جَرَسٌ». [صحيح] - [رواه مسلم]

(41) - ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል: "መላእክት ውሻ እና ቃጭል ካላቸው መንገደኞች ጋር አብረው (አይጎዳኙም) አይሄዱም።" [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) በጉዞ ወቅት በመካከላቸው ውሻ ካለ ወይም በእንስሶች ላይ የሚንጠለጠለውና ሲንቀሳቀስ ድምፅ የሚያወጣው ቃጭል ካለ መላእክት ከነርሱ ጋር በወዳጅነት እንደማይጎዳኙ ተናገሩ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ከአደን ውሻና ከጥበቃ ውሻ በቀር ውሻ መያዝና መጎዳኘት መከልከሉን እንረዳለን።
2. ከመጎዳኘት የሚቆጠቡት መላእክቶች የእዝነት መላእክት ናቸው። የሰውን ስራ የሚቆጣጠሩት መላእክት ግን ባሮችን ቤታቸውም ውስጥ ሆነው ጉዞም ላይ አይለዩዋቸውም።
3. ቃጭል መከልከሉን እንረዳለን። ምክንያቱም እርሱ ከሰይጣን መዝሙሮች መካከል አንዱ ነውና። ቃጭል በውስጡ የክርስቲያኖች ደወል ጋር መመሳሰልን ያቀፈ ነው።
4. አንድ ሙስሊም መላእክትን የሚያርቅ ከሆነ ነገር ሁሉ በመራቅ ላይ ሊጓጓ እንደሚገባ እንረዳለን።

(8951)

(٤٢) - عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ رَضِيَ اللهُ عَنْهُ: قَالَ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ: «يَأْتِي الشَّيْطَانُ أَحَدَكُمْ فَيَقُولُ: مَنْ خَلَقَ كَذَا؟ مَنْ خَلَقَ كَذَا؟ حَتَّى يَقُولَ: مَنْ خَلَقَ رَبَّكَ؟ فَإِذَا بَلَغَهُ فَلْيَسْتَعِذْ بِاللهِ وَلْيَنْتَهِ».

[صحيح] - [متفق عليه]

(42) - ከአቡ ሁረይራ -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው፡- የአላህ መልክተኛ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ አሉ፡- "ሰይጣን አንዳችሁ ዘንድ በመምጣት "ይህን የፈጠረው ማነው? ይህንንስ የፈጠረው?" እያለ ይጠይቃችኋል "ጌታህንስ የፈጠረው ማነው?" ብሎ እስኪጠይቃችሁ ድረስ ይደርሳል፤ ይህ ጥያቄ የደረሰው ጊዜ በአላህ ይጠበቅም ይከልከልም።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

የአላህ መልክተኛ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ሰይጣን አማኞችን ለመጎትጎት ለሚያቀርባቸው ጥያቄዎች ፍቱን መድኃኒት ተናገሩ። "ይህን ማን ፈጠረው? ይህንንስ ማን ፈጠረው? ሰማይን ማን ነው የፈጠረው? ምድርንስ ማን ነው የፈጠረው?" በማለት ሰይጣን ጥያቄ ያቀርብልናል። አማኙም በእምነቱም ፣ በተፈጥሮውም፣ በአይምሮውም ተጠቅሞ "አላህ" በማለት ይመልስለታል። ሰይጣን ግን በዚህ የጉትጎታ ወሰን ላይ ከመቆም ይልቅ "ጌታህን ማን ፈጠረው?" ወደሚል የጉትጎታ ደረጃ ይሸጋገራል። በዚህ ጊዜ አንድ አማኝ ይህንን ጉትጎታ በሦስት ነገሮች ይከላከላል፡-

በአላህ በማመን

ከሰይጣን በአላህ በመጠበቅ

ከጉትጎታው ጋር አብሮ መቀጠልን በማቆም

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. የሰይጣንን ጉትጎታና ውልታ ችላ ማለት፤ ስለ እሱ ማሰብ እንደማይገባ እና ይህን ለማስወገድ ወደ አላህ መጠጋት የሚገባ መሆኑን።

2. ሁሉም በሰው ልጅ ቀልብ ውስጥ የሚከሰት ሸሪዐን ተፃራሪ የሆነ ጉትጎታ ከሰይጣን መሆኑን፤
3. በአላህ ህልውና ጉዳይ ማስተንተን መከልከሉና ስለፍጡራኑና አንቀፆቹ ማስተንተን መበረታታቱን ተረድተናል።

(65013)

(٤٣) - عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ رضي الله عنه قَالَ: قَالَ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ: «إِنَّ اللهَ قَالَ: مَنْ عَادَى لِي وَلِيًّا فَقَدْ آذَنْتُهُ بِالحَرْبِ، وَمَا تَقَرَّبَ إِلَيَّ عَبْدِي بِشَيْءٍ أَحَبَّ إِلَيَّ مِمَّا افْتَرَضْتُ عَلَيْهِ، وَمَا يَزَالُ عَبْدِي يَتَقَرَّبُ إِلَيَّ بِالنَّوَافِلِ حَتَّى أُحِبَّهُ، فَإِذَا أَحْبَبْتُهُ: كُنْتُ سَمْعَهُ الَّذِي يَسْمَعُ بِهِ، وَبَصَرَهُ الَّذِي يُبْصِرُ بِهِ، وَيَدَهُ الَّتِي يَبْطِشُ بِهَا، وَرِجْلَهُ الَّتِي يَمْشِي بِهَا، وَإِنْ سَأَلَنِي لَأُعْطِيَنَّهُ، وَلَئِنِ اسْتَعَاذَنِي لَأُعِيذَنَّهُ، وَمَا تَرَدَّدْتُ عَنْ شَيْءٍ أَنَا فَاعِلُهُ تَرَدُّدِي عَنْ نَفْسِ المُؤْمِنِ، يَكْرَهُ المَوْتَ وَأَنَا أَكْرَهُ مَسَاءَتَهُ». [صحيح] - [رواه البخاري]

(43) - ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: "የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል: 'አላህ እንዲህ ብሏል: ‹የኔን ወዳጅ (ወሊይ) ጠላት አድርጎ የያዘን ሰው በርግጥም ጦርነት እንዳወጀኩበት አሳውቄዋለሁ። ባሪያዬ ግዴታ ካደረግኩበት በበለጠ ወደ እኔ ተወዳጅ በሆነ በአንዳችም ነገር አይቃረብም። ባሪያዬ ወደ እኔ በትርፍ ስራዎች ከመቃረብ አይወገድም የምወደው ቢሆን እንጂ፤ የወደድኩትም ጊዜ የሚሰማበት መስሚያው እሆነዋለሁ፣ የሚያይበት መመልከቻ እሆነዋለሁ፣ የሚጨብጥበት እጅ እሆነዋለሁ፣ የሚራመድበት እግር እሆነዋለሁ፣ ቢጠይቀኝ እሰጠዋለሁ፣ ከኔ ጥበቃ ከፈለገ እጠብቀዋለሁ። እኔ ከማደርገው መካከል የሙእሚን ነፍስን ለመውሰድ እንደማመነታው በአንዳችም ነገር አላመነታሁም። እርሱ ሞትን ይጠላል እኔ ደግሞ እርሱን መጉዳት እጠላለሁ።›'" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪ ዘግበውታል።]

**ትንታኔ:**

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) በሐዲሠል ቁድስ አላህ እንዲህ እንዳለ ተናገሩ: ከወዳጆቼ መካከል አንድን የኔን ወዳጅ ያወከውና ያስቆጣው ከኔ ጋር ጠላት እንደሆነ አውጀያለሁም አሳውቄዋለሁም፤

"ወሊይ" (የአላህ ወዳጅ) የሚባለው: አላህን ፈሪ አማኝ ነው። አንድ ባሪያ ባለው ኢማንና አላህን ፈሪነት ልክ የአላህ ወዳጅነት ይኖረዋል። አንድ ሙስሊም አላህ ግዴታ ካደረገበት ትእዛዛትን መፈፀምና ክልክሎችን ከመተው በበለጠ ወደ ጌታው ተወዳጅ የሚሆንበት አንዳችም ነገር አይቃርበውም። አንድ ሙስሊም ወደ ጌታው ከግዴታዎች ጋር በትርፍ ስራዎች ከመቃረብ አይወገድም የአላህን ውዴታ የሚያገኝ ቢሆን እንጂ፤ አላህ የወደደው ጊዜ በነዚህ አራት አካላቱ ላይ ለርሱ አጋዥ ይሆነዋል።

በመስሚያው ያግዘዋል። አላህን ከሚያስደስት ነገር በቀር አይሰማም።

በመመልከቻው ያግዘዋል። ቢመለከተው አሏህ የሚወድለትንና የሚያስደስተውን ነገር እንጂ አይመለከትም።

በእጁም ያግዘዋል። በእጁ አላህን ከሚያስደስት ነገር በቀር አይሰራም።

በእግሩም ያግዘዋል። አላህን ወደሚያስደስት ነገር ካልሆነ በቀር አይራመድም። መልካም ነገር ወዳለበት ካልሆነ በቀር አይሮጥም።

ከዚህም ጋር አላህን አንዳች ነገር ከጠየቀው አላህ የጠየቀውን ይሰጠዋል፤ ተማፅኖውንም የሚሰማው ይሆናል። በአላህ ጥበቃን ካስፈለገውና የአሏህን ከለላ ፈልጎ ከተጠጋ ጥራት የተገባው አላህም ከሚፈራው ነገር ይጠብቀዋል።

ቀጥሎም አላህ እንዲህ አለ: የሙእሚንን ነፍስ ስወስድ ለርሱ በማዘን እንደማመነታው እኔ ከምሰራው በአንዳችም ነገር አላመነታሁም። ምክንያቱም እርሱ ካለው ህመም አንፃር ሞትን ይጠላል። አላህ ደግሞ ሙእሚንን የሚያሳምም ነገር ይጠላል።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ይህ ሐዲሥ ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ከጌታቸው ከሚዘግቡት ሐዲሥ አንዱ ነው። "ሐዲሠል ቁድስ" ወይም "ሓዲሠል ኢላሂይ" በመባል ይጠራል። እርሱም ቃሉም ሆነ መልዕክቱ ከአላህ የሆነ ሲሆን ነገር ግን ቁርአን ከሌላው የተለየበት የሆኑ መለዮዎች የሉትም። ለምሳሌ: ሲያነብ በየፊደላቱ አጅር ማስገኘቱ፣ እርሱን ለማንበብ ዉዱእ ማድረግ፣ ከቻሉ አምሳያውን እንዲያመጡ የተሞገተበት መሆን፣ የቃል አወቃቀሩ መለኮታዊነትና ከዚህም ውጪ ያሉ የቁርአን መለዮዎች የሉትም ማለት ነው።
2. የአላህን ወዳጆች ከማወክ መከልከሉ፤ እነርሱን በመውደድና ደረጃቸውን በማወቅ ላይም መነሳሳቱን እንረዳለን።
3. የአላህን ጠላቶችን በመጣላት ላይ መታዘዙንና እነርሱን መወዳጀት መከልከሉን እንረዳለን።
4. የአላህን ሸሪዓ ሳይከተል የአላህን ወዳጅነት የሞገተ ሰው በሙግቱ ውሸታም መሆኑን እንረዳለን።
5. የአላህ ወዳጅነት ግዴታዎችን በመፈፀምና ክልክሎችን በመተው ነው የሚገኘው።
6. ለአንድ ባሪያ የአላህን ውዴታና የዱዓን ተቀባይነት ከሚያስተርፉ ምክንያቶች መካከል ግዴታዎችን ከፈፀሙና ክልክሎችን ከተዉ በኋላ ትርፍ ስራዎችን መስራት ነው።
7. የወሊዮች ልቅናና የደረጃቸው ከፍታ መጠቆሙን እንረዳለን።

(6337)

(٤٤)- عن العِرْباضِ بن ساريةَ رضي الله عنه قال: قام فينا رسول الله صلى الله عليه وسلم ذات يوم، فوَعَظَنا مَوعظةً بليغةً وَجِلتْ منها القلوبُ، وذَرَفتْ منها العيونُ، فقيل: يا رسول الله، وعظتَنَا موعظةَ مُودِّعٍ فاعهد إلينا بعهد. فقال: «عليكم بتقوى الله، والسمع والطاعة، وإن عبدًا حبشيًّا، وسترون من بعدي اختلافًا شديدًا، فعليكم بسنتي وسنة الخلفاء الراشدين المهديين، عَضُّوا عليها بالنواجِذ، وإياكم والأمور المحدثات، فإن كل بدعة ضلالة».
[صحيح] - [رواه أبو داود والترمذي وابن ماجه وأحمد]

(44) - ከዒርባድ ቢን ሳሪያህ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አለ: "የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) አንድ ቀን በመካከላችን ቆሙና በርሷ ምክንያት ልቦናዎች የራዱበት፣ ዓይኖች ያነቡበትን ጥግ የደረሰን ምክር መከሩን። 'የአላህ መልክተኛ ሆይ! የመከሩን ምክር የተሰናባች ምክር ሆኖብናልና ለእኛ የሚሰጡን አደራ አለን?' ተባሉ። እርሳቸውም ' አላህን በመፍራት፤ የሐበሻ ባሪያ እንኳ ቢሆን (መሪያችሁ) እንድትሰሙና እንድትታዘዙ አደራ እላችኋለሁ። ከኔ በኋላ ከባድ ልዩነትን ታያላችሁ፤ ስለሆነም በኔ ሱናና የተመሩ ቅን በሆኑት ምትኮቼ ሱና አደራችሁን! እርሷን በማኘኪያ ጥርሳችሁ ነክሳችሁ ያዙ! አደራችሁን አዳዲስ መጤ ነገሮችን ተጠንቀቁ! ሁሉም ቢድዓ (አዲስ መጤ) ጥመት ነውና።' አሏቸው።" [ሶሒሕ ነው።] - [አቡዳውድ፣ ቲርሚዚ፣ ኢብኑማጀህና አሕመድ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ሶሐቦችን ልቦች በርሷ ምክንያት የራዱበትና ዓይኖች ያነቡበትን ጥግ የደረሰ ምክር መከሩ። ሰሐቦችም የነቢዩን (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ምክራቸው ጥግ የደረሰ መሆኑን ስላዩ "የአላህ መልክተኛ ሆይ! ምክሮት የተሰናባች ምክር ትመስላለች።" በማለት ከርሳቸው ህልፈት በኋላ አጥብቀው የሚይዙትን አደራ ጠየቁ። እርሳቸውም "አላህን በመፍራት አደራ እላቹኃለሁ። " አሉ። ይህም ግዴታዎችን በመፈፀምና ክልክሎችን በመተው ነው። "ባሪያ

በናንተ ላይ ቢሾም ወይም መሪ ሆኖ ቢመጣባችሁ እንኳ ለመሪዎች መስማትና መታዘዝን አደራ እላችኋለሁ።" ማለትም በናንተ ላይ ደረጃው የወረደ (አርጋችሁ የምታስቡት) ፍጡር መሪ ቢሆን እንኳ ፈተና ይቀጣጠላል ተብሎ ስለሚሰጋ በዚህ ላይ እምቢተኛ አትሁኑ ታዘዙት ማለት ነው። "እነሆ ከናንተ መካከል የሚኖር ሰው ብዙ ልዩነትን ያያል።" ቀጥለውም ከዚህ ልዩነት መውጫውን ገለፁላቸው። እሱም የርሳቸውን ሱና(ፈለግ) እና ከርሳቸው በኋላ የተመሩ የሆኑት ቅን ምትኮቻቸውን ሱና አጥብቆ በመያዝ ነው። እነሱም: አቡ በክር አስሲዲቅ፣ ዑመር ቢን አልኸጧብ፣ ዑሥማን ቢን ዐፋንና ዐሊይ ቢን አቢ ጧሊብ (ረዲየሏሁ ዐንሁም) - አላህ የሁሉንም መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና ናቸው። አጥብቃችሁ የምትይዙትም በማኘኪያ ጥርስ ነክሶ እንደመያዝ ነው። በዚህም ለማለት የፈለጉት ሱናን በመያዝና በማጥበቅ ላይ መጠንከርን ለመጠቆም ነው። በሃይማኖት ውስጥ ከተፈበረኩ አዳዲስ መጤ ጉዳዮችም አስጠነቀቋቸው። ሁሉም አዲስ መጤ ነገር ጥመት ነውና።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ሱናን አጥብቆ መያዝና ሱናን መከተል አንገብጋቢ ጉዳይ መሆኑን እንረዳለን።
2. ለምክሮችና ልቦችን ለሚያለሰልሱ ነገሮች ትኩረት መስጠት እንደሚገባ እንረዳለን።
3. ከርሳቸው በኋላ ያሉት አራቱ የተመሩ ቅን ምትኮቻቸውን መከተል መታዘዙን እንረዳለን። እነሱም አቡ በክር፣ ዑመር፣ ዑሥማንና ዐሊይ (ረዲየሏሁ ዐንሁም) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና ናቸው።
4. በሃይማኖት ውስጥ አዲስ ነገር መፍጠር መከልከሉንና ሁሉም መጤ ነገር ጥመት መሆኑንም እንረዳለን።
5. የአማኞችን ጉዳይ እንዲመራ ለተሾመ ሰው ከወንጀል ውጪ በሆኑ ጉዳዮች እርሱን መስማትና መታዘዝ እንደሚገባ እንረዳለን።
6. አላህን በሁሉም ወቅትና ሁኔታ የመፍራትን አንገብጋቢነት እንረዳለን።

7. በዚህ ኡመት ውስጥ ልዩነት ይከሰታል። በሚከሰት ወቅት ግን ወደ አላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ሱና እና ወደ ቅን ምትኮቻቸው ሱና መመለስ ግድ ይላል።

(65057)

(٤٥) - عن أبي هريرة رضي الله عنه عن النبي صلى الله عليه وسلم أنه قال: «مَنْ خَرَجَ مِنَ الطَّاعَةِ، وَفَارَقَ الْجَمَاعَةَ فَمَاتَ، مَاتَ مِيتَةً جَاهِلِيَّةً، وَمَنْ قَاتَلَ تَحْتَ رَايَةٍ عِمِّيَّةٍ، يَغْضَبُ لِعَصَبَةٍ، أَوْ يَدْعُو إِلَى عَصَبَةٍ، أَوْ يَنْصُرُ عَصَبَةً، فَقُتِلَ، فَقِتْلَةٌ جَاهِلِيَّةٌ، وَمَنْ خَرَجَ عَلَى أُمَّتِي، يَضْرِبُ بَرَّهَا وَفَاجِرَهَا، وَلَا يَتَحَاشَى مِنْ مُؤْمِنِهَا، وَلَا يَفِي لِذِي عَهْدٍ عَهْدَهُ، فَلَيْسَ مِنِّي وَلَسْتُ مِنْهُ».
[صحيح] - [رواه مسلم]

(45) - ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ አሉ: "ከመሪ ትእዛዝ አምፆ በመውጣት የሙስሊሙን ህብረት ተለይቶ የሞተ የድንቁርና አሟሟት ሙቷል። ለወገኑ ሲል እየተቆጣ ወይም ወደ ወገንተኝነት እየተጣራ ወይም ወገን ለይቶ እየረዳ በዕውር ባንዲራ ስር እየተዋጋ ቢገደል የድንቁርና አሟሟት ሙቷል። በኡመቴ ላይ (ሊመራ) የወጣ መልካሙንም መጥፎውንም የሚማታ ስለአማኙ ህዝብ ምንም ደንታ የሌለው የቃል ኪዳን ባለቤት ለሆኑትም በቃል ኪዳኑ የማይሞላ ሰው ከኔም አይደለም እኔም ከርሱ አይደለሁም።" [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ከመሪዎች ትእዛዝ አምፆ በመውጣት ሙስሊሙ ማህበረሰብ ከተስማሙበት መሪ ያፈነገጠ ሰው በዚህ ያለመታዘዝና አማፂነት ሁኔታ ላይ ሆኖ ቢሞት የእነዚያ መሪን የማይታዘዙ፣ ወደ አንድ ህብረት የማይጠጉ በተቃራኒ ቡድንተኛና ወገንተኛ ሁነው ከፊሉ ከፊሉን ይዋጉ የነበሩት የድንቁርና ዘመን ባለቤቶችን አይነት አሟሟት ሙቷል።

-ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እውነተኛው ከውሸተኛው ባልተለየበት ባንዲራ ስር የተዋጋ ሰው ቁጣውና እምነቱ ሐቅን ለመርዳት ሳይሆን ለጠራ ህዝባዊ ወይም ጎሳዊ ወገንተኝነት የሆነ ፤ ያለእውቀትና እርግጠኝነት ለወገንተኝነት የሚዋጋ ሰው በዚህ ሁኔታ ላይ ሆኖ ከተገደለ ሞቱ እንደ ድንቁርና ዘመን ሞት ነው የሚሆነው ብለው ተናገሩ።

በነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ኡመት ላይ ለመሪነት የወጣ መልካሙንም መጥፎውንም የሚማታ፣ በሚፈፅመው ድርጊት ላይ ደንታ የሌለው፣ አማኞችን በመግደል የሚደርስበትን ቅጣት የማይፈራ፤ ከከሀዲያንና ከመሪዎች ጋር ያለውን ቃል ኪዳን ከመጠበቅ ይልቅ ቃል ኪዳኑን የሚያፈርስ (ይህ ትልቅ ወንጀለም ነው።) ይህን የሰራ ሰው ለዚህ ትልቅ ዛቻ የተገባ ይሆናል።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. አላህን ማመፅ ላይ እስካልሆነ ድረስ መሪዎችን መታዘዝ ግዴታ መሆኑን እንረዳለን።
2. እዚህ ሐዲሥ ውስጥ ከመሪ ትእዛዝ የወጣና ከሙስሊሙ ማህበረሰብ ያፈነገጠ ላይ ከባድ ማስጠንቀቂያ አለ። በዚህ ሁኔታ ላይ ሆኖ ቢሞት የድንቁርናው ዘመን ሰዎች መንገድ ላይ ሆኖ ሙቷል።
3. ሐዲሡ ውስጥ ለወገንተኝነት ብሎ መዋጋት ክልክል መሆኑ ተገልጿል።
4. ቃል ኪዳንን መሙላት ግዴታ መሆኑን እንረዳለን።
5. መሪን በመታዘዝና አንድነትን በመጠበቅ ደህንነት፣ መረጋጋት፣ የሁኔታዎች መስተካከልና የመሳሰሉት ብዙ በጎ ነገሮች ይገኛሉ።
6. ከድንቁርና ዘመን ባለቤቶች ሁኔታ ጋር መመሳሰል መከልከሉን እንረዳለን።
7. የሙስሊሙን ህብረት አጥብቆ መያዝ መታዘዙን እንረዳለን።

(58218)

(٤٦) - عن مَعقِلِ بن يَسار المُزَنِيّ رضي الله عنه قال: إني سمعت رسول الله صلى الله عليه وسلم يقول: «مَا مِنْ عَبْدٍ يَسْتَرْعِيهِ اللهُ رَعِيَّةً، يَمُوتُ يَوْمَ يَمُوتُ وَهُوَ غَاشٌّ لِرَعِيَّتِهِ، إِلَّا حَرَّمَ اللهُ عَلَيْهِ الْجَنَّةَ». [صحيح] - [متفق عليه]

(46) - ከመዕቂል ቢን የሳር አልሙዘኒይ -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: እኔ የአላህን መልክተኛ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንዲህ ሲሉ ሰምቻቸዋለሁ: "አላህ አንድ ሀላፊነት ላይ ሹሞት የተሰጠውን ሀላፊነት የሚያታልል ሆኖ የሚሞት ባሪያ የለም አላህ በርሱ ላይ ጀነትን እርም የሚያደርግ ቢሆን እንጂ።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

እያንዳንዱ አላህ በሰዎች ላይ ተጠያቂና ሀላፊ ያደረገው ሁሉ እንደመሪነት ጠቅላይ ሀላፊነትን የሚያስተዳድርም ይሁን ወይም በቤቱ ሀላፊ እንደሆነ ወንድና በቤቷ ሀላፊ እንደሆነች ሴት ውስን ሀላፊነትም ይሁን የሀላፊነት ግዴታውን ካጓደለ፣ ቅን ሳይሆን ካጭበረበረና ዲናዊና ዓለማዊ ግዴታውን ካጠፋ ለከባድ ቅጣት እንደተገባ ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ተናገሩ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ይህ ዛቻ በጠቅላይ መሪውና ሚኒስትሮቹ ላይ ብቻ የተገደበ ሳይሆን አላህ በሀላፊነት የሾመውን ሁሉ የሚያጠቃልል ነው።
2. በአንዳች የሙስሊሞች ጉዳይ ላይ የተሾመ ሰው ያለበት ግዴታ ለነሱ ቅን መሆን፣ አደራውን በመወጣት ላይ መታገልና ማጭበርበርን መጠንቀቅ ነው።
3. ጠቅላይም ይሁን ውስን፣ ትልቅም ይሁን ትንሽ ሀላፊነት ላይ የተሾመ ሁሉ ተጠያቂነቱ ትልቅ መሆኑን እንረዳለን።

(5335)

(٤٧) - عَنْ أُمِّ سَلَمَةَ أُمِّ المُؤمنين رضي الله عنها: أَنَّ رَسُولَ اللهِ صلى الله عليه وسلم قَالَ: «سَتَكُونُ أُمَرَاءُ فَتَعْرِفُونَ وَتُنْكِرُونَ، فَمَنْ عَرَفَ بَرِئَ، وَمَنْ أَنْكَرَ سَلِمَ، وَلَكِنْ مَنْ رَضِيَ وَتَابَعَ» قَالُوا: أَفَلَا نُقَاتِلُهُمْ؟ قَالَ: «لَا، مَا صَلَّوْا». [صحيح] - [رواه مسلم]

(47) - ከኡሙ ሰለማ ኡሙል ሙእሚኒን (ረዲየሏሁ ዐንሃ) - አላህ መልካም ሥራዋን ይውደድላትና - እንደተላለፈው: የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል: "እነሆ በናንተ ላይ መሪዎች ይሾማሉ። የምታውቁትንም የምታወግዙትንም ስራ ይሰራሉ። (የሚሰሩትን ውግዝ ስራ) የጠላ ሰው (ከወንጀል) ጠራ። ያወገዘም ሰው ሰላም ሆነ። ነገር ግን (የነሱን ውግዝ ተግባር) የወደደና የተከተለ (ወንጀል ውስጥ ወደቀ)" ሶሓቦችም "ታዲያ አንዋጋቸውምን?" ብለው ጠየቁ። ነቢዩም "ሶላትን እስከሰገዱ ድረስ በፍፁም (እንዳትዋጓቸው!)" ብለው መለሱ። [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል። ]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) በኛ ላይ መሪዎች እንደሚሾሙና ከፊል ስራዎቻቸው ከሸሪዓ ጋር የተስማማ ስለሆነ መልካም እንደምንለውና፤ ከፊሉን ደግሞ ከሸሪዓ ጋር ስለሚፃረር እንደምናወግዘው ተናገሩ። ውግዝ ተግባሮቻቸውን ማውገዝ ያልቻለና በቀልቡ የጠላ ሰው በርግጥም ከወንጀልና ንፍቅና ጠራ። በእጁ ወይም በአንደበቱ ማውገዝ የቻለ ሰውና በነርሱ ላይ ይህንን ያወገዘ በርግጥ ከወንጀልና ከወንጀል ተባባሪነት ሰላም ሆኗል። ነገር ግን ድርጊታቸውን የወደደና በርሱ ላይ የተከተላቸው እነርሱ እንደጠፉት ይጠፋል።

ከዚያም ሶሐቦች ነቢዩን (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) "ይህን አይነት ባህሪ የተላበሱ መሪዎችን አንዋጋምን?" ብለው ጠየቁ። ነቢዩም (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) "በመካከላችሁ ሶላትን ቀጥ አድርገው እስከሰገዱ ድረስ በፍፁም እንዳትዋጓቸው!" በማለት ከዚህ ከለከሏቸው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ለወደፊት የሚከሰቱ ሩቅ ነገሮችን መናገራቸውና እንደተናገሩት መከሰቱ የነቢዩን (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ነቢይነት ከሚጠቁሙ ነገሮች መካከል አንዱ ነው።
2. ውግዝ ተግባርን መውደድና በርሱ ላይ መተባበር አይፈቀድም። ውግዝን ማውገዝም ግዴታ ነው።
3. መሪዎች ከሸሪዓ የተፃረረን ነገር የፈጠሩ ጊዜ በዚህ ላይ እነርሱን መታዘዝ አይፈቀድም።
4. በሙስሊም መሪዎች ላይ አምፆ መውጣት ያልተፈቀደው ይህን ተከትሎ ብክለት፣ ደም መፋሰስና የደህንነት ቀውስ ስለሚከሰት ነው። የወንጀለኛ መሪዎችን ውግዝ ተግባር መቻልና አስቸጋሪነታቸውን መታገስ ከነዚህ ነገሮች አንፃር እጅግ ቀላል ነው።
5. ሶላት ጉዳዩዋ (ደረጃዋ) ትልቅ ነው። ሶላት በክህደትና ኢስላም መካከል የምትለይ መሆኗን እንረዳለን።

(3481)

(٤٨) - عَنِ ابْنِ مَسْعُودٍ رضي الله عنه عَنِ النَّبِيِّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ قَالَ: «سَتَكُونُ أَثَرَةٌ وَأُمُورٌ تُنْكِرُونَهَا» قَالُوا: يَا رَسُولَ اللهِ فَمَا تَأْمُرُنَا؟ قَالَ: «تُؤَدُّونَ الحَقَّ الَّذِي عَلَيْكُمْ، وَتَسْأَلُونَ اللهَ الَّذِي لَكُمْ». [صحيح] - [متفق عليه]

(48) - ከኢብኑ መስዑድ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል፦ "ለወደፊት የምታወግዟቸው ጉዳዮችና አድልዎ ይከሰታል!' ሶሐቦችም 'የአላህ መልክተኛ ሆይ! ምን ያዙናል?' አሉ። እርሳቸውም 'በናንተ ላይ ያለባችሁን ግዴታ ትወጣላችሁ። ለናንተ ያላችሁን ሐቅ ደግሞ ከአላህ ትጠይቃላችሁ።' አሉ።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) የሙስሊሞችን ገንዘብና ሌሎችንም አለማዊ ጉዳዮች በማዳላት ሙስሊሞችን በርሱ ላይ ካላቸው መብት በመከልከል እንደፈለጉ የሚያወጡ መሪዎች በሙስሊሞች ላይ እንደሚሾሙ ተናገሩ። በነርሱ ላይም የሚወገዙ ሃይማኖታዊ ጉዳዮች እንደሚኖራቸው ተናገሩ። ሶሐቦችም (ረዲየሏሁ ዐንሁም) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና በዚህ ሁኔታ ላይ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ጠየቁ። ነቢዩም (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) በገንዘብ ጉዳይ ብቻቸውን መጠቀማቸው በናንተ ላይ ለነርሱ ልታሟሉ ግዴታ የሆነባችሁን ከመስማትና ከመታዘዝ እንዳይገታችሁ። ይልቁንም ታግሳችሁ መስማትና መታዘዝ ላይ አደራችሁን። በትእዛዞቻቸውም አትቃረኗቸው (አትከራከሯቸው)። እንዲያስተካክላቸው፣ ክፋታቸውንና ግፋቸውን እንዲከላከልላችሁ ለናንተ ያላችሁንም ሐቅ ከአላህ ጠይቁ!

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ሐዲሡ የርሳቸውን ነቢይነት ከሚጠቁሙ ሐዲሶች መካከል አንዱ ነው። ይህም ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና)

በኡመታቸው ውስጥ የሚከሰተውን መናገራቸውና እንደተናገሩት ከመከሰቱ አንፃር ነው።

2. ነፍሱን ዝግጁ እንዲያደርግና ባጋጠመው ወቅት ታጋሽና ምንዳውን የሚያስብ ሊሆን ዘንድ ለተፈተነ ሰው ለወደፊት ያጋጥመዋል ተብሎ የሚታሰብ መከራን ማሳወቅ እንደሚፈቀድ እንረዳለን።
3. ከቁርአንና ሐዲሥ ጋር ያለ ትስስርን ማጠንከር ከፈተናና ልዩነት መውጫ መንገድ እንደሆነ እንረዳለን።
4. ለመሪዎች በመልካም ጉዳይ መስማትና መታዘዝ ላይና ግፍ እንኳ ቢያደርሱ በነርሱ ላይ አምፆ ባለመውጣት ላይ መነሳሳቱን እንረዳለን።
5. በፈተና ዘመን ሱናን መከተልና ጥበብን መጠቀም እንደሚገባ እንረዳለን።
6. አንድ ሰው በርሱ ላይ ግፍ እንኳ ቢደርስበት ባለበት እውነት ላይ መቆም እንደሚገባው እንረዳለን።
7. ይህ ሐዲሥ አንድ መርህን ይጠቁመናል። እርሱም፦ ከሁለት ክፋቶች ዝቅተኛውን ክፋት ይመረጣል፤ ወይም ከሁለት ጉዳዮች ቀላሉ ጉዳት ይመረጣል የሚል ነው።

(3156)

(٤٩) - عَنْ عَبْدِ اللهِ بنِ عُمرَ رَضِيَ اللهُ عَنْهُما أَنَّ رَسُولَ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ قَالَ: «كُلُّكُمْ رَاعٍ فَمَسْئُولٌ عَنْ رَعِيَّتِهِ، فَالأَمِيرُ الَّذِي عَلَى النَّاسِ رَاعٍ وَهُوَ مَسْئُولٌ عَنْهُمْ، وَالرَّجُلُ رَاعٍ عَلَى أَهْلِ بَيْتِهِ وَهُوَ مَسْئُولٌ عَنْهُمْ، وَالمَرْأَةُ رَاعِيَةٌ عَلَى بَيْتِ بَعْلِهَا وَوَلَدِهِ وَهِيَ مَسْئُولَةٌ عَنْهُمْ، وَالعَبْدُ رَاعٍ عَلَى مَالِ سَيِّدِهِ وَهُوَ مَسْئُولٌ عَنْهُ، أَلَا فَكُلُّكُمْ رَاعٍ وَكُلُّكُمْ مَسْئُولٌ عَنْ رَعِيَّتِهِ». [صحيح] - [متفق عليه]

(49) - ከዐብደላህ ቢን ዑመር (ረዲየሏሁ ዐንሁማ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል: "ሁላችሁም እረኞች (ሀላፊ) ናችሁ። ስለምትጠብቁት ነገርም ትጠየቃላችሁ። በሰዎች ላይ የተሾመ መሪ እረኛ (ሀላፊ) ነው። ስለነርሱም ይጠየቃል። ወንድ በቤተሰቡ ላይ እረኛ (ሀላፊ) ነው። ስለነርሱም ይጠየቃል። ሴት ልጅ በሏሏ ቤትና በልጆቹ ላይ እረኛ (ሀላፊ) ናት። ስለነርሱም ትጠየቃለች። ባሪያ በአለቃው ገንዘብ ላይ እረኛ (ሀላፊ) ነው። ስለርሱም ይጠየቃል። አዋጅ! ሁላችሁም እረኞች (ሀላፊ) ናችሁ። ስለምትጠብቁት ነገርም ትጠየቃላችሁ።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ማህበረሰቡ ውስጥ በሚገኝ ሁሉም ሙስሊም ላይ የሚሸከመውና የሚጠብቀው ኃላፊነት እንዳለበት ተናገሩ። ኢማምና መሪ አላህ ባስጠበቃቸው ኃላፊነት እረኞች (ኃላፊዎች) ናቸው። በርሱ ላይም ሸሪዓቸውን መጠበቅ፣ በነርሱ ላይ ግፈኛ ከሆነ መጠበቅ፣ ጠላቶቻቸውን መታገልና ሐቃቸውን አለማጥፋት ይገባዋል። ወንድም ለቤተሰቡ ቀለብ በማሟላት፣ መልካም አኗኗር በማኖር፣ በማስተማርና ስርዓት በማስያዝ ላይ ኃላፊነት አለበት። ሴትም በባሏ ቤት ውስጥ ቤቱን ባማረ መልኩ በማስተናበርና ልጆቹን በማነፅ ላይ ኃላፊነት አለባት። ስለዚህም ትጠየቃለች። አገልጋይ ባሪያና ተቀጣሪም በአለቃው ገንዘብ ላይ በእጁ ያለውን የአለቃውን ገንዘብ በመጠበቅ፣ እርሱን በማገልገል ሀላፊ

ነው። ስለዚህም ይጠየቃል። እያንዳንዱ ሰው አላህ በሰጠው ሀላፊነት ላይ እረኛ (ሀላፊ) ነው። እያንዳንዱም ሰው ስለ ሀላፊነቱ ይጠየቃል።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. በአጠቃላይ የሙስሊሙ ማህበረሰብ ላይ ተጠያቂነት ያለ ሲሆን ሁሉም በልኩ፣ በችሎታውና በሀላፊነቱ ልክ ተጠያቂ ው።
2. የሴት ኃላፊነት ትልቅ መሆኑን እንረዳለን። ይህም በባሏ ቤት እና በልጆቿ ላይ ያላትን ግዴታዎች መወጣት ስለሆነ ነው።

(5819)

(٥٠) - عن عائشة رضي الله عنها قالت: سمعتُ من رسول الله صلى الله عليه وسلم يقول في بيتي هذا: «اللَّهُمَّ مَنْ وَلِيَ مِنْ أَمْرِ أُمَّتِي شَيْئًا فَشَقَّ عَلَيْهِمْ فَاشْقُقْ عَلَيْهِ، وَمَنْ وَلِيَ مِنْ أَمْرِ أُمَّتِي شَيْئًا فَرَفَقَ بِهِمْ فَارْفُقْ بِهِ». [صحيح] - [رواه مسلم]

(50) - ከእናታችን ዓኢሻህ -አላህ መልካም ስራዋን ይውደድላትና- እንደተላለፈው እንዲህ አለች: የአላህ መልክተኛን ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ቤቴ ውስጥ ይህንን ሲሉ ሰምቻለሁ: "አላህ ሆይ! ከኡመቴ ጉዳይ በአንዳች ነገር የተሾመና እነርሱን ለችግር የዳረገ እርሱንም የሚቸገር አድርገው ። ከኡመቴ ጉዳይ በአንዳች ነገር የተሾመና ለነሱ የራራን ለርሱም ራራለት።" [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

የሙስሊሞች ጉዳዮች ውስጥ በየትኛውም ትንሽም ይሁን ትልቅ ሹመት ፣ አጠቃላይም ይሁን ቁንፅል ሹመትን የተሾመ ከዚያም ለሙስሊሞች ሳይራራ ችግርን በነርሱ ላይ የሚያባብስባቸው የሆነን ሰው ሁሉ ላይ አላህ በሰራው ስራ ተመሳሳይ እሱንም ለችግር እንዲዳርገው የአላህ መልክተኛ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ዱዓእ አደረጉበት።

ለነርሱ የራራና ጉዳዮቻቸውን ባቀለለ ላይም አላህ ለርሱ እንዲራራና ጉዳዮቹን እንዲያገራለት ዱዓ አደረጉለት።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ከሙስሊሞች ጉዳዮች መካከል አንድ ነገር ላይ የተሾመ ሰው በቻለው መጠን ለነርሱ መራራት ግዴታው መሆኑን ፤
2. ምንዳ የሚሰጠን በስራችን አይነት መሆኑን፤
3. የመራራትና የሀይለኝነት መለኪያ ሚዛኑ ቁርአንና ሐዲሥና ባልተፃረረ መልኩ መሆኑን እንረዳለን።

(5330)

(٥١) - عن تميم الداري رضي الله عنه أن النبي صلى الله عليه وسلم قال: «الدِّينُ النَّصِيحَةُ» قُلْنَا: لِمَنْ؟ قَالَ: «لِلَّهِ وَلِكِتَابِهِ وَلِرَسُولِهِ وَلِأَئِمَّةِ الْمُسْلِمِينَ وَعَامَّتِهِمْ». [صحيح] - [رواه مسلم]

(51) - ከተሚም አድዳሪይ -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸው - እንደተላለፈው ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ አሉ፦ "ሃይማኖት (ኢስላም) መቆርቆር (ታማኝነት) ነው።" እኛም "ለማን ነው (የምንቆረቆረው)" አልናቸው። እሳቸውም "ለአላህ፣ ለመጽሐፉ፣ ለመልክተኛው፣ ለሙስሊሞች መሪዎችና ለአጠቃላይ ሙስሊም ማህበረሰብ። " አሉ። [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን የኢስላም ሃይማኖት በኢኽላስና በእውነተኝነት ላይ የቆመ መሆኑን ተናገሩ። ይህም ሁሉም አማኝ የታዘዘውን አላህ ግዴታ ባደረገው መልኩ ምንም ሳያጓድልና ሳያታልል በተሟላ መልኩ እስኪፈፅም ድረስ ነው ቅን እንዲሆን የታዘዘው።

ነቢዩም የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን "ለማን ነው ተቆርቋሪነቱ?" ተብለው ተጠየቁ። እሳቸውም እንዲህ አሉ፦

በመጀመሪያ: ጥራት ለተገባውና ከፍ ላለው አላህ ተቆርቋሪ (ታማኝ) መሆን ነው። ይህም፡- ለሱ የምንሰራውን ስራ በማጥራትና ባለማጋራት፣ በጌትነቱ፣ በተመላኪነቱ፣ በስሞቹና በባህሪያቶቹ በማመን፣ ትእዛዞቹን በማላቅና በሱ ወደማመን ሌሎችን በመጣራት ነው።

ሁለተኛ: ለመጽሐፉ ተቆርቋሪ (ታማኝ) መሆን ነው። እሱም የተከበረው ቁርአን ነው። ይህም: ቁርአን የአላህ ቃል መሆኑንና የመጨረሻው መጽሐፉ መሆኑን በማመን፣ ከእሱ በፊት የነበሩትን ሁሉ ድንጋጌዎች የሻረ መሆኑን በማመን፣ እሱን በማላቅ፣ ትክክለኛ በሆነ መልኩ በማንበብ፣ ግልፅ የሆኑትን በመተግበር አሻሚ የሆኑትን በማመን፣ ከአጥማሚዎች ትርጓሜም በመከላከል፣ በተግሳፆቹ በመመከር፣ ውስጡ ያሉትን እውቀቶች በማሰራጨትና ወደርሱ በመጣራት ነው።

ሶስተኛ: ለመልክተኛው ሙሐመድ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ተቆርቋሪ (ቅን/ ታማኝ) መሆን ነው። ይህም: እሳቸው ከመልክተኞች የመጨረሻ መሆናቸውን በማመን፣ ከሳቸው የመጣውን ሁሉ እውነትነቱን በመቀበል፣ ትእዛዛቸውን በመፈፀም፣ ክልከላቸውን በመራቅ፣ እሳቸው ባመጡት ድንጋጌ ካልሆነ በቀር አላህን ባለማምለክ፣ ሐቃቸውን በማላቅና በማክበር፣ ጥሪያቸውን በማሰራጨት፣ ሸሪዐቸውን በማስፋፋት፣ እሳቸው ላይ የሚቀርቡ ክሶችን ውድቅ በማድረግ ነው።

አራተኛ: ለሙስሊም መሪዎች ቅን ተቆርቋሪ (ቅን/ ታማኝ) መሆን ነው። ይህም: በሀቅ ላይ በመተባበር፣ ጉዳያቸውን ባለመጋፋትና በአላህ ትእዛዛቶች ሲያዙን እነሱን ሰምቶ በመታዘዝ ነው ።

አምስተኛ: ለሙስሊሞች ተቆርቋሪ (ቅን/ ታማኝ) መሆን ነው። ይህም: ለነሱ በጎ በማድረግ፣ እነሱን ወደ በጎ በመጣራት፣ እነሱ ላይ ጉዳት ከማድረስ በመቆጠብ፣ ለነሱ መልካምን በመውደድ፣ በበጎና አላህን በመፍራት ላይ ከነርሱ ጋር በመተባበር ነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ለሁሉም ተቆርቋሪ (ቅን/ ታማኝ) መሆን መታዘዙ፤
2. በእስልምና ሃይማኖት ውስጥ የተቆርቋሪነት (ቅን/ ታማኝ) ደረጃ የላቀ መሆኑን፤
3. የእስልምና ሃይማኖት እምነቶችን፣ ንግግሮችንና ተግባራቶችን ያጠቀለለ መሆኑን፤
4. ከነሲሓ መካከል አንዱ ቅንነቱ ለተገባው አካል ከማታለል ነፍሳችንን ማፅዳትና ለሱ መልካምን መፈለግ ነው።
5. መልክተኛው ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም አንድን ነገር በጥቅሉ አውስተው ከዚያም መዘርዘራቸው የሳቸውን የማስተማር ብቃታቸው ውበትን ይጠቁማል።
6. ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ለአላህ ተቆርቋሪ (ቅን/ ታማኝ) በመሆን ጀምረው ከዚያም ለመጽሐፉ ከዚያም ለመልክተኛው ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ከዚያም ለሙስሊም መሪዎች ከዚያም ለሙስሊሙ ማህበረሰብ ተቆርቋሪ (ቅን/ ታማኝ) በመሆን ማጠቃለላቸው የትኛውንም ነገር እጅግ አንገብጋቢ ከሆነው ጉዳይ ሊጀመር እንደሚገባው እንረዳለን።

(4309)

(٥٢) - عَنْ عَائِشَةَ رَضِيَ اللهُ عَنْهَا قَالَتْ: تَلَا رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ هَذِهِ الْآيَةَ: {هُوَ الَّذِي أَنْزَلَ عَلَيْكَ الْكِتَابَ مِنْهُ آيَاتٌ مُحْكَمَاتٌ هُنَّ أُمُّ الْكِتَابِ وَأُخَرُ مُتَشَابِهَاتٌ فَأَمَّا الَّذِينَ فِي قُلُوبِهِمْ زَيْغٌ فَيَتَّبِعُونَ مَا تَشَابَهَ مِنْهُ ابْتِغَاءَ الْفِتْنَةِ وَابْتِغَاءَ تَأْوِيلِهِ، وَمَا يَعْلَمُ تَأْوِيلَهُ إِلَّا اللهُ وَالرَّاسِخُونَ فِي الْعِلْمِ يَقُولُونَ آمَنَّا بِهِ كُلٌّ مِنْ عِنْدِ رَبِّنَا وَمَا يَذَّكَّرُ إِلَّا أُولُو الْأَلْبَابِ} [آل عمران: ٧]. قَالَتْ: قَالَ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ: «فَإِذَا رَأَيْتِ الَّذِينَ يَتَّبِعُونَ مَا تَشَابَهَ مِنْهُ فَأُولَئِكَ الَّذِينَ سَمَّى اللهُ، فَاحْذَرُوهُمْ».

[صحيح] - [متفق عليه]

(52) - የምእመናን እናት ዓኢሻ -አላህ መልካም ሥራዋን ይውደድላትና- እንዲህ ብላለች፦ የአላህ መልክተኛ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ይህቺን አንቀፅ አነበቡ {እርሱ ያ በአንተ ላይ መጽሀፉን ያወረደ ነው። ከእርሱ (ከመፅሀፉ) ግልጽ የሆኑ አንቀጾች አሉ። እነሱ የመጽሐፉ መሠረቶች ናቸው። ሌሎችም ተመሳሳዮች አሉ። እነዚያማ በልቦቻቸው ውስጥ ጥመት ያለባቸው ሰዎች ማሳሳትን በመፈለግና ማጣመምን በለመፈለግ ከርሱ የተመሳሰለውን ይከታተላሉ። (ትክክለኛ) ፍቺውንም አላህ ብቻ እንጂ ሌላ አያውቀውም። በዕውቀትም የጠለቁት "በርሱ አምነናል፤ ሁሉም ከጌታችን ዘንድ ነው" ይላሉ። የአእምሮ ባለቤቶችም እንጅ (ሌላው) አይገሰጽም።} [አሉ ዒምራን: 7] ቀጥለው የአላህ መልክተኛ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ አሉ፦ " እነዚያ ከቁርኣን የተመሳሰለውን የሚከተሉትን ከተመለከትሽ አላህ ተጠንቀቁዋቸው ብሎ የጠቀሳቸው እነሱ ናቸው።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

የአላህ መልክተኛ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ይህቺን አንቀፅ አነበቡ {እርሱ ያ በአንተ ላይ መጽሀፉን ያወረደ ነው። ከእርሱ (ከመጽሐፉ) ግልጽ የሆኑ አንቀጾች አሉ። እነሱ የመጽሀፉ መሠረቶች ናቸው። ሌሎችም ተመሳሳዮች አሉ። እነዚያማ በልቦቻቸው ውስጥ ጥመት ያለባቸው ሰዎች ማሳሳትን በመፈለግና ማጣመምን በመፈለግ ከርሱ የተመሳሰለውን ይከታተላሉ። (ትክክለኛ) ፍቺውንም አላህ ብቻ እንጂ ሌላ አያውቀውም።

በዕውቀትም የጠለቁት "በርሱ አምነናል፤ ሁሉም ከጌታችን ዘንድ ነው" ይላሉ። የአእምሮ ባለቤቶችም እንጅ (ሌላው) አይገሰጽም።} አላህ በዚህ አንቀፅ ውስጥ በነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ላይ ቁርኣንን ያወረደው እርሱ አላህ መሆኑን ይናገራል። ከቁርኣን ውስጥም መልእክታቸው ግልፅ የሆኑና ያለምንም ማደናገር ድንጋጌያቸው የታወቁ አንቀፆች አሉ። እርሱም የመጽሐፉ መሰረትና በልዩነት ወቅት የሚዳኝ ምንጭ ነው።

ቁርኣን ውስጥ በርካታ ትርጓሜን የሚሰጡ አሻሚ አንቀፆችም አሉ። እነዚህ አንቀፆችን አንዳንድ ሰዎች ወይ በትርጓው ይደናገራሉ ወይም ከሌላ አንቀፅ ጋር እንደተጋጨ ያስባሉ። ቀጥሎ አላህ ሰዎች ከነዚህ አንቀፆች ጋር ያላቸውን መስተጋብር አብራራ። እነዚያ ልቦቻቸውን ከሀቅ መጣመም የተጠናወተው ሰዎች ሰውን ማሳሳትና ብዥታን ማቀጣጠል በመፈለግ ግልፅ የሆኑትን አንቀፆች በመተው አሻሚ የሆኑትን አንቀፆች ይወስዳሉ። ይህንንም ያደረጉት ዝንባሌያቸውን በሚስማማ መልኩ መፍታትን በመፈለጋቸው ነው። በእውቀት የፀኑት ግን እነዚህን አሻሚ አንቀፆች ያውቃሉ ፍቻቸውንም ወደ ግልፅ አንቀፆች ይመልሳሉ፤ ከአላህ ዘንድ ስለሆነም እርስ በርስ ምንም መጋጨትና ማደናገር ሊከሰት እንደማይችል ያምናሉ። ነገር ግን የንፁህ አይምሮ ባለቤት ካልሆነ በቀር ሊገሰፅም ሆነ ሊመከር እንደማይችል አላህ ገለፀ። ቀጥለው ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ለአማኞች እናት ዓኢሻህ - አላህ መልካም ስራዋን ይውደድላትና - "እነዚያ አሻሚ አንቀፆችን የሚከታተሉትን ከተመለከተች አላህ {እነዚያማ በልቦቻቸው ውስጥ ጥመት ያለባቸው} በማለት የጠቀሳቸው ናቸውና ተጠንቀቋቸው አታድምጧቸው።" አሏት።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ከቁርኣን አንቀፆች ግልፅ የሚባሉት መልእክቱ ፍንትው ያለና ትርጉሙ ግልፅ የሆነ ነው። አሻሚ የሚባሉት ደግሞ ከአንድ በላይ በርካታ ትርጓሜ ያዘለ እንዲሁም ለመረዳት ጥናትና ግንዛቤ ያስፈለገው አንቀፅ ነው።
2. የጥመትና የቢድዐ ባለቤቶችን፣ ሰዎችን ለማሳሳትና ጥርጣሬ ውስጥ ለመክተት አወናባጅ ነጥቦችን የሚጥል ሰውን ከመቀላቀል መጠንቀቅ፤

3. የአንቀፁ መጨረሻ ክፍል ላይ {የአእምሮ ባለቤቶችም እንጅ (ሌላው) አይገሰጽም።} በሚለው የአላህ ንግግር ውስጥ ጠማሞችን መቃወምና በእውቀት የጠለቁትን ማሞገስ አለ። ማለትም፡- ያልተገሰፀና ያልተመከረ ስሜቱንም የተከተለ ከአእምሮ ባለቤቶች አይደለም ማለቱ ነው።
4. አሻሚ አንቀጾችን መከታተል ለልበና ጥመት መንስኤ ነው።
5. ትርጉማቸው የማይገባ የሆኑ አሻሚ አንቀጾችን ወደ ግልፅ አንቀጾች መመለስ ግዴታ መሆኑን፤
6. አላህ ሰዎችን ለመፈተንና የኢማን ባለቤቶች ከጥመት ባለቤቶች እንዲለዩ የቁርኣንን ከፊል ግልፅ ከፊሉን ደግሞ አሻሚ አድርጓል።
7. ቁርኣን ውስጥ አሻሚ አንቀጾች መካተታቸው ዑለሞች ከሌላው አንፃር ያላቸውን ደረጃ የሚገልፅና አይምሮ አቅሟ የተገደበ መሆኑን አውቃ ለፈጣሪዋ እጅ መስጠትና ድክመቷን ማወቅ እንዳለባት እንረዳለን።
8. በዕውቀት መጥለቅ ያለው ደረጃና በዕውቀት መፅናት አስፈላጊነቱን እንረዳለን።
9. {(ትክክለኛ) ፍቺውንም አላህ ብቻ እንጂ ሌላ አያውቀውም። በዕውቀትም የጠለቁትም} በሚለው አንቀፅ ላይ "አላህ" የሚለው ላይ ሲደርስ በመቆም ዙሪያ የተፍሲር ልሂቃን ዘንድ ሁለት አቋም አለ። "አላህ" የሚለው ጋር ሲደርስ የቆመ "ፍቺውን" በማለት የሚፈለገው:- ለማወቅ የማይቻል የሆኑ የአንድን ነገር ትክክለኛ ምንነትን ፍቺ አላህ እንጂ አያውቀውም። ለምሳሌ ስለነፍስ፣ ስለቂያማ ዕለትና ሌሎችም አላህ በዕውቀቱ የተነጠለበት ጉዳዮች። በእውቀት የጠለቁት ግን በሱ ያምናሉም ይቀበላሉም በዚህም ምክንያት ይድናሉ።
10. "አላህ" የሚለው ጋር ሲደርስ ያልቆመ "ፍቺውን" በማለት የተፈለገው "ትርጓሜውን" ማለት ይሆናል። ትርጓሜውን አላህና በእውቀት የጠለቁት ያውቁታል። ያምኑበታልም ወደ ግልፅ የቁርኣን አንቀፅም ይመልሱታል ማለት ይሆናል።

(65062)

(٥٣) - عن أبي سعيد الخُدْرِيِّ رضي الله عنه قال: سمعت رسول الله صلى الله عليه وسلم يقول: «مَنْ رَأَى مِنْكُمْ مُنْكَرًا فَلْيُغَيِّرْهُ بِيَدِهِ، فَإِنْ لَمْ يَسْتَطِعْ فَبِلِسَانِهِ، فَإِنْ لَمْ يَسْتَطِعْ فَبِقَلْبِهِ، وَذَلِكَ أَضْعَفُ الْإِيمَانِ». [صحيح] - [رواه مسلم]

(53) - አቡ ሰዒድ አል'ኹድሪይ አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንዲህ አሉ ፡- የአላህ መልክተኛ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ ሲሉ ሰምቻለሁ፡- "ከእናንተ መካከል መጥፎ ሢሠራ የተመለከተ፥በእጁ ይለውጠው (ያስተካክለው)፤ ይህንን ካልቻለ በምላሱ ይከላከል፤ ይህንንም ካልቻለ በቀልቡ (ልቡ) ይጥላ ይህ ግን ደካማው የኢማን ክፍል ነው።" [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን በቻልነው መጠን መጥፎ ነገርን እንድንለውጥ ( እንድናስወግድ) አዘዋል። መጥፎ ነገር የሚባለውም፥ አላህና መልክተኛው የከለከሏቸው ሁሉም ነገሮች ናቸው። መጥፎ ነገርን ከተመለከተ አቅም ካለው በእጁ የመለወጥ 0(የማስወግድ)ግዴታ አለበት። ይህን ማድረግ ከተሳነው ደግሞ መጥፎ ነገር ፈፃሚውን በመከልከል፣ ጉዳቱን ለሱ በማብራራት፣ ከዚህ እኩይ ተግባር ፈንታ እሱን ወደ መልካም በመምራት በአንደበቱ ይለውጠው። ይህኛዉ የመለወጥ እርከን ከተሳነውም ይህን መጥፎ ነገር በመጥላት፣ ለመለወጥ አቅም ቢኖረው ኖሮ እንደሚለውጠው በመቁረጥ በቀልቡ ይለውጠው። በቀልብ መለወጥ (መጥላት) መጥፎ ነገርን የመለወጥ እጅግ ደካማው የኢማን እርከን ነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ይህ ሐዲሠ መጥፎ ነገርን የማስወገድ እርከኖችን በማብራራት ረገድ መሰረት ነው ።
2. መጥፎን ነገር ደረጃ በደረጃ መከልከል እንደሚገባና፤ ሁሉም በችሎታውና በአቅሙ ልክ መከልከል እንደሚገባው መታዘዙ።

3. መጥፎን ነገር መከልከል ከማንም ላይ የማይወርድ ሀላፊነትና ሁሉም ሙስሊም በችሎታው ልክ እንዲሰራው የሚገደድበት የእስልምና ትልቅ ህግ (የዲን ምዕራፍ) ነው።
4. በመልካም ማዘዝና ከመጥፎ መከልከል ከኢማን ክፍሎች መካከል አንዱ መሆኑ፤ እንዲሁም ኢማን የሚጨምርና የሚቀንስ መሆኑ።
5. ከመጥፎ ለመከልከል የሚከለክሉት ድርጊት መጥፎ መሆኑን ማወቅ መስፈርት ነው።
6. መጥፎን ነገር ለመለወጥ ከተቀመጡ መስፈርቶች መካከል ፦ ከሚለውጠው መጥፎ ነገር የባሰ መጥፎ ውጤት አለማስከተሉ አንዱ ነው።
7. እያንዳንዱ ሙስሊም ሊያውቃቸው የሚገቡ ከመጥፎ ለመከልከል የተቀመጡ ስርአቶችና መስፈርቶች አሉ።
8. መጥፎን ማውገዝ ሸሪዓዊ ብልሀት ፣ ዕውቀት እና እርግጠኝነት (ማስረጃ) ይፈልጋል።
9. በቀልብ አለማውገዝ የኢማን ድክመትን ይጠቁማል።

(65001)

(٥٤) - عَنِ النُّعْمَانِ بْنِ بَشِيرٍ رَضِيَ اللهُ عَنْهُمَا عَنِ النَّبِيِّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ قَالَ: «مَثَلُ القَائِمِ عَلَى حُدُودِ اللهِ وَالوَاقِعِ فِيهَا، كَمَثَلِ قَوْمٍ اسْتَهَمُوا عَلَى سَفِينَةٍ، فَأَصَابَ بَعْضُهُمْ أَعْلاَهَا وَبَعْضُهُمْ أَسْفَلَهَا، فَكَانَ الَّذِينَ فِي أَسْفَلِهَا إِذَا اسْتَقَوْا مِنَ المَاءِ مَرُّوا عَلَى مَنْ فَوْقَهُمْ، فَقَالُوا: لَوْ أَنَّا خَرَقْنَا فِي نَصِيبِنَا خَرْقًا وَلَمْ نُؤْذِ مَنْ فَوْقَنَا، فَإِنْ يَتْرُكُوهُمْ وَمَا أَرَادُوا هَلَكُوا جَمِيعًا، وَإِنْ أَخَذُوا عَلَى أَيْدِيهِمْ نَجَوْا، وَنَجَوْا جَمِيعًا». [صحيح] - [رواه البخاري]

(54) - ከኑዕማን ቢን በሺር (ረዲየሏሁ ዐንሁማ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል፡- "በአላህ ድንበር ላይ በአግባቡ የቆሙና የርሱን ድንበር የሚተላለፉ ሰዎች ምሳሌ በመርከብ ላይ (ቦታ ለመምረጥ) እጣ እንደተጣጣሉ ሰዎች ምሳሌ ነው። (በእጣው መሰረት) ከፊሉን የመርከቡ የላይኛው ክፍል ሲደርሰው ከፊሉን ደግሞ የታችኛው ክፍል ደረሰው። የመርከቡ ታችኛው ክፍል ያሉት ውሃ ለመጠጣት የፈለጉ ጊዜ ላይኛው ክፍል ባሉት በኩል ያልፉ ነበርና "እኛም (ውሃ ለማግኘት) ፋንታችንን መርከቡን ብንሸነቁርና ከኛ በላይ ያሉትን ባናውካቸው መልካም ነው።" ተባባሉ። ከላይ ያሉት የታችኞቹ ፍላጎታቸውን እንዲፈፅሙ ከተዋቸው ሁሉም ይጠፋሉ። እጃቸውን ከያዙ ደግሞ እነሱም ይድናሉ። ሁሉም ይድናሉ።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) በአላህ ድንበር ላይ ለቆሙ፣ በአላህ ትእዛዝ ላይ ቀጥ ላሉ፣ በመልካም ለሚያዙና ከመጥፎ ለሚከለክሉ ሰዎች ምሳሌ አደረጉ። የአላህን ድንበር የሚተላለፉ፣ መልካምን የተዉና ውግዝን የሚተገብሩ ሰዎች በማህበረሰቡ መዳን ላይ የሚያሳድሩት አሻራ ምሳሌው በመርከብ እንደተሳፈሩ ሰዎች ምሳሌ ነው። የመርከቡ የላይኛው ክፍልና የታችኛው ክፍል የሚቀመጡውን ለመወሰን እጣ ተጣጣሉ። ከፊሉ የላይኛው ክፍል ሲደርሰው ከፊሉ ደግሞ ታችኛው ክፍል ደረሰው። ከታች በኩል ያሉት ውሃ ማምጣት የፈለጉ ጊዜ ከላያቸው ወዳሉት ያልፉ ነበር። ከታች

በኩል ያሉት "ባለንበት ስፍራ ከታች ብንቀደው ኖሮ በርሱ በኩል ውሃ እናገኝ ነበር። ከላያችን ያሉትንም አናስቸግርም ነበር።" አሉ። ከላይ በኩል ያሉት ይህንን እንዲፈፅሙ ከተዋቸው ሁሉንም እንደያዘች መርከቧ ትሰምጣለች። ከዚህ ተግባራቸው ለመከልከል ቆመው ማቀብ ከቻሉ ደሞ ሁለቱም ክፍሎች ባጠቃላይ ይድናሉ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ማህበረሰቡን ለመጠበቅና ለማዳን በመልካም ማዘዝና ከመጥፎ መከልከል አንገብጋቢ መሆኑን እንረዳለን።
2. ሀሳቡ ህዋሳዊ (በተጨባጭ ምስል ከሳች) በሆነ መልኩ ለአእምሮ ቀለል እንዲል ምሳሌዎችን መጠቀም ከማስተማር መንገዶች መካከል አንዱ ነው።
3. ግልፅ የሆነ ውግዝ ተግባር ያለምንም አውጋዥ መፈፀሙ ጉዳቱ ወደ ሁሉም የሚመለስ ብክለት ነው።
4. የማህበረሰብ ውድመት መጥፎ ሰዎች በምድር ላይ ብልሽትን ሲያሰራጩ ችላ ማለትን ተከትሎ የሚመጣ መዘዝ ነው።
5. የተሳሳተ እርምጃ በጥሩ ኒያም ቢሆን ስራን አያስተካክልም።
6. በሙስሊሙ ማህበረሰብ ውስጥ ያለ ተጠያቂነት የጋራ ነው እንጂ በግለሰብ ላይ ብቻ የሚወሰን አይደለም።
7. የውስን ሰዎች ወንጀል ካልተወገዘ ህዝቡን የሚጠቀልል ቅጣት እንደሚያስከስት እንረዳለን።
8. ልክ እንደሙናፊቆቹ የክፉ ስራ ባለቤቶችም መጥፎ ስራቸውን ለማህበረሰቡ ግልፅ የሚያደርጉት መልካም ስራ አስመስለው ነው።

(3341)

(٥٥) - عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ رضي الله عنه أَنَّ رَسُولَ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ قَالَ: «مَنْ دَعَا إِلَى هُدًى كَانَ لَهُ مِنَ الْأَجْرِ مِثْلُ أُجُورِ مَنْ تَبِعَهُ، لَا يَنْقُصُ ذَلِكَ مِنْ أُجُورِهِمْ شَيْئًا، وَمَنْ دَعَا إِلَى ضَلَالَةٍ كَانَ عَلَيْهِ مِنَ الْإِثْمِ مِثْلُ آثَامِ مَنْ تَبِعَهُ، لَا يَنْقُصُ ذَلِكَ مِنْ آثَامِهِمْ شَيْئًا». [صحيح] - [رواه مسلم]

(55) - ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል፦ "ወደ ቅናቻ የተጣራ ሰው የተከተሉትን ሰዎች አምሳያ ምንዳ ያገኛል። ይህም (ለርሱ የሚሰጠው ምንዳ) ከምንዳቸው አንዳች ሳይቀነስ ነው። ወደ ጥመት የተጣራ ሰውም የተከተሉትን ሰዎች አምሳያ ወንጀል ይኖርበታል። ይህም (በርሱ ላይ የሚኖረው ወንጀል) ከወንጀሎቻቸው ምንም ሳይቀነስ ነው።" [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

በንግግሩ ወይም በተግባሩ እውነትና መልካም ወዳለበት መንገድ ሰዎችን የመራ፣ የጠቆመና የቀሰቀሰ ሰው የተከታዩን አምሳያ ምንዳ እንደሚያገኝና ይህም ከተከታዩ ምንዳ አንዳችም ሳይቀነስ እንደሆነ ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ገለፁ። በንግግር ወይም በተግባር ወንጀልና ኃጢአት ወይም የማይፈቀድ ነገር ወዳለበት የጥመትና የክፋት መንገድ ሰዎችን የጠቆመ ሰውም የተከታዩን አምሳያ ወንጀልና ኃጢአት ይኖርበታል። ይህም ከነርሱ ወንጀል አንዳችም ሳይቀነስ ነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. በትንሹም ሆነ በብዛት ወደ ቅናቻ መጣራት ያለውን ደረጃ እንረዳለን። ተጣሪ ሰው በርሱ ጥሪ የሰሩ ሰዎችን ምንዳ አምሳያ ይኖረዋል። ይህም የአላህን ትልቅ ችሮታና ሙሉ ቸርነት ያስረዳናል።
2. በትንሹም ሆነ በብዛት ወደ ጥመት የመጣራትን አደጋ እንረዳለን። ወደ ጥመት የሚጣራም ሰው በሰበካው የሰራን ሰው ወንጀል አምሳያ በርሱ ላይ ይኖርበታል።

3. ምንዳ የሚሰጠው በስራው አይነት እንደሆነ እንረዳለን። ወደ መልካም የተጣራ ሰው በጥሪው የሰራን ሰው ምንዳ አምሳያ ለርሱ ይኖረዋል። ወደ መጥፎ የሰበከ ሰውም በሰበካው የሰራን ሰው ወንጀል አምሳያ በርሱ ላይ ይኖርበታል።
4. አንድ ሙስሊም ወንጀልን ግልፅ በማድረጉ ሰዎች አይተው እንዳይከተሉት መጠንቀቅ አለበት። በዚህ ላይ ሆን ብሎ ባይቀሰቅስ እንኳ በተከተሉት ሰዎች ልክ ወንጀል ላይ ይወድቃልና።

(3373)

(٥٦) - عن أبي مسعود الأنصاري رضي الله عنه قال: جَاءَ رَجُلٌ إِلَى النَّبِيِّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ فَقَالَ: إِنِّي أُبْدِعَ بِي فَاحْمِلْنِي، فَقَالَ: «مَا عِنْدِي»، فَقَالَ رَجُلٌ: يَا رَسُولَ اللهِ، أَنَا أَدُلُّهُ عَلَى مَنْ يَحْمِلُهُ، فَقَالَ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ: «مَنْ دَلَّ عَلَى خَيْرٍ فَلَهُ مِثْلُ أَجْرِ فَاعِلِهِ».

[صحيح] - [رواه مسلم]

(56) - ከአቡ መስዑድ አልአንሷሪይ -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው እንዲህ ብለዋል: አንድ ሰውዬ ወደ ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም በመምጣት "መንገድ ተቋርጦብኛልና የምጓጓዝበት እንስሳ ይስጡኝ?" አላቸው። እሳቸውም "የለኝም!" አሉት። ሌላ ሰውም "የአላህ መልክተኛ ሆይ! እኔ መጓጓዣ የሚሰጠውን እጠቁመዋለሁ!" አለ። የአላህ መልክተኛም ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም "ወደ መልካም የጠቆመ ሰው የሰሪውን ምንዳ አምሳያ ይመነዳል።" አሉ። [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

አንድ ሰውዬ ወደ ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም በመምጣት "እኔ ግመሌ ስለጠፋች የሚያደርሰኝን አንድ መጓጓዣ ይስጡኝ!" አላቸው። ነቢዩም ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እሳቸው የሚሰጡት ምንም ነገር እንደሌለ ነገሩት። እሳቸው ዘንድ የነበረ አንድ ሰውዬም "የአላህ መልክተኛ ሆይ! እኔ የሚሰጠውን ሰው እጠቁመዋለሁ።" አለ። የአላህ መልክተኛም ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ምፅዋት

ፈላጊን ለሚመፀውተው አካል በመጠቆሙ ምክንያት ከሚመፀውተው ሰው ጋር በአጅር እንደሚጋራ ተናገሩ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ወደ መልካም ነገር መጠቆም መበረታታቱን ፤
2. መልካም በመፈፀም ላይ መቀስቀስ የሙስሊሙ ማህበረሰብ እርስ በርስ እንዲተባበሩና እንዲዋሃዱ ከሚያደርጉ ምክንያቶች መካከል አንዱ መሆኑን ፤
3. የአላህ ችሮታ ሰፊ መሆኑን ፤
4. ሀዲሱ ሁሉን የሚያካትት መርህ ስለሆነ በውስጡ ሁሉም መልካም ስራዎች የሚገቡ መሆኑን ፤
5. የሰው ልጅ የጠያቂን ፍላጎት ማሳካት ካልተመቻቸለት ለጠያቂው የሚያሳካለትን ሌላ አካል መጠቆም እንዳለበት እንረዳለን።

(5354)

(٥٧) - عَنْ سَهْلُ بْنُ سَعْدٍ رَضِيَ اللهُ عَنْهُ أَنَّ رَسُولَ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ قَالَ يَوْمَ خَيْبَرَ: «لَأُعْطِيَنَّ هَذِهِ الرَّايَةَ غَدًا رَجُلًا يَفْتَحُ اللهُ عَلَى يَدَيْهِ، يُحِبُّ اللهَ وَرَسُولَهُ وَيُحِبُّهُ اللهُ وَرَسُولُهُ»، قَالَ: فَبَاتَ النَّاسُ يَدُوكُونَ لَيْلَتَهُمْ أَيُّهُمْ يُعْطَاهَا، فَلَمَّا أَصْبَحَ النَّاسُ غَدَوْا عَلَى رَسُولِ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ كُلُّهُمْ يَرْجُو أَنْ يُعْطَاهَا، فَقَالَ: «أَيْنَ عَلِيُّ بْنُ أَبِي طَالِبٍ؟» فَقِيلَ: هُوَ يَا رَسُولَ اللهِ يَشْتَكِي عَيْنَيْهِ، قَالَ: «فَأَرْسِلُوا إِلَيْهِ»، فَأُتِيَ بِهِ فَبَصَقَ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ فِي عَيْنَيْهِ وَدَعَا لَهُ، فَبَرَأَ حَتَّى كَأَنْ لَمْ يَكُنْ بِهِ وَجَعٌ، فَأَعْطَاهُ الرَّايَةَ، فَقَالَ عَلِيٌّ: يَا رَسُولَ اللهِ أُقَاتِلُهُمْ حَتَّى يَكُونُوا مِثْلَنَا؟ فَقَالَ: «انْفُذْ عَلَى رِسْلِكَ حَتَّى تَنْزِلَ بِسَاحَتِهِمْ، ثُمَّ ادْعُهُمْ إِلَى الإِسْلَامِ، وَأَخْبِرْهُمْ بِمَا يَجِبُ عَلَيْهِمْ مِنْ حَقِّ اللهِ فِيهِ، فَوَاللهِ لَأَنْ يَهْدِيَ اللهُ بِكَ رَجُلًا وَاحِدًا، خَيْرٌ لَكَ مِنْ أَنْ يَكُونَ لَكَ حُمْرُ النَّعَمِ».

[صحيح] - [متفق عليه]

(57) - ከሰህል ቢን ሰዕድ (ረዲየላሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) የኸይበር ቀን እንዲህ አሉ: "ነገ ይህንን ባንዲራ አላህ

በርሱ እጅ ድልን ለሚያጎናፅፍ፣ አላህና መልክተኛውን ለሚወድ፣ አላህና መልክተኛውም የሚወዱት ለሆነ ሰው እሰጠዋለሁ።" ሰዎችም ለማን ነው የሚሰጠው? በሚል ሌሊታቸውን ተጠምደውበት አደሩ። ሰዎችም ያነጉ ጊዜ ሁሉም ባንዲራው እንዲሰጠው ተስፋ በማድረግ የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ዘንድ ማልደው ሄዱ። እርሳቸውም "ዐሊይ ቢን አቢ ጧሊብ የት አለ? አሉ። ለርሳቸውም "የአላህ መልክተኛ ሆይ! አይኑን አሞታል" ተባሉ። እርሳቸውም "ሰው ላኩበት!" አሏቸው። እርሱም ተይዞ መጣና የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ዓይኑ ላይ ተፉና ዱዓ አደረጉለት። እርሱም ከዚህ በፊት ምንም በሽታ እንዳልነበረበት ሆኖ ተፈወሰ። ባንዲራውንም ሰጡት። ዐሊይም "የአላህ መልክተኛ ሆይ! እንደኛው አምሳያ እስኪሆኑ ድረስ ልዋጋቸውን?" በማለት ጠየቃቸው። እርሳቸውም አሉት: "ቀያቸው እስክትሰፍር ድረስ ተረጋግተህ ተጓዝ። ቀጥሎ ወደ እስልምና ጥራቸው። በነርሱ ላይ ግዴታ የሚሆንባቸውንም የአላህ ሐቅ ንገራቸው። በአላህ እምላለሁ! ለአንተ ቀይ ግመል ከሚኖርህ በአንተ ሰበብ አላህ አንድ ሰው ቢመራልህ የተሻለ ነው።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

በማግስቱ በኸይበር አይሁዶች ላይ ሙስሊሞች ድልን እንደሚጎናፀፉ ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ለሶሐቦች ነገሯቸው። ይህም እሳቸው ባንዲራ በሚሰጡት ሰው እጅ ነው። ይህም (ባንዲራ) ሰራዊቶች ለምልክትነት የሚይዙት አርማ ነው። ባንዲራው የሚሰጠው ሰው ባህሪም አላህና መልክተኛውን ይወዳል፣ አላህና መልክተኛውም ይወዱታል። ሶሐቦችም ይህንን ትልቅ ክብር በመፈለግ ባንዲራውን ስለሚሰጠው ሰው ማንነት ሲያወጉ ሌሊታቸውን ተጠምደውበት አደሩ። በማግስቱም ሁሉም ይህን ክብር መጎናፀፍን ተስፋ በማድረግ ወደ ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ሄዱ።

ነቢዩም (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ስለ ዐሊይ ቢን አቢጧሊብ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና ጠየቁ።

አይኖቹን እንደታመመ ነገሯቸው።

ነቢዩም (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ወደርሱ ሰው ላኩና ይዘውት መጡ። ከተከበረው ምራቃቸውም በዐሊ አይኖች ላይ ተፉና ዱዓ አደረጉለት። ምንም በሽታ እንዳልያዘው ሰው እስኪመስል ድረስ ከበሽታው ተፈወሰ። ባንዲራውንም ሰጡትና የጠላት ምሽግ እስኪቀርብ ድረስ በእርጋታ እንዲጓዝ አዘዙት። በነርሱ ላይም ወደ እስልምና እንዲገቡ ጥሪ እንዲያቀርብላቸው፤ እስልምናን ከተቀበሉት በነርሱ ላይ ያለባቸውን ግዴታ እንዲነግራቸው አዘዙት።

ቀጥለውም ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ወደ አላህ የመጣራት ትሩፋቱ አንድ ተጣሪ ለአንድ ሰው መመራት ሰበብ ከሆነ ይህ ለርሱ ዐረቦች ዘንድ ውድ ንብረት የሚባለውን ቀይ ግመል ከሚኖረው ወይም ኑሮት ሰደቃ ከሚሰጠው የበለጠ የተሻለ መሆኑን ለዐሊይ ገለፁለት።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. መልክተኛው (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ዐሊይን አላህና መልክተኛው እንደሚወዱት እርሱም አላህና መልክተኛውን እንደሚወድ መመስከራቸው የዐሊይን ቢን አቢ ጧሊብ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና ደረጃ ያስረዳናል።
2. ሶሐቦች ለመልካም ነገር ያላቸውን ጉጉትና እሽቅድድም እንረዳለን።
3. በውጊያ ወቅትም ቢሆን ስነ-ስርዓት እንደተደነገገና አላስፈላጊ የሆኑ አስደንጋጭ ድምጾችና መራወጥ መተው እንደሚገባ እንረዳለን።
4. የርሳቸውን ነቢይነትን (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ከሚጠቁሙ ነገሮች መካከል በየሁዶች ላይ ድል እንደሚያደርጉ ተናግረው መከሰቱና በአላህ ፈቃድ በርሳቸው እጅ የዐሊ ቢን አቢጧሊብ አይኖች መፈወሱ ነው።

5. ከጂሃድ የሚፈለገው ትልቁ አላማ ሰዎች ወደ እስልምና እንዲገቡ ማድረግ ነው።
6. ዳዕዋ (ጥሪ) ቀስ በቀስ ነው የሚከወነው። ከከሀዲ መጀመሪያ የሚፈለገው ሁለቱን የምስክርነት ቃላቶችን ተናግሮ ወደ እስልምና እንዲገባ ነው። ቀጥሎ ከዚህ በኋላ የእስልምና ግዴታዎችን ይታዘዛል።
7. ወደ እስልምናና እስልምና ውስጥ ወዳሉ መልካሞች በመጣራት የሚገኘው ትሩፋት ለተጣሪውም ለተጠሪውም ነው። ተጠሪው ቅኑን ጎዳና ያገኛል፤ ተጣሪው ደግሞ ትልቅ ምንዳ ይመነዳል።

(3409)

(٥٨) - عن ابنِ عُمَرَ رضي الله عنهما قال: قال رسولُ الله صلَّى الله عليه وسلم: «مَن تَشَبَّهَ بِقَوْمٍ فَهُوَ مِنْهُمْ». [حسن] - [رواه أبو داود وأحمد]

(58) - ከኢብኑ ዑመር -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው እንዲህ አለ: የአላህ መልክተኛ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንዲህ አሉ: "ከህዝቦች ጋር የተመሳሰለ እርሱ ከነርሱው ይመደባል።" [ሐሰን ነው።] - [አቡዳውድና አሕመድ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

የነርሱ መለዮ የሆነን እምነት ወይም አምልኮ ወይም ተለምዷዊ ነገርን በማድረግ ከከሀዲያን ወይም ከአመፀኞች ወይም ከደጋግ ህዝቦችም ጋር የተመሳሰለ ሰው ከነርሱ እንደሚመደብ ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ተናገሩ። ምክንያቱም በውጫዊ ማንነት ከነርሱ ጋር መመሳሰል በውስጣዊ ማንነት ከነርሱ ጋር ወደ መመሳሰል ያደርሳልና። ከሆኑ ህዝቦች ጋር መመሳሰል በነሱ የመደነቅ ውጤት መሆኑ ጥርጥር የሌለው ጉዳይ ነው። ቀስ በቀስም እነሱን ወደመውደድ ፣ ወደማላቅ፣ ወደነርሱ ጥገኛ ወደመሆን ያደርሳል። ይህም አላህ ይጠብቀንና ሰውዬውን በውስጣዊ አመለካከቱና አምልኮው ሳይቀር ከነርሱ ጋር ወደመመሳሰል ይጎትተዋል።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ከከሀዲያንና አመፀኛ ህዝቦች ጋር መመሳሰል መከልከሉን ፤
2. ከደጋጎች ጋር መመሳሰልና እነሱን መከተል መበረታታቱን ፤
3. በውጫዊ ማንነት መመሳሰል በውስጥ መውደድን እንደሚያወርስ ፤
4. ሰውዬው በተመሳሰለው ልክና አይነት ወንጀልና ዛቻ እንደሚያጋጥመው ፤
5. ከከሀዲያን ጋር እነሱ የተለዩበት በሆኑ እምነታቸውና ተለምዷቸው መመሳሰል መከልከሉን እንረዳለን። ይህ ባልሆነበት የተለያዩ ሙያዎችን መማርና የመሳሰሉት ግን ክልከላው ውስጥ አይካተትም።

(5353)

(٥٩) - عن أبي هريرة رضي الله عنه أن النبيَّ صَلّى اللهُ عَلَيْهِ وسَلَّم قَالَ: «الرَّجُلُ عَلَى دِينِ خَلِيلِهِ، فَلْيَنْظُرْ أَحَدُكُم مَنْ يُخَالِل». [حسن] - [رواه أبوداود والترمذي وأحمد]

(59) - ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው : ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል: "ሰውዬው በጓደኛው ሃይማኖት ላይ ነው። አንዳችሁ የሚጎዳኘውን ሰው ይመልከት።" [ሐሰን ነው።] - [አቡዳውድ፣ ቲርሚዚና አሕመድ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) የሰው ልጅ ፍፁም ጓደኛውንና ባልደረባውን በልማዱና ኑሮው እንደሚመሳሰል፤ ጓደኝነትም በስነምግባር፣ በባህሪና የኑሮ ዘይቤ ላይ ተፅዕኖ እንደሚያሳድር ገለፁ። ለዚህም ጓደኛ አመራረጣችንን እንድናሳምር ጠቆሙ። ምክንያቱም ጥሩ ጓደኛ ወደ ኢማን፣ ቅናቻና መልካም ነገር ይጠቁማል። ለባልደረባውም አጋዥ ይሆናልና።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. መልካሞችን በመወዳጀትና በመምረጥ መታዘዙን፤ መጥፎዎችን መወዳጀት ደግሞ መከልከሉን እንረዳለን።
2. ከዘመድ ይልቅ ጓደኛን ብቻ ለይተው መጥቀሳቸው ጓደኛ አንተ ራስህ ነህ የምትመርጠው ስለሆነ፤ ወንድምና ቅርብ ዘመድ ግን አንተ ምንም ምርጫ ስለሌለህ ነው።
3. ጓደኛን መያዝ የግድ ከማስተዋል በኋላ የመጣ መሆን አለበት።
4. አንድ ሰው አማኞችን በመወዳጀት ዲኑን እንደሚያጠነክርና አመፀኞችን በመወዳጀት ደግሞ እንደሚያደክመው እንረዳለን።

(3122)

(٦٠) - عن تَميم الداري رضي الله عنه، قال: سمعتُ رسول الله صلى الله عليه وسلم يقول: «لَيَبْلُغَنَّ هَذَا الْأَمْرُ مَا بَلَغَ اللَّيْلُ وَالنَّهَارُ، وَلَا يَتْرُكُ اللهُ بَيْتَ مَدَرٍ وَلَا وَبَرٍ إِلَّا أَدْخَلَهُ اللهُ هَذَا الدِّينَ، بِعِزِّ عَزِيزٍ أَوْ بِذُلِّ ذَلِيلٍ، عِزًّا يُعِزُّ اللهُ بِهِ الإِسْلَامَ، وَذُلًّا يُذِلُّ اللهُ بِهِ الكُفْرَ» وَكَانَ تَمِيمٌ الدَّارِيُّ يَقُولُ: قَدْ عَرَفْتُ ذَلِكَ فِي أَهْلِ بَيْتِي، لَقَدْ أَصَابَ مَنْ أَسْلَمَ مِنْهُمُ الْخَيْرُ وَالشَّرَفُ وَالْعِزُّ، وَلَقَدْ أَصَابَ مَنْ كَانَ مِنْهُمْ كَافِرًا الذُّلُّ وَالصَّغَارُ وَالْجِزْيَةُ. [صحيح] - [رواه أحمد]

(60) - ከተሚም አድዳሪይ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: «የአላህ መልክተኛን (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ሲሉ ሰምቻቸዋለሁ: "የዚህ ሃይማኖት ጉዳይ ቀንና ምሽት የደረሰበት ስፍራ ሁሉ ይደርሳል። አላህ፤ በሀያሉ ሀይልም ይሁን በውርደታሞች ውርደት ይህንን ሃይማኖት እያንዳንዱ የግንብ (የከተማ) ቤት ውስጥም ይሁን የሳር ቤት (የገጠር ቤት) ውስጥ ሳያስገባው አይቀርም። ወይ አላህ በርሱ ኢስላምን የበላይ በሚያደርግበት ሀይል አልያም አላህ በርሱ ክህደትን በሚያዋርድበት ውርደት (ኢስላም የበላይነቱን ይጎናፀፋል)።"» ተሚም አድዳሪም እንዲህ ይል ነበር "ይህንንም በወገኖቼ አወቅኩት። ከወገኖቼ የሰለሙት መልካምን፣ ልቅናና ክብርን አገኙ። ከወገኖቼ

መካከል የካዱትንም ውርደት፣ የበታችነትና ግብር አገኛቸው።" [ሶሒሕ ነው።] - [አሕመድ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ይህ ሃይማኖት የምድርን አጠቃላይ ክፍል እንደሚያዳርስ፣ ማንኛውም ሌሊትና ቀን የተፈራረቀበት ስፍራ ሁሉ ይህ እምነት እንደሚደርሰው ተናገሩ። አላህ አንድንም ከተማና መንደር ሆነ አልያም ገጠርና በረሃ ይህ እምነት እንዲገባበት ሳያደርግ እንደማይተወው ተናገሩ። ይህንን ሃይማኖት ተቀብሎ ያመነበት ሰው በእስልምና ልቅና የበላይ ይሆናል። ይህንን ሃይማኖት አልቀበል ያለና የካደበት ደግሞ የተዋረደና የበታች ይሆናል።

ቀጥሎ ሶሐባው ተሚም አድዳሪይ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና ይህን የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) የተናገሩበትን ጉዳይ ልዩ በሆነ መልኩ በቤተሰቦቹ ውስጥ እንዳስተዋለው ተናገረ። ከነርሱ መካከል የሰለሙት መልካምን፣ ክብርና ልቅናን ያገኙ ሲሆን ከነርሱ መካከል የካዱት ደግሞ ለሙስሊሞች ከሚሰጡት ገንዘብ ተጨማሪ ውርደትና የበታቸኝነትን አግኝቷቸዋል።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ሙስሊሞች ሃይማኖታቸው በምድር ክፍል ባጠቃላይ መሰራጨቱ እንደማይቀር ተነግሯቸው መበሰራቸው።
2. ልቅና የእስልምናና የሙስሊሞች ሲሆን ውርደት ደግሞ የክህደትና የከሀዲያን ነው።
3. እዚህ ሐዲሥ ውስጥ ከነቢይነት ምልክቶች መካከል አንዱ አለ። ይህም ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንደተናገሩት በመከሰቱ ነው።

(11220)

(٦١) - عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ رضي الله عنه عَنْ رَسُولِ اللهِ صلى الله عليه وسلم أنه قال: «وَالَّذِي نَفْسُ مُحَمَّدٍ بِيَدِهِ لَا يَسْمَعُ بِي أَحَدٌ مِنْ هَذِهِ الْأُمَّةِ يَهُودِيٌّ وَلَا نَصْرَانِيٌّ، ثُمَّ يَمُوتُ وَلَمْ يُؤْمِنْ بِالَّذِي أُرْسِلْتُ بِهِ إِلَّا كَانَ مِنْ أَصْحَابِ النَّارِ». [صحيح] - [رواه مسلم]

(61) - ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል: "ያ የሙሐመድ ነፍስ በእጁ በሆነችው ጌታ እምላለሁ! ከዚህ ኡመት ውስጥ አንድም አይሁድ ይሁን ክርስቲያን ስለኔ ሰምቶ ከዚያም በዛ በተላኩበት ሳያምን የሚሞት የለም። ከእሳት ጓዶች መካከል ቢሆን እንጂ" [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ከዚህ ሕዝብ (ኡመት) ሆኖ የነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ጥሪ የደረሰውና ስለርሳቸው የሚሰማ ሆኖ ከዚያም በርሳቸው ሳያምን የሚሞት አንድም አይሁዳዊም ይሁን ክርስቲያን ወይም ሌላ እምነት ተከታይ የለም ዘልአለሙን የእሳት ሰው ቢሆን እንጂ።' ብለው ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ማሉ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. የነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) መልክተኝነት ዓለምን በሙሉ የሚጠቀልል መሆኑን፣ እሳቸውን መከተልም ግዴታ መሆኑን፣ በሳቸው ድንጋጌ ሁሉም ድንጋጌዎች መሻራቸውንም እንረዳለን።
2. በነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) የካደ ሰው ከሳቸው ውጪ ባሉ ነቢያቶች የአላህ ሶላትና ሰላም በነርሱ ላይ ይስፈንና እንደሚያምን መሞገቱ አይጠቅመውም።
3. ስለ ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ያልሰማና የኢስላም ጥሪ ያልደረሰው ሰው ተቀባይነት ያለው ምክንያት ስላለው የርሱ ጉዳይ በመጨረሻው አለም አላህ ዘንድ ነው።

4. ነፍስ ልትወጣ ጉሮሮ ላይ እስካልደረሰች ድረስ ከባድ በሽታ ላይ ሆኖ እንኳ ቢሆን የሰለመ እስልምናው ከመሞቱ በፊት እስከሆነ ድረስ በኢስላም የሚገኘው ጥቅም የተረጋገጠ ነው።
5. የከሀዲያንን ሃይማኖት ትክክለኛ እምነት አድርጎ ማሰብ ክህደት ነው። (ከነርሱም ውስጥ አይሁድና ክርስትና ይገኛሉ።)
6. አይሁድና ክርስትናን በሐዲሡ ውስጥ መጠቀሳቸው ከነርሱ ውጪ ያሉትን አፅንኦት ለመስጠት ነው። ይህም አይሁድና ክርስቲያኖች መጽሐፍ እያላቸውም የነርሱ ጉዳይ እንዲህ ከሆነ ከነርሱ ውጪ መጽሐፍ የሌላቸው ደሞ በበለጠ መልኩ መንገድ የሐዲሡ መልእክት ውስጥ ይገባሉ። ስለሆነም ሁሉም በነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እምነትና መመርያ ውስጥ መግባት ግዴታቸው ነው።

(3272)

(٦٢) - عَنْ ابْنِ عَبَّاسٍ رضي الله عنهما قَالَ: قَالَ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ غَدَاةَ الْعَقَبَةِ وَهُوَ عَلَى نَاقَتِهِ: «الْقُطْ لِي حَصًى» فَلَقَطْتُ لَهُ سَبْعَ حَصَيَاتٍ، هُنَّ حَصَى الْخَذْفِ، فَجَعَلَ يَنْفُضُهُنَّ فِي كَفِّهِ وَيَقُولُ: «أَمْثَالَ هَؤُلَاءِ فَارْمُوا» ثُمَّ قَالَ: «أَيُّهَا النَّاسُ، إِيَّاكُمْ وَالْغُلُوَّ فِي الدِّينِ، فَإِنَّمَا أَهْلَكَ مَنْ كَانَ قَبْلَكُمْ الْغُلُوُّ فِي الدِّينِ». [صحيح] - [رواه ابن ماجه والنسائي وأحمد]

(62) - ከኢብኑ ዓባስ (ረዲየሏሁ ዐንሁማ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: "የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) የጀምረተል ዐቀባህ መወርወሪያ ንጋት ላይ ግመላቸው ላይ ሆነው 'ጠጠር ልቀምልኝ!' አሉኝ። ሰባት ጠጠርም ለቀምኩላቸው። እነርሱም ትናንሽ በጣት መሀል የሚወረወሩ ጠጠሮች ነበሩ። መዳፋቸው ላይ አኑረው እያገላበጧቸውም 'እንደነዚህ ልክ ወርውሩ!' አሉ። ቀጥለውም 'እናንተ ሰዎች ሆይ! በሃይማኖት ላይ ወሰን ከማለፍ ተጠንቀቁ! ከናንተ በፊት የነበሩትን ህዝቦች ያጠፋቸው በሃይማኖት ላይ ወሰን ማለፍ ነው።' አሉ።" [ሶሒሕ ነው።] - [ኢብኑ ማጀህ፣ ነሳኢና አሕመድ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ኢብኑ ዓባስ (ረdiየሏሁ ዐንሁማ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - የመሰናበቻ ሐጅ ወቅት የእርድ ቀን ጀምረተል ዐቀባ ንጋት ላይ ከነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ጋር እንደነበረ ተናገሩ። የሚወረውሩት ጠጠር እንዲለቅምላቸው አዘዙት። እርሱም ሰባት ጠጠሮች ለቀመላቸው። እያንዳንዱም ጠጠር የሽንብራ ወይም የለውዝ ፍሬ መጠን ነበር ያላቸው። ነቢዩም (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) በእጃቸው ላይ አኑረውት ጠጠሮቹን መደፋቸው ላይ እያንከባለሉ እንዲህ አሉ: የምትወረውሩት ጠጠር በዚህ ልክ ይሁን። ቀጥለውም ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) በሃይማኖታዊ ጉዳዮች ወሰን ከማለፍና ከማክረር አስጠነቀቁ። የቀደሙ ህዝቦችን ያጠፋው ወሰን ማለፍና በሃይማኖት ላይ ከልክ በላይ ማክረር መሆኑንም ተናገሩ።

## ከሐዲሡ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. በሃይማኖት ላይ ወሰን ከማለፍ መከልከሉንና ፍፃሜው የከፋ መሆኑን እንዲሁም ለጥፋትም ምክንያት መሆኑ መገለፁን እንረዳለን።
2. ከወደቁበት ስህተት ለመራቅ ሲባል ከቀደሙን ህዝቦች ትምህርት መውሰድ ተገቢ መሆኑን እንረዳለን።
3. ሱናን በመከተል ላይ መነሳሳቱን እንረዳለን።

(3395)

(٦٣) - عن عبد الله بن مسعود قال: قال رسول الله صلى الله عليه وسلم: «هلك المُتَنَطِّعُون» قالها ثلاثًا. [صحيح] - [رواه مسلم]

(63) - ዐብደሏህ ቢን መስዑድ ረዲየሏሁ ዐንሁ እንዲህ ማለቱ ተላልፏል፡ "የአሏህ መልዕክተኛ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ አሉ፡ 'ፅንፈኞች (ወሰን አላፊዎች) ጠፉ!' ሶስት ጊዜ ደጋገሟት።" [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ያመጡትን ሸሪዓዊ ወሰን ያለ ምንም መመሪያና እውቀት ወሰን ተላልፈው በንግግራቸውም ይሁን በተግባራቸው በእምነታቸውም ይሁን በአለማዊ ጉዳያቸው ፅንፍ የሚረግጡ ሰዎች ያለባቸውን ውርደትና ኪሳራ ተናገሩ።

## ከሐዲሡ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. በየትኛውም ጉዳይ በተለይም በዒባዳና ፃድቃንን በማላቅ ረገድ ወሰን ማለፍና ያላቅም መንጠራራት መከልከሉ፤ ከእንዲህ አይነቱ ነገር መራቁ በየትኛውም ጉዳይ ላይ እንደሚበረታታ፤
2. በአምልኮም ይሁን በሌላው ጉዳይ ተስተካክሎ የተሟላውን መፈለግ እንደሚገባ፤ ይህም የሚሆነው ሸሪዓውን በመከተል መሆኑ፤

3. አሳሳቢ ጉዳይ ላይ ጠንከር ማድረግ እንደሚገባ፤ ምክንያቱም ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ይህንኑ እንኳ ሲናገሩ ሶስት ጊዜ ደጋግመው ነውና የተናገሩት።
4. የእስልምና ገራገርነትና ቀላልነትን እንረዳለን።

(3420)

(٦٤) - عَنْ عَدِيِّ بْنِ حَاتِمٍ عَنِ النَّبِيِّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ قَالَ: «الْيَهُودُ مَغْضُوبٌ عَلَيْهِمْ، وَالنَّصَارَى ضُلَّالٌ». [صحيح] - [رواه الترمذي]

(64) - ከዓዲይ ቢን ሓቲም እንደተላለፈው: "ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ አሉ፦ "አይሁዶች ቁጣ የሰፈነባቸው ሲሆኑ ክርስቲያኖች ደግሞ የተሳሳቱ ናቸው።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቲርሚዚ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) አይሁዶች እውነትን እያወቁ ባለመተግበራቸው አላህ የተቆጣባቸው ህዝቦች እንደሆኑ ተናገሩ። ክርስቲያኖች ደግሞ ያለ ዕውቀት የሚሰሩ ስለሆኑ የተሳሳቱ ህዝቦች ናቸው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ዕውቀትና ተግባርን ሰብስቦ መሄድ ቁጣ ከሰፈነባቸውም ከተሳሳቱትም ሰዎች መንገድ መዳኛ መሆኑን እንረዳለን።
2. ከአይሁዶችና ክርስቲያኖች መንገድ መጠንቀቅና ቀጥተኛ የሆነውን የኢስላምን ጎዳና አጥብቀን መያዝ እንዳለብን እንረዳለን።
3. በመሰረቱ አይሁዶችም ክርስቲያኖችም የተሳሳቱና ቁጣ የሰፈነባቸው ህዝቦች ናቸው። ነገር ግን ልዩ መገለጫቸው የአይሁዶቹ ቁጣ የሰፈነባቸው መሆናቸው ሲሆን የክርስቲያኖች ልዩ መገለጫ ደግሞ መሳሳታቸው ነው።

(65061)

(٦٥) - عَنْ عَبْدِ اللهِ بْنِ عَمْرِو بْنِ الْعَاصِ رضي الله عنهما قَالَ: سَمِعْتُ رَسُولَ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ يَقُولُ: «كَتَبَ اللهُ مَقَادِيرَ الْخَلَائِقِ قَبْلَ أَنْ يَخْلُقَ السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضَ بِخَمْسِينَ أَلْفَ سَنَةٍ، قَالَ: وَعَرْشُهُ عَلَى الْمَاءِ». [صحيح] - [رواه مسلم]

(65) - ዐብደላህ ቢን ዐምር ቢን ዐስ -አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንዲህ አሉ፦ የአላህን መልክተኛ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ ሲሉ ሰምቻቸዋለሁ፦ "አላህ ሰማያትንና ምድርን ከመፍጠሩ ከሀምሳ ሺህ ዓመት በፊት የፍጡራንን ውሳኔ ፅፏል።" እንዲህም አሉ፦ " ዐርሹ ውኃ ላይ ነው።" [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

**ትንታኔ:**

ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን አላህ በፍጡራኖች ላይ የሚከሰተውን ውሳኔዎች ህይወት፣ ሞት፣ ሲሳይና ሌሎችንም ሰማያትንና ምድርን ከመፍጠሩ ከሀምሳ ሺህ ዓመት በፊት በዝርዝር በጥብቅ ሰሌዳ ውስጥ እንደፃፈውና እሱም አላህ በወሰነው መልኩ የሚከሰት መሆኑን ተናገሩ። ሁሉም የሚከሰቱ ነገሮች በአላህ ፍርድና ውሳኔ መሰረት ነው። አንድ ሰውን ያገኘው ነገር ቀድሞውኑ ሊስተው አይችልም ነበር፤ የሳተውም ነገር ሊያገኘው አይችልም ነበር።

**ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:**

1. በአላህ ፍርድና ቅድመ ውሳኔ ማመን ግዴታ መሆኑ፤
2. ቀደር (ውሳኔ) ሲባል :- አላህ በነገሮች ላይ ያለውን ዕውቀት፣ መፃፉን፣ መሻቱንና መፍጠሩን የሚያጠቃልል መሆኑን።
3. ሰማያትና ምድር ከመፈጠራቸው በፊት ውሳኔዎች እንደተፃፉ ማመን በሚያጋጥሙን ነገሮች መውደድና መቀበልን ይፈይደናል።
4. ሰማያትና ምድር ከመፈጠራቸው በፊት የአርረሕማን ዐርሽ ውኃ ላይ ነበር።

(65038)

(٦٦) - عَنْ عَبْدِ اللهِ بْنِ مَسْعُودٍ رَضِيَ اللهُ عَنْهُ: حَدَّثَنَا رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ وَهُوَ الصَّادِقُ المَصْدُوقُ: «أَنَّ خَلْقَ أَحَدِكُمْ يُجْمَعُ فِي بَطْنِ أُمِّهِ أَرْبَعِينَ يَوْمًا وَأَرْبَعِينَ لَيْلَةً، ثُمَّ يَكُونُ عَلَقَةً مِثْلَهُ، ثُمَّ يَكُونُ مُضْغَةً مِثْلَهُ، ثُمَّ يُبْعَثُ إِلَيْهِ المَلَكُ، فَيُؤْذَنُ بِأَرْبَعِ كَلِمَاتٍ، فَيَكْتُبُ: رِزْقَهُ وَأَجَلَهُ وَعَمَلَهُ وَشَقِيٌّ أَمْ سَعِيدٌ، ثُمَّ يَنْفُخُ فِيهِ الرُّوحَ، فَإِنَّ أَحَدَكُمْ لَيَعْمَلُ بِعَمَلِ أَهْلِ الجَنَّةِ حَتَّى لاَ يَكُونَ بَيْنَهَا وَبَيْنَهُ إِلَّا ذِرَاعٌ، فَيَسْبِقُ عَلَيْهِ الكِتَابُ، فَيَعْمَلُ بِعَمَلِ أَهْلِ النَّارِ فَيَدْخُلُ النَّارَ، وَإِنَّ أَحَدَكُمْ لَيَعْمَلُ بِعَمَلِ أَهْلِ النَّارِ حَتَّى مَا يَكُونُ بَيْنَهَا وَبَيْنَهُ إِلَّا ذِرَاعٌ، فَيَسْبِقُ عَلَيْهِ الكِتَابُ، فَيَعْمَلُ عَمَلَ أَهْلِ الجَنَّةِ فَيَدْخُلُهَا». [صحيح] - [متفق عليه]

(66) - ዐብደላህ ቢን መስዑድ -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንዲህ አሉ: እውነተኛና (ይዘውት በመጡትም ሁሉ) እውነተኛ የተባሉት የአላህ መልክተኛ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም (ይህንን) ነገሩን፦ "የአንዳችሁ ፍጥረት በእናቱ ሆድ ውስጥ ለአርባ ቀንና ምሽት ይሰበሰባል። ከዚያም የዛኑ ቀናት አምሳያ የረጋ ደም ይሆናል፤ ከዚያም የዛኑ ቀናት አምሳያ ቁራጭ ስጋ ይሆናል፤ ከዚያም ወደርሱ መልዐክ ይላካል ፤ መልዐኩ አራት መልእክቶች ይታዘዛል፤ ሲሳዩን፣ የሞት ቀጠሮውን፣ ስራውንና እድለቢስ ወይም እድለኛ መሆኑን ይጻፋል። ከዚያም በውስጡ ነፍስ ይነፋበታል። አንዳችሁ በርሱና በጀነት መካከል የክንድ ያህል ርቀት እስኪቀር ድረስ የጀነት ሰዎችን ስራ ይሰራል። በርሱ ላይ የተጻፈው መጽሐፉ

(ወሰኔ) ይቀድምና የእሳት ጉዶችን ስራ ይሰራና እሳት ይገባል። አንዳችሁ በርሱና በእሳት መካከል የክንድ ያህል ርቀት እስኪቀር ድረስ የእሳት ሰዎችን ስራ ይሰራል። በርሱ ላይ የተጻፈው መጽሐፉ (ወሰኔ) ይቀድምና የጀነት ባለቤቶችን ስራ ይሰራና ጀነት ይገባል።"[ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ኢብኑ መስዑድ እንዲህ አለ፦ በንግግራቸው እውነተኛ የሆኑትና አላህ እውነተኛነታቸውን በማረጋገጡ እውነተኛ የተባሉት የአላህ መልክተኛ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ነገሩን: ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም

በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ አሉ፦ "አንዳችሁ ፍጥረቱ ይሰበሰባል" ይህም አንድ ወንድ ባለቤቱን የተገናኘ ጊዜ የተበታተነው ዘር ፈሳሹ በሴቷ ማህጸን ውስጥ ለአርባ ቀን የዘር ፈሳሽ ሆኖ ይሰበሰባል። ከዚያም የረጋ ደም ይሆናል። ይህም የደረቀ ወፍራም ደም ነው። ይህ በሁለተኛው አርባ የሚከሰት ነው። ከዚያም ቁራጭ ስጋ ይሆናል። ይህም የሚታኘክ የሚያህል ቁራጭ ስጋ ነው። ይህ በሶስተኛው አርባ የሚከሰት ነው። ከዚያም ወደርሱ አላህ መልዐክ ይልካል። ሶስተኛው አርባ ከተጠናቀቀ በኋላ ፅንሱ ውስጥ ሩሕ (ነፍስ) ይነፋበታል። መልዐኩ አራት ን መልእክቶችን እንዲጽፍ ይታዘዛል። እነሱም:- ሲሳዩን: ይህም በእድሜው ውስጥ ምን ያህል መጠን ነው የሚያገኘው ፀጋ የሚለውን ነው። የሞት ቀጠሮውን:- ይህም በዱንያ ውስጥ የሚቆይበትን ዘመን ነው። ሥራውን:- ምንድነው እሱ? እድለቢስ ነው ወይስ እድለኛ? ከዚያም ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ማሉ። አንዱ የጀነት ሰዎችን ሥራ ይሠራል፤ ሥራው ለሰዎች በሚታየው መልካም ይሆናል፤ በርሱና በጀነት መካከል የክንድ ያህል እስኪቀር በዚው መልክ ይቀጥላል። ማለትም አንድ ያሰበው ቦታ ለመድረስ አንድ ክንድ እንደቀረው ሰው በርሱና ጀነት በመግባት መካከልም አንድ ክንድ በስተቀር ምንም አይቀርም። በርሱ ላይ የተወሰነው መጽሐፉ ይቀድምና በዛን ወቅት የእሳት ሰዎችን ስራ ይሰራና በዛው ላይ ፍፃሜው ይሆናል። እሳትም ይገባል። ሥራ ተቀባይነት እንዲያገኝ አንዱ መስፈርት በዛው ላይ መፅናትና አለመለወጥ ነውና። ከሰዎች ሌላኛው ደግሞ እሳት ለመግባት እስኪቀርብ ድረስ የእሳት ባለቤቶችን ሥራ ይሠራል፤ በርሱና በእሳት መካከል የምድር አንድ ክንድ ያህል የቀረው እስኪመስል ድረስ፤ በርሱ ላይ የተወሰነው መጽሐፉ ይቀድምና የጀነት ባለቤቶችን ስራ ይሰራና ጀነት ይገባል።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. የነገሮች ፍፃሜ መዳረሻቸው በቀደመው ውሳኔና በተፃፈው ፍርድ መሰረት ነው።

2. ሥራዎች የሚለኩት በፍፃሜያቸው ስለሆነ በሥራዎች ይዘት ከመሸወድ ማስጠንቀቅን ተረድተናል።

(65037)

(٦٧) - عن ابن مسعود رضي الله عنه قال: قال النبي صلى الله عليه وسلم: «الْجَنَّةُ أَقْرَبُ إِلَى أَحَدِكُمْ مِنْ شِرَاكِ نَعْلِهِ، وَالنَّارُ مِثْلُ ذَلِكَ». [صحيح] - [رواه البخاري]

(67) - ኢብኑ መስዑድ ረዲየሏሁ ዐንሁ እንዲህ ማለቱ ተላልፏል፡ "የአሏህ መልዕክተኛ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ ብለዋል፡ "ጀነት ወደ እያንዳንዳችሁ ከጫማው ማሰሪያ የበለጠ ቅርብ ናት። እሳትም እንደዚሁ።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ለሰው ልጅ ጀነትም ይሁን ጀሀነም በእግሩ ላይ እንዳለው የጫማው ማሰሪያ ቅርብ መሆናቸውን ተናገሩ። ምክንያቱም (ሳያስበው) አሏህን የሚያስደስት የሆነን መልካም ስራ ይሰራና በዛ ሰበብ ጀነት ይገባል። ወይም መጥፎ ስራ ይሰራና ጀሀነም ለመግባት ሰበብ ይሆንበታል።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ትንሽ ቢሆንም መልካም ስራ ላይ መበርታት፤ ትንሽ ቢሆንም ከክፋት መጠንቀቅ እንደሚገባ፤
2. ሙስሊም በህይወቱ በራሱ ሁኔታ ሳይሸወድ ሁሌም በተስፋና በስጋት መካከል ሊሆን እና እውነት ላይ እንዲያፀናውም ጥራት የተገባው አሏህን ሊማፀን የግድ እንደሚገባው እንረዳለን።

(3581)

(٦٨) - عن أبي هريرة رضي الله عنه أن رسول الله صلى الله عليه وسلم قال: «حُجِبَتِ النَّارُ بِالشَّهَوَاتِ، وَحُجِبَتِ الْجَنَّةُ بِالْمَكَارِهِ». [صحيح] - [رواه البخاري]

(68) - ከአቢ ሁረይራ ረዲየሏሁ ዐንሁ እንደተላለፈው ረሱል የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ ብለዋል፡ "ጀሀነም ነፍስያ በምትወዳቸው ስሜታዊ ነገሮች ተጋረደች፤ ጀነት ደግሞ ነፍስ በምትጠላቸው ነገሮች ተጋረደች።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ጀሀነም ክልክልን በመዳፈርና ግዴታን ባለመወጣት የመሰሉ ነፍስያ በምትፈልጋቸው ነገሮች መሸፈኗን መከበቧን ገለፁ። በመሆኑም የነፍስያውን ፍላጎት በዚህ ረገድ የተከተለ ለጀሀነም ተገባ። ጀነት ደግሞ ትእዛዝ ላይ በመዘውተር፣ ክልከላን በመተውና በዚሁ ላይ ትዕግስት በማድረግ በመሰሉ ነፍስያ በምትጠላቸው ነገሮች መሸፈኗንና መከበቧን አብራሩ። ስለዚህም በዚህ ረገድ በቁርጠኝነት ነፍስያውን የታገለ ለጀነት የተገባ ሆነ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. በስሜት ላይ ለመውደቅ ሰበብ ከሚሆኑ መሰናክሎች መካከል አስቀያሚና የተወገዘ የሆነውን ነገር ነፍስያ ወዳው እስክትዘነበልለት ድረስ ሸይጧን ማስዋቡ አንዱ መሆኑን፤
2. ወደ ጀሀነም እሳት መዳረሻ ከመሆናቸው አንፃር ከተከለከሉ ፍላጎቶች መራቅና ወደ ጀነት የሚያደርሱ ከመሆናቸው አንፃርም የምንጠላቸው ነገሮች ላይ መታገስን መታዘዛችን ፤
3. ነፍስያን መታገል፣ በዒባዳ ላይም መትጋት፣ በአምልኮ ዙርያ ያሉ የምንጠላቸውና የሚያስቸግሩን ነገሮች ላይም መታገስ ያለውን ትሩፋት እንረዳለን።

(3702)

(٦٩) - عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ رضي الله عنه عَنْ رَسُولِ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ قَالَ: «لَمَّا خَلَقَ اللهُ الْجَنَّةَ وَالنَّارَ أَرْسَلَ جِبْرِيلَ عَلَيْهِ السَّلَامُ إِلَى الْجَنَّةِ، فَقَالَ: انْظُرْ إِلَيْهَا وَإِلَى مَا أَعْدَدْتُ لِأَهْلِهَا فِيهَا. فَنَظَرَ إِلَيْهَا فَرَجَعَ، فَقَالَ: وَعِزَّتِكَ لَا يَسْمَعُ بِهَا أَحَدٌ إِلَّا دَخَلَهَا. فَأَمَرَ بِهَا فَحُفَّتْ بِالْمَكَارِهِ، فَقَالَ: اذْهَبْ إِلَيْهَا فَانْظُرْ إِلَيْهَا وَإِلَى مَا أَعْدَدْتُ لِأَهْلِهَا فِيهَا. فَنَظَرَ إِلَيْهَا، فَإِذَا هِيَ قَدْ حُفَّتْ بِالْمَكَارِهِ، فَقَالَ: وَعِزَّتِكَ لَقَدْ خَشِيتُ أَنْ لَا يَدْخُلَهَا أَحَدٌ. قَالَ: اذْهَبْ فَانْظُرْ إِلَى النَّارِ وَإِلَى مَا أَعْدَدْتُ لِأَهْلِهَا فِيهَا. فَنَظَرَ إِلَيْهَا فَإِذَا هِيَ يَرْكَبُ بَعْضُهَا بَعْضًا، فَرَجَعَ فَقَالَ: وَعِزَّتِكَ لَا يَدْخُلُهَا أَحَدٌ. فَأَمَرَ بِهَا فَحُفَّتْ بِالشَّهَوَاتِ، فَقَالَ: ارْجِعْ فَانْظُرْ إِلَيْهَا. فَنَظَرَ إِلَيْهَا فَإِذَا هِيَ قَدْ حُفَّتْ بِالشَّهَوَاتِ، فَرَجَعَ وَقَالَ: وَعِزَّتِكَ لَقَدْ خَشِيتُ أَنْ لَا يَنْجُوَ مِنْهَا أَحَدٌ إِلَّا دَخَلَهَا». [حسن] - [رواه أبو داود والترمذي والنسائي]

(69) - ከአቡ ሁረይራ -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው የአላህ መልክተኛ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ ብለዋል፦ "አላህ ጀነትና እሳትን እንደፈጠረ ጂብሪልን ዐለይሂ ሰላም እንዲህ በማለት ወደ ጀነት ላከው። "ወደ ርሷና በውስጧ ለባለቤቶቿ ያዘጋጀሁትን ተመልከት!" ወደ እርሷ ተመልክቶ በመመለስ እንዲህ አለ፦ "በልቅናህ ይሁንብኝ ስለርሷ ማንኛውም ሰው ቢሰማ ከመግባት ወደኋላ የሚል የለም" አላህም በሷ ጉዳይ ትእዛዙን አስተላልፎ (ለነፍስ) በሚከብዱ ነገሮች ተከበበች። በድጋሚ ጂብሪልን "ወደርሷ ሂድና ወደርሷና በውስጧ ለባለቤቶቿ ያዘጋጀሁትን ተመልከት!" አለው። ወደርሷ ተመለከተ፥ ድንገት (ለነፍስ) በሚከብዱ ነገሮች ተከባ ተመለከታት። "በልቅናህ እምላለሁ! በርግጥም ማንም አይገባትም ብዬ ፈራሁ።" ብሎ ለአላህ መለሰ። አላህም፦ " ወደ እሳትና ለባለቤቶቿ በውስጧ ያዘጋጀሁትን ሂድና ተመልከት" በማለት አዘዘው። ጂብሪልም ወደርሷ ሲመለከት ያንጊዜ እሷ ከፊሏ ከፊሉን ሲበላ ተመለከተ። በመመለስም እንዲህ አለ "በልቅናህ እምላለሁ ማንም አይገባትም" አላህም በሷ ጉዳይ ለስሜት በሚያስደስቱ ነገሮች እንድትከበብ አዘዘ። ቀጥሎም ደግመህ ወደርሷ ሂድና ተመልከት አለው ድንገት ለስሜት በሚያስደስቱ ነገሮች ተከባ ወደርሷ ተመለከተ። "በልቅናህ እምላለሁ! ወደርሷ አንድም ከሷ

አይድንም ይገባታል ብዬ ፈራሁ።" [ሐሰን ነው።] - [አቡዳውድ፣ ቲርሚዚና ነሳኢ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን አላህ ጀነትና እሳትን እነደፈጠራቸው ለጂብሪል ዐለይሂ ሰላም እንዲህ እንዳለ ተናገሩ። "ወደጀነት ሂድና ወደርሷ ተመልከት!" ጂብሪልም ሄዶ ወደርሷ ተመልክቶ ተመለሰ። ጂብሪልም እንዲህ አለ:- "ጌታዬ ሆይ በልቅናህ እምላለሁ! በውስጧ ስለሚገኘው ፀጋ፣ መከበሪያና መልካም ነገሮች ማንም ቢሰማ ወደርሷ መግባት የሚወድና ስለርሷም ከመስራት አይታቀብም።" በማለት መለሰ። ከዚያም አላህ ጀነትን ለነፍስ የሚከብዱና አስቸጋሪ በሆኑ ትእዛዛቶችን መፈፀምና ክልከላዎችን መራቅ ከበባት። ይህም ወደ ጀነት መግባት የፈለገ ይህን አስቸጋሪ መንገድ ማለፍ እንዲጠበቅበት ነው። ከዚያም የተከበረውና የላቀው አላህ ለነፍስ በሚከብዱ ነገሮች ከከበባት በኋላ እንዲህ አለ:- " ጂብሪል ሆይ! ወደ ጀነት ሂድና ተመልከታት!" ሄዶ ወደርሷ ተመልክቶ በመምጣት እንዲህ አለ:- " ጌታዬ ሆይ በልቅናህ እምላለሁ! ወደርሷ በሚያደርገው ጉዞ በሚያጋጥሙት ችግሮችና መከራዎች ምክንያት ማንም አይገባትም ብዬ እፈራለሁ።" አላህ እሳትን የፈጠረ ጊዜ:- "ጂብሪል ሆይ! ሂድና ወደርሷ ተመልከት" አለው። ወደርሷ ሂዶም ተመለከተ። ከዚያም በመምጣት እንዲህ አለ:- "ጌታዬ ሆይ በልቅናህ እምላለሁ! ውስጧ ስላለው ቅጣትና ጭንቀቶች አንድም አይሰማም ውስጧ መግባትን በመጥላት ወደርሷ ከሚያስገቡ ምክንያቶችም የራቀ ቢሆን እንጂ። " ከዚያም የተከበረውና የላቀው አላህ እሳትን ከበባት፤ ወደርሷ መድረሻ መንገድንም ለነፍስ የሚያስደስትና የሚያረካትን ነገሮች አደረገ። ከዚያም "ጂብሪል ሆይ! ሂድና ወደርሷ ተመልከት " አለው። ጂብሪልም ወደርሷ ሂዶ ተመልክቶ በመምጣት እንዲህ አለ:- " ጌታዬ ሆይ በልቅናህ እምላለሁ! በዙሪያዋ ባሉት ለነፍስ አርኪና አስደሳች ነገሮች ምክንያት በርግጥም ከሷ አንድም አይድንም ብዬ ሰጋሁ፤ ፈራሁ።"

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ጀነትና እሳት አሁን ላይ ያሉ መሆናቸውን ማመን እንደሚገባ፤
2. በሩቅ ምስጢር ነገሮች እና ከአላህና መልክተኛው የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን በመጡ ነገሮች ሁሉ ማመን ግዴታ መሆኑን፤
3. ወደጀነት የምታደርስ መንገድ ስለሆነች በአስቸጋሪ ነገሮች ላይ መታገስ አንገብጋቢ ጉዳይ መሆኑን፤
4. ወደ እሳት የሚያደርስ መንገድ ስለሆነ ክልክል ነገሮችን መራቅ አንገብጋቢ ጉዳይ መሆኑን፤
5. ጀነት በአስቸጋሪ ነገሮች እሳት ደግሞ ለስሜት በሚያስደስቱ ነገሮች የተከበቡ መደረጋቸው በዱንያ ህይወት ውስጥ ፈተናዎችና ሙከራዎች እንዳሉ የሚያሲዝ ነው።
6. የጀነት መንገድ አስቸጋሪና ከባድ ስለሆነ ትእግስትና ከኢማን ጋር ትኩረት ይፈልጋል። የእሳት መንገድ በዱንያ ውስጥ ለነፍስ በሚያስደስትና በሚያረካ ነገሮች የተሞላ መሆኑን እንረዳለን።

(65034)

(٧٠) - عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ رَضِيَ اللهُ عَنْهُ أَنَّ رَسُولَ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ قَالَ: «نَارُكُمْ جُزْءٌ مِنْ سَبْعِينَ جُزْءًا مِنْ نَارِ جَهَنَّمَ»، قِيلَ: يَا رَسُولَ اللهِ إِنْ كَانَتْ لَكَافِيَةً. قَالَ: «فُضِّلَتْ عَلَيْهِنَّ بِتِسْعَةٍ وَسِتِّينَ جُزْءًا كُلُّهُنَّ مِثْلُ حَرِّهَا». [صحيح] - [متفق عليه]

(70) - ከአቡ ሁረይራ -አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው የአላህ መልክተኛ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ ብለዋል፦ "የምድራችሁ እሳት ከጀሀነም እሳት ሰባ ክፍል አንዷ ክፍል ናት።" "የአላህ መልክተኛ ሆይ! (የምድር እሳት ለቅጣት) በቂ ነበረች'እኮ" ተባሉ። እሳቸውም፦ "የጀሀነም እሳት ከምድር እሳት በስልሳ ዘጠኝ ክፍል እንድትበልጥ ተደርጋለች። ሁሉም ክፍል የምድር እሳት አምሳያ ሀሩርነት (አቃጣይነት) ነው ያላቸው።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን የዱንያ እሳት ከሰባ የጀሀነም እሳት ክፍል አንዷ ክፍል መሆኗን ተናገሩ። የአኺራ እሳት ከዱንያ እሳት በስልሳ ዘጠኝ እጥፍ የማቃጠል ደረጃዋ ይበልጣል። እያንዳንዱ የጀሀነም ክፍል ከዱንያ እሳት አቃጣይነት ጋር እኩል ነው። "የአላህ መልክተኛ ሆይ! ጀሀነም ውስጥ የሚገቡን ለመቅጣት የዱንያ እሳት'እኮ በቂ ነበረች።" ተባሉ። እርሳቸውም "የጀሀነም እሳት ከዱንያ እሳት በስልሳ ዘጠኝ ክፍል እንድትበልጥ ተደርጓል። የእያንዳንዱ ክፍል ሀሩርነት (የማቃጠል) ኃይልም እንደ ዱንያ እሳት አምሳያ ነው።" አሉ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ሰዎች ወደ እሳት ከሚያደርሱ ሥራዎች እንዲርቁ ከእሳት ማስጠንቀቅ፤
2. የጀሀነም እሳት ትልቅነቷ፣ ቅጣቷና የሀሩርነቷን ኃይለኝነት ተረድተናል።

(65036)

(٧١) - عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ رضي الله عنه قَالَ: سَمِعْتُ رَسُولَ اللَّهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ يَقُولُ: «يَقْبِضُ اللَّهُ الأَرْضَ، وَيَطْوِي السَّمَوَاتِ بِيَمِينِهِ، ثُمَّ يَقُولُ: أَنَا المَلِكُ، أَيْنَ مُلُوكُ الأَرْضِ».

[صحيح] - [متفق عليه]

(71) - ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: እንዲህ አሉ: "የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ሲሉ ሰምቻለሁ፡- 'አላህ ምድርን በጭብጡ ያደርጋል፤ ሰማያትንም በቀኝ እጁ ይጠቀልልና ከዚያም ‹እኔ ነኝ ንጉሱ! የምድር ነገስታት የት አሉ?!› ይላል።'" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) የትንሳኤ ቀን አላህ ምድርን እንደሚጨብጥና እንደሚሰበስባት፤ ሰማይንም ከፊሉን ከከፊሉ በላይ አድርጎ በቀኝ እጁ እንደሚጠቀልልና ገፍፎ እንደሚያጠፋቸው ከዚያም "እኔ ነኝ ንጉስ! የምድር ነገስታት የት አሉ?!" እንደሚል ተናገሩ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. የአላህ ንግስና ዘውታሪ፤ የሌላው ንግስና ግን ጠፊ መሆኑን ማስታወስ እንደሚገባ እንረዳለን።
2. የአላህን ግርማዊነት፣ የችሎታውና ስልጣኑ ልቅና እንዲሁም የንግስናውን ምሉዕነት እንረዳለን።

(65028)

(٧٢) - عَنْ عَائِشَةَ أُمِّ المُؤمنينَ رضي الله عنها قَالَتْ: دَخَلَ عَلَيَّ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ، وَقَدْ سَتَرْتُ سَهْوَةً لِي بِقِرَامٍ فِيهِ تَمَاثِيلُ، فَلَمَّا رَآهُ هَتَكَهُ وَتَلَوَّنَ وَجْهُهُ وَقَالَ: «يَا عَائِشَةُ، أَشَدُّ النَّاسِ عَذَابًا عِنْدَ اللهِ يَوْمَ الْقِيَامَةِ الَّذِينَ يُضَاهُونَ بِخَلْقِ اللهِ» قَالَتْ عَائِشَةُ: «فَقَطَعْنَاهُ فَجَعَلْنَا مِنْهُ وِسَادَةً أَوْ وِسَادَتَيْنِ». [صحيح] - [متفق عليه]

(72) - ከአማኞች እናት ዓኢሻ (ረዲየሏሁ ዐንሃ) - አላህ መልካም ሥራዋን ይውደድላትና - እንደተላለፈው እንዲህ አለች: "እቃ ክፍሌን (የተንቀሳቃሽ እንስሳ) ምስል ባለበት መጋረጃ ሸፍኜው ሳለ የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እኔ ዘንድ መጡ። የተመለከቱት ጊዜም ፊታቸው ተለዋውጦ ቀደዱትና እንዲህም አሉ 'ዓኢሻ ሆይ! የትንሳኤ ቀን አላህ ዘንድ ከሰዎች ሁሉ እጅግ ብርቱ ቅጣት የሚቀጡት እነዚያ በአላህ ፍጥረት የሚፎካከሩት ናቸው።'" ዓኢሻም እንዲህ አለች "ቆርጠነው በርሱ አንድ ትራስ ወይም ሁለት ትራስ አደረግንበት።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ቤታቸው ዓኢሻ (ረዲየሏሁ ዐንሃ) - አላህ መልካም ሥራዋን ይውደድላትና - ዘንድ ሲገቡ እቃ የምታስቀምጥበትን ትንሽዬ ክፍል ነፍስ ያላቸው ምስሎች ባለበት መጋረጃ ሸፍናው አገኟት። የፊታቸው ቀለምም ለአላህ ብለው በመቆጣታቸው ምክንያት ተለዋውጦ መጋረጃውን አወለቁት። እንዲህም አሉ: የትንሳኤ ቀን ከሰዎች ሁሉ እጅግ ብርቱ ቅጣት የሚቀጡት የአላህን ፍጥረት አስመስለው ምስል የሚያደርጉት ናቸው። ዓኢሻም እንዲህ አለች: እርሱን አንድ ትራስ ወይም ሁለት ትራስ አደረግነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. መጥፎን ነገር በማውገዛችን ሳቢያ የሚከሰት ትልቅ ብልሽት እስከሌለ ድረስ በተመለከትነው ቅፅበት ማውገዝ እንደሚገባና ማቆየትም እንደሌለብን እንረዳለን።
2. የትንሳኤ ቀን ቅጣት እንደ ወንጀሉ ትልቀት ይበላለጣል።
3. ነፍስ ያላቸው ነገሮችን ምስል ማድረግ ከትላልቅ ወንጀሎች መካከል አንዱ ነው።
4. ምስል ማድረግ ከተከለከለባቸው ጥበቦች አንዱ ከአላህ አፈጣጠር ጋር መፎካከር ስለሆነ ነው። ይህም ምስል አድራጊው መፎካከር አሰበም አላሰበም እኩል ነው።
5. ከጉዳዩ የተከለከለበትን ጎን ካራቅን በኋላም በርሱ መጠቀማችን ሸሪዓ ገንዘቦችን በመጠበቅ ላይ ያለውን ጉጉት ያስረዳናል።
6. ነፍስ ያላቸውን ምስሎች በማንኛውም ቅርፅ ቢሆኑ እንኳ፣ ፕሮፌሽናል የሆነ ምስል ቢሆን እንኳ መፈብረክ ክልክል መሆኑን እንረዳለን።

(5931)

(٧٣) - عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ رَضِيَ اللهُ عَنْهُ قَالَ: قَالَ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ: «وَالَّذِي نَفْسِي بِيَدِهِ، لَيُوشِكَنَّ أَنْ يَنْزِلَ فِيكُمْ ابْنُ مَرْيَمَ حَكَمًا مُقْسِطًا، فَيَكْسِرَ الصَّلِيبَ، وَيَقْتُلَ الخِنْزِيرَ، وَيَضَعَ الجِزْيَةَ، وَيَفِيضَ المَالُ حَتَّى لاَ يَقْبَلَهُ أَحَدٌ». [صحيح] - [متفق عليه]

(73) - ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: "የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል: "ነፍሴ በእጁ በሆነው ጌታ እምላለሁ። በናንተ ውስጥ የመርየም ልጅ ፍትሃዊ ዳኛ በቅርቡ ሆኖ ይወርዳል። መስቀልን ይሰባብራል፣ አሳማን ይገድላል፣ ግብርን ያነሳል፣ አንድም ሰው እስከማይቀበለው ድረስም ገንዘብ (ሀብት) ይበዛ።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) የመርየም ልጅ ዒሳ የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና በሰዎች መካከል በነቢያችን ድንጋጌ በፍትህ ሊፈርዱ መውረጃ ጊዜያቸው ቅርብ እንደሆነ ምለው ተናገሩ። በሚመጡ ወቅትም ክርስቲያኖች የሚያልቁትን መስቀል ይሰባብራሉ፤ ዒሳ የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና አሳማዎችንም ይገድላሉ፤ ዒሳ የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ግብርንም ያስቀራሉ፤ ሰዎች ባጠቃላይ ወደ ኢስላም እንዲገቡም ይታገላሉ፤ ገንዘብ (ሀብት) ይትረፈረፋል አንዱ ከሌላው አይቀበለውም። ይህም ገንዘብ ከመብዛቱ፣ ሁሉም እያንዳንዱ እርሱ ዘንድ ባለው ገንዘብ የተብቃቃ ከመሆኑ፣ በረካ ሰፍኖ መልካምነትም ከመከታተሉ አኳያ ነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ዒሳ የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና በመጨረሻ ዘመን እንደሚወርዱ መረጋገጡንና የርሳቸው መምጣት የትንሳኤ ቀን ምልክት መሆኑን እንረዳለን።

2. የነቢዩን (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ድንጋጌ የሚሽር ሌላ ድንጋጌ እንደሌለ እንረዳለን።
3. በመጨረሻ ዘመን ሰዎች ከገንዘብ ቸልተኛ ከመሆናቸውም ጋር የገንዘብ በረከት ግን እንደሚሰፍን እንረዳለን።
4. በመጨረሻ ዘመን ዒሳ የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና በኢስላም ሃይማኖት ስለሚፈርዱ ኢስላም ዘውታሪ ሃይማኖት መሆኑ መበሰሩን እንረዳለን።

(65025)

(٧٤) - عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ رضي الله عنه قَالَ: قَالَ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ لِعَمِّهِ: «قُلْ: لَا إِلَهَ إِلَّا اللهُ، أَشْهَدُ لَكَ بِهَا يَوْمَ الْقِيَامَةِ»، قَالَ: لَوْلَا أَنْ تُعَيِّرَنِي قُرَيْشٌ، يَقُولُونَ: إِنَّمَا حَمَلَهُ عَلَى ذَلِكَ الْجَزَعُ لَأَقْرَرْتُ بِهَا عَيْنَكَ. فَأَنْزَلَ اللهُ: {إِنَّكَ لا تَهْدِي مَنْ أَحْبَبْتَ وَلَكِنَّ اللهَ يَهْدِي مَنْ يَشَاءُ} [القصص: 56]. [صحيح] - [رواه مسلم]

(74) - አቡ ሁረይራ -አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና- እንዲህ ብለዋል፦ የአላህ መልክተኛ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ለአጎታቸው እንዲህ አሏቸው፦ " ላ ኢላሀ ኢለላህ በል የትንሳኤ ቀን ላንተ በርሱ እመሰክርልሀለሁ" አቡ ጣሊብም "የቁረይሾች ማነወር ባልነበር "ለመስለም ያነሳሳው የሞት ፍራቻ ነው" ይላሉ ብዬ ባልሰጋ (እሰልም ነበር)" (ይህ ስጋት ባልነበር) ላ ኢላሀ ኢለላህ በማለት ደስታን አሰርፅልህ ነበር።" አላቸው። አላህም ይህን አንቀፅ አወረደ {አንተ የወደድከውን ሰው ፈፅሞ አታቀናም። ግን አላህ የሚሻውን ሰው ያቀናል እርሱም ቅኖቹን አዋቂ ነው።} [አልቀሶስ: 56] [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን አጎታቸው አቡ ጣሊብ ጣእረ ሞት ላይ ሳሉ ላኢላሀ ኢለላህን እንዲናገር ፈለጉ። ይህም የትንሳኤ ቀን በሷ ምክንያት ሊያማልዱትና በእስልምናው ሊመሰክሩለት ብለው ነው።

እርሳቸው ግን ቁረይሾች እንዳይሰድቧቸው ፈርተውና "እርሱ የሰለመው ሞትና ደካማነትን በመፍራቱ ምክንያት ነው!" እንዳይባሉ በመስጋት የምስክርነት ቃሏን መናገር እምቢ አሉ። ለነቢዩም የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን "ይህ ስጋቴ ባልነበር የምስክር ቃሏን በመናገር በልብዎ ውስጥ ደስታን አስገባም ነበር እስኪደሰቱ ድረስም ምኞቶን አሳካ ነበር" አሏቸው። አላህም የፈለገውን ሰው እርሱ ብቻ እንጂ ነቢዩም የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ኢስላምን በሰው ቀልብ ውስጥ በማስረፅ መምራት እንደማይችሉ የሚጠቁም አንቀፅ አወረደ። ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ፍጡራንን ወደ ቀጥተኛው መንገድ በመጠቆም ፣ በማብራራት፣ በማቅናትና በመጣራት ነው የሚመሩት።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. የሰዎችን ወሬ በመፍራት ሐቅ እንደማትተው!
2. ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን የመጠቆምና የማቅናት መምራት እንጂ የሚችሉት ልብ ውስጥ የማስረፅ መምራት እንደማይችሉ፤
3. ወደ ኢስላም ለመጥራት ብሎ የታመመን ከሀዲ መዘየር በኢስላም የተደነገገ መሆኑን፤
4. ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን በማንኛውም ሁኔታዎች ወደ አላህ በመጥራት ላይ የነበራቸውን ጉጉት ተረድተናል።

(65069)

(٧٥) - عَنْ عَبْدِ اللهِ بْنِ عَمْرٍو رضي الله عنهما قَالَ: قالَ النَّبِيُّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ: «حَوْضِي مَسِيرَةُ شَهْرٍ، مَاؤُهُ أَبْيَضُ مِنَ اللَّبَنِ، وَرِيحُهُ أَطْيَبُ مِنَ المِسْكِ، وَكِيزَانُهُ كَنُجُومِ السَّمَاءِ، مَنْ شَرِبَ مِنْهَا فَلاَ يَظْمَأُ أَبَدًا». [صحيح] - [متفق عليه]

(75) - ዐብደላህ ቢን ዐምር -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንዲህ አሉ፦ ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ ብለዋል፦ "የሐውዴ ( ኩሬ ስፋቱ) አንድ ወር ያስኬዳል ፤ ውኃው ከወተት የነጣ፣ ሽታው ከሚስክ እጅግ የሚያውድ፣ የብርጭቆዎቹ ብዛት የሰማያት ኮከቦች ያህል ናቸው። ከሷ አንዴ የጠጣ ከቶም መቼም አይጠማም።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን የውመል ቂያማ የሚሰጣቸው ኩሬ እንዳለ እንዲሁም እርዝማኔውና ጎኑ አንድ ወር እንደሚያስኬድ ተናገሩ። ውኃው ከወተት እጅግ የበለጠ ንጣት እንዳለው፤ ሽታው ከሚስክ መአዛ የበለጠ ምርጥና ማራኪ መአዛ እንዳለው፤ የብርጭቆዎቹ ብዛት አምሳያ የሰማይ ኮከቦች ያህል እንደሆነ፤ በዚህ ብርጭቆ ከኩሬው የጠጣ ሰው መቼም እንደማይጠማ ተናገሩ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. የነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ኩሬ የውመል ቂያማ ከሳቸው ኡመት የሆኑ አማኞች ለመጠጣት የሚወርዱበት የግዙፍ ውኃ ጥርቅም ነው።
2. ከኩሬው የሚጠጣ ሰው መቼም ያለመጠማት ፀጋን እንደሚያገኝ።

(65030)

(٧٦) - عَنْ أَبِي سَعِيدٍ الخُدْرِيِّ رَضِيَ اللهُ عَنْهُ قَالَ: قَالَ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ: «يُؤْتَى بِالْمَوْتِ كَهَيْئَةِ كَبْشٍ أَمْلَحَ، فَيُنَادِي مُنَادٍ: يَا أَهْلَ الجَنَّةِ، فَيَشْرَئِبُّونَ وَيَنْظُرُونَ، فَيَقُولُ: هَلْ تَعْرِفُونَ هَذَا؟ فَيَقُولُونَ: نَعَمْ، هَذَا المَوْتُ، وَكُلُّهُمْ قَدْ رَآهُ، ثُمَّ يُنَادِي: يَا أَهْلَ النَّارِ، فَيَشْرَئِبُّونَ وَيَنْظُرُونَ، فَيَقُولُ: وهَلْ تَعْرِفُونَ هَذَا؟ فَيَقُولُونَ: نَعَمْ، هَذَا المَوْتُ، وَكُلُّهُمْ قَدْ رَآهُ، فَيُذْبَحُ ثُمَّ يَقُولُ: يَا أَهْلَ الجَنَّةِ خُلُودٌ فَلاَ مَوْتَ، وَيَا أَهْلَ النَّارِ خُلُودٌ فَلاَ مَوْتَ، ثُمَّ قَرَأَ: {وَأَنْذِرْهُمْ يَوْمَ الحَسْرَةِ إِذْ قُضِيَ الأَمْرُ وَهُمْ فِي غَفْلَةٍ} [مريم: 39]، وَهَؤُلاَءِ فِي غَفْلَةٍ أَهْلُ الدُّنْيَا {وَهُمْ لاَ يُؤْمِنُونَ} [مريم: 39]».

[صحيح] - [متفق عليه]

(76) - አቡ ሰዒድ አልኹድሪይ -አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንዲህ አሉ፡- የአላህ መልክተኛ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ ብለዋል፡- "ሞት በቡራቡሬ ሙክት ተመስሎ ተይዞ ይመጣል። ተጣሪም እንዲህ በማለት ይጣራል: "የጀነት ባለቤቶች ሆይ!" ተንጠራርተው ይመለከታሉ። "ይህንን ታውቁታላችሁን?" ይላቸዋል። "አዎን ይህ ሞት ነው ሁሉም ተመልክቶታል።" ይላሉ። ቀጥሎ ተጣሪው እንዲህ በማለት ይጣራል "የእሳት ባለቤቶች ሆይ!" ተንጠራርተው ይመለከታሉ። "ይህንን ታውቁታላችሁን?" ይላቸዋል። "አዎን ይህ ሞት ነው ሁሉም ተመልክቶታል።" ይላሉ። ይታረዳል ቀጥሎ እንዲህ ይላቸዋል "የጀነት ባለቤቶች ሆይ! (ከዚህ በኋላ) ዘላለማዊ ሕይወት እንጂ ሞት የለባችሁም። የእሳት ባለቤቶች ሆይ! (ከዚህ በኋላ) ዘላለማዊ ሕይወት እንጂ ሞት የለባችሁም።" ከዚያም ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን፡- {እነሱም (አሁን) በዝንጋቴ ላይ ሆነው ሳሉ ነገሩ በሚፈረድበት ጊዜ የቁጭቱን ቀን አስፈራራቸው።} [መርየም: 39] የሚለውን አንቀፅ አነበቡ። "እነዚህ በዱንያ ዝንጋቴ ውስጥ ናቸው።" {እነሱም የማያምኑ ናቸው።} [መርየም: 39]" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## **ትንታኔ:**

ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን የትንሳኤ ቀን ሞት ጥቁርና ነጭ በሆነ ወንድ በግ ተመስሎ ተይዞ እንደሚመጣ አብራሩ። "የጀነት ባለቤቶች ሆይ!" ተብሎ ይጠራል። አንገቶቻቸውንና ትከሻዎቻቸውን በመለጠጥ ጭንቅላታቸውንም በማንጠራራት ይመለከታሉ። ለነሱም "ይህንን ታውቁታላችሁን?" ይላቸዋል። እነሱም "አዎን ይህ ሞት ነው። ሁሉም አይቶታል ያውቀዋል።" ይላሉ። ከዚያም ተጣሪው "የእሳት ባለቤቶች ሆይ!" በማለት ይለፍፋል። አንገቶቻቸውንና ትከሻዎቻቸውን በመለጠጥ ጭንቅላታቸውንም በማንጠራራት ይመለከታሉ። ለነሱም "ይህንን ታውቁታላችሁን?" ይላቸዋል። እነሱም "አዎን ይህ ሞት ነው። ሁሉም አይቶታል።" ይላሉ። ሙክቱ ይታረዳል ከዚያም ተጣሪው፡- "የጀነት ባለቤቶች ሆይ! እጣፈንታችሁ ያለሞት ዘውትርና ዘላለም መኖር ነው። የእሳት ባለቤቶች ሆይ! እጣፈንታችሁ ያለሞት ዘውትርና ዘላለም መኖር ነው።" ይላቸዋል። ይህም ለአማኞች ተጨማሪ ፀጋ ለከሀዲያን የቅጣት አለንጋ እንዲሆን ነው። ከዚያም ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ይህን አንቀፅ አነበቡ። {እነሱም (አሁን) በዝንጋቴ ላይ ሆነው ሳሉ እነሱም የማያምኑ ሲኾኑ ነገሩ በሚፈረድበት ጊዜ የቁጭቱን ቀን አስፈራራቸው።} [መርየም: 39] የትንሳኤ ቀን በጀነትና እሳት ባለቤቶች መሀል ይፈረዳል። ሁሉም ወደሚዘወትርባት ይገባል። ወንጀለኛ በጎ ባለመሥራቱ ይፀፀታልም ይቆጫልም። መልካም ከመስራት ያጓደለም ባለመጨመሩ ይቆጫል።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. የሰው ልጅ በመጪው ዓለም መመለሻው ጀነት ውስጥ ወይም እሳት ውስጥ መዘውተር ነው።
2. ስለ ትንሳኤ ቀን መከራ ከባድ ማስፈራሪያ መምጣቱ። እሱ የቁጭትና ፀፀት ቀን ነው።
3. የጀነት ባለቤቶች ደስታ እንደሚዘወትር፤ የእሳት ባለቤቶች ሀዘንም እንደሚዘወትር መገለፁ።

(65035)

(٧٧) - عن عمر بن الخطاب رضي الله عنه قال: إنه سمع نبي الله صلى الله عليه وسلم يقول: «لَو أَنَّكُمْ تَتَوَكَّلُونَ عَلَى اللهِ حَقَّ تَوَكُّلِهِ، لَرَزَقَكُمْ كَمَا يَرْزُقُ الطَّيْرَ، تَغْدُو خِمَاصًا وَتَرُوحُ بِطَانًا».
[صحيح] - [رواه الترمذي وابن ماجه وأحمد]

(77) - ከዑመር ቢን አልኸጧብ -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: የአላህን ነቢይ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንዲህ ሲሉ ሰማ: "በአላህ ላይ ትክክለኛውን መመካት ብትመኩ ኖሮ ወፍን እንደሚለግሰው ለናንተም ሲሳይን ይለግሳቹህ ነበር። (ወፍ) ተርባ ማልዳ ትወጣለች። ሆዷ (በጥጋብ) ሞልቶ ትመለሳለች።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቲርሚዚ፣ ኢብኑ ማጀህና አሕመድ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም በዱንያዊም በዲናዊም ጉዳይ ጥቅምን በማምጣትና ጉዳትን በመከላከል ረገድ በአላህ ላይ እንድንደገፍ እያነሳሱን ነው። ምክንያቱም ከአላህ በስተቀር የሚሰጥም፣ የሚከለክልም ፣ የሚጎዳም፣ የሚጠቅምም የለምና ነው። ጥቅሞችን የሚያመጡና ጉዳቶችን የሚከላከሉ ሰበቦችን በአላህ ላይ ከእውነተኛ መመካት ጋር እንድንፈፅምም አነሳሱ። ይህንን በማንኛውም ወቅት ከፈፀምን አላህ ወፍን በንጋት የተራበች ሆና ወጥታ ከዚያም በምሽት ሆዷ ሞልቶ በመመለስ እንደሚቀልባት እኛንም ይቀልበን ነበር። ይህ የወፏ ድርጊት ያለመሳነፍና መዳከም ሲሳይን ለመፈለግ የሰራችው የሰበብ አይነት ነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. የመመካት ትሩፋትን ፤ መመካት ሲሳይን ከሚያመጡ መንስኤዎች መካከል ትልቁ ነው ።

2. መመካት ሰበቦችን ከመፈፀም ጋር አይጋጭም። ምክንያቱም እሳቸው ሲሳይ ለመፈለግ ማልዶ መውጣትና አምሽቶ መመለስ ትክክለኛውን መመካት እንደማይጣረሰው ተናግረዋልና።
3. ሸሪዐ ለቀልብ ተግባራት ትኩረት መስጠቱን፤ መመካት የቀልብ ተግባር ነውና።
4. በሰበብ ላይ ብቻ መንጠልጠል የዲን ጉድለት ሲሆን ሰበቦችን መተው ደግሞ የአይምሮ ጉድለት ነው።

(4721)

(٧٨) - عَن أَبِي هُرَيْرَةَ رضي الله عنه قَالَ: قَالَ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ: «يُسَلِّمُ الرَّاكِبُ عَلَى المَاشِي، وَالمَاشِي عَلَى القَاعِدِ، وَالقَلِيلُ عَلَى الكَثِيرِ». [صحيح] - [متفق عليه]

(78) - ከአቡ ሁረይራ (ረዲየላሁ ዐንሁ) -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ ብለዋል፡- "የአላህ መልዕክተኛ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንዲህ ብለዋል፡- "የሚጋልብ ሰው በእግረኛ ላይ ሰላምታን ያቅርብ፤ እግረኛ በተቀማጬ ላይ ሰላምታን ያቅርብ፤ ጥቂት ሰዎች በብዙ ሰዎች ላይ ሰላምታን ያቅርቡ።"" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል። ]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) በሰዎች መካከል "አስሰላሙ ዐለይኩም ወረሕመቱሏሂ ወበረካቱሁ" የሚለውን ሰላምታን የማቅረብ ስነ-ስርዓትን ጠቆሙ። ህፃን በትልቅ ላይ፣ ጋላቢ በእግረኛ ላይ፣ እግረኛ በተቀማጬ ላይ፣ ጥቂት ቁጥር ያላቸው በብዙዎቹ ላይ ሰላምታን ያቅርቡ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ሐዲሥ ላይ በመጣው መልኩ ሰላምታን ማቅረብ እንደሚወደድ እንረዳለን። ነገር ግን እግረኛ በጋላቢ ላይ ወይም ከዚህም ውጪ ሐዲሡ ላይ

ከተጠቀሰው በተቃራኒው ሰላምታ ቢያቀርብ ከበላጩና ከተሻለው ተቃራኒ ቢሆንም ይፈቀዳል።

2. በሐዲሡ ላይ በተጠቀሰው አፈፃፀም መልኩ ሰላምታን ማስፋፋት ውዴታንና ትስስርን ከሚያመጡ ነገሮች መካከል አንዱ ነው።
3. በሐዲሡ ላይ ከተጠቀሱት ተመሳሳይና ተመጣጣኝ ከሆኑ የተሻለው ሰላምታውን የሚጀምረው ነው።
4. የሰው ልጅ የሚያስፈልገውን ሁሉ በማብራራት ረገድ የሸሪዓን ምሉዕነት እንረዳለን።
5. የሰላምታን ስነ-ስርዓት ማስተማርና ለሁሉም የሚገባውን ሐቅ (መብት) መስጠት እንደሚገባ እንረዳለን።

(4243)

(٧٩) - عن أبي ذر رضي الله عنه: عَنِ النَّبِيِّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ فِيمَا رَوَى عَنِ اللهِ تَبَارَكَ وَتَعَالَى أَنَّهُ قَالَ: «يَا عِبَادِي إِنِّي حَرَّمْتُ الظُّلْمَ عَلَى نَفْسِي، وَجَعَلْتُهُ بَيْنَكُمْ مُحَرَّمًا، فَلَا تَظَالَمُوا، يَا عِبَادِي كُلُّكُمْ ضَالٌّ إِلَّا مَنْ هَدَيْتُهُ، فَاسْتَهْدُونِي أَهْدِكُمْ، يَا عِبَادِي كُلُّكُمْ جَائِعٌ إِلَّا مَنْ أَطْعَمْتُهُ، فَاسْتَطْعِمُونِي أُطْعِمْكُمْ، يَا عِبَادِي كُلُّكُمْ عَارٍ إِلَّا مَنْ كَسَوْتُهُ، فَاسْتَكْسُونِي أَكْسُكُمْ، يَا عِبَادِي إِنَّكُمْ تُخْطِئُونَ بِاللَّيْلِ وَالنَّهَارِ وَأَنَا أَغْفِرُ الذُّنُوبَ جَمِيعًا فَاسْتَغْفِرُونِي أَغْفِرْ لَكُمْ، يَا عِبَادِي إِنَّكُمْ لَنْ تَبْلُغُوا ضَرِّي فَتَضُرُّونِي، وَلَنْ تَبْلُغُوا نَفْعِي فَتَنْفَعُونِي، يَا عِبَادِي لَوْ أَنَّ أَوَّلَكُمْ وَآخِرَكُمْ وَإِنْسَكُمْ وَجِنَّكُمْ كَانُوا عَلَى أَتْقَى قَلْبِ رَجُلٍ وَاحِدٍ مِنْكُمْ مَا زَادَ ذَلِكَ فِي مُلْكِي شَيْئًا، يَا عِبَادِي لَوْ أَنَّ أَوَّلَكُمْ وَآخِرَكُمْ وَإِنْسَكُمْ وَجِنَّكُمْ كَانُوا عَلَى أَفْجَرِ قَلْبِ رَجُلٍ وَاحِدٍ مَا نَقَصَ ذَلِكَ مِنْ مُلْكِي شَيْئًا، يَا عِبَادِي لَوْ أَنَّ أَوَّلَكُمْ وَآخِرَكُمْ وَإِنْسَكُمْ وَجِنَّكُمْ قَامُوا فِي صَعِيدٍ وَاحِدٍ فَسَأَلُونِي فَأَعْطَيْتُ كُلَّ إِنْسَانٍ مَسْأَلَتَهُ مَا نَقَصَ ذَلِكَ مِمَّا عِنْدِي إِلَّا كَمَا يَنْقُصُ الْمِخْيَطُ إِذَا أُدْخِلَ الْبَحْرَ، يَا عِبَادِي إِنَّمَا هِيَ أَعْمَالُكُمْ أُحْصِيهَا لَكُمْ ثُمَّ أُوَفِّيكُمْ إِيَّاهَا، فَمَنْ وَجَدَ خَيْرًا فَلْيَحْمَدِ اللهَ، وَمَنْ وَجَدَ غَيْرَ ذَلِكَ فَلَا يَلُومَنَّ إِلَّا نَفْسَهُ». [صحيح] - [رواه مسلم]

(79) - ከአቢ ዘር -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ከፍ ካለውና ከጠራው አላህ ባወሩት (ሐዲሠል

ቁድሲይ) አላህ እንዲህ ብሏል: "ባሮቼ ሆይ! እኔ በደልን በነፍሴ ላይ እርም አድርጌያለሁ! በመካከላችሁም እርም አድርጌዋለሁ! ስለሆነም አትበዳደሉ! ባሮቼ ሆይ! ከመራሁት በስተቀር ሁላችሁም ጠማማ ናችሁና ምራቻን ከኔ ጠይቁ እመራችኋለሁ! ባሮቼ ሆይ! ካበላሁት በስተቀር ሁላችሁም ረሀብተኞች ናችሁና መብልን ከኔ ጠይቁ እመግባችኋለሁ! ባሮቼ ሆይ! እኔ ካለበስኩት በስተቀር ሁላችሁም የታረዛችሁ ናችሁና ልብስን ከኔ ጠይቁ አለብሳችኋለሁ! ባሮቼ ሆይ! እናንተ በሌሊትም ሆነ በቀን ትሳሳታላችሁ። እኔ ደግሞ ሁሉንም ወንጀሎችን እምራለሁ። ስለሆነም ምህረትን ከኔ ፈልጉ እምራችኋለሁ! ባሮቼ ሆይ! እናንተ እኔን ጉዳትን ልትጎዱኝ አትችሉም። ጥቅምን ልትጠቅሙኝ ዘንድም አትችሉም። ባሮቼ ሆይ! ከመጀመሪያዎቻችሁ እስከመጨረሻዎቻችሁ ሰዎችም ጂኖችም ሁሉም ከናንተ መካከል እንደሚገኝ አንድ እጅግ አላህን ፈሪ ቀልብ ያለው ሰውዬ ቢሆኑ ይህ ከንግስናዬ አንዳችም አይጨምርም። ባሮቼ ሆይ! ከመጀመሪያዎቻችሁ እስከመጨረሻዎቻችሁ ሰዎችም ጂኖችም ሁሉም እንደ አንድ እጅግ ጠማማ ቀልብ ያለው ሰው ቢሆኑ ይህ ከንግስናዬ አንዳችም አይቀንስም። ባሮቼ ሆይ! ከመጀመሪያዎቻችሁ እስከመጨረሻዎቻችሁ ሰዎችም ጂኖችም በአንድ ሰፊ ሜዳ ላይ ቢቆሙና ቢጠይቁኝ ለእያንዳንዱም የጠየቀኝን ብሰጠው መርፌ ባህር የገባች ጊዜ እንደምትቀንሰው ያህል ካልሆነ በቀር ይህ (መስጠቴ) እኔ ዘንድ ካለው (ሀብት) ምንም አይቀንስም። ባሮቼ ሆይ! ይህቺ ስራችሁ ናት ለናንተ አስቀምጥላችኋለሁ ከዚያም እራሷን እመነዳችኋለሁ። ምንዳውን መልካም ሆኖ ያገኘ አላህን ያመስግን ፤ ከዛ ውጪ ሆኖ ያገኘ ግን ከነፍሱ በስተቀር ማንንም እንዳይወቅስ።" [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ከፍ ያለውና ጥራት የተገባው አላህ በደልን በነፍሱ ላይ እርም እንዳደረገና አንዱ አንዱን እንዳይበድል በደልን በፍጡራኑ መካከልም እርም እንዳደረገው መናገሩን አብራሩ። ሁሉም ፍጡራን በአላህ መምራትና መግጠም ካልሆነ በቀር ከእውነተኛው መንገድ የጠመሙ ናቸው።

መመራትን ከአላህ የጠየቀ ሰው አላህም ይገጥመዋል ይመራዋልም። ፍጡራን በሁሉም ጉዳዮቻቸው ወደ አላህ ፈላጊዎች ናቸው። አላህን የጠየቀን ሰው አላህም ጉዳዩን ይፈፅምለታል ይበቃዋልም። ፍጡራን ሌት ተቀን ወንጀል ይፈፅማሉ። አላህ ደግሞ ባሪያው ምህረትን በሚጠይቀው ወቅት ይሸሽገዋልም ያልፈዋልም። ፍጡራን አላህን አንዳችም ሊጎዱም ወይም ሊጠቅሙ አይችሉም። ፍጡራን ሁሉ እንደ አንድ አላህን እጅግ የሚፈራ ቀልብ ያለው ግለሰብ ቢሆኑ ፍራቻቸው በአላህ ንግስና ላይ አትጨምርም። ሁሉም እንደ አንድ ጠማማ ቀልብ ያለው ሰውዬ ቢሆኑም ጥመታቸው በንግስናው ላይ አንዳችም አይቀንስም። ምክንያቱም ደካሞችና ወደ አላህ ፈላጊዎች ናቸውና። በሁሉም ሁኔታ፣ ዘመንና ስፍራ ወደርሱ ፈላጊዎች ናቸው። የተብቃቃም እሱ ብቻ ነው። ፍጡራን ሁሉ ሰዉም ጋኔኑም ከመጀመሪያቸው እስከመጨረሻቸው አላህን ለመጠየቅ በአንድ ስፍራ ላይ ቢቆሙና ከነርሱም ለእያንዳንዱ ሁሉ የጠየቀውን ቢሰጥ ይህ መስጠቱ አላህ ዘንድ ካለው አንዳችም አይቀንስም። ልክ እንደ መርፌ ባህር ውስጥ ገብታ ብትወጣ ባህሩ በዚህ አንዳችም እንደማይቀነሰው ማለት ነው። ይህም የሆነው ከተሟላው ሀብቱ አንፃር ነው። ጥራት ተገባው!

ጥራት የተገባው አላህ የባሮችን ስራዎች ይጠብቃልም ያስቀምጣልም። ከዚያም እሷኑ የትንሳኤ ቀን ይመነዳቸዋል። የስራውን ምንዳ መልካም ሆኖ ያገኘው ሰው አላህ ትእዛዙን ለመፈፀም ስለገጠመው አላህን ያመስግን። የስራውን ምንዳ ከዚህ ውጪ ሆኖ ያገኘ ሰውም ወደ ክስረት የመራቸውን በመጥፎ የምታዘው ነፍሱን እንጂ ሌላን እንዳይወቅስ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ይህ ሐዲሥ ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ከጌታቸው ከሚዘግቡት ሐዲሦች መካከል አንዱ ነው። ሐዲሠል ቁድስ ወይም ሓዲሠል ኢላሂይ በመባልም ይጠራል። ይህም ቃሉም ሆነ መልዕክቱ ከአላህ የሆነ ሲሆን ነገር ግን ቁርአን ከሌሎች የተለየበት የሆኑ የቁርአን መለዮች የሉትም። ለምሳሌ: - በማንበቡ (ሓሰና የሚያስገኝ) አምልኮን መፈፀም፣ ለሱ ጦሀራ ማድረግ ፣ የሱን

አምሳያ ከቻላቹ አምጡ የተባለለት ተዓምራዊነቱና ሌሎችም ቁርአን የተለየበት መለዮዎች ይጠቀሳሉ።

2. ባሮች የሚጎናፀፉት እውቀትና መመራት በአላህ መምራትና ማሳወቅ ነው።
3. አንድ ባሪያ የሚያገኘው መልካም ነገር በአላህ ችሮታ ነው። የሚያገኘው መጥፎ ነገር ግን በነፍሱና በስሜቱ ሳቢያ ነው።
4. መልካምን የሰራ በአላህ መግጠም ነው። የአላህ መመንዳትም ከአላህ የሆነ ችሮታ ስለሆነ ምስጋናው ለአሏህ ነው። መጥፎን የሰራ ግን ከነፍሱ በቀር ማንንም እንዳይወቅስ።

(4810)

(٨٠) - عَنْ جَابِرِ بْنِ عَبْدِ اللهِ رضي الله عنهما أَنَّ رَسُولَ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ قَالَ: «اتَّقُوا الظُّلْمَ، فَإِنَّ الظُّلْمَ ظُلُمَاتٌ يَوْمَ الْقِيَامَةِ، وَاتَّقُوا الشُّحَّ، فَإِنَّ الشُّحَّ أَهْلَكَ مَنْ كَانَ قَبْلَكُمْ، حَمَلَهُمْ عَلَى أَنْ سَفَكُوا دِمَاءَهُمْ وَاسْتَحَلُّوا مَحَارِمَهُمْ». [صحيح] - [رواه مسلم]

(80) - ከጃቢር ቢን ዐብደላህ (ረዲየሏሁ ዐንሁማ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል: "በደልን ተጠንቀቁ! በደል የትንሳኤ ቀን ድርብርብ ጨለማዎች ነውና። ስስትንም ተጠንቀቁ! ስስት ከናንተ በፊት የነበሩትን ህዝቦች አጥፍቷልና። ስስታምነት ደማቸውን እንዲያፈሱና ሐራም (ያልተፈቀደውን) እንደ ሐላል አድርገው እንዲቆጥሩ አነሳስቷቸዋልና።" [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ከበደል አስጠነቀቁ። ከበደል መካከልም: ሰዎችን መበደል፣ ነፍስን መበደል፣ በአላህ ሐቅ ላይ በደል መፈፀም ይጠቀሳሉ። በደል ማለት ሁሉንም የሐቅ ባለቤቶችን ሐቃቸውን ከመስጠት መተው ነው። በደል የትንሳኤ ቀን በባለቤቱ ላይ ከሚያጋጥመው መከራዎችና አስፈሪ ክስተቶች አኳያ ጨለማ ነው። ከስስትም ከለከሉ። እርሱም

ከመጓጓት (መንሰፍሰፍ) ጋር እጅግ ስስታምነት ነው። ከስስታምነት መካከል: ገንዘባዊ ሐቆችን ከመወጣት ቸል ማለትና ለዱንያ እጅግ መንገብገብን ይጠቀሳል። ይህኛው የበደል ክፍል ማለትም ስስታምነት ከእኛ በፊት የነበሩትን ህዝቦች አጥፍቷቸዋል። ይህም ከፊሉ ከፊሉን እንዲገድሉና አላህ እርም ያደረጋቸውን ክልክሎች የተፈቀዱ እንዲያደርጉ አነሳስቷቸዋል።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ገንዘብን ማውጣትና ወንድማዊ መረዳዳት ከመዋደድና ከመቀራረብ ሰበቦች መካከል አንዱ ነው።
2. ስስታምነትና ስግብግብነት ወደ ወንጀል፣ ኃጢአትና ብልግና ይጎትታል።
3. ካለፉት ህዝቦች ሁኔታ ትምህርት መውሰድ እንደሚገባ እንረዳለን።

(5787)

(٨١) - عن أبي موسى رضي الله عنه قال: قال رسول الله صلى الله عليه وسلم: «إِنَّ اللهَ لَيُمْلِي لِلظَّالِمِ، حَتَّى إِذَا أَخَذَهُ لَمْ يُفْلِتْهُ» قَالَ: ثُمَّ قَرَأَ: «{وَكَذَلِكَ أَخْذُ رَبِّكَ إِذَا أَخَذَ الْقُرَى وَهِيَ ظَالِمَةٌ إِنَّ أَخْذَهُ أَلِيمٌ شَدِيدٌ}[هود: 102]» [صحيح] - [متفق عليه]

(81) - ከአቡ ሙሳ -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: "የአላህ መልክተኛ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንዲህ ብለዋል: 'አላህ በዳይን ያዘገየዋል። የያዘው ጊዜ ግን አይለቀውም!'" አቡ ሙሳ እንዲህ አለ: "ቀጥለውም {የጌታህም ቅጣት የከተሞችን ሰዎች እነሱ በዳዮች ሲሆኑ በቀጣቸው ጊዜ እንደዚህ ነው። ቅጣቱ በእርግጥ አሳማሚ ብርቱ ነው።} [ሁድ: 102] የሚለውን አነበቡ።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም በወንጀል፣ በሽርክና ሰዎችን በመብታቸው በመበደል ላይ ከመዘውተር አስጠነቀቁ። ምክንያቱም አላህ በዳይን ያዘገየዋል፣ ያቆየዋል ፣ እድሜውንና ገንዘቡንም ያረዝምለታል። በቅጣትም

አያቻኩለውም። ካልቶበተ ግፉ ስለበዛ ይይዘዋል አይለቀውምም አይተወውምም።

ቀጥለውም ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም {የጌታህም ቅጣት የከተሞችን ሰዎች እነሱ በዳዮች ሲሆኑ በቀጣቸው ጊዜ እንደዚህ ነው። ቅጣቱ በእርግጥ አሳማሚ ብርቱ ነው።} [ሁድ: 102] የሚለውን አነበቡ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. አስተዋይ የሆነ ሰው ወደ ተውበት መቻኮል ይገባዋል። በበደል ላይ የዘወተረ ጊዜ አላህ አዘናግቶ እንደሚይዘው መጠራጠር የለበትም።
2. አላህ በዳዮችን ማዘግየቱና እነሱን በመቅጣት አለመቻኮሉ እነሱን ማዘናጊያና ካልቶበቱ ቅጣታቸውን ማነባበርያ ነው።
3. ግፍ የአላህን ቅጣት ህዝቦች ላይ የሚያመጣ አንዱ ምክንያት ነው።
4. አላህ አንድን መንደር ሲያጠፋ በውስጧ ደጋጎችም ሊኖሩ ይችላሉ። እነዚህ ደጋጎች የትንሳኤ ቀን በሞቱበት መልካምነት ላይ ሆነው ነው የሚቀሰቀሱት። ምድራዊ ቅጣቱ እነሱንም ማካተቱ በመጪው አለም አይጎዳቸውም።

(5811)

(٨٢) - عن ابن عباس رضي الله عنهما عَنِ النَّبِيِّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ فِيمَا يَرْوِي عَنْ رَبِّهِ عَزَّ وَجَلَّ قَالَ: قَالَ: «إِنَّ اللهَ كَتَبَ الْحَسَنَاتِ وَالسَّيِّئَاتِ، ثُمَّ بَيَّنَ ذَلِكَ، فَمَنْ هَمَّ بِحَسَنَةٍ فَلَمْ يَعْمَلْهَا كَتَبَهَا اللهُ لَهُ عِنْدَهُ حَسَنَةً كَامِلَةً، فَإِنْ هُوَ هَمَّ بِهَا فَعَمِلَهَا كَتَبَهَا اللهُ لَهُ عِنْدَهُ عَشْرَ حَسَنَاتٍ إِلَى سَبْعِمِائَةِ ضِعْفٍ، إِلَى أَضْعَافٍ كَثِيرَةٍ، وَمَنْ هَمَّ بِسَيِّئَةٍ فَلَمْ يَعْمَلْهَا كَتَبَهَا اللهُ لَهُ عِنْدَهُ حَسَنَةً كَامِلَةً، فَإِنْ هُوَ هَمَّ بِهَا فَعَمِلَهَا كَتَبَهَا اللهُ لَهُ سَيِّئَةً وَاحِدَةً». [صحيح] - [متفق عليه]

(82) - ከኢብኑ ዐባስ -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ከተከበረውና ከላቀው ጌታቸው በሚያስተላልፉት (ሐዲሠል ቁድሲይ) እንዲህ አሉ፦ አላህ እንዲህ አለ፦ "አላህ መልካሞችና ኃጢዐቶችን ፅፏል ከዚያም ይህንን አብራርቷል። አንድን መልካም ስራ (ለመስራት) ያሰበና ያልሰራት አላህ እሱ ዘንድ ለሱ ሙሉ ምንዳን ይጻፍለታል ። እሱ (ለመስራት) አስቧት ከሰራት ደግሞ አላህ እሱ ዘንድ ለሱ ከአስር እስከ ሰባት መቶ እጥፍ (ከዛም አልፎ) እስከ ብዙ እጥፍ ድርብ የሚደርስ ምንዳዎች ይጻፍለታል። አንድን ኃጢዐት (ለመስራት) ያሰበና ያልሰራት አላህ እሱ ዘንድ ለሱ ሙሉ ምንዳ ይጻፍለታል። እሱ (ለመስራት) ካሰባትና ከሰራት አላህ ለሱ አንዲት ኃጢዐት ይጽፍበታል።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

መልክተኛው ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም አላህ መልካሞችና ኃጢዐቶችን እንደወሰነ ከዚያም ለሚፅፉት ሁለት መላእክቶች እንዴት እንደሚፅፉት እንዳብራራ ገለፁ።

መልካምን ለመስራት የፈለገ፣ ያሰበና የቆረጠ ሰው ባይሰራትም እንኳ ለሱ አንድ ምንዳ ትፃፍለታለች። ከሰራት ደግሞ በስራዋ አምሳያ ከአስር እስከ ሰባት መቶ እጥፍ ከዚያም አልፎ እስከ ብዙ እጥፍ ድርብ ትባዛለች። ይህ የምንዳ ጭማሪው ቀልቡ ውስጥ ባለው ኢኽላስ፣ በጥቅሙ ወደ ሌሎች ተሻጋሪነትና በመሳሰሉት ልክ ተንተርሶ ነው ።

ኃጢዐትን ለመስራት የፈለገ፣ ያሰበና የቆረጠ ከዚያም ለአላህ ብሎ ሳይሰራት የተዋት ሰው ለሱ አንድ ምንዳ ይጻፍለታል። ወደዛቹ ኃጢዐት የሚያዳርሱ መንስኤዎችን ካለመፈፀም ጋር በሌላ ነገር በመጠመዱ ሳቢያ ከተዋት ምንም ነገር አይፃፍለትም። ኃጢዐቱን መስራት ስለተሳነው ከተወ ደግሞ በሱ ላይ ያለመው ትፃፍበታለች። ከሰራት ደግሞ አንዲት ሀጢዐት ትፃፍበታለች።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. መልካም ስራዎችን ማነባበሩ፣ እሱ ዘንድ መፃፉና ሀጢዐቶችን ስንሰራ ደግሞ አለማነባበሩ አላህ ለዚህ ኡመት የዋለውን ትልቅ ቸሮታ ያብራራል።
2. በስራዎች ላይ የኒያ አስፈላጊነትና ተፅእኖን ተረድተናል።
3. መልካምን ሊሰራ አስቦ ላልሰራ ሰው አላህ ለሱ ምንዳ መፃፉ የአላህን ቸሮታ፣ እዝነትና መልካምነትን ያስረዳል።

(4322)

(٨٣) - عَنِ ابْنِ مَسْعُودٍ رَضِيَ اللهُ عَنْهُ، قَالَ: قَالَ رَجُلٌ: يَا رَسُولَ اللهِ، أَنُؤَاخَذُ بِمَا عَمِلْنَا فِي الْجَاهِلِيَّةِ؟ قَالَ: «مَنْ أَحْسَنَ فِي الْإِسْلَامِ لَمْ يُؤَاخَذْ بِمَا عَمِلَ فِي الْجَاهِلِيَّةِ، وَمَنْ أَسَاءَ فِي الْإِسْلَامِ أُخِذَ بِالْأَوَّلِ وَالْآخِرِ». [صحيح] - [متفق عليه]

(83) - ከኢብኑ መስዑድ - አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ ብለዋል፦ “አንድ ሰውዬ እንዲህ አለ፦ " የአላህ መልክተኛ ሆይ! በጃሂሊያ (ከእርሶ መላክ በፊት ባለው የድንቁርና ዘመን) በሠራነው ሥራ እንቀጣለን?" ነቢዩም (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) እንዲህ አሉት፦ "በኢስላም ሥራውን ያሳመረ፥ በጃሂሊያ በሠራው ሥራ ተጠያቂ አይሆንም። እስልምናን ተቀብሎም መጥፎ የሠራ ግን በቀድሞውም በኋለኛውም ስራው ይጠየቅበታል። " [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ወደ እስልምና የመግባትን ትሩፋት አብራሩ። እስልምናውን አሳምሮ፣ እውነተኛና ሙኽሊስ (ያጠራ) ሆኖ የሰለመ ሰው ከመስለሙ በፊት በሠራው ወንጀል አይጠየቅም። ወደ እስልምና ከገባ በኋላ ሙናፊቅ በመሆን ወይም ከእምነቱ በመውጣት መጥፎ የሠራ ግን በክህደት ዘመኑም ሆነ በእስልምና ዘመኑ ስለ ሠራው ሥራ ይጠየቃል።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ሰሓቦች አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና በጃሂሊያ ዘመን ለሰሩት ስራ የሰጡት ትኩረትና ፍርሃታቹውን እንረዳለን።
2. በእስልምና ላይ መፅናት መበረታታቱ፤
3. ወደ እስልምና የመግባትን ትሩፋት እንረዳለን። እሱም ያለፈውን መጥፎ ስራዎች ማስማሩ ነው።

4. ከእስልምና የወጣና ሙናፊቅ የሆነ ሰው ቀደም ብሎ ከመስለሙ በፊት ስለ ሠራቸው ሁሉ ሥራዎችና በእስልምና ውስጥም ስለ ሰራቸው ሁሉ ወንጀሎች ይጠየቃል።

(65002)

(٨٤) - عَنِ ابْنِ عَبَّاسٍ رَضِيَ اللهُ عَنْهُمَا: أَنَّ نَاسًا مِنْ أَهْلِ الشِّرْكِ، كَانُوا قَدْ قَتَلُوا وَأَكْثَرُوا، وَزَنَوْا وَأَكْثَرُوا، فَأَتَوْا مُحَمَّدًا صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ فَقَالُوا: إِنَّ الَّذِي تَقُولُ وَتَدْعُو إِلَيْهِ لَحَسَنٌ، لَوْ تُخْبِرُنَا أَنَّ لِمَا عَمِلْنَا كَفَّارَةً، فَنَزَلَ {وَالَّذِينَ لا يَدْعُونَ مَعَ اللهِ إِلَهًا آخَرَ وَلا يَقْتُلُونَ النَّفْسَ الَّتِي حَرَّمَ اللهُ إِلا بِالْحَقِّ وَلا يَزْنُونَ}[الفرقان: 68]، وَنَزَلَت: {قُلْ يَا عِبَادِيَ الَّذِينَ أَسْرَفُوا عَلَى أَنْفُسِهِمْ لا تَقْنَطُوا مِنْ رَحْمَةِ اللهِ} [الزمر: 53]. [صحيح] - [متفق عليه]

(84) - ከኢብኑ ዓባስ (ረዲየሏሁ ዐንሁማ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ ብለዋል: "ከዚህ በፊት አብዝተው ነፍስ የሚገድሉ፣ አብዝተው ዝሙት የሚሰሩ የነበሩ የሺርክ ባለቤት የሆኑ ሰዎች ሙሐመድ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) ዘንድ በመምጣት እንዲህ አሉ ' የምትናገረውና የምትጣራበት ጉዳይ መልካም ነው። ለሰራነው ፀያፍ ተግባር ማስማረያ እንዳለው እንደው ብትነግረን?' {እነዚያም ከአላህ ጋር ሌላን አምላክ የማይግገዙት፤ ያችንም አላህ እርም ያደረጋትን ነፍስ ያለ ህግ የማይገድሉት፤ የማያመነዝሩትም ናቸው።} [ፉርቃን:68] የሚለውና {በላቸው «እናንተ በነፍሶቻችሁ ላይ ድንበር ያለፋችሁ ባሮቼ ሆይ! ከአላህ እዝነት ተስፋ አትቁረጡ።»} [አዝዙመር: 53] የሚለው አንቀፅ ወረደች።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ከሙሽሪኮች የሆኑ ሰዎች ወደ ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) መጡ። አብዝተው የገደሉና የዘሞቱ ነበሩ። ለነቢዩ የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ አሉ: የምትጣራው ኢስላምና

አስተምህሮቶቹ መልካም ጉዳይ ነው። ነገር ግን የወደቅንበት ሺርክና ከባድ ወንጀል ለርሱ ማስማሪያ አለውን?

ወንጀላቸው ከመብዛቱና ከመተለቁ ጋርም አላህ ከሰዎቹ ተውበታቸውን እንደተቀበለ የሚጠቁሙ ሁለት አንቀፆች ወረዱ። ይህ ባልነበር ኖሮ በክህደታቸውና ጥመታቸው ላይ ይቀጥሉ ነበር። ወደዚህ ሃይማኖትም አይገቡም ነበር።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. የኢስላም ትሩፋትና ልቅናውን እንረዳለን። ኢስላም ያለፈውን ወንጀል ያስምራል (ያወድማል)።
2. አላህ በባሮቹ ላይ ያለው እዝነት ስፋቱን፣ ምህረቱንና ይቅር ባይነቱን እንረዳለን።
3. የሺርክን ክልክልነት፣ ያለ ህግ ነፍስን የመግደልን ክልክልነት፣ የዝሙትን ክልክልነት፣ እነዚህን ወንጀሎች የሚዳፈር ላይ የመጣውንም ዛቻ እንረዳለን።
4. ከኢኽላስና መልካም ስራ ጋር የተቆራኘ እውነተኛ ተውበት በአላህ መካድንም ጨምሮ ሁሉንም ትላልቅ ወንጀሎች ያስምራል።
5. ከአላህ እዝነት ተስፋ መቁረጥ ክልክል መሆኑን እንረዳለን።

(65071)

(٨٥) - عَنْ حَكِيمِ بْنِ حِزَامٍ رَضِيَ اللهُ عَنْهُ، قَالَ: قُلْتُ: يَا رَسُولَ اللهِ أَرَأَيْتَ أَشْيَاءَ كُنْتُ أَتَحَنَّثُ بِهَا فِي الجَاهِلِيَّةِ مِنْ صَدَقَةٍ أَوْ عَتَاقَةٍ، وَصِلَةِ رَحِمٍ، فَهَلْ فِيهَا مِنْ أَجْرٍ؟ فَقَالَ النَّبِيُّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ: «أَسْلَمْتَ عَلَى مَا سَلَفَ مِنْ خَيْرٍ». [صحيح] - [متفق عليه]

(85) - ሐኪም ቢን ሒዛም -አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንዲህ አሉ፦ "የአላህ መልክተኛ ሆይ! በጃሂሊያ ዘመን በምፅዋት፣ ነፃ በማውጣትና ዝምድና በመቀጠል የምፈፅማቸው አምልኮዎች ነበሩ በእነሱ እመነዳለውን?" አልኳቸው። ነቢዩም የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ ብለው መለሱለት፦ "ካሳለፍከው መልካም ተግባር ጋር ነው የሰለምከው።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ካፊር የሰለመ ጊዜ ከመስለሙ በፊት በጃሂሊያ ዘመን ይሠራቸው በነበሩት እንደ ሰደቃ፣ ባሪያን ነፃ ማውጣትና ዝምድና መቀጠል የመሰሉ መልካም ሥራዎች እንደሚመነዳ አብራሩ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ካፊር በዱንያ ለሠራቸው መልካም ሥራዎች በዛው ክህደት ላይ ከሞተ በአኺራ አይመነዳበትም።

(65016)

(٨٦) - عَنْ أَنَسِ بْنِ مَالِكٍ رضي الله عنه قَالَ: قَالَ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ: «إِنَّ اللهَ لَا يَظْلِمُ مُؤْمِنًا حَسَنَةً، يُعْطَى بِهَا فِي الدُّنْيَا وَيُجْزَى بِهَا فِي الْآخِرَةِ، وَأَمَّا الْكَافِرُ فَيُطْعَمُ بِحَسَنَاتِ مَا عَمِلَ بِهَا لِلهِ فِي الدُّنْيَا، حَتَّى إِذَا أَفْضَى إِلَى الْآخِرَةِ، لَمْ تَكُنْ لَهُ حَسَنَةٌ يُجْزَى بِهَا». [صحيح] - [رواه مسلم]

(86) - አነስ ቢን ማሊክ -አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና- እንዲህ አሉ: የአላህ መልክተኛ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ አሉ፦ "አላህ አማኝን አንድም መልካም ሥራውን አይበድለውም በዱንያ በሷ ምክንያት (መልካም ነገር) ሲሰጠው በአኺራም በሷ ምክንያት ይመነዳዋል። ካፊር ግን ለአላህ ብሎ በሠራው መልካም ሥራ ምክንያት በዱንያ እንዲበላ ይደረጋል። ወደ አኺራ የተሸጋገረ ጊዜ በአኺራ የሚመነዳበት መልካም ሥራ አይኖረውም።" [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን አላህ በአማኞች ላይ የዋለውን ትልቅ ችሮታና ከከሀዲያን ጋር ያለውን ፍትሀዊነት ያብራራሉ። አማኝ የሆነ ሰው የመልካም ሥራው ምንዳ ምንም አትጎድልም። በአኺራ ከሚደለብለት (ከሚከማችለት) ምንዳ በተጨማሪ በዱንያም በአምልኮው ምክንያት መልካምን ይሰጠዋል። ይህ ካልሆነ እንኳ ሁሉም ምንዳው ለሱ አኺራ ላይ ይጠበቅለታል። ካፊር ግን ለሠራው መልካም ሥራ የሚመነዳው በዱንያ አላህ በሚሰጠው መልካም ነገር ነው። ወደ አኺራ የተሸጋገረ ጊዜ ምንም የሚመነዳው ክፍያ አይኖረውም። ምክንያቱም በመልካም ሥራ በሁለቱም ዓለም ለመጠቀም የግድ ባለቤቱ አማኝ መሆን ይጠበቅበታል።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. በክህደት ላይ የሞተ ሰው ምንም ተግባር አይጠቅመውም።

(65015)

(٨٧) - عَنْ أَنَسِ بْنِ مَالِكٍ رضي الله عنه قَالَ: سَمِعْتُ رَسُولَ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ يَقُولُ: «قَالَ اللهُ تَبَارَكَ وَتَعَالَى: يَا ابْنَ آدَمَ إِنَّكَ مَا دَعَوْتَنِي وَرَجَوْتَنِي غَفَرْتُ لَكَ عَلَى مَا كَانَ فِيكَ وَلاَ أُبَالِي، يَا ابْنَ آدَمَ لَوْ بَلَغَتْ ذُنُوبُكَ عَنَانَ السَّمَاءِ ثُمَّ اسْتَغْفَرْتَنِي غَفَرْتُ لَكَ، وَلاَ أُبَالِي، يَا ابْنَ آدَمَ إِنَّكَ لَوْ أَتَيْتَنِي بِقُرَابِ الأَرْضِ خَطَايَا ثُمَّ لَقِيتَنِي لاَ تُشْرِكُ بِي شَيْئًا لأَتَيْتُكَ بِقُرَابِهَا مَغْفِرَةً».

[حسن] - [رواه الترمذي]

(87) - ከአነስ ቢን ማሊክ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: «የአላህን መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ሲሉ ሰምቻቸዋለሁ: "አላህ ተባረከ ወተዓላ እንዲህ ብሏል: ‹የአደም ልጅ ሆይ አንተ እስከለመንከኝና እስከከጀልከኝ ድረስ አንተ ላይ ካለብህ ወንጀልህ ጋርም እምርሃለሁ። (በመማሬም) ምንም አይመስለኝም፤ የአደም ልጅ ሆይ! ወንጀሎችህ የሰማይ ደመና ቢደርሱና ከዚያም ምህረት ብትጠይቀኝ እምርሃለሁ። (በመማሬም) ምንም አይመስለኝም፤ የአደም ልጅ ሆይ! ምድርን ሊሞላ በቀረበ ወንጀል እኔ ጋር ብትመጣ ከዚያም በኔ አንድንም ሳታጋራብኝ ብትገናኘኝ እኔም ምድርን ሊሞላ በቀረበ ምህረት ወዳንተ እመጣለሁ።›"» [ሐሰን ነው።] - [ቲርሚዚ ዘግበውታል። ]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና በሐዲሠል ቁድስ ውስጥ አላህ እንዲህ እንዳለ ተናገሩ: የአደም ልጅ ሆይ! እኔን በመለመን፣ እዝነቴን በመከጀልና ተስፋ ባለመቁረጥ ላይ እስከዘወተርክ ድረስ ይህ ወንጀልህና ሀጢዐትህ ከትላልቅ ወንጀሎች ቢሆንም እንኳ እሸሽገዋለሁ፣ ምንም ሳይመስለኝም አብሰዋለሁ። የአደም ልጅ ሆይ! ወንጀልህ በሰማይና በምድር መካከል ያለውን በሚሞላና ምድርንም ከጫፍ እስከጫፍ በሚደርስና ጎኖቿን በሚያጠቃልል መልኩ ቢበዛ ከዚያም ምህረት ብትጠይቀኝ ብዛቱ ምንም ሳይመስለኝ ሁሉንም ላንተ አብሰዋለሁም እምርሃለሁኝም።

የአደም ልጅ ሆይ! አንተ ከሞት በኋላ ወደኔ ምድርን በሚሞላ ወንጀሎችና ሀጢዐቶች ብትመጣ በብቸኝነቴ አምልከሀኝ በኔ አንድንም ሳታጋራ ከሆነ የሞትከው እነዚህን ወንጀሎችህንና ሀጢዐቶችህን ምድርን በሚሞላ ምህረት እገናኛቸዋለሁ። እኔ ምህረተ ሰፊ ነኝና። ከሺርክ በስተቀርም ሁሉንም ወንጀሎችህን እምራለሁ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. የአላህ እዝነትና ምህረት ሰፊ መሆኑንና ደረጃውንም እንረዳለን።
2. የተውሒድን ትሩፋት እንረዳለን። አላህ ለተውሒድ ሰዎች ወንጀልና ሀጢዐታቸውን ይምራል።
3. የሺርክን አደጋና አላህ አጋርያንን እንደማይምርም እንረዳለን።
4. ኢብኑ ረጀብ እንዲህ ብለዋል: «ይህ ሐዲሥ ወንጀልን የሚያስምሩትን ሶስት ሰበቦች አጠቃልሏል። የመጀመሪያው: ከመከጀል ጋር ዱዓ ማድረግ ነው። ሁለተኛ: ምህረትን መጠየቅና ንስሀን መፈለግ ነው። ሶስተኛ: በተውሒድ ላይ መሞት ነው።»
5. ይህ ሐዲሥ ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ከጌታቸው ከሚያወሩት ሐዲሥ መካከል አንዱ ነው። "ሐዲሠል ቁድሲይ" ወይም "ሐዲሠል ኢላሂይ" በመባልም ይጠራል። ይህም ማለት ቃሉም መልዕክቱም ከአላህ የሆነና ነገር ግን በማንበቡ እንደማምለክ፣ ለርሱ ዉዱእ ማድረግና የርሱን አምሳያ አምጡ ብሎ አላህ መገዳደሩን የመሰሉ የቁርአን መለዮዎች የሌለው ነው።
6. ወንጀሎች ሶስት አይነቶች ናቸው: የመጀመሪያው: በአላህ ማጋራት ነው። ይህም አላህ የማይምረው ወንጀል ነው። አላህ ዐዘ ወጀል እንዲህ ብሏል {እነሆ! በአላህ የሚያጋራ ሰው አላህ በርሱ ላይ ገነትን በእርግጥ እርም አደረገ።} ሁለተኛው: አንድ ባሪያ በርሱና በጌታው መካከል ባለው ጉዳይ በወንጀልና ሀጢዐት ነፍሱን መበደሉ ነው። ይህንንም አላህ ከሻ የሚያልፈውና ይቅር የሚለው ነው። ሶስተኛ: አላህ አንዳችም የማይተወው

ወንጀል ነው። እርሱም: ባሮች አንዳቸው አንዳቸውን መበደላቸው ነው። ይህንንም የግድ የማመሳሰል ፍርድ ተፈፃሚ ይሆንበታል።

(5456)

(٨٨) - عن أبي هريرة رضي الله عنه عَنِ النَّبِيِّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ، فِيمَا يَحْكِي عَنْ رَبِّهِ عَزَّ وَجَلَّ، قَالَ: «أَذْنَبَ عَبْدٌ ذَنْبًا، فَقَالَ: اللَّهُمَّ اغْفِرْ لِي ذَنْبِي، فَقَالَ تَبَارَكَ وَتَعَالَى: أَذْنَبَ عَبْدِي ذَنْبًا، فَعَلِمَ أَنَّ لَهُ رَبًّا يَغْفِرُ الذَّنْبَ، وَيَأْخُذُ بِالذَّنْبِ، ثُمَّ عَادَ فَأَذْنَبَ، فَقَالَ: أَيْ رَبِّ اغْفِرْ لِي ذَنْبِي، فَقَالَ تَبَارَكَ وَتَعَالَى: عَبْدِي أَذْنَبَ ذَنْبًا، فَعَلِمَ أَنَّ لَهُ رَبًّا يَغْفِرُ الذَّنْبَ، وَيَأْخُذُ بِالذَّنْبِ، ثُمَّ عَادَ فَأَذْنَبَ، فَقَالَ: أَيْ رَبِّ اغْفِرْ لِي ذَنْبِي، فَقَالَ تَبَارَكَ وَتَعَالَى: أَذْنَبَ عَبْدِي ذَنْبًا، فَعَلِمَ أَنَّ لَهُ رَبًّا يَغْفِرُ الذَّنْبَ، وَيَأْخُذُ بِالذَّنْبِ، اعْمَلْ مَا شِئْتَ فَقَدْ غَفَرْتُ لَكَ». [صحيح] - [متفق عليه]

(88) - ከአቡ ሁረይራ -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ከላቀውና ከተከበረው ጌታቸው ባስተላለፉት (ሐዲሥ) እንዲህ አሉ "አንድ ባሪያ አንድን ወንጀል ሰራና እንዲህ አለ "አላህ ሆይ! ወንጀሌን ማረኝ! " የጠራውና ከፍ ያለውም እንዲህ አለ "ባሪያዬ ወንጀልን ሰርቶ ወንጀልን የሚምርና በወንጀሉም የሚይዘው ጌታ እንዳለው አወቀ!" ከዚያም ደግሞ ወንጀል ሰራና እንዲህ አለ "ጌታዬ ሆይ! ወንጀሌን ማረኝ!" የጠራውና ከፍ ያለውም እንዲህ አለ "ባሪያዬ ወንጀልን ሰርቶ ወንጀልን የሚምርና በወንጀሉም የሚይዘው ጌታ እንዳለው አወቀ!" ከዚያም አሁንም ደግሞ ወንጀል ሰራና እንዲህ አለ "ጌታዬ ሆይ! ወንጀሌን ማረኝ!" የጠራውና ከፍ ያለውም እንዲህ አለ "ባሪያዬ ወንጀልን ሰርቶ ወንጀልን የሚምርና በወንጀሉም የሚይዘው ጌታ እንዳለው አወቀ! የፈለግከውን ስራ በርግጥ ላንተ ምሬሃለሁ።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ከጌታቸው በሚያወሩት ሐዲሥ አንድ ባሪያ አንድ ወንጀል ሰርቶ ከዚያም "አላህ ሆይ! ወንጀሌን ማረኝ!" ካለ አላህ "ባሪያዬ ወንጀልን ሰርቶ ወንጀሉን የሚምረው ጌታ እንዳለው አወቀ!" ብሎ

ይሸሽገዋልም ከሱ ይቅር ይለዋልም። ወይም ምሬዋለሁ የሚል ንግግር እንደሚያስከትልለት ነገሩን። ከዚያም ባሪያው በድጋሚ ወንጀል ይሰራና "ጌታዬ ወንጀሌን ማረኝ!" ይላል። አላህም "ባሪያዬ ወንጀልን ሰራ። ለሱ ወንጀልን የሚምር ጌታ እንዳለው አወቀ።" ይልና ይሸሽገዋልም ከሱ ይቅር ይለዋልም። ወይም የሚቀጣውን ቀጥቶ "ለባሪያዬ ምሬዋለሁ" ይላል። ከዚያም ባሪያው በድጋሚ ወንጀል ይሰራና "ጌታዬ ወንጀሌን ማረኝ!" ይላል። አላህም "ባሪያዬ ወንጀልን ሰርቶ ወንጀልን የሚምር ጌታ እንዳለው አወቀ!" ይልና ይሸሽገዋልም ከሱ ይቅር ይለዋልም። ወይም የሚቀጣውን ቀጥቶ "ለባሪያዬ ምሬዋለሁ" ይላል። አላህ እንዲህም ይላል: ወንጀልን በሰራ ቁጥር ወንጀሉን በመተውና በመፀፀት ዳግም ወደ ወንጀል ላለመመለስም ቆርጦ እየወሰነ ነገር ግን ነፍሱ እያሸነፈችው ወንጀል ላይ በድጋሚ እየወደቀ በዚህ መልኩ ወንጀል ቢሰራም ተውበት ማድረግን እስካዘወተረ ድረስ የሰራውን ቢሰራ እምረዋለሁ። ተውበት ያለፈውን ወንጀል ታብሳለችና።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. አላህ በባሮቹ ላይ ያለው እዝነት ስፋቱን ፤ የሰው ልጅ ምንም ያክል ወንጀል ቢሰራ ወደ አላህ ተውበት ካደረገና ከተመለሰ አላህ ተውበቱን እንደሚቀበለው፤
2. በአላህ ያመነ የጌታውን ይቅርታ ተስፋ ያደርጋል፣ ቁጣውንም ይፈራል፣ ወደ ተውበት ይቻኮላል እንጂ በወንጀል ላይ አይቀጥልም።
3. የትክክለኛ ተውበት መስፈርቶች: ከወንጀል መውጣት፣ በወንጀሉም መፀፀት፣ ዳግም ወደ ወንጀል ላለመመለስ መቁረጥ ነው። ተውበት የሚያደርገው ባሮችን በገንዘብ ወይ በክብር ወይ በነፍስ ከመበደል ወንጀል ከሆነ አራተኛ መስፈርት ይጨመራል። እሱም: ተበዳዩ ባለመብት ሀላል እንዲያደርግለት (ዓውፍ እንዲለው) መጠየቅ ወይም ሓቁን መስጠት ነው።
4. አንድን ባሪያ ስለዲኑ ጉዳይ አዋቂ የሚያደርገው የሆነውን አላህን ማወቅ አንገብጋቢ ጉዳይ መሆኑን ተረድተናል። ስለአላህ ማወቁ ወንጀል በሰራ ቁጥር ተስፋ ሳይቆርጥና ወንጀሉ ላይ ሳይዘልቅ እንዲቶብት ያደርገዋልና።

(4817)

(٨٩) - عن عَلِيٍّ قَالَ: إِنِّي كُنْتُ رَجُلًا إِذَا سَمِعْتُ مِنْ رَسُولِ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ حَدِيثًا نَفَعَنِي اللهُ مِنْهُ بِمَا شَاءَ أَنْ يَنْفَعَنِي بِهِ، وَإِذَا حَدَّثَنِي رَجُلٌ مِنْ أَصْحَابِهِ اسْتَحْلَفْتُهُ، فَإِذَا حَلَفَ لِي صَدَّقْتُهُ، وَإِنَّهُ حَدَّثَنِي أَبُو بَكْرٍ، وَصَدَقَ أَبُو بَكْرٍ، قَالَ: سَمِعْتُ رَسُولَ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ يَقُولُ: «مَا مِنْ رَجُلٍ يُذْنِبُ ذَنْبًا، ثُمَّ يَقُومُ فَيَتَطَهَّرُ، ثُمَّ يُصَلِّي، ثُمَّ يَسْتَغْفِرُ اللهَ، إِلَّا غَفَرَ اللهُ لَهُ»، ثُمَّ قَرَأَ هَذِهِ الْآيَةَ: {وَالَّذِينَ إِذَا فَعَلُوا فَاحِشَةً أَوْ ظَلَمُوا أَنْفُسَهُمْ ذَكَرُوا اللهَ فَاسْتَغْفَرُوا لِذُنُوبِهِمْ} [آل عمران: 135]. [صحيح] - [رواه أبو داود والترمذي والنسائي في الكبرى وابن ماجه وأحمد]

(89) - ከዐሊይ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: "እኔ ከአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) አንድን ሐዲሥ የሰማሁ ጊዜ አላህ በዛ ሐዲሥ በሻው መንገድ የሚጠቅመኝ ሰው ነበርኩ፤ ከሶሐቦቻቸው መካከል አንድ ሰው ሐዲሥ የነገረኝ ጊዜ ታዲያ አስምለዋለሁ። ከማለልኝ አምነዋለሁ። አቡበከር ለኔ አንድ ሐዲሥ ነግሮኛል። አቡበከር የነገረኝም እውነት ነበር። አቡበከር እንዲህ አሉ: 'የአላህን መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ሲሉ ሰምቻቸዋለሁ: "ኃጢዓትን የሠራ ከዚያም ተነስቶ ዉዱእ አድርጎ የሚሰግድ ከዚያም ለኃጢዓቱ ከአሏህ ምህረት የሚጠይቅ አንድም ሰው የለም፤ አላህ ለርሱ የሚምረው ቢሆን እንጂ።› ቀጥለውም ይህቺን አንቀፅ አነበቡ {ለእነዚያም መጥፎ ስራን በሰሩ ወይም ነፍሶቻቸውን በበደሉ ጊዜ አላህን የሚያስታውሱና ለሀጢዐቶቻቸው ምህረትን የሚለምኑ ለሆኑት} [ኣሊ ዒምራን:135] '" [ሶሒሕ ነው።] - [አቡዳወድ፣ ቲርሚዚ፣ ነሳኢ በኩብራ፣ ኢብኑማጀህና አሕመድ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) አላህ ለርሱ የሚምረው ቢሆን እንጂ ዉዱእን አሳምሮ ከዚያም ከወንጀሉ ወደ አላህ በመመለስ ኒያ ቁሞ ሁለት ረከዓ ሰግዶ ከዚያም አላህን ምህረት የሚጠይቅ አንድም ኃጢዓት የሚሰራ ባሪያ እንደሌለ ተናገሩ። ቀጥለውም ነቢዩ (የአላህ

ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ይህንን የአላህ ቃል አነበቡ: {ለእነዚያም መጥፎ ስራን በሰሩ ወይም ነፍሶቻቸውን በበደሉ ጊዜ አላህን የሚያስታውሱና ለሀጢዐቶቻቸው ምህረትን የሚለምኑ ለሆኑት ከአላህም ሌላ ኀጢዐቶችን የሚምር አንድም የለ። (በስህተት) በሰሩትም ላይ እነርሱ የሚያውቁ ሲሆኑ የማይዘወትሩ ለሆኑት (ተደግሳለች)።} [ኣሊ ዒምራን:135]

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ሶላት ላይ እና ለወንጀል ምህረት መጠየቅ ላይ መነሳሳቱን እንረዳለን።
2. የአላህ ምህረት ሰፊ መሆኑንና፤ ተውበትና ምህረት ሲጠየቅ እንደሚቀበል እንረዳለን።

(65063)

(٩٠) - عَنْ أَبِي مُوسَى رضي الله عنه عَنِ النَّبِيِّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ قَالَ: «إِنَّ اللهَ عَزَّ وَجَلَّ يَبْسُطُ يَدَهُ بِاللَّيْلِ لِيَتُوبَ مُسِيءُ النَّهَارِ، وَيَبْسُطُ يَدَهُ بِالنَّهَارِ لِيَتُوبَ مُسِيءُ اللَّيْلِ، حَتَّى تَطْلُعَ الشَّمْسُ مِنْ مَغْرِبِهَا». [صحيح] - [رواه مسلم]

(90) - ከአቡ ሙሳ (ረዲየላሁ ዐንሁ) -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ አሉ: "አላህ ዐዘ ወጀል በቀን ኃጢዓት የፈፀሙ እንዲፀፀቱ (ተውበት እንዲያደርጉ) በምሽት እጁን ይዘረጋል። በምሽት ኃጢዓት የፈፀሙ እንዲፀፀቱ (ተውበት እንዲያደርጉ) ደግሞ በቀን እጁን ይዘረጋል። ይህም ፀሀይ በመግቢያዋ በኩል እስክትወጣ ድረስ ቀጣይ ነው።" [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) አላህ ከባሮቹ ንስሀቸውን እንደሚቀበል ተናገሩ። አንድ ባሪያ በቀን ወንጀል ሰርቶ በምሽት ንስሀ ከገባም አላህ ንስሀውን ይቀበለዋል። በምሽት ወንጀል ሰርቶ በቀን ንስሀ

ከገባም አላህ ንስሀውን ይቀበለዋል። አሏህ ንስሀ ለሚገቡ ሰዎች እጁን የሚዘረጋውም በንስሀቸው ስለሚደሰትና ንስሀቸውንም ለመቀበል ነው። የዚህ አለም ፍፃሜን የምታሳውቀው የፀሀይ ከመግቢያዋ በኩል መውጣት እስኪከሰት ድረስም የንስሀ በር ክፍት ከመሆን አይወገድም። ፀሀይ በመግቢያዋ በኩል የወጣች ጊዜ ግን የንስሀ በር ይዘጋል።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. የተውበት በር ክፍት እስከሆነ ድረስ ተቀባይነቷም ይቀጥላል። ፀሀይ ከመግቢያዋ በመውጣቷ ደግሞ በሩ ይዘጋል። ልክ እንደዚሁ ጣእረ ሞት - ማለትም ነፍስ ልትወጣ ጉሮሮ ጋር - ከመድረሱ በፊት ንስሀ መግባትም ይገባዋል።
2. በወንጀል ተስፋ መቁረጥ እንደማይገባ፤ የአላህ ይቅር ባይነትና እዝነት ሰፊ መሆኑን እንዲሁም የተውበት በርም ክፍት መሆኑን እንረዳለን።
3. የተውበት (ንስሀ) መስፈርቶች: የመጀመሪያው: ከወንጀሉ መውጣት ነው። ሁለተኛው: ወንጀሉን በመፈፀሙ መፀፀት ነው። ሶስተኛው: ወደ ወንጀሉ ዳግመኛ ላይመለስ መቁረጥ ነው። እነዚህ መስፈርቶች ግን የተጣሰው የአላህ መብቶች ብቻ ከሆነ ነው። ከፍጡራን ሐቆች ጋር የተያያዘ ወንጀል ከሆነ ግን ንስሀው ትክክለኛ እንዲሆን ይህን ሀቅ ወደ ባለቤቱ መመለስ ወይም ከባለቤቱ ይቅርታን ማግኘት ተጨማሪ መስፈርት ነው።

(4318)

(٩١) - عن أبي هريرة رضي الله عنه: أن رسول الله صلى الله عليه وسلم قال: «يَنْزِلُ رَبُّنَا تَبَارَكَ وَتَعَالَى كُلَّ لَيْلَةٍ إِلَى السَّمَاءِ الدُّنْيَا حِينَ يَبْقَى ثُلُثُ اللَّيْلِ الْآخِرُ، يَقُولُ: «مَنْ يَدْعُونِي فَأَسْتَجِيبَ لَهُ؟ مَنْ يَسْأَلُنِي فَأُعْطِيَهُ؟ مَنْ يَسْتَغْفِرُنِي فَأَغْفِرَ لَهُ؟». [صحيح] - [متفق عليه]

(91) - ከአቡ ሁረይራ -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው የአላህ መልክተኛ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንዲህ አሉ: "የላቀውና ከፍ ያለው ጌታችን በሁሉም ሌሊት የመጨረሻ ሲሶ ወደ ቅርቢቱ ሰማይ ይወርዳል። እንዲህም ይላል 'ማን ነው የሚለምነኝ የምመልስለት? ማን ነው የሚጠይቀኝ ለርሱ የምሰጠው? ማን ነው ምህረትን ከኔ የሚፈልገው ለርሱ የምምረው?'" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

የጠራውና ከፍ ያለው አላህ በሁሉም ሌሊት የሌሊቱ የመጨረሻ ሲሶ ሲቀር ወደ ቅርቢቱ ሰማይ በመውረድ ባሮቹ እንዲለምኑት እንደሚያነሳሳ፤ እርሱ ለለመነው ተቀባይ፤ ለጠየቀው ሰጪ ነውና፤ የሚፈልጉትን እንዲጠይቁት የሚያነሳሳ፤ እርሱ ለአማኝ ባሮቹ መሀሪ ነውና ለወንጀሎቻቸውም ከርሱ ምህረትን እንዲፈልጉ የሚያብረታታቸው መሆኑን ነቢዩ ሶለሏሁ ዓለይሂ ወሰለም ገለፁ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. የሌሊቱ የመጨረሻው ሲሶ ትሩፋቱንና በዚህ ወቅት ሶላት መስገድ ፣ ዱዓእ ማድረግና ምህረትን መፈለግ ያለውን ደረጃ እንረዳለን።
2. አንድ ሰው ይህንን ሐዲሥ በሚሰማበት ጊዜ ዱዓእ ተቀባይነት የሚገኝበት ወቅትን በመሸመት ላይ እጅግ የሚጓጓ ሊሆን ይገባል።

(10412)

(٩٢) - عن النُّعمان بن بَشير رضي الله عنه قال: سَمِعْتُ رَسُولَ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ يَقُولُ - وَأَهْوَى النُّعْمَانُ بِإِصْبَعَيْهِ إِلَى أُذُنَيْهِ-: «إِنَّ الْحَلَالَ بَيِّنٌ وَإِنَّ الْحَرَامَ بَيِّنٌ، وَبَيْنَهُمَا مُشْتَبِهَاتٌ لَا يَعْلَمُهُنَّ كَثِيرٌ مِنَ النَّاسِ، فَمَنِ اتَّقَى الشُّبُهَاتِ اسْتَبْرَأَ لِدِينِهِ وَعِرْضِهِ، وَمَنْ وَقَعَ فِي الشُّبُهَاتِ وَقَعَ فِي الْحَرَامِ، كَالرَّاعِي يَرْعَى حَوْلَ الْحِمَى يُوشِكُ أَنْ يَرْتَعَ فِيهِ، أَلَا وَإِنَّ لِكُلِّ مَلِكٍ حِمًى، أَلَا وَإِنَّ حِمَى اللهِ مَحَارِمُهُ، أَلَا وَإِنَّ فِي الْجَسَدِ مُضْغَةً، إِذَا صَلَحَتْ صَلَحَ الْجَسَدُ كُلُّهُ، وَإِذَا فَسَدَتْ فَسَدَ الْجَسَدُ كُلُّهُ، أَلَا وَهِيَ الْقَلْبُ». [صحيح] - [متفق عليه]

(92) - ከኑዕማን ቢን በሺር -አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: የአላህን መልክተኛ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንዲህ ሲሉ ሰምቻቸዋለሁ: -ኑዕማን (መስማቱን ለማረጋገጥ) በሁለት ጣቶቹ ወደ ጆሮዎቹ እየጠቆመ፡- "ሐላል (የተፈቀደ) ነግር ሁሉ ግልፅ ነው። ሐራሙም (እርም የተደረገ) ነግር ሁሉ ግልፅ ነው። በመካከላቸው አብዛኛው ሰዎች የማያውቃቸው አሻሚ ጉዳዮች አሉ። አሻሚ ጉዳዮችን የተጠነቀቀ ሰው ሃይማኖቱንና ክብሩን ጠብቋል። አሻሚ ጉዳዮች ላይ የወደቀም ሰው ሐራም ላይ ወድቋል። የዚህ ሰው አምሳያ ልክ የተከለከለ ክልል ወሰን ዙሪያ እንደሚጠብቅና እንስሳዎቹም ወሰን አልፈው የሰው እርሻ ሊገቡ እንደቀረቡበት እረኛ ነው። አዋጅ! ለሁሉም ንጉስ ወሰን (ድንበር) አለው። አዋጅ! የአላህ ወሰን (ድንበር) ደግሞ ክልከላው ነው። አዋጅ! ሰውነት ውስጥ የምትገኝ ቁራጭ ስጋ አለች። እሷ ከተስተካከለች ሁሉም ሰውነት ይስተካከላል። እሷ ከተበላሸች ደግሞ ሁሉም ሰውነት ይበላሻል። አዋጅ! እሷም ልብ ናት።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ለነገሮች ሁሉ የሚያገለግል አጠቃላይ መርህን እያብራሩ ነው። ነገሮች ሁሉ በሸሪዐ መሰረት ወደ ሶስት ክፍሎች ይከፈላሉ: ግልፅ ሐላል ፣ ግልፅ ሐራምና ከፍቁድነትና ክልክልነት አንፃር ብዙ ሰው ብይናቸውን የማያውቃቸው ግልፅ ያልሆኑ አሻሚ ጉዳዮች ናቸው።

በሱ ላይ አሻሚ የሆኑበትን ጉዳዮች የተወ ሰው ሀራም ላይ ከመውደቅ በመራቁ ሳቢያ እምነቱ ሰላም ይሆናል፤ ይህን አሻሚ የሆነ ጉዳይ በመፈፀሙ ሳቢያ እሱ ላይ የሚደርስን የሰዎች ትችት ስለማይኖርም ክብሩ ከትችት ሰላም ይሆናል። አሻሚ ጉዳዮችን ያልራቀ ሰው ግን ወይ ሐራም ላይ በመውደቅ ወይ በሰዎች ክብሩ በመዘለፉ ሳቢያ ነፍሱን (ለችግር) ያጋልጣታል። መልክተኛው ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም አሻሚ ጉዳዮች የሚፈፅምን ሰው ሁኔታ ለማብራራት ምሳሌ ጠቀሱ። እሱም ልክ ባለቤቱ በከለላት ስፍራ አስጠግቶ ከብቶቹን እንደሚያሰማራ እረኛ ነው። ቀስ በቀስ የእረኛው ከብቶች ወደተከለለው ስፍራ ቅርብ ስለሆኑ ክልሉ ውስጥ ዘልቀው ሊበሉ ይቀርባሉ። ልክ እንደዚሁ አሻሚ የሆኑ ጉዳዮችን የሚሰራ ሰው በዚህ መዳፈሩ ሳቢያ ወደ ሐራም ይቃረባል። ቀስበቀስ ሐራም ውስጥ ሊወድቅም ይቀርባል። ቀጥለውም ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ሰውነት ውስጥ የምትገኝ ቁራጭ ስጋ እንዳለች ገለፁ። (እሷም ልብ ናት።) በሷ መስተካከል ሰውነት ይስተካከላል በሷ መበላሸትም ሰውነት ይበላሻል።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ብይናቸው ግልፅ ያልሆኑ አሻሚ ጉዳዮችን መተው መበረታታቱ።

(4314)

(٩٣) - عَنْ أَبِي سَعِيدٍ الخُدْرِيِّ رَضِيَ اللهُ عَنْهُ قَالَ: قَالَ النَّبِيُّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ: «لاَ تَسُبُّوا أَصْحَابِي، فَلَوْ أَنَّ أَحَدَكُمْ أَنْفَقَ مِثْلَ أُحُدٍ ذَهَبًا مَا بَلَغَ مُدَّ أَحَدِهِمْ، وَلاَ نَصِيفَهُ».
[صحيح] - [متفق عليه]

(93) - ከአቡ ሰዒድ አልኹድሪይ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) -አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንዲህ አሉ፡- «የአላህ መልክተኛ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ ብለዋል፡- "ባልደረቦቼን አትሳደቡ፤ ከናንተ መካከል አንዱ የኡሑድን ተራራ አምሳያ የሚያህል ቢመፀውት የአንዳቸውንም እፍኝ ሆነ የእፍኙን ግማሽ የመፀወቱት ጋር አይደርስም።"» [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ሶሐቦችን ከመሳደብ ከለከሉ። በተለይ የመጀመሪያ ቀዳሚ የሆኑትን ሙሃጂሮችና አንሷሮችን መሳደብን ከለከሉ። ከሰዎች መካከል አንዱ የኡሑድን ተራራ የሚያህል ወርቅ ቢመፀውት የሚያገኘው ምንዳ አንድ ሶሐባ አንድ እፍኝ እህል -እፍኝ የተባለው መካከለኛ ሰው በሁለት እጆቹ የሚዘግነው መጠን ነው። - ወይም የእፍኙን ግማሽ እህል ቢመፀውት የሚያገኘው ምንዳ ጋር እኩል እንደማይሆን ተናገሩ። ይህም ከፍተኛ ኢኽላስ ስላላቸው፣ መካ ከመከፈቱ በፊት መመፅወት እጅግ አስፈላጊ በሆነበት በዛ ወቅት በመመፅወታቸውና በመዋጋታቸው ስለቀደሙ ነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ሶሐቦችን (ረዲየሏሁ ዐንሁም) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - መሳደብ ክልክልና ከትላልቅ ወንጀሎች መካከል እንደሚመደብ እንረዳለን።

(11000)

(٩٤) - عن ابن عباس رضي الله عنهما قال: كُنْتُ خَلْفَ رَسُولِ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ يَوْمًا، فَقَالَ: «يَا غُلَامُ، إِنِّي أُعَلِّمُكَ كَلِمَاتٍ، احْفَظِ اللهَ يَحْفَظْكَ، احْفَظِ اللهَ تَجِدْهُ تُجَاهَكَ، إِذَا سَأَلْتَ فَاسْأَلِ اللهَ، وَإِذَا اسْتَعَنْتَ فَاسْتَعِنْ بِاللهِ، وَاعْلَمْ أَنَّ الْأُمَّةَ لَوِ اجْتَمَعَتْ عَلَى أَنْ يَنْفَعُوكَ بِشَيْءٍ، لَمْ يَنْفَعُوكَ إِلَّا بِشَيْءٍ قَدْ كَتَبَهُ اللهُ لَكَ، وَلَوِ اجْتَمَعُوا عَلَى أَنْ يَضُرُّوكَ بِشَيْءٍ، لَمْ يَضُرُّوكَ إِلَّا بِشَيْءٍ قَدْ كَتَبَهُ اللهُ عَلَيْكَ، رُفِعَتِ الْأَقْلَامُ وَجَفَّتِ الصُّحُفُ». [صحيح] - [رواه الترمذي]

(94) - ከኢብኑ ዐባስ -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው እንዲህ አለ: አንድ እለት ከአላህ መልክተኛ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ኋላ ሳለሁ እንዲህ አሉኝ "አንተ ልጅ ሆይ! እኔ ቃላቶችን አስተምርሃለሁኝ! አላህን ጠብቅ ይጠብቅሀል፤ አላህን ጠብቅ ፊት ለፊትህ ታገኘዋለህ፤ የጠየቅክ ጊዜ አላህን ጠይቅ! ፤ እገዛን የፈለግክ ጊዜም በአላህ ታገዝ! እወቅ! ህዝብ ባጠቃላይ በአንዳች ነገር ሊጠቅሙህ ቢሰባሰቡ እንኳ አላህ ለአንተ በፃፈልህ ነገር ካልሆነ በስተቀር አይጠቅሙህም። በአንዳች ነገር ሊጎዱህ ቢሰባሰቡም አላህ ለአንተ ፅፎብህ ካልሆነ በስተቀር አይጎዱህም። ብእሮቹም ተነስተዋል ጽሑፉም ደርቋል።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቲርሚዚ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ኢብኑ ዓባስ -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- ህፃን እንደነበሩና ከነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ጋር እየጋለበ ሳለ ለሱ ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንዲህ እንዳሏቸው ይነግሩናል : እኔ አላህ በሷ የሚጠቅምህን ነገሮችንና ጉዳዮችን አሳውቅሀለሁ።

አላህ ትእዛዙንና ወደርሱ መቃረቢያን እየፈፀምክ በሚያገኝህ ሁኔታና ወንጀልና ሀጢዐቶች ውስጥም በማያገኝህ ሁኔታ የአላህን ትእዛዛት በመጠበቅና ክልከላውንም በመራቅ አላህን ጠብቅ! ይህንን ከፈፀምክ ምንዳህ በዓለማዊም በአኺራዊም ጣጣዎች የአላህ ጥበቃና ወደየትም ብትዞር የቸገረህን በመርዳት አላህም የሚጠብቅህ ይሆናል።

አንዳች ነገር መጠየቅ የፈለግክ ጊዜም ከአላህ በስተቀር ማንንም አትጠይቅ! የጠያቂዎችን ልመና የሚቀበለው እሱ ብቻ ነውና።

እገዛን የፈለግክ ጊዜም ከአላህ በስተቀር በማንም አትታገዝ!

የምድር ነዋሪዎች ባጠቃላይ አንተን ለመጥቀም ቢሰባሰቡ እንኳ አላህ ላንተ ከፃፈልህ በስተቀር አንድም ጥቅም እንደማታገኝና የምድር ነዋሪዎች ባጠቃላይ አንተን በመጉዳት ላይ ቢሰባሰቡም አለህ ባንተ ላይ ከወሰነብህ በስተቀር ባንተ ላይ አንድም ጉዳት እንደማይደርሱብህ አንተ ዘንድ እርግጠኝነት ይኑር!

ይህንን ጉዳይ የላቀውና የተከበረው አላህ ጥበቡና እውቀቱ ባስፈረደው መልኩ ፅፏታልም ወስኗታልም። አላህ የፃፈው ነገርም አይለወጥም።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ህፃናትና ትናንሽ ልጆችን እንደ ተውሒድ፣ አዳቦችና ሌሎችንም የዲን ጉዳዮችን የማስተማር አንገብጋቢነት ፤
2. ምንዳ በስራው አይነት እንደሆነ ፤
3. ከሱ ውጪ ያለን ሁሉ በመተው በአላህ ላይ ብቻ መደገፍና በሱ ላይ ብቻ መመካት መታዘዙን ፤ እሱስ ምንኛ ያማረ መመኪያ ነው!
4. በአላህ ውሳኔና ፍርድ ማመንና በፍርዱ መውደድ እንዳለብን ፤ አላህ ሁሉንም ነገር ወስኗልና።
5. የአላህን መመርያ የጣሰ ሰው አላህ ያጠፋዋል እንጂ እንደማይጠብቀው ተምረናል።

(4811)

(٩٥) - عَنْ سُفْيان بنِ عَبْدِ اللهِ الثَّقَفِيِّ رضي الله عنه قال: قُلْتُ: يَا رَسُولَ اللهِ، قُلْ لِي فِي الْإِسْلَامِ قَوْلًا لَا أَسْأَلُ عَنْهُ أَحَدًا غَيْرَكَ، قَالَ: «قُلْ: آمَنْتُ بِاللهِ، ثُمَّ اسْتَقِمْ». [صحيح] - [رواه مسلم وأحمد]

(95) - ከሱፍያን ቢን ዐብደላህ አሥሠቀፊይ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: "የአላህ መልክተኛ ሆይ! በኢስላም ውስጥ ከርሶ ውጪ ስለርሱ አንድንም ሰው የማልጠይቀው የሆነን አንድን ንግግር ንገሩኝ አልኳቸው። እርሳቸውም 'በአላህ አምኛለሁ በል ከዚያም ቀጥ በል።' አሉኝ" [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊምና አሕመድ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ሶሐቢዩ ሱፍያን ቢን ዐብደላህ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - ስለርሱ አንድንም ሳይጠይቅ እርሱን አጥብቆ የሚይዘው የሆነን የኢስላምን ሀሳቦች የጠቀለለ የሆነን ንግግር እንዲያስተምሩት ነቢዩን (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ጠየቀ። ነቢዩም (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ለርሱ "አላህ ብቻውን ጌታዬ፣ አምላኬ፣ ፈጣሪዬ፣ አጋር የሌለው በእውነት የሚመለከው ብቸኛ መሆኑን አረጋግጫለሁ። በል!" አሉት። ከዚያም ለአላህ ትእዛዝ የአላህን ግዴታዎች በመፈፀምና የአላህን ክልከላዎች በመተው ታዛዥ ይሁን፤ በርሱ ላይም ይዘውትር።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. የሃይማኖቱ መሰረት በአላህ ጌትነት፣ ተመላኪነትና በስምና ባህሪያቶቹ ማመን ነው።
2. ከማመን በኋላ ቀጥ የማለትን፣ በአምልኮ ላይ የመዘውተርና በዚህም ላይ የመፅናትን አንገብጋቢነት እንረዳለን።
3. ኢማን ሥራዎች ተቀባይነት እንዲኖራቸው መስፈርት ነው።

4. በአላህ ማመን ሲባል ማመን ግዴታ የሚሆንባቸውን እምነታዊ ጎዳዮችና መሰረቶችን፣ ይህንንም ተከትለው የሚመጡ የቀልብ ተግባራትን፣ በውስጥም ይሁን በውጪ ታዛዥነትንና እጅ መስጠትን ያጠቃልላል።
5. "ኢስቲቃማ" (ቀጥ ማለት) ሲባል ግዴታዎችን በመስራትና ክልክሎችን በመተው ቀጥተኛውን ጎዳና አጥብቆ መያዝ ማለት ነው።

(65018)

(٩٦) - عَنِ النُّعْمَانِ بْنِ بَشِيرٍ رضي الله عنه قَالَ: قَالَ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ: «مَثَلُ الْمُؤْمِنِينَ فِي تَوَادِّهِمْ وَتَرَاحُمِهِمْ وَتَعَاطُفِهِمْ مَثَلُ الْجَسَدِ، إِذَا اشْتَكَى مِنْهُ عُضْوٌ تَدَاعَى لَهُ سَائِرُ الْجَسَدِ بِالسَّهَرِ وَالْحُمَّى». [صحيح] - [متفق عليه]

(96) - ከኑዕማን ቢን በሺር (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: "የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል፡- "የአማኞች እርስ በርስ የመዋደዳቸው፣ የመተዛዘናቸውና የመራራታቸው ምሳሌ እንደ አንድ የሰውነት ክፍል ነው። ከርሱ አንድ አካል የታመመ ጊዜ የተቀረው ሰውነት በእንቅልፍ እጦትና ትኩሳት ይሰቃያል።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ከመውደድ፣ ከማዘን፣ ከመርዳት፣ ከማገዝና እነርሱ ላይ በሚደርስ ጉዳት አብሮ ከመጎዳት አንፃር ሙስሊሞች ከፊሉ ለከፊሉ ሊኖረው የሚገባውን ሁኔታ ልክ እንደ አንድ ሰውነት ምሳሌ ሊሆን እንደሚገባው ግዴታነቱን ገለፁ። አንድ አካል የታመመ ጊዜ የተቀረው አካል በእንቅልፍ እጦትና ትኩሳት አብሮት ይሰቃያል።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. የሙስሊሞችን ሐቅ ማላቅ፤ እነርሱን በማገዝና ከፊሉ ለከፊሉ ማዘን ላይ ማነሳሳት ይገባል።
2. በእምነት ባለቤቶች መካከል መዋደድና መረዳዳት ሊኖር ይገባል።

(4969)

(٩٧) - عن عثمان بن عفان رضي الله عنه قال: قال رسول الله صلى الله عليه وسلم: «مَنْ تَوَضَّأَ فَأَحْسَنَ الْوُضُوءَ خَرَجَتْ خَطَايَاهُ مِنْ جَسَدِهِ حَتَّى تَخْرُجَ مِنْ تَحْتِ أَظْفَارِهِ». [صحيح] - [رواه مسلم]

(97) - ከዑሥማን ቢን ዐፋን -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው እንዲህ አለ: "የአላህ መልዕክተኛ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንዲህ ብለዋል፦ "ውዱእን አሳምሮ ያደረገ ወንጀሎቹ ከጥፍሮቹ ስር ሳይቀር ከሰውነቱ ባጠቃላይ ይወጣሉ።"" [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ውዱእን ሱናዎቹና አዳቦቹን ከመጠባበቅ ጋር ያደረገ ሰው ይህ ውዱኡ ወንጀሎቹ ከእጆቹና እግሮቹ ጣቶች ስር ጭምር እስኪወጡ ድረስ ወንጀሎቹ እንዲማሩና ሀጢአቶቹ እንዲረግፉ ከሚያደርጉ ምክንያቶቹ አንዱ መሆኑን እየነገሩን ነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ውዱእን ሱናዎቹንና አዳቦቹን ተምሮ በመተግበር ላይ ትኩረት እንድናደርግ መነሳሳቱን እንረዳለን።
2. የውዱእን ትሩፋት እንረዳለን። ውዱእ ትናንሽ ወንጀሎችን የሚያስምር ነው። ትላልቅ ወንጀሎች ግን የግድ ተውበት ያስፈልጋቸዋል።
3. ወንጀሎች ከሰውነታችን እንዲወጡ ውዱእን ማሟላቱና ያለምንም ጉድለት ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንደገለፁት መፈፀሙ መስፈርት ነው።

4. እዚህ ሐዲሥ ውስጥ የተጠቀሰው ወንጀሎችን ማስማር ትላልቅ ወንጀሎችን በመራቅና ከርሱ ተውበት በማድረግ ላይ የተገደበ ነው። አላህ እንዲህ ብሏልና {ከእርሱ ከተከላችሁት ታላላቆቹን (ሀጢአቶች) ብትርቁ (ትናንሾቹን) ሀጢአቶቻችሁን ከእናንተ እናብሳለን።} [አንኒሳእ:31]

(6263)

(٩٨) - عَن أَبِي هُرَيْرَةَ رضي الله عنه قَالَ: سَأَلَ رَجُلٌ رَسُولَ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ، فَقَالَ: يَا رَسُولَ اللهِ، إِنَّا نَرْكَبُ البَحْرَ، وَنَحْمِلُ مَعَنَا القَلِيلَ مِنَ الْمَاءِ، فَإِنْ تَوَضَّأْنَا بِهِ عَطِشْنَا، أَفَنَتَوَضَّأُ مِنَ الْبَحْرِ؟ فَقَالَ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ: «هُوَ الطَّهُورُ مَاؤُهُ، الحِلُّ مَيْتَتُهُ».

[صحيح] - [رواه أبو داود والترمذي والنسائي وابن ماجه وأحمد]

(98) - ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው እንዲህ አሉ፦ «አንድ ሰው የአላህን መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና እንዲህ በማለት ጠየቀ "የአላህ መልክተኛ ሆይ! እኛ በባህር እንሳፈራለን፣ ከኛ ጋርም የተወሰነ ውሃ እንሰንቃለን። በዚህ በያዝነው ውሃ ዉዱእ ብናደርግበት እንጠማለንና በባህር ውሃ ዉዱእ እናድርግን?" የአላህ መልክተኛም (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና እንዲህ በማለት መለሱ: "እርሱ ውሃው አፅጂ ነው፤ ውስጡ የሞተም ሐላል ነው።"» [ሶሒሕ ነው።]

## ትንታኔ:

አንድ ሰውዬ ነቢዩን (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና እንዲህ በማለት ጠየቀ "እኛ ለማደን ወይም ለንግድና ለመሳሰሉት በባህር ላይ ጀልባዎችን እንሳፈራለን። ለመጠጥ የሚሆን ትንሽ ውሃንም ከኛ ጋር እንጭናለን። የመጠጡን ውሃ ለዉዱእና ለገላ ትጥበት ከተገለገልን ያልቅብንና የምንጠጣውን አናገኝም። ታዲያ በባህር ውሃ ዉዱእ ማድረግ ለኛ ይፈቀድልናል እንዴ?"

ነቢዩም (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ስለባህሩ ውሃ እንዲህ አሉ "ውሃው ንፁህም አፅጂም ነው። በርሱም ዉዱእ ማድረግ፣ ገላ መታጠብ ይፈቀዳል። ከርሱ የሚወጡን አሳዎችንና ሌሎች የባህር እንስሳዎችንም ሙተው ሳይታደኑ ከላይ ተንጣለው ቢገኙ ራሱ መብላት ይፈቀዳል።"

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. የባህር እንስሳ ቢሞት ሐላል ነው። ውስጡ የሞተ በማለት የሚፈለገው: በባህር ውስጥ ካልሆነ በቀር የማይኖር ሆኖ እዛው ውስጥ የሞተን ነው።
2. የተሟላ ጥቅም እንዲገኝ ጠያቂ ከጠየቀው በበለጠ መመለስ እንደሚገባ እንረዳለን።
3. ውሃ ውስጡ በገባበት ንፁህ ነገር ጣዕሙ ወይም ቀለሙ ወይም ሽታው ቢለወጥ ውሃው በተፈጥሮ ባህሪው ላይ እስከቀረ ድረስ ጨዋማነቱ ወይም ትኩስነቱ ወይም ቀዝቃዛነቱና የመሳሰሉ ነገሮች ቢበረቱ ራሱ አፅጂ እንደሆነ ይቀራል።
4. የባህር ውሃ ትንሹንም ሆነ ትልቁን ሐደሥ ያነሳል። ንፁህ በሆነ ሰውነት ወይም ልብስ ወይም ከዛ ውጪ ላይ ያረፈን ነጃሳ ራሱ ያስወግዳል።

(8355)

(٩٩) - عَن عَبْدِ اللهِ بْنِ عُمَرَ رضي الله عنهما قَالَ: سُئِلَ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ عَنِ الْمَاءِ وَمَا يَنُوبُهُ مِنَ الدَّوَابِّ وَالسِّبَاعِ، فَقَالَ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ: «إِذَا كَانَ الْمَاءُ قُلَّتَيْنِ لَمْ يَحْمِلِ الْخَبَثَ».
[صحيح] - [رواه أبو داود والترمذي والنسائي وابن ماجه وأحمد]

(99) - ከዐብደላህ ቢን ዑመር (ረዲየሏሁ ዐንሁማ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: «የአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና እንስሶችና አውሬዎች ተመላልሰው ስለሚጠጡት ውሃ ተጠየቁ። ነቢዩም (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና እንዲህ አሉ: "ውሃው ሁለት 'ቁለተይን' ከደረሰ ነጃሳን አይሸከምም።"» [ሶሒሕ ነው።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና እንስሳዎችና አውሬዎች ለመጠጣትና ለመሳሰሉት ስለሚመላለሱበት ውሃ ንፁህነት ብይን ተጠየቁ። ነቢዩም (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ውሃ መጠኑ ሁለት ትላልቅ እንስራዎችን የደረሰ ጊዜ - 210 ሊትር የሚሆን ብዛት ማለት ነው። - ብዙ ውሃ ስለሆነ ከሶስቱ ባህሪያቶቹ አንዱ በነጀሳ እስካልተለወጠ ድረስ እነርሱም ቀለሙ ወይም ጣዕሙ ወይም ሽታው እስካልተለወጠ ድረስ አይነጀስም አሉ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ውሃ ከሶስቱ ባህሪያቶቹ አንዱ በነጃሳ የተለወጠ ጊዜ ማለትም ቀለሙ ወይም ጣዕሙ ወይም ሽታው የተለወጠ ጊዜ ይነጀሳል። ሐዲሡ በአብዛኛው ጊዜ ከሚከሰተው በመንተራስ ነው የተነገረው እንጂ በመገደብ ደረጃ አይደለም።
2. ውሃ በነጃሳ የተለወጠ ጊዜ ውሃው አነሰም በዛ እንደሚነጀስ ዑለማዎች ባጠቃላይ ተስማምተዋል።

(8357)

(١٠٠) - عَنْ أَبِي أَيُّوبَ الأَنْصَارِيِّ رضي الله عنه أَنَّ النَّبِيَّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ قَالَ: «إِذَا أَتَيْتُمُ الغَائِطَ فَلاَ تَسْتَقْبِلُوا القِبْلَةَ، وَلاَ تَسْتَدْبِرُوهَا وَلَكِنْ شَرِّقُوا أَوْ غَرِّبُوا» قَالَ أَبُو أَيُّوبَ: فَقَدِمْنَا الشَّأْمَ فَوَجَدْنَا مَرَاحِيضَ بُنِيَتْ قِبَلَ القِبْلَةِ فَنَنْحَرِفُ، وَنَسْتَغْفِرُ اللَّهَ تَعَالَى. [صحيح] - [متفق عليه]

(100) - ከአቡ አዩብ አልአንሷሪይ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል: "መፀዳጃ ቦታ የመጣችሁ ጊዜ ወደ ቂብላ አትዙሩም ጀርባ አትስጡም! ነገር ግን ወደ ምስራቅ ወይም ምዕራብ ዙሩ" አቡ አዩብ እንዲህ አለ "ሻም ስንገባ ወደ ቂብላ አቅጣጫ የተገነባ መፀዳጃ ቤት አገኘን። ትንሽ ዘንበል እያልን እየተፀዳዳን አላህንም ምህረት እንጠይቀዋለን።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ለሽንትም ይሁን ለሰገራ መፀዳዳት የፈለገ ሰው ወደ ካዕባ አቅጣጫ ዞሮም ይሁን ለካዕባ ጀርባን ሰጥቶ መፀዳዳቱን ከለከሉ። ቂብላው እንደ መዲና ነዋሪዎች ከሆነ ማድረግ ያለበት ወደ ምስራቅ ወይም ምዕራብ አቅጣጫ ዘንበል ማለት ነው። ቀጥሎ አቡ አዩብ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- ወደ ሻም የገቡ ጊዜ ወደ ካዕባ አቅጣጫ የተገነባ ለመፀዳጃነት የተዘጋጀ መፀዳጃ ቤት እንዳገኙ፤ በአካላቸውም ከቂብላ ዘንበል እንደሚሉና ከዚህም ጋር ግን አላህን ምህረት እንደሚጠይቁ ተናገረ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. በዚህ ድንጋጌ የተፈለገው ጥበብ የላቀውን ካዕባ ማላቅና ማክበር ነው።
2. ከመፀዳጃ ስፍራ ከወጣን በኋላ ኢስቲግፋር ማድረግ እንደሚገባ እንረዳለን።

3. የነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) የማስተማር ዘዴ ማማሩን እንረዳለን። ይህም ክልክሉን ከጠቀሱ በኋላ የሚፈቀደውን በመጠቆማቸው ነው።

(3078)

(١٠١) - عَنْ أَبِي قَتَادَةَ رضي الله عنه قَالَ: قَالَ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ: «لَا يُمْسِكَنَّ أَحَدُكُمْ ذَكَرَهُ بِيَمِينِهِ وَهُوَ يَبُولُ، وَلَا يَتَمَسَّحْ مِنَ الْخَلَاءِ بِيَمِينِهِ، وَلَا يَتَنَفَّسْ فِي الْإِنَاءِ».

[صحيح] - [متفق عليه]

(101) - ከአቡ ቀታዳ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል: "አንዳችሁ እየሸና ሳለ ብልቱን በቀኝ እጁ አይያዘው፤ ሲፀዳዳም በቀኝ እጁ አይጥረግ፤ በእቃ ውስጥም አይተንፍስ!" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) አንዳንድ ስርዓቶችን አብራሩ። ወንድ ልጅ በሚሸናበት ወቅት ብልቱን በቀኝ እጁ መያዙን ከለከሉ፤ ከፊት ለፊት ብልትም ይሁን ከኋላ ብልት የሚወጣን ነጃሳ በቀኝ እጅ ማስወገዱንም ከለከሉ፤ ምክንያቱም ቀኝ እጅ የተዘጋጀችው የተከበሩ ድርጊቶችን ለመፈፀም ነውና። ልክ እንደዚሁ አንድ ሰው የሚጠጣበት እቃ ውስጥ መተንፈሱንም ከልክለዋል።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. በስነ-ስርዓት እና በንፅህና እስልምና ቀዳሚ መሆኑን መገለፁ።
2. ቆሻሻ ነገሮችን መራቅ እንደሚገባና የግድ መንካት ካለበትም በግራ መሆን እንዳለበት እንረዳለን።
3. የቀኝ እጅ ደረጃና ከግራ እጅ በላጭ መሆኑን መገለፁ።

4. እስላማዊ ድንጋጌ ምሉዕና አስተምህሮቶቹ ሁሉን አቀፍ መሆናቸውን እንረዳለን።

(3079)

(١٠٢) - عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ رضي الله عنه أَنَّ النَّبِيَّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ قَالَ: «إِذَا اسْتَيْقَظَ أَحَدُكُمْ مِنْ مَنَامِهِ فَلْيَسْتَنْثِرْ ثَلَاثَ مَرَّاتٍ، فَإِنَّ الشَّيْطَانَ يَبِيتُ عَلَى خَيَاشِيمِهِ». [صحيح] - [متفق عليه]

(102) - ከአቡ ሁረይራ (ረዲየላሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው : ነቢዩ (ሶለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና እንዲህ ብለዋል: "አንዳችሁ ከእንቅልፉ የነቃ ጊዜ ሶስት ጊዜ አፍንጫው ውስጥ ውሃ እየከተተ ያውጣ፤ ሸይጧን በአፍንጫው ውስጥ ያድራልና።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ከእንቅልፉ የነቃ ሰው ሶስት ጊዜ አፍንጫው ውስጥ ውሃ እየከተተ እንዲያወጣ አነሳሱ። ይህም ሸይጧን በአፍንጫ ውስጥ ስለሚያድር ነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ከእንቅልፉ ለነቃ ሰው ሁሉ ከአፍንጫው የሸይጧንን ፋና ለማስወገድ አፍንጫው ውስጥ ውሃ እየከተተ ማውጣት እንደተደነገገ እንረዳለን። ዉዱእ የሚያደርግ ከሆነ ደግሞ በዚህ ጊዜ አፍንጫው ውስጥ ውሃ እየከተተ በማውጣት መታዘዙ ይበልጥ አፅንዖት የተሰጠው ጉዳይ ይሆናል።
2. ከአፍንጫ ውሃ ማስወጣቱ አሟልቶ ወደ አፍንጫ ውሃ ከማስገባት የሚመደብ ነው። ወደ አፍንጫ ውስጥ ውሃ ማስገባት የአፍንጫን ውስጥ ማፅዳት ነው። ማስወጣቱ ደግሞ ከውሃው ጋር ቆሻሻውን እንዲወጣ ማድረግ ነውና።

3. ሐዲሡ ውስጥ "ያድራልና" የሚለው ቃል ይህ ድርጊት በምሽት እንቅልፍ መገደቡን ያስረዳናል። ማደር ከምሽት እንቅልፍ ውጪ አይሆንምና። ይህም የምሽት እንቅልፍ መርዘምና ጥልቅ እንቅልፍ የሚጠረጠርበት ቦታ ስለሆነ ነው።
4. እዚህ ሐዲሥ ውስጥ ሸይጧን የሰው ልጅ በማያውቀው መልኩ ከርሱ ጋር አብሮ እንደሚቆራኝ ይጠቁማል።

(8377)

(١٠٣) - عَنْ أَنَسٍ رضي الله عنه قَالَ: كَانَ النَّبِيُّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ يَغْسِلُ، أَوْ كَانَ يَغْتَسِلُ، بِالصَّاعِ إِلَى خَمْسَةِ أَمْدَادٍ، وَيَتَوَضَّأُ بِالْمُدِّ. [صحيح] - [متفق عليه]

(103) - ከአነስ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) -አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው እንዲህ ብለዋል፦ "ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ገላቸውን ከአንድ ቁና ውሃ እስከ አምስት እፍኝ ድረስ ባለ ውሃ ያጥቡ ወይም ይታጠቡ ነበር። በአንድ እፍኝ ደግሞ ዉዱእ ያደርጉ ነበር።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ከአንድ ቁና እስከ አምስት እፍኝ በሚደርስ ውሃ ከጀናባ ይታጠቡ ነበር። በአንድ እፍኝ ደግሞ ዉዱእ ያደርጉ ነበር። ቁና ማለት አራት እፍኝ ውሃ ማለት ሲሆን እፍኝ ማለት ደግሞ መካከለኛ ተፈጥሮ ያለው ሰው በሁለቱ መዳፎቹ ሙሉ የሚያክል ነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. የዉዱእና የትጥበት ውሃ ላይ ቆጣቢ መሆንና ውሃው ትንሽ ቢሆን እንኳ አለማባከን እንደሚገባ እንረዳለን።

2. የነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና መመሪያ ስለሆነ እንደአስፈላጊነቱ የዉዱእና የትጥበት ውሃን ማሳነስ እንደሚወደድ እንረዳለን።
3. ከዉዱእና ትጥበት የሚፈለገው ሳይሰስቱና ሳያባክኑ አዳቡና ሱናውን ከመጠበቅ ጋር አሟልቶ መፈፀም ነው። ወቅቱን፣ የውሃውን ብዛትና ማነስ የመሳሰሉትን ግምት ውስጥ አስገብቶ ማድረግ ነው።
4. ጀናባ የሚለው ስም የዘር ፈሳሽ ያፈሰሰ ወይም ግንኙነት የፈፀመ ሁሉ የሚገለፅበት ስም ነው። በዚህም የተሰየመው እስኪፀዳ ድረስ ግለሰቡ ከሶላትና ከአምልኮ ስለሚርቅ ነው።
5. ቁና: የታወቀ መለኪያ ነው። የተፈለገውም ነቢያዊው ቁና ነው። የሚመዝነውም ጥሩ በሆነ የስንዴ ዘር (480) ግራም የሚመዝን ነው። በሊትር ደግሞ (3 ሊትር) የሚይዝ ነው።
6. እፍኝ: አንዱ ሸሪዓዊ መስፈሪያ ነው። እርሱም መካከለኛ የሆነ ሰው መዳፍ እጁን ዘርግቶ በሁለት እጁ የሚዘግነውን ያህል ማለት ነው። አንድ እፍኝ በፉቀሃዎች ባጠቃላይ ስምምነት የአንድ ቁና ሩብ ነው። መጠኑም (750) ሚ.ሊ ይመዝናል።

(8387)

(١٠٤) - عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ رضي الله عنه عَنِ النَّبِيِّ صلى الله عليه وسلم قَالَ: «لَا يَقْبَلُ اللهُ صَلَاةَ أَحَدِكُمْ إِذَا أَحْدَثَ حَتَّى يَتَوَضَّأَ». [صحيح] - [متفق عليه]

(104) - ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል: "አንዳችሁ ዉዱእ በሌለው ጊዜ ዉዱእ እስኪያደርግ ድረስ አላህ ሶላቱን አይቀበለውም።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ለሶላት ትክክለኛነት ከሚያስፈልጉ መስፈርቶች መካከል ጠሀራ አንዱ መሆኑን ገለፁ። ስለሆነም ሶላት መስገድ በፈለገ ሰው ላይ እንደሰገራ ወይም ሽንት ወይም እንቅልፍና መሰል ሌላ ዉዱእ ከሚያፈርሱ ነገሮች መካከል አንድም አፍራሽ ነገር ከተከሰተ ዉዱእ ማድረግ ግዴታው ነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ዉዱእ የሌለው ሰው ከትልቁ ሐደሥ በትጥበት፤ ከትንሹ ሐደሥ ደግሞ በዉዱእ እስኪፀዳ ድረስ ሶላቱ ተቀባይነት አይኖረውም።
2. ዉዱእ ማለት ውሀን አፍ ውስጥ በመያዝ አመላልሶ በመትፋት ከዚያም ውሀን ወደ አፍንጫ ውስጥ መሳብ ከዚያም ማውጣት፤ ቀጥሎ ፊቱን ሶስት ጊዜ ማጠብ፤ ቀጥሎ ሁለት እጆችን ክርንን ጨምሮ ሶስት ጊዜ ማጠብ፤ ቀጥሎ ጭንቅላትን ባጠቃላይ አንድ ጊዜ ማበስ፤ ቀጥሎ ሁለት እግሮችን ከቁርጭምጭሚቱ ጋር ሶስት ጊዜ ማጠብ ነው።

(3534)

(١٠٥) - عَنْ جَابِرٍ رضي الله عنه قال: أَخْبَرَنِي عُمَرُ بْنُ الْخَطَّابِ: أَنَّ رَجُلًا تَوَضَّأَ فَتَرَكَ مَوْضِعَ ظُفُرٍ عَلَى قَدَمِهِ فَأَبْصَرَهُ النَّبِيُّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ فَقَالَ: «ارْجِعْ فَأَحْسِنْ وُضُوءَكَ» فَرَجَعَ، ثُمَّ صَلَّى.
[صحيح بشواهده] - [رواه مسلم]

(105) - ከጃቢር (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና እንደተላለፈው: እንዲህ አለ: "ዑመር ቢን አልኸጧብ እንዲህ ብሎ ነገረኝ: 'አንድ ሰውዬ ውዱእ አደረገና እግሩ ላይ ጥፍር የምታክል ስፍራ ተወ። ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ተመለከቱትና እንዲህ አሉት: ‹ተመለስና ዉዱእህን አሳምር!› ተመልሶ (አስተካከለና) ከዚያም ሰገደ።'" [በማመሳከሪያዎቹ ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ዑመር (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) አንድ ዉዱእ አድርጎ የጨረሰን ሰውዬ እግሩ ላይ ጥፍር የምታክል የዉዱእ ውሃ ያልነካት ስፍራን እንደተመለከቱበት ተናገሩ። ነቢዩም (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ወደ ተወው ስፍራ እየጠቆሙ እንዲህ አሉት: ተመለስና ዉዱእህን አሳምር! አሟልተህ አድርግ! ለሁሉም አካልህ ከውዱኡ ውሃ የሚገባውን ሐቅ ስጠው አሉት! ሰውዬውም ተመለሰና ዉዱኡን አሟልቶ ሰገደ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. በመልካም ለማዘዝ መፍጠን፣ መሃይማንንና ዝንጉዎችን ማንቃት በተለይ የሚሰራው ውግዝ ስራን ተከትሎ አምልኮ የሚበላሽበት ከሆነ ግዴታ መሆኑን እንረዳለን።
2. የዉዱእ አካላትን በውሃ ማዳረስ ግዴታ ነው። ከውዱእ አካላት ትንሽ እንኳ ብትሆን የተወሰነን የተወ ሰው ዉዱኡ ትክክል አይደለም። ዉዱእ ያደረገበት ወቅት ከረዘመ ደግሞ መድገም ግዴታው መሆኑን እንረዳለን።

3. ዉዱኡን ማሳመር የተደነገገ መሆኑን እንረዳለን። ይህም አሟልቶ በማድረግና በሸሪዓ በታዘዘው መልኩ በማዳረስ ነው።
4. ሁለት እግሮች ከዉዱእ አካላት መሆናቸውን እንረዳለን። እነርሱን ማበስም በቂ አይደለም። የግድ መታጠብ አለባቸው።
5. ሁሉንም የዉዱእ አካል ከበስተፊቱ ያለው ከመድረቁ በፊት በሚያጥብበት ልክ በዉዱእ አካላት መካከል ማከታተል ይገባል።
6. አለማወቅና መርሳት ወንጀለኝነትን እንጂ ግዴታን አያነሱም። ዉዱኡን ያላዳረሰው ይህን ሰውዬ ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ባለማወቁ ምክንያት እንዲደግመው አዘዙት እንጂ ውዱእ የማድረግ ግዴታውን አላነሱለትም።

(8386)

(١٠٦) - عَنْ عَبْدِ اللهِ بْنِ عَمْرٍو رَضِيَ اللهُ عنهما قَالَ: رَجَعْنَا مَعَ رَسُولِ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ مِنْ مَكَّةَ إِلَى الْمَدِينَةِ حَتَّى إِذَا كُنَّا بِمَاءٍ بِالطَّرِيقِ تَعَجَّلَ قَوْمٌ عِنْدَ الْعَصْرِ، فَتَوَضَّؤُوا وَهُمْ عِجَالٌ، فَانْتَهَيْنَا إِلَيْهِمْ وَأَعْقَابُهُمْ تَلُوحُ لَمْ يَمَسَّهَا الْمَاءُ فَقَالَ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ: «وَيْلٌ لِلْأَعْقَابِ مِنَ النَّارِ أَسْبِغُوا الْوُضُوءَ». [صحيح] - [متفق عليه]

(106) - ከዐብደላህ ቢን ዐምር (ረዲየሏሁ ዐንሁማ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: «ከአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ጋር ከመካ ወደ መዲና ተመለስን። ውሃ የሚገኝበት መንገድ ላይ የደረስን ጊዜ ሰዎች ዐስርን በወቅቱ ለመስገድ በመቻኮል ፈጥነው ዉዱእ አደረጉ። ወደነርሱም ተረከዞቻቸው ውሃ ያልነካው ግልፅ ሆኖ ደረስንባቸው። በዚህ ወቅትም የአላህ መልክተኛም (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ አሉ " ተረከዞቻችሁን ከእሳት አድኑ! ዉዱእን አዳርሳችሁ አድርጉ!"» [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ባልደረቦቻቸው ጋር ሆነው ከመካ ወደ መዲና እየተጓዙ ሳለ መንገዳቸው ላይ ውሃ አገኙ። ከፊል ሶሐቦችም ዐስርን ለመስገድ ዉዱእ በማድረግ ተቻኮሉ። ከመቻኮላቸውም የተነሳ ተረከዞቻቸው ደረቅ እንደሆነና ውሃ እንዳልነካው ለተመልካችም በግልፅ ያስታውቅ ነበር። ነቢዩም (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ዉዱእ በሚያደርጉ ወቅት የእግራቸውን ተረከዝ ከመታጠብ ቸላ ለሚሉ ሰዎች የእሳት ውስጥ ቅጣትና ጥፋት እንዳለባቸው ተናገሩ። ዉዱእን አሟልቶ በመፈፀም ላይ ከፍተኛ ጥረት እንዲያደርጉም አዘዟቸው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. በዉዱእ ወቅት ሁለት እግሮችን መታጠብ ግዴታ መሆኑን እንረዳለን። (ከመታጠብ ይልቅ) ማበሱ ብቻ ቢፈቀድ ኖሮ ተረከዙን ማጠብ የተወን ሰው በእሳት አይዝቱበትም ነበርና።
2. የሚታጠቡ አካላቶችን በትጥበት ማዳረስ ግዴታ መሆኑን እንረዳለን። ማጠብ ግዴታ ከሆነበት አካል ሆነ ብሎም ይሁን ተዘናግቶ ትንሽ አካል ብትሆን እንኳ የተወ ሰው ሶላቱ ትክክለኛ አይሆንም።
3. አላዋቂን ማስተማርና ማረም አንገብጋቢ መሆኑን እንረዳለን።
4. ዐሊም (አዋቂ) የሆነ ሰው ግዴታዎችንም ይሁን ሱናዎችን ትተው ሲያይ ተገቢ በሆነ መልኩ ያወግዛል።
5. ሙሐመድ ኢስሐቅ አድደህለዊ እንዲህ ብለዋል: ዉዱእን ማዳረስ ሶስት አይነት ነው። ግዴታ: ይህ የዉዱእን ቦታ አንድ ጊዜ ማዳረስ ነው። ሱና: ይህም ሶስት ጊዜ ማጠቡ ነው። ተወዳጅ: ይህም ሶስት ሶስት ጊዜ ከማጠብም ጋር ቦታዎቹን እያረዘመ መታጠብ ነው።

(66392)

(١٠٧) - عن عَمْرُو بْنُ عَامِرٍ عَنْ أَنَس بن مالك قَالَ: كَانَ النَّبِيُّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ يَتَوَضَّأُ عِنْدَ كُلِّ صَلَاةٍ، قُلْتُ: كَيْفَ كُنْتُمْ تَصْنَعُونَ؟ قَالَ: يُجْزِئُ أَحَدَنَا الْوُضُوءُ مَا لَمْ يُحْدِثْ.
[صحيح] - [رواه البخاري]

(107) - ዐምር ቢን ዓሚር ከአነስ ቢን ማሊክ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንዳስተላለፈው እንዲህ አሉ፦ "ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) በሁሉም ሶላት ወቅት ዉዱእ ያደርጉ ነበር። 'እናንተስ እንዴት ነበር የምታደርጉት?' አልኩኝ። አነስም 'ዉዱእ እስካላጠፋን ድረስ (የነበረን) ዉዱእ ይበቃን ነበር።' አለ።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ዉዱእ ባያጠፉ ራሱ ለሁሉም ግዴታ ሶላቶች ዉዱእ ያደርጉ ነበር። ይህም ተጨማሪ ምንዳና ትሩፋትን ለማግኘት ነው።

ዉዱእ እስካለው ድረስ በአንድ ዉዱእ ከአንድ ግዴታ ሶላት በላይ መስገድም ይፈቀድለታል።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) አብዝተው ይሰሩት የነበረው የበለጠ ሙሉ የሆነውን በመፈለግ ለሁሉም ሶላት ዉዱእ ማድረግ ነው።
2. ለሁሉም ሶላት ዉዱእ ማድረግ እንደሚወደድ እንረዳለን።
3. በአንድ ዉዱእ ከአንድ ሶላት በላይ መስገድ እንደሚፈቀድ እንረዳለን።

(65080)

(١٠٨) - عَنِ ابْنِ عَبَّاسٍ رضي الله عنهما قَالَ: تَوَضَّأَ النَّبِيُّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ مَرَّةً مَرَّةً.
[صحيح] - [رواه البخاري]

(108) - ከኢብኑ ዓባስ (ረዲየሏሁ ዐንሁማ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: "ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) አንድ አንድ ጊዜ ዉዱእ አደርገዋል።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) በአንድ አንድ ወቅቶች ዉዱእ ያደረጉ ጊዜ ሁሉንም የዉዱእ አካላቶቻቸው አንድ አንድ ጊዜ ብቻ ያጥቡ ነበር። ፊታቸውን - መጉመጥመጥና ውሀውን ወደ አፍንጫ ውስጥ ስቦ መልሶ ማውጣትን ጨምሮ- ፣ ሁለት እጃቸውንና ሁለት እግራቸውን አንድ አንድ ጊዜ ያጥቡ ነበር። ይህም ዝቅተኛው የግዴታ መጠን ነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. አካላቶቻችንን ስናጥብ ግዴታ ያለብን አንድ ጊዜ ብቻ ነው። ከዚህ በላይ መጨመር ተወዳጅ ነው።
2. በአንድ አንድ ወቅቶች ላይ አንድ አንድ ጊዜ ብቻ ዉዱእ ማድረግ የተደነገገ መሆኑን እንረዳለን።
3. ጭንቅላትን በማበስ ዙሪያ የተደነገገው አንድ ጊዜ ብቻ ማበስ ነው።

(65081)

(١٠٩) - عَنْ عَبْدِ اللهِ بْنِ زَيْدٍ رضي الله عنه: أَنَّ النَّبِيَّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ تَوَضَّأَ مَرَّتَيْنِ مَرَّتَيْنِ.
[صحيح] - [رواه البخاري]

(109) - ከዐብደላህ ቢን ዘይድ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: "ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ሁለት ሁለት ጊዜ ዉዱእ አድርገዋል።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) አንድ አንድ ወቅት ላይ ዉዱእ ያደረጉ ጊዜ ሁሉንም የዉዱእ አካላቶቻቸው ሁለት ሁለት ጊዜ ያጥቡ ነበር። ፊታቸውን - መጉመጥመጥና ውሀውን ወደ አፍንጫ ውስጥ ስበ መልሶ ማውጣትን ጨምሮ- ፣ ሁለት እጃቸውንና ሁለት እግራቸውን ሁለት ሁለት ጊዜ ያጥቡ ነበር።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. አካላቶቻችንን ስናጥብ ግዴታ ያለብን አንድ ጊዜ ብቻ ነው። ከዚህ በላይ መጨመር ተወዳጅ ነው።
2. አንድ አንድ ወቅት ላይ ሁለት ሁለት ጊዜ ዉዱእ ማድረግ የተደነገገ መሆኑን እንረዳለን።
3. ጭንቅላትን በማበስ ዙሪያ የተደነገገው አንድ ጊዜ ብቻ ማበስ ነው።

(65082)

(١١٠) - عَنْ حُمْرَانَ مَوْلَى عُثْمَانَ بْنِ عَفَّانَ أَنَّهُ رَأَى عُثْمَانَ بْنَ عَفَّانَ دَعَا بِوَضُوءٍ، فَأَفْرَغَ عَلَى يَدَيْهِ مِنْ إِنَائِهِ، فَغَسَلَهُمَا ثَلَاثَ مَرَّاتٍ، ثُمَّ أَدْخَلَ يَمِينَهُ فِي الْوَضُوءِ، ثُمَّ تَمَضْمَضَ وَاسْتَنْشَقَ وَاسْتَنْثَرَ، ثُمَّ غَسَلَ وَجْهَهُ ثَلَاثًا، وَيَدَيْهِ إِلَى الْمِرْفَقَيْنِ ثَلَاثًا، ثُمَّ مَسَحَ بِرَأْسِهِ، ثُمَّ غَسَلَ كُلَّ رِجْلٍ ثَلَاثًا، ثُمَّ قَالَ: رَأَيْتُ النَّبِيَّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ يَتَوَضَّأُ نَحْوَ وُضُوئِي هَذَا، وَقَالَ: «مَنْ تَوَضَّأَ نَحْوَ وُضُوئِي هَذَا ثُمَّ صَلَّى رَكْعَتَيْنِ لَا يُحَدِّثُ فِيهِمَا نَفْسَهُ غَفَرَ اللهُ لَهُ مَا تَقَدَّمَ مِنْ ذَنْبِهِ». [صحيح] - [متفق عليه]

(110) - በዑሥማን ነፃ የወጣ የሆነው ሑምራን እንዳስተላለፈው እሱ "ዑሥማንን የውዱእ እቃ እንዲያመጡላቸው ሲጣሩ አየ። (የውዱእ እቃ ሲቀርብላቸውም) ከእቃው ውሀ በእጆቻቸው ላይ አፈሰሱ። እያፈሰሱም ሶስት ጊዜ አጠቧቸውቸው። ከዚያም ቀኝ እጃቸውን በውዱእ እቃ ውስጥ አስገብተው ውሀ ዘገኑና በዚያው ተጉመጠመጡ አፍንጫቸው ውስጥም ውሀውን አስገብተው ድጋሚ አስወጡ። ከዚያም ፊታቸውን ሶስት ጊዜ፣ ሁለት እጆቻቸውንም እስከ ክርኖቻቸው ሶስት ጊዜ አጠቡ። ከዚያም ጭንቅላታቸውን አበሱ። ከዚያም ሁለት እግሮቻቸውን ሶስት ጊዜ አጠቡ። ከዚያም እንዲህ አሉ 'ነቢዩን ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም በዚህ መልኩ ውዱእ ሲያደርጉ ተመልክቻቸዋለሁ። ከዚያም 'እኔ እንዳደረጉት አይነት ዉዱእ አድርጎ ከዚያም ነፍሱን ምንም በሃሳብ ሳያደፈርስ ሁለት ረከዐ የሰገደ ሰው ያሳለፈው ወንጀሉ ተምሮለታል።' አሉ።'" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ዑሥማን (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - የነቢዩን (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ዉዱእ አደራረግ እጅግ በጣም የተብራራ እንዲሆን ተግባራዊ በሆነ መንገድ አስተማሩ። በውዱእ እቃ ውሀ እንዲያመጡላቸው ጠየቁ። ቀጥሎም በእጆቻቸው ላይ ሶስት ጊዜ አፈሰሱ። ከዚያም ቀኝ እጃቸውን እቃ ውስጥ ከተው ውሀ በማውጣት ውሀውን አፋቸው ውስጥ ከተው ካመላለሱ በኋላ ተፉት። ቀጥሎም ውሀውን ወደ አፍንጫቸው ውስጥ ከሳቡ በኋላ መልሰው አወጡት። ከዚያም ፊታቸውን

ሶስት ጊዜ አጠቡ። ከዚያም እጃቸውን ከክርናቸው ጋር ሶስት ጊዜ አጠቡ። ከዚያም እጃቸውን አርጥበው ጭንቅላታቸው ላይ አንድ ጊዜ አበሱ። ከዚያም ሁለት እግሮቻቸውን ከቁርጭምጭሚታቸው ጋር ሶስት ጊዜ አጠቡ።

ዑሥማን (ረዲየላሁ ዐንሁ) -አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና- ዉዱአቸውን ባጠናቀቁ ጊዜ ነቢዩን (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) በዚህ መልኩ ዉዱእ ሲያደርጉ እንደተመለከቱና በዚህ መልኩ ዉዱእ አድርጎ ልቡንም ጌታው ዘንድ ጥዶ በተመስጦ ሁለት ረከዐ የሰገደ ሰው አላህ በዚህ የተሟላ ዉዱእና የጠራ ሶላት ምክንያት ያለፈውን ወንጀሉ በመማር እንደሚመነዳው እንዳበሰሯቸው ነገሯቸው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ከእንቅልፍ ተነስቶ እንኳ ባይሆን ዉዱእን ሲጀምር እጁን እቃ ውስጥ ከመክተቱ በፊት ሁለት እጆቹን መታጠቡ እንደሚወደድለት እንረዳለን። ከሌሊት እንቅልፍ ነቅቶ ከሆነ ግን እጆቹን ማጠቡ ግዴታ ነው።
2. አንድ አስተማሪ ተማሪዎቹ ዕውቀቱን የሚገነዘቡበትንና የሚሰርፅበትን ቀላል መንገድ መጠቀም ይገባዋል። ከዚህም መካከል በተግባር ማስተማር ነው።
3. አንድ ሰጋጅ ከዱንያ ጉዳዮች ጋር የተያያዙ አዘናጊ ውልታዎችን ማስወገድ ይገባዋል። የተሟላ ሶላት ልብን ሶላቱ ውስጥ በመጣድ ነው የሚገኘው። ያለበለዚያ ከማሰብ ሙሉ ለሙሉ መፅዳት አስቸጋሪ ነው። እሱም ነፍሱን መታገልና ሀሳቡን ሶላቱ ላይ መገደብ ይገባዋል።
4. ዉዱእ ላይ ቀኝን ማስቀደም እንደሚወደድ፤
5. በመጉመጥመጥና አፍንጫ ውስጥ ውሀ አስገብቶ በማስወጣት መካከል ቅደም ተከተሉን መጠበቅ የተደነገገ መሆኑን ፤
6. ፊትን፣ ሁለት እጅንና ሁለት እግርን ሶስት ሶስት ጊዜ መታጠብ እንደሚወደድ እንረዳለን። ግዴታው ግን አንድ ጊዜ ነው።

7. ላሳለፍነው ወንጀል የአላህን ምህረት ለማግኘት ሁለት ነገሮች መሰባሰባቸውን ተከትሎ ነው የሚገኘው፤ እነሱም ዉዱእ እና ሐዲሡ ላይ በተጠቀሰው መልኩ ሁለት ረከዓ መስገድ ናቸው።
8. ሁሉም የዉዱእ አካላቶች ክልል አላቸው። የፊት ክልል: በርዝመት ከተለመደው የራስ ፀጉር መብቀያ እስከ ፂም መውረጃና አገጬ ድረስ በጎን ደግሞ ከጆሮ እስከ ጆሮ ነው። የእጅ ክልል ደግሞ: ከጣቶች ጫፍ እስከ ክርን ነው። የጭንቅላት ክልሉ ደግሞ ከተለመደው ፀጉር መብቀያና የፊት ጎኖች እስከ ላይኛው ማጅራት ነው። ሁለት ጆሮዎችን ማበስ ጭንቅላትን ማበስ ውስጥ የሚካተት ነው። የእግር ክልሉ ደግሞ: ሙሉ ተረከዝን በእግሩና በባቱ መካከል ከሚለየው አጥንት ጋር ማጠብ ነው።

(3313)

(١١١) - عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ رضي الله عنه أَنَّ رَسُولَ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ قَالَ: «إِذَا تَوَضَّأَ أَحَدُكُمْ فَلْيَجْعَلْ فِي أَنْفِهِ ثُمَّ لِيَنْثُرْ، وَمَنِ اسْتَجْمَرَ فَلْيُوتِرْ، وَإِذَا اسْتَيْقَظَ أَحَدُكُمْ مِنْ نَوْمِهِ فَلْيَغْسِلْ يَدَهُ قَبْلَ أَنْ يُدْخِلَهَا فِي وَضُوئِهِ، فَإِنَّ أَحَدَكُمْ لاَ يَدْرِي أَيْنَ بَاتَتْ يَدُهُ».
ولفظ مسلم: «إِذَا اسْتَيْقَظَ أَحَدُكُمْ مِنْ نَوْمِهِ فَلَا يَغْمِسْ يَدَهُ فِي الْإِنَاءِ حَتَّى يَغْسِلَهَا ثَلَاثًا، فَإِنَّهُ لَا يَدْرِي أَيْنَ بَاتَتْ يَدُهُ». [صحيح] - [متفق عليه]

(111) - ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል፦ "አንዳችሁ ዉዱእ ባደረገ ጊዜ አፍንጫው ውስጥ ውሀ አድርጎ ከዚያም ያውጣው፣ በድንጋይ ያደራረቀ ሰውም (የድንጋዩን ቁጥር) ጎዶሎ ያድርገው። አንዳችሁ ከእንቅልፉ የነቃ ጊዜ እጁን ወደ ዉዱእ እቃ ውስጥ ከመክተቱ በፊት እጁን ይጠብ! አንዳችሁ እጁ የት እንዳደረች አያውቅምና።" የሙስሊም ዘገባ ላይ ደግሞ "አንዳችሁ ከእንቅልፉ የነቃ ጊዜ እጁን ሶስት ጊዜ ከማጠቡ በፊት ወደ እቃ ውስጥ አይንከረው! እርሱ እጁ የት እንዳደረች አያውቅምና።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ ( የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) አንዳንድ የጠሀራ ህግጋትን ገለፁ። ከነርሱም ውስጥ: የመጀመሪያው: ዉዱእ ያደረገ ሰው ውሀን ወደ አፍንጫው ውስጥ ስቦ ማስገባትና ድጋሚ ከአፍንጫው ማስወጣት ይገባዋል። ሁለተኛው: ሽንት ቤት ውስጥ ከርሱ የሚወጣውን ቆሻሻ ከውሃ ውጪ በድንጋይና በመሰሰሉ ነገሮች ማንፃትና ማስወገድ የፈለገ ሰው የመፀዳጃው ብዛት በጎዶሎ ቁጥር መሆን እንደሚገባ፤ ቢያንስ ሶስት ሲሆን ከፍተኛው ከርሱ የሚወጣውን ቆሻሻ የሚቆርጥና ቦታውን የሚያፀዳለት ያህል ነው። ሶስተኛው: ከሌሊት እንቅልፍ የነቃ ሰው እጁ የት እንዳደረች አያውቅምና ነጃሳ አለመንካቱን ስለማይተማመን እንዲሁም ለሰው ልጅ የሚጎዳ ወይም ውሃውን የሚያበላሽ ነገርን ሰይጣን ወደ እጁ ተሸክሞ አምጥቶ ተጫውቶበት ሊሆንም ስለሚችል እጁን ከእቃው ውጪ ሶስት ጊዜ ሳያጥብ ዉዱእ ለማድረግም መዳፉን እቃ ውስጥ መክተት አይገባውም።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ዉዱእ ላይ ውሃን ወደ አፍንጫ መክተት ግዴታ ነው። እርሱም: ውሃን በትንፋሽ አማካኝነት ወደ አፍንጫ ውስጥ መክተት ሲሆን ልክ እንደዚሁ ውሃውን በትንፋሽ አማካኝነት ከአፍንጫው ማውጣትም ግዴታ ነው።
2. በጎዶሎ ቁጥር ማደራረቅ እንደሚወደድ እንረዳለን።
3. ከሌሊት እንቅልፍ በኋላ ሶስት ጊዜ ሁለት እጆችን ማጠብ እንደተደነገገ እንረዳለን።

(3033)

(١١٢) - عَنِ ابْنِ عَبَّاسٍ رضي الله عنهما قَالَ: مَرَّ النَّبِيُّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ بِقَبْرَيْنِ، فَقَالَ: «إِنَّهُمَا لَيُعَذَّبَانِ، وَمَا يُعَذَّبَانِ فِي كَبِيرٍ، أَمَّا أَحَدُهُمَا فَكَانَ لاَ يَسْتَتِرُ مِنَ البَوْلِ، وَأَمَّا الآخَرُ فَكَانَ يَمْشِي بِالنَّمِيمَةِ» ثُمَّ أَخَذَ جَرِيدَةً رَطْبَةً، فَشَقَّهَا نِصْفَيْنِ، فَغَرَزَ فِي كُلِّ قَبْرٍ وَاحِدَةً، قَالُوا: يَا رَسُولَ اللَّهِ لِمَ فَعَلْتَ هَذَا؟ قَالَ: «لَعَلَّهُ يُخَفِّفُ عَنْهُمَا مَا لَمْ يَيْبَسَا». [صحيح] - [متفق عليه]

(112) - ከኢብኑ ዓባስ (ረዲየሏሁ ዐንሁማ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: "ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) በሁለት ቀብሮች በኩል አለፉና እንዲህ አሉ ' እነርሱ እየተቀጡ ነው። (በናንተ እይታ) ትልቅ በሆነ ወንጀልም አይደለም የሚቀጡት። አንደኛቸው ከሽንት አይጥራራም ነበር። ሌላኛው ደግሞ ነገር በማመላለስ የሚዞር ነበር።' ቀጥለውም እርጥብ ቅጠል በመያዝ ለሁለት ሰነጠቁትና በእያንዳንዱ ቀብር ላይ አንድ አንድ ተከሉ። ሶሐቦችም 'የአላህ መልክተኛ ሆይ! ለምን ይህን ፈፀሙ?' ብለው ጠየቁ። እርሳቸውም ‘ቅጠሎቹ እስካልደረቁ ድረስ ከነርሱ ላይ ቅጣቱን ያቀልላቸዋል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ።' ብለው መለሱ።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) በሁለት ቀብሮች በኩል አለፉና እንዲህ አሉ፦ የነዚህ ሁለት ቀብር ባለቤቶች እየተቀጡ ነው። አላህ ዘንድ ትልቅ ወንጀል ቢሆንም በናንተ እይታ ግን ትልቅ በሆነ ወንጀል አይደለም የሚቀጡት። አንደኛው: በሚፀዳዳ ወቅት ሰውነቱንና ልብሱን ከሽንት መጠበቅን ትኩረት አይሰጠውም ነበር። ሌላኛው ደግሞ በሰዎች መካከል ነገር በማመላለስ ይዞር ነበር። በሰዎች መካከል መጎዳዳትን፣ ልዩነትን ማምጣትና ሀሜትን አስቦ የሌላን ሰው ነገር ያዋስድ ነበር።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ነገር ማሳበቅ (ማዋሰድ) እና ከሽንት መጥራራትን መተው ከትላልቅ ወንጀሎች የሚመደብና ከቀብር ቅጣት ምክንያቶችም አንዱ ነው።

2. ጥራት የተገባው አላህ እንደ ቀብር ቅጣት የመሰሉ አንዳንድ የሩቅ ምስጢሮችን ለርሳቸው መግለጡ የነቢዩን (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) የነቢይነት ምልክት ግልፅ ለማድረግ ነው።
3. ቅጠልን ለሁለት ሰንጥቆ ቀብር ላይ ማድረግ ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ላይ ብቻ የተለዩበት ስራ ነው። ምክንያቱም አላህ ለርሳቸው የቀብሩን ባለቤቶች ሁኔታ አሳውቋቸው ነውና ያደረጉት። የቀብርን ባለቤቶች ሁኔታ አንድም የሚያውቅ ስለሌለ ከርሳቸው ውጪ ያለን አካል በርሳቸው አንቀይስም (የርሳቸው ተመሳሳይ ብይን አንሰጠውም)።

(3010)

(١١٣) - عَنْ أَنَسٍ رضي الله عنه قَالَ: كَانَ النَّبِيُّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ إِذَا دَخَلَ الخَلَاءَ قَالَ: «اللَّهُمَّ إِنِّي أَعُوذُ بِكَ مِنَ الخُبُثِ وَالخَبَائِثِ». [صحيح] - [متفق عليه]

(113) - ከአነስ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: "ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) መፀዳጃ ቤት የገቡ ጊዜ 'አልላሁመ ኢንኒ አዑዙ ቢከ ሚነል ኹብሢ ወልኸባኢሥ' ይሉ ነበር።" ትርጉሙም "አላህ ሆይ! እኔ ከወንድ ሰይጣንና ከሴት ሰይጣናት በአንተ እጠበቃለሁ።" ማለት ነው። [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ከሽንት ወይም ከሰገራ ለመፀዳዳት ወደ ስፍራው መግባት የፈለጉ ጊዜ ከወንድ ሰይጣኖችና ከሴት ሰይጣናት ክፋት በአላህ ይጠበቁና ወደርሱም ይጠጉ ነበር። በተጨማሪ "አልኹብሢ ወልኸባኢሥ" የሚለው ቃል ክፋትና ነጃሳ ተብሎም ተተርጉሟል።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. መፀዳጃ ቤት መግባት በሚፈለግ ጊዜ ይህን ዱዓ ማድረግ እንደሚወደድ እንረዳለን።
2. ሁሉም ፍጡራን በሁሉም ሁኔታዎቻቸው ላይ የሚያውካቸውን ወይም የሚጎዳቸውን ለመከላከል ወደ ጌታቸው ፈላጊዎች መሆናቸውን እንረዳለን።

(3150)

(١١٤) - عَنْ عَائِشَةَ أُمِّ المؤْمنينَ رَضِيَ اللهُ عنها: أَنَّ النَّبِيَّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ كَانَ إِذَا خَرَجَ مِنَ الغَائِطِ قَالَ: «غُفْرَانَكَ». [صحيح] - [رواه أبو داود والترمذي وابن ماجه وأحمد]

(114) - የአማኞች እናት ከሆነችው ከዓኢሻ (ረዲየሏሁ ዐንሃ) - አላህ መልካም ሥራዋን ይውደድላትና - እንደተላለፈው፡- «ነቢዩ (ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ከመፀዳጃ ቤት የወጡ ጊዜ "ጉፍራነክ" ይሉ ነበር።» (ትርጉሙም "ምህረትህን እለምንሃለሁ" ማለት ነው።) [ሶሒሕ ነው።] - [አቡዳውድ፣ ቲርሚዚ፣ ኢብኑማጀህና አሕመድ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ከመፀዳጃ ቤት ተፀዳድተው ሲወጡ አላህ ሆይ ምህረትህን እጠይቃለሁ ይሉ ነበር።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ከመፀዳጃ ስፍራ ሲወጣ "ጉፍራነክ" ማለት እንደሚወደድ እንረዳለን።
2. ነቢዩ (ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና በሁሉም ሁኔታቸው ጌታቸውን ምህረት እንደሚጠይቁ እንረዳለን።

3. ከመፀዳጃ ቤት ሲወጣ ምህረትን የሚጠየቅበት ምክንያት አላህን ለብዙ ፀጋዎቹ ከማመስገን ስላኳደልን ሲሆን ከነዛም ፀጋዎቹ መካከል የሚያውከንን ነገር እንዲወጣ ማቅለሉ አንዱ ነው። በምፀዳዳበት ወቅት አንተን ከማውሳት ስለተጠመድኩ ምህረትህን እጠይቅሃለሁ ይባላልም ብለዋል።

(10046)

(١١٥) - عن عائشة رضي الله عنها قالت: قال رسول الله صلى الله عليه وسلم: «السِّوَاكُ مَطْهَرَةٌ لِلْفَمِ، مَرْضَاةٌ لِلرَّبِّ». [صحيح] - [رواه النسائي وأحمد]

(115) - ዓኢሻህ ረዲየሏሁ ዐንሀ እንዲህ ማለቷ ተላልፏል፡ "የአሏህ መልዕክተኛ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ ብለዋል፡ 'ሲዋክ አፍን የሚያጠራ (የሚያፀዳ)፤ የአሏህንም ውዴታ የሚያስገኝ ነው።'" [ሶሒሕ ነው።] - [ነሳኢና አሕመድ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን አራክ በተባለው ወይም በአምሳያው በሆነ መፋቂያ ጥርስን መፋቅ አፍን ከቆሻሻ እና ከመጥፎ ጠረን እንደሚያፀዳ ነገሩን። ይህንኑ ማድረግም ለአሏህ ታዛዥነትና ለትእዛዙ ምላሽ መስጠት ከመሆኑ ባሻገር አሏህ የሚወደውን ንፅህናንም የሚያስተርፍ ስለሆነ ድርጊቱ የአሏህን ውዴታ ማግኛ ሰበብ መሆኑን ነገሩን።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ጥርስን መፋቅ ያለውን ትሩፋትና ነቢዩም የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ዑመታቸው ድርጊቱን ያበዛ ዘንድ ማነሳሳታቸውን እንረዳለን።
2. ቢፍቁበት የተሻለው "አራክ" የተባለውን የዛፍ ግንድ (መፋቂያ) ከመሆኑም ጋር በምትኩ የጥርስ ብሩሽ ከሳሙናው ጋር መጠቀምም ይቻላል።

(3588)

(١١٦) - عَنْ حُذَيْفَةَ رضي الله عنه قَالَ: كَانَ النَّبِيُّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ إِذَا قَامَ مِنَ اللَّيْلِ يَشُوصُ فَاهُ بِالسِّوَاكِ. [صحيح] - [متفق عليه]

(116) - ከሑዘይፋ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ሌሊት የተነሱ ጊዜ አፋቸውን በመፋቂያ ይፍቁ ነበር። [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) አብዝተው የሚፍቁና በመፋቅም ላይ የሚያዙ ነበሩ። አንዳንድ ወቅቶች ላይም አጠንክረው ሱናውን ይተገብሩ ነበር። ከነዛም ወቅቶች መካከል: ሌሊት በሚቆሙበት ወቅት መፋቅ ነው። ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) አፋቸውን በመፋቂያ ይፍቁና ያፀዱ ነበር።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ከሌሊት እንቅልፍ በኋላ የመፋቅ ድንጋጌ አፅንዖት የተሰጠው መሆኑን እንረዳለን። ይህም እንቅልፍ የአፍ ጠረን እንዲለወጥ አንዱ ምክንያት ስለሆነ ነው። መፋቂያም የማፅጃ አንዱ መሳሪያ ነው።
2. የአፍ ጠረን ወደ መጥፎ ጠረን በሚለወጥበት ወቅት ባጠቃላይ መፋቅ አፅንዖት ተሰጥቶት የተደነገገ ጉዳይ መሆኑን እንረዳለን። ይህም ቀደም ተብሎ የተጠቀሰውን ሀሳብ በመያዝ ነው።
3. ጥቅል በሆነ መልኩ ማፅዳት የተደነገገ ጉዳይ መሆኑን እንረዳለን። ንፅህና ከነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ሱናና ከምርጥ ስነ ምግባር አንዱ ነው።
4. አፍን ባጠቃላይ መፋቅ ሲባል ጥርሶችን፣ ድድንና ምላስንም ያካትታል።

5. መፋቂያ ማለት "አራክ" ከሚባል ዛፍ ወይም ከሌላ የዛፍ አይነት የሚቆረጥ እንጨት ነው። አፍንና ጥርስን ለማፅዳትም ያገለግላል። አፍን ያፀዳል፣ መጥፎ ጠረንንም ያስወግዳል።

(3063)

(١١٧) - عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ رضي الله عنه عَنِ النَّبِيِّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ قَالَ: «لَوْلَا أَنْ أَشُقَّ عَلَى الْمُؤْمِنِينَ -أَوْ: عَلَى أُمَّتِي- لَأَمَرْتُهُمْ بِالسِّوَاكِ عِنْدَ كُلِّ صَلَاةٍ». [صحيح] - [متفق عليه]

(117) - ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና እንዲህ ብለዋል፦ "በአማኞች ላይ ወይም በኡመቴ ላይ እንዳይከብዳቸው ብዬ ነው እንጂ በሁሉም ሶላቶች ወቅት መፋቂያ እንዲጠቀሙ አዛቸው ነበር።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል። ]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ከኡመታቸው መካከል አማኞች ለሆኑት እንዳይከብድባቸው ባይሰጉላቸው ኖሮ ከሁሉም ሶላቶች ጋር መፋቂያን መጠቀም ግዴታ ያደርጉት እንደነበር ተናገሩ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና በኡመታቸው ላይ ያላቸው እዝነትና እንዳይከብድባቸውም የሚጠነቀቁላቸው መሆናቸውን እንረዳለን።
2. የነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ትእዛዝ ሱና መሆኑን የሚጠቁም ማስረጃ እስካልመጣ ድረስ በመሰረቱ ግዴታ ነው።
3. ሁሉም ሶላት ዘንድ የመፋቅን ተወዳጅነትና ያለውን ትሩፋት እንረዳለን።

4. ኢብኑ ደቂቅ አልዒድ እንዲህ ብለዋል: «ወደ ሶላት በሚቆም ወቅት መፋቅ የተወደደበት ጥበብ ሶላት ወደ አላህ መቃረቢያ ወቅት ስለሆነ ነው። ይህ ደሞ አምልኮውን ማላቅህን ለማንፀባረቅ ሲባል የተሟላ ሁኔታንና ንፁህ መሆንን ይጠይቃል።»
5. የሐዲሡ ጥቅል ሀሳብ ፆመኛ እንኳን ቢሆን ፀሃይ ዘንበል ካለች በኋላም መፋቁ እንደሚወደድለት ያካትታል። (ፆመኛ ሁኖ) በዙህርና ዐስር ሶላት ወቅት መፋቅን ይመስል።

(3364)

(١١٨) - عن أبي هريرة قال: قال رسول الله صلى الله عليه وسلم: «حَقٌّ عَلَى كُلِّ مُسْلِمٍ أَنْ يَغْتَسِلَ فِي كُلِّ سَبْعَةِ أَيَّامٍ يَوْمًا، يَغْسِلُ فِيهِ رَأْسَهُ وَجَسَدَهُ». [صحيح] - [متفق عليه]

(118) - ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ ብለዋል: "የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል: "እያንዳንዱ ሙስሊም በየሰባት ቀኑ አንድ ጊዜ ገላውን መታጠብ አለበት። ሲታጠብም ጭንቅላቱንም ገላውንም መታጠብ አለበት።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) በሁሉም ለአቅመ አዳምና የደረሰና አዕምሮው ጤነኛ በሆነ ሙስሊም ላይ ሁሉ በሳምንት ውስጥ ካሉት ሰባት ቀናት አንዱን ቀን የመታጠብ የጠበቀ ሀቅ እንዳለበት ተናገሩ። በዚህ ቀንም ንፅህናንና ፅዳትን በመፈለግ ጭንቅላቱንና ሰውነቱን ይታጠባል። ይህንን ሀሳብ ከሚያንፀባርቁ አንዳንድ ዘገባዎች እንደምንረዳው ከነዚህ ቀናቶች ሁሉ ለመታጠብ በላጩ ቀን የጁሙዐ ቀን ነው። ለምሳሌ ያህል ሀሙስ ቀን እንኳ ታጥቦ የጁሙዐ ቀን ከሶላት በፊት መታጠቡ አፅንኦት የተሰጠው ተወዳጅ ጉዳይ ነው። የጁሙዐ ቀን መታጠብን ከግዴታነት

የሚያዘረው (ግዴታ አለመሆኑን የሚያሳየው) የእናታችን ዓኢሻ (ረዲየሏሁ ዐንሃ) - አላህ መልካም ሥራዋን ይውደድላትና እንዲህ የሚለው ንግግር ነው "ሰዎች ነፍሶቻቸውን ለመቀለብ የሚሰሩ ነበሩ። ወደ ጁሙዐ የመጡ ጊዜም በዛው በስራ ድባባቸው ይመጡ ነበር። ለነርሱም 'ብትታጠቡስ' ተባሉ።" (ቡኻሪ ዘግበውታል) በሌላ ዘገባቸው "እየሸተቱም ይመጡ ነበር።" ማለትም የላብና የመሳሰሉት ሽታ እየሸተቱ ይመጡ ነበር። ከዚህ ሁኔታቸው ጋርም ሆነው "ብትታጠቡስ" መባላቸው ከነርሱ ውጪ ያለው ግዴታው ላይሆን ይበልጥ የተገባ ነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ኢስላም ለንፅህናና ፅዳት ትኩረትና ቦታ መስጠቱን እንረዳለን።
2. የጁሙዐ ቀን ለሶላቱ ብሎ መታጠብ አፅንኦት የተሰጠው ተወዳጅ ጉዳይ ነው።
3. ገላን መታጠብ ሲባል ጭንቅላትም አብሮ ቢካተትም፤ ለብቻው የተጠቀሰው ትኩረት እንዲሰጠው ነው።
4. ሰዎች በሚታወኩበት መልኩ መጥፎ ጠረን ያለበት ሰው የመታጠብ ግዴታ አለበት።
5. ከመታጠቢያ ቀናቶች ሁሉ ተወዳጅነቱ የጠነከረ የሆነው ቀን ጁሙዐ ነው። ይህም ቀኑ ብልጫ ስላለው ነው።

(65084)

(١١٩) - عن أبِي هريرة رضي الله عنه: سمعتُ النبِيّ صلى الله عليه وسلم يقول: «الفِطْرَةُ خمسٌ: الخِتَانُ والاستحدادُ وقصُّ الشَّارِبِ وتقليمُ الأظفارِ وَنَتْفُ الآبَاطِ». [صحيح] - [متفق عليه]

(119) - ከአቡ ሁረይራ (ረዲየላሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ ብለዋል፡- "ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ሲሉ ሰምቻቸዋለሁ፡- "አምስቱ ከተፈጥሯዊ (ኢስላማዊ ሱናዎች) ናቸው፡- መገረዝ፣ የብልትን ፀጉር መላጨት፣ ቀድሞ ቀመስን (ከአፍንጫ ስር ያለን ፂም) ማሳጠር፣ ጥፍሮችን መቁረጥና የብብትን ፀጉር መንጨት ። [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ከመልክተኞች ሱናዎችና ከኢስላማዊ መገለጫዎች አምስቱን አብራሩ፡-

የመጀመሪያው፡- መገረዝ ነው። እሱም ከወንድ ልጅ ብልት ከክርክሩ ከፍ ብሎ ያለውን ጭማሪ ቆዳና ከሴት ልጅ ብልት ደግሞ ከወንድ ብልት መግቢያ ስፍራ ከፍ ብሎ ያለውን ቆዳ ከጫፉ ቀንሶ መቁረጥ ነው።

ሁለተኛው: የብልትን ፀጉር መቁረጥ ነው። ይህም ከብልት ዙሪያ ያለውን ፀጉር መላጨት ነው።

ሶስተኛው: ቀድሞ ቀመስን ማሳጠር: እሱም በወንድ ልጅ የላይኛው ከንፈር ላይ የበቀለን ፂም ከንፈሩ በግልፅ እስኪታይ መቁረጥ ነው።

አራተኛው: ጥፍሮችን መቁረጥ ነው።

አምስተኛው: የብብትን ፀጉር መንጨት ነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. አላህ የሚወዳቸው፣ የሚቀበላቸውና ያዘዘባቸው የሆኑ የመልክተኞቹ ሱናዎች ወደ ምሉእነት፣ ንፅህናና ቁንጅና የሚጣሩ መሆናቸውን እንረዳለን።

2. እነዚህን ነገሮች ተጠባብቆ መፈፀም የተደነገገ መሆኑንና ከነዚህ ጉዳዮች አለመዘናጋት እንደሚገባ እንረዳለን።
3. እነዚህን ጉዳዮች በአግባቡ መፈፀም ዲናዊና አለማዊ ጥቅሞች አሉት። ከነሱም ውስጥ፦ አካልን ማስዋብ፣ ሰውነትን ማፅዳት፣ ለንፅህና ጥንቁቅ መሆን፣ ከሀዲያንን መቃረንና የአላህን ትእዛዝ መፈፀም ይገኙበታል።
4. በሌላ ሐዲሥ ውስጥ ከነዚህ አምስት ተፈጥሯዊ ሱናዎች ውጪ ያሉ ተጨማሪ ሱናዎች፤ ለምሳሌ: ፂምን መልቀቅ (ማፋፋት)፣ ሲዋክና ሌሎችም ተጠቅሰዋል።

(3144)

(١٢٠) - عَنْ عَلِيٍّ رضي الله عنه قَالَ: كُنْتُ رَجُلًا مَذَّاءً وَكُنْتُ أَسْتَحْيِي أَنْ أَسْأَلَ النَّبِيَّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ لِمَكَانِ ابْنَتِهِ فَأَمَرْتُ الْمِقْدَادَ بْنَ الْأَسْوَدِ فَسَأَلَهُ فَقَالَ: «يَغْسِلُ ذَكَرَهُ وَيَتَوَضَّأُ».
وَلِلْبُخَارِيِّ: فَقَالَ: «تَوَضَّأْ وَاغْسِلْ ذَكَرَكَ». [صحيح] - [متفق عليه]

(120) - ከዐሊ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: "መዚይ (ስሜት በሚቀሰቀስ ወቅት የሚወጣ ፈሳሽ ነው።) የሚበዛብኝ ሰው ነበርኩ። ልጃቸው እኔ ዘንድ በመሆኗ ነቢዩን (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) (ስለብይኑ) መጠየቅ አፈርኩና ሚቅዳድ ቢን አስወድን እንዲጠይቃቸው አዘዝኩት፤ ጠየቃቸው። እርሳቸውም 'ብልቱን ይታጠብና ዉዱእ ያድርግ።' አሉ።" በቡኻሪ ዘገባ ደሞ "ዉዱእ አድርግ፤ ብልትህንም እጠብ።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል። ]

## ትንታኔ:

ዐሊይ ቢን አቢ ጧሊብ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና መዚይ (ነጭ፣ ቀጭን፣ የሚዝለገለግ፣ ስሜት በሚቀሰቀስ ወቅት ወይም ከግንኙነት በፊት የሚወጣ ፈሳሽ ነው።) ብዙ ጊዜ ይወጣቸው እንደነበር ተናገሩ። መውጣቱን ተከትሎ እንዴት ማድረግ እንዳለባቸውም

አያውቁም። የነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ልጅ ፋጢማ ባለቤት ስለሆኑ ነቢዩን (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) መጠየቅ አፈሩ። ሚቅዳድ ቢን አስወድ ነቢዩን (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ስለዚህ ጉዳይ እንዲጠይቅላቸው አድርገው ላኩት። ነቢዩም (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ብልቱን አጥቦ ዉዱእ ማድረግ እንደሚገባው በመንገር መልስ ሰጡት።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. አይነ አፋርነቱ በሰው አማካኝነት እንኳ ከማስጠየቅ አለማቀቡ የዐሊይ ቢን አቢጧሊብን (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና ደረጃ ያስረዳናል።
2. ፈትዋ ለመጠየቅ ሰው መተካት እንደሚፈቀድ እንረዳለን።
3. አንድ ሰው ስለራሱ የሚያሳፍር ነገርንም አስፈላጊ በሆነ ጊዜ መናገሩ እንደሚፈቀድ እንረዳለን።
4. የመዚይን ነጃሳነትና ከሰውነትም ከልብስም ላይ ማጠብ ግዴታ መሆኑን እንረዳለን።
5. የመዚይ መውጣት ዉዱእን ከሚያፈርሱ ነገሮች መካከል አንዱ መሆኑን እንረዳለን።
6. ብልትንና ሁለቱን ፍሬዎች ማጠብ እንደሚገባ የሚያዝ ሌላ ሐዲሥ ስላለ ብልትንና ሁለቱን ፍሬዎች ማጠብም ግዴታ መሆኑን እንረዳለን።

(3348)

(١٢١) - عَنْ عَائِشَةَ أُمِّ المؤمنين رضي الله عنها قَالَتْ: كَانَ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ إِذَا اغْتَسَلَ مِنَ الجَنَابَةِ، غَسَلَ يَدَيْهِ، وَتَوَضَّأَ وُضُوءَهُ لِلصَّلاَةِ، ثُمَّ اغْتَسَلَ، ثُمَّ يُخَلِّلُ بِيَدِهِ شَعَرَهُ، حَتَّى إِذَا ظَنَّ أَنَّهُ قَدْ أَرْوَى بَشَرَتَهُ، أَفَاضَ عَلَيْهِ المَاءَ ثَلاَثَ مَرَّاتٍ، ثُمَّ غَسَلَ سَائِرَ جَسَدِهِ، وَقَالَتْ: كُنْتُ أَغْتَسِلُ أَنَا وَرَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ مِنْ إِنَاءٍ وَاحِدٍ، نَغْرِفُ مِنْهُ جَمِيعًا.

[صحيح] - [رواه البخاري]

(121) - ከአማኞች እናት ዓኢሻ (ረዲየሏሁ ዐንሃ) - አላህ መልካም ሥራዋን ይውደድላትና - እንደተላለፈው እንዲህ አለች: "የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ከጀናባ በሚታጠቡ ጊዜ ሁለት እጃቸውን ይታጠቡና ለሶላት የሚያደርጉትን አምሳያ ዉዱእ ያደርጋሉ። ከዚያም (ሙሉ ገላቸውን) ይታጠቡ ነበር። ከዚያም በእጃቸው ፀጉራቸውን ይፈለፍላሉ። (የፀጉራቸው) ቆዳ በውሃ መራሱን እስከሚያስቡ ድረስም እየፈለፈሉ በጭንቅላታቸው ላይ ሶስት ጊዜ ውሃን ያፈሳሉ። ከዚያም ቀሪ ሰውነታቸውን ያጥባሉ።" ዓኢሻ እንዲህም ብላለች: "እኔና የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ከአንድ እቃ ሁለታችንም እየዘገንን እንታጠብ ነበር።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ከጀናባ መታጠብን በፈለጉ ጊዜ እጃቸውን በመታጠብ ይጀምሩ ነበር። ቀጥለውም ልክ ለሶላት እንደሚያደርጉት አምሳያ ዉዱእ ያደርጉ ነበር። ቀጥለውም ውሃን በሰውነታቸው ላይ ያፈሳሉ። ቀጥለው የጭንቅላታቸውን ፀጉር በእጆቻቸው ይፈለፍላሉ። ውሃው ወደ ፀጉራቸው ስር መድረሱንና የጭንቅላታቸውን ቆዳ ማራሱን ያሰቡ ጊዜ በጭንቅላታቸው ላይ ሶስት ጊዜ ውሃን ያፈሳሉ። ቀጥለው ቀሪ ሰውነታቸውን ያጥባሉ። ዓኢሻ (ረዲየሏሁ ዐንሃ) - አላህ መልካም ሥራዋን ይውደድላትና - "እኔና የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ከአንድ እቃ ሁለታችንም እየዘገንን እንታጠብ ነበር።" ብላለች።

## ከሐዲሡ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ትጥበት ሁለት አይነት ነው። እነሱም: ከግዴታ የሚያብቃቃ ትጥበትና የተሟላ ትጥበት ናቸው። ከግዴታ የሚያብቃቃው ትጥበት: ሰውዬው ጦሀራ ማድረግን ነይቶ ከመጉመጥመጥና አፍንጫ ውስጥ ውሃን ከመክተት ጋር ሰውነቱን በውሃ ማዳረሱ ነው። የተሟላው ትጥበት ደግሞ: በዚህ ሐዲሥ ውስጥ ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንደታጠቡት መታጠብ ነው።
2. ጀናባ የሚለው ቃል የዘር ፈሳሽ ያፈሰሰን ወይም የዘር ፈሳሽ ባያፈስ እንኳ ግንኙነት የፈፀመን ሁሉ የምትገልፅ ቃል ናት።
3. ባለ ትዳሮች የሆኑ አንዱ የሌላኛውን ሀፍረተ ገላ መመልከትና ከአንድ እቃ ውሃ እየወሰዱ መታጠብ እንደሚፈቀድላቸው እንረዳለን።

(3316)

(١٢٢) - عَنْ عَمَّارِ بنِ ياسِرٍ رضي الله عنه قال: بَعَثَنِي رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ فِي حَاجَةٍ، فَأَجْنَبْتُ فَلَمْ أَجِدِ الْمَاءَ، فَتَمَرَّغْتُ فِي الصَّعِيدِ كَمَا تَمَرَّغُ الدَّابَّةُ ثُمَّ أَتَيْتُ النَّبِيَّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ، فَذَكَرْتُ ذَلِكَ لَهُ فَقَالَ: «إِنَّمَا كَانَ يَكْفِيكَ أَنْ تَقُولَ بِيَدَيْكَ هَكَذَا» ثُمَّ ضَرَبَ بِيَدَيْهِ الْأَرْضَ ضَرْبَةً وَاحِدَةً، ثُمَّ مَسَحَ الشِّمَالَ عَلَى الْيَمِينِ، وَظَاهِرَ كَفَّيْهِ وَوَجْهَهُ. [صحيح] - [متفق عليه]

(122) - ከዓማር ቢን ያሲር (ረዲየሏሁ ዐንሁማ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: "የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ለአንድ ጉዳይ ላኩኝና የዘር ፈሳሽ ወጣኝ። ውሃ አላገኘሁምና እንስሳ መሬት ላይ እንደምትንከባለለው ተንከባለልኩኝ። ከዚያም ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ዘንድ መጣሁና ይህን ድርጊቴ አወሳሁላቸው። እርሳቸውም 'በእጅህ እንዲህ ብታደርግ በቂህ ነበር።' አሉና ከዚያም በሁለት እጃቸው መሬቱን አንድ ጊዜ መቱ። ከዚያም በግራ እጃቸው ቀኝ እጃቸውን አበሱ። የላይኛውን የመዳፋቸው ክፍልንና ፊታቸውን አበሱ።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ዓማር ቢን ያሲርን (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - ለሆነ ጉዳይ ጉዞ ላኩት። በግንኙነት ወይም በተኛበት በስሜት የዘር ፈሳሽ በመውጣቱ ምክንያት ጀናባ አገኘው። የሚታጠብበት ውሃም አላገኘም። የሚያውቀው ዉዱእ ሲያጠፋ ለትንሹ ሐደሥ የሚደረገውን የተየሙም ብይን እንጂ፤ ጀናባ ሲያጋጥም የሚደረገውን የተየሙም ብይን አያውቅም ነበር። ስለ አፈፃፀሙ ከተመራመረ በኋላ ዉዱእ ሲጠፋ የምድር ገፅ ላይ በሚገኝ አፈር ከፊል የዉዱእ አካላትን እንደሚታበሰው ለጀናባ የሚደረገው የተየሙም አፈፃፀም ደግሞ የግድ መላ ሰውነትን በአፈር ማዳረስ መሆን አለበት ብሎ አሰበ። ይህም በውሃ ቀይሶት ነው። ሰውነቱን ባጠቃላይ እንዲነካም አፈር ላይ ተንከባለለና ሰገደ። ወደ ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) የመጣ ጊዜም ትክክል ነው የፈፀምኩት ወይስ አይደለም? የሚለውን ለማወቅ ያደረገውን አወሳላቸው። ነቢዩም (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ከሁለቱም ሐደሦች ማለት እንደሽንት ካለው ዉዱእ የሚያጠፋው ትንሹ ሐደሥ እና እንደብጀናባ ካለው ገላ የሚያስታጥበው ትልቁ ሐደሥ የአፀዳድ አፈፃፀምን ገለፁለት። እርሱም በሁለት እጆቹ አንድ ጊዜ አፈርን በመምታት ከዚያም በግራ እጁ ቀኝ እጁን ያብሰል፤ የመዳፎቹን የላይኛውን ክፍልና ፊቱን ያብሰል።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ከተየሙም በፊት ውሃ መፈለግ ግዴታ መሆኑን እንረዳለን።
2. ጀናባ ላይ ሆኖ ውሃ ላላገኘ ሰው ተየሙም እንደተደነገገለት እንረዳለን።
3. ለትልቁ ሐደሥ የሚደረገው ተየሙም ለትንሹ ሐደሥ እንደሚደረገው ተየሙም እንደሆነ እንረዳለን።

(3461)

(١٢٣) - عَنْ المُغِيرَةِ رضي الله عنه قَالَ: كُنْتُ مَعَ النَّبِيِّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ فِي سَفَرٍ، فَأَهْوَيْتُ لِأَنْزِعَ خُفَّيْهِ، فَقَالَ: «دَعْهُمَا، فَإِنِّي أَدْخَلْتُهُمَا طَاهِرَتَيْنِ» فَمَسَحَ عَلَيْهِمَا. [صحيح] - [متفق عليه]

(123) - ከሙጊራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ ብለዋል: "አንድ ጉዞ ላይ ከነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ጋር ነበርኩና ኹፋቸውን (የቆዳ ካልሲያቸውን) ላወልቅ ዝቅ አልኩ፤ እሳቸውም: ' እኔ ንፁህ እንደሆነ ነው ያደረግኳቸውና ተዋቸው።' አሉኝና በነርሱ ላይ አበሱ።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) በአንድ ጉዟቸው ላይ ሳሉ ዉዱእ አደረጉ። ሁለት እግራቸውን ማጠብ ላይ በደረሱ ጊዜ ሙጚራ ቢን ሹዕባ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና እግራቸውን እንዲያጥቡ ብለው ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) አድርገውት የነበረውን ኹፍ ሊያወልቁ እጃቸውን ዘረጉ ነቢዩም (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) "አታውልቃቸው ተዋቸው! እኔ ሁለት እግሬን ኹፎቹ ውስጥ ያስገባሁት በጦሀራ ላይ ሁኜ ነው " አሏቸው። ነቢዩም (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እግራቸውን በማጠብ ምትክ ኹፋቸውን አበሱ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ሁለት ኹፎች ላይ ማበስ የተደነገገው ከትንሹ ሐደሥ (ዉዱእ አጥፍቶ) ዉዱእ በሚደረግበት ወቅት ነው። ለትልቁ ሐደሥ (ገላን ለሚያስታጥብ ጉዳይ) መታጠብ አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ ግን የግድ ሁለት እግሮችን መታጠብ ይኖርበታል።
2. ኹፍ ላይ ማበስ የሚገኘው በውሃ በረጠበ እጅ ታችኛውን ሳይሆን ላይኛውን የኹፉ ክፍል አንድ ጊዜ በመዳበስ ነው።

3. በሁለት ኹፎች ላይ ለማበስ ሊሟሉ የሚገቡ መስፈርቶች አሉ። እነሱም: ኹፎቹን የሚለብሰው ሁለት እግሮቹን በውሃ ካጠበበት የተሟላ ዉዱእ በኋላ መሆን ይገባዋል፤ ኹፉ ንፁህና በትጥበት ወቅት ማጠብ ግዴታ የሆነውን የእግሩን ክፍል የሸፈነ መሆን ይገባዋል፤ የሚያብሰው በጀናባ (የዘር ፈሳሽ መጥቶት ወይም ግንኙነት በማድረጉ) ወይም ገላን የሚያስታጥቡ ነገሮች ሲያጋጥሙት ሳይሆን በትንሹ ሐደሥ (ዉዱእ የሚያስደርጉ ምክንያቶች ሲያጋጥሙት) ብቻ መሆን ይገባዋል፤ የሚያብሰውም በሸሪዓ በተወሰነው ወቅት መሆን ይገባዋል። እሱም መንገደኛ ላልሆነ አንድ ቀን ከነምሽቱ ሲሆን ጉዞ ላይ ላለ ደግሞ ሶስት ቀን ከነሌሊቱ ነው።
4. እንደካልሲና የመሳሰሉት ሁለት እግሮችን የሚሸፍኑ ሁሉ እንደ ሁለቱ ኹፎች ተመሳሳይ ፍርድ ስላላቸው በነርሱ ላይም ማበስ ይበቃል።
5. ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ሙጊራ ኹፋቸውን እንዳያወልቅ ሲከለክሉት ነፍሱ እንድትረጋጋና ብይኑን እንዲያውቅ ምክንያታቸውን መግለፃቸው የርሳቸው ስነምግባርና የማስተማር መንገዳቸው ማማሩን ያስረዳናል።

(3014)

(١٢٤) - عَنْ عَائِشَةَ أُمِّ المؤمنين رضي الله عنها أَنَّ فَاطِمَةَ بِنْتَ أَبِي حُبَيْشٍ سَأَلَتِ النَّبِيَّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ قَالَتْ: إِنِّي أُسْتَحَاضُ فَلاَ أَطْهُرُ، أَفَأَدَعُ الصَّلاَةَ؟ فَقَالَ: «لَا، إِنَّ ذَلِكِ عِرْقٌ، وَلَكِنْ دَعِي الصَّلاَةَ قَدْرَ الأَيَّامِ الَّتِي كُنْتِ تَحِيضِينَ فِيهَا، ثُمَّ اغْتَسِلِي وَصَلِّي». [صحيح] - [متفق عليه]

(124) - የአማኞች እናት ከሆነችው ከዓኢሻ (ረዲየሏሁ ዐንሃ) - አላህ መልካም ሥራዋን ይውደድላትና - እንደተላለፈው ፋጢማ ቢንት አቢ ሑበይሽ ነቢዩን (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ በማለት ጠየቀች: " 'እኔ የበሽታ ደም ይፈሰኛልና አልፀዳም። ሶላት ልተውን?' እርሳቸውም 'በፍፁም! ይህ የደም ስር መቆረጥ ነው። ባይሆን የወር አበባ ስታይበት በነበርሽው የቀናት ልክ ሶላትን ተይ! ከዚያም ታጠቢና ስገጂ።' አሏት።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

**ትንታኔ:**

ፋጢማ ቢንት ሑበይሽ ነቢዩን (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና): "እኔ የሚፈሰኝ ደም ከወር አበባ ጊዜዬም ውጪ መፍሰሱ አልቋረጥ አለ። ታዲያ የዚህ ደም ብይን እንደ ወር አበባ ደም ብይን ነውን? ሶላትንስ ልተውን?" በማለት ጠየቀች። ነቢዩም (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ አሏት: "ይህ በማህፀን ውስጥ የሚገኝ ደም ስር በመቆረጡ ሳቢያ የሚመጣ የበሽታ ደም እንጂ የወር አበባ ደም አይደለም። በበሽታ ደም ከመታመምሽ በፊት በወርሃዊ ልምድሽ የወር አበባን ታይበት የነበርሽበትን የጊዜ መጠን ልክ ሲመጣ ሶላት፣ ፆምና ሌሎችንም የወር አበባ ላይ ያለች ሴት በወር አበባ ወቅት የምትከለከላቸውን ነገሮች ተይ! የወር አበባ ቀናትሽ መጠን በተጠናቀቀ ጊዜ ከወር አበባ ነፅተሻልና የደሙን ስፍራ እጠቢ ከዚያም ሐደሥሽን (ከሶላት የከለከለሽን) ለማስወገድ ሰውነትሽን ሙሉ ትጥበት ታጥበሽ ከዚያም ስገጂ።" አሏት።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ሴት ልጅ የወር አበባ ቀናቷ በሚጠናቀቅበት ወቅት መታጠብ ግዴታዋ መሆኑን እንረዳለን።
2. የበሽታ ደም በሚፈሳት ላይም ሶላት ግዴታ መሆኑን እንረዳለን።
3. የወር አበባ ማለት: ተፈጥሯዊ ደም ሲሆን የደረሰች ሴት ማህፀን በብልት በኩል የሚለቀው ደም ነው። የሚከሰትባትም በታወቁ ቀናት ውስጥ ነው።
4. የበሽታ ደም ማለት: ያለ ወቅቱ ከማህፀን ጥልቁ ክፍል ሳይሆን ከማህፀን አቅራቢያ ክፍል የሚፈስ ደም ነው።
5. በወር አበባና በበሽታ ደም መካከል ያለው ልዩነት: የወር አበባ ደም ጥቁር፣ ወፍራምና ሽታው የሚከረፋ ነው። የበሽታ ደም ግን ቀይ፣ ቀጭንና የሚከረፋ ሽታም የሌለው ነው።

(3029)

(١٢٥) - عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ رضي الله عنه قَالَ: قَالَ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ: «إِذَا وَجَدَ أَحَدُكُمْ فِي بَطْنِهِ شَيْئًا، فَأَشْكَلَ عَلَيْهِ أَخَرَجَ مِنْهُ شَيْءٌ أَمْ لَا، فَلَا يَخْرُجَنَّ مِنَ الْمَسْجِدِ حَتَّى يَسْمَعَ صَوْتًا، أَوْ يَجِدَ رِيحًا». [صحيح] - [رواه مسلم]

(125) - ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: "የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል: 'አንዳችሁ ከሆዱ ውስጥ አንዳችን ነገር ያገኘ ጊዜ ከሆዱ አንዳች ነገር ወጥቷል ወይስ አልወጣም የሚለውን መለየት ካስቸገረው ድምፅ እስኪሰማ ወይም ሽታ እስኪያገኝ ድረስ (ሶላቱን አቋርጦ) ከመስጂድ አይውጣ።'" [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

### ትንታኔ:

ሰጋጅ ከሆዱ ውስጥ አንዳች ነገር መውጣት አለመውጣቱን አስመልክቶ ከተጠራጠረ የፈስ ድምፅ በመስማት ወይም ጠረን በማሽተት ዉዱእ የሚያጠፋ ነገር መከሰቱን እርግጠኛ እስኪሆን ድረስ ዉዱእ ለመድገም ብሎ

ሶላቱን አቋርጦ አይውጣ። የተረጋገጠ ነገር በጥርጣሬ አይበላሽምና። እሱ ዉዱእ እንደነበረው እርግጠኛ ነው፤ ዉዱእ ማጥፋቱ ግን አጠራጣሪ ነገር ነውና።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ይህ ሐዲሥ ከኢስላም መሰረቶች አንዱና ከፊቅህ መርሆዎች መካከል አንዱ መርህ ነው። እርሱም: የተረጋገጠ ነገር በጥርጣሬ አይወገድም ነው። መሰረቱ ተቃራኒው እስኪረጋገጥ ድረስ ሁሉም ነገር በነበረበት መጽናቱ ነው።
2. ጥርጣሬ በጠሀራ ላይ ተፅእኖ እንደማያሳድር እንረዳለን። አንድ ሰጋጅ ዉዱእ ማጥፋቱን እርግጠኛ እስካልሆነ ድረስ በዉዱኡ ላይ እንደፀና ይቆያል።

(65083)

(١٢٦) - عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ رضي الله عنه قَالَ: إِنَّ رَسُولَ اللهِ صلى الله عليه وسلم قَالَ: «إِذَا شَرِبَ الْكَلْبُ فِي إِنَاءِ أَحَدِكُمْ فَلْيَغْسِلْهُ سَبْعًا».

ولمسلم: « أولاهُنَّ بالتُّراب». [صحيح] - [متفق عليه]

(126) - ከአቡ ሁረይራ (ረዲየላሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: «የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል: "ውሻ ከአንዳችሁ እቃ የጠጣ ጊዜ (እቃውን) ሰባት ጊዜ ይጠበው።"» [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ውሻ እቃ ውስጥ ምላሱን ያስገባ ጊዜ እቃው ሰባት ጊዜ እንዲታጠብ አዘዙ። ከነዚህ ሰባት ትጥበቶች የመጀመሪያውን በአፈር ቀላቅሎ ይጠበው ይህም ከዛ በኋላ ውሃ

በተደጋጋሚ እንዲፈስበት ነው። በዚህም ከነጃሳውና ከጉዳቶቹ የተሟላ መፅዳት ይገኛል።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. የውሻ ምራቅ ከባድ ነጃሳ ነው።
2. ውሻ እቃ ውስጥ ምላሱን በመንከር መጠጣቱ እቃውንም ውስጡ ያለውን ውሃም ይነጅሰዋል።
3. በአፈር ማፅዳትና በውሃም ሰባት ጊዜ መደጋገም የውሻ ሽንት፣ ሰገራና ሌሎችም ውሻ ያቆሸሻቸው ነገሮች የሚፀዱበት አፀዳድ ሳይሆን በአፉ የነካ ጊዜ ብቻ የሚፈፀም የአፀዳድ አይነት ነው።
4. እቃ በአፈር የሚፀዳበት የአፀዳድ አፈፃፀም: እቃ ውስጥ ውሃ ያደርግና አፈር ይጨምርበታል። ቀጥሎ በዚህ ከአፈር ጋር በተቀላቀለ ውሃ የተነጀሰውን እቃ ያጥባል።
5. የሐዲሡ ግልፅ መልዕክት ሸሪዓ ቤታችን እንድናደርጋቸው የፈቀዳቸውን ውሻዎችንም ሳይቀር የአደን፣ የጥበቃ፣ ለአዝርእትና ከብቶች ጥበቃ የምናሳድጋቸውን ውሻዎች ይመስል ሁሉንም ውሻዎች ያጠቃልላል።
6. ሳሙናና እንዶድ የአፈርን ቦታ አይተኩም። ይህም ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ለይተው አፈር ብለው በግልፅ ስላስቀመጡ ነው።

(3143)

(١٢٧) - عن عمر بن الخطاب رضي الله عنه قال: قال رسول الله صلى الله عليه وسلم: «إِذَا قَالَ الْمُؤَذِّنُ: اللهُ أَكْبَرُ اللهُ أَكْبَرُ، فَقَالَ أَحَدُكُمْ: اللهُ أَكْبَرُ اللهُ أَكْبَرُ، ثُمَّ قَالَ: أَشْهَدُ أَنْ لَا إِلَهَ إِلَّا اللهُ، قَالَ: أَشْهَدُ أَنْ لَا إِلَهَ إِلَّا اللهُ، ثُمَّ قَالَ: أَشْهَدُ أَنَّ مُحَمَّدًا رَسُولُ اللهِ، قَالَ: أَشْهَدُ أَنَّ مُحَمَّدًا رَسُولُ اللهِ، ثُمَّ قَالَ: حَيَّ عَلَى الصَّلَاةِ، قَالَ: لَا حَوْلَ وَلَا قُوَّةَ إِلَّا بِاللهِ، ثُمَّ قَالَ: حَيَّ عَلَى الْفَلَاحِ، قَالَ: لَا حَوْلَ وَلَا قُوَّةَ إِلَّا بِاللهِ، ثُمَّ قَالَ: اللهُ أَكْبَرُ اللهُ أَكْبَرُ، قَالَ: اللهُ أَكْبَرُ اللهُ أَكْبَرُ، ثُمَّ قَالَ: لَا إِلَهَ إِلَّا اللهُ، قَالَ: لَا إِلَهَ إِلَّا اللهُ مِنْ قَلْبِهِ دَخَلَ الْجَنَّةَ». [صحيح] - [رواه مسلم]

(127) - ከዑመር ቢን ኸጧብ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ፦ "ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል፦ 'አዛን ባዩ: 'አላሁ አክበሩ አላሁ አክበር' (አላህ ታላቅ ነው።) ያለ ጊዜ አንዳቻሁ ከልቡ 'አላሁ አክበሩ አላሁ አክበር' ካለ፤ ከዚያም አዛን ባዩ: 'አሽሀዱ አንላ ኢላሃ ኢለሏህ' (ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ እንደሌለ እመሰክራለሁ።) ያለ ጊዜም 'አሽሀዱ አንላ ኢላሃ ኢለሏህ' ካለ፤ ከዚያም አዛን ባዩ: 'አሽሀዱ አንነ ሙሐመደን ረሱሉሏህ' (ሙሐመድ የአላህ መልዕክተኛ መሆናቸውን እመሰክራለሁ።) ያለ ጊዜም 'አሽሀዱ አንነ ሙሐመደን ረሱሉሏህ' ካለ፤ ቀጥሎ አዛን ባዩ: 'ሐይየ ዐለስ-ሶላህ' (ኑ ወደ ሶላት) ባለ ጊዜም 'ላ ሐውለ ወላ ቁውወተ ኢላ ቢላህ' (ብልሀትም ሆነ ኃይል በአላህ ካልሆነ በቀር የለም።) ካለ፤ ቀጥሎ አዛን ባዩ: 'ሐይየ ዐለል ፈላሕ' (ኑ ወደ ስኬት!) ባለ ጊዜም 'ላ ሐውለ ወላ ቁውወተ ኢላ ቢላህ' (ብልሀትም ሆነ ኃይል በአላህ ካልሆነ በቀር የለም።) ካለ፤ ቀጥሎ አዛን ባዩ: 'አላሁ አክበሩ አላሁ አክበር' (አላህ ታላቅ ነው።) ያለ ጊዜም 'አላሁ አክበሩ አላሁ አክበር' ካለ፤ ቀጥሎ አዛን ባዩ: 'ላ ኢላሀ ኢለሏህ' (ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ የለም።) ያለ ጊዜም 'ላ ኢላሀ ኢለሏህ' ካለ ጀነት ገባ። [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

አዛን ማለት የሶላት ወቅት መግባቱን ለሰዎች ማሳወቂያ ነው። የአዛን ቃላቶች የኢማንን መሰረተ ሀሳቦች የጠቀለሉ ቃላቶች ናቸው።

በዚህ ሐዲሥ ውስጥ ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) አዛን በሚሰማ ወቅት የተደነገገውን ገለፁ። እሱም አዛን ሰሚው አዛን ባዩ እንደሚለው ማለቱ ነው። አዛን ባዩ 'አላሁ አክበር' ያለ ጊዜ ሰሚውም 'አላሁ አክበር' ይላል በዚህ መልኩ አዛን ባዩ ያለውን በማለት ይቀጥላል። 'ሐይየ ዐለስ-ሶላህ' እና 'ሐይየ ዐለል ፈላሕ' በሚልበት ጊዜ ግን ሰሚው 'ላ ሐውለ ወላ ቁውወተ ኢላ ቢላህ ' ይበል።

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እነዚህን ቃላቶች ከልቡ አጥርቶ ከአዛን ባዩ ጋር የመላለሰ ሰው ጀነት እንደሚገባ ገለፁ።

የአዛን ቃላቶች ትርጉም: "አላሁ አክበር" ማለት ጥራት የተገባው አላህ ከሁሉም ነገር እጅግ ታላቅና የላቀ ነው ማለት ነው።

"አሽሀዱ አንላ ኢላሀ ኢለሏህ" ማለት ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ የለም ማለት ነው።

"አሽሀዱ አንነ ሙሐመደን ረሱሉሏህ" ማለት ሙሐመድ አላህ የላካቸው የአላህ መልዕክተኛ መሆናቸውንና እሳቸውን መታዘዝም ግዴታ መሆኑን በምላሴና በልቤ እርግጠኛ ሆኜ እመሰክራለሁ ማለት ነው።

"ሐይየ ዐለስ-ሶላህ" ማለት ወደ ሶላት ኑ! ማለት ሲሆን ሰሚው የሚለው "ላ ሐውለ ወላ ቁወተ ኢላ ቢላህ" ማለት ደግሞ የአላህን ትእዛዝ ለመተግበር ከሚከለክሉ ነገሮች ለመዳን የሚያስችል ብልሀትም፤ ለመተግበር የሚያስችል ሀይልም፤ በማንኛውም ነገር ላይም ችሎታ የለም በአላህ መግጠም ቢሆን እንጂ ማለት ነው።

"ሐይየ ዐለል ፈላሕ" ማለት ወደ ስኬት መንገድ ኑ! ማለት ነው። ስኬቱም ጀነትን ማግኘትና ከእሳት መዳን ነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ከሁለቱ "ሀይየዐለተይን" ("ሐይየ ዐለስ-ሶላህ" እና "ሐይየ ዐለል ፈላሕ") ውጪ የአዛን ባይን ጥሪ በሚለው አምሳያ መመለስ፤ በሁለቱ "ሐይዐለተይን" ወቅት ደግሞ "ላ ሐውለ ወላ ቁውወተ ኢላ ቢላሂ" በማለት መመለስ ያለውን ትሩፋት እንረዳለን።

(65086)

(١٢٨) - عَنْ عَبْدِ اللهِ بْنِ عَمْرِو بْنِ الْعَاصِ رضي الله عنها أَنَّهُ سَمِعَ النَّبِيَّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ يَقُولُ: «إِذَا سَمِعْتُمُ الْمُؤَذِّنَ فَقُولُوا مِثْلَ مَا يَقُولُ، ثُمَّ صَلُّوا عَلَيَّ، فَإِنَّهُ مَنْ صَلَّى عَلَيَّ صَلَاةً صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ بِهَا عَشْرًا، ثُمَّ سَلُوا اللهَ لِيَ الْوَسِيلَةَ، فَإِنَّهَا مَنْزِلَةٌ فِي الْجَنَّةِ، لَا تَنْبَغِي إِلَّا لِعَبْدٍ مِنْ عِبَادِ اللهِ، وَأَرْجُو أَنْ أَكُونَ أَنَا هُوَ، فَمَنْ سَأَلَ لِيَ الْوَسِيلَةَ حَلَّتْ لَهُ الشَّفَاعَةُ». [صحيح] - [رواه مسلم]

(128) - ከዐብደላህ ቢን ዐምር ቢን ዓስ (ረዲየሏሁ ዐንሁማ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው ነቢዩን (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ሲሉ ሰምቻለሁ ብለዋል፦ "ሙአዚኑን የሰማችሁ ጊዜ የሚለውን አምሳያ በሉ። ከዚያም በኔ ላይ ሶለዋት አውርዱ። እነሆ በኔ ላይ አንዲትን ሶላት ያወረደ በርሱ ምክንያት አላህ በርሱ ላይ አስር ሶለዋት ያወርድለታል። ከዚያም ለኔ ከአላህ ወሲላን ጠይቁልኝ። እርሷም ጀነት ውስጥ ያለች ደረጃ ናት። ከአላህ ባሮች መካከል ለአንድ ባሪያ እንጂ አትገባም። እርሱም እኔ እሆናለሁ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። ወሲላን ለኔ የጠየቀልኝ ሰው ለርሱ ምልጃዬ ትፀናለታለች።" [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ለሶላት አዛን የሚያደርግን ሰው የሰማ ከ"ሐይየዐለተይን" ውጪ ከኋላው አስከትሎ (ሙአዚኑ) የሚለውን አምሳያ እንዲል ጠቆሙ። ከ"ሐይየዐለተይን" በኋላ ግን "ላ ሐውለ ወላ ቁውወተ ኢላ ቢላህ" ይላል። አዛኑ ከተጠናቀቀ በኃላም በነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ላይ ሶላትን ያወርዳል። እነሆ በርሳቸው ላይ አንዲትን ሶላት ያወረደ በርሱ ምክንያት አላህ በርሱ ላይ አስር ሶላት ያወርድበታልና። አላህ በባሪያው ላይ ሶላት አወረደ ማለት መላኢኮች ዘንድ ባሪያውን ማወደሱ ነው።

ቀጥለውም ወሲላን ከአላህ ለሳቸው (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንድንጠይቅ አዘዙ። እርሷም በጀነት ውስጥ የምትገኝ ከፍተኛዋ

ደረጃ ናት። ይህቺ ስፍራም ከሁሉም የአላህ ባሮች መካከል ለአንድ ባሪያ እንጂ ለማንም አትሰጥም አትበጅምም (አትገባም)። ያ ባሪያ እኔ እሆናለሁ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። ነቢዩም (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) በዚህ መልኩ የተናገሩት ለመተናነስ ብለው ነው እንጂ ይህቺ ከፍተኛ ደረጃ ለአንድ ባሪያ እንጂ ለማንም የማትሆን ከሆነች ያ አንድ ባሪያ ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንጂ ማንም አይሆንም። እሳቸው ከፍጡራን ሁሉ በላጬ ፍጡር ናቸውና።

ቀጥለው ለነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ወሲላን ከአሏህ የለመነ ሰው የርሳቸውን ምልጃ እንደሚያገኝ ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ገለፁ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. የሙአዚንን ጥሪ በመመለስ ላይ መነሳሳቱን እንረዳለን።
2. ለሙአዚን ከመለስን በኋላ በነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ላይ ሶላት የማውረድን ትሩፋት እንረዳለን።
3. ሶላት ካወረድንባቸው በኋላ ለነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ወሲላን በመጠየቅ ላይ መነሳሳቱን እንረዳለን።
4. የወሲላ ምንነትና ጉዳዩዋ ከፍ ያለ መሆኑ መገለፁ። ለአንድ ባሪያ እንጂ አትበጅምና (አትገባም)።
5. በዚህች ከፍተኛ ደረጃ በመነጠላቸው የነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ደረጃ መገለፁ።
6. ለነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ከአሏህ ወሲላን የጠየቀላቸው ሰው የርሳቸው ምልጃ ትፀድቅለታለች።
7. ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ይህቺ ደረጃ የርሳቸው ከመሆኗም ጋር ኡመታቸው ዱዓ እንዲያደርጉላቸው መፈለጋቸው ትህትናቸውን ይገልፃል።
8. መልካም ስራ በአስር ማብዛቱ የአላህ ትሩፋትና እዝነት ስፋቱን ያስረዳናል።

(65087)

(١٢٩) - عَنْ سَعْدِ بْنِ أَبِي وَقَّاصٍ رضي الله عنه عَنْ رَسُولِ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ أَنَّهُ قَالَ: «مَنْ قَالَ حِينَ يَسْمَعُ الْمُؤَذِّنَ أَشْهَدُ أَنْ لَا إِلَهَ إِلَّا اللهُ وَحْدَهُ لَا شَرِيكَ لَهُ، وَأَنَّ مُحَمَّدًا عَبْدُهُ وَرَسُولُهُ، رَضِيتُ بِاللهِ رَبًّا وَبِمُحَمَّدٍ رَسُولًا، وَبِالْإِسْلَامِ دِينًا، غُفِرَ لَهُ ذَنْبُهُ». [صحيح] - [رواه مسلم]

(129) - ከሰዕድ ቢን አቢ ወቃስ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል: "አዛን ሲባል የሰማ ጊዜ: 'አሽሃዱ አን ላኢላሃ ኢለሏሁ ወሕደሁ ላሸሪከ ለህ ወአነ ሙሐመደን ዐብዱሁ ወረሱሉህ ረዲቱ ቢላሂ ረበን ወቢሙሐመደን ረሱለን ወቢል ኢስላሚ ዲና' ያለ ሰው ወንጀሉ ይማራል።" (ትርጉሙም: ከአላህ በቀር በእውነት የሚመለክ የለም። ብቸኛና አጋር የሌለው ነው። ሙሐመድም የአላህ ባሪያውና መልክተኛው ናቸው ብዬ እመሰክራለሁ፤ በአላህ ጌትነት፣ በሙሐመድ መልክተኝነት፣ በኢስላም ሃይማኖትነት ወድጃለሁ።) [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ አሉ: አዛን አድራጊውን የሰማ ጊዜ እንዲህ ያለ ሰው: "አሽሃዱ አን ላኢላሃ ኢለሏሁ ወሕደሁ ላሸሪከ ለህ" ማለትም: ከአላህ በቀር በእውነት የሚመለክ እንደሌለና ከርሱ ውጪ የሚመለኩ ሁሉ ከንቱ እንደሆኑ አረጋግጣለሁ፣ አውቃለሁ፣ እናገራለሁ። "ወአነ ሙሐመደን ዐብዱሁ ወረሱሉህ" ማለትም: እርሳቸው ባሪያ ናቸውና አይመለኩም፣ መልክተኛ ናቸውና አይስተባበሉም። "ረዲቱ ቢላሂ ረበን" ማለትም: በአላህ ጌትነት፣ ተመላኪነትና በስሞቹና በባህሪያቱ ወድጃለሁ። ማለት ነው። "ወቢሙሐመደን ረሱላ" ማለትም ረሱል በተላኩበት ነገር ሁሉና ባደረሱን ነገር ወድጃለሁ። ማለት ነው። "በእስልምናም" ማለትም: ትእዛዛትም ሆኑ ክልከላዎች በሁሉም የኢስላም ህግጋት "ዲና" ማለትም በማመንና በመመራት ወድጃለሁ። ማለት ነው። "ወንጀሉ ይማራል።" ማለትም ትናንሽ ወንጀሎቹን ይማሩለታል።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ይህን ዱዓ አዛን በሚሰሙ ጊዜ መደጋገም ወንጀልን ያስምራል።

(6272)

(١٣٠) - عَنْ أَنَسِ بْنِ مَالِكٍ رضي الله عنه قَالَ: قَالَ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ: «الدُّعَاءُ لاَ يُرَدُّ بَيْنَ الأَذَانِ وَالإِقَامَةِ». [صحيح] - [رواه أبو داود والترمذي والنسائي]

(130) - ከአነስ ቢን ማሊክ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው እንዲህ ብለዋል: «የአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና እንዲህ ብለዋል: "በአዛንና ኢቃም መካከል የሚባል ዱዓ አይመለስም (ተቀባይነቱ ጥርጥር የለውም)።"» [ሶሒሕ ነው።] - [አቡዳውድ፣ ቲርሚዚና ነሳኢ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና በአዛንና ኢቃም መካከል የሚባል ዱዓ ያለውን ደረጃና እርሱ ለተቀባይነት የተገባና የማይመለስ ስለሆነ በዚህ ወቅት አላህን እንድንማፀን ገለፁ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ይህ ወቅት ዱዓ ለማድረግ ያለውን በላጭነት እንረዳለን።
2. አንድ ዱዓ አድራጊ የዱዓን ስነስርዓቶች ካሟላ፣ ዱዓ ለማድረግ በላጩን ወቅትናና ስፍራ ካለመ፣ አላህን ከማመፅ ከራቀ፣ ነፍሱ አምታታችና አጠራጣሪ ነገር ውስጥ እንዳትገባ ከተጠነቀቀ፣ በአላህ ላይ ያለውን እሳቤ ካሳመረ በአላህ ፈቃድ ዱዓው ተቀባይነት ለማግኘት የተገባ ነው።
3. ስለዱዓ ተቀባይነት ማግኘት መናዊ እንዲህ ብለዋል: «ማለትም የዱዓ መስፈርቶችን፣ ማዕዘናቶችንና ስነስርዓቶች ካሟላ በኋላ ከለመነው እንጂ ያጓደለው ነገር ካለ በመስተጓጎሉ ከነፍሱ በቀር ማንንም አይውቀስ።»

4. የዱዓ ተቀባይነት ማግኘት: ወይ የለመነው በፍጥነት ትገኝለታለች ወይም በለመነው አምሳያ ጉዳት ዘር ይደረግለታል ወይም በመጪው አለም ለርሱ ድልብ ይደረግለታል። ይህም እንደአላህ ጥበብና እዝነት የሚወሰን ነው።

(5479)

(١٣١) - عن أبي هريرة رضي الله عنه قال: أَتَى النَّبِيَّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ رَجُلٌ أَعْمَى، فَقَالَ: يَا رَسُولَ اللهِ، إِنَّهُ لَيْسَ لِي قَائِدٌ يَقُودُنِي إِلَى الْمَسْجِدِ، فَسَأَلَ رَسُولَ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ أَنْ يُرَخِّصَ لَهُ فَيُصَلِّيَ فِي بَيْتِهِ، فَرَخَّصَ لَهُ، فَلَمَّا وَلَّى دَعَاهُ، فَقَالَ: «هَلْ تَسْمَعُ النِّدَاءَ بِالصَّلَاةِ؟» فَقَالَ: نَعَمْ، قَالَ: «فَأَجِبْ». [صحيح] - [رواه مسلم]

(131) - ከአቡ ሁረይራ -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: "ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ዘንድ አንድ ማየት የተሳነው ሰውዬ መጣ። 'የአላህ መልክተኛ ሆይ! እኔ ወደ መስጂድ የሚመራኝ መሪ የለኝም።' በማለት የአላህ መልክተኛ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም በቤቱ መስገድን እንዲያገሩለት ጠየቀ። ለርሱም አግራሩለት። ለመሄድ የዞረ ጊዜ ጠሩትና 'የሶላትን ጥሪ ትሰማለህን?' አሉት። እርሱም 'አዎን' አላቸው። እሳቸውም 'እንግዲያውስ ለጥሪው መልስ ስጥ!' አሉት።" [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

አንድ አይነ ስውር ሰውዬ ወደ ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም በመምጣት "የአላህ መልክተኛ ሆይ! እኔ ዘንድ ለአምስቱ ሶላቶች እጄን ይዞ ወደ መስጂድ የሚወስደኝና የሚያግዘኝ የለም።" አለ። ፍላጎቱ ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ጀማዓን በመተው ለርሱ እንዲያግራሩለት ነው። ለርሱም አግራሩለት። ለመሄድ የዞረ ጊዜም ጠሩትና "የሶላትን አዛን ትሰማለህን?" አሉት። እርሱም "አዎን" አለ። እሳቸውም "የሶላቱን ተጣሪ ጥሪ መልስ" አሉት።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ግዴታ ለሆነ ነገር ካለሆነ በቀር ማግራራት ስለማይኖር የጀማዓ ሶላት ግዴታ መሆኑን እንረዳለን።
2. "ጥሪውን መልስ!" ከሚለው ቃላቸው አዛን የሚሰማ ሰው ላይ የጀማዓ ሶላት ግዴታ መሆኑን ይጠቁማል። ትእዛዝ በመሰረቱ የሚያስፈርደው ግዴታን ነውና።

(11287)

(١٣٢) - عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ رضي الله عنه أَنَّهُ سَمِعَ رَسُولَ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ يَقُولُ: «أَرَأَيْتُمْ لَوْ أَنَّ نَهَرًا بِبَابِ أَحَدِكُمْ يَغْتَسِلُ فِيهِ كُلَّ يَوْمٍ خَمْسًا، مَا تَقُولُ ذَلِكَ يُبْقِي مِنْ دَرَنِهِ؟» قَالُوا: لَا يُبْقِي مِنْ دَرَنِهِ شَيْئًا، قَالَ: «فَذَلِكَ مِثْلُ الصَّلَوَاتِ الخَمْسِ، يَمْحُو اللهُ بِهِ الخَطَايَا». [صحيح] - [متفق عليه]

(132) - ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: የአላህን መልዕክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ሲሉ ሰምቻለሁ አሉ፡- "'ንገሩኝ እስኪ! አንዳችሁ በር ላይ በየቀኑ አምስት ጊዜ የሚታጠብበት ወንዝ ቢኖር ይህ ከእድፉ ያስቀራል ትላላችሁን?' ሶሐቦችም 'ከእድፉ አንዳችም አያስቀርም።' አሉ። እርሳቸውም 'ይህ የአምስቱ ሶላቶች ምሳሌ ነው። አላህ በሶላት ወንጀሎችን ያብሳል።' አሉ።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) በጧትም በማታም የሚሰገዱትን አምስቱ ሶላቶች ትናንሽ ወንጀሎችንና ኃጢአቶችን ማስማራቸውና ማስወገዳቸውን፤ አንድ ሰው በየቀኑ አምስት ጊዜ የሚታጠብበት በሆነ በሩ ላይ እንዳለ ወንዝ መሰሉት። ከእድፉና ቆሻሻው አንዳችም አይቀርምና።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ይህ ትሩፋት ትናንሽ ወንጀሎችን ብቻ በማስማር የተገደበ ነው። ትላልቅ ወንጀሎች የግድ ተውበት ያስፈልጋቸዋል።
2. አምስቱን ሶላቶች የመፈፀምና የእነርሱን መስፈርቶች፣ ማእዘናቶች፣ ግዴታዎችና ሱናዎችን የመጠባበቅን ትሩፋት እንረዳለን።

(4968)

(١٣٣) - عَنْ عَبْدِ اللهِ بِن مَسْعُودٍ رضي الله عنه قَالَ: سَأَلْتُ النَّبِيَّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ: أَيُّ العَمَلِ أَحَبُّ إِلَى اللهِ؟ قَالَ: «الصَّلاَةُ عَلَى وَقْتِهَا»، قَالَ: ثُمَّ أَيٌّ؟ قَالَ: «ثُمَّ بِرُّ الوَالِدَيْنِ» قَالَ: ثُمَّ أَيٌّ؟ قَالَ: «الجِهَادُ فِي سَبِيلِ اللهِ» قَالَ: حَدَّثَنِي بِهِنَّ، وَلَوِ اسْتَزَدْتُهُ لَزَادَنِي. [صحيح] - [متفق عليه]

(133) - ከዐብደላህ ቢን መስዑድ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ፦ "ነቢዩን (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) አላህ ዘንድ እጅግ ተወዳጁ ስራ ምን እንደሆነ ጠየቅኳቸው። እሳቸውም 'ሶላትን በወቅቱ መስገድ።' አሉ። 'ከዚያስ ቀጥሎ' አልኳቸው። እርሳቸውም 'ቀጥሎ ለወላጆች መልካም መዋል ነው።' አሉኝ። 'ከዚያስ ቀጥሎ' አልኳቸው። እርሳቸውም 'በአላህ መንገድ መታገል ነው።' አሉ። እነዚህን ነገሩኝ። ጥያቄዬን ብጨምር እርሳቸውም ይጨምሩልኝ ነበር።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) አላህ ዘንድ እጅግ ተወዳጁ ስራ ምን እንደሆነ ተጠየቁ። እርሳቸውም "ግዴታ ሶላቶችን አላህ በገደበው ወቅት መስገድ ነው።" ብለው መለሱ። ቀጥሎም በጎ በማድረግ፣ ሐቃቸውን በመጠበቅ፣ ሐቃቸውን ከመጨፍለቅ በመቆጠብ ለወላጆች መልካም መዋል ነው። ቀጥሎም የአላህን ንግግር የበላይ ለማድረግ፣ ከኢስላምና ከተከታዮቹ ጠላቶችን ለመመከትና የኢስላምን ምልክቶች ይፋ ለማድረግ በአላህ መንገድ መታገል ነው። ይህም በነፍስና በገንዘብ ነው።

ኢብኑ መስዑድ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - "ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እነዚህን ስራዎች ነገሩኝ። ለርሳቸው 'ከዚያስ ቀጥሎ' ብላቸው ኖሮ ግን ይጨምሩልኝ ነበር።" አሉ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ስራዎች በመካከላቸው የሚበላለጡት አላህ ለስራዎቹ ባለው ውዴታ ልክ ነው።
2. ሙስሊምን እጅግ በላጭ በሆነ ስራ ላይ እንዲጓጓ መነሳሳቱን እንረዳለን።
3. ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ስለ በላጭ ስራዎች ተጠይቀው የሚመልሱት መልስ እንደጠያቂዎቹ ሰዎችና ሁኔታቸው መለያየት ይበላለጣል። እያንዳንዱን ጠያቂ ለነርሱ እጅግ በጣም ጠቃሚ የሆነውን መልስ ነው የሚመልሱት።

(3365)

(١٣٤) - عَنْ عُثْمَانَ رضي الله عنه قَالَ: سَمِعْتُ رَسُولَ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ يَقُولُ: «مَا مِنَ امْرِئٍ مُسْلِمٍ تَحْضُرُهُ صَلَاةٌ مَكْتُوبَةٌ فَيُحْسِنُ وُضُوءَهَا وَخُشُوعَهَا وَرُكُوعَهَا، إِلَّا كَانَتْ كَفَّارَةً لِمَا قَبْلَهَا مِنَ الذُّنُوبِ، مَا لَمْ يُؤْتِ كَبِيرَةً، وَذَلِكَ الدَّهْرَ كُلَّهُ». [صحيح] - [رواه مسلم]

(134) - ከዑሥማን (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አለ: "የአላህን መልዕክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ሲሉ ሰምቻዋለሁ: 'ትልቅ ወንጀል እስካልፈፀመ ድረስ ግዴታ ሶላት አጋጥሞት ዉዱኡን፣ ተመስጦውንና ሩኩዑን አሳምሮ የሚሰግድ አንድም ሙስሊም የለም፤ ከሶላቷ በፊት የነበረበትን ወንጀል ማስማሪያ ቢሆነው እንጂ፤ ይህም እድሜልኩን ነው።'" [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

አንድም ሙስሊም የግዴታ ሶላት ወቅት የሚገባበትና ዉዱኡን አሳምሮና አሟልቶ የሚያደርግ፤ ቀጥሎም ቀልቡና አካሉ ሁሉ ወደ አላህ የዞሩና የአላህን ልቅና ያስተዋሉ በሚሆኑበት መልኩ በሶላቱ የሚመሰጥ፤ እንደ ሩኩዕ፣ ሱጁድና ሌሎችንም የመሳሰሉትን የሶላቱን ድርጊቶች የሚያሟላ አይሆንም ይህ ሶላቱ ላሳለፈው ትናንሽ ወንጀሎች ማስማሪያ ቢሆን እንጂ፤ ነገር ግን ይህ የሚሆነው ከትላልቅ ወንጀሎች መካከል የሆነን አንድም ወንጀል እስካልሰራ ነው። ይህ ትሩፋትም ዘመናት በነጎዱ ቁጥር በሁሉም ሶላቶች ላይ እንደሚቀጥል ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ገለፁ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. የባሪያውን ወንጀል የሚያስምረው ሶላት ዉዱኡን ያሳመረበትና የአላህን ፊት በመፈለግ በተመስጦ የሰገደው ሶላት ነው።
2. በአምልኮ ላይ የመዘውተር ትሩፋትን እንረዳለን። አምልኮ ትናንሽ ወንጀሎችን የሚያስምር አንዱ ሰበብ ነው።
3. ዉዱእን የማሳመር፣ ሶላትን የማሳመርና በሶላት ውስጥ የመመሰጥን ትሩፋት እንረዳለን።
4. ትናንሽ ወንጀሎች እንዲማሩ ትላልቅ ወንጀሎችን መራቅ ወሳኝ እንደሆነ እንረዳለን።
5. ትላልቅ ወንጀሎች በተውበት ካልሆነ በቀር አይማሩም።

(6254)

(١٣٥) - عن أبي هريرة رضي الله عنه أن رسول الله صلى الله عليه وسلم كان يقول: «الصَّلَوَاتُ الْخَمْسُ، وَالْجُمُعَةُ إِلَى الْجُمُعَةِ، وَرَمَضَانُ إِلَى رَمَضَانَ، مُكَفِّرَاتٌ مَا بَيْنَهُنَّ إِذَا اجْتَنَبَ الْكَبَائِرَ».
[صحيح] - [رواه مسلم]

(135) - ከአቢ ሁረይራ ረዲየሏሁ ዓንሁ እንደተላለፈው ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ ይሉ ነበር፡ "ከባባዶቹን ወንጀሎች ከተጠነቀቁ አምስቱ ሰላቶች፣ ከጁሙዐ እስከ ጁሙዐ፣ ከረመዳን እስከ ረመዳን በመካከላቸው የተሰሩትን ወንጀሎች ያስሰርዛሉ።" [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ከባባዶቹን ወንጀሎች መጠንቀቅ እንደቅድመ መስፈርት ከተሟላ አምስቱ በቀንና ሌሊት የሚከናወኑት ሰላቶች፣ በየሳምንቱ የሚሰገደው የጁምዐ ሰላትና በየአመቱ የረመዳንን ወር መፆም በመካከላቸው የሚፈፀምን ትናንሽ ወንጀሎችን እንደሚያስምሩ ነገሩን። ዝሙትና መጠጥን የመሰሉ ከባባድ ወንጀሎች በተውባ ካልሆነ በቀር አይሰረዙም።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ከወንጀሎች መካከል ከባባድና ትናንሽ የሚባሉ እንዳሉ፤
2. ትናንሽ ወንጀሎች የሚሰረዙት ከባባዶቹን ወንጀሎች መራቅን እንደመስፈርት ማሟላት ከተቻለ መሆኑን እንረዳለን።
3. ከባባድ ወንጀሎች የሚባሉት ወይ በዱኒያ ቅጣት የተወሰነባቸው፣ ወይም በአኼራ የሚያስከትሉትን የቅጣት አይነት የተነገረባቸው፣ ወይም የአላህ ቁጣ የመጣባቸው፣ ወይም ከባድ ዛቻ ያለባቸው፣ ወይም ደግሞ አድራጊው የተረገመባቸው ሲሆኑ ነው። ለምሳሌ፡ ዝሙት፣ መጠጥ መጠጣት ይጠቀሳሉ።

(3591)

(١٣٦) - عن عمرو بن شُعيب عن أبيه عن جدِّه قال: قال رسولُ الله صلى الله عليه وسلم: «مُرُوا أولادكم بالصلاةِ وهم أبناءُ سبعِ سِنينَ، واضرِبوهم عليها وهم أبناءُ عَشرٍ، وفرِّقوا بينهم في المَضاجِعِ». [حسن] - [رواه أبو داود]

(136) - ዐምር ቢን ሹዐይብ ከአባቱና ከአያቱ እንዳስተላለፈው እንዲህ አለ: "የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ አሉ: "ልጆቻችሁን ሰባት አመት ሲሆኑ በሶላት እዘዟቸው፤ አስር አመት ሲሞላቸው ሶላት ላለመስገዳቸው ምቷቸው፤ በመካከላቸውም የመኝታ ስፍራቸውን ለዩ!" [ሐሰን ነው።] - [አቡዳውድ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) አባት ወንድና ሴት ልጆቹን ገና ሰባት ዓመት እያሉ ሶላት እንዲሰግዱ ማዘዝና ሶላትን በማስተካከል ላይ የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ ማስተማር እንዳለበት ገለፁ። አስር ዓመት የደረሱ ጊዜም ትእዛዙን ይጨምራል። ሶላትን በማጓደላቸው ይመታቸዋልም፤ በመኝታ ስፍራም በመካከላቸውም ይለያያቸዋል።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ህፃናት ልጆችን አቅመ አዳም ከመድረሳቸውም በፊት የዲን ጉዳዮችን ማስተማር እንደሚገባ እንረዳለን። ከአንገብጋቢዎቹ መካከልም አንዱ ሶላት ነው።
2. መምታቱ ለሥርዓት (ለማስተማር) እንጂ ለመቅጣት አይደለምና ሁኔታውን በሚመጥን መልኩ መቅጣት ይገባል።
3. ሸሪዓ ክብርን ለመጠበቅ የሰጠውን ትኩረትና ወደ ብክለት የሚያደርስን መንገድ ሁሉ መዝጋቱን እንረዳለን።

(5272)

(١٣٧) - عن أبي هريرة رضي الله عنه: سمعت رسول الله صلى الله عليه وسلم يقول: «قَالَ اللهُ تَعَالَى: قَسَمْتُ الصَّلَاةَ بَيْنِي وَبَيْنَ عَبْدِي نِصْفَيْنِ، وَلِعَبْدِي مَا سَأَلَ، فَإِذَا قَالَ الْعَبْدُ: {الْحَمْدُ لِلهِ رَبِّ الْعَالَمِينَ}، قَالَ اللهُ تَعَالَى: حَمِدَنِي عَبْدِي، وَإِذَا قَالَ: {الرَّحْمَنِ الرَّحِيمِ}، قَالَ اللهُ تَعَالَى: أَثْنَى عَلَيَّ عَبْدِي، وَإِذَا قَالَ: {مَالِكِ يَوْمِ الدِّينِ}، قَالَ: مَجَّدَنِي عَبْدِي، -وَقَالَ مَرَّةً: فَوَّضَ إِلَيَّ عَبْدِي-، فَإِذَا قَالَ: {إِيَّاكَ نَعْبُدُ وَإِيَّاكَ نَسْتَعِينُ}، قَالَ: هَذَا بَيْنِي وَبَيْنَ عَبْدِي وَلِعَبْدِي مَا سَأَلَ، فَإِذَا قَالَ: {اهْدِنَا الصِّرَاطَ الْمُسْتَقِيمَ، صِرَاطَ الَّذِينَ أَنْعَمْتَ عَلَيْهِمْ غَيْرِ الْمَغْضُوبِ عَلَيْهِمْ وَلا الضَّالِّينَ}، قَالَ: هَذَا لِعَبْدِي وَلِعَبْدِي مَا سَأَلَ». [صحيح] - [رواه مسلم]

(137) - ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ሲሉ ሰምቻቸዋለሁ ብለዋል፦ "ከፍ ያለው አላህ እንዲህ አለ: 'ሶላትን በኔና በባሪያዬ መካከል ለሁለት ከፈልኩት። ለባሪያዬም የጠየቀው አለው። ባሪያዬ {الْحَمْدُ لِلهِ رَبِّ الْعَالَمِينَ} (ምስጋና ሁሉ ለአላህ የተገባ ነው፤ የዓለማት ጌታ ለሆነው።) ያለ ጊዜ አላህ 'ባሪያዬ አመሰገነኝ!' ይላል። ባሪያው {الرَّحْمَنِ الرَّحِيمِ} (እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ ለሆነው።) ያለ ጊዜ አላህ 'ባሪያዬ እኔን አወደሰ!' ይላል። ባሪያው {مَالِكِ يَوْمِ الدِّينِ} (የፍርዱ ቀን ባለቤት ለሆነው።) ያለ ጊዜ አላህም 'ባሪያዬ አላቀኝ!' ይላል። - እንዲሁም 'ባርያዬ ጉዳዩን ወደ እኔ አስጠጋ።' - ይላል። ባሪያው {إِيَّاكَ نَعْبُدُ وَإِيَّاكَ نَسْتَعِينُ} (አንተን ብቻ እንግገዛለን፤ አንተንም ብቻ እርዳታ እንለምናለን።) ያለ ጊዜ አላህም 'ይህ በኔና በባሪያዬ መካከል ያለ ቃል ኪዳን ነው። ለባሪያዬም የጠየቀውን አለው።' ይላል። ባሪያው { اهْدِنَا الصِّرَاطَ الْمُسْتَقِيمَ، صِرَاطَ الَّذِينَ أَنْعَمْتَ عَلَيْهِمْ غَيْرِ الْمَغْضُوبِ عَلَيْهِمْ وَلا الضَّالِّينَ} (ቀጥተኛውን መንገድ ምራን፤ የእነዚያን በነርሱ ላይ በጎ የዋልክላቸውን በነሱ ላይ ያልተቆጣህባቸውንና ያልተሳሳቱትንም ሰዎች መንገድ (ምራን በሉ።) ) ያለ ጊዜ አላህም 'ይህ ለባሪያዬ ነው። ለባሪያዬም የጠየቀው አለው።' ይላል።" [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።
]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ከፍ ያለው አላህ በሐዲሠል ቁድስ እንዲህ እንዳለ ተናገሩ። "የፋቲሐን ምእራፍ በሶላት ውስጥ በኔና በባሪያዬ መካከል ለሁለት ከፈልኩት። ግማሹ ለኔ ግማሹ ለርሱ ነው።

የመጀመሪያው ክፍል: ለአላህ ምስጋና፣ ውዳሴና ልቅና ማቅረብ ሲሆን በዚህ ላይ ምርጥ ምንዳን እመነዳዋለሁ።

ሁለተኛው ክፍል: መዋደቅ፣ ዱዓ ማድረግ ሲሆን እቀበለዋለሁም የጠየቀኝንም እሰጠዋለሁ።

ሰጋጁ {الْحَمْدُ لِلهِ رَبِّ الْعَالَمِينَ} (ምስጋና ሁሉ ለአላህ የተገባ ነው፤ የዓለማት ጌታ ለሆነው።) ያለ ጊዜ አላህ "ባሪያዬ አመሰገነኝ!" ይላል። ሰጋጁ {الرَّحْمَنِ الرَّحِيمِ}(እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ ለሆነው።) ያለ ጊዜ አላህም "ባሪያዬ በኔ ላይ አወደሰ፣ አሞገሰኝም፣ በፍጡሮቼ ላይ አጠቃላይ ፀጋዎችን መዋሌንም እውቅናን ሰጠ።" ይላል። ሰጋጁ {مَالِكِ يَوْمِ الدِّينِ} (የፍርዱ ቀን ባለቤት ለሆነው።) ያለ ጊዜ አላህም "ባሪያዬ አላቀኝ!" ይላል። ይህም ትልቅ ክብር ነው።

ሰጋጁ {إِيَّاكَ نَعْبُدُ وَإِيَّاكَ نَسْتَعِينُ} (አንተን ብቻ እንግገዛለን፤ አንተንም ብቻ እርዳታ እንለምናለን።) ያለ ጊዜ አላህም: "ይህ በኔና በባሪያዬ መካከል ያለ ቃል ኪዳን ነው። ይላል።

የዚህ አንቀፅ የመጀመሪያው ግማሽ ለአላህ ነው። እሱም (አንተን ብቻ እንግገዛለን።) የሚለው ነው። ይህም በአላህ ተመላኪነት እውቅና መስጠትና በዒባዳ ምላሽ መስጠት ነው። በዚህም በአንቀፁ ውስጥ ለአላህ የሆነው የመጀመሪያው ግማሽ ይጠናቀቃል።

የአንቀፁ ሁለተኛው ግማሽ ደግሞ ለባሪያው ነው። እሱም (አንተንም ብቻ እርዳታ እንለምናለን።) የሚለው ነው። ይህም ከአላህ እገዛ መፈለግና አላህ ባሮቹን ለማገዝ የገባውን ቃልኪዳኑን መከጀል ነው።

ሰጋጁ {اهْدِنَا الصِّرَاطَ الْمُسْتَقِيمَ، صِرَاطَ الَّذِينَ أَنْعَمْتَ عَلَيْهِمْ غَيْرِ الْمَغْضُوبِ عَلَيْهِمْ وَلَا الضَّالِّينَ}(ቀጥተኛውን መንገድ ምራን፤ የእነዚያን በነርሱ ላይ በጎ የዋልክላቸውን በነሱ ላይ ያልተቆጣህባቸውንና ያልተሳሳቱትንም ሰዎች

መንገድ (ምራን በሉ።) ) ያለ ጊዜ አላህም "ይህ ከባሪያዬ የመጣ መዋደቅና ተማፅኖ ነው። ለባሪያዬም የጠየቀው አለው። ልመናውን ተቀብዬዋለሁ።" ይላል።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. የፋቲሐን ታላቅነት እንረዳለን። የላቀው አላህ "ሶላት" ብሎ ጠርቷታል።
2. ባሪያው አላህን በማመስገኑ፣ በማወደሱና በማላቁ ብቻ አላህም ባሪያውን ማወደሱ የጠየቀውንም እንደሚሰጠው ቃል መግባቱ አላህ ለባሪያው የሰጠውን ትኩረት ግልፅ ያደርግልናል።
3. ይህቺ የተከበረች ምእራፍ አላህን ማመስገንን፣ የመመለሻውን ዓለም ማስታውስን፣ አላህን መለመንን፣ አምልኮን ለአላህ ማጥራትን፣ ወደ ቀጥተኛው መንገድ መመራትን መጠየቅን፣ ከጥመት መንገዶች ማስጠንቀቅን ሰብስባለች።
4. አንድ ሰጋጅ ፋቲሐን በሚቀራ ጊዜ ይህንኑ ሐዲሥ ማስተዋሉ ሶላቱ ውስጥ የሚኖረውን ተመስጦ ይጨምርለታል።

(65099)

(١٣٨) - عن بريدة رضي الله عنه قال: قال رسول الله صلى الله عليه وسلم: «إِنَّ الْعَهْدَ الَّذِي بَيْنَنَا وَبَيْنَهُمُ الصَّلَاةُ، فَمَنْ تَرَكَهَا فَقَدْ كَفَرَ». [صحيح] - [رواه الترمذي والنسائي وابن ماجه وأحمد]

(138) - ከቡረይደህ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: "ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል: 'በኛና በነርሱ (በከሀዲዎች) መካከል ያለው (መለያ) ቃል ኪዳን ሶላት ነው። ሶላትን የተወ ሰው በርግጥም ክዷል።'"
[ሶሒሕ ነው።] - [ቲርሚዚ፣ ነሳኢ፣ ኢብኑማጀህና አሕመድ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) በሙስሊሞችና በሌሎች ከሀዲያንና መናፍቃን መካከል ያለው መተማመኛና ቃል ኪዳን ሶላት እንደሆነና ሶላትን የተወ ሰውም በርግጥ እንደካደ ገለፁ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. የሶላት ጉዳይ ትልቅ እንደሆነና በአማኝና በከሀዲ መካከል መለያም እንደሆነ እንረዳለን።
2. የሙስሊምነት ፍርድ በሰውዬው ውስጣዊ ማንነት ላይ ሳይሆን ውጫዊ ማንነቱ ላይ በመንተራስ እንደሚፀና።

(65094)

(١٣٩) - عن جابرٍ رضي الله عنه قال: سمعت النبي صلى الله عليه وسلم يقول: «إِنَّ بَيْنَ الرَّجُلِ وَبَيْنَ الشِّرْكِ وَالْكُفْرِ تَرْكَ الصَّلَاةِ». [صحيح] - [رواه مسلم]

(139) - ከጃቢር (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: "ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ሲሉ ሰምቻቸዋለሁ፦ 'በሰውየውና በሺርክ፣ በክህደት መካከል ያለው (ግርዶ) ሶላትን መተው ነው።'" [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ግዴታ ሶላትን ከመተው አስጠነቀቁ። በሰውዬውና ሺርክና ክህደት ላይ በመውደቅ መካከል ያለው ግርዶ ሶላትን መተው እንደሆነም ተናገሩ። ሶላት ከኢስላም ማእዘናቶች መካከል ሁለተኛው ማእዘን ነው፣ በኢስላም ትልቅ ጉዳይ ነው። ግዴታነቱን አስተባብሎ የተወ ሰው በሁሉም ዑለማእ (የኢስላም ሊቃውንት) ስምምነት መሰረት ክዷል። በስንፍናና ድክመት ምክንያት ሙሉ ለሙሉ የተወም እንደዚሁ ከሀዲ ነው። በዚህ ዙሪያ የሶሐቦች ሙሉ ስምምነት እንዳለም ተሰምቷል። አንዳንዴ የሚተው አንዳንዴ የሚሰግድ ከሆነ ደግሞ ለዚህ ከባድ ዛቻ የተጋረጠ ይሆናል።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ሶላትና በርሱ ላይ መጠባበቅ ያለውን አንገብጋቢነት እንረዳለን። ሶላት በክህደትና ኢማን መካከል ያለ መለያ ነው።
2. ሶላትን የተወና ያጓደሉ ሰው ላይ ብርቱ ማስጠንቀቂያ መምጣቱን እንረዳለን።

(65093)

(١٤٠) - عن سالم بن أبي الجَعْدِ قال: قال رجل: ليتني صَلَّيتُ فاسترحْتُ، فكأنّهم عابُوا ذلك عليه، فقال: سمعتُ رسولَ الله صلى الله عليه وسلم يقول: «يا بلالُ، أقِمِ الصَّلاةَ، أرِحْنا بها».
[صحيح] - [رواه أبو داود]

(140) - ከሳሊም ቢን አቢ ጀዕድ እንደተዘገበው እንዲህ አሉ: "አንድ ሰውዬ እንዲህ አለ: 'ምናለ ሰግጄ እረፍት ባገኘሁ።' አለ። ሰዎቹ በዚህ ንግግሩ ላይ ያነወሩት መስሎ ሲታይም እንዲህ አለ: 'የአላህን መልዕክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ሲሉ ሰምቻቸዋለሁ: ‹ቢላል ሆይ! ሶላትን ኢቃም ብለህ በሶላት እረፍት ስጠን።›'" [ሶሒሕ ነው።] - [አቡዳውድ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ከሶሐቦች መካከል አንዱ "ምናለ ሰግጄ እረፍት ባገኘሁ።" አለ። በዙሪያው ያሉ ሰዎች በዚህ ንግግሩ ላይ ያነወሩት መሰሉ። በዚህ ጊዜም እንዲህ አለ: "ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ሲሉ ሰምቻቸዋለሁ: 'ቢላል ሆይ! የሶላትን አዛንና ኢቃም አድርግ በርሷ እረፍት እንድናገኝ!'" ይህም ሶላት ውስጡ አላህን ማናገር፣ ለነፍስና ለቀልብ እርካታ ስላለው ነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ሶላት ውስጥ አላህን ማናገር ስላለ የቀልብ እርካታ የሚገኘው በሶላት ነው።
2. አምልኮ መፈፀም በከበደው ላይ መወገዙን እንረዳለን።
3. ያለበትን ግዴታ የተወጣና ጫንቃውን ካለበት ግዴታ ያጠራ በዚህ እርካታና የእረፍት ስሜትን ያገኛል።

(65095)

(١٤١) - عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ رضي الله عنه قَالَ: كَانَ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ، إِذَا كَبَّرَ فِي الصَّلَاةِ، سَكَتَ هُنَيَّةً قَبْلَ أَنْ يَقْرَأَ، فَقُلْتُ: يَا رَسُولَ اللهِ بِأَبِي أَنْتَ وَأُمِّي أَرَأَيْتَ سُكُوتَكَ بَيْنَ التَّكْبِيرِ وَالْقِرَاءَةِ، مَا تَقُولُ؟ قَالَ «أَقُولُ: اللهُمَّ بَاعِدْ بَيْنِي وَبَيْنَ خَطَايَايَ كَمَا بَاعَدْتَ بَيْنَ الْمَشْرِقِ وَالْمَغْرِبِ، اللهُمَّ نَقِّنِي مِنْ خَطَايَايَ كَمَا يُنَقَّى الثَّوْبُ الْأَبْيَضُ مِنَ الدَّنَسِ، اللهُمَّ اغْسِلْنِي مِنْ خَطَايَايَ بِالثَّلْجِ وَالْمَاءِ وَالْبَرَدِ».
[صحيح] - [متفق عليه]

(141) - ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: «የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ለሶላት ተክቢራ ያደረጉ ጊዜ ከመቅራታቸው በፊት ትንሽ ዝም ይሉ ነበር። እኔም የአላህ መልክተኛ ሆይ! እናትና አባቴ ፊዳ ይሁንሎና በተክቢራ እና በፋቲሓ መካከል ዝምታዎን አይቻለሁና ምንድን ነው የሚሉት? አልኳቸው። እርሳቸውም " 'አልላሁምመ ባዒድ በይኒ ወበይነ ኸጧያየ ከማ ባዐድተ በይነል መሽሪቂ ወልመግሪብ አልላሁምመ ነቂኒ ሚን ኸጧያየ ከማ ዩነቃ አሥሠውቡል አብየዱ ሚነድደነስ፣ አልላሁምመ ኢግሲልኒ ሚን ኸጧያየ ቢሥሠልጂ ወልማኢ ወልበረድ' ነው የምለው" አሉኝ። (ትርጉሙም: አላህ ሆይ! በምስራቅና በምዕራብ መካከል እንዳራራቅከው በኔና በወንጀሌ መካከል አራርቅ! አላህ ሆይ! ነጭ ልብስ ከእድፋ እንደሚጠራው እኔንም ከወንጀሎቼ አጥራኝ! አላህ ሆይ በጤዛ፣ በውሃና በበረዶ ከወንጀሎቼ እጠበኝ። ማለት ነው።)» [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ለሶላት ተክቢራ ያደረጉ ጊዜ ፋቲሓ ከመቅራታቸው በፊት ትንሽ ዝም ይሉ ነበር። በዚህ ዝም ባሉበት ወቅትም ሶላታቸውን በአንዳንድ ዱዓ ይከፍታሉ። ከነዚህ ከተላለፉልን ዱዓዎች መካከልም: "አልላሁምመ ባዒድ በይኒ ወበይነ ኸጧያየ ከማ ባዐድተ በይነል መሽሪቂ ወልመግሪብ አልላሁመ ነቂኒ ሚን ኸጧያየ ከማ ዩነቃ አሥሠውቡል አብየዱ ሚነደነስ፣ አልላሁመ ኢግሲልኒ ሚን ኸጧያየ ቢሥሠልጂ

ወልማኢ ወልበረድ።" ሰውዬው በዚህ ዱዓ በምስራቅና ምዕራብ መካከል ፈፅሞ መገናኘት እንደማይኖረው ሁሉ ከርሱ ጋር በማይገናኙ መልኩ በርሱና በወንጀሎቹ መካከልም አላህ ዐዘ ወጀል እንዲያራርቅ እና ወንጀል ላይ እንዳይወድቅ፤ ወንጀል ላይ ከወደቀ እንኳ ነጭ ልብስ ከእድፍ እንደሚጠራው ከወንጀሉ እንዲያጠራውና እንዲያስወግድለት፣ ከወንጀሉ እንዲያጥበውና የወንጀሉን ሀሩርና ወላፈንንም በውሃ፣ በጤዛና በረዶ እንዲያቀዘቅዝለት ነው ዱዓ የሚያደርገው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ሶላቱ ጮክ ተብሎ የሚቀራበት ቢሆን እንኳ ዱዓንና የሶላት መክፈቻን ዝግ አድርጎ ማድረግ እንደሚገባ እንረዳለን።
2. ሶሐቦች (ረዲየሏሁ ዐንሁም) አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና መልክተኛው (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) በእንቅስቃሴም ይሁን እርጋታ ላይ ያላቸውን ሁኔታ በማወቅ ላይ ያላቸውን ጥረት እንረዳለን።
3. ሌሎችም የመክፈቻ ዱዓዎች መጥተዋል። በላጩ ሰውዬው ከነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) የመጡትንና የፀኑትን የመክፈቻ ዱዓዎች በመከተልና በመሸምደድ አንዳንዴ ይሄንን አንዳንዴ ደግሞ ሌሎቹን እየቀያየረ ቢል ነው።

(3104)

(١٤٢) - عَنِ ابْنِ عُمَرَ رضي الله عنهما: أَنَّ رَسُولَ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ كَانَ يَرْفَعُ يَدَيْهِ حَذْوَ مَنْكِبَيْهِ إِذَا افْتَتَحَ الصَّلَاةَ، وَإِذَا كَبَّرَ لِلرُّكُوعِ، وَإِذَا رَفَعَ رَأْسَهُ مِنَ الرُّكُوعِ، رَفَعَهُمَا كَذَلِكَ أَيْضًا، وَقَالَ: «سَمِعَ اللهُ لِمَنْ حَمِدَهُ، رَبَّنَا وَلَكَ الحَمْدُ»، وَكَانَ لَا يَفْعَلُ ذَلِكَ فِي السُّجُودِ.
[صحيح] - [متفق عليه]

(142) - ከኢብኑ ዑመር (ረዲየሏሁ ዐንሁማ) -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው: «የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ሶላት በሚከፍቱበት ወቅትና ለሩኩዕ ተክቢራ በሚያደርጉ ጊዜ እጃቸውን በትከሻቸው ትይዩ ከፍ ያደርጉ ነበር። ልክ እንደዚሁ ከሩኩዕ ራሳቸውን ቀና ያደረጉ ጊዜም እጃቸውን ከፍ ያደርጉ ነበር። "ሰሚዐሏሁ ሊመን ሐሚደህ፣ ረበና ወለከል ሐምድ" ይሉም ነበር። ሱጁድ ላይ ግን ይህንን አያደርጉም ነበር።» [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ሶላት ውስጥ በሶስት ስፍራዎች በትከሻቸው ትይዩ እጃቸውን ከፍ ያደርጉ ነበር።

የመጀመሪያው ወቅት: የመክፈቻ ተክቢራ ወቅት ሶላትን የጀመሩ ጊዜ ነው።

ሁለተኛው: ለሩኩዕ ተክቢራ ያደረጉ ጊዜ ነው።

ሶስተኛው: ጭንቅላታቸውን ከሩኩዕ ቀና ያደረጉና "ሰሚዐሏሁ ሊመን ሐሚደህ ረበና ወለከል ሐምድ" ያሉ ጊዜ ነው።

ሱጁድ ማድረግ በሚጀምሩበት ወቅትም ሆነ ከሱጁድ በሚነሱበት ወቅት ግን እጃቸውን ከፍ አያደርጉም ነበር።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ሶላት ውስጥ እጆችን ከፍ ከማድረግ ጥበቦች መካከል: የሶላት ውበት መሆኑና አላህን ማላቂያ መሆኑ ተጠቃሽ ነው።

2. ከነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እጅ ከፍ የሚደረግበት አራተኛ ስፍራ መጥቷል። እሱም ከአቡ ሑመይድ አስሳዒዲይ እንደተወራውና አቡዳውድና ሌሎቹም በዘገቡት ሐዲሥ ባለሶስትና ባለአራት ረከዓ ሶላቶች ላይ የመጀመሪያውን ተሸሁድ ብለው (ለሶስተኛው ረከዓ) በሚቆምበት ወቅት ነው።
3. በተጨማሪ ከነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እጃቸውን በጆሯቸው ትይዩ ጆሯቸውን ሳይነኩ ከፍ ያደርጉ እንደነበር መጥቷል። ይህም ማሊክ ቢን ሑወይሪሥ ባስተላለፉትና ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲሥ "የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ተክቢራ ያደረጉ ጊዜ እጃቸውን በጆሯዋቸው ትይዩ እስኪሆን ድረስ ከፍ ያደርጉት ነበር።"
4. "ሰሚዐሏሁ ሊመን ሐሚደህ" እና "ረበና ለከል ሐምድ" አንድ ላይ የሚለው ኢማምና ብቻውን የሚሰግድ ሰው ብቻ ናቸው። ተከታይ የሆነ ሰው ግን "ረበና ወለከል ሐምድ" ብቻ ነው የሚለው።
5. ከሩኩዕ በኋላ "ረበና ወለከል ሐምድ" ማለት ከነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) በአራት የቃላት ይዘት የመጣ ሲሆን ይህቺም አንዷ ናት። በላጬ ግን አራቱንም የቃላት ይዘት ("ረበና ወለከል ሐምድ" ፤ "አልላሁምመ ረበና ወለከል ሐምድ" ፤ "ረበና ለከል ሐምድ" ፤ "አልላሁምመ ረበና ለከል ሐምድ") በመከታተልና በመሸምደድ አንዳንዴ በዚህ አንዳንዴ በዛ እያቀያየሩ ማለቱ ነው።

(3095)

(١٤٣) - عَنْ عُبَادَةَ بْنِ الصَّامِتِ رضي الله عنه أَنَّ رَسُولَ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ قَالَ: «لَا صَلَاةَ لِمَنْ لَمْ يَقْرَأْ بِفَاتِحَةِ الكِتَابِ». [صحيح] - [متفق عليه]

(143) - ከዑባዳህ ቢን ሷሚት (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል: "የመጽሐፉን መክፈቻ (ፋቲሓን) ያላነበበ ሰው ሶላት የለውም።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) የፋቲሓን ምዕራፍ በመቅራት ካልሆነ በቀር ሶላት ትክክለኛ እንደማትሆን ገለፁ። ፋቲሓ በሁሉም ረከዓዎች ከሚደረጉ የሶላት ማእዘናት መካከል አንዷ ናት።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ፋቲሓን መቅራት እየቻለ ፋቲሓን ከመቅራት ፋንታ ሌላ ምእራፍ መቅራት አያብቃቃም።
2. አውቆም ሆነ ሳያውቅ ወይም ረስቶ ፋቲሓ ያልተቀራበት ረከዓ የተበላሸ መሆኑን እንረዳለን። ምክንያቱም ፋቲሓ የሶላት ማእዘን ናት። ማእዘን ደግሞ በማንኛውም ሁኔታ ላይ ቢሆን አይወድቅም።
3. ተከታይ የሆነ ሰው ኢማሙን ሩኩዕ ላይ ቢደርስበት ፋቲሓን የመቅራት ግዴታው ይነሳለታል።

(5378)

(١٤٤) - عن أَبي هُرَيْرَةَ رضي الله عنه: أنه كَانَ يُكَبِّرُ فِي كُلِّ صَلَاةٍ مِنَ الْمَكْتُوبَةِ وَغَيْرِهَا، فِي رَمَضَانَ وَغَيْرِهِ، فَيُكَبِّرُ حِينَ يَقُومُ، ثُمَّ يُكَبِّرُ حِينَ يَرْكَعُ، ثُمَّ يَقُولُ: سَمِعَ اللهُ لِمَنْ حَمِدَهُ، ثُمَّ يَقُولُ: رَبَّنَا وَلَكَ الْحَمْدُ، قَبْلَ أَنْ يَسْجُدَ، ثُمَّ يَقُولُ: اللهُ أَكْبَرُ حِينَ يَهْوِي سَاجِدًا، ثُمَّ يُكَبِّرُ حِينَ يَرْفَعُ رَأْسَهُ مِنَ السُّجُودِ، ثُمَّ يُكَبِّرُ حِينَ يَسْجُدُ، ثُمَّ يُكَبِّرُ حِينَ يَرْفَعُ رَأْسَهُ مِنَ السُّجُودِ، ثُمَّ يُكَبِّرُ حِينَ يَقُومُ مِنَ الْجُلُوسِ فِي الِاثْنَتَيْنِ، وَيَفْعَلُ ذَلِكَ فِي كُلِّ رَكْعَةٍ، حَتَّى يَفْرُغَ مِنَ الصَّلَاةِ، ثُمَّ يَقُولُ حِينَ يَنْصَرِفُ: وَالَّذِي نَفْسِي بِيَدِهِ، إِنِّي لَأَقْرَبُكُمْ شَبَهًا بِصَلَاةِ رَسُولِ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ، إِنْ كَانَتْ هَذِهِ لَصَلَاتَهُ حَتَّى فَارَقَ الدُّنْيَا. [صحيح] - [متفق عليه]

(144) - ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: አቡ ሁረይራ ግዴታ ሶላቶችም ሆኑ ሱና ሶላቶች በረመዳን ውስጥም ሆነ በሌላ ወቅት በሁሉም ሶላቶች ሲሰግድ ተክቢራ ያደርግ ነበር። በሚቆም ጊዜ ተክቢራ ያደርጋል፤ ከዚያም ሩኩዕ በሚያደርግ ጊዜ ተክቢራ ያደርጋል፤ ከዚያም "ሰሚዐሏሁ ሊመን ሐሚደህ" "አላህ ላመሰገነው ሰው ሰሚ ነው።" ይላል፤ ከዚያም ሱጁድ ከመውረዱ በፊትም "ረበና ወለከል ሐምድ" "ጌታችን ላንተ ምስጋና የተገባ ነው።" ይላል፤ ከዚያም ወደ ሱጁድ በሚወርድ ጊዜም "አሏሁ አክበር" ይላል፤ ከዚያም ራሱን ከሱጁድ በሚያነሳ ጊዜም ተክቢራ ያደርጋል፤ ከዚያም መልሶ ወደ ሱጁድ በሚወርድ ጊዜም ተክቢራ ያደርጋል፤ ከዚያም መልሶ ራሱን ከሱጁድ በሚያነሳ ጊዜም ተክቢራ ያደርጋል፤ ከዚያም ከሁለተኛው ረከዐ መቀመጥ በኋላ በሚነሳ ጊዜም ተክቢራ ያደርጋል። ሶላቱን እስኪያጠናቅቅ ድረስ በየሁሉም ረከዐ ይህንን ይፈፅማል። ከዚያም በጨረሰ ጊዜ እንዲህ ይላል: " ነፍሴ በእጁ በሆነው እምላለሁ እኔ ከአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ሶላት ጋር ለመመሳሰል እጅግ የቀረበውን ሶላት የምሰግድ ነኝ። ዱንያን እስኪለያዩ ድረስ ይህቺው ነበረች አሰጋገዳቸው።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

**ትንታኔ:**

አቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - ከነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) አሰጋገድ ባህሪ ከፊሉን ተናገሩ። እርሳቸው ወደ ሶላት የቆሙ ጊዜ ተክቢረተል ኢሕራም እንደሚያደርጉ፤ ቀጥለው ወደ ሩኩዕ በሚሸጋገሩ ጊዜ፣ ሱጁድ በሚያደርጉ ጊዜ፣ ከሱጁድ ራሳቸውን በሚያነሱ ጊዜ፣ ሁለተኛውን ሱጁድ በሚወርዱ ጊዜ፣ ከርሱም ራሳቸውን ቀና በሚያደርጉበት ጊዜ፣ ባለሶስት ወይም ባለአራት ረከዓ ሶላት ውስጥ ለመጀመሪያው ተሸሁድ ከተቀመጡ በኋላ ከሁለተኛው ረከዓ ሲነሱም ተክቢራ እንደሚያደርጉ፤ ቀጥለውም ሶላቱ እስኪጠናቀቅ ድረስ በሁሉም የሶላቱ ክፍል ይህንን ይፈፅሙ እንደነበር ተናገሩ። ወገባቸውን ከሩኩዕ በሚያነሱ ጊዜም "ሰሚዐሏሁ ሊመን ሐሚደህ" ይሉ ነበር። ከዚያም ከቆሙ በኋላ "ረበና ለከል ሐምድ" ይሉ እንደነበርም ተናገሩ።

ከዚያም አቡ ሁረይራ ሶላታቸውን ያጠናቀቁ ጊዜ እንዲህ አሉ: ነፍሴ በእጁ በሆነችው ጌታ እምላለሁ! እኔ የአላህ መልዕክተኛን (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ሶላት በማመሳሰል ከናንተ እጅግ የቀረብኩኝ ነኝ። ይህቺን አለም እስከሚለያዩ ድረስም የአሰጋገዳቸው ባህሪ ይህቺው ነበረች።

**ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:**

1. ከሩኩዕ በሚነሱነት ጊዜ ካልሆነ በቀር በየሁሉም መነሳትና መውረድ መካከል ተክቢራ እንደሚደረግ እንረዳለን። ከሩኩዕ ሲነሱ ግን "ሰሚዐሏሁ ሊመን ሐሚደህ" ነው የሚባለው።
2. ሶሐቦች ነቢዩን (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) በመከተልና ሱናቸውን በመጠበቅ ላይ ያላቸውን ጉጉት እንረዳለን።

(65098)

(١٤٥) - عن ابنِ عَبَّاسٍ رضي الله عنهما عن النبيِّ صلى الله عليه وسلم قال: «أُمِرْتُ أَنْ أَسْجُدَ عَلَى سَبْعَةِ أَعْظُمٍ: عَلَى الْجَبْهَةِ وَأَشَارَ بِيَدِهِ عَلَى أَنْفِهِ، وَالْيَدَيْنِ، وَالرُّكْبَتَيْنِ، وَأَطْرَافِ الْقَدَمَيْنِ، وَلَا نَكْفِتَ الثِّيَابَ وَالشَّعَرَ». [صحيح] - [متفق عليه]

(145) - ከኢብኑ ዓባስ (ረዲየሏሁ ዐንሁማ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል: "በሰባት አጥንቶቼ ሱጁድ እንዳደርግ ታዝዣለሁ። በግንባሬ በማለት በእጃቸው ወደ አፍንጫቸው አመላከቱ፣ በሁለቱ እጆቼ፣ በሁለቱ ጉልበቴ፣ በሁለቱ እግር ጣቶቼ ፤ ልብሳችንንም ይሁን (ለወንዶች) ፀጉራችንን እንዳንሰበስብም ታዘናል።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል። ]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ሶላት ላይ በሰባት አካላቶች ሱጁድ እንዲወርዱ አላህ ያዘዛቸው መሆኑን ገለፁ።

የመጀመሪያው: ግንባር ነው። እርሱም: ከአፍንጫና ሁለት አይኖች በላይ ያለው የተዘረጋ የፊት ክፍል ነው። ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ግንባርና አፍንጫ ከሰባቱ አካላት እንደ አንድ አካል መሆናቸውን ለመግለፅና ሱጁድ አድራጊ በአፍንጫው መሬት መንካት እንዳለበት ለመግለፅ በእጃቸው ወደ አፍንጫቸው ጠቆሙ።

ሁለተኛውና ሶስተኛው አካል: ሁለት እጆች ናቸው።

አራተኛውና አምስተኛው: ሁለቱ ጉልበቶች ናቸው።

ስድስተኛውና ሰባተኛው: የሁለት እግሮች ጣቶች ናቸው።

ወደ መሬት ሱጁድ በምናደርግበት ወቅት መሬቱን እንዳይነካ ለመጠበቅ ብለን ፀጉራችንን ከመጠቅለል ወይም ልብሶቻችንን ከመሰብሰብ ከለከሉን። በተቃራኒው መሬት ላይ እንዲያርፍና ከሰውነታችን ጋር አብሮ ሱጁድ እንዲወርድ መልቀቅ እንዳለብን አዘዙን።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ሶላት ላይ በሰባት አካላት ሱጁድ ማድረግ ግዴታ መሆኑን እንረዳለን።
2. ልብስንና ፀጉርን ሶላት ውስጥ መሰብሰብና መጠቅለል እንደሚጠላ እንረዳለን።
3. አንድ ሰጋጅ ሶላት ውስጥ የመረጋጋት ግዴታ አለበት። ይህም ሰባቱን የሱጁድ አካላት መሬት ላይ በማሳረፍና የተደነገገውን ውዳሴ እስኪፈፅም ድረስ እዛው ላይ በመርጋት ነው።
4. ፀጉርን የመጠቅለል ክልከላው በወንዶች ላይ ብቻ የተገደበ ነው። ሴት ልጅ ሶላት ውስጥ እንድትሸፋፈን (እንድትሰተር) የታዘዘች ናትና።

(10925)

(١٤٦) - عَن أَبِي أُمَامَةَ قَالَ: حَدَّثَنِي عَمْرُو بْنُ عَبَسَةَ رضي الله عنه أَنَّهُ سَمِعَ النَّبِيَّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ يَقُولُ: «أَقْرَبُ مَا يَكُونُ الرَّبُّ مِنَ العَبْدِ فِي جَوْفِ اللَّيْلِ الآخِرِ، فَإِنْ اسْتَطَعْتَ أَنْ تَكُونَ مِمَّنْ يَذْكُرُ اللهَ فِي تِلْكَ السَّاعَةِ فَكُنْ». [صحيح] - [رواه أبو داود والترمذي والنسائي]

(146) - ከአቡ ኡማማ እንደተላለፈው እንዲህ አለ: «ዐምር ቢን ዐበሳህ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ሲሉ እንደሰማቸው ነገረኝ: "ጌታ ወደ ባሪያ እጅግ ቅርብ የሚሆነው በመጨረሻው የሌሊቱ አጋማሽ ነው። በዚህ ወቅት አላህን ከሚያወሱ መሆን ከቻልክ ሁን!"» [ሶሒሕ ነው።] - [አቡዳውድ፣ ቲርሚዚና ነሳኢ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ጥራት የተገባው ጌታ ወደ ባሪያ እጅግ ቅርብ የሚሆነው በመጨረሻው የሌሊቱ ሲሶ በመሆኑ አንተ አማኝ ሆይ! በዚህ ወቅት ከሚያመልኩት፣ ከሚሰግዱ፣ ከሚያወሱ፣ በወንጀላቸው ከሚፀፀቱ ሰዎች መካከል ለመሆን ከተሳካልህና ከቻልክ በዚህ ወቅት አጅር መሸመትና መታገል የሚገባ ጉዳይ መሆኑን ተናገሩ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. አንድ ሙስሊም በሌሊቱ የመጨረሻ ወቅት ላይ ዚክር እንዲያደርግ መነሳሳቱን እንረዳለን።
2. በተለያዩ ወቅቶች ዚክር ለማለት፣ ዱዓ ለማድረግና ለመስገድ አንዱ አምልኮ ከአንዱ እንደሚበላለጥ እንረዳለን።
3. "ጌታ ወደ ባሪያው እጅግ ቅርብ የሚሆነው" በሚለው ሐዲሥና "አንድ ባሪያ ወደ ጌታው እጅግ ቅርብ የሚሆነው ሱጁድ ላይ ሆኖ ነው።" በሚለው ሐዲሥ መካከል ባለው ልዩነት ሚረክ እንዲህ ብለዋል: እዛኛው ላይ የተፈለገው ጌታ ወደ ባሪያ እጅግ ቅርብ የሚሆነው የሌሊቱ አጋማሽ ላይ ሲሆን እዚህኛው ላይ የተፈለገው ደግሞ አንድ ባሪያ ካሉት ሁኔታዎች መካከል ወደ ጌታ የሚቀርበው በሱጁድ ሁኔታው መሆኑን ለመግለፅ ነው።

(3236)

(١٤٧) - عن جَرِيْر بنِ عبدِ الله رضي الله عنه قال: كُنَّا عِنْدَ النَّبِيِّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ، فَنَظَرَ إِلَى الْقَمَرِ لَيْلَةً -يَعْنِي الْبَدْرَ- فَقَالَ: «إِنَّكُمْ سَتَرَوْنَ رَبَّكُمْ كَمَا تَرَوْنَ هَذَا الْقَمَرَ، لَا تُضَامُونَ فِي رُؤْيَتِهِ، فَإِنِ اسْتَطَعْتُمْ أَنْ لَا تُغْلَبُوا عَلَى صَلَاةٍ قَبْلَ طُلُوعِ الشَّمْسِ وَقَبْلَ غُرُوبِهَا فَافْعَلُوا» ثُمَّ قَرَأَ: «{وَسَبِّحْ بِحَمْدِ رَبِّكَ قَبْلَ طُلُوعِ الشَّمْسِ وَقَبْلَ الْغُرُوبِ}» [صحيح] - [متفق عليه]

(147) - ጀሪር ቢን ዐብደላህ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንዲህ ማለታቸው ተላልፏል: "ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ዘንድ ነበርን። የ14ኛዋን ሌሊት ጨረቃ ተመለከቱና እንዲህ አሉ: ' ይህን ጨረቃ እንደምትመለከቱት ጌታችሁንም በርግጥ ታያላችሁ። እርሱን ለማየትም ምንም አትቸገሩም። ፀሀይ ከመውጣቷና ከመግባቷ በፊት ባለው ሶላት ላይ አለመሸነፍን ከቻላቹ አድርጉት።' ቀጥሎ ይህንን አንቀፅ አነበቡ: '{ጌታህንም ከማመስገን ጋር ፀሀይ ከመውጣቷ በፊት ከመግባቷም በፊት አወድሰው።}'" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

አንድ ምሽት ላይ ሶሐቦች ከነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ጋር ነበሩ። የ14ኛዋን ምሽት ጨረቃ ተመለከቱና እንዲህ አሉ: አማኞች ጌታቸውን ያለምንም ጥርጥር በዓይኖቻቸው በእውነት ያዩታል። የበላይ የሆነውን አላህ በሚያዩት ወቅት ምንም አይገፋፉምም፤ ልፋትና ችግርም አያገኛቸውም። ቀጥለውም የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ አሉ: ከፈጅር ሶላትና ከዐስር ሶላት የሚከለክሏችሁን ምክንያቶች መግታት ከቻላችሁ አድርጉት። ሁለቱንም ሶላቶች በወቅታቸው በህብረት በተሟላ መልኩ ፈፅሙ። ይህ ወደ አላህ ፊት ለመመልከት ከምክንያቶች መካከል አንዱ ነውና። ቀጥለው ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ይህቺን አንቀፅ አነበቡ: {ጌታህንም ከማመስገን ጋር ፀሀይ ከመውጣቷ በፊት ከመግባቷም በፊት አወድሰው።}

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. የኢማን ባለቤቶች ጀነት ውስጥ አላህን እንደሚመለከቱት ብስራት እንዳላቸው እንረዳለን።
2. ከዳዕዋ መንገዶች መካከል: ጉዳይን ማጠንከር፣ ማነሳሳትና ምሳሌን መጥቀስ ጥቂቶቹ ናቸው።

(5657)

(١٤٨) - عن أَبِي مُوسَى الأَشْعَرِيِّ رضي الله عنه: أَنَّ رَسُولَ اللهِ صلى الله عليه وسلم قَالَ: «مَنْ صَلَّى الْبَرْدَيْنِ دَخَلَ الْجَنَّةَ» [صحيح] - [متفق عليه]

(148) - ከአቡ ሙሳ አልአሽዐሪይ (ረዲየላሁ ዐንሁ) -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና-እንደተላለፈው የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል: "ሁለቱን ቀዝቃዛ ወቅቶች ሶላት የሰገደ ሰው ጀነት ገባ።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) የሁለቱን ቀዝቃዛ ወቅቶች ሶላት ለመስገድ በመጣር ላይ አነሳሱ። እነሱም: የፈጅርና የዐስር ሶላቶች ናቸው። በጊዜው፣ በጀመዓና ሌሎቹንም የሶላት ሐቆች አሟልቶ እነዚህን ሶላቶች የሰገደ ሰውን ጀነት መግቢያ ሰበብ እንደሚሆኑት በመንገር አበሰሩ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. የፈጅርና የዐስር ሶላት ላይ መጠባበቅ ያለውን ትሩፋት እንረዳለን። የፈጅር ሶላት ጣፋጭ እንቅልፍ የሚኖርበት ወቅት ሲሆን ዐስር ደግሞ ሰዎች በስራ የሚጠመዱበት ወቅት ነው። እነዚህን ሶላቶች ተጠባብቆ የሰገደ ሰው ሌሎቹንም ሶላቶች ተጠባብቆ መስገዱ አይቀርም።
2. የፈጅርና የዐስር ሶላት በቀዝቃዛ ወቅት የተሰየሙት የፈጅር ሶላት የምሽት ቅዝቃዜ ያለባት ወቅት ስለሆነ ሲሆን የዐስር ሶላት ደግሞ የቀኑ ቅዝቃዜ ስላለባት ነው። በሙቀት ወቅት ብትሆንም እንኳ ሙቀቷ ከርሷ በፊት

ካለው ሙቀት አንፃር ቀዝቀዝ ያለ ነው። ወይም በዚህ የተሰየመው በማቆረኘት መልኩ ነው። ልክ ለፀሀይና ለጨረቃ ሁለቱ ጨረቃዎች እንደሚባለው ማለት ነው።

(4198)

(١٤٩) - عن جُندب بن عبد الله القَسْرِي رضي الله عنه قال: قال رسول الله صلى الله عليه وسلم: «مَنْ صَلَّى صَلَاةَ الصُّبْحِ فَهُوَ فِي ذِمَّةِ اللهِ، فَلَا يَطْلُبَنَّكُمُ اللهُ مِنْ ذِمَّتِهِ بِشَيْءٍ، فَإِنَّهُ مَنْ يَطْلُبْهُ مِنْ ذِمَّتِهِ بِشَيْءٍ يُدْرِكْهُ، ثُمَّ يَكُبَّهُ عَلَى وَجْهِهِ فِي نَارِ جَهَنَّمَ». [صحيح] - [رواه مسلم]

(149) - ከጁንዱብ ቢን ዐብደላህ አልቀስሪይ -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: የአላህ መልክተኛ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንዲህ አሉ: "የሱብሒን ሶላት የሰገደ ሰው በአላህ ከለላ ስር ነው። ከናንተ አንዳችሁ በአላህ ጥበቃ ስር ያለውን ሰው በምንም መንገድ አይጉዳ። ያንን የሠራ ሰው የአላህ ቁጣ በእርግጥ ይይዘዋል ከዚያም በአፍጢሙ በጀሀነም እሳት ውስጥ ይደፋዋል።" [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም የፈጅርን ሶላት የሰገደ ሰው በአላህ ጥበቃና ከለላ ስር ስላለ እንደሚከላከልለትና እንደሚረዳው ተናገሩ።

ከዚያም ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም የፈጅርን ሶላት በመተው ወይም ሰጋጁን በመተናኮልና ሰጋጁ ላይ ወሰን በማለፍ ይህንን ከለላ ከማፍረስ አስጠነቀቁ። ይህንን የፈፀመም ይህንን ጥበቃ ስለጣሰ ለብርቱ ዛቻ የተጋለጠ ይሆናል። የአላህን ሀቅ ወሰን ስላለፈም በአላህ ይፈለጋል። አላህም የሚፈልገውን ያገኘዋል፤ ከዚያም በአፍጢሙ እሳት ውስጥ ይደፋዋል።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. የፈጅር ሶላት አንገብጋቢነትና ትሩፋቷ መገለፁን ፤
2. ፈጅር የሰገደን ሰው በሚተናኮል ላይ ብርቱ ማስጠንቀቂያ መምጣቱን ፤

3. አላህ ደጋግ ባሮቹን የሚተናኮል ሰውን እንደሚበቀል ተረድተናል።

(5435)

(١٥٠) - عن بريدة بن الحصيب رضي الله عنه أنه قال: بَكِّرُوا بِصَلَاةِ الْعَصْرِ، فَإِنَّ النَّبِيَّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ قَالَ: «مَنْ تَرَكَ صَلَاةَ الْعَصْرِ فَقَدْ حَبِطَ عَمَلُهُ». [صحيح] - [رواه البخاري]

(150) - ከቡረይዳህ ቢን ሑሰይብ -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው እንዲህ አሉ፦ "የዐስርን ሰላት ወቅቱ እንደገባ ቶሎ ስገዱ ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንዲህ ብለዋልና: ' የዐስርን ሶላት የተወ ሰው በርግጥም ስራው ተበላሸ።'" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም የዐስርን ሶላት ሆን ብሎ ወቅቱን ከማዘግየት አስጠነቀቁ። ይህንን የፈፀመ ሰው ስራው ተበላሽቶ ከንቱ ይቀራል።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. የዐስርን ሶላት በመጀመሪያ ወቅቱ በመጠባበቅ ላይና ወደዚህ ተግባር በመቻኮል ላይ መነሳሳቱ፤
2. የዐስርን ሶላት የተወ ሰው ላይ ብርቱ ዛቻ መምጣቱንና ዐስርን ከወቅቱ ማሳለፍ ሌሎችን ሶላቶች ከወቅቱ ከማሳለፍ የበለጠ እጅግ ከባድ መሆኑን እንረዳለን። የዐስር ሶላት {በሶላቶች (በተለይ) በመካከለኛይቱም ሶላት ላይ ተጠባበቁ፡፡} [አልበቀራህ: 238] በሚለው የአላህ ንግግር ላይ ባለው ትእዛዝ ልዩ ሆና የተወሳች ምርጧ ሶላት ናትና።

(6261)

(١٥١) - عن أنس بن مالك رضي الله عنه عن النبي صلى الله عليه وسلم قال: «مَنْ نَسِيَ صَلَاةً فَلْيُصَلِّ إِذَا ذَكَرَهَا، لَا كَفَّارَةَ لَهَا إِلَّا ذَلِكَ: {وَأَقِمِ الصَّلَاةَ لِذِكْرِي} [طه: 14]». [صحيح] - [متفق عليه]

(151) - ከአነስ ቢን ማሊክ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል፡- "ሶላትን የረሳ ሰው ባስታወሰው ጊዜ ይስገድ። ከዚህ በቀር ማካካሻ የለውም። {ሶላትንም (በርሷ) እኔን ለማስታወስ ስገድ።} [ጣሀ:14] [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

የትኛውንም የግዴታ ሶላት ወቅቱ እስኪወጣ ድረስ መስገድን የረሳ ሰው ባስታወሰ ወቅት ቀዷእ ለማድረግ መፍጠን እንደሚገባው፤ አንድ ሙስሊም በወቅቱ መስገድን በመተዉ ለፈፀመው ወንጀልም ባስታወሰ ወቅት መስገዱ እንጂ ሌላ ምንም ማበሻና ማስማሪያ እንደሌለው ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ገለፁ። አላህ በተከበረው መጽሐፉ እንዲህ ብሏል {ሶላትንም (በርሷ) እኔን ለማስታወስ ስገድ።} [ጣሀ:14] ማለትም የተረሳን ሶላት ባስታወስካት ወቅት ቀጥ አድርገህ ስገድ ማለትም ነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. የሶላት አንገብጋቢነት እና በወቅቱ ከመፈፀምና ቀዷእ ከማድረግ መሳነፍ እንደማይገባ መገለፁን እንረዳለን።
2. ያለሸሪዓዊ ምክንያት ሶላትን ከወቅቱ ሆን ብሎ ማዘግየት እንደማይፈቀድ እንረዳለን።
3. የረሳ ሰው ባስታወሰ ወቅት፣ የተኛ ሰው ደግሞ በነቃ ወቅት ሶላትን ቀዷእ ማድረግ ግዴታ መሆኑን እንረዳለን።
4. በተከለከለ ወቅት እንኳን ቢሆን ሶላትን በፍጥነት ቀዷእ ማድረግ ግዴታ መሆኑን እንረዳለን።

(65088)

(١٥٢) - عن أبي هريرة رضي الله عنه قال: قال رسول الله صلى الله عليه وسلم: «إِنَّ أَثْقَلَ صَلَاةٍ عَلَى الْمُنَافِقِينَ صَلَاةُ الْعِشَاءِ وَصَلَاةُ الْفَجْرِ، وَلَوْ يَعْلَمُونَ مَا فِيهِمَا لَأَتَوْهُمَا وَلَوْ حَبْوًا، وَلَقَدْ هَمَمْتُ أَنْ آمُرَ بِالصَّلَاةِ فَتُقَامَ، ثُمَّ آمُرَ رَجُلًا فَيُصَلِّيَ بِالنَّاسِ، ثُمَّ أَنْطَلِقَ مَعِي بِرِجَالٍ مَعَهُمْ حُزَمٌ مِنْ حَطَبٍ إِلَى قَوْمٍ لَا يَشْهَدُونَ الصَّلَاةَ، فَأُحَرِّقَ عَلَيْهِمْ بُيُوتَهُمْ بِالنَّارِ». [صحيح] - [متفق عليه]

(152) - ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: "የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ አሉ፦ "በመናፍቃን ላይ እጅግ ከባዱ ሶላት የዒሻእ ሶላትና የፈጅር ሶላት ናቸው። በውስጧ ያለውን ምንዳ ቢያውቁ ኖሮ እየዳሁም ቢሆን ይመጡ ነበር። በርግጥ ሶላት እንዲሰገድ አዝዤ፤ ሰዎችን እንዲያሰግድም አንድ ሰው ላዝ፤ ከዚያም ሶላትን በመስጂድ ተገኝተው ወደማይሰግዱ ሰዎች ቤት የታሰረ እንጨት ከያዙ ወንዶች ጋር በመሄድ በነሱ ላይ ቤቶቻቸውን በእሳት ላቃጥል አስቤም ነበር።"" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ስለሙናፊቆችና ሶላት መገኘት ላይ በተለይ የዒሻእና ፈጅር ሶላት ላይ ስላላቸው ስንፍና፤ እነርሱ ሁለቱን ሶላት ከሙስሊም ጀመዓ ጋር መስገድ የሚያስገኘውን አጅር እና ምንዳ መጠን ቢያውቁ ኖሮ ህፃን ልጅ በሁለት እጆቹና ጉልበቱ እንደሚዳኸው እንሱም እየዳኹ ይመጡ እንደነበር ተናገሩ።

_ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ሶላት ኢቃም እንድትባል አዘው በሳቸው ምትክ አንድ የሚያሰግድ ሰው ሊመድቡና ከዚያም የታሰረ እንጨት ከተሸከሙ ሰዎች ጋር በመሆን ጀመዓ ሶላት ወደማይገኙ ወንዶች ሂደው ጀመዓ ባለመገኘት የሰሩት ወንጀል ከባድ ስለሆነ ቤታቸውን በእሳት ሊያቃጥሉ ቆርጠው ነበር። ነገር ግን ቤት ውስጥ ንፁህ ሴቶች፣ ህፃናትና ሌሎችም የሚያስቀር ምክንያት ያላቸው ስላሉ አላደረጉትም።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ሶላተል ጀመዓን በመስጊድ ከመስገድ የመራቅ አደገኝነትን እንረዳለን።
2. ሙናፊቆች በአምልኳቸው ይዩልኝና ይስሙልኝ በስተቀር ሌላ ምንም አያስቡም። ሰዎች በሚያያቸው ጊዜ ካልሆነ በቀር ወደ ሶላት አይመጡም።
3. ከጀመዓ ጋር ዒሻና ፈጅርን የመስገድ ምንዳ ትልቅነቱን እንረዳለን። እየዳኹ እንኳ ቢሆን ወደነሱ መምጣት የተገባ ነው።
4. ዒሻና ፈጅር በመስገድ ላይ መጠባበቅ ከንፍቅና መንፃት መሆኑን ከነርሱ መቅረት ደግሞ የሙናፊቆች ባህሪ መሆኑን እንረዳለን።

(3366)

(١٥٣) - عَنِ ابْنِ أَبِي أَوْفَى رضي الله عنه قَالَ: كَانَ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ إِذَا رَفَعَ ظَهْرَهُ مِنَ الرُّكُوعِ قَالَ: «سَمِعَ اللهُ لِمَنْ حَمِدَهُ، اللَّهُمَّ رَبَّنَا لَكَ الْحَمْدُ، مِلْءَ السَّمَاوَاتِ وَمِلْءَ الْأَرْضِ وَمِلْءَ مَا شِئْتَ مِنْ شَيْءٍ بَعْدُ». [صحيح] - [رواه مسلم]

(153) - ከኢብኑ አቢ አውፋ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ከሩኩዕ ወገባቸውን ቀና ያደረጉ ጊዜ "ሰሚዐሏሁ ሊመን ሐሚደህ አላሁመ ረበና ለከል ሐምዱ ሚልአስ-ሰማዋቲ ወልአርድ ወሚልአ ማ ሺእተ ሚን ሸይኢን በዕዱ" ይሉ ነበር። ትርጉሙም "አላህ ላመሰገነው ሰው ሰሚ ነው። አላህ ሆይ! ሰማያትን የሞላ፣ ምድርን የሞላ፣ ከነዚህም በኋላ ያሉ የፈለግከውን ነገሮችን የሞላ ምስጋና ላንተ የተገባ ነው።" [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ሶላት ውስጥ ከሩኩዕ ወገባቸውን ቀና ያደረጉ ጊዜ "ሰሚዐሏሁ ሊመን ሐሚደህ" ይሉ ነበር። አላህን ያመሰገነ ሰው አላህ ይቀበለዋል፤ ምስጋናውን ተቀብሎ ይመነዳዋል ማለት ነው። ከዚያም "አላሁመ ረበና ለከል ሐምዱ ሚልአስ-ሰማዋቲ ወልአርድ

ወሚልአ ማ ሺእተ ሚን ሸይኢን በዕዱ" በሚለው ንግግራቸው ሰማያትን፣ ምድሮችን፣ በመካከላቸው ያለውን፣ አላህ የሻውን ነገርንም ሁሉ በሚሞላ ምስጋና አላህን ያመሰግናል።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ሰጋጅ የሆነ ሰው ራሱን ከሩኩዕ ቀና ያደረገ ጊዜ ማለቱ የሚወደድለት ዚክር መገለፁ።
2. ከሩኩዕ ከተነሳ በኋላ መረጋጋትና ቀጥ ማለት መደንገጉን እንረዳለን። ምክንያቱም ይህን ዚክር ቀጥ ብሎና ተረጋግቶ ካልሆነ በቀር ማለቱም አይመችምና።
3. በሁሉም ሰላቶች ግዴታም ሆነ ሱና ሰላት ይህንኑ ዚክር ማለቱ የተደነገገ መሆኑን እንረዳለን።

(65101)

(١٥٤) - عن حُذَيْفَةَ رضي الله عنه: أَنَّ النَّبِيَّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ كَانَ يَقُولُ بَيْنَ السَّجْدَتَيْنِ: «رَبِّ اغْفِرْ لِي، رَبِّ اغْفِرْ لِي». [صحيح] - [رواه أبو داود والنسائي وابن ماجه وأحمد]

(154) - ከሑዘይፋ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: "ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) በሁለቱ ሱጁዶች መካከል 'ረቢግፊርሊ ረቢግፊርሊ' 'ጌታዬ ሆይ! ማረኝ! ጌታዬ ሆይ! ማረኝ!' ይሉ ነበር።" [ሶሒሕ ነው።] - [አቡዳውድ፣ ነሳኢ፣ ኢብኑማጀህና አሕመድ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) በሁለቱ ሱጁዶች መካከል በሚቀመጡ ጊዜ "ረቢግፊርሊ ረቢግፊርሊ" "ጌታዬ ሆይ! ማረኝ! ጌታዬ ሆይ! ማረኝ!" ይሉ ነበር። ይደጋግሟትም ነበር።

"ረቢግፊርሊ" ማለት አንድ ባሪያ ከጌታው ወንጀሎቹን እንዲምረውና ነውሮቹን እንዲሸሽግለት መፈለጉ ነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. በግዴታም ሆነ ሱና ሶላት ውስጥ በሁለቱ ሱጁዶች መካከል ይህንን ዱዓ ማድረግ የተደነገገ መሆኑን እንረዳለን።
2. "ረቢግፊርሊ" "ጌታዬ ሆይ! ማረኝ" የሚለውን ዚክር መደጋገም እንደሚወደድ እንረዳለን። ግዴታው ግን አንድ ጊዜ ማለት ነው።

(65104)

(١٥٥) - عن ابن عباس رضي الله عنهما: كان النبي صلى الله عليه وسلم يقول بين السجدتين:
«اللَّهمَّ اغْفِرْ لي، وارْحَمْنِي، وعافِنِي، واهْدِنِي، وارزقْنِي».
[حسن بشواهده] - [رواه أبو داود والترمذي وابن ماجه وأحمد]

(155) - ከኢብኑ ዐባስ -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም በሁለቱ ሱጁዶች መካከል "አላሁመግፊር ሊ ወርሐምኒ ወዓፊኒ ወህዲኒ ወርዙቅኒ" (አላህ ሆይ! ማረኝ፣ እዘንልኝም፣ ጤናን ለግሰኝም፣ ምራኝም፣ ሲሳይን ለግሰኝም) ይሉ ነበር። [በማመሳከሪያዎቹ ሐሰን ነው።] - [አቡዳውድ፣ ቲርሚዚ፣ ኢብኑማጀህና አሕመድ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም በሶላታቸው ውስጥ በሁለቱ ሱጁዶች መካከል ሙስሊም የሆነ ሰው በእጅጉ የሚፈልጋቸው ጉዳዮችንና የዱንያንም ሆነ የአኺራን መልካም የሰበሰቡ የሆኑትን: ምህረትን፤ የወንጀል መሸሸግን፤ ይቅር መባልን መፈለግ፤ እዝነቱ እንዲያዳርሰው መፈለግ ፤ ከሚያምታታ፣ ዝንባሌው ከሚገፋፋውና ከበሽታዎችም ጤናማ መሆንን መፈለግ ፤ አላህን ለእውነትና በርሱ ላይ በመፅናት ላይ እንዲመራው መጠየቅ፤ የኢማን፣ የእውቀት ፣ የመልካም ስራ፣ ምርጥና ሐላል የገንዘብ ሲሳይ እንዲለግሰው መለመንን ሁሉ ያጠቃለሉ የሆኑትን እነዚህ አምስት ዱዓዎችን ይለምኑ ነበር።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. በሁለቱ ሱጁዶች መካከል በምንቀመጥ ወቅት ይህ ዱዓእ መደንገጉን እንረዳለን።
2. ይህ ዱዓእ የዱንያንም ሆነ የአኺራን መልካም ነገሮች ስለጠቀለለ የዚህ ዱዓን ትሩፋትንም እንረዳለን።

(10930)

(١٥٦) - عَنْ حِطَّانَ بْنِ عَبْدِ اللهِ الرَّقَاشِيِّ قَالَ: صَلَّيْتُ مَعَ أَبِي مُوسَى الْأَشْعَرِيِّ صَلَاةً، فَلَمَّا كَانَ عِنْدَ الْقَعْدَةِ قَالَ رَجُلٌ مِنَ الْقَوْمِ: أُقِرَّتِ الصَّلَاةُ بِالْبِرِّ وَالزَّكَاةِ، قَالَ: فَلَمَّا قَضَى أَبُو مُوسَى الصَّلَاةَ وَسَلَّمَ انْصَرَفَ فَقَالَ: أَيُّكُمُ الْقَائِلُ كَلِمَةَ كَذَا وَكَذَا؟ قَالَ: فَأَرَمَّ الْقَوْمُ، ثُمَّ قَالَ: أَيُّكُمُ الْقَائِلُ كَلِمَةَ كَذَا وَكَذَا؟ فَأَرَمَّ الْقَوْمُ، فَقَالَ: لَعَلَّكَ يَا حِطَّانُ قُلْتَهَا؟ قَالَ: مَا قُلْتُهَا، وَلَقَدْ رَهِبْتُ أَنْ تَبْكَعَنِي بِهَا، فَقَالَ رَجُلٌ مِنَ الْقَوْمِ: أَنَا قُلْتُهَا، وَلَمْ أُرِدْ بِهَا إِلَّا الْخَيْرَ، فَقَالَ أَبُو مُوسَى: أَمَا تَعْلَمُونَ كَيْفَ تَقُولُونَ فِي صَلَاتِكُمْ؟ إِنَّ رَسُولَ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ خَطَبَنَا فَبَيَّنَ لَنَا سُنَّتَنَا وَعَلَّمَنَا صَلَاتَنَا، فَقَالَ: «إِذَا صَلَّيْتُمْ فَأَقِيمُوا صُفُوفَكُمْ، ثُمَّ لِيَؤُمَّكُمْ أَحَدُكُمْ فَإِذَا كَبَّرَ فَكَبِّرُوا، وَإِذْ قَالَ: {غَيْرِ الْمَغْضُوبِ عَلَيْهِمْ وَلَا الضَّالِّينَ} [الفاتحة: 7]، فَقُولُوا: آمِينَ، يُجِبْكُمُ اللهُ، فَإِذَا كَبَّرَ وَرَكَعَ فَكَبِّرُوا وَارْكَعُوا، فَإِنَّ الْإِمَامَ يَرْكَعُ قَبْلَكُمْ، وَيَرْفَعُ قَبْلَكُمْ»، فَقَالَ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ: «فَتِلْكَ بِتِلْكَ، وَإِذَا قَالَ: سَمِعَ اللهُ لِمَنْ حَمِدَهُ، فَقُولُوا: اللَّهُمَّ رَبَّنَا لَكَ الْحَمْدُ، يَسْمَعِ اللهُ لَكُمْ، فَإِنَّ اللهَ تَبَارَكَ وَتَعَالَى قَالَ عَلَى لِسَانِ نَبِيِّهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ: سَمِعَ اللهُ لِمَنْ حَمِدَهُ، وَإِذَا كَبَّرَ وَسَجَدَ فَكَبِّرُوا وَاسْجُدُوا، فَإِنَّ الْإِمَامَ يَسْجُدُ قَبْلَكُمْ وَيَرْفَعُ قَبْلَكُمْ»، فَقَالَ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ: «فَتِلْكَ بِتِلْكَ، وَإِذَا كَانَ عِنْدَ الْقَعْدَةِ فَلْيَكُنْ مِنْ أَوَّلِ قَوْلِ أَحَدِكُمُ: التَّحِيَّاتُ الطَّيِّبَاتُ الصَّلَوَاتُ لِلَّهِ، السَّلَامُ عَلَيْكَ أَيُّهَا النَّبِيُّ وَرَحْمَةُ اللهِ وَبَرَكَاتُهُ، السَّلَامُ عَلَيْنَا وَعَلَى عِبَادِ اللهِ الصَّالِحِينَ، أَشْهَدُ أَنْ لَا إِلَهَ إِلَّا اللهُ وَأَشْهَدُ أَنَّ مُحَمَّدًا عَبْدُهُ وَرَسُولُهُ». [صحيح] - [رواه مسلم]

(156) - ከሒጥጧን ቢን ዐብደሏህ አርረቃሺይ እንደተላለፈው እንዲህ ብሏል: "ከአቡ ሙሳ አልአሽዐሪይ ጋር ሶላትን ሰገድኩ። ልክ ተሸሁድ ላይ የደረሱ ጊዜም ከሰዎች መካከል አንድ ሰውዬ 'ሶላት ከበጎነትና ከዘካ ጋር ተቆራኘች።' አለ። አቡ

ሙሳ ሶላቱን አጠናቆ አሰላመተና ወደ ሰዎች በመዞር 'እንዲህ እንዲህ የሚል ንግግር የተናገረው ማነው?' አለ። ሰዎቹም ዝም አሉ። በድጋሚ 'እንዲህ እንዲህ የሚል ንግግር የተናገረው ማነው?' አለ። አሁንም ሰዎቹ ዝም አሉ። አቡ ሙሳም 'ሒጧን ሆይ! አንተ ነህ መሰለኝ ይህን የተናገርከው?' አለኝ። ሒጧንም 'እኔ አላልኩም! በሷ ምክንያት ትወቅሰኛለህ ብዬ እኔም ፈርቼ ነበር።' አለ። በዚህ ወቅት ከሰዎቹ መካከል አንድ ሰውዬ 'እኔ ነኝ ያልኩት። መልካምን እንጂ ሌላ አልፈለግኩበትም።' አለ። አቡ ሙሳም 'ሶላታችሁ ውስጥ እንዴት እንደምትሉ አታውቁምን? የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ኹጥባ አደረጉ። ለኛ ሱናቸውን ገለፁልን አሰጋገዳችንንም አስተማሩን።' እንዲህም አሉን: ‹ሶላትን መስገድ የፈለጋችሁ ጊዜ ሰልፋችሁን አስተካክሉ። ከዚያም አንድ ሰው ይምራችሁ። ኢማሙ ተክቢራ ያደረገ ጊዜ እናንተም ተክቢራ አድርጉ! ፣ {غَيرِ المَغضوبِ عَلَيهِم وَلَا الضّالّينَ} [አልፋቲሐ:7] ያለ ጊዜ አሚን በሉ አላህ ይቀበላችኋልና፤ ተክቢራ አድርጎ ሩኩዕ ያደረገ ጊዜ እናንተም ተክቢራ አድርጋችሁ ሩኩዕ አድርጉ። ኢማሙ ከናንተ በፊት ሩኩዕ ያድርግ ከናንተ በፊትም ቀና ይበል።› የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህም አሉ "ይህቺ (ኢማሙ ቀና ያለበት ቅፅበት) በዚህች (እናንተ ከኢማሙ ከዘገያችሁበት) ጋር ይካካሳል ፤ ኢማሙ 'ሰሚዐሏሁ ሊመን ሐሚደህ' ያለ ጊዜ 'አላሁመ ረበና ለከል ሐምድ' በሉ። አላህ ይሰማችኋልና። የጠራውና ከፍያለው አላህ በነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) አንደበት 'ሰሚዐሏሁ ሊመን ሐሚደህ' 'አላህ ያመሰገነውን ሰሚ ነው' ብሏልና። ኢማሙ ተክቢራ አድርጎ ሱጁድ የወረደ ጊዜ እናንተም ተክቢራ አድርጋችሁ ሱጁድ ውረዱ። ኢማሙ ከናንተ በፊት ሱጁድ ይውረድ ከናንተ በፊትም ቀና ይበል። የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህም አሉ 'ይህቺ (ኢማሙ ሱጁድ ሲወርድ የቀደማቹ ቅፅበት) በዚህች (እናንተ እርሱ ቀና ሲል በምትዘገዩት ቅፅበት) ይካካሳል።' የምትቀመጡበት በሆነ ወቅት የአንዳችሁ የመጀመሪያ ቃሉ 'አትተሒይያቱ፣ አጥጦይዪባቱ፣ አስሶለዋቱ ሊላሂ አስሰላሙ ዐለይከ አይዩሀን-

ነቢዩ ወረሕመቱላሂ ወበረካቱሁ አስሰላሙ ዐለይና ወዐላ ዒባዲልላሂ አስሷሊሒን አሽሀዱ አንላ ኢላሀ ኢለሏህ ወአሽሀዱ አንነ ሙሐመደን ዐብዱሁ ወረሱሉህ' ይሁን። ትርጉሙም 'ክብሮች ባጠቃላይ፣ ጥሩ ነገሮች ባጠቃላይ፣ ሶላቶች ባጠቃላይ ለአላህ የተገቡ ናቸው። አንቱ ነቢይ ሆይ ሰላም፣ የአላህ እዝነትና በረከቱ በርሶ ላይ ይሁን። ሰላም በኛ ላይና በአላህ ደጋግ ባሮች ላይም ይስፈን። ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ። ሙሐመድም የአላህ ባሪያና መልዕክተኛው መሆናቸውንም እመሰክራለሁ።' ማለት ነው።›" [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ሶሐቢዩ አቡ ሙሳ አልአሽዐሪይ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - ሶላትን አሰገዱ። ተሸሁድ በሚባልበት ስፍራ ላይ የደረሱ ጊዜም ከኋላቸው ከሚሰግዱ ሰጋጆች መካከል አንዱ "ቁርአን ውስጥ ሶላት ከበጎነትና ዘካ ጋር ተቆራኘች።" አለ። አቡ ሙሳ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - ሶላቱ ባጠናቀቁ ጊዜ ወደ ተከታዮቹ በመዞር "ከመካከላችሁ 'ቁርአን ውስጥ ሶላት ከበጎነትና ዘካ ጋር ተቆራኘች።' ብሎ የተናገረው ማን ነው?" በማለት ጠየቋቸው። ሰዎቹም ዝም አሉ። ከነርሱ ውስጥ ማንም አልተናገረም። ጥያቄያቸውን ለሁለተኛ ጊዜ ደገሙት። አቡ ሙሳ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - የሚመልስላቸው ያጡ ጊዜ ደፋርነቱን ስለሚያውቁ፣ ከርሳቸው ጋር ቅርርብና ትስስር ስላለው መጠርጠሩ በማያስከፋው መልኩ ትክክለኛውን ተናጋሪ ለማጋለጥ "ሒጧን ሆይ! አንተ ነህ መሰለኝ ያልከው?" አሉ። ሒጧንም አለመናገሩን በመግለፅ ከራሱ ላይ ለመከላከል እንዲህ አለ: "እኔም የተናገርኩ መስሎህ ትወቅሰኛለህ ብዬ ፈርቼ ነበር።" በዚህ ወቅት ከሰዎቹ መካከል አንዱ እንዲህ አለ "እኔ ነኝ ያልኩት መልካምን አስቤ እንጂ አልተናገርኩም።" አቡ ሙሳም እሱን እያወገዙ ለማስተማር እንዲህ አሉ: "ሶላታችሁ ውስጥ ምን እንደምትሉ አታውቁምን?" ቀጥለውም አቡ ሙሳ ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም

በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) አንድ ጊዜ ኹጥባ እንዳደረጉላቸውና ሸሪዓውን እንዳብራሩላቸው፣ ሶላታቸውንም እንዳስተማሯቸው ተናገሩ። ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ አሉ:

"የሰገዳችሁ ጊዜ ሰልፋችሁን አስተካክሉ፣ ቀጥ በሉ ከዚያም ከመካከላቸው አንዱ ሰዎችን ይምራ። ኢማሙ የመክፈቻ ተክቢራ ያለ ጊዜ እንደርሱ አምሳያ ተክቢራ አድርጉ፤ ፋቲሐን የቀራ ጊዜና {غَيرِ المَغضوبِ عَلَيهِم وَلَا الضّالّينَ} [አልፋቲሐ:7] የሚለው ጋር የደረሰ ጊዜ አሚን በሉ ይህንን ከፈፀማችሁ አላህ ዱዓችሁን ይቀበላችኋልና፤ ኢማሙ ተክቢራ አድርጎ ሩኩዕ ያደረገ ጊዜ እናንተም ተክቢራ አድርጋችሁ ሩኩዕ አድርጉ። ኢማሙ ከናንተ በፊት ሩኩዕ ያደርጋል ከናንተ በፊትም ቀና ይላልና እንዳትቀድሙት። ኢማሙ ወደ ሩኩዕ ሲወርድ የቀደማችሁ ቅፅበት እናንተ ኢማሙ ቀና በሚልበት ቅፅበት ወቅት ሩኩዕ ላይ በመዘግየታችሁ ይካካሳል። ያቺ ቅፅበት በዚህች ቅፅበት ትካካሳለች። በዚህ የናንተም የሩኩዕ ቆይታ እንደርሱ የሩኩዕ ቆይታ ይሆናል። ኢማሙ 'ሰሚዐሏሁ ሊመን ሐሚደህ' ያለ ጊዜ 'አላሁመ ረበና ለከል ሐምድ' በሉ። ሰጋጆች ይህንን ያሉ ጊዜ አላህ ዱዓቸውንና ንግግራቸውን ይሰማቸዋል። ምክንያቱም የጠራውና ከፍያለው አላህ በነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) አንደበት 'ሰሚዐሏሁ ሊመን ሐሚደህ' 'አላህ ያመሰገነውን ሰሚ ነው' ብሏልና። ቀጥሎ ኢማሙ ተክቢራ አድርጎ ሱጁድ የወረደ ጊዜ ተከታዮቹም ተክቢራ አድርገው ሱጁድ መውረድ ይገባቸዋል። ኢማሙ ሱጁድ የሚወርደውም ሆነ የሚነሳው ከነርሱ በፊት ነውና። ያቺ ቅፅበት በዚህች ቅፅበት ትካካሳለች። የተከታዩ (የመእሙሙ) የሱጁድ መጠን እንደ ኢማሙ የሱጁድ መጠን ይሆናል። ለተሸሁድ የተቀመጠ ጊዜ የሰጋጅ የመጀመሪያ ቃሉ እንዲህ ማለት ይሁን: 'አትተሒይያቱ፣ አጥጦይዪባቱ፣ አስሶለዋቱ ሊላሂ'፤ 'ንግስና፣ ዘውታሪነትና ልቅና ሁሉ እንዲሁም አምስቱ ሶላቶችም ለአላህ የተገቡ ናቸው።' 'አስሰለሰሙ ዐለይከ አይዩሀን-ነቢዩ ወረሕመቱላሂ ወበረካቱሁ አስሰላሙ ዐለይና ወዐላ ዒባዲልላሂ አስሷሊሒን' ከሁሉም ነውር፣ መከራ፣ ጉድለትና ብልሽት ሰላም እንዲያደርጋችሁ አላህን ተማፀኑ። ነቢያችንን

ሙሐመድ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) በሰላምታ ለብቻ እንነጥላቸዋለን። ከዚያም ከአላህ ሀቆችና ከባሮቹ ሀቆች ያለባቸው ግዴታዎችን በተወጡ የአላህ ደጋግ ባሪያዎች ላይም ሰላም እንዲሰፍን ዱዐ እናደርጋለን። ከዚያም ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ እንደሌለና ሙሐመድም የአላህ ባሪያና መልዕክተኛው እንደሆኑ እንመሰክራለን።"

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ከተሸሁድ አባባች መካከል አንዱ አባባል መገለፁን እንረዳለን።
2. የሶላት ድርጊቶችና ንግግሮች ከነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) የተረጋገጠ መሆኑ የግድ ነው። ለአንድም ሰው በሶላት ውስጥ በሱና ያልተረጋገጠን ቃል ወይም ድርጊት መፈልሰፍ እንደማይፈቀድ እንረዳለን።
3. ኢማምን መቅደምም ሆነ ከርሱ መዘግየት እንደማይፈቀድ እንረዳለን። ለተከታይ የተደነገገው ኢማምን በድርጊቶች መከተሉ ነው።
4. ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ዲኑን ለማድረስና ለኡመታቸው የዲን ህግጋትን ለማስተማር የሰጡት ትኩረት መወሳቱን እንረዳለን።
5. ኢማም ለተከታይ መሪ ስለሆነ ተከታይ ከኢማሙ ጋር በሶላት ድርጊቶች ሊቀድመው፣ እኩል ሊሆንና ሊዘገይ አይፈቀድለትም። በተቃራኒ የመከተሉ ጅማሮ መሆን ያለበት ሊሰራው ወደ ፈለገው ድርጊት ኢማሙ መግባቱን እርግጠኛ ከሆነ በኋላ ነው። ሱናው በሶላት ድርጊቶች ኢማሙን መከተል ነው።
6. በሶላት ውስጥ ሰልፎችን ማስተካከል መደንገጉን እንረዳለን።

(65097)

(١٥٧) - عَنِ ابْنَ مَسْعُودٍ رضي الله عنه قَالَ: عَلَّمَنِي رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ، وَكَفِّي بَيْنَ كَفَّيْهِ، التَّشَهُّدَ، كَمَا يُعَلِّمُنِي السُّورَةَ مِنَ القُرْآنِ: «التَّحِيَّاتُ لِلَّهِ وَالصَّلَوَاتُ وَالطَّيِّبَاتُ، السَّلَامُ عَلَيْكَ أَيُّهَا النَّبِيُّ وَرَحْمَةُ اللهِ وَبَرَكَاتُهُ، السَّلَامُ عَلَيْنَا وَعَلَى عِبَادِ اللهِ الصَّالِحِينَ، أَشْهَدُ أَنْ لاَ إِلَهَ إِلَّا اللهُ، وَأَشْهَدُ أَنَّ مُحَمَّدًا عَبْدُهُ وَرَسُولُهُ».

وفي لفظ لهما: «إِنَّ اللهَ هُوَ السَّلَامُ، فَإِذَا قَعَدَ أَحَدُكُمْ فِي الصَّلَاةِ فَلْيَقُلْ: التَّحِيَّاتُ لِلَّهِ وَالصَّلَوَاتُ وَالطَّيِّبَاتُ السَّلَامُ عَلَيْكَ أَيُّهَا النَّبِيُّ وَرَحْمَةُ اللهِ وَبَرَكَاتُهُ، السَّلَامُ عَلَيْنَا وَعَلَى عِبَادِ اللهِ الصَّالِحِينَ، فَإِذَا قَالَهَا أَصَابَتْ كُلَّ عَبْدٍ لِلَّهِ صَالِحٍ فِي السَّمَاءِ وَالْأَرْضِ، أَشْهَدُ أَنْ لَا إِلَهَ إِلَّا اللهُ، وَأَشْهَدُ أَنَّ مُحَمَّدًا عَبْدُهُ وَرَسُولُهُ، ثُمَّ يَتَخَيَّرُ مِنَ الْمَسْأَلَةِ مَا شَاءَ». [صحيح] - [متفق عليه]

(157) - ከኢብኑ መስዑድ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: "የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እጄ በእጃቸው መካከል ሆኖ አንድን የቁርአን ምእራፍ እንደሚያስተምሩኝ ተሸሁድን አስተማሩኝ። 'አትተሒይያቱ ሊላሂ ወስሶለዋቱ ወጥጦይዪባቱ አስ-ሰላሙ ዐለይከ አይዩሃን-ነቢዩ ወረሕመቱሏሂ ወበረካቱህ፤ አስ-ሰላሙ ዐለይና ወዓላ ዒባዲልላሂ አስ-ሷሊሒን፤ አሽሀዱ አን ላኢላሃ ኢለሏህ ወአሽሀዱ አንነ ሙሐመደን ዐብዱሁ ወረሱሉህ' (ትርጉሙም: "ክብርና ልዕልና እንዲሁም ሶላቶችና መልካም ነገሮች ሁሉ ለአላህ ናቸው። አንቱ ነቢዩ ሆይ! የአላህ ሰላም፣ እዝነቱና በረከቶች በእርሶ ላይ ይስፈን ፤ ሰላም በእኛና በአላህ ደጋግ ባሮችም ላይ ይስፈን፤ ከአላህ ሌላ በእውነት የሚመለክ አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፤ ሙሐመድም የአላህ አገልጋይና መልዕክተኛ መሆናቸውን እመሰክራለሁ።"።)" በሌላ የቡኻሪና ሙስሊም ዘገባ "አላህ እርሱ ሰላም ነው። አንዳችሁ ሶላት ላይ በተቀመጠ ወቅት 'አትተሒይያቱ ሊላሂ ወስሶለዋቱ ወጥጦይዪባቱ አስሰላሙ ዐለይከ አይዩሃን-ነቢዩ ወረሕመቱሏሂ ወበረካቱህ፤ አስሰላሙ ዐለይና ወዓላ ዒባዲልላሂ አስሷሊሒን' ይበል። ይህንን ያለ ጊዜ በሰማይም ውስጥ ሆነ በምድር ውስጥ የሚገኝ ደግ የአላህ ባሪያ ሁሉ ዱዓው ይደርሰዋል። ቀጥሎ 'አሽሀዱ አን ላኢላሃ

ኢለሏህ ወአሽሀዱ አንነ ሙሐመደን ዐብዱሁ ወረሱሉህ' ይበል ከዚያም የፈለገውን ዱዓእ መርጦ ያድርግ!" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

**ትንታኔ:**

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ለኢብኑ መስዑድ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና አንድ የቁርኣን ምእራፍ እንደሚያስተምሩት ትኩረቱ ወደርሳቸው ለመሰብሰብ እጁን በእጃቸው ውስጥ አድርገው ሶላት ውስጥ የሚባለውን ተሸሁድ አስተማሩት። ይህም ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ለተሸሁድ በቃል ደረጃም ይሁን በመልዕክት ደረጃ የሰጡትን ትኩረት የሚጠቁም ነው። እንዲህም አሉ: "አትተሒይያቱ ሊላህ... " ይህ ማለት: ክብርና ልቅናን የሚጠቁም ንግግርም ይሁን ተግባር ሁሉ ለአላህ የተገባ ነው ማለት ነው። "... አስሶለዋቱ... " ይህም ማለት የታወቁት ግዴታ ሶላቶችም ይሁኑ ሱና ሶላቶች ለአላህ ናቸው ነው። "... አጥጦይዪባቱ... " ይህም ማለት: ምሉዕነትን የሚጠቁሙ ጥሩ ንግግሮች፣ ተግባሮችና ባህሪያቶች ሁሉ ለአላህ የተገቡ ናቸው ማለት ነው። "... አስሰላሙ ዐለይከ አይዩሀን-ነቢዩ ወረሕመቱሏሂ ወበረካቱህ... " "አንቱ ነቢይ ሆይ! ሰላም፣ የአላህ እዝነትና በረከቱ በርሶ ላይ ይሁን" ይህም ለርሳቸው ከሁሉም መከራና ጉዳት ሰላም እንዲሆኑና ሁሉም መልካም ነገሮች እንዲጨምርላቸውና እንዲበዛላቸው የምናደርገው ዱዓእ ነው። "... አስሰላሙ ዐለይና ወዓላ ዒባዲልላሂ አስሷሊሒን... " (በአላህ ደጋግ ባሮችና በኛ ላይም ሰላም ይስፈን።) ይህም በሰማይ ውስጥም ሆነ በምድር ውስጥ ለሚገኝ ደግ ባሪያና ለሰጋጁ ሁሉ ሰላም እንዲሰፍንበት የሚደረግ ዱዓእ ነው። ... አሽሀዱ አን ላኢላሃ ኢለሏህ... " "ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ እንደሌለ እመሰክራለሁ።" ማለትም ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ እንደሌለ ቁርጥ የሆነ ማረጋገጥን አረጋግጣለሁ ማለት ነው። "... ወአንነ ሙሐመደን ዐብዱሁ ወረሱሉህ" "ሙሐመድ የአላህ ባሪያና መልክተኛ

መሆናቸውን እመሰክራለሁ።" ማለትም: ለርሳቸው በባርነትና በመጨረሻ መልዕክተኛነት አረጋግጣለሁ።

ቀጥለውም ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ሰጋጁ የፈለገውን ዱዓእ እንዲመርጥ አነሳሱ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. በሁሉም ሶላት ውስጥ የዚህ ተሸሁድ ስፍራው ከመጨረሻው ሱጁድ በኋላ በምንቀመጥበት ወቅት እና ባለ ሶስትና አራት ረከዓ ሶላት ከሆነ ደግሞ ከሁለተኛው ረከዓ በኋላም ነው።
2. በተሸሁድ ወቅት "አትተሒያቱ" ግዴታ መሆኑን እንረዳለን። ከነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ከተረጋገጡ የተሸሁድ ቃላቶች መካከል በማንኛውም ቢጠቀም ይበቃለታል።
3. ሶላት ውስጥ በወንጀል እስካልሆነ ድረስ በማንኛውም ደስ ባለው ዱዓእ ማድረግ እንደሚፈቀድ እንረዳለን።
4. ዱዓ ላይ ከነፍስ መጀመር እንደሚወደድ እንረዳለን።

(3096)

(١٥٨) - عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ رَضِيَ اللهُ عَنْهُ قَالَ: كَانَ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ يَدْعُو وَيَقُولُ: «اللَّهُمَّ إِنِّي أَعُوذُ بِكَ مِنْ عَذَابِ القَبْرِ، وَمِنْ عَذَابِ النَّارِ، وَمِنْ فِتْنَةِ المَحْيَا وَالمَمَاتِ، وَمِنْ فِتْنَةِ المَسِيحِ الدَّجَّالِ».

وفِي لَفْظٍ لِمُسْلِمٍ: «إِذَا فَرَغَ أَحَدُكُمْ مِنَ التَّشَهُّدِ الْآخِرِ، فَلْيَتَعَوَّذْ بِاللهِ مِنْ أَرْبَعٍ: مِنْ عَذَابِ جَهَنَّمَ، وَمِنْ عَذَابِ الْقَبْرِ، وَمِنْ فِتْنَةِ الْمَحْيَا وَالْمَمَاتِ، وَمِنْ شَرِّ الْمَسِيحِ الدَّجَّالِ». [صحيح] - [متفق عليه]

(158) - ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ ብለዋል፡- "የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና): 'አሏሁመ ኢኒ አዑዙ ቢከ ሚን ዓዛቢል ቀብሪ ወሚን ዓዛቢ-ን-ናር ወሚን ፊትነቲል መሕያ ወል መማት ወሚን ፊትነቲል መሲሒ-ድ-ደጃል' 'ትርጉሙም: አላህ ሆይ! እኔ ከቀብር ቅጣት፣

ከእሳት ቅጣት፣ ከህይወትና ሞት ፈተና እና ከመሲሕ ደጃል ፈተና ባንተው እጠበቃለሁ።' እያሉ ዱዓእ ያደርጉ ነበር።" በሙስሊም ዘገባ 'አንዳችሁ ከመጨረሻው ተሸሁድ ያጠናቀቀ ጊዜ ከአራት ነገሮች በአላህ ይጠበቅ: ከጀሀነም ቅጣት፣ ከቀብር ቅጣት፣ ከህይወትና ሞት ፈተናና ከመሲሕ ደጃል ክፋት።'"
[ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ከመጨረሻው ተሸሁድ በኋላ ከሶላት ከማሰላመታቸው በፊት ከአራት ነገሮች በአላህ ይጠበቁ ነበር። እኛንም በአላህ ከነርሱ እንድንጠበቅ አዘዙን።

የመጀመሪያው: ከቀብር ቅጣት ነው።

ሁለተኛው: የትንሳኤ ቀን ከእሳት ቅጣት ነው።

ሶስተኛው: ከህይወት ፈተናዎች ሲባል ክልክል ከሆኑ ዓለማዊ ዝንባሌዎችና አጥማሚ ማደናገሪያዎች፤ እንዲሁም በሞት ሰአት ከሚያጋጥሙ ፈተናዎች ሲባል ደግሞ በጣእረ ሞት ሰአት ከኢስላም ወይም ሱና መጥመምን የመሰሉ ወይም በሁለቱ መላእክት መጠየቅን ከመሰለ የቀብር ፈተና ማለት ነው።

አራተኛ: በመጨረሻ ዘመን የሚወጣ ከሆነው ከመሲሕ ደጃል ፈተና ነው። አላህ በርሱ አማካኝነት ባሮቹን ይፈትናል። ዱዓው ላይ እርሱ ተለይቶ የተጠቀሰው የርሱ ፈተናና ማጥመሙ ከባድ ስለሆነ ነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. እነዚህ መጠበቂያ ዱዓዎች ከዱንያና ከመጨረሻው ዓለም ክፋቶች መጠበቅን ከሰበሰቡ አንገብጋቢና ጠቅላይ ከሆኑ ዱዓዎች መካከል ናቸው።
2. የቀብር ቅጣት የተረጋገጠና እውነት መሆኑን እንረዳለን።
3. የፈተናን አደገኝነት እና ከፈተና ለመዳን በአላህ መታገዝና ዱዓ ማድረግ እንደሚገባ እንረዳለን።
4. የደጃል መውጣት የተረጋገጠ መሆኑንና ፈተናው ከባድ መሆኑን እንረዳለን።

5. ከመጨረሻው ተሸሁድ በኋላ ይህን ዱዓ ማለት እንደሚወደድ እንረዳለን።
6. ከመልካም ስራ በኋላ ዱዓ ማድረግ እንደሚወደድ እንረዳለን።

(3103)

(١٥٩) - عَنْ مَعْدَانَ بْنِ أَبِي طَلْحَةَ الْيَعْمَرِيُّ قَالَ: لَقِيتُ ثَوْبَانَ مَوْلَى رَسُولِ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ، فَقُلْتُ: أَخْبِرْنِي بِعَمَلٍ أَعْمَلُهُ يُدْخِلُنِي اللهُ بِهِ الْجَنَّةَ؟ أَوْ قَالَ قُلْتُ: بِأَحَبِّ الْأَعْمَالِ إِلَى اللهِ، فَسَكَتَ. ثُمَّ سَأَلْتُهُ فَسَكَتَ. ثُمَّ سَأَلْتُهُ الثَّالِثَةَ فَقَالَ: سَأَلْتُ عَنْ ذَلِكَ رَسُولَ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ، فَقَالَ: «عَلَيْكَ بِكَثْرَةِ السُّجُودِ لِلَّهِ فَإِنَّكَ لَا تَسْجُدُ لِلَّهِ سَجْدَةً، إِلَّا رَفَعَكَ اللهُ بِهَا دَرَجَةً، وَحَطَّ عَنْكَ بِهَا خَطِيئَةً» قَالَ مَعْدَانُ: ثُمَّ لَقِيتُ أَبَا الدَّرْدَاءِ فَسَأَلْتُهُ فَقَالَ لِي: مِثْلَ مَا قَالَ لِي: ثَوْبَانُ.

[صحيح] - [رواه مسلم]

(159) - ከመዕዳን ቢን አቢ ጦልሐ አልየዕመሪይ እንደተላለፈው እንዲህ አለ: «የአላህ መልክተኛ ነፃ ወጪ ባሪያ የነበረውን ሠውባንን አገኘሁትና እንዲህ አልኩት: አላህ በርሱ ጀነት እንድገባ የሚያደርግብኝን የምሰራውን ስራ ንገረኝ? ወይም አላህ ዘንድ ተወዳጅ የሆነውን ስራ ንገረኝ? እርሱም ዝም አለ። በድጋሚ ጠየቅኩት አሁንም ዝም አለ። አሁንም ለሶስተኛ ጊዜ ጠየቅኩት እርሱም: "ስለዚህ ጉዳይ የአላህን መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ጠየቅኳቸውና እንዲህ አሉኝ ‹ለአላህ ሱጁድ እንድታበዛ አደራ እልሀለሁ። ለአላህ አንድ ሱጁድ አትወርድም አላህ በርሷ ደረጃህን ከፍ ቢያደርግና ወንጀልህንም የሚሰርዝ ቢሆን እንጂ›"» መዕዳን እንዲህ አለ «ቀጥሎ አቡ ደርዳእን አገኘሁና ጠየቅኩት። እርሱም ሠውባን ያለኝን አምሳያ ነገረኝ።» [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ጀነት ለመግባት ሰበብ ስለሆነ ወይም አላህ ዘንድ ተወዳጅ ስለሆነ ስራ ተጠየቁ።

ነቢዩም (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ለጠያቂው እንዲህ አሉት: ሶላት ውስጥ ሱጁድ ማብዛትን አዘውትር! አላህ በርሷ ደረጃህን

ከፍ ቢያደርግና ወንጀልህንም ቢምርህ እንጂ አንድም ሱጁድ ለአላህ አትወርድም።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ሶላት ሱጁድን ስለሚያካትት ግዴታም ሆነ ሱና ሶላት ለመስገድ ጥረት በማድረግ ላይ ሙስሊሞች መበረታታታቸው፤
2. የሶሐቦች ግንዛቤና እውቀት መገለፁ። ይህም ጀነት ከአላህ እዝነት በኋላ በስራ ካልሆነ በቀር እንደማትገኝ ማወቃቸው ነው።
3. ሶላት ውስጥ ሱጁድ ማድረግ ደረጃን ከፍ ለማድረግና ወንጀሎችን ለማስማር ትልቁ ምክንያት ነው።

(3732)

(١٦٠) - عن عَائِشَةَ رضيَ الله عنها قالت: إِنِّي سمعْتُ رسولَ الله صلى الله عليه وسلم يقول: «لَا صَلَاةَ بِحَضْرَةِ الطَّعَامِ، وَلَا هُوَ يُدَافِعُهُ الْأَخْبَثَانِ». [صحيح] - [رواه مسلم]

(160) - ከእናትችን ዓኢሻ (ረዲየሏሁ ዐንሃ) - አላህ መልካም ሥራዋን ይውደድላትና እንደተላለፈው እንዲህ ብላለች፦ "የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ሲሉ ሰምቻቸዋለሁ፦ "ምግብ ቀርቦ አልያም ሁለቱ ቆሻሻዎች እያጨናነቁት ሶላት የለም።" [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) የሰጋጅ ነፍስ የሚጓጓውና ልቡ የተንጠለጠለበት ምግብ ቀርቦ መስገድን ከለከሉ።

ልክ እንደዚሁ በቆሻሻው ግፊት ስለሚጠመድም ሁለቱ ቆሻሾች እያጨናነቁት (እነርሱም ሽንትና አይነ ምድር ናቸው።) ከመስገድ ከለከሉ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. አንድ ሰጋጅ ወደ ሶላት ከመግባቱ በፊት ከሶላቱ የሚያዘናጋውን ነገር ባጠቃላይ ማራቅ ይገባዋል።

(3088)

(١٦١) - عن عُثْمَانَ بْنَ أَبِي الْعَاصِ رضي الله عنه: أنه أَتَى النَّبِيَّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ فَقَالَ: يَا رَسُولَ اللهِ، إِنَّ الشَّيْطَانَ قَدْ حَالَ بَيْنِي وَبَيْنَ صَلَاتِي وَقِرَاءَتِي يَلْبِسُهَا عَلَيَّ، فَقَالَ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ: «ذَاكَ شَيْطَانٌ يُقَالُ لَهُ خِنْزَبٌ، فَإِذَا أَحْسَسْتَهُ فَتَعَوَّذْ بِاللهِ مِنْهُ، وَاتْفُلْ عَلَى يَسَارِكَ ثَلَاثًا»، قَالَ: فَفَعَلْتُ ذَلِكَ فَأَذْهَبَهُ اللهُ عَنِّي. [صحيح] - [رواه مسلم]

(161) - ከዑሥማን ቢን አቢል ዓስ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እርሱ ወደ ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ዘንድ በመምጣት "የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ሰይጣን በኔና በሶላቴ እንዲሁም በቁረአቴ መካከል አዘናጋኝና በኔ ላይ ያለባብስብኛል።" አላቸው። የአላህ መልዕክተኛም (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) "ይሄ ሰይጣን ነው። ኺንዘብ ይባላል። ይህ ስሜት የተሰማህ ጊዜ ከርሱ በአላህ ተጠበቅ! ወደ ግራህም ሶስት ጊዜ ትፋ!" አሉት። እርሱም "ይህንን ፈፀምኩ አላህም አስወገደልኝ።" አለ። [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ዑሥማን ቢን አቢልዓስ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራውን ይውደድለትና - ወደ ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) በመምጣት እንዲህ አለ: "የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ሰይጣን በኔና በሶላቴ መካከል ጋሬጣ ሆነ በርሷ ውስጥ ከመመሰጥም ከለከለኝ። በኔ ላይ ሶላቴ ውስጥ የምቀራውን ቁረአቴን ቀላቀለብኝም አጠራጠረኝም።" የአላህ መልዕክተኛም (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ አሉት: "ይህ ሰይጣን ነው። ኺንዘብ ይባላል። ይህንን ያገኘህና የተሰማህ ጊዜ ከርሱ

በአላህ ተጠበቅ። ወደ ግራህም ዘረህ ከትንሽ ምራቅ ጋር ሶስት ጊዜ ትፋ።" ዑሥማንም እንዲህ አለ "ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ያዘዙኝን ነገር ፈፀምኩ። አላህም ከኔ ላይ አስወገደልኝ።"

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ሶላት ውስጥ መመሰጥና ልብን መጣድ አንገብጋቢ መሆኑን እንረዳለን። ሰይጣንም ሶላት ውስጥ በመወስወስና በመጎትጎት ይታገላል።
2. ሰይጣን ሶላት ውስጥ በሚወሰውስ ወቅት ወደ ግራ ከመትፋት ጋር ሶስት ጊዜ "አዑዙ ቢላሂ ሚነሽሸይጧኒ አርረጂም" ሶስት ማለት እንደሚወደድ እንረዳለን።
3. ሶሐቦች (ረዲየሏሁ ዐንሁም) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - በሚያጋጥማቸው ችግሮች ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ችግራቸውን እስኪፈቱላቸው ድረስ ወደርሳቸው እንደሚመለሱ መገለፁን እንረዳለን።
4. የሶሐቦች ልብ ህያው መሆኑን እንረዳለን። ሀሳባቸው ሁሉ መጪው አለም ነው።

(65105)

(١٦٢) - عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ رضي الله عنه قَالَ: قَالَ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ: «أَسْوَأُ النَّاسِ سَرَقَةً الَّذِي يَسْرِقُ صَلَاتَهُ» قَالَ: وَكَيْفَ يَسْرِقُ صَلَاتَهُ؟ قال: «لَا يُتِمُّ رُكُوعَهَا، وَلَا سُجُودَهَا».

[صحيح] - [رواه ابن حبان]

(162) - ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: "የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል: ‹ከሚሰርቁ ሰዎች ሁሉ እጅግ መጥፎው ሶላቱን የሚሰርቅ ነው።› እርሱም ‹እንዴት ሶላቱን ይሰርቃታል?› አላቸው። እርሳቸውም ‹ሩኩዑንም ሆነ ሱጁዱን ባለማሟላት።› ብለው መለሱለት።" [ሶሒሕ ነው።] - [ኢብኑ ሒባን ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) በስርቆት እጅግ በጣም መጥፎ ሰው ከሶላቱ የሚሰርቅ ሰው መሆኑን ገለፁ። ይህም ከዚህ ሌባ ተቃራኒ የሌላን ሰው ገንዘብ የወሰደ በዚህች አለም ሊጠቀምበትም ይችል ይሆናል። ይህ ሌባ ግን ከራሱ የምንዳና አጅር ሐቅ የሚሰርቅ ነው። ሶሐቦችም "የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! እንዴት አንድ ሰው ከሶላቱ ይሰርቃል?" ብለው ጠየቁ። እርሳቸውም "ሩኩዑንም ሆነ ሱጁዱን አያሟላም።" ብለው መለሱ። ይህም በሩኩዑም በሱጁዱም ሲጣደፍ በተሟላ መልኩ እነርሱን አለመፈፀሙ ነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ሶላትን ማሳመር፣ ማእዘናቶቿንም በእርጋታና በተመስጦ መፈፀም አንገብጋቢ ጉዳይ መሆኑን እንረዳለን።
2. ሩኩዑም ሱጁዱም የማያሟላ ሰው ከዚህ ተግባሩ ለማራቅና ክልክልነቱን ለማስገንዘብ ሲባል በሌባነት መገለፁን፤
3. ሶላት ውስጥ ሩኩዕና ሱጁድን መሙላትና እነርሱንም ቀጥ ብሎ መፈፀሙ ግዴታ መሆኑን እንረዳለን።

(65100)

(١٦٣) - عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ رضي الله عنه عَنِ النَّبِيِّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ قَالَ: «أَمَا يَخْشَى أَحَدُكُمْ - أَوْ: لاَ يَخْشَى أَحَدُكُمْ - إِذَا رَفَعَ رَأْسَهُ قَبْلَ الإِمَامِ، أَنْ يَجْعَلَ اللهُ رَأْسَهُ رَأْسَ حِمَارٍ، أَوْ يَجْعَلَ اللهُ صُورَتَهُ صُورَةَ حِمَارٍ». [صحيح] - [متفق عليه]

(163) - ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል፡- "አንዳችሁ ከኢማም በፊት ጭንቅላቱን ቀና ያደረገ ጊዜ አላህ ጭንቅላቱን የአህያ ጭንቅላት እንዳያደርገው ወይም አላህ የሰውነት ቅርፁን የአህያ የሰውነት ቅርፅ እንዳያደርግበት አይፈራምን?!" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ጭንቅላቱን ከኢማሙ በፊት ቀና የሚያደርግ ሰው አላህ ጭንቅላቱን የአህያ ጭንቅላት ሊያደርግበት ወይም የሰውነት ቅርፁን የአህያ ቅርፅ ሊያደርግበት እንደሚችል በመግለፅ ከባድ ዛቻን አስተላለፉ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. አንድ ተከታይ ከኢማሙ ጋር ያለው የመከተል ሁኔታ አራት ነው። ከአራቱ ሶስቱ የተከለከሉ ናቸው። እነርሱም: መቅደም፣ እኩል መፈፀምና ኋላ መቅረት ናቸው። ለተከታይ የተደነገገው ኢማሙን መከተል ነው።
2. ተከታይ የሆነ ሰው ሶላት ውስጥ ኢማሙን መከተል ግዴታው እንደሆነ እንረዳለን።
3. ከኢማሙ በፊት ራሱን ቀና የሚያደርግ ሰው ላይ የሰውነት ቅርፁ ወደ አህያ ቅርፅ እንደሚለወጥ የመጣው ዛቻ ሊሆን የሚችል ነገር ነው። ይህም ወደ ሌላ ፍጥረት ከመለወጥ የሚመደብ ነው።

(3086)

(١٦٤) - عَنْ أَبِي سَعِيدٍ الْخُدْرِيِّ رضي الله عنه قَالَ: قَالَ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ: «إِذَا شَكَّ أَحَدُكُمْ فِي صَلَاتِهِ، فَلَمْ يَدْرِ كَمْ صَلَّى ثَلَاثًا أَمْ أَرْبَعًا، فَلْيَطْرَحِ الشَّكَّ، وَلْيَبْنِ عَلَى مَا اسْتَيْقَنَ، ثُمَّ يَسْجُدُ سَجْدَتَيْنِ قَبْلَ أَنْ يُسَلِّمَ، فَإِنْ كَانَ صَلَّى خَمْسًا شَفَعْنَ لَهُ صَلَاتَهُ، وَإِنْ كَانَ صَلَّى إِتْمَامًا لِأَرْبَعٍ كَانَتَا تَرْغِيمًا لِلشَّيْطَانِ». [صحيح] - [رواه مسلم]

(164) - ከአቡ ሰዒድ አልኹድሪይ (ረዲየላሁ ዐንሁ) -አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ፡- «የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል፡- "አንዳችሁ ሰላቱ ውስጥ የተጠራጠረ ጊዜ ሶስት ይሁን አራት ስንት እንደሰገደ ካላወቀ ጥርጣሬውን ይጣልና እርግጠኛ በሆነበት ላይ ይገንባ። ከዛም ከማሰላመቱ በፊት ሁለት ሱጁዶችን ይውረድ። አምስት ከሰገደ ሁለቱ ሱጁዶች ሰላቱን ጥንድ ያደርጉለታል። አራት ሞልቶ ከሰገደ ደግሞ ሱጁዶቹ ሰይጣንን ማዋረጃ ይሆኑለታል።"» [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) አንድ ሰጋጅ ሰላቱ ውስጥ የተጠራጠረ ጊዜና ሶስት ይሁን አራት ስንት እንደሰገደ ካላወቀ ምን ማድረግ እንዳለበት ገለፁ። ሶስተኛው ስለሆነ የተረጋገጠው አጠራጣሪውን የረከዓ ብዛት (አራትን) ሳይቆጥር አራተኛውን ረከዓ ይሰግዳል። ከዚያም ከማሰላመቱ በፊት ሁለት ሱጁዶችን ይወርዳል።

የሰገደው እውነትም አራት ከነበር አንድ ረከዓ በመጨመሩ አምስተኛ ይሆናል። ሁለቱ የመርሳት ሱጁዶችም እንደ አንድ ረከዓ ይሆኑለትና ስለዚህ የረከዓው ብዛት ሙሉ እንጂ ጎዶሎ አይሆንም። ጭማሪዋ ረከዓ እውነትም አራተኛ ከሆነች ደግሞ በርሱ ላይ ያለበትን ግዴታ ሳይጨምርና ሳይቀንስ ተወጥቷል።

ሁለቱ ሱጁዶችም ሰይጣንን ማዋረጃና ማራቂያ እንዲሁም ፍላጎቱን ሳያሳካ ባዶ እጁን መመለሻ ይሆናሉ። ምክንያቱም ሰላቱ ውስጥ አወሳስቦበት

እንዲበላሽበት ተጋረጠበት፤ ሰጋጁ የአደም ልጅም - ለአደም ሱጁድ ውረድ የሚለውን የአላህን ትእዛዝ ባለመፈፀም ኢብሊስ ያመፀበት የሆነውን - የሱጁድን ትእዛዝ በመፈፀሙ ሶላቱ ሞላለት።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ሰጋጅ የሆነ ሰው ሶላቱ ውስጥ የተጠራጠረ ጊዜና እርሱ ዘንድ አንዱ ሚዛን ካልደፋ ጥርጣሬውን ይጥልና እርግጠኛ በሆነበት ነገር ላይ ይሰራል። ይሀውም አነስተኛ የሆነውን ነው (የሰገድኩት ሶስት ረከዓ ነው ወይስ አራት ብሎ ከተጠራጠረ ሶስት የሚለውን ይወስዳል)። ሶላቱን አሟልቶ ይሰግድና ከማሰላመቱ በፊት የመርሳት ሱጁድን ይወርዳል፤ ከዚያም ያሰላምታል።
2. እነዚህ ሁለት ሱጁዶች ሶላትን መጠገኛ መንገድና ሰይጣንን ከፍላጎቱ የተዋረደ፣ የራቀና ባዶውን መመለሻ ናቸው።
3. ሐዲሡ ውስጥ የተጠቀሰው ጥርጣሬ ሚዛን ያልደፋውን ጥርጣሬ ነው እንጂ ጥርጣሬው ሚዛን የሚደፋ ከሆነ ግን ሚዛን በሚደፋው ነው የሚሰራው።
4. ሸሪዓዊን ትእዛዝ በመፈፀም ወስዋስን መዋጋትና መከላከል ላይ መነሳሳቱን እንረዳለን።

(11231)

(١٦٥) - عَنْ عَبْدِ اللهِ بنِ مسعُودٍ رَضِيَ اللهُ عَنْهُ قَالَ: ذُكِرَ عِنْدَ النَّبِيِّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ رَجُلٌ نَامَ لَيْلَهُ حَتَّى أَصْبَحَ، قَالَ: «ذَاكَ رَجُلٌ بَالَ الشَّيْطَانُ فِي أُذُنَيْهِ، أَوْ قَالَ: فِي أُذُنِهِ».

[صحيح] - [متفق عليه]

(165) - ከዐብደላህ ቢን መስዑድ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: «ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ዘንድ እስኪነጋ ድረስ ምሽቱን የተኛ ሰውዬ ተወሳ። እርሳቸውም "ይህ ሸይጧን ጆሮዎቹ ውስጥ ወይም ጆሮው ውስጥ የሸናበት ሰው ነው።" አሉ።» [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ዘንድ እስኪነጋና ፀሐይ እስክትወጣ ድረስ የተኛ፤ ግዴታ ሶላትን ለመስገድም ስላልተነሳ ሰውዬ ተወሳ። ነቢዩም (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ይህ ሸይጧን ጆሮው ውስጥ የሸናበት ሰው ነው አሉ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. የሌሊት ሶላት መቆምን መተው እንደሚጠላና ይህም በሸይጧን አማካይነት እንደሚሆን ተረድተናል።
2. በርሱና አላህን በመታዘዝ መካከል እንቅፋት ለመሆን በሁሉም መንገድ ላይ የሰውን ልጅ ለመከልከል ከሚቀመጠው ሸይጧን መጠንቀቅ እንደሚገባ ተረድተናል።
3. ኢብኑ ሐጀር እንዲህ ብለዋል: (ወደ ሶላት ያልቆመ) በሚለው የተፈለገው ማንኛውም የሶላት አይነትም ሊሆን ይችላል፤ ተለይቶ የታወቀን ሶላት ሊሆንም ይችላል፤ የለይል ሶላትም ሊሆን ይችላል፤ የግዴታ ሶላትም ሊሆን ይችላል።
4. ጢቢይ እንዲህ ብለዋል: «ቦታው ላይ ለመጥቀስ ከእንቅልፍ ጋር አብሮ የሚሄደው አካል አይን ከመሆኑም ጋር ጆሮን ለይተው የጠቀሱት የእንቅልፉን ክብደት ለመግለፅ ነው። መስሚያዎች መንቂያ አካላቶች ናቸውና። ሽንት የተለየበት ምክንያትም ደሞ ወደ ውስጥ ለመግባት ቀላልና ወደ ደም ስር ለመስረፅ ፈጣን ስለሆነ ነው። ይህም ከሆነ በኋላ ለሁሉም አካል መስነፍን ያወርሳል።»

(3714)

(١٦٦) - عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ رضي الله عنه أَنَّ النَّبِيَّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ قَالَ: «خَيْرُ يَوْمٍ طَلَعَتْ عَلَيْهِ الشَّمْسُ يَوْمُ الْجُمُعَةِ، فِيهِ خُلِقَ آدَمُ، وَفِيهِ أُدْخِلَ الْجَنَّةَ، وَفِيهِ أُخْرِجَ مِنْهَا، وَلَا تَقُومُ السَّاعَةُ إِلَّا فِي يَوْمِ الْجُمُعَةِ». [صحيح] - [رواه مسلم]

(166) - ከአቡ ሁረይራ (ረዲየላሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው : ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል: "ፀሀይ ከወጣችባቸው ቀናቶች ሁሉ በላጩ ቀን የጁመዓ ቀን ነው። በዚህ ቀን ኣደም ተፈጠረ፣ በዚሁ ቀን ጀነት ገባ፣ በዚሁ ቀን ከርሷ ወጣ፣ ሰአቲቱም በጁመዓ ቀን ካልሆነ በቀር አትከሰትም።" [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ፀሀይ ከወጣችባቸው ቀናቶች ሁሉ በላጩ ቀን የጁሙዓ ቀን እንደሆነ ተናገሩ። የጁሙዓን ቀን ልዩ ከሚያደርገው ነገሮች መካከል: አላህ አደምን (ዐለይሂ ሰላም) የፈጠረው፣ ጀነት ውስጥ ያስገባው፣ ከጀነት አስወጥቶ ወደ ምድር ያወረደው በዚሁ ቀን ነው። ሰአቲቱም በጁሙዓ ቀን ካልሆነ በቀር አትከሰትም።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ከሁሉም የሳምንቱ ቀናቶች የጁሙዓ ቀን በላጭ መሆኑን እንረዳለን።
2. በጁሙዓ ቀን መልካም ስራዎችን በማብዛት ላይ፣ የአላህን እዝነት ለማግኘት በመዘጋጀትና መአቱን በመከላከል ላይ መነሳሳቱን እንረዳለን።
3. ሐዲሡ ውስጥ የተጠቀሱት እነዚህ የጁመዓ ቀን መለዮዎች እንጂ የጁመዓን ቀን ደረጃ ለመጥቀስ ተብለው የተወሱ አይደሉም። የአደም ከጀነት መውጣትና የትንሳኤ ቀን መቆም ደረጃ ተደርገው አይቆጠሩም ያሉ ሲኖሩ፤ በሌላ በኩል ደሞ እዚህ ሐዲሥ ውስጥ የተጠቀሱት ሁሉም ደረጃዎች ናቸው። የአደም ከጀነት መውጣት ከመልክተኞች፣ ከነቢያቶችና ከደጋጎች የሆኑ ዘሮችን ለማግኘት ሰበብ ሲሆን የትንሳኤ መቆም ደግሞ የደጋጎች

ምንዳ ለመፍጠኑና አላህ ለነርሱ ያዘጋጀላቸውን መከበሪያ ለማግኘት ሰበብ ስለሆነ ያሉም አሉ።

4. በዚህ ዘገባ ያልተጠቀሱ በሌላ ዘገባ ግን የተጠቀሱ የጁመዓ ቀን ሌሎች መለዮዎችም አሉ። ከነሱም መካከል: በጁመዓ እለት አላህ የአደምን ተውበት ተቀበለ፣ በጁመዓ እለት ሞተ፣ በዚህች ቀን አንድ አማኝ ባሪያ እየሰገደ አላህን አንዳች ነገር እየጠየቀ ይህቺን ሰዓት አያገኝም አላህ የጠየቀውን የሚሰጠው ቢሆን እንጂ የተባለላት አንዲት ሰዓት አለች።
5. በዓመት ከሚገኙ ቀናቶች በላጩ ቀን የዐረፋ ቀን ነው። የእርድ ቀን ነው ያሉም አሉ። ከሳምንት ቀናቶች ሁሉ በላጩ ቀን የጁሙዓ ቀን ነው። በላጩ ምሽት ደግሞ የለይለተል ቀደር ምሽት ነው።

(3711)

(١٦٧) - عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ رَضِيَ اللهُ عَنْهُ أَنَّ رَسُولَ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ قَالَ: «مَنِ اغْتَسَلَ يَوْمَ الجُمُعَةِ غُسْلَ الجَنَابَةِ ثُمَّ رَاحَ، فَكَأَنَّمَا قَرَّبَ بَدَنَةً، وَمَنْ رَاحَ فِي السَّاعَةِ الثَّانِيَةِ، فَكَأَنَّمَا قَرَّبَ بَقَرَةً، وَمَنْ رَاحَ فِي السَّاعَةِ الثَّالِثَةِ، فَكَأَنَّمَا قَرَّبَ كَبْشًا أَقْرَنَ، وَمَنْ رَاحَ فِي السَّاعَةِ الرَّابِعَةِ، فَكَأَنَّمَا قَرَّبَ دَجَاجَةً، وَمَنْ رَاحَ فِي السَّاعَةِ الخَامِسَةِ، فَكَأَنَّمَا قَرَّبَ بَيْضَةً، فَإِذَا خَرَجَ الإِمَامُ حَضَرَتِ المَلاَئِكَةُ يَسْتَمِعُونَ الذِّكْرَ». [صحيح] - [متفق عليه]

(167) - ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) -አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል፦ «የጁመዓ ቀን ልክ እንደ ጀናባ ትጥበት ከታጠበ በኋላ ማልዶ የሄደ ሰው ልክ የግመል ቁርባን እንዳቀረበ ነው። በሁለተኛው ወቅት ማልዶ የሄደ ሰው ልክ የከብት ቁርባን እንዳቀረበ ነው። በሶስተኛው ወቅት ማልዶ የሄደ ሰው ልክ ቀንዳም ሙክት ቁርባን እንዳቀረበ ነው። በአራተኛው ወቅት ማልዶ የሄደ ሰው ልክ የዶሮ ቁርባን እንዳቀረበ ነው። በአምስተኛው ወቅት ማልዶ የሄደ ሰው ልክ የእንቁላል ቁርባን እንዳቀረበ ነው። ኢማሙ ለኹጥባ የወጣ ጊዜ መላእክቶቹም ተግሳፁን ለመስማት ይገኛሉ።» [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ወደ ጁመዓ ሰላት ማልዶ የመሄድን ትሩፋት ተናገሩ። መማለዱም ፀሐይ ከወጣችበት ወቅት ጀምሮ ኢማሙ ለኹጥባ እስከሚመጣበት ወቅት ይቆያል። ይህም አምስት ወቅቶች ይኖሩታል። አከፋፈሉም ፀሐይ ከወጣችበት ወቅት ኢማሙ መስጂድ ገብቶ ለኹጥባ ሚንበር ላይ እስኪወጣ ያሉትን ወቅቶች ለአምስት በመክፈል ይገኛል።

የመጀመሪያው: እንደ ጀናባ ትጥበት የተሟላ ትጥበትን ከታጠበ በኋላ በመጀመሪያው ወቅት ጁሙዓ ወደሚሰግድበት መስጂድ የሄደ ሰው ሲሆን ይህም ግመል ሶደቃ እንደሰጠ ሰው ነው።

ሁለተኛው: በሁለተኛው ሰዓት የሄደ ሲሆን ይህም ከብት እንደመፀወተ ሰው ነው።

ሶስተኛ: በሶስተኛው ሰዓት የሄደ ሰው ሲሆን ይህም ቀንዳም ሙክት እንደመፀወተ ሰው ነው።

አራተኛ: በአራተኛው ሰዓት የሄደ ሰው ሲሆን ይህም ዶሮ እንደመፀወተ ሰው ነው።

አምስተኛ: በአምስተኛው ሰዓት የሄደ ሰው ሲሆን ይህም እንቁላል እንደመፀወተ ሰው ነው።

ኢማሙ ለኹጥባ የወጣ ጊዜም መስጂድ በር ላይ ተቀምጠው መስጂድ ለሚገቡ ሰዎች አንድ በአንድ የሚጽፉ መላዕክቶች መመዝገባቸውን ትተው ዚክርና ኹጥባ ለማዳመጥም ይመጣሉ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. የጁመዓ ቀን በመታጠብ ላይ መነሳሳቱን እንረዳለን። ይህም ወደ ሰላት ከመሄድ በፊት ነው የሚፈፀመው።
2. ወደ ጁመዓ ሰላት በቀኑ የመጀመሪያ ሰአት ማልዶ የመሄድን ትሩፋት እንረዳለን።

3. ወደ መልካም ስራዎች በመቻኮል ላይ መነሳሳቱን እንረዳለን።
4. መላዕክቶች የጁመዓ ሶላትንና ኹጥባን ለማዳመጥ እንደሚገኙ እንረዳለን።
5. መላዕክቶች በመስጂድ በሮች ላይ ሆነው ወደ ጁመዓ ሶላት የሚመጡ ሰዎችን አንድ በአንድ ይፅፋሉ።
6. ኢብኑ ረጀብ እንዲህ ብለዋል: "የጁመዓ ቀን የታጠበና ቀጥሎ ማልዶ የሄደ ሰው" የሚለው አነጋገር ለጁመዓ ተብሎ መታጠብ የሚወደደው መጀመሪያው ጎህ ሲወጣ ሲሆን የመጨረሻው ደግሞ ወደ ጁመዓ ሲሄድ መሆኑን ይጠቁማል።

(5393)

(١٦٨) - عن ثَوْبَانَ رضي الله عنه قال: كَانَ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ إِذَا انْصَرَفَ مِنْ صَلَاتِهِ اسْتَغْفَرَ ثَلَاثًا، وَقَالَ: «اللَّهُمَّ أَنْتَ السَّلَامُ، وَمِنْكَ السَّلَامُ، تَبَارَكْتَ ذَا الْجَلَالِ وَالْإِكْرَامِ»، قَالَ الْوَلِيدُ: فَقُلْتُ لِلْأَوْزَاعِيِّ: كَيْفَ الْاسْتِغْفَارُ؟ قَالَ: تَقُولُ: أَسْتَغْفِرُ اللهَ، أَسْتَغْفِرُ اللهَ.

[صحيح] - [رواه مسلم]

(168) - ከሠውባን -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: "የአላህ መልክተኛ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ሶላታቸውን ያጠናቀቁ ጊዜ ሶስት ጊዜ ኢስቲግፋር ያደርጉ (ምህረት ይጠይቁ) ነበር። እንዲህም ይሉ ነበር: 'አላሁመ አንተ አስሰላም ወሚንከ አስሰላም ተባረክተ ዘል ጀላሊ ወልኢክራም' (አላህ ሆይ! አንተ ሰላም ነህ ሰላም የሚገኘውም ካንተ ነው። የግርማና ክብር ባለቤት የሆንከው ጠራህ!) ወሊድ ለአውዛዒይ 'እንዴት ነው ኢስቲግፋር የሚደረገው? አልኩት' አለ። እሳቸውም 'አሰተግፊሩላህ አስተግፊሩላህ' በማለት ነው ብለው መለሱልኝ።' አለ።" [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ሶላታቸውን ያጠናቀቁ ጊዜ "አስተግፊሩላህ አስተግፊሩላህ አስተግፊሩላህ" ይሉ ነበር።

ቀጥለውም ጌታቸውን "አላሁመ አንተ አስሰላም ወሚንከ አስሰላም ተባረክተ ዘል ጀላሊ ወልኢክራም" (አላህ ሆይ! አንተ ሰላም ነህ ሰላም የሚገኘውም ካንተ ነው። የግርማና ክብር ባለቤት የሆንከው ጠራህ!) በማለት ጌታቸውን ያልቃሉ። አላህ በባህሪያቶቹ የተሟላና ሰላም ነው፤ ከሁሉም ጉድለትና ነውርም የጠራ ነው። ከዱንያና አኺራ ክፉት ሰላም የሚፈለገውም ከሌላ ሳይሆን ከርሱ ነው። እርሱ ጥራት ይገባውና በሁለቱም ዓለም መልካሙ የበዛ ፣ የልቅናና መልካም ባለቤት ነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ከሶላት በኋላ ኢስቲግፋር ማለትና በርሱ ላይ መዘውተር እንደሚወደድ እንረዳለን።
2. አምልኮ ውስጥ የጎደለውን እንዲሞላ፣ አምልኮ ውስጥ ያሳነስነውን እንዲጠግን ኢስቲሻፋር እንደሚወደድ እንረዳለን።

(10947)

(١٦٩) - عَنْ أَبِي الزُّبَيْرِ قَالَ: كَانَ ابْنُ الزُّبَيْرِ يَقُولُ فِي دُبُرِ كُلِّ صَلَاةٍ حِينَ يُسَلِّمُ: «لَا إِلَهَ إِلَّا اللهُ وَحْدَهُ لَا شَرِيكَ لَهُ، لَهُ الْمُلْكُ وَلَهُ الْحَمْدُ وَهُوَ عَلَى كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ، لَا حَوْلَ وَلَا قُوَّةَ إِلَّا بِاللهِ، لَا إِلَهَ إِلَّا اللهُ، وَلَا نَعْبُدُ إِلَّا إِيَّاهُ، لَهُ النِّعْمَةُ وَلَهُ الْفَضْلُ وَلَهُ الثَّنَاءُ الْحَسَنُ، لَا إِلَهَ إِلَّا اللهُ مُخْلِصِينَ لَهُ الدِّينَ وَلَوْ كَرِهَ الْكَافِرُونَ» وَقَالَ: «كَانَ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ يُهَلِّلُ بِهِنَّ دُبُرَ كُلِّ صَلَاةٍ».

[صحيح] - [رواه مسلم]

(169) - ከአቡ ዙበይር እንደተላለፈው እንዲህ አሉ፡- "ኢብኑ ዙበይር በሁሉም ሶላት ካሰላመተ በኃላ እንዲህ ይሉ ነበር። 'ላ ኢላሃ ኢለሏህ ወሕደሁ ላ ሸሪከ ለሁ፤ ለሁል ሙልኩ ወለሁል ሐምዱ ወሁወ ዓላ ኩሊ ሸይኢን ቀዲር ፤ ላ ሐውለ ወላ ቁውወተ ኢላ ቢላህ ፤ ላ ኢላሃ ኢለሏህ ወላነዕቡዱ ኢላ ኢያህ ለሁ አንኒዕመህ ወለሁልፈድል ወለሁ አሠሠናኡል ሐሰን፤ ላኢላሃ ኢለሏሁ ሙኽሊሲነ ለሁ ዲነ ወለው ከሪሃል ካፊሩን' አስከትለውም እንዲህ አሉ ' የአላህ መልክተኛ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ከሁሉም ሶላቶች በኋላ እነዚህን ውዳሴዎች ይሉ ነበር።'" [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

የአላህ መልክተኛ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ሁሉንም ግዴታ ሶላት ካሰላመቱ በኋላ በዚህ ታላቅ ውዳሴ ያወድሱ ነበር። ትርጉሙም:

"ላኢላሃ ኢለሏህ" ማለትም ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ አምላክ የለም።

"ወሕደሁ ላሸሪከ ለሁ" ማለትም አላህ በተመላኪነቱ፣ በጌትነቱ፣ በስሞቹና በባህሪያቶቹ ለሱ ተጋሪ የለውም።

"ለሁል ሙልክ" ማለትም ገደብአልባ ሰፊ ፣ ጠቅላይ ንግስና የሰማያትና የምድር በመካከላቸውም ያለው ሁሉ ንግስና ለሱ ነው።

"ወለሁል ሐምድ" ማለትም ልቅ በሆነ ምሉእነት የሚገለፅ ፣ በደስታም ይሁን በችግር ወቅት በማንኛውም ሁኔታ በውዴታና በልቅና ምሉዕ በመሆኑ የሚመሰገን ነው።

"ወሁወ ዐላ ኩሊ ሸይኢን ቀዲር" ማለትም ችሎታው በሁሉም መልኩ የሞላ አንዳችም የማይሳነው ማንኛውም ጉዳይ ለሱ የማያቅተው ነው።

"ላ ሐውለ ወላ ቁወተ ኢላ ቢላህ" ማለት በአላህ እገዛ ቢሆን እንጂ ከአንድ ሁኔታ ወደ አንድ ሁኔታ መለወጥ የለም፤ አላህን ከመወንጀል እርሱን ወደማምለክ መለወጥም ሀይልም የለም። እርሱ አጋዥ ነውና፤ መመኪያም በርሱ ላይ ነው።

"ላኢላሃ ኢለሏህ ወላነዕቡዱ ኢላ ኢያህ" "ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ አምላክ የለም። ከርሱ በስተቀርም አናመልክም።" የሚለው የአላህን ተመላኪነትና ሺርክን ውድቅ የማድረግን ሀሳብ የሚያጠናክር ነው። ከርሱ በስተቀርም አምልኮ የሚገባው የለም።

"ለሁ አንኒዕመህ ወለሁል ፈድል" (ፀጋ የርሱ ነው። ችሮታም የርሱ ነው።) እርሱ የፀጋዎች ባለቤትና የሚፈጥር ነው። ለፈለገው ባሮቹም የሚቸረው እሱ ነው።

"ወለሁ አሥሠናኡል ሐሰን" በሁለመናው፣ በባህሪያቶቹ፣ በድርጊቶቹ፣ በፀጋዎቹ ሁሉ መልካም ውዳሴዎች ለርሱ የተገባ ነው።

"ላኢላሃ ኢለሏህ ሙኽሊሲነ ለሁ ዲን" (አምልኮን ለርሱ ያጠራን ስንሆን ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ የለም።) ማለትም በአላህ አምልኮ ያለምንም ይዩልኝና ይስሙልኝ ብቸኛ ያደረግነው ስንሆን ነው የምናመልከው።

"ከሀዲያን ቢጠሉ እንኳ" ማለትም ከሀዲያን ቢጠሉ እንኳ አላህን በመነጠልና በማምለክ ላይ እንፀናለን።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ከሁሉም ግዴታ ሶላቶች በኋላ በዚህ ውዳሴ ላይ መጠባበቅ እንደሚወደድ እንረዳለን።
2. አንድ ሙስሊም ከሀዲያን ቢጠሉ እንኳ በእምነቱ ከፍ ያለ ስሜት ሊሰማውና የእምነቱን መገለጫዎች ይፋ ማድረግ ይገባዋል።

3. ሐዲሥ ውስጥ "ከሶላት በኋላ" የምትለዋ ቃል ስትመጣ ሐዲሡ ውስጥ የተጠቀሰው ውዳሴ ከሆነ ካሰላመተ በኃላ መሆኑ ዱዓእ ከሆነ ደግሞ ሶላት ውስጥ ከማሰላመቱ በፊት መሆኑ መሰረት ነው።

(6203)

(١٧٠) - عَنْ وَرَّادٍ كَاتِبِ الْمُغِيرَةِ بْنِ شُعْبَةَ قَالَ: أَمْلَى عَلَيَّ الْمُغِيرَةُ بْنُ شُعْبَةَ فِي كِتَابٍ إِلَى مُعَاوِيَةَ: أَنَّ النَّبِيَّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ كَانَ يَقُولُ فِي دُبُرِ كُلِّ صَلَاةٍ مَكْتُوبَةٍ: «لَا إِلَهَ إِلَّا اللهُ وَحْدَهُ لَا شَرِيكَ لَهُ، لَهُ الْمُلْكُ وَلَهُ الْحَمْدُ، وَهُوَ عَلَى كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ، اللَّهُمَّ لَا مَانِعَ لِمَا أَعْطَيْتَ، وَلَا مُعْطِيَ لِمَا مَنَعْتَ، وَلَا يَنْفَعُ ذَا الْجَدِّ مِنْكَ الْجَدُّ». [صحيح] - [متفق عليه]

(170) - የሙኺራ ቢን ሹዕባ ጸሐፊ ከሆነው ወራድ እንደተላለፈው እንዲህ አለ: "ሙኺራ ቢን ሹዕባ ወደ ሙዐዊያህ የሚጻፍን እንዲህ የሚል ደብዳቤ አጻፈኝ: 'ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ከሁሉም ግዴታ ሶላቶች በኋላ እንዲህ ይሉ ነበር ‹ላኢላሀ ኢለሏሁ ወሕደሁ ላ ሸሪከ ለህ፤ ለሁል ሙልኩ ወለሁል ሐምዱ ወሁወ ዓላ ኩሊ ሸይኢን ቀዲር፤ አላሁመ ላማኒዐ ሊማ አዕጦይተ ወላሙዕጢየ ሊማ መነዕተ ወላ የንፈዑ ዘልጀዲ ሚንከልጀድ› ትርጉሙም 'ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ አምላክ የለም። ብቸኛና ለርሱ አጋር የሌለው ነው። ንግስናም ምስጋናም ለርሱ ነው። እርሱ በሁሉ ነገር ላይ ቻይ ነው። አላህ ሆይ! ለሰጠኸው ማንም ከልካይ የለውም። ለከለከልከውም ማንም ሰጪ የለውም። የክብር ባለቤትም ክብሩ ካንተ (ቅጣት) አያድንም።'" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ከሁሉም ግዴታ ሶላት በኋላ "ላኢላሀ ኢለሏሁ ወሕደሁ ላ ሸሪከ ለህ፤ ለሁል ሙልኩ ወለሁል ሐምዱ ወሁወ ዓላ ኩሊ ሸይኢን ቀዲር፤ አላሁመ ላማኒዐ ሊማ አዕጦይተ ወላ ሙዕጢየ ሊማ መነዕተ ወላየንፈዑ ዘልጀዲ ሚንከልጀድ" "ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ አምላክ የለም። ብቸኛና ለርሱ አጋር የሌለው ነው።

ንግስናም ምስጋናም ለርሱ ነው። እርሱ በሁሉ ነገር ላይ ቻይ ነው። አላህ ሆይ! ለሰጠኸው ማንም ከልካይ የለውም። ለከለከልከውም ማንም ሰጪ የለውም። የክብር ባለቤትም ክብሩ ካንተ (ቅጣት) አያድንም።" ይሉ ነበር።

ማለትም: የተውሒድ ቃል በሆነችው "ላኢላሀ ኢለሏህ" አረጋግጣለሁም አምናለሁም። ትክክለኛዋን አምልኮም ለአላህ አፅንቼ ከርሱ ውጪ ካሉ አካላቶችም ውድቅ አደርጋታለሁ። ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ የለም። እውነተኛውና የተሟላው ንግስና፣ የሰማያትና የምድር ባለቤቶችም ምስጋና ሁሉ ለአላህ የተገባ መሆኑን አረጋግጣለሁ። እርሱም በሁሉም ነገር ላይ ቻይ ነው። አላህ የወሰነው መስጠትም ይሁን መከልከል ማንም መላሽ የለውም። እርሱ ዘንድ የሀብት ባለቤት ሀብቱ አይጠቅመውም። ብቸኛ የሚጠቅመው መልካም ስራ ነው።

### ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ይህ ዚክር የተውሒድና የምስጋና ቃላቶችን የሰበሰበ ስለሆነ ከሶላቶች በኋላ ማለቱ እንደሚወደድ እንረዳለን።
2. ሱናን ወደ መተግበርና ማሰራጨት መቻኮል እንደሚገባ እንረዳለን።

(65102)

(١٧١) - عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ رضي الله عنه عَنْ رَسُولِ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ: «مَنْ سَبَّحَ اللهَ فِي دُبُرِ كُلِّ صَلَاةٍ ثَلَاثًا وَثَلَاثِينَ، وَحَمِدَ اللهَ ثَلَاثًا وَثَلَاثِينَ، وَكَبَّرَ اللهَ ثَلَاثًا وَثَلَاثِينَ، فَتِلْكَ تِسْعَةٌ وَتِسْعُونَ، وَقَالَ: تَمَامَ الْمِائَةِ: لَا إِلَهَ إِلَّا اللهُ وَحْدَهُ لَا شَرِيكَ لَهُ، لَهُ الْمُلْكُ وَلَهُ الْحَمْدُ وَهُوَ عَلَى كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ غُفِرَتْ خَطَايَاهُ وَإِنْ كَانَتْ مِثْلَ زَبَدِ الْبَحْرِ». [صحيح] - [رواه مسلم]

(171) - ከአቡ ሁረይራ (ረዲየላሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል: «ከሁሉም (ግዴታ) ሶላት በኋላ ሰላሳ ሶስት ጊዜ አላህን ያጠራ (ሱብሓነሏህ) ያለ፤ ሰላሳ ሶስት ጊዜ አላህን ያመሰገነ (አልሐምዱ ሊላህ) ያለ፣ ሰላሳ ሶስት ጊዜ ተክቢራ (አላሁ አክበር) ያለ፤ ይህም በድምሩ ዘጠና ዘጠኝ ሲሆን መቶ መሙያውንም "ላኢላሃ ኢለላሁ ወሕደሁ ላሸሪከ ለሁ፣ ለሁል ሙልኩ ወለሁል ሐምዱ ወሁወ ዓላ ኩሊ ሸይኢን ቀዲር" ያለ ሰው ወንጀሉ የባህር አረፋ አምሳያ ቢደርስ እንኳ ይማራል።» [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ግዴታ ሶላቶች ከተጠናቀቁ በኋላ እነዚህን ያለ ሰው የሚያገኘውን ምንዳ ገለፁ:

ሰላሳ ሶስት ጊዜ "ሱብሓነላህ": ይህም አላህን ከጉድለቶች ሁሉ ማጥራት ነው።

ሰላሳ ሶስት ጊዜ "አልሐምዱ ሊላህ": ይህም አላህን ከመውደድና ከማላቅ ጋር በምሉዕ ባህሪያቱ ማወደስ ነው።

ሰላሳ ሶስት ጊዜ "አላሁ አክበር": ማለት ይህም አላህ ከሁሉም ነገር እጅግ የላቀ ነው ማለት ነው።

መቶ መሙያውንም "ላኢላሃ ኢለላሁ ወሕደሁ ላሸሪከ ለሁ፣ ለሁል ሙልኩ ወለሁል ሐምዱ ወሁወ ዓላ ኩሊ ሸይኢን ቀዲር" ያለ ሰው - ትርጉሙም:- ከአላህ በቀር በእውነት የሚመለክ የለም። ብቸኛና አጋር የለውም። ጥራት የተገባው አላህ  በምሉዕ ንግስና የተለየና ከርሱ ውጪ ያሉት የማይገባቸውን

ከውዴታና ልቅና ጋር ውዳሴና ሙገሳ የተገባው ነው። እርሱም ምንም የማይሳነው ቻይ ነው።-

እነዚህን ቃላት ያለ ሰው ወንጀሉ ባህር በሚናወጥና በሚላተም ሰአት ከላይ በሚሆነው ነጭ አረፋ ልክ ቢበዛ ራሱ ትማራለችም ትሰረዛለችም።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ከግዴታ ሶላቶች በኋላ ይህን ዚክር ማለት ተወዳጅ እንደሆነ እንረዳለን።
2. ይህ ዚክር ለወንጀል መማር ምክንያት ነው።
3. የአላህን ትልቁን ችሮታ፣ እዝነትና ምህረት እንረዳለን።
4. ይህ ዚክር ወንጀሎችን ለማስማር ምክንያት ነው። የተፈለገውም: ትናንሽ ወንጀሎችን ማስማር ነው፤ ትላልቅ ወንጀሎች ግን ከተውበት በቀር ምንም አያስምራቸውም።

(10948)

(١٧٢) - عَنْ أَبِي أُمَامَةَ رضي الله عنه قَالَ: قَالَ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ: «مَنْ قَرَأَ آيَةَ الْكُرْسِيِّ فِي دُبُرِ كُلِّ صَلَاةٍ مَكْتُوبَةٍ لَمْ يَمْنَعْهُ مِنْ دُخُولِ الْجَنَّةِ إِلَّا أَنْ يَمُوتَ».

[صحيح] - [رواه النسائي في الكبرى]

(172) - ከአቡ ኡማማ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: «የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል: "ከሁሉም ግዴታ ሶላት በኋላ አየተል ኩርሲይን የቀራ ሰው ጀነት ለመግባት ከሞት በቀር ምንም አይከለክለውም።"» [ሶሒሕ ነው።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ግዴታ ሶላት ከተጠናቀቀ በኋላ አየቱል ኩርሲይን የቀራ ሰው ከሞት በቀር ጀነት ለመግባት ምንም እንደማይከለክለው ተናገሩ። ይህቺም አንቀጽ በበቀራ ምእራፍ ውስጥ የምትገኝ ሲሆን እርሷም ይህቺ የአላህ ቃል ናት: ትርጉሟ: {አላህ ከርሱ በቀር

ሌላ አምላክ የለም። ህያው ራሱን ቻይ ነው። ማንገላጀትም እንቅልፍም አትይዘውም። በሰማያት ውስጥና በምድር ውስጥ ያለው ሁሉ የርሱ ብቻ ነው። ያ እርሱ ዘንድ በፍቃዱ ቢሆን እንጂ የሚያማልደው ማነው? (ከፍጡሮች) በፊታቸው ያለውንና ከኋላቸው ያለውን ሁሉ ያውቃል። በሻውም ነገር እንጂ ከእውቀቱ በምንም ነገር አያካብቡም። (አያውቁም)። መንበሩ ሰማያትንና ምድርን ሰፋ። ጥበቃቸውም አያቅተውም። እርሱም የሁሉ በላይ ታላቅ ነው።} [አልበቀራህ: 255]

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ይህቺ ታላቅ አንቀፅ የአላህን ውብ ስሞችና የላቁ ባህሪያቱን በማካተቷ ያላትን ትሩፋት እንረዳለን።
2. ይህቺን ታላቅ አንቀፅ ከሁሉም ግዴታ ሶላቶች በኋላ መቅራት ተወዳጅ መሆኑን እንረዳለን።
3. መልካም ስራዎች ጀነት ለመግባት ሰበብ እንደሆኑ እንረዳለን።

(10950)

(١٧٣) - عَنِ ابْنِ عُمَرَ رَضِيَ اللهُ عَنْهُمَا قَالَ: حَفِظْتُ مِنَ النَّبِيِّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ عَشْرَ رَكَعَاتٍ: رَكْعَتَيْنِ قَبْلَ الظُّهْرِ، وَرَكْعَتَيْنِ بَعْدَهَا، وَرَكْعَتَيْنِ بَعْدَ المَغْرِبِ فِي بَيْتِهِ، وَرَكْعَتَيْنِ بَعْدَ العِشَاءِ فِي بَيْتِهِ، وَرَكْعَتَيْنِ قَبْلَ صَلاَةِ الصُّبْحِ، وَكَانَتْ سَاعَةً لاَ يُدْخَلُ عَلَى النَّبِيِّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ فِيهَا، حَدَّثَتْنِي حَفْصَةُ أَنَّهُ كَانَ إِذَا أَذَّنَ المُؤَذِّنُ وَطَلَعَ الفَجْرُ صَلَّى رَكْعَتَيْنِ، وَفِي لَفْظٍ: أَنَّ النَّبِيَّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ كَانَ يُصَلِّي بَعْدَ الْجُمُعَةِ رَكْعَتَيْنِ. [صحيح] - [متفق عليه بجميع رواياته]

(173) - ከኢብኑ ዑመር (ረዲየሏሁ ዐንሁማ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አለ: "ከነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) አስር ረከዓዎችን ሸምድጃለሁ። እነርሱም ከዙህር በፊት ሁለት ረከዓ፣ ከዙህር በኋላም ሁለት ረከዓ፣ ከመግሪብ በኋላ ቤታቸው ውስጥ ሁለት ረከዓ፣ ከዒሻእ በኋላም ቤታቸው ውስጥ ሁለት ረከዓ፣ ከሱብሒ ሶላት በፊት ሁለት ረከዓ ናቸው። የሱብሒ ወቅት ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም

በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ዘንድ የማይገባበት ሰአት ነበረች። ስለሰአቲቱም ሙአዚኑ አዛን ያለ ጊዜና ጎህ የወጣ ጊዜ ሁለት ረከዓ ይሰግዱ እንደነበር ሐፍሷ ነገረችኝ።" በሌላ ዘገባ "ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ከጁመዓ ሶላት በኋላም ሁለት ረከዓ ይሰግዱ ነበር።" [ሶሒሕ ነው።] - [በሁሉም ዘገባዎቹ ቡኻሪና ሙስሊም ተስማምተውበታል።]

## ትንታኔ:

ዐብደላህ ቢን ዑመር (ረዲየሏሁ ዐንሁማ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና ከነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) የሸመደዱትን አስር የሱና ረከዓዎች ገለጹ። እነዚህ ሱናዎች "ሱነን አርረዋቲብ" (ከግዴታ ሶላት በፊት ወይም በኋላ የሚሰገዱ ሱና ሶላቶች) ተብለው ይጠራሉ። ሁለት ረከዓ ከዙህር በፊትና ሁለት ረከዓ ከዙህር በኋላ፤ ከመግሪብ በኋላ ሁለት ረከዓ ቤታቸው ውስጥ፤ ሁለት ረከዓ ከዒሻ ሶላት በኋላ ቤታቸው ውስጥ፤ ከፈጅር በፊት ሁለት ረከዓ ይሰግዱ ነበር። ይህም አስር ረከዓ ሞላ። ከጁመዓ ሶላት በኋላም ሁለት ረከዓ ይሰግዱ ነበር።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. እነዚህ ከፈርድ በፊትና በኋላ የሚሰገዱ ሶላቶች ተወዳጅ መሆናቸውንና በነርሱ ላይ መዘውተርም እንደሚወደድ እንረዳለን።
2. ሱና ሶላቶችን ቤት ውስጥ መፈፀም መደንገጉን እንረዳለን።

(3062)

(١٧٤) - عَنْ عَبْدِ اللهِ بْنِ مُغَفَّلٍ رضي الله عنه قَالَ: قَالَ النَّبِيُّ صلى الله عليه وسلم: «بَيْنَ كُلِّ أَذَانَيْنِ صَلَاةٌ، بَيْنَ كُلِّ أَذَانَيْنِ صَلَاةٌ» ثُمَّ قَالَ فِي الثَّالِثَةِ: «لِمَنْ شَاءَ». [صحيح] - [متفق عليه]

(174) - ከዐብደላህ ቢን ሙገፈል (ረዲየሏሁ ዐንሁ) -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው እንዲህ አሉ፦ «ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና እንዲህ ብለዋል፦ "በየሁሉም ሁለት አዛኖች መካከል ሶላት አለ። በየሁሉም ሁለት አዛኖች መካከል ሶላት አለ።" ቀጥለው በሶስተኛው "ለፈለገ ሰው" አሉ።» [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና በየሁሉም አዛንና ኢቃም መካከል ሱና ሶላት እንዳለ ገለፁ። ይህንንም ሶስት ጊዜ ደጋገሙት። በሶስተኛውም ይህን ሶላት መስገድ ለፈለገ ሰው ተወዳጅ እንደሚሆንለት ተናገሩ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. በአዛንና ኢቃም መካከል ሶላት መስገድ ተወዳጅ መሆኑን እንረዳለን።
2. ንግግርን መደጋገም የነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና መመሪያ እንደሆነ እንረዳለን። ይህም የሚናገሩት ነገር አንገብጋቢ መሆኑን አፅንዖት ለመስጠትና ለማሰማት ብለው ነው።
3. በሁለት አዛን በማለት የተፈለገው: አዛንና ኢቃምን ነው። (ሁለቱ አዛኖች) ያሉት ወደ አንዱ በማመዘን ነው። (ፀሃይና ጨረቃን) ሁለቱ ጨረቃዎች እንደሚባሉት፣ (አቡበከርና ዑመር) ሁለቱ ዑመሮች እንደሚባሉት ማለት ነው።
4. አዛን ማለት ወቅት መግባቱን ማሳወቂያ ነው። ኢቃማህ ማለት ደግሞ ሶላት መፈፀሚያ ወቅቱ መድረሱን ማሳወቂያ ነው።

(65479)

(١٧٥) - عَنْ أَبِي قَتَادَةَ السَّلَمِيِّ رضي الله عنه أَنَّ رَسُولَ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ قَالَ: «إِذَا دَخَلَ أَحَدُكُمُ الْمَسْجِدَ فَلْيَرْكَعْ رَكْعَتَيْنِ قَبْلَ أَنْ يَجْلِسَ». [صحيح] - [متفق عليه]

(175) - ከአቡ ቀታዳ አስሰለሚይ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል: "አንዳችሁ መስጂድ የገባ ጊዜ ከመቀመጡ በፊት ሁለት ረከዓ ይስገድ።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

በማንኛውም ወቅትና ለማንኛውም አላማ መስጂድ የመጣና የገባ ሰው ከመቀመጡ በፊት ሁለት ረከዓ እንዲሰግድ ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) አነሳሱ። ይሀውም ሁለቱ የተሒየተል መስጂድ ረከዓዎች ናቸው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ከመቀመጥ በፊት የተሒየተል መስጂድ ሁለት ረከዓ መስገድ እንደሚወደድ እንረዳለን።
2. ይህ ትእዛዝ መቀመጥ ለፈለገ ሰው ነው። መስጂድ ገብቶም ሳይቀመጥ የወጣን ሰው ትእዛዙ አይመለከተውም።
3. አንድ ሰጋጅ ሰዎች ሶላት ውስጥ ሆነው መስጂድ ቢገባና ቀጥታ እነርሱ ወደሚሰግዱት ሶላት ቢገባ ከሁለቱ የተሒየተል መስጂድ ረከዓ ያብቃቃዋል።

(65091)

(١٧٦) - عن أبي هُرَيرةَ رضي الله عنه أنَّ رسول الله صلى الله عليه وسلمَ قال: «إذا قُلْتَ لِصَاحِبِكَ: أَنْصِتْ، يومَ الجمعةِ، والْإِمامُ يَخْطُبُ، فَقَدْ لَغَوْتَ». [صحيح] - [متفق عليه]

(176) - ከአቡ ሁረይራ (ረዲየላሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል፡- "የጁሙዐ ቀን ኢማሙ ኹጥባ እያደረገ ሳለ ለባልደረባህ 'ዝም በል!' ካልከው በርግጥም ውድቅ ንግግርን ተናግረሀል።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) የጁሙዓ ኹጥባ ላይ የተሳተፈ ሰው ሊያሟላቸው ከሚገባ ግዴታ ስርዐቶች መካከል ተግሳፁን ሊያስተነትን ዘንድ ኹጥባ አድራጊውን በጥሞና ማዳመጥ እንደሚገባ ግልፅ አደረጉ። ኢማሙ ኹጥባ እያደረገ ለሌላ ሰው "ዝም በል!" "አዳምጥ!" እንደማለት ትንሽ ነገር እንኳ ያወራ ሰውም ቢሆን የጁመዐ ሰላት ትሩፋት አምልጦታል።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ኹጥባ በሚደመጥበት ወቅት መጥፎን ማውገዝ ወይም ሰላምታን መመለስና ያስነጠሰን "የርሐሙከላህ" ማለትን እንኳ ቢሆን ማንኛውም ንግግር መናገር ክልክል መሆኑን እንረዳለን።
2. ኢማሙን የሚያወራ ወይም ኢማሙ የሚያወራው ሰው እዚህ ክልከላ ውስጥ አይካተትም።
3. አስፈላጊ ከሆነ በሁለቱ ኹጥባዎች መካከል ማውራት ይፈቀዳል።
4. ኢማሙ ኹጥባ እያደረገ ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ከተወሱ ድምፅህን ቀንሰህ በሳቸው ላይ ሶላትና ሰላም ታወርዳለህ። ልክ እንደዚሁ ዱዓ ሲደረግም በዝግታ (ድምፅህን ቀንሰህ) አሚን ትላለህ።

(3107)

(١٧٧) - عن عمران بن حصين رضي الله عنه قال: كَانَتْ بِي بَوَاسِيرُ، فَسَأَلْتُ النَّبِيَّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ عَنِ الصَّلَاةِ، فَقَالَ: «صَلِّ قَائِمًا، فَإِنْ لَمْ تَسْتَطِعْ فَقَاعِدًا، فَإِنْ لَمْ تَسْتَطِعْ فَعَلَى جَنْبٍ».

[صحيح] - [رواه البخاري]

(177) - ከዒምራን ቢን ሑሰይን -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው እንዲህ አለ: "ኪንታሮት ነበረብኝና ስለ አሰጋገዴ ነቢዩን ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ጠየቅኳቸው። እሳቸውም እንዲህ አሉኝ:- 'ቁመህ! ካልቻልክ ተቀምጠህ ካልቻልክ በጎንህ ተጋድመህ ስገድ። '" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪ ዘግበውታል። ]

## ትንታኔ:

መቆም ባልተቻለበት ወቅት ካልሆነ በቀር ለሶላት አሰጋገድ መሰረቱ መቆም እንደሆነና መቆም ካልቻለ ተቀምጦ እንደሚሰግድ ተቀምጦ መስገድም ካልቻለ በጎኑ ተጋድሞ መስገድ እንደሚችል ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ገለፁ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. በአቅም ልክ ከሁኔታ ወደ ሁኔታ መሸጋገር እንጂ አይምሮ ጤነኛ እስከሆነ ድረስ ሶላት የማትቀር ግዴታ ናት።
2. አንድ ሰው አምልኮን የሚፈፅመው በአቅሙ ልክ መሆኑ የኢስላምን ገርነትና ቀላልነትን ያስረዳናል።

(10951)

(١٧٨) - عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ رَضِيَ اللهُ عَنْهُ: أَنَّ النَّبِيَّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ قَالَ: «صَلَاةٌ فِي مَسْجِدِي هَذَا خَيْرٌ مِنْ أَلْفِ صَلَاةٍ فِيمَا سِوَاهُ إِلَّا الْمَسْجِدَ الْحَرَامَ». [صحيح] - [متفق عليه]

(178) - ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው : ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል: "በዚህ መስጂዴ የሚሰገድ ሶላት ከርሱ ውጪ ከሚሰገዱ አንድ ሺህ ሶላቶች የተሻለ ነው። የተከበረው መስጊድ (መስጂደል ሐራም) ሲቀር።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና በርሳቸው መስጂድ የሚሰገድ ሶላትን ደረጃ ገለፁ። እርሱም መካ ውስጥ ከሚገኘው ከተከበረው መስጂድ ውጪ ምድር ላይ በሚገኙ መስጂዶች ከሚሰገድ ሶላት ሁሉ በአንድ ሺህ እጥፍ ይበልጣል። በተከበረው መስጂድ (መስጂደል ሐራም) የሚሰገድ ሶላት ግን በርሳቸው መስጂድ ከሚሰገድ ሶላትም ይበልጣል።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. በተከበረው መስጂድና በነቢዩ መስጂድ የሚሰገድ ሶላት ምንዳ እጥፍ ድርብ መሆኑን እንረዳለን።
2. በተከበረው መስጊድ የሚሰገድ ሶላት ከርሱ ውጪ በሚገኙ መስጂዶች ከሚሰገዱ ሶላቶች በመቶ ሺህ በላጭ ነው።

(65090)

(١٧٩) - عَنْ مَحْمُودِ بْنِ لَبِيدٍ رضي الله عنه: أَنَّ عُثْمَانَ بْنَ عَفَّانَ أَرَادَ بِنَاءَ الْمَسْجِدِ فَكَرِهَ النَّاسُ ذَلِكَ، وَأَحَبُّوا أَنْ يَدَعَهُ عَلَى هَيْئَتِهِ، فَقَالَ: سَمِعْتُ رَسُولَ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ يَقُولُ: «مَنْ بَنَى مَسْجِدًا لِلهِ بَنَى اللهُ لَهُ فِي الْجَنَّةِ مِثْلَهُ». [صحيح] - [متفق عليه]

(179) - ከመሕሙድ ቢን ለቢድ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: "ዑሥማን ቢን ዐፋን (የነቢዩን) መስጂድ መገንባት ፈለጉ። ይህንንም ሰዎች ጠሉ። ባለበት እንዲተወውም ፈለጉ። እርሳቸውም እንዲህ አሉ: 'የአላህን መልዕክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ሲሉ ሰምቻቸዋለሁ: ‹ ለአላህ ብሎ መስጂድን የገነባ አላህም ለርሱ አምሳያውን ጀነት ውስጥ ይገነባለታል።›' አለ። " [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ዑሥማን ቢን ዐፋን አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና የነቢዩን (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) መስጂዱ መጀመሪያ ከነበረበት ባማረ መልኩ አድሶ መገንባት ፈለጉ። ሰዎችም መስጂዱ በነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ዘመን ከነበረበት ሁኔታ ስለሚለወጥ ይህንን የዑሥማን ሀሳብ ጠሉ። የመስጂዱ ግድግዳ በጡብ የተገነባ ሲሆን ጣሪያው በዘንባባ ቅጠል ነበር የተሰራው። ዑሥማን ግን በድንጋይና በጀሶ ነበር መገንባት የፈለጉት። በዚህ ጊዜ ዑሥማን (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና ነቢዩን (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) "ለይዩልኝና ይስሙልኝ ሳይሆን የአላህን ውዴታ ፈልጎ መስጂድ የገነባ አላህ በስራው አይነት የበለጠ ምንዳ ይመነዳዋል። ይህም ምንዳ በገነባው ቤት አምሳያ አሏህም ለርሱ ጀነት ውስጥ የሚገነባለት መሆኑ ነው።" ሲሉ መስማታቸውን ነገሯቸው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. መስጂዶችን በመገንባት ላይ መነሳሳቱና የዚህንም ትሩፋት እንረዳለን።

2. መስጂድን ማስፋትና ማደስ የመገንባት ትሩፋት ውስጥ ይካተታል።
3. በሁሉም ስራዎች ስራን ለአላህ ማጥራት አንገብጋቢነቱን እንረዳለን።

(65089)

(١٨٠) - عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ رضي الله عنه قَالَ: قَالَ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ: «مَا مِنْ صَاحِبِ ذَهَبٍ وَلَا فِضَّةٍ، لَا يُؤَدِّي مِنْهَا حَقَّهَا، إِلَّا إِذَا كَانَ يَوْمُ الْقِيَامَةِ، صُفِّحَتْ لَهُ صَفَائِحُ مِنْ نَارٍ، فَأُحْمِيَ عَلَيْهَا فِي نَارِ جَهَنَّمَ، فَيُكْوَى بِهَا جَنْبُهُ وَجَبِينُهُ وَظَهْرُهُ، كُلَّمَا بَرَدَتْ أُعِيدَتْ لَهُ، فِي يَوْمٍ كَانَ مِقْدَارُهُ خَمْسِينَ أَلْفَ سَنَةٍ، حَتَّى يُقْضَى بَيْنَ الْعِبَادِ، فَيَرَى سَبِيلَهُ، إِمَّا إِلَى الْجَنَّةِ، وَإِمَّا إِلَى النَّارِ»

قِيلَ: يَا رَسُولَ اللهِ، فَالْإِبِلُ؟ قَالَ: «وَلَا صَاحِبُ إِبِلٍ لَا يُؤَدِّي مِنْهَا حَقَّهَا، وَمِنْ حَقِّهَا حَلَبُهَا يَوْمَ وِرْدِهَا، إِلَّا إِذَا كَانَ يَوْمُ الْقِيَامَةِ، بُطِحَ لَهَا بِقَاعٍ قَرْقَرٍ، أَوْفَرَ مَا كَانَتْ، لَا يَفْقِدُ مِنْهَا فَصِيلًا وَاحِدًا، تَطَؤُهُ بِأَخْفَافِهَا وَتَعَضُّهُ بِأَفْوَاهِهَا، كُلَّمَا مَرَّ عَلَيْهِ أُولَاهَا رُدَّ عَلَيْهِ أُخْرَاهَا، فِي يَوْمٍ كَانَ مِقْدَارُهُ خَمْسِينَ أَلْفَ سَنَةٍ، حَتَّى يُقْضَى بَيْنَ الْعِبَادِ، فَيَرَى سَبِيلَهُ إِمَّا إِلَى الْجَنَّةِ، وَإِمَّا إِلَى النَّارِ»

قِيلَ: يَا رَسُولَ اللهِ، فَالْبَقَرُ وَالْغَنَمُ؟ قَالَ: «وَلَا صَاحِبُ بَقَرٍ، وَلَا غَنَمٍ، لَا يُؤَدِّي مِنْهَا حَقَّهَا، إِلَّا إِذَا كَانَ يَوْمُ الْقِيَامَةِ بُطِحَ لَهَا بِقَاعٍ قَرْقَرٍ، لَا يَفْقِدُ مِنْهَا شَيْئًا، لَيْسَ فِيهَا عَقْصَاءُ، وَلَا جَلْحَاءُ، وَلَا عَضْبَاءُ تَنْطَحُهُ بِقُرُونِهَا وَتَطَؤُهُ بِأَظْلَافِهَا، كُلَّمَا مَرَّ عَلَيْهِ أُولَاهَا رُدَّ عَلَيْهِ أُخْرَاهَا، فِي يَوْمٍ كَانَ مِقْدَارُهُ خَمْسِينَ أَلْفَ سَنَةٍ، حَتَّى يُقْضَى بَيْنَ الْعِبَادِ، فَيَرَى سَبِيلَهُ إِمَّا إِلَى الْجَنَّةِ، وَإِمَّا إِلَى النَّارِ»

قِيلَ: يَا رَسُولَ اللهِ، فَالْخَيْلُ؟ قَالَ: «الْخَيْلُ ثَلَاثَةٌ: هِيَ لِرَجُلٍ وِزْرٌ، وَهِيَ لِرَجُلٍ سِتْرٌ، وَهِيَ لِرَجُلٍ أَجْرٌ، فَأَمَّا الَّتِي هِيَ لَهُ وِزْرٌ، فَرَجُلٌ رَبَطَهَا رِيَاءً وَفَخْرًا وَنِوَاءً عَلَى أَهْلِ الْإِسْلَامِ، فَهِيَ لَهُ وِزْرٌ، وَأَمَّا الَّتِي هِيَ لَهُ سِتْرٌ، فَرَجُلٌ رَبَطَهَا فِي سَبِيلِ اللهِ، ثُمَّ لَمْ يَنْسَ حَقَّ اللهِ فِي ظُهُورِهَا وَلَا رِقَابِهَا، فَهِيَ لَهُ سِتْرٌ وَأَمَّا الَّتِي هِيَ لَهُ أَجْرٌ، فَرَجُلٌ رَبَطَهَا فِي سَبِيلِ اللهِ لِأَهْلِ الْإِسْلَامِ، فِي مَرْجٍ وَرَوْضَةٍ، فَمَا أَكَلَتْ مِنْ ذَلِكَ الْمَرْجِ، أَوِ الرَّوْضَةِ مِنْ شَيْءٍ، إِلَّا كُتِبَ لَهُ، عَدَدَ مَا أَكَلَتْ حَسَنَاتٌ، وَكُتِبَ لَهُ، عَدَدَ أَرْوَاثِهَا وَأَبْوَالِهَا، حَسَنَاتٌ، وَلَا تَقْطَعُ طِوَلَهَا فَاسْتَنَّتْ شَرَفًا، أَوْ شَرَفَيْنِ، إِلَّا كَتَبَ اللهُ لَهُ عَدَدَ آثَارِهَا وَأَرْوَاثِهَا حَسَنَاتٍ، وَلَا مَرَّ بِهَا صَاحِبُهَا عَلَى نَهْرٍ، فَشَرِبَتْ مِنْهُ وَلَا يُرِيدُ أَنْ يَسْقِيَهَا، إِلَّا كَتَبَ اللهُ لَهُ، عَدَدَ مَا شَرِبَتْ، حَسَنَاتٍ»

قِيلَ: يَا رَسُولَ اللهِ، فَالْحُمُرُ؟ قَالَ: «مَا أُنْزِلَ عَلَيَّ فِي الْحُمُرِ شَيْءٌ، إِلَّا هَذِهِ الْآيَةَ الْفَاذَّةُ الْجَامِعَةُ»: {فَمَنْ يَعْمَلْ مِثْقَالَ ذَرَّةٍ خَيْرًا يَرَهُ، وَمَنْ يَعْمَلْ مِثْقَالَ ذَرَّةٍ شَرًّا يَرَهُ} [الزلزلة: 8].

[صحيح] - [متفق عليه]

(180) - ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: «የአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና እንዲህ ብለዋል: "የወርቅና የብር ባለቤት ሆኖ ሐቃቸውን የማይወጣ ሰው የትንሳኤ ቀን ለርሱ የእሳት ዝርግ ተዘርግቶለት በርሷ በጀሃነም እሳት ውስጥ ሳይቃጠል የሚቀር የለም። ጎኑም፣ ግንባሩና ጀርባውም የሚተኮስ መሆኑ አይቀርም።" በቀዘቀዘች ቁጥር እየተመላለሰች መጠኑ ሀምሳ ሺህ አመት የሚያህል ለሆነ ቀን ይተኮሳል። ይህም በባሮች መካከል ፍርድ ተፈርዶ መንገዱ ወደ ጀነት ወይስ ወደ እሳት ነው የሚለውን እስኪመለከት ድረስ የሚዘልቅ ነው።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

**ትንታኔ:**

ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና የተለያዩ የገንዘብ አይነቶችንና የትንሳኤ ቀን ዘካቸውን ያላወጣ ሰው ምንዳ ምን እንደሆነ ገለፁ።

የመጀመሪያው: ወርቅ፣ ብርና በነርሱ ደረጃ ያለ ገንዘብና መገበያያ ሸቀጥ ነው። ይሀውም ዘካ ግዴታ ሆኖበት ያልወጣለትን ወርቅና ብር ነው። የትንሳኤ ቀን ሲሆን በዝርግ መልኩ የሚቃጠልም የሚቀልጥም ይደረጋል። በጀሃነም እሳት ውስጥም ትቀጣጠላለች በርሷም ባለቤቱ ይቀጣበታል። በርሷም ጎኑም፣ ግንባሩና ጀርባውም ይተኮሳል። በቀዘቀዘች ቁጥር ግለቷ ይመለሳል። አላህ በፍጡራን መካከል ፈርዶ ከጀነት ነዋሪዎች ወይም ከእሳት ነዋሪዎች መካከል ከአንዱ እስኪሆን የአንዱ ቀን መጠን ሀምሳ ሺህ አመት የሚያህል በሆነበት የእለተ ትንሳኤ ሙሉ ጊዜው በዚህ ሁኔታ ቅጣቱ ይቀጥላል።

ሁለተኛው: ግዴታ የሆነው ዘካዋንና ሐቋን ያልተወጣላት የግመል ባለቤት ነው። ከግመል ሐቅም እርሷ ዘንድ ለሚገኙ ድሆች በማለብ ማጠጣት ነው። ይህቺ ግመልም ተልቃ፣ ሰብታና ከነበሩበት ቁጥር በዝተው ይመጣሉ። የትንሳኤ ቀን የተስተካከለ ሰፊ መሬት ላይ ባለቤቱ ይዘረጋል፣ ይጣላል፣ ለርሷ ይለጠጣል።

በእግሮቻቸውም ይረገጣል፣ በጥርሶቻቸውም ይነከሳል። የመጨረሻዋ ግመል ባለፈች ቁጥር የመጀመሪያው ይመለሳል። አላህ በፍጡራን መካከል ፈርዶ ከጀነት ነዋሪዎች ወይም ከእሳት ነዋሪዎች መካከል ከአንዱ እስኪሆን ድረስም የአንዱ ቀን መጠን ሀምሳ ሺህ አመት የሚያህል በሆነበት በእለተ ትንሳኤ ሙሉ ጊዜውን በዚህ ሁኔታ ቅጣቱ ይቀጥላል።

ሶስተኛው: ግዴታ የሆነበትን ዘካ የማያወጣለት የከብት፣ የፍየልና የበግ ባለቤት የሆነ ሰው ነው። ከነበሩበት መጠን ምንም ሳይቀነስ በዝተው ይመጣሉ። የትንሳኤ ቀን የተስተካከለ ሰፊ መሬት ላይ ባለቤቱ ተዘርግቶ ይጣላል፣ ለርሷ ይለጠጣል። ከነርሱም መካከል ቀንዱ የተጠመዘዘ፣ ቀንድ የሌለውና ቀንዱ የተሰበረ አይኖርም። ይልቁንም የተሟላ ባህሪ ተላብሰው ነው የሚመጡት። በቀንዶቻቸውም ይወጉታል፣ በእግራቸውም ይረግጡታል። የመጨረሻዋ ባለፈች ቁጥር የመጀመሪያዋ ትመለሳለች። አላህ በፍጡራን መካከል ፈርዶ ከጀነት ነዋሪዎች ወይም ከእሳት ነዋሪዎች መካከል ከአንዱ እስኪሆን ድረስ የአንዱ ቀን መጠን ሀምሳ ሺህ አመት የሚያህል በሆነበት በእለተ ትንሳኤ ሙሉ ጊዜውን በዚህ ሁኔታ ቅጣቱ ይቀጥላል።

አራተኛው: ፈረስ የሚያደልብ ነው። ይህም ሶስት አይነት ናቸው።

አንደኛ: እርሷ ለርሱ ወንጀል የሆነችበት ናት። ይህም ለይዩልኝ፣ ለፉከራና ሙስሊሞችን ለመዋጋት የያዛት እንደሆነ ነው።

ሁለተኛ: እርሷ ለርሱ የምትሸሽገው የሆነች ናት። ይህም በአላህ መንገድ ለመዋጋት የያዛት እንደሆነ ነው። ከዚያም ለፈረሷ በመቀለብ፣ ጣጣዋን በመቻል ከዚህም ውስጥ ኮርማዋን በማዘጋጀት ለርሷ መልካም የዋለ እንደሆነ ነው።

ሶስተኛ: እርሷ ለርሱ ምንዳ የምታስገኝ የሆነች ናት። ይህም በአላህ መንገድ ለሙስሊሞች ለመዋጋት የያዛትና በቡቃያ ስፍራና በጨፌ ውስጥ ያሰማራት እንደሆነ ነው። ይህቺ ፈረስ አንድም አትበላም ለርሱ በበላችው ቁጥር ምንዳ ቢፃፍለት እንጂ፤ በእበቷና ሽንቷ ቁጥር ልክ እንኳ ምንዳ ቢፃፍለት እንጂ፤ የምትታሰርበትን ገመድ ቆርጣ በምድር ከፍታ ላይ አትሮጥም አላህ ለርሱ

በኮቴዋና እበቷ ቁጥር ልክ ምንዳን ቢፅፍለት እንጂ፤ ባለቤቱ እርሷን ይዞ በወንዝ በኩል ሲያልፍ እርሷን ማጠጣት ሳይፈልግም አትጠጣም አላህ በጠጣችው ቁጥር ለርሱ ምንዳ የሚፅፍለት ቢሆን እንጂ።

ቀጥሎ ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ስለአህያ እርሷም እንደ ፈረስ አምሳያ ናትን? ተብለው ተጠየቁ።

እርሳቸውም: ከዚህች የሚያስተውላት አጭር ከሆነችው አንቀፅ በቀር እርሷን የሚመለከት አንቀፅ አልወረደም። ይህቺ አንቀፅም ሁሉንም የአምልኮና የወንጀል አይነቶችን የምታጠቃልል ናት። ይህቺም አንቀፅ {የብናኝ ክብደት ያክልም መልካም የሰራ ሰው ያገኘዋል። የብናኝ ክብደት ያክልም ክፉን የሰራ ሰው ያገኘዋል።} [አዝዘልዘላህ:8] የምትለዋ የአላህ ንግግር ናት። አህያን ሲያደልብ አላህ የታዘዘባት የዚህን ምንዳ ያገኛል። ወንጀል ከሰራ ደግሞ የዚህን ቅጣት ያገኛል። ይህ አንቀፅ ሁሉንም ስራዎች የሚጠቀልል ነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ዘካ የመስጠት ግዴታነትንና ዘካ የከለከለ ሰውም ብርቱ ዛቻ እንደተዛተበት እንረዳለን።
2. ዘካን በስንፍና የሚከለክል ሰው ከሃዲ ባይሆንም ነገር ግን ከባድ አደጋ ውስጥ እንደሆነ እንረዳለን።
3. የሰው ልጅ አምልኮ ሲተገብር የአምልኮውን መሰረት አስቦ ዝርዝሩን ባያስብም በሚከሰቱ ዝርዝር ነገሮች ሁሉ እንደሚመነዳ እንረዳለን።
4. በገንዘብ ላይ ከዘካ ውጪም ሐቆች እንዳሉ እንረዳለን።
5. ከግመል ሐቆች መካከል አንዱ የምትጠጣበት ስፍራ ባለችበት ወቅት ለሚገኙ ሚስኪኖች አልቦ ማጠጣት ነው። ይህም ፈላጊዎች ቤት ድረስ አስበው ከመምጥት ይልቅ ቀላል ስለሆነና ለግመሎቹም ምቹ ስለሆነ ነው። ኢብኑ በጧል እንዲህ ብለዋል: ገንዘብ ሁለት ሐቆች አሉት: የነፍስ ወከፍ ሐቅና ሌላ ሐቅ ነው። አልቦ ማጠጣት የመልካም ስነምግባር መገለጫ ከሆኑ ሐቆች መካከል አንዱ ነው።

6. ከግመል፣ ከከብትና ከፍየል ግዴታ ሐቆች መካከል ኮርማዋን የፈለገች ጊዜ ኮርማዋን ማዘጋጀት ነው።
7. የአህያና ማስረጃ ያልመጣባቸው ነገሮች ባጠቃላይ ብይን: {የብናኝ ክብደት ያክልም መልካም የሰራ ሰው ያገኘዋል። የብናኝ ክብደት ያክልም ክፉን የሰራ ሰው ያገኘዋል።} በሚለው የአላህ ንግግር ውስጥ የሚካተቱ ናቸው።
8. በአንቀፁ ውስጥ መልካም ስራ ትንሽ እንኳ ብትሆን በመስራት ማነሳሳትና መጥፎ ስራ ብታንስ እንኳ ከመስራት ማስጠንቀቂያ አለበት።

(6611)

(١٨١) - عن أبي هريرة رضي الله عنه عن رسول الله صلى الله عليه وسلم قال: «مَا نَقَصَتْ صَدَقَةٌ مِنْ مَالٍ، وَمَا زَادَ اللهُ عَبْدًا بِعَفْوٍ إِلَّا عِزًّا، وَمَا تَوَاضَعَ أَحَدٌ لِلهِ إِلَّا رَفَعَهُ اللهُ».

[صحيح] - [رواه مسلم]

(181) - ከአቡ ሁረይራ -አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው የአላህ መልክተኛ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ ብለዋል:- "ምፅዋት (ከሰጪው) ገንዘብ ላይ አታጎድልም፤ አላህ ለአንድ ባሪያ ይቅር በማለቱ (ምክንያት) ከልቅና በስተቀር አይጨምርለትም፤ አንድም ሰው ለአላህ ብሎ አይተናነስም አላህ ከፍ ያደረገው ቢሆን እንጂ።" [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ምፅዋት ከሰጪው ላይ መከራን ትከላከላለች እንጂ ገንዘቡን እንደማታጎድል፤ አላህ ለሰጪው ትልቅ መልካምን እንደሚተካለትና መመፅወቱ ጭማሪ እንጂ ጉድለት እንደማይሆን ገለፁ።

መበቀል ወይም ባለቤቱን መቅጣት እየተቻለም ይቅር ማለት ኃይልና ልቅናን እንጂ አይጨምርም።

አንድም ሰው ማንንም ፈርቶ፣ ለማስመሰልና ከሱ ጥቅም ፈልጎ ሳይሆን ለአላህ ፊት ብሎ አይተናነስምም ዝቅ አይልምም ምንዳው ልቅናና ከፍታ ቢሆን እንጂ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. አንዳንድ ሰዎች ከዚህ ተቃራኒ ቢያስቡም መልካምና ስኬት የሚገኘው ሸሪዐን በመተግበርና መልካምን በመፈፀም ነው።

(5512)

(١٨٢) - عن أبي هريرة رضي الله عنه أن رسول الله صلى الله عليه وسلم قال: «قَالَ اللهُ: أَنْفِقْ يَا ابْنَ آدَمَ أُنْفِقْ عَلَيْكَ». [صحيح] - [متفق عليه]

(182) - ከአቡ ሁረይራ -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው የአላህ መልክተኛ ሶለሏሁ ዓለይሂ ወሰለም እንዲህ ብለዋል፡- "አላህ እንዲህ ብሏል 'የአደም ልጅ ሆይ! ስጥ ላንተም ይሰጥሃል!'" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ከፍ ያለውና የላቀው አላህ "የአደም ልጅ ሆይ! ግዴታም ይሁን ተወዳጅ የሆኑብህን ወጪዎች ለግስ! ላንተም ሲሳይን አሰፋልሃለሁ፣ ያዋጣኸውን ወጪ ልውጫ እሰጥሃለሁ፣ በሰጠሁህም ነገር ላንተ እባርክልሃለሁ" ማለቱን ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ተናገሩ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. በአላህ መንገድ መስጠትና መመፅወት መበረታታቱን እንረዳለን።
2. መልካም በሆኑ መንገዶች ላይ ወጪ ማድረግ ሲሳያችን በረከት እንዲያገኝና እንዲባዛ ከሚያደርጉ እንዲሁም ሰውዬው ያወጣውን ወጪ አላህ እንዲተካለት ከሚያደርጉ ትልልቅ ምክንያቶች መካከል ነው።

3. ይህ ሐዲሥ ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ከጌታቸው ከሚያስተላልፉት ሐዲሥ መካከል አንዱ ነው። ሐዲሠል ቁድሲይ ወይም ሐዲሠል ኢላሂይ በመባል ይጠራል። ቃሉም ሀሳቡም ከአላህ ሲሆን ነገር ግን ቁርአን ከሌሎች የተለየበት የሆኑ በማንበቡ (በየፊደላቱ ሐሰና የሚያስገኘውን) አምልኮን መፈፀም፣ እሱን ለማንበብ ውዱእ ማድረግና አምሳያውን ማንም እንደማያመጣ መነገሩ፣ ተአምራዊነቱና ከዚህም ውጪ ያሉ የቁርአን መለዮዎችን አልያዘም።

(5805)

(١٨٣) - عن أبي مسعود رضي الله عنه عن النبي صلى الله عليه وسلم قال: «إِذَا أَنْفَقَ الرَّجُلُ عَلَى أَهْلِهِ يَحْتَسِبُهَا فَهُوَ لَهُ صَدَقَةٌ». [صحيح] - [متفق عليه]

(183) - ከአቡ መስዑድ -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላትና- እንደተላለፈው ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንዲህ ብለዋል: "ሰውዬው (ምንዳ እንደሚያገኝበት) እያሰበ ለቤተሰቡ ወጪ ያወጣ ጊዜ ለርሱ ምፅዋት ትሆንለታለች።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

**ትንታኔ:**

ሰውዬው እንደሚስቱ፣ ወላጆቹ፣ ልጁና ሌሎችንም እነርሱ ላይ ወጪ ማውጣት ግዴታ ለሆነበት አካል ሲሰጥ ወደ አላህ መቃረብንና አላህ ዘንድ ምንዳን እያሰበ ከሆነ ለርሱ የምፅዋት ምንዳ እንደሚሰጠው ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ተናገሩ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ለቤተሰቦች ወጪ በማውጣት ምንዳና አጅር እንደሚገኝ እንረዳለን።
2. ሙእሚን የሆነ ሰው በስራው የአላህን ፊትና እርሱ ዘንድ ያለውን ምንዳና አጅር እንደሚፈልግ እንረዳለን።

3. በሁሉም ስራዎች መልካምን ኒያ ማድረግ ይገባል። ከነዚህም ስራዎች መካከል ለቤተሰቦች ወጪ በምናወጣ ጊዜ አንዱ ነው።

(6460)

(١٨٤) - عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ رضي الله عنه أَنَّ رَسُولَ اللهِ صلى الله عليه وسلم قَالَ: «إِذَا مَاتَ الْإِنْسَانُ انْقَطَعَ عَنْهُ عَمَلُهُ إِلَّا مِنْ ثَلَاثَةٍ: إِلَّا مِنْ صَدَقَةٍ جَارِيَةٍ، أَوْ عِلْمٍ يُنْتَفَعُ بِهِ، أَوْ وَلَدٍ صَالِحٍ يَدْعُو لَهُ».
[صحيح] - [رواه مسلم]

(184) - ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: የአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና እንዲህ ብለዋል: "የሰው ልጅ ሲሞት ከሶስት ስራዎቹ ውጪ ስራዎቹ ከርሱ ይቋረጣሉ። ሰደቀቱል ጃሪያህ (ተሻጋሪ ምፅዋቶቹ) ወይም ጠቃሚ ዕውቀት ያስተላለፈ ወይም ለርሱ ዱዓ የሚያደርግለት መልካም ልጅ ያለው ሲቀር ሌሎቹ ስራዎቹ ይቋረጣሉ።" [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና የሞተ ሰው በመሞቱ ስራው እንደሚቋረጥ፤ ከነዚህ ሶስት ስራዎች ውጪም ከሞተ በኋላ ምንዳ የሚያገኝበት እንደሌለው ተናገሩ። ሶስቱ ስራዎች ግን ሰበባቸው እርሱ ስለሆነ አይቋረጡም።

የመጀመሪያው: እንደወቅፍ፣ መስጂድ መገንባት፣ ጉድጓድ መቆፈርና ሌሎች ምንዳቸው የማይቋረጥና የሚዘወትር ምፅዋት ናቸው።

ሁለተኛው: ጠቃሚ ዕውቀትን ያስተላለፈ፡ ዕውቀት ሰጪ መጽሐፍትን እንደመፃፍ፣ የሆነን ግለሰብ ማስቀራትና ከሞተ በኋላ ይህ የቀራው ግለሰብ እውቀቱን በማሰራጨት ላይ መሳተፍን የመሰለ ሰዎች የሚጠቀሙበት እውቀት ነው።

ሶስተኛው: ለወላጆቹ ዱዓ የሚያደርግ አማኝ መልካም ልጅ ነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. የሰው ልጅ ከሞተ በኋላ የሚደርሰው ምንዳ ተሻጋሪ ምፅዋት፣ በርሱ ሰዎች የሚጠቀሙበት እውቀት ያስተላለፈ እና ዱዓ እንደሆነ የእውቀት ባለቤቶች ባጠቃላይ ተስማምተዋል። ልክ እንደዚሁ ሐጅም ከሞተ በኋላ እንደሚደርሰው በሌላ ሐዲሥ መጥቷል።
2. ሐዲሡ ውስጥ ሶስቱ ብቻ የተጠቀሱት ሶስቱም የመልካም ስራ መሰረቶች ስለሆኑ እና አብዛኛው ጊዜ ባለፀጋዎቹ ከነርሱ ህልፈት በኋላ ይቀራሉ ብለው የሚያስቧቸው እነዚህን ስለሆነ ነው።
3. ማንኛውም ሰዎች በርሱ የሚጠቀሙበት እውቀት ምንዳ ይገኝበታል። ነገር ግን ዋናውና ቁንጮው ሸሪዓዊ እውቀትና የሸሪዓን እውቀት ለመረዳት የሚያግዙ እውቀቶች ናቸው።
4. እውቀት ከሶስቱም እጅግ ጠቃሚው ነው። ምክንያቱም በእውቀት የሚማረው ሰው ይጠቀምበታል፤ በእውቀት ሸሪዓን መጠበቅ ይገኝበታል፤ በእውቀት ፍጡራን ባጠቃላይ ይጠቀማሉ። እውቀት አዳራሽና አጠቃላይ ነው። በህይወት እያለህ ያሉትም ይሁኑ ከሞትክ በኋላ ያሉትም ትተህ ያለፍከው እውቀትህን ይቀስማሉ።
5. መልካም ልጆችን በማነፅ ላይ መነሳሳቱን እንረዳለን። በመጪው አለም ወላጆቻቸውን የሚጠቅሙት እነርሱ ናቸውና። ከመልካም ልጆች ጥቅም መካከል ለወላጆቻቸው የሚያደርጉት ዱዓ አንዱ ነው።
6. ወላጆች ከሞቱ በኋላ ለነርሱ በጎ በመስራት ላይ መነሳሳቱን እንረዳለን። ይህ እነርሱ ብቻ ሳይሆኑ ልጅም ጭምር የሚጠቀምበት በጎ ስራ ነው።
7. ከልጅ ውጪ ቢሆን ራሱ ለሞተ ሰው ዱዓ ማድረግ ሟችን ይጠቅማል። ነገር ግን ተለይቶ ልጅ የተጠቀሰው አብዛኛው ጊዜ እስኪሞት ድረስ ሳያቋርጥ ለአንድ ሰው ዱዓ ሊያደርግ የሚችለው ልጅ ስለሆነ ነው።

(65566)

(١٨٥) - عَنْ مَالِكِ بْنِ أَوْسِ بْنِ الْحَدَثَانِ أَنَّهُ قَالَ: أَقْبَلْتُ أَقُولُ مَنْ يَصْطَرِفُ الدَّرَاهِمَ؟ فَقَالَ طَلْحَةُ بْنُ عُبَيْدِ اللهِ وَهُوَ عِنْدَ عُمَرَ بْنِ الْخَطَّابِ رضي الله عنهما: أَرِنَا ذَهَبَكَ، ثُمَّ ائْتِنَا، إِذَا جَاءَ خَادِمُنَا، نُعْطِكَ وَرِقَكَ، فَقَالَ عُمَرُ بْنُ الْخَطَّابِ: كَلَّا، وَاللهِ لَتُعْطِيَنَّهُ وَرِقَهُ، أَوْ لَتَرُدَّنَّ إِلَيْهِ ذَهَبَهُ، فَإِنَّ رَسُولَ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ قَالَ: «الْوَرِقُ بِالذَّهَبِ رِبًا، إِلَّا هَاءَ وَهَاءَ، وَالْبُرُّ بِالْبُرِّ رِبًا، إِلَّا هَاءَ وَهَاءَ، وَالشَّعِيرُ بِالشَّعِيرِ رِبًا، إِلَّا هَاءَ وَهَاءَ، وَالتَّمْرُ بِالتَّمْرِ رِبًا، إِلَّا هَاءَ وَهَاءَ». [صحيح] - [متفق عليه]

(185) - ከማሊክ ቢን አውስ ቢን ሐደሣን እንደተላለፈው እንዲህ አለ: «ዲርሃም የሚመነዝርልኝ እያልኩኝ ተዘዋወርኩኝ። ጦልሓ ቢን ዑበይዲላህ ከዑመር ቢን ኸጧብ (ረዲየሏሁ ዐንሁማ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና ዘንድ እያለ እንዲህ አለኝ: "ወርቅህን አሳየንና ከዚያም ተመልሰህ ና! አገልጋያችን የመጣ ጊዜ ገንዘብህን እንሰጥሃለን።" በዚህ ጊዜ ዑመር ቢን ኸጧብ እንዲህ አለ: "በፍፁም! በአላህ እምላለሁ! ወይ አሁን ብሩን ትሰጠዋለህ ወይም ወርቁን ትመልስለታለህ! የአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና እንዲህ ሲሉ ሰምቻቸዋለሁ: ‹ብር በወርቅ እጅ በእጅ ካልሆነ በቀር አራጣ ነው፤ ስንዴ በስንዴ መለዋወጥ እጅ በእጅ ካልሆነ በቀር አራጣ ነው፤ ገብስ በገብስ መለዋወጥ እጅ በእጅ ካልሆነ በቀር አራጣ ነው፤ ተምር በተምር መለዋወጥ እጅ በእጅ ካልሆነ በቀር አራጣ ነው።›"» [ሶሒሕ ነው። ] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ታቢዒዩ ማሊክ ቢን አውስ እርሱ ዘንድ በብር ዲርሃም ሊመነዝራቸው የፈለጋቸው የወርቅ ዲናሮች እንደነበሩት ተናገረ። ጦልሓ ቢን ዑበይዲላህ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - ለርሱ "ዲናርህን አምጣና እንየው።" አለ። ቀጥሎ አይቶ ለመግዛት ከወሰነ በኋላ "የብሩን ዲርሃም እንድንሰጥህ በኋላ አገልጋያችን ከመጣ በኋላ ና።" አለው። ዑመር ቢን አልኸጧብ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - ቦታው ላይ ነበሩና የዚህን አይነት ግብይይት አወገዙ።

ለጦልሓም ብሩን አሁኑኑ እንዲሰጥ አልያም የወሰደውን ወርቅ እንዲመልስ ምሎ ነገረው። የዚህም ምክንያት የአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ብር በወርቅ መለዋወጥ ወይም በተገላቢጦሹ መለዋወጥ ተለዋዋጩ በቀጥታ መቀባበል እንዳለበት ያለበለዚያ ግን ይህ ግብይት የተከለከለው አራጣዊና ትክክል ያልሆነ ግብይት እንደሚሆን ማውሳታቸውን ስለዚህም ወርቅ በብር ብር በወርቅ እጅ በእጅ ካልሆነና የተሟላ የሆነ ቅብብል ከሌለ በቀር መገበያየት እንደማይፈቀድ፤ ልክ እንደዚሁ ስንዴ በስንዴ፣ ገብስ በገብስ፣ ተምር በተምር መለዋወጥ አምሳያውን በአምሳያው፣ ኪሎ በኪሎ፣ ስፍር በስፍር፣ እጅ በእጅ ካልሆነ በቀር መገበያየት እንደማይፈቀድ፤ ከነዚህ ውስጥ አንዳቸውም አንዱን አሁን አንዱን ዘግይቶ መሰጣጠት እንደማይፈቀድና ከመቀባበል በፊት መለያየትም አለመፈቀዱን ነቢዩ የአላህ ሶዋትና ሰላም (ሶለሏሁ ዓለይሂ ሰለም) ማውሳታቸውን ዑመር ገለፁ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. እዚህ ሐዲሥ ውስጥ የተጠቀሱት የገንዘብ አይነቶች አምስት ናቸው: ወርቅ፣ ብር፣ ስንዴ፣ ገብስና ተምር ናቸው። ወርቅን በወርቅ እንደመገበያየት አይነቱ ግብይቱ ተመሳሳይ አይነቶችን በመለዋወጥ ከሆነ ግብይቱ ተቀባይነት እንዲያገኝ ሁለት መስፈርቶች ሊሟሉ ይገባል: በውሉ ስፍራ ላይ መለዋወጥና ሚዛኑም መመሳሰል ይገባዋል። ይህ ካልሆነ ግን ግብይቱ የማበላለጥ አራጣ ይሆናል። በስንዴ ብር መለዋወጥን ይመስል ግብይቱ የሚካሄደው በተለያዩ የገንዘብ አይነቶች ከሆነ ግን ግብይቱ ተቀባይነት እንዲያገኝ አንድ መስፈርት ነው ያለው: እርሱም በውሉ ስፍራ ዋጋውን መቀባበል ነው። ያለበለዚያ ግን የማዘግየት አራጣ ይሆናል።
2. የውሉ ስፍራ በማለት የተፈለገበት: ተቀምጠውም ሆነ፣ እየሄዱም ሆነ፣ እየጋለቡም ሆነ የመገበያያው ስፍራውን ነው። ከግብይይቱ ሲለያዩ በማለት የተፈለገው ደግሞ በተለምዶ ተገበያዮች በመካከላቸው ተለያዩ ተብሎ የሚታሰበው ሲከሰት ማለት ነው።

3. ሐዲሡ ውስጥ ያለው ክልከላ ለመገበያያ የተበጀውንም ይሁን ሌሎቹን የወርቅና የብር አይነቶችን ባጠቃላይ ያካትታል።
4. በዚህ ዘመን የምንጠቀመው መገበያያ ገንዘብም ምንዛሬም በወርቅና ብር ላይ ግዴታ የሆነው ነገር እርሱም ላይ ግዴታ ይሆናል። ማለትም አንድን ጥሬ ገንዘብ በሌላ ጥሬ ገንዘብ መመንዘር ከፈለግክ ሪያልን በዲርሃም መመንዘር ይመስል ሁለቱ ወገኖች በተስማማቸው መልኩ ማበላለጥ ይፈቀድላቸዋል። ነገር ግን ግብይቱ በተፈፀመበት ስፍራ (ወዲያውኑ) መለዋወጥ ግዴታ ነው። ያለበለዚያ ስምምነታቸውም ተቀባይነት አይኖረውም፤ ግብይታቸውም ክልክል የሆነው አራጣዊ ግብይት ይሆናል።
5. አራጣዊ ግብይት አይፈቀድም። ሁለቱ ወገኖች ቢስማሙ እንኳ ስምምነቱም ተቀባይነት የለውም። እስልምና ግለሰብም ይሁን ማህበረሰብ ሐቁን ችላ ቢልም እንኳ ሐቁን ይጠብቅለታልና።
6. የቻለ ሰው መጥፎን ነገር መከልከልና ማውገዝ እንዳለበት እንረዳለን።
7. ዑመር ቢን አልኸጧብ እንዳደረጉት መጥፎን በምናወግዝበት ወቅት ማስረጃን መጥቀስ እንደሚገባ እንረዳለን።

(5889)

(١٨٦) - عَنْ عَبْدُ اللهِ بْنُ سَلَامٍ رضي الله عنه قَالَ: لَمَّا قَدِمَ النَّبِيُّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ الْمَدِينَةَ انْجَفَلَ النَّاسُ قِبَلَهُ، وَقِيلَ: قَدِمَ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ، قَدِمَ رَسُولُ اللهِ، قَدِمَ رَسُولُ اللهِ ثَلَاثًا، فَجِئْتُ فِي النَّاسِ لِأَنْظُرَ، فَلَمَّا تَبَيَّنْتُ وَجْهَهُ، عَرَفْتُ أَنَّ وَجْهَهُ لَيْسَ بِوَجْهِ كَذَّابٍ، فَكَانَ أَوَّلُ شَيْءٍ سَمِعْتُهُ تَكَلَّمَ بِهِ أَنْ قَالَ: «يَا أَيُّهَا النَّاسُ، أَفْشُوا السَّلَامَ، وَأَطْعِمُوا الطَّعَامَ، وَصِلُوا الْأَرْحَامَ، وَصَلُّوا بِاللَّيْلِ وَالنَّاسُ نِيَامٌ، تَدْخُلُوا الْجَنَّةَ بِسَلَامٍ». [صحيح] - [رواه الترمذي وابن ماجه وأحمد]

(186) - ከዐብደላህ ቢን ሰላም (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: «ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) መዲና የገቡ ጊዜ ሰዎች ወደርሳቸው በፍጥነት ሄዱ። የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ገቡ፤ የአላህ መልክተኛ ገቡ፤ የአላህ መልክተኛ ገቡ - ሶስት ጊዜ - እየተባለ ተወራ። ለመመልከትም ከሆኑ ሰዎች ጋር መጣሁ። ፊታቸውን የተመለከትኩኝ ጊዜ ፊታቸው የውሸታም ፊት እንዳልሆነ አወቅኩ። መጀመሪያ ሲናገሩ የሰማሁት ነገር እንዲህ ሲሉ ነው: "እናንተ ሰዎች ሆይ! ሰላምታን አስፋፉ፣ ምግብንም አብሉ፣ ዝምድናን ቀጥሉ፣ ሰዎች በተኙበት በሌሊት ስገዱ ጀነት ትገባላችሁ በሰላም።"» [ሶሒሕ ነው።] - [ቲርሚዚ፣ ኢብኑ ማጀህና አሕመድ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና መዲና መጥተው ሰዎች የተመለከቷቸው ጊዜ ወደርሳቸው አቅጣጫ በፍጥነት ሄዱ። ዐብደላህ ቢን ሰላምም ያኔ አይሁድ ነበርና ወደርሳቸው ከመጡት መካከል አንዱ ነው። እርሳቸውን ሲያይም በርሳቸው ላይ ብርሃንን፣ ውበትንና እውነተኛ ግርማን በማየቱ ፊታቸው የውሸታም ፊት እንዳልሆነ አወቀ። ከነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) አንደበት ለመጀመሪያ የሰማውም ነገር ሰዎችን ጀነት ለመግባት ሰበብ የሚሆናቸውን ተግባራት ላይ ማነሳሳታቸውን ነው።

መጀመሪያ: ባወቅከውም ይሁን ባላወቅከውም ሰው ላይ ሰላምታን ማሰራጨት፣ ከፍ ማድረግና ማብዛት ነው።

ሁለተኛ: ምግብን በሶደቃ፣ በስጦታና በእንግድነት መልክ ማብላት ነው።

ሶስተኛ: በአባት ወይም በእናት በኩል ቅርበትና ዝምድና ከምታስተሳስርህ አካል ጋር ዝምድናን መቀጠል ነው።

አራተኛ: ሰዎች በተኙበት ለሱና (ግዴታ ላልሆነ) ሶላት ሌሊት መቆም ነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. በሙስሊሞች መካከል ሰላምታን ማሰራጨት እንደሚወደድ እንረዳለን። ሙስሊም ያልሆኑ ሰዎችን ግን (አሰላሙ ዓለይኩም) በሚል ሰላምታ አይጀመሩም። ሙስሊም ያልሆነ ሰው ራሱ "አሰላሙ ዐለይኩም" በማለት ሰላምታን ካቀረበ "ወዐለይኩም" በማለት ይመልስለታል።

(5520)

(١٨٧) - عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ رضي الله عنه قَالَ: قَالَ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ: «أَيُّهَا النَّاسُ، إِنَّ اللهَ طَيِّبٌ لَا يَقْبَلُ إِلَّا طَيِّبًا، وَإِنَّ اللهَ أَمَرَ الْمُؤْمِنِينَ بِمَا أَمَرَ بِهِ الْمُرْسَلِينَ، فَقَالَ: {يَا أَيُّهَا الرُّسُلُ كُلُوا مِنَ الطَّيِّبَاتِ وَاعْمَلُوا صَالِحًا، إِنِّي بِمَا تَعْمَلُونَ عَلِيمٌ} [المؤمنون: 51] وَقَالَ: {يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا كُلُوا مِنْ طَيِّبَاتِ مَا رَزَقْنَاكُمْ} [البقرة: 172] ثُمَّ ذَكَرَ الرَّجُلَ يُطِيلُ السَّفَرَ أَشْعَثَ أَغْبَرَ، يَمُدُّ يَدَيْهِ إِلَى السَّمَاءِ: يَا رَبِّ، يَا رَبِّ، وَمَطْعَمُهُ حَرَامٌ، وَمَشْرَبُهُ حَرَامٌ، وَمَلْبَسُهُ حَرَامٌ، وَغُذِيَ بِالْحَرَامِ، فَأَنَّى يُسْتَجَابُ لِذَلِكَ؟». [صحيح] - [رواه مسلم]

(187) - ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: «የአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና እንዲህ ብለዋል: "እናንተ ሰዎች ሆይ! አላህ መልካም (ጥሩ) ነውና ከመልካም (ከጥሩ) በቀር አይቀበልም። አላህ መልክተኞችን ባዘዘው ነገር አማኞችንም አዟል። አላህ እንዲህ ብሏል: {እናንተ መልክተኞች ሆይ! ከተፈቀዱት ምግቦች ብሉ። በጎ

ስራንም ስሩ። እኔ የምትሰሩትን ሁሉ አዋቂ ነኝ።} [አልሙእሚኑን:51] እንዲህም ብሏል: {እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ከነዚያ ከሰጠናችሁ ጣፋጮችን ብሉ።} [አልበቀራህ: 172]" ቀጥለውም ጉዞ የሚያረዝም፣ ጨብራራ፣ ፊቱንና ልብሱን አቧራ ያለበሰው አንድ ሰውዬ አወሱ። እጁን ወደ ሰማይ እየዘረጋ: "ጌታዬ ሆይ! ጌታዬ ሆይ! እያለ ይለምናል። ምግቡ ሐራም ነው። መጠጡ ሐራም ነው። ልብሱ ሐራም ነው። በሐራም ነው የተገነባው። እንዴት ለርሱ ዱዓው ተቀባይነት ይኖረዋል?" አሉ።» [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና አላህ መልካም፣ ከጉድለትና ነውር የጠራና የፀዳ፣ በምሉዕነት የሚገለፅ መሆኑን ተናገሩ፤ ከተግባርም፣ ከንግግርና ከእምነትም መልካም የሆነውን እንጂ እንደማይቀበል ተናገሩ። እርሱም ለአላህ ጥርት ተደርጎ የተሰራና የነቢዩን (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና መመሪያ የተከተለ ስራ ነው። በዚህ ካልሆነ በቀርም ወደ አላህ መቃረብ አይገባም። ለአንድ አማኝ ስራው መልካም ከሚሆንበት ትላልቅ ነገሮች መካከል ምግቡ መልካም መሆኑ ነው። ይህም የተፈቀደውን መመገቡ ነው። በዚህም ስራው ይፀዳል። ስለዚህም የተፈቀደን በመብላትና መልካም በመስራት አላህ መልክተኞችን እንዳዘዘው ሁሉ አማኞችንም አዘዘ። አላህ እንዲህ አለ: {እናንተ መልክተኞች ሆይ! ከተፈቀዱት ምግቦች ብሉ። በጎ ስራንም ስሩ። እኔ የምትሰሩትን ሁሉ አዋቂ ነኝ።} እንዲህም አለ: {እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ከነዚያ ከሰጠናችሁ ጣፋጮችን ብሉ።}

ቀጥለው ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ምንም ያህል ተቀባይነትን የሚያስገኙ ግልፅ ሰበቦችን ቢፈፅም ስራን የሚያበላሽና ተቀባይነቱን የሚያሳጣ ከሆነው ሐራም ምግብ ከመብላት አስጠነቀቁ። ለዱዓ ተቀባይነትን ያስገኛሉ ከተባሉት ግልፅ ሰበቦች መካከልም:

የመጀመሪያ: እንደ ሐጅ፣ ጂሃድ፣ ዝምድናን መቀጠልና ከዚህም ውጪ ላሉ ነገሮች ለአምልኳዊ አላማዎች ጉዞን ማርዘም ነው።

ሁለተኛው: ባለማበጠር ምክንያት የፀጉሩ መበታተንና በአፈር (በአቧራ) ምክንያት የልብሱ ቀለምና የሰውነት መልኩ መለወጡ ነው። ይህም አስገዳጅ ችግር የገጠመው መሆኑ ነው።

ሶስተኛው: ወደ ሰማይ ዱዓ በማድረግ እጁን ከፍ ያደርጋል።

አራተኛው: ጌታዬ ሆይ! ጌታዬ ሆይ! እያለ ወደ አላህ በስሞቹ ይቃረባል፣ በዚህም ችክ ይላል።

ከነዚህ ለዱዓ ተቀባይነትን ከሚያስገኙ ምክንያቶች ጋር ሆኖም ግን ዱዓው አልተሰማም። ይህም ምግቡ፣ መጠጡና ልብሱ ሐራም ስለሆነና በሐራም ስለተገነባ ነው። ባህሪው ይህ የሆነ ሰው ተቀባይነት ማግኘቱም ሩቅ ነው። አላህስ እንዴት ዱዓውን ይቀበለዋል?

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. አላህ ዐዘ ወጀል በዛቱ፣ በባህሪው፣ በድርጊቱና በህግጋቶቹ ምሉዕ መሆኑን እንረዳለን።
2. ስራን ለአላህ ዐዘ ወጀል በማጥራት ላይና ነቢዩን (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና በመከተል ላይ መነሳሳቱን እንረዳለን።
3. "አላህ መልክተኞችን ባዘዘው ነገር አማኞችንም አዟል።" ከሚለው የነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ንግግር ለስራ የሚያነሳሳን አገላለፅ መጠቀም እንደሚገባ እንረዳለን። አንድ አማኝ ይህ ነገር መልክተኞችም የታዘዙት ነገር መሆኑን ሲያውቅ ለመተግበር ይበራታልም ይነሳሳልም።
4. ዱዓን ተቀባይነት ከሚያሳጡ ነገሮች መካከል ሐራም መብላት አንዱ ነው።
5. ዱዓ ተቀባይነት እንዲኖረው ከሚያደርጉ ሰበቦች መካከል አምስት ነገሮች ይገኛሉ: አንደኛ: ጉዞ ማርዘም ነው። በጉዞ ውስጥ ዱዓ ተቀባይነት ከሚያስገኙ ሰበቦች መካከል ትልቁ ሰበብ የሆነው ስብር (በጣም

መተናነስን) ማለትን አቅፏልና። ሁለተኛ: በጭንቅ ሁኔታ ላይ መሆን። ሶስተኛ: እጆችን ወደ ሰማይ መዘርጋት። አራተኛ: የአላህን ጌትነት ደጋግሞ በማውሳት አላህ ላይ ችክ ማለት ሲሆን ይህም ዱዓ ተቀባይነት ያስገኛል ከሚባሉት መካከል ትልቁ ሰበብ ነው። አምስተኛ: ምግብና መጠጥን ማሳመር ናቸው።

6. መልካምና ሐላል መብላት ለመልካም ስራ ከሚያግዙ ምክንያቶች መካከል አንዱ ነው።
7. ቃዲ እንዲህ ብለዋል: መልካም (ጥሩ) ማለት የቆሻሻ ተቃራኒ ነው። በዚህ ባህሪ የተገለፀው አሏህ ሲሆን የሚፈለገው እርሱ ከጉድለቶች የፀዳ መሆኑንና ከእንከኖች የጠራ መሆኑን ነው። የተገለፀው በጥቅሉ ባሪያ ሲሆን ደግሞ ከውዳቂ ስነምግባርና ከፀያፍ ተግባራት የፀዳ መሆኑንና ከዚህ ተቃራኒ የሆነን ማንነት የተላበሰ መሆኑን የሚገልፅ ነው። ገንዘብ ሲገለፅበት ደግሞ ገንዘቡ ሐላል መሆኑንና ከምርጥ ገንዘብ መካከል እንደሆነ የሚገልፅ ነው።

(4316)

(١٨٨) - عن أبي هريرة رضي الله عنه قال: قال رسول الله صلى الله عليه وسلم: «مَنْ أَنْظَرَ مُعْسِرًا، أَوْ وَضَعَ لَهُ، أَظَلَّهُ اللهُ يَوْمَ الْقِيَامَةِ تَحْتَ ظِلِّ عَرْشِهِ يَوْمَ لَا ظِلَّ إِلَّا ظِلُّهُ».
[صحيح] - [رواه الترمذي وأحمد]

(188) - ከአቡ ሁረይራ -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸው - እንዳስተላለፉት እንዲህ ብለዋል፦ የአላህ መልዕክተኛ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ ብለዋል፦ "ለተቸገረ (ባለዕዳ) ጊዜ የሰጠ ወይም ይቅር ያለ አላህ ከጥላው በስተቀር ጥላ በሌለበት የትንሳኤ ቀን ከዐርሹ ጥላ ስር ያስጠልለዋል።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቲርሚዚና አሕመድ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ለተበዳሪ የእዳ መክፈያ ጊዜውን ያዘገየለት ወይም ያለበትን እዳ ከሱ ላይ ይቅር ያለ ምንዳው፦

የትንሳኤ ቀን ፀሀይ ወደ ሰዎች አናት ቀርባ ሀሩሯ በነሱ ላይ በሚበረታበት ወቅት አላህ ከዐርሹ ስር እንደሚያስጠልላቸው ተናገሩ። አላህ ያስጠለለው ሰው ካልሆነ በስተቀር አንድም ሰው ጥላ አያገኝም።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ለአላህ ባሮች ነገሮችን የማቅለል ትሩፋቱ፤ እሱም ከትንሳኤ ቀን መከራዎች የመዳኛ ምክንያት ነው።
2. ምንዳ የሚሰጠን በስራችን ልክ ነው።

(4186)

(١٨٩) - عن جابر رضي الله عنه أن رسول الله صلى الله عليه وسلم قال: «رَحِمَ اللَّهُ رَجُلًا سَمْحًا إِذَا بَاعَ، وَإِذَا اشْتَرَى، وَإِذَا اقْتَضَى». [صحيح] - [رواه البخاري]

(189) - ከጃቢር ረዲየሏሁ ዐንሁ እንደተላለፈው የአሏህ መልዕክተኛ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ ብለዋል፡ "ሲሸጥም፣ ሲገዛም ይሁን ያበደረውን ሲያስመልስ ገር የሆነን ሰው አሏህ ይዘንለት።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ሲሸጥ ለስላሳ፣ ቸርና ለጋስ ለሆነ ሁሉ የአሏህን እዝነት እንዲያገኝ ዱዓእ አደረጉለት፤ ይህም ዋጋውን በማናር ገዥን አያጨናንቅም፤ ይልቁን በመልካም ምግባር የሚደኗኗር ነው። ሲገዛም ለስላሳ፣ ቸርና ለጋስ ስለሆነ እቃውን በማሳነስና በማጣጣል ዋጋውን አያራክስም። ያበደረውን እዳ ሲያስመልስም ለስላሳ፣ ቸርና ለጋስ ስለሆነ ገንዘቡ እጅግ ያስፈለገውን ድሀ አያካብድበትም፤ ይልቁንም በእዝነትና ርህራሄ ይጠይቃል፤ ለተጨናነቀም የጊዜ ፋታ ይሰጣል።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. በሰዎች መካከል ያለን መስተጋብር ማስተካከል ሸሪዓው ከሚፈልጋቸው ዋንኛ ተፈላጊ ጉዳዮች መካከል መሆኑ፤
2. በሽያጭና በግዢም ይሁን በሌላም መስክ ከሰዎች ጋር ባለን መስተጋብር እጅግ ያማረውን ስነምግባር መላበስ የሚበረታታ መሆኑን እንረዳለን።

(3716)

(١٩٠) - عن أبي هريرة رضي الله عنه أن رسول الله صلى الله عليه وسلم قال: «كان رجلٌ يُدَايِنُ الناسَ، فكان يقول لفتاه: إذا أتيتَ مُعسِرًا فتجاوز عنه، لعل اللهَ يَتجاوزُ عنا، فلقي اللهَ فتجاوز عنه». [صحيح] - [متفق عليه]

(190) - ከአቢ ሁረይራ ረዲየሏሁ ዐንሁ እንደተላለፈው ረሱል የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ ብለዋል፡ "ሰዎች ጋር የሚበዳደር አንድ ሰውዬ ነበር። ለሰራተኛውም እንዲህ ይለው ነበር፡ 'ምናልባት አላህ እኛንም ይቅር ቢለን የተቸገረ ካጋጠመህ እለፈው።' (ሞተና) አላህንም ተገናኘ፤ አላህም ይቅር አለው።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

**ትንታኔ:**

ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ሰዎች ጋር በመበዳደር የሚንቀሳቀስ ወይም በዱቤ የሚሸጥላቸው ስለሆነ ሰው ተናገሩ። ለሰዎች ያበደረውን ብድር ለሚቀበልለት ሰራተኛውም እንዲህ ይለው ነበር፡ "ተበዳሪ ዘንድ ስትሄድ እዳውን መክፈል ተስኖት ካገኘሀው እለፈው" ይህም የሚከፍልበትን ፋታ በመስጠት፣ እዳውን በመፈለግ ላይ ችክ ባለማለት ወይም ጥቂት ቢጎድልም ያለውን በመቀበል ሊሆን ይችላል። ይህንንም የሚያደርገው አሏህ የእርሱንም ወንጀል እንዲያልፍለትና ይቅር እንዲለው ከመከጀል አኳያ ነበር። በሞተም ጊዜ አሏህም ማረው፤ ወንጀሉንም ይቅር አለለት።

**ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:**

1. ከሰዎች ጋር ባለ መስተጋብር መልካሙን መዋል፣ ይቅር ማለትና ሰው ሲቸግረው ብድሩን ማለፍ አንድ ባርያ በቂያማ እለት ከሚድንባቸው ትላልቅ ሰበቦች መካከል እንደሆነ፤
2. ለፍጡራን በጎ መዋል፣ ለአሏህ ስራን ጥርት ማድረግና እዝነቱንም መከጀል ለወንጀል መሀርታን ከሚያስገኙ ሰበቦች መካከል መሆኑን እንረዳለን።

(3753)

(١٩١) - عن خَولة الأنصاريةِ رضي الله عنها قالت: سمعت النبي صلى الله عليه وسلم يقول: «إِنَّ رِجَالًا يَتَخَوَّضُونَ فِي مَالِ اللهِ بِغَيْرِ حَقٍّ، فَلَهُمُ النَّارُ يَوْمَ الْقِيَامَةِ». [صحيح] - [رواه البخاري]

(191) - ከኸውለህ አልአንሷሪይ -አላህ መልካም ስራዋን ይውደድላትና- እንደተላለፈው እንዲህ አለች: ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንዲህ ሲሉ ሰምቻለሁ: "በአላህ ገንዘብ ያለአግባብ የሚገለገሉ ሰዎች ለነርሱ የትንሳኤ ቀን እሳት ተዘጋጅቶላቸዋል።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪ ዘግበውታል።]

**ትንታኔ:**

ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም የሙስሊሞችን ገንዘብ ያለአግባብ ስለሚጠቀሙና ያለአግባብ ስለሚበዘብዙ ሰዎች ተናገሩ። ይህም ገንዘብን ባልተፈቀደ መልኩ ማጠራቀምና ማግኘትን እንዲሁም ትክክለኛ ባልሆነ ቦታ ፈሰስ ማድረግን የሚጠቀልል ሀሳብ ነው። የየቲሞችን ገንዘብ መብላት፣ ወቅፍ የተደረገን ገንዘብ መብላት፣ አደራዎችን መካድ፣ የማህበረሰቡን ገንዘብ ያለአግባብ መውሰድ ሁሉ እዚህ ውስጥ ይካተታል።

ቀጥለውም ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም የትንሳኤ ቀን የነዚህ ሰዎች ምንዳ እሳት መሆኑን ተናገሩ።

**ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:**

1. በሰዎች እጅ ያሉ ገንዘቦች እሱ በደነገገላቸው መንገድ እንዲያወጡትና ያለአግባብ ከመገልገል ይርቁ ዘንድ ሰዎችን ምትክ ያደረገበት የአሏህ ገንዘቡ

ነው። ይህም መሪዎችንም ሆነ ሌሎችንም አጠቃላይ ሰዎችን የሚጠቀልል ነው።

2. ሸሪዓ በማህበረሰቡ ገንዘብ ዙሪያ ጥብቅ መሆኑን እንረዳለን። ከገንዘብ በጥቂቱም ቢሆን የተሾመ ሰው የትንሳኤ ቀን ስለገንዘቡ አሰባሰብም ሆነ ስለአወጣጡ ይተሳሰባል።
3. የራሱንም ገንዘብ ሆነ የሌላውን ገንዘብ ሸሪዓዊ ባልሆነ መልኩ የሚገለገልም በዚህ ዛቻ ይካተታል።

(5331)

(١٩٢) - عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ رَضِيَ اللهُ عَنْهُ قَالَ: قَالَ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ: «قَالَ اللهُ: كُلُّ عَمَلِ ابْنِ آدَمَ لَهُ، إِلَّا الصِّيَامَ، فَإِنَّهُ لِي وَأَنَا أَجْزِي بِهِ، وَالصِّيَامُ جُنَّةٌ، وَإِذَا كَانَ يَوْمُ صَوْمِ أَحَدِكُمْ فَلاَ يَرْفُثْ وَلاَ يَصْخَبْ، فَإِنْ سَابَّهُ أَحَدٌ أَوْ قَاتَلَهُ، فَلْيَقُلْ إِنِّي امْرُؤٌ صَائِمٌ، وَالَّذِي نَفْسُ مُحَمَّدٍ بِيَدِهِ، لَخُلُوفُ فَمِ الصَّائِمِ أَطْيَبُ عِنْدَ اللهِ مِنْ رِيحِ المِسْكِ، لِلصَّائِمِ فَرْحَتَانِ يَفْرَحُهُمَا: إِذَا أَفْطَرَ فَرِحَ، وَإِذَا لَقِيَ رَبَّهُ فَرِحَ بِصَوْمِهِ». [صحيح] - [متفق عليه]

(192) - ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: «የአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል: "አላህ እንዲህ ብሏል: ‹ሁሉም የአደም ልጅ ስራ ለርሱ ነው ፆም ሲቀር፤ ፆም ለኔ ነው። በርሱ የምመነዳውም እኔው ነኝ።› ፆም ጋሻ ነው። አንዳችሁ የፆም ቀኑ የሆነ ጊዜ ፀያፍ ቃልንም አይናገር አይጨህም። አንድ ሰው ከተሰዳደበው ወይም ከተጋደለው እኔ ፆመኛ ሰው ነኝ ይበል። የሙሐመድ ነፍስ በእጁ በሆነው ጌታ እምላለሁ! የፆመኛ ሰው የአፍ ጠረን አላህ ዘንድ ከሚስክ ሽታ የበለጠ ታውዳለች። ፆመኛ የሚደስትባቸው ሁለት ደስታ አሉት። ሲያፈጥርም ይደሰታል። ጌታውን የተገናኘ ጊዜም በመፆሙ ይደሰታል።"» [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና አላህ በሐዲሠል ቁድስ እንዲህ እንደሚል ተናገሩ:-

ሁሉም የአደም ልጅ መልካም ስራ ከአስር እስከ ሰባት መቶ እጥፍ ይነባበራል ፆም ሲቀር፤ ፆም ይዩልኝ የማይገባበት ስራ ነውና ለኔ ነው። እኔ ነኝ በርሱ የምመነዳው፤ የምንዳውን መጠንም ይሁን የአጅሩን መነባበር መጠን በማወቅ የተነጠልኩት እኔ ብቻ ነኝ።

ቀጥለው (ፆም ጋሻ ነው) አሉ። ከእሳት የሚጠብቅ ጋሻ፣ መሸሸጊያና መጠበቂያ ነው። ፆም ወንጀል ላይ ከመውደቅ ስሜትን የሚያቅብ ነው። እሳት በስሜቶች የተከበበች ናትና።

(አንዳችሁ የፆም ቀኑ የሆነ ጊዜ ፀያፍ ቃልን አይናገር) በግንኙነት ጉዳይም ይሁን ወደ ግንኙነት በሚያነሳሱ ነገሮች፤ በጥቅሉ የትኛውንም ፀያፍ ንግግር አይናገር።

(አይጬህም) በክርክርና በጩኸት አይናገር።

በረመዷን (አንድ ሰው ከተሰዳደበው ወይም ከተጋደለው) ከርሱ ሊቆጠብ ይከጀላልና እኔ ፆመኛ ሰው ነኝ ይበል። ሰውዬው ካልተጋደልኩ ብሎ ከደረቀ ሰው ሊያጠቃው ሲመጣ እንደሚያደርገው በቀላል መልኩ ይከላከለው።

ቀጥለው ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና በፆም ምክንያት የተለወጠ የፆመኛ አፍ ጠረን መዓዛው የትንሳኤ ቀን አላህ ዘንድ -እናንተ ዘንድ ካለው የሚስክ መአዛ የበለጠ- እንደሚያውድ፤ ምንዳው ደሞ በጁመዓና በዚክር መቀማመጥ ወቅት መቀባቱ ተወዳጅ ከሆነው ሚስክ የበለጠ ምንዳም እንደሚያስገኝ ነፍሳቸው በእጁ በሆነው ጌታ ምለው ተናገሩ።

ፆመኛ የሚደሰትባቸው ሁለት ደስታዎች አሉት: በሚያፈጥር ወቅት ማፍጠሩ ተፈቅዶለት አፍጥሮ ረሃቡና ጥሙ በመወገዱ፣ ፆሙ በመሙላቱና አምልኮው በመጠናቀቁ፣ በጌታው ማቅለያና ለቀጣይ ፆሙ ማገዣ በመቅመሱ ይደሰታል።

(ጌታውን የተገናኘ ጊዜም በፆሙ ይደሰታል።) በምንዳውና በክፍያው ይደሰታል።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. የፆም ትሩፋትን እንረዳለን። ፆም በዱንያ ፆመኛውን ከስሜት ይጠብቀዋል። በመጪው አለም ደግሞ ከእሳት ቅጣት ይጠብቀዋል።

2. ከፆም ስነ ስርዓቶች መካከል ፀያፍ ንግግርና ጫጫታን መተው፤ ሰው በሚያውከን ሰአት መታገስ፣ የነርሱን መጥፎ ተግባር አፀፋ በትእግስትና በመልካም መመለስ ይጠቀሳሉ።
3. ፆመኛ ወይም አንድ ባሪያ አምልኮው በመጠናቀቁና በመሙላቱ ምክንያት መደሰቱ በመጪው አለም ከሚያገኘው ምንዳ ምንም አያጎድልበትም።
4. የተሟላ ደስታ የሚገኘው አላህን በመገናኘት ነው። ይህም ታጋሾችና ፆመኞች ምንዳቸውን ያለቁጥር በሚመነዱበት ወቅት ማለት ነው።
5. አስፈላጊና ጠቃሚ ሆኖ በሚገኝበት ወቅት አምልኮ ላይ መሆንን ለሰዎች ማሳወቅ ይዩልኝ አያስብልም። (እኔ ፆመኛ) ነኝ ይበል ስላሉ።
6. አንድ ሰው የተሟላ ፆም ፆመ የሚባለው አካላቱ ወንጀል ከመፈፀም የቆጠበ ጊዜ፤ ምላሱ ከውሸት፣ ከፀያፍ ንግግርና የቅጥፈት ንግግር ከመናገር ዝም ያለ ጊዜ፤ ሆዱም ከምግብና መጠጥ የተከለከለ ጊዜ ነው።
7. ከጫጫታ፣ ከክርክርና ከመጬህ በአፅንዖት መከልከሉ ለፆመኛ ይበልጥ የበረታ ይሁን እንጂ ፆመኛ ያልሆነም ሰው ከነዚህ ተግባራት ተከልክሏል።
8. ይህ ሐዲሥ ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ከጌታቸው ከሚያወሩት ሐዲሥ መካከል ነው። "ሐዲሠል ቁድስ" ወይም "ሐዲሠል ኢላሂይ" በመባልም ይጠራል። ይህም ቃሉም መልዕክቱም ከአላህ ቢሆንም ቁርአን ከሌሎች የተለየበት የሆኑ - ማለትም ማንበቡ ብቻ አምልኮ መሆኑ፣ ለማንበብ ዉዱእ ማስፈለጉ፣ አላህ የርሱን አምሳያ አምጡ ብሎ መገዳደሩ፣ ተአምራዊነትና ሌሎችም- የቁርአን መገለጫዎች የሌሉት ነው።

(3546)

(١٩٣) - عن أبي هريرة رضي الله عنه قال: قال رسول الله صلى الله عليه وسلم: «مَنْ صَامَ رَمَضَانَ إِيمَانًا وَاحْتِسَابًا غُفِرَ لَهُ مَا تَقَدَّمَ مِنْ ذَنْبِهِ» [صحيح] - [متفق عليه]

(193) - ከአቡ ሁረይራ -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸው - እንዳስተላለፉት እንዲህ ብለዋል፡- የአላህ መልዕክተኛ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ ብለዋል፡- "(ግዴታነቱን) አምኖ እና ምንዳውን ከአላህ አስቦ የረመዳንን ወር የፆመ ሰው ያለፈ ወንጀሉ ይማርለታል።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን የረመዳንን ወር በአላህ አምኖ፣ በፆም ግዴታነትና አላህ ለፆመኞች ያዘጋጀውን የደለበ ምንዳና አጅር እውነት ብሎ እንዲሁም ፆሙም ለይዩልኝና ይስሙልኝ ሳይሆን የአላህን ፊት ፈልጎበት የፆመ ሰው ያለፈው ወንጀሉን እንደሚማር ነገሩን።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. በረመዳን ፆምም ይሁን በሌሎች መልካም ስራዎች ላይ ኢኽላስ ያለውን ትሩፋትና አንገብጋቢነትን እንረዳለን።

(4196)

(١٩٤) - عَنْ عَائِشَةَ أُمِّ الْمُؤْمِنِينَ رَضِيَ اللهُ عَنْهَا: كَانَ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ يَجْتَهِدُ فِي الْعَشْرِ الْأَوَاخِرِ مَا لَا يَجْتَهِدُ فِي غَيْرِهِ. [صحيح] - [رواه مسلم]

(194) - የአማኞች እናት ከሆነችው ከዓኢሻ (ረዲየሏሁ ዐንሃ) - አላህ መልካም ሥራዋን ይውደድላትና - እንደተላለፈው:- "የአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና በሌላ ጊዜያት ለአምልኮ ከሚጥሩት የተለየ በመጨረሻዎቹ አስሩ የረመዷን ቀናት ይጥሩ ነበር።" [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና የመጨረሻዎቹ አስሩ የረመዷን ቀናት የመጡ ጊዜ በአምልኮና ትርፍ ስራዎች ላይ ጥረት ያደርጉ ነበር። በሌላ ወቅት ይጥሩ ከነበሩት የበለጠ በመልካም ስራ አይነቶች፣ በአምልኮና፣ በበጎ አድራጎት ዘርፎች አበዝተው ይጥሩ ነበር። ይህም እንዚህ ሌሊቶች ያላቸው ደረጃ የላቀና ከፍያለ ስለሆነ እንዲሁም ለይለተል ቀደርንም ለመፈለግ ነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. በረመዷን ወር ባጠቃላይ በተለይ የመጨረሻዎቹ አስር ቀናት ላይ መልካም ስራዎችንና የተለያዩ አምልኮዎችን በማብዛት መነሳሳቱን እንረዳለን።
2. የመጨረሻዎቹ አስር የረመዷን ቀናት ከሀያ አንደኛው ምሽት ጀምሮ እስከ ወሩ መጨረሻ ድረስ ይሄዳል።
3. የላቁ ወቅቶችን በአምልኮ ማሳለፍ እንደሚወደድ እንረዳለን።

(3755)

(١٩٥) - عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ رَضِيَ اللهُ عَنْهُ قَالَ: أَوْصَانِي خَلِيلِي صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ بِثَلَاثٍ: صِيَامِ ثَلَاثَةِ أَيَّامٍ مِنْ كُلِّ شَهْرٍ، وَرَكْعَتَيِ الضُّحَى، وَأَنْ أُوتِرَ قَبْلَ أَنْ أَنَامَ. [صحيح] - [متفق عليه]

(195) - ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ ብለዋል፡- "ፍፁም ወዳጄ የሆኑት ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ሶስት ነገሮች ላይ አደራ ብለውኛል። ከሁሉም ወር ሶስት ቀናት በመጾምን፣ የዱሓን ሁለት ረከዓ በመስገድንና ከመተኛቴ በፊት ዊትር መስገድን አደራ ብለውኛል።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

አቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - ተወዳጁና ባልደረባው የሆኑት ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና በሶስት ነገሮች አደራ እንዳሏቸውና ቃልኪዳንም እንዳስገቧቸው ተናገሩ:

የመጀመሪያው: ከሁሉም ወር ሶስት ቀናትን መጾም ነው።

ሁለተኛው: በየቀኑ ሁለት ረከዓ ዱሓ መስገድ ነው።

ሶስተኛው: ከመተኛት በፊት ዊትር መስገድ ነው። ይህ ግን የሌሊቱ መጨረሻ ላይ አልነቃም ብሎ ለፈራ ነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ለሶሐቦቻቸው የሚመክሩት ምክር የሚለያየው ስለባልደረቦቻቸው ሁኔታ ባላቸው እውቀት ላይና ለእያንዳንዱ ሁሉ የሚስማማውን በማወቃቸው ላይ የተመሰረተ ነው። ጠንካራው ጂሃድ ይስማማዋል፤ አምላኪው አምልኮ ይስማማዋል፤ አዋቂው እውቀት ይስማማዋል፤ ልክ እንደዚሁ ሌሎቹንም እንደሚስማማቸው ይመክሯቸዋል።

2. ኢብኑ ሐጀር አልዐስቀላኒ እንዲህ ብለዋል: "በየሁሉም ወር ሶስት ቀን መጾም ሲሉ በግልፅ የሚፈለገው ጨረቃ የምትደምቅባቸው ቀኖችን ነው። እነሱም በሂጅሪያ አቆጣጠር የወሩ አስራ ሶስተኛ፣ አስራ አራተኛና አስራ አምስተኛ ቀኖች ናቸው።"
3. ኢብኑ ሐጀር አልዓስቀላኒ እንዲህ ብለዋል: "እዚህ ሐዲሥ ውስጥ ዊትርን ከእንቅልፍ ማስቀደም እንደሚወደድ እንረዳለን። ይህ ግን መንቃቱን ላልተማመነ ሰው ነው።"
4. ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና በርካታ ባልደረቦቻቸውን በነርሱ ማዘዛቸው የነዚህን ሶስት ስራዎች አንገብጋቢነት ያስረዳናል።
5. ኢብኑ ደቂቅ አልዒድ (የዱሓ ሁለት ረከዓ) በሚለው ንግግር ዙሪያ እንዲህ ብለዋል: "ምናልባት ቢያንስ መሰራት ያለበትን መጥቀሳቸው ይሆናል። በዚህም የዱሓ ሶላት ተወዳጅ መሆኑንና ትንሹም ሁለት ረከዓ መሆኑን ያስረዳናል።"
6. የዱሓ ሶላት ወቅት: ፀሐይ ከወጣች ከአስራ አምስት ደቂቃ በኋላ አካባቢ ይጀምርና እስከ ዙህር አስር ደቂቃ አካባቢ እስኪቀረው ነው። ቁጥሩም: ትንሹ ሁለት ረከዓ ነው። ብዙውስ በሚለው በዑለሞች መካከል የሃሳብ ልዩነት አለ። ስምንት ረከዓም ተብሏል። ገደብ የለውምም ተብሏል።
7. የዊትር ወቅት: ከዒሻ ሶላት በኋላ ጎህ እስኪወጣ ድረስ ነው። ትንሹ አንድ ረከዓ ነው። ብዙው አስራ አንድ ረከዓ ነው።

(4538)

(١٩٦) - عن أبي هريرة رضي الله عنه قال: قال رسول الله صلى الله عليه وسلم: «مَنْ يَقُمْ لَيْلَةَ الْقَدْرِ إِيمَانًا وَاحْتِسَابًا غُفِرَ لَهُ مَا تَقَدَّمَ مِنْ ذَنْبِهِ» [صحيح] - [متفق عليه]

(196) - ከአቡ ሁረይራ -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸው - እንዳስተላለፉት እንዲህ ብለዋል፦ የአላህ መልዕክተኛ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ ብለዋል፦ "መወሰኛይቱን ሌሊት (ለይለቱል ቀድርን) በአላህ አምኖና ምንዳውን አስቦ የቆመ ሰው ያለፈው ኃጢዓቱ ይማርለታል።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን በረመዳን ከመጨረሻዎቹ አስር ቀናት ውስጥ የምትገኘው መወሰኛይቱ ሌሊትን (ለይለቱል ቀድርን) የመቆም ትሩፋትን ተናገሩ። በዚህች ሌሊት በሷና ስለሷ ትሩፋት በመጡ ሐዲሦች አምኖ እንዲሁም በስራው ይዩልኝና ይስሙልኝን ሳይሆን የአላህን ምንዳ ከጅሎ በሶላት፣ በዱዓእ፣ ቁርአን በመቅራትና በዚክር የታገለ ሰው ያለፈውን ኃጢዓቱ ይማራል።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. የመወሰኛይቱ ሌሊት (የለይለቱል ቀድር) ትሩፋትና ይህቺን ሌሊት መቆም ላይ የሚበረታታ መሆኑ፤
2. መልካም ስራዎች ከእውነተኛ ኒያ ጋር ካልሆነ በቀር ተቀባይነት አያገኙም።
3. የመወሰኛይቱ ሌሊትን (የለይለቱል ቀድርን) አምኖና ምንዳውን አስቦ የቆመ ሰው ያለፈው ወንጀሉ ለሱ መማሩ የአላህን እዝነትና ትሩፋት እንረዳበታለን።

(4202)

(١٩٧) - عن أبي هريرة رضي الله عنه قال: سمعت النبي صلى الله عليه وسلم يقول: «مَنْ حَجَّ لِلَّهِ فَلَمْ يَرْفُثْ وَلَمْ يَفْسُقْ رَجَعَ كَيَوْمِ وَلَدَتْهُ أُمُّهُ». [صحيح] - [متفق عليه]

(197) - ከአቢ ሁረይራ ረዲየሏሁ ዐንሁ እንደተላለፈው፡ ነብዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንዲህ ሲሉ ሰምቻቸዋለሁ ብሏል፡- "ሚስቱን ሳይገናኝ እንዲሁም ሳያምፅ ለአሏህ ሐጅ አድርጎ የተመለሰ ልክ እናቱ እንደወለደችበት ቀን (ከወንጀል ንፁህ) ሆኖ ይመለሳል።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ሚስቱን ሳይገናኝ - "ረፈሥ" የሚለው ቃል ፆታዊ ግንኙነትንም ይሁን መሳሳምና መተሻሸትን የመሰሉ የግንኙነት መንደርደሪያዎችን እንዲሁም ፀያፍ የቃል አጠቃቀምንም የሚያጠቃልል ቃል ነው። ወንጀልና ኃጢዓት በመፈፀም - ሳያምፅ - ሐጅን ያከናወነ ያለውን ደረጃ ገለፁ። አመጽ ውስጥ ከሚካተቱት መካከል በኢሕራም ጊዜ የተከለከለን ማድረግ ይገኝበታል። በዚህ መልኩ ሐጅን ያከናወነ ሰው ልክ ህፃን ልጅ ከወንጀል የፀዳ ሆኖ እንደሚወለደው እርሱም ከወንጀሉ የተማረ ሆኖ ከሐጅ ይመለሳል።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ወንጀል ምንም እንኳ በማንኛውም ሁኔታ የተከለከለ ቢሆንም የሐጅን የአምልኮ ስርአት ለማላቅ ሲባል በሐጅ ወቅት ክልክልነቱ የበረታ እንደሚሆን፤
2. የሰው ልጅ ሲወለድ ከወንጀል የፀዳ ሆኖ የሚወለድ በመሆኑ የሌላ ወንጀል የሚጫንበት እንዳልሆነ፤

(2758)

(١٩٨) - عن ابن عباس رضي الله عنهما قال: قال رسول الله صلى الله عليه وسلم: «ما مِنْ أيَّامٍ العمَلُ الصَّالِحُ فيها أحبُّ إلى اللهِ مِن هذه الأيام» يعني أيامَ العشر، قالوا: يا رسُولَ الله، ولا الجهادُ في سبيلِ الله؟ قال: «ولا الجهادُ في سبيلِ الله، إلا رجلٌ خَرَجَ بنفسِه ومالِه فلم يَرْجِعْ من ذلك بشيءٍ». [صحيح] - [رواه البخاري وأبو داود، واللفظ له]

(198) - ከኢብኑ ዐባስ -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: "የአላህ መልክተኛ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንዲህ አሉ: 'ከነዚህ ቀናቶች የበለጠ መልካም ስራዎች ወደ አላህ ተወዳጅ የሚሆኑበት ምንም ቀን የለም።' ማለትም አስሩ የዙልሂጃ ቀናቶች ናቸው። ሰሐቦችም 'የአላህ መልክተኛ ሆይ! በአላህ መንገድ ጂሃድ ማድረግም ቢሆን?' በማለት ጠየቁ። እሳቸውም 'በአላህ መንገድ ጂሃድም ቢሆን እንኳ (አይበልጥም) ነፍሱና ገንዘቡን ይዞ የወጣና ከነዚህ መካከል አንዱም ያልተመለሰለት ሙጃሂድ ሲቀር' አሉ።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና፣አቡዳውድ ሲዘግቡት የዚህ ዘገባ ቃልም የአቡዳውድ ዘገባ ነው።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም በዙልሒጃ ወር የመጀመሪያ አስር ቀናቶች ውስጥ መልካም ስራዎችን መስራት በአመቱ ውስጥ ከሚገኙ ቀናቶች ሁሉ የበለጠ መሆኑን ገለፁ።

ሰሐቦችም አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና ነቢዩን ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ከነዚህ አስር ቀናት ውጪ ጂሃድ ማድረግ? ወይስ ከጂሃድ ውጪ ያሉ መልካም ስራዎችን በነዚህ ቀናት ውስጥ መስራት? የትኛው እንደሚበልጥ ጠየቁ። ይህም እነርሱ ዘንድ ጂሃድ ከሁሉም በላጭ ስራ መሆኑ የተረጋገጠ ጉዳይ ስለሆነ ነው።

ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለምም በነዚህ ቀናቶች መልካም ስራዎችን መስራት ከነዚህ ውጭ ባሉት ቀናት ከሚደረግ ጂሃድም ይሁን ሌሎች ስራዎች የበለጠ እንደሆነ ተናገሩ። ይህ ግን በአላህ መንገድ ገንዘቡንና ነፍሱን አጋልጦ ሙጃሂድ ሆኖ የወጣና በአላህ መንገድ ገንዘቡንም ያጣ ነፍሱንም የሰዋ ሲቀር ነው። በነዚህ ከፍ ባሉት ቀናቶች የሚሰሩ ስራዎችን የሚበልጠው ይህ ነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. የዙልሒጃ አስሩ ቀናት መልካም ስራዎች ትሩፋትን እንረዳለን። ሙስሊም የሆነ ሰው እነዚህ ቀናትን አላህን በማውሳት፣ ቁርአን በመቅራት፣ በተክቢር፣ በተሕሊል፣ በተሕሚድ፣ ሶላት በመስገድ፣ በሶደቃ፣ በፆምና በሁሉም በጎ ስራዎች ሊሸምትበትና አምልኮን ሊያበዛበት ይገባል።

(6255)

(١٩٩) - عَنْ أَبِي الحَوْرَاءِ السَّعْدِيِّ قَالَ: قُلْتُ لِلْحَسَنِ بْنِ عَلِيٍّ رضي الله عنهما: مَا حَفِظْتَ مِنْ رَسُولِ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ؟ قَالَ: حَفِظْتُ مِنْ رَسُولِ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ: «دَعْ مَا يَرِيبُكَ إِلَى مَا لاَ يَرِيبُكَ، فَإِنَّ الصِّدْقَ طُمَأْنِينَةٌ، وَإِنَّ الكَذِبَ رِيبَةٌ». [صحيح] - [رواه الترمذي والنسائي وأحمد]

(199) - ከአቡል ሐውራእ አስሰዕዲይ እንደተላለፈው እንዲህ አለ: ለሐሰን ቢን ዐሊይ (ረዲየሏሁ ዐንሁማ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - «ከአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ምን ሸምድደሃል? አልኩት። እርሱም: "ከአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ይህን ሸምድጃለሁ አለኝ። ‹የሚያጠራጥርህን ነገር ተውና ወደ ማያጠራጥርህ ሂድ! እውነት እርጋታን የተላበሰ ነው። ውሸት ደሞ ጥርጣሬን የተላበሰ ነው።›"» [ሶሒሕ ነው።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ክልክል ነው ወይስ አይደለም፣ ሐላል ነው ወይስ ሐራም ነው እያልክ የምትጠራጠርበት ንግግርና ተግባር በመተው መልካምነቱንና ፍቁድነቱን እርግጠኛ ወደሆንክበትና ወዳልተጠራጠርክበት መሄድን አዘዙ። ቀልብ እርግጠኛ በሆነበት ነገር ላይ ይረጋል። አጠራጣሪ በሆነ ነገር ደግሞ ይወዛገባል።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ሙስሊም የሆነ ሰው ጉዳዮቹን በርግጠኝነት ላይ መመስረት አለበት። የሚጠራጠርበትን ነገር ትቶ በሃይማኖቱም እውቀት ላይ መሆን አለበት።
2. አጠራጣሪ ነገር ላይ ከመውደቅ መከልከሉን እንረዳለን።
3. እርጋታና እረፍትን ከፈለግክ አጠራጣሪ ነገርን ትተህ ወደ ጎን መጣል አለብህ።
4. አላህ ለባሮቹ ነፍሳቸውና ሀሳባቸው እረፍት የሚያገኙበትን ማዘዙና ጭንቀትና መዋለል ውስጥ ከሚከታቸው ነገርም መከልከሉ ለነርሱ ያለውን እዝነት ያስረዳናል።

(4564)

(٢٠٠) - عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ رَضِيَ اللهُ عَنْهُ عَنِ النَّبِيِّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ قَالَ: «إِنَّ اللهَ تَجَاوَزَ عَنْ أُمَّتِي مَا حَدَّثَتْ بِهِ أَنْفُسَهَا، مَا لَمْ تَعْمَلْ أَوْ تَتَكَلَّمْ». [صحيح] - [متفق عليه]

(200) - ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና እንዲህ ብለዋል: "አላህ ከኡመቴ በውስጣቸው የሚናገሩትን ነገር እስካልሰሩት ወይም እስካልተናገሩት ድረስ ይቅር ብሏቸዋል።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና አላህ ወንጀልነቱን ስላነሳና ይቅር ስላለ አንድ ሙስሊም በውስጡ አስቦ ለተወው መጥፎ ነገር እስካልሰራበት ወይም እስካልተናገረው ድረስ እንደማይያዝበት ተናገሩ። የነቢዩ ሙሐመድ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ኡመት በአይምሯቸው በሚገኝ፣ ልባቸው ላይ ሳይረጋጋና ሳይፀናበት ውስጣቸው ላይ በመጣ መጥፎ ነገር አይያዙም። እንደኩራት፣ መንጠባረርና ንፍቅና ቀልቡ ላይ ከፀናበት፣ በአካሉ ከተገበረ ወይም በምላሱ ከተናገረ ግን ይያዝበታል።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. አላህ ተባረከ ወተዓላ በነፍስ ላይ የምትመጣንና ሰውዬው በውስጡ የሚናገራትንና ውል የምትልበትን አስተሳሰብና ሹክሹክታ ይቅር ብሏልም አልፏልም።
2. አንድ ሰው ሚስቱን መፍታት ቢያስብና በውስጡ ውል ቢልበትም ነገር ግን ካልተናገረና ካልፃፈው ፍቺ ተደርጎ አይቆጠርበትም።
3. በውስጥ የሚወራ ወሬ ምንም ያህል ቢገዝፍ በውስጡ እስካልፀና፣ በርሱ እስካልሰራ ወይም እስካልተናገረ ድረስ አይያዝበትም።
4. የሙሐመድ ኡመት (ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ከኛ በፊት ከነበሩት ህዝቦች በተቃራኒ ከራሳቸው ጋር በውስጥ በማውራታቸው ባለመያዝ የተለዩ መሆናቸው ደረጃቸው የላቀ መሆኑን ያስረዳናል።

(58144)

(٢٠١) - عن أبي هريرة رضي الله عنه قال: قال رسول الله صلى الله عليه وسلم: «إِنَّ اللهَ لَا يَنْظُرُ إِلَى صُوَرِكُمْ وَأَمْوَالِكُمْ، وَلَكِنْ يَنْظُرُ إِلَى قُلُوبِكُمْ وَأَعْمَالِكُمْ». [صحيح] - [رواه مسلم]

(201) - ከአቡ ሁረይራ -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ ብለዋል: የአላህ መልዕክተኛ ሰለላሁ ዐለይሂ ወስለም እንዲህ ብለዋል፡- "አላህ ወደ ቅርፃችሁና ገንዘቦቻችሁ አይመለከትም ነገር ግን ወደ ልቦቻችሁና ስራዎቻችሁ ይመለከታል።" [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም አላህ ወደ ሰዎች ቅርፅና ሰውነት ያምራል ወይስ አስቀያሚ? ትልቅ ወይስ ትንሽ? ጤነኛ ወይስ በሽተኛ? በማለት እንደማይመለከት ገለፁ። ወደ ገንዘቦቻቸውም ብዙ ወይስ ትንሽ? በማለት አይመለከትም። አላህ ባሮቹን በነዚህ ጉዳዮች ላይ ባላቸው መበላለጥ ተንተርሶ አይቀጣቸውምም አይተሳሰባቸውምም። ነገር ግን በቀልቦቻቸው ውስጥ

ወዳለው ፍራቻ፣ የእምነት እርግጠኝነት፣ እውነተኝነት፣ ኢኽላስ (ፍፁማዊነት) ወይም የይዩልኝ ፣ የይስሙልኝ አስተሳሰብ ነው የሚመለከተው። ወደ ስራዎቻቸው ከመስተካከሏና ከመበላሸቷ አንፃር ይመለከትና በዛም መሰረት ይመነዳል።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ቀልብን ከሁሉም ውግዝ ባህሪያት ማስተካከልና ማፅዳት ላይ ትኩረት መስጠት እንዳለብን፤
2. ቀልብ የሚስተካከለው በኢኽላስ ሲሆን ስራ የሚስተካከለው ደግሞ ነቢዩን ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም በመከተል ነው። አላህ ዘንድ ትኩረት የሚቸራቸውና ግምት ውስጥ የሚገቡት እነዚህ ሁለቱ ናቸው።
3. የሰው ልጅ በገንዘቡም፣ በውበቱም፣ በሰውነቱም ሆነ በዚህች ዓለማዊ መገለጫዎች በአንዳችም ነገር መሸወድ እንደሌለበት ፤
4. ውስጣዊ ማንነትን ሳያስተካክሉ ውጫዊ የሆኑ መገለጫዎችን ከመደገፍ መጠንቀቅ እንዳለብን ተረድተናል።

(4555)

(٢٠٢) - عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ رضي الله عنه قال: قال رَسُولُ الله صلى الله عليه وسلم: «إِنَّ اللهَ يَغَارُ، وَإِنَّ الْمُؤْمِنَ يَغَارُ، وَغَيْرَةُ اللهِ أَنْ يَأْتِيَ الْمُؤْمِنُ مَا حَرَّمَ عَلَيْهِ». [صحيح] - [متفق عليه]

(202) - ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: "የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል: ‹አላህ ይቀናል። የአላህ መቅናት ሰውዬው አላህ በሱ ላይ ክልክል ያደረገበትን ሲዳፈር ነው።›" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) አንድ አማኝ እንደሚቀናውና እንደሚጠላው ሁሉ አላህም እንደሚቀና እንደሚጠላ ተናገሩ።

የአላህ ቅናት ምክንያትም አንድ አማኝ እንደዝሙት፣ ሰዶማዊነት፣ ስርቆት፣ አስካሪ መጠጥ መጠጣትና ሌሎችንም አላህ በርሱ ላይ ክልክል የተደረጉ ፀያፍ ተግባራትን ሲዳፈር ነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. የአላህ ክልከላ የተደፈረ ጊዜ ቁጣውና ቅጣቱን መፍራት እንደሚገባ እንረዳለን።

(3354)

(٢٠٣) - عن أبي هريرة رضي الله عنه عن النبي صلى الله عليه وسلم قال: «اجْتَنِبُوا السَّبْعَ الْمُوبِقَاتِ»، قَالُوا: يَا رَسُولَ اللهِ وَمَا هُنَّ؟ قَالَ: «الشِّرْكُ بِاللهِ، وَالسِّحْرُ، وَقَتْلُ النَّفْسِ الَّتِي حَرَّمَ اللهُ إِلَّا بِالْحَقِّ، وَأَكْلُ الرِّبَا، وَأَكْلُ مَالِ الْيَتِيمِ، وَالتَّوَلِّي يَوْمَ الزَّحْفِ، وَقَذْفُ الْمُحْصَنَاتِ الْمُؤْمِنَاتِ الْغَافِلَاتِ». [صحيح] - [متفق عليه]

(203) - አቢ ሁረይራ ረዲየሏሁ ዐንሁ ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንዲህ ማለታቸውን አስተላልፈዋል፡ "ሰባት አጥፊዎችን ተጠንቀቁ!" ሶሓቦችም: "የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ምን ምን ናቸው?" ብለው ጠየቁ፤ ነቢዩም ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም "በአላህ ማጋራት፣ ድግምት፣ አላህ እርም ያደረጋትን ነፍስ በአግባቡ ካልሆነ በስተቀር መግደል፣ አራጣ መብላት፣ የየቲምን ገንዘብ መብላት፣ ጦርነት በተፋፋመ እለት ማፈግፈግ፣ ከዝሙት ዝንጉ የሆኑ ጥብቅ ምእመናትን በዝሙት መዝለፍ ናቸው።" አሉ። [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

የአላህ መልዕክተኛ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ኡመታቸውን ከሰባት አጥፊ ወንጀሎች እንዲርቁ አዘዙ። ምን ምን እንደሆኑ በተጠየቁ ጊዜም ተከታዮቹን ዘረዘሩ፡

የመጀመሪያው : በየትኛውም መልኩ ቢሆን ጥራት ለተገባው አላህ ቢጤን በማድረግ፤ ከአምልኮዎች መካከል ማንኛውም የአምልኮ ዘርፍን ከአሏህ ውጭ ላለ አካል በመስጠት አላህ ላይ ማጋራት መሆኑን ገለፁ፤ በሽርክ የጀመሩበት ምክንያትም ከወንጀሎች ሁሉ ትልቁ ወንጀል ስለሆነ ነው።

ሁለተኛ ድግምት፡ - እየቋጠሩ፣ እያነበነቡ፣ መድኃኒትና ጭሳጭስ እያደረጉ የሚሸርቡትን የሚጠቁም ገላጭ ቃል ሲሆን - ድግምቱ የተደረገበትን ሞት ወይም ህመም ላይ በመጣል፣ ወይም በባልና ሚስት መካከል መለያየትን በመፍጠር ተፅእኖ የሚያሳድር ነው። ድርጊቱ ሰይጣናዊ ስራም እንደመሆኑ አብዛኛውን ጊዜ በሽርክ እና መጥፎ መናፍስት የሚወዱትን ነገር እያደረጉ ወደነርሱ በመቃረብ የሚከናወን ነው።

ሶስተኛ አስተዳደሩ ተግባራዊ በሚያደርገው ሸሪዓዊ ምክንያት ካልሆነ በቀር አሏህ እርም ያደረጋትን ነፍስ መግደል፤

አራተኛ በመብላትም ይሁን በሌላ መልኩ በመጠቃቀም ወለድን መውሰድ፤

አምስተኛ ለአቅመ አዳም ሳይደርስ አባቱ በሞተበት ታዳጊ ገንዘብ ላይ ወሰን ማለፍ፤

ስድስተኛ ከከሀዲያን ጋር ከሚደረገ ፍልሚያ ማፈግፈግ፤

ሰባተኛ ጥብቅ የሆኑ ጨዋ እንስቶችን መዝለፍ፤ እንደዚሁም ጨዋ ወንዶችን መዝለፍ፤

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ከባባድ ወንጀሎች በነዚህ ብቻ የተገደበ ሆኖ አይደለም፤ እነዚህ ለብቻ ሊጠቀሱ የቻሉት ከከባድነታቸውና ከአደገኝነትቸው አኳያ ነው።
2. አንድ ሰው ነፍስን በመግደሉ ወይም ከእስልምና በኋላ በመካዱ ወይም ትዳር ቀመስ ከሆነ በኋላ ዝሙት በመፈፀሙ መግደል የተፈቀደ ሲሆን ይህም ተግባራዊ የሚደረገው በአስተዳደሩ ነው።

(3331)

(٢٠٤) - عن أبي بكرة رضي الله عنه قال: قال النبي صلى الله عليه وسلم: «أَلَا أُنَبِّئُكُمْ بِأَكْبَرِ الْكَبَائِرِ؟» ثَلَاثًا، قَالُوا: بَلَى يَا رَسُولَ اللهِ، قَالَ: «الْإِشْرَاكُ بِاللهِ، وَعُقُوقُ الْوَالِدَيْنِ» وَجَلَسَ وَكَانَ مُتَّكِئًا، فَقَالَ: «أَلَا وَقَوْلُ الزُّورِ»، قَالَ: فَمَا زَالَ يُكَرِّرُهَا حَتَّى قُلْنَا: لَيْتَهُ سَكَتَ. [صحيح] - [متفق عليه]

(204) - ከአቢ በክረህ (ረዲየላሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ሶስት ጊዜ እንዲህ አሉ፦ "'ከትልልቅ ወንጀሎች ትልቁን አልነግራችሁምን?' እኛም 'እንዴታ የአላህ መልዕክተኛ ሆይ!' አልናቸው። እሳቸውም፦ 'በአላህ ማጋራት ፣ የወላጆችን ሐቅ ማጓደል' አሉ። ደገፍ ብለው ከነበረበትም ተስተካክለው ተቀመጡና 'ንቁ! የውሸት ንግግርን (ተጠንቀቁ)።' አሉ። ምነው ዝም ባሉ እስክንል ድረስም ይህንን ከመደጋገም አልተወገዱም።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

**ትንታኔ:**

ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ለባልደረቦቻቸው እጅግ ትልቅ ስለሆነ ወንጀል ነገሯቸው። እነዚህን ሶስት ወንጀሎችንም ጠቀሱ፦

- 1በአላህ ማጋራት፦ ይህም ከአምልኮ አይነቶች መካከል ማንኛውንም አምልኮ ከአላህ ውጪ ለሆነ አካል መስጠት ፣ ከአላህ ውጪ የሆነን አካል ከአላህ ጋር በተመላኪነቱ ወይ በጌትነቱ ወይም በስምና ባህሪያቱ እኩል ማድረግ ማለት ነው።

- 2የወላጆችን ሐቅ ማጓደል፦ ይህም ወላጆች ላይ በንግግርም ይሁን በተግባር በማንኛውም መልኩ ማወክና ለነርሱ በጎ ማድረግን መተው ማለት ነው።

- 3ውሸት መናገር ነው። በውሸት መመስከርም እዚህ ውስጥ ይካተታል: ይህም ከተቀጠፈበት አካል ንብረቱን ለመውሰድ ወይም ክብሩ ላይ ወሰን

ለማለፍ ወይም የመሳሰሉትን በመፈለግ የተቀጠፈና የተዋሸ ንግግር ሁሉ ማለት ነው።

ከመደጋገማቸው የተነሳ ሶሐቦች ለነቢዩ ካላቸው እዝነትና የሳቸውን መረበሽ ጠልተው ምነው ዝም ባሉ ብለው እስኪመኙ ድረስ ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና የውሸትን ፀያፍነት እና ማህበረሰቡ ላይ የሚያሳድረውን መጥፎ አሻራ ለማስገንዘብ ከሐሰተኛ ቃል ደጋግመው አስጠነቀቁ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. እጅግ ትልቁ ወንጀል በአላህ ላይ ማጋራት ነው። ምክንያቱም ሐዲሡ ላይ ከትላልቅ ወንጀሎች ሁሉ ግንባር ቀደምና ትልቁ አድርገው ጠቀሰውታልና። ይህንንም {አላህ በእርሱ ማጋራትን በፍፁም አይምርም። ከዚህ ሌላ ያለውንም (ሀጢዐት) ለሚሻው ሰው ይምራል።} የሚለው የአላህ ንግግር ያጠናክረዋል።
2. ሐዲሡ ላይ የወላጆች ሐቅ ከአላህ ሐቅ ጋር በመቆራኘቱ የወላጆችን ሐቅ ታላቅነት እንረዳለን።
3. ወንጀሎች ወደ ትላልቅና ትናንሽ ይከፈላሉ። ትላልቅ የሚባሉት: ማንኛውም አለማዊ ቅጣት የተቀመጠለት ወንጀል ለምሳሌ :- ቅጣቱ በሸሪዓዊ መቅጫ ህግ ውስጥ ያለ (ሑዱድ)፣ መረጋገም ያለበት፤ ወይም እሳት መግባትን የመሰለ አኺራዊ ዛቻ የመጣበት ናቸው። ትላልቅ ወንጀሎች የተለያዩ ደረጃዎች አላቸው። የክልከላ ደረጃውም ከፊሉ ከከፊሉ ይከብዳል። ትናንሽ ወንጀሎች የሚባሉት ደግሞ ከትላልቅ ወንጀሎች ውጪ ያሉት ናቸው።

(٢٠٥) - عن عبد الله بن عمرو بن العاص رضي الله عنهما عن النبي صلى الله عليه وسلم قال: «الْكَبَائِرُ: الْإِشْرَاكُ بِاللهِ، وَعُقُوقُ الْوَالِدَيْنِ، وَقَتْلُ النَّفْسِ، وَالْيَمِينُ الْغَمُوسُ». [صحيح] - [رواه البخاري]

(205) - ከዐብደላህ ቢን ዐምር ቢን አልዐስ (ረዲየሏሁ ዓንሁማ) አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና እንደተላለፈው ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንዲህ ብለዋል፦ "ትላልቅ ወንጀሎች፦ በአላህ ማጋራት፣ የወላጆችን ሐቅ ማጓደል፣ ነፍስ ማጥፋትና የውሸት መሀላ ናቸው።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ስለትላልቅ ወንጀሎች አብራሩ። ትልቅ ወንጀል የሚባለውም ሰሪው በዱንያ ወይም በአኺራ ስለሚቀጣው ቅጣት ከባድ ዛቻ የተዛተበት ነው።

የመጀመሪያውም:- "በአላህ ማጋራት ነው።" ይህም ከአምልኮ አይነቶች መካከል ማንኛውንም አምልኮ ከአላህ ውጪ ለሆነ አካል መስጠት ፤ እንዲሁም ከአላህ ውጪ የሆነን አካል በተመላኪነቱ ፣ በጌትነቱ ወይም በስምና ባህሪያቱ አላህ በተለየበት ነገር ላይ ከአላህ ጋር እኩል ማድረግ ማለት ነው።

ሁለተኛው:- "የወላጆችን ሐቅ ማጓደል": ይህም ማንኛውም ወላጆችን ወደ ማወክ የሚዳርግ ንግግርም ይሁን ተግባር መፈፀምና ለነርሱ በጎ ማድረግን መተው ማለት ነው።

ሶስተኛው: "ነፍስን ያለ አግባብ ማጥፋት ነው።" ይህም በግፍ ወይም ወሰን በማለፍ መግደል ማለት ነው።

አራተኛው: "(የሚን አልገሙስ) አስማጭ መሀላ ነው።" ይህም እየዋሸ እንደሆነ እያወቀ በውሸት መማል ነው። በዚህም ስያሜ የተጠራቸው ሰውየውን ወንጀል ውስጥ ወይም እሳት ውስጥ ስለምታሰምጠው ነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. የውሸት መሀላ አደገኝነቱና ወንጀልነቱ ከባድ ከመሆኑ አንፃር ተውበት እንጂ ምንም ማካካሻ የለውም።
2. ሐዲሡ ውስጥ እነዚህ አራት ወንጀሎች ብቻ መጠቀሳቸው ወንጀልነታቸው ከባድ ስለሆነ እንጂ የቁጥር ገደብ አይደለም።
3. ወንጀሎች ወደ ትላልቅና ትናንሽ ይከፈላሉ። ትላልቅ የሚባሉት: ማንኛውም አለማዊ ቅጣት የተቀመጠለት ወንጀል ለምሳሌ :- ቅጣቱ በሸሪዓዊ መቅጫ ህግ ውስጥ ያለ (ሑዱድ)፣ መረጋገም ያለበት፤ ወይም እሳት መግባትን የመሰለ አኺራዊ ዛቻ የመጣበት ናቸው። ትላልቅ ወንጀሎች የተለያዩ ደረጃዎች አላቸው። የክልከላ ደረጃውም ከፊሉ ከከፊሉ ይከብዳል። ትናንሽ ወንጀሎች የሚባሉት ደግሞ ከትላልቅ ወንጀሎች ውጪ ያሉት ናቸው።

(3044)

(٢٠٦) - عَنْ عَبْدِ اللهِ بنِ مَسْعُودٍ رضي الله عنه قَالَ: قَالَ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ: «أَوَّلُ مَا يُقْضَى بَيْنَ النَّاسِ يَوْمَ الْقِيَامَةِ فِي الدِّمَاءِ». [صحيح] - [متفق عليه]

(206) - ከዐብደላህ ቢን መስዑድ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: "የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል: «የትንሳኤ ቀን በሰዎች መካከል መጀመሪያ የሚፈረደው ጉዳይ የደም ጉዳይ ነው።» [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) የትንሳኤ ቀን በሰዎች መካከል መጀመሪያ የሚፈረደው ጉዳይ ከፊሉ ከፊሉን የሚበድልበት በሆነው እንደመግደልና ማቁሰል ያሉ የደም ጉዳዮች መሆኑን አወሱ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. የደም ጉዳይ ከባድ መሆኑን እንረዳለን። ፍርድ የሚጀመረው በአንገብጋቢው ጉዳይ ነውና።
2. ወንጀሎች የሚተልቁት በርሱ ምክንያት የሚከሰቱ ብክለቶች እንደመተለቃቸው መጠን ነው። ንፁህ ነፍስን ማጥፋት ደሞ ከትላልቅ ብክለቶች መካከል አንዱ ነው። በአላህ ማጋራትና ኩፍር (ክህደት) እንጂ ምንም ከርሱ የሚከፋ ወንጀልም የለም።

(2962)

(٢٠٧) - عن عبد الله بن عمرو رضي الله عنهما عن النبي صلى الله عليه وسلم قال: «مَنْ قَتَلَ مُعَاهَدًا لَمْ يَرَحْ رَائِحَةَ الْجَنَّةِ، وَإِنَّ رِيحَهَا تُوجَدُ مِنْ مَسِيرَةِ أَرْبَعِينَ عَامًا». [صحيح] - [رواه البخاري]

(207) - ከዐብደሏህ ቢን ዓምር (ረዲየሏሁ ዓንሁማ) አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ማለታቸው ተላልፏል፡ "በቃል ኪዳን ስር ያለን (ሙዓሀድን) የገደለ ሰው የጀነትን ሽታ አያሸትም። የጀነት ሽታዋ የሚገኘው አርባ አመት ከሚያስኬድ ርቀት በኋላ ነው።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ሙዓሀድን በገደለ ሰው ላይ ያለበትን ከባድ ዛቻ ገለፁ። ሙዓሀድ ማለት ከከሀዲያን መካከል በቃል ኪዳንና በደህንነት ከለላ ወደ ኢስላም ሀገር የገባ ነው። እሱን የገደለ የጀነትን ሽታ አያሸትም። የጀነት ሽታ የሚገኘው አርባ አመት ከሚያስኬድ ርቀት ነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ከከሀዲያን መካከል "ሙዓሀድን" ፣ "ዚሚይን" እና "ሙስተእመንን" መግደል ክልክልና ከትላልቅ ወንጀል የሚመደብም ነው።

2. "ሙዓሀድ" ማለት: ከከሀዲያን መካከል በሀገሩ እየኖረ ሙስሊሞችን ላይዋጋ እነሱም ላይዋጉት ከሙስሊሞች ጋር ቃል ኪዳን የተጋባ ነው።
3. "ዚሚይ" ማለት: በሙስሊሞች ሀገር እንደሀገሩ እየኖረ ግብር የሚከፍል ነው።
4. "ሙስተእመን" ማለት ደግሞ ለተወሰነ ወቅት በቃል ኪዳንና ደህንነት ከለላ ወደ ሙስሊሞች ሀገር የገባ ሰው ነው።
5. ከሙስሊሞች ውጪ ካሉ ጋር ቃል ኪዳንን ማፍረስ መከልከሉን እንረዳለን።

(64637)

(٢٠٨) - عن جُبَير بن مُطْعِم رضي الله عنه أنه سمع النبي صلى الله عليه وسلم يقول: «لَا يَدْخُلُ الْجَنَّةَ قَاطِعُ رَحِمٍ». [صحيح] - [متفق عليه]

(208) - ከጁበይር ቢን ሙጥዒም -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው እሱ ነቢዩን ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንዲህ ሲሉ ሰማቸው: "ዝምድናን ቆራጭ ጀነት አይገባም።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ለቅርብ ዘመዶቹ ያለበትን ግዴታ ከመወጣት ይልቅ ዝምድናውን የቆረጠ ሰው ወይም ያወካቸውና ያስከፋቸው ጀነት ላለመግባት የተገባ ነው ብለው ተናገሩ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ዝምድናን መቁረጥ ከትላልቅ ወንጀሎች መካከል አንዱ ነው።
2. ዝምድናን መቀጠል በተለምዶ በሚታወቀው መልኩ ነው የሚሆነው። በታ፣ ዘመንና ሰዎቹ እንደመለያየታቸው ይለያያል።
3. ዝምድናን መቀጠል በመዘየር፣ ሶደቃ በመስጠት፣ ለነርሱ በጎ በመዋል፣ ሲታመሙ በመጠየቅ፣ በመልካም በማዘዝ፣ ከመጥፎ በመከልከልና በሌሎችም መልኩ ይፈፀማል።

4. ዝምድናው የሚቆረጠው ሰው እጅግ ቅርብ ዘመድ በሆነ ቁጥር ወንጀሉም እጅግ የከፋ ይሆናል።

(5367)

(٢٠٩) - عن أنس بن مالك رضي الله عنه أن رسول الله صلى الله عليه وسلم قال: «مَنْ أَحَبَّ أَنْ يُبْسَطَ لَهُ فِي رِزْقِهِ، وَيُنْسَأَ لَهُ فِي أَثَرِهِ، فَلْيَصِلْ رَحِمَهُ». [صحيح] - [متفق عليه]

(209) - ከአነስ ቢን ማሊክ -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው የአላህ መልክተኛ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንዲህ አሉ: "ሲሳዩ እንዲሰፋለትና እድሜው እንዲረዝምለት የወደደ ሰው ዝምድናውን ይቀጥል። " [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ቅርብ ዘመዶችን በመዘየር ፣ በአካላዊና ገንዘባዊ ጉዳይ በማገዝና በሌሎችም መልኩ ዝምድናን በመቀጠል ላይ አነሳሱ። በተጨማሪም ዝምድናን መቀጠል ለሲሳይ መስፋትና ለእድሜ መርዘም ምክንያት መሆኑንም ተናገሩ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ዝምድና በማለት የተፈለገው በአባትና በእናት በኩል ያሉ ቅርብ ሰዎች ናቸው። እጅግ ቅርብ ዘመድ በሆኑ ቁጥር በዛው ልክ መቀጠሉም የተገባ ይሆናል።
2. ምንዳ በስራው አምሳያ ነው የሚሰጠው። ዝምድናውን በበጎና መልካምነት የቀጠለ ሰውን አላህም እድሜውና ሲሳዩን ይቀጥልለታል።
3. ዝምድናን መቀጠል ለሲሳይ መስፋትና መዘርጋት እንዲሁም ለእድሜ መርዘም ምክንያት ነው። ምንም እንኳ የመሞቻ ቀኑና ሲሳዩ የተወሰነ ቢሆን ባለው ሲሳይና እድሜ በረከት ይሰፍንበታል። የተሰጠውን እድሜ ሌላው ከሚጠቀምበት በላይ ይጠቀምበታል። በርግጥ የሲሳይና እድሜ መጨመሩ እውነተኛ መጨመር ነውም ተብሏል። አላህ እጅግ አዋቂ ነው!

(5372)

(٢١٠) - عن عبد الله بن عمرو رضي الله عنهما عن النبي صلى الله عليه وسلم قال: «لَيْسَ الْوَاصِلُ بِالْمُكَافِئِ، وَلَكِنِ الْوَاصِلُ الَّذِي إِذَا قُطِعَتْ رَحِمُهُ وَصَلَهَا». [صحيح] - [رواه البخاري]

(210) - ከዐብደሏህ ቢን ዐምር ረዲየሏሁ ዐንሁማ እንደተላለፈው ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ ብለዋል፡ "ዝምድና ቀጣይ የሚባለው ላደረጉለት መልካም ነገር ምላሹን የሚሰጥ የሆነው አይደለም፤ ይልቁንም ዝምድና ቀጣይ የሚባለው ዝምድናው በተቆረጠ ጊዜ የሚቀጥል የሆነው ነው።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እየነገሩን ያሉት ዝምድናን በመቀጠል የተሟላና ለዘመዶቹም በጎ ሰሪ የሚባለው ላደረጉለት መልካም ነገር መልካሙን በመመለስ የተብቃቃው አይደለም፤ ይልቁንም ዝምድናውን በመቀጠል በኩል የተሟላ የሚባለው ዝምድናው በተቆረጠ ጊዜ የሚቀጥል፤ ሰዎቹ እየከፉበትም ለነርሱ መልካሙን በማድረግ ምላሽ የሚሰጣቸው የሆነ ነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ዝምድናን መቀጠል ሲባል በሸሪዓ የሚፈለግበት ካንተ᎒ጋ የተቆራረጡትን ስትቀጥል፤ የበደሉህን ይቅር ስትላቸው፤ የነፈጉህን ስትለግሳቸው እንጂ ብድር በመመለስ መልኩ ላደረጉልህ ነገር ተመሳሳዩን ምላሽ መስጠትህ አይደለም።
2. ዝምድናን መቀጠል የሚፈፀመው በገንዘብ፣ በዱዓእ፣ መልካሙን በማዘዝና ከመጥፎ በመከልከል ረገድ እና መሰል በሆኑ ነገራቶች ለነርሱ በጎ በማድረግ እንዲሁም ክፋትን ከነርሱ በተቻለ መጠን በማስወገድ ነው።

(3854)

(٢١١) - عن أبي هريرة رضي الله عنه أن رسول الله صلى الله عليه وسلم قال: «أَتَدْرُونَ مَا الْغِيبَةُ؟»، قَالُوا: اللهُ وَرَسُولُهُ أَعْلَمُ، قَالَ: «ذِكْرُكَ أَخَاكَ بِمَا يَكْرَهُ»، قِيلَ: أَفَرَأَيْتَ إِنْ كَانَ فِي أَخِي مَا أَقُولُ؟ قَالَ: «إِنْ كَانَ فِيهِ مَا تَقُولُ فَقَدِ اغْتَبْتَهُ، وَإِنْ لَمْ يَكُنْ فِيهِ فَقَدْ بَهَتَّهُ». [صحيح] - [رواه مسلم]

(211) - ከአቡ ሁረይራ -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው የአላህ መልክተኛ ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም እንዲህ አሉ፡ "ሀሜት ምን እንደሆነ ታውቃላችሁን?" ሶሐቦችም "አላህና መልክተኛው ያውቃሉ።" አሉ። እሳቸውም "ወንድምህን በሚጠላው ነገር ማውሳትህ ነው።" አሉ። "የምናገረው ነገር ወንድሜ ላይ ካለስ (ሀሜት ይባላልን?)" ተብለው ተጠየቁ። እሳቸውም "የምትናገረው ነገር እሱ ላይ ካለ በርግጥ አምተሀዋል። እሱ ላይ ከሌለ ደግሞ በርግጥም ቀጥፈህበታል።" [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም የተከለከለውን ሀሜት እውነታ : ሙስሊምን በሌለበት በሚጠላው ነገር ማውሳት መሆኑን አብራሩ። ይህም ተፈጥሯዊውም ሆነ ስነ ምግባሪያዊ ባህሪውን ቢያወሳ ተመሳሳይ ነው። እውሩ ፣ አጭበርባሪ ፣ ውሸታምና የመሳሰሉትን እሱ ላይ የሚገኙ የተወገዙ መገለጫዎችን በማውሳት ማማትን የመሳሰለው ነው።

እሱ ላይ የሌሉ ባህሪያት ከሆኑ ግን የተወሱት ከሀሜትም የባሰ ነው። እሱም መቅጠፍ (ቡህታን) ነው የሚሆነው :- ማለትም በሰው ላይ የሌሉበትን ባህሪያት መቅጠፍ ነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እውቀትን ጥያቄያዊ በሆነ መንገድ ማስተላለፋቸውን ስናይ የሳቸው የማስተማር ስልት ውብ መሆኑን እንረዳለን ፤
2. ሶሐቦች "አላህና መልክተኛው ያውቃሉ።" ማለታቸውን ስናይ ከነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ጋር ያላቸው አደብ ውብ መሆኑን እንረዳለን ፤

3. ተጠያቂ ስለማያውቀው ነገር "አላህ ያውቃል።" ማለት እንዳለበት እንረዳለን ፤
4. ሸሪዐ ሐቆችን በመጠበቅና በማህበረሰቡ መካከል ወንድማማችነትን በመፍጠር ማህበረሰቡን መጠበቁን እንረዳለን ፤
5. ሀሜት እንደአስፈላጊነቱ በአንዳንድ ሁኔታዎች ላይ ካልሆነ በስተቀር ክልክል ነው። ከነዚህም ውስጥ: - በደልን ለመከላከል : ይህም "እከሌ በድሎኛል ወይም በኔ ላይ እንዲህ ፈፅሟል።" በማለት ተበዳይ ሀቁን ማስመለስ የሚችል ሰው ዘንድ የበደለውን በማውሳት ነው። በትዳር ጉዳይ ወይም በሽርክና ወይም በጉርብትናና በመሳሰሉት ጉዳይ ለማማከር ሰውዬውን ማማት ከሚፈቀዱት መካከል የሚመደብ ነው።

(5326)

(٢١٢) - عن ابن عمر رضي الله عنهما قال: قال رسول الله صلى الله عليه وسلم: «كل مُسْكِرٍ خَمْرٌ، وكل مُسْكِرٍ حرام، ومن شرِب الخمر في الدنيا فمات وهو يُدْمِنُهَا لَمْ يَتُبْ، لَمْ يَشْرَبْهَا في الآخرة».
[صحيح] - [رواه مسلم وأخرج البخاري الجملة الأخيرة منه]

(212) - ከኢብኑ ዑመር (ረዲየላሁ ዐንሁ) -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: «የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል: "አስካሪ ሁሉ ኸምር ነው። አስካሪ ሁሉ ክልክል ነው። በዚህ ዓለም አስካሪ መጠጥ አዘውትሮ ጠጥቶ ንስሀ ሳይገባ የሞተ ሰው በመጪው ዓለም አይጠጣም።"» [ሶሒሕ ነው።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) አይምሮን የሚያደነዝዝና የሚያስወግድ የሚጠጣም ይሁን የሚበላም ይሁን የሚሸተት ወይም ከዚህ ውጪ ያለ ነገር ሁሉ ኸምርና አስካሪ መሆኑን ገለፁ። ሁሉም አስካሪና አይምሮን የሚያስወግድ ነገርም አነሰም በዛም አላህ ከልክሎታል። ከነዚህ የአስካሪ አይነቶች መካከል ማንኛውንም አይነት የወሰደና በመውሰድ

ላይም የዘወተረ እስኪሞት ድረስም ንስሀ ያልገባ ሰውም ጀነት ውስጥ መጠጣትን በመነፈግ የአላህ ቅጣት ይገባዋል።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. የኸምር ክልክልነት ምክንያቱ ማስከሩ ነው። ስለዚህ ማንኛውም አይነት አስካሪ ክልክል ነው።
2. አላህ አስካሪ መጠጥን የከለከለው ትላልቅ ጉዳትና ብልሽቶችን ስለያዘ ነው።
3. ኸምርን ጀነት ውስጥ ሲሆን መጠጣቱ የድሎትና የእርካታ ማሟያ ነው።
4. በዚህ አለም አስካሪ መጠጥ ከመጠጣት ነፍሱን ያላቀበ አላህ ጀነት ውስጥ ከመጠጣት ይከለክለዋል። ምንዳ የሚሆነው በሰራው ስራ አይነት ነውና።
5. ከሞት በፊት ከወንጀሎች ንስሀ በማድረግ ላይ መቻኮል እንደሚገባ መነሳሳቱን እንረዳለን።

(58259)

(٢١٣) - عن أبي هريرة رضي الله عنه قال: لَعَنَ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ الرَّاشِيَ وَالْمُرْتَشِيَ فِي الْحُكْمِ. [صحيح] - [رواه الترمذي وأحمد]

(213) - ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: "የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) በፍርድ አሰጣጥ ዙሪያ ጉቦ ሰጪንም ተቀባይንም ረገሙ።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቲርሚዚና አሕመድ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ጉቦ በሚሰጥ፣ በሚቀበልና በሚበላ ሰው ላይ ከአላህ እዝነት እንዲርቅና እንዲባረር ዱዓ አደረጉበት።

ከዚህም መካከል ጉቦ ሰጪው ያለአግባብ ወደፍላጎቱ ለመዳረስ ሲል ለዳኞች በተሸሙበት ፍርድ እንዲያዘነብሉ (ኢፍትሃዊ እንዲሆኑ) የሚሰጠው ጉቦ እዚህ ውስጥ ይመደባል።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ጉቦ መስጠት፣ መቀበል፣ አገናኝ መሆንና ተባባሪ መሆን በተሳሳተ ነገር ላይ መተባበር ስለሆነ ክልክል ነው።
2. የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ጉቦ ተቀባይንም ሆነ ሰጪን ስለረገሙ ጉቦ ከትላልቅ ወንጀሎች የሚመደብ ነው።
3. ጉቦ በዳኝነትና ፍርድ ላይ ከሆነ የተከናወነው በውስጡ አላህ ካወረደው ፍርድ ውጪ በግፍ መፍረድም ስላለው ከባድ ወንጀልና አደገኛ ኃጢአት ይሆናል።

(64689)

(٢١٤) - عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ رضي الله عنه عَنِ النَّبِيِّ صلى الله عليه وسلم قَالَ: «إِيَّاكُمْ وَالظَّنَّ؛ فَإِنَّ الظَّنَّ أَكْذَبُ الْحَدِيثِ، وَلَا تَحَسَّسُوا، وَلَا تَجَسَّسُوا، وَلَا تَحَاسَدُوا، وَلَا تَدَابَرُوا، وَلَا تَبَاغَضُوا، وَكُونُوا عِبَادَ اللهِ إِخْوَانًا». [صحيح] - [متفق عليه]

(214) - አቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ማለታቸውን አስተላልፈዋል: "አደራችሁን ጥርጣሬን ተጠንቀቁ! ጥርጣሬ እጅግ ውሸት የሆነ ወሬ ነውና። አትፈላፈሉ፣ አትሰልሉ፣ አትመቀኛኙ፣ ጀርባም አትሰጣጡ፣ አትጠላሉ (ይልቁንም) ወንድማማች የአላህ ባሮች ሁኑ።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

**ትንታኔ:**

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) በሙስሊሞች መካከል ወደ ክፍፍልና ጠላትነት ከሚያደርሱ አንዳንድ ነገሮች ከለከሉን፤ አስጠነቀቁንም። ከነዚህም መካከል:

(ጥርጣሬ) ያለማስረጃ በቀልብ ውስጥ የሚወድቅ መጥፎ እሳቤ ነው። ከወሬዎች ሁሉ እጅግ ውሸት መሆኑን ገለፁ።

(መፈላፈል): ይህም በአይን ወይም በጆሮ የሰዎችን ነውር መፈለግ ነው።

(መሰለል): ይህም ማለት ድብቅ የሆኑ ነገሮችን መፈለግ ነው። በብዛት ይህ ቃል የሚውለው የሰዎችን መጥፎ ነገር መፈለግን ለማመልከት ነው።

(ምቀኝነት): ይህም ማለት ሌሎች ፀጋ ማግኘታቸውን መጥላት ማለት ነው።

(ጀርባ መሰጣጠት) : ለሙስሊም ወንድሙ ሰላምታን ላይሰጥና ላይዘይር ከፊሉ ከከፊሉ መዞሩ ነው።

(መጠላላት) : ሌሎችን በማስቸገር፣ ፊትን በማጨፍገግና በመጥፎ መስተጋብር በመሳሰሉት ሰዎችን መጥላትና ማሸሽ ነው።

ቀጥለውም ሙስሊሞች የእርስ በርስ ሁኔታቸው የሚስተካከሉበትን ጠቅላይ ንግግር እንዲህ በማለት ተናገሩ "ወንድማማች የአሏህ ባሮች ሁኑ።" ወንድማማችነት በሰዎች መካከል ያለውን ግንኙነት የሚሰበስብ፣ በመካከላቸው መዋደድንና ቅርርብን የሚጨምር ማሰሪያ ገመድ ነው።

**ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:**

1. በመጥፎ የሚያስጠረጥር ምልክት ግልፅ የሆነበትን ሰው መጠራጠር ምንም አይጎዳም። አማኝ የሆነ ሰውም በመጥፎዎችና አመፀኞች እንዳይሸወድ ብልጥና ጮሌ መሆን ይገባዋል።
2. በሐዲሱ የተፈለገው ነፍስ ውስጥ ፀንቶ በሚቆይ መልኩ (በጥርጣሬ) መወንጀል እና በጥርጣሬም ላይ ከመዘውተር ማስጠንቀቅ ነው። ነፍስ ላይ ባልፀና መልኩ መጠርጠር ከሆነ ግን ይህ ተጠያቂ አያደርግም።

3. በሙስሊሙ ማህበረሰብ ውስጥ በሚገኙ ግለሰቦች መካከል ለመናቆርና ለመቆራረጥ ምክንያት የሚሆኑ እንደ መሰለል፣ መመቅኘትና የመሳሰሉት ነገሮች መከልከላቸውን እንረዳለን።
4. በተቆርቋሪነትና በመዋደድ ረገድ ከሙስሊም ጋር ሊኖረን የሚገባው መስተጋብር ወንድማዊ መስተጋብር መሆን እንዳለበት መታዘዛችንን እንረዳለን።

(5332)

(٢١٥) - عن حذيفة رضي الله عنه قال: سمعت النبي صلى الله عليه وسلم يقول: «لَا يَدْخُلُ الْجَنَّةَ قَتَّاتٌ». [صحيح] - [متفق عليه]

(215) - ከሑዘይፋ -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: ነቢዩን ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንዲህ ሲሉ ሰምቻለሁ: "ነገር አዋሳጅ ጀነት አይገባም።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም በሰዎች መካከል መቃቃርን ለመፍጠር በማሰብ ወሬን የሚያዋስድ ለቅጣትና ጀነት ላለመግባት የተገባ መሆኑን ተናገሩ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ወሬ ማዋሰድ ከትላልቅ ወንጀሎች መሆኑን ፤
2. ወሬ ማዋሰድ በግለሰቦችም ሆነ በማህበረሰብ ደረጃ ጉዳትና ብልሽትን ስለሚያስከትል ወሬ ማዋሰድ መከልከሉን እንረዳለን።

(5368)

(٢١٦) - عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ رضي الله عنه قَالَ: سَمِعْتُ رَسُولَ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ يَقُولُ: «كُلُّ أُمَّتِي مُعَافًى إِلَّا المُجَاهِرِينَ، وَإِنَّ مِنَ المُجَاهَرَةِ أَنْ يَعْمَلَ الرَّجُلُ بِاللَّيْلِ عَمَلًا، ثُمَّ يُصْبِحَ وَقَدْ سَتَرَهُ اللَّهُ عَلَيْهِ، فَيَقُولَ: يَا فُلَانُ، عَمِلْتُ البَارِحَةَ كَذَا وَكَذَا، وَقَدْ بَاتَ يَسْتُرُهُ رَبُّهُ، وَيُصْبِحُ يَكْشِفُ سِتْرَ اللَّهِ عَنْهُ». [صحيح] - [متفق عليه]

(216) - ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: እንዲህ አለ: "የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ሲሉ ሰምቻለሁ፦ 'ወንጀላቸውን ይፋ ከሚያደርጉ በስተቀር ሁሉም ህዝቦቼ ይማርላቸዋል። ይፋ ከማውጣትም መካከል ሰውዬው ምሽት ላይ አንድ ወንጀልን ይሰራል ከዚያም አላህ በርሱ ላይ (ወንጀሉን) ሸሽጎለት አንግቶ ሳለ ‹እከሌ ሆይ! ትናንት ምሽት እንዲህ እንዲህ ሰራሁ።› ይላል። ጌታው (ወንጀሉን) ሸሽጎለት አድሮ ሳለ የአላህን ግርዶሽ ከራሱ ላይ የሚገፍ ሆኖ ያነጋል።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ሙስሊም ወንጀለኛ ወንጀሉን በፉከራና በብልግና ይፋ የሚያወጣ ካልሆነ በቀር የአላህን ይቅርታና ምህረት የማግኘት ተስፋ እንዳለው ገለፁ። ወንጀሉን ይፋ የሚያደርግ ግን ይቅርታ አይገባውም። ምሽት ላይ ወንጀል ይሰራል ከዚያም አላህ ሸሽጎለት አንግቶ ሳለ ለሌላ ሰው ትናንት የሆነች ወንጀልን እንደሰራ ይናገራል። ጌታው ሸሽጎለት አድሮ ሳለ የአላህን ግርዶሽ የገለጠ ሆኖ ያነጋል።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. አላህ በርሱ ላይ ከሸሸገለት በኋላ ወንጀልን ይፋ ማውጣት ፀያፍ መሆኑን እንረዳለን።
2. ወንጀልን ይፋ ማድረግ በአማኞች መካከል ብክለት እንዲሰራጭ ያደርጋል።

3. አላህ በዱንያ የሸሸገው ሰው በመጨረሻው አለምም ይሸሽገዋል። ይህም አላህ በባሮቹ ላይ ካለው እዝነት ስፋት ነው።
4. በወንጀል የተፈተነ ሰው ወንጀሉን በራሱ ሸሽጎ ወደ አላህ መመለስ ይገባዋል።
5. ወንጀላቸውን ይፋ የሚያደርጉ ሰዎች ወንጀል ትልቅ መሆኑን እንረዳለን። እነሱም ወንጀላቸውን ይፋ ማድረግን በማሰብ ለነፍሳቸው ይቅርታን ያስመለጡ ናቸው።

(3756)

(٢١٧) - عَنِ ابْنِ عُمَرَ رضي الله عنهما: أَنَّ رَسُولَ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ خَطَبَ النَّاسَ يَوْمَ فَتْحِ مَكَّةَ، فَقَالَ: «يَا أَيُّهَا النَّاسُ، إِنَّ اللهَ قَدْ أَذْهَبَ عَنْكُمْ عُبِّيَّةَ الْجَاهِلِيَّةِ وَتَعَاظُمَهَا بِآبَائِهَا، فَالنَّاسُ رَجُلَانِ: بَرٌّ تَقِيٌّ كَرِيمٌ عَلَى اللهِ، وَفَاجِرٌ شَقِيٌّ هَيِّنٌ عَلَى اللهِ، وَالنَّاسُ بَنُو آدَمَ، وَخَلَقَ اللهُ آدَمَ مِنْ تُرَابٍ، قَالَ اللهُ: {يَا أَيُّهَا النَّاسُ إِنَّا خَلَقْنَاكُمْ مِنْ ذَكَرٍ وَأُنْثَى وَجَعَلْنَاكُمْ شُعُوبًا وَقَبَائِلَ لِتَعَارَفُوا إِنَّ أَكْرَمَكُمْ عِنْدَ اللهِ أَتْقَاكُمْ إِنَّ اللهَ عَلِيمٌ خَبِيرٌ} [الحجرات: 13]».

[صحيح] - [رواه الترمذي وابن حبان]

(217) - ከኢብኑ ዑመር (ረዲየሏሁ ዐንሁማ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: "የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) መካ የተከፈተ እለት ለሰዎች ኹጥባ አደረጉ። እንዲህም አሉ ' እናንተ ሰዎች ሆይ! አላህ ከናንተ ላይ የድንቁርና ዘመንን ኩራትና በአባቶች መኮፈስን አስወግዷል። ሰዎች ሁለት አይነት ናቸው። በጎ፣ አላህን ፈሪና አላህ ዘንድ የተከበረ፤ አመፀኛ፣ ጠማማና አላህ ዘንድ የወረደ ናቸው። ሰዎች የአደም ልጆች ናቸው። አላህም አደምን ከአፈር ነው የፈጠረው። አላህ እንዲህ ብሏል፦ {እናንተ ሰዎች ሆይ! እኛ ከወንድና ከሴት ፈጠርናችሁ። እንድትተዋወቁም ጎሳዎችና ነገዶች አደረግናችሁ። አላህ ዘንድ በላጫችሁ በጣም አላህን ፈሪያችሁ ነው። አላህ ግልፅን አዋቂ ውስጥንም አዋቂ ነው።} [ሑጁራት: 13]'" [ሶሒሕ ነው።] - [ቲርሚዚና ኢብኑ ሒባን ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) መካ የተከፈተ እለት ለሰዎች ኹጥባ አደረጉ። እንዲህም አሉ፦ እናንተ ሰዎች ሆይ! አላህ ከናንተ ላይ የድንቁርናን ዘመን ኩራት፣ ትዕቢትንና በአባቶች መኮፈስን አስወግዷል። ሰዎች ሁለት አይነት ብቻ ናቸው።

ወይ አማኝ፣ በጎ፣ አላህን ፈሪና ለአላህ ባሪያ የሆነ ነው። ይህ ግለሰብ ሰዎች ዘንድ የተከበረ ዘርና ጎሳ ባለቤት ባይሆን እንኳ አላህ ዘንድ የተከበረ ነው።

ወይም ደግሞ ከሀዲ፣ አመፀኛና ጠማማ ነው። ይህም ስልጣንና ክብር ያለው ከተከበረ ዘር እንኳ ቢሆን አላህ ዘንድ ከምንም ነገር ጋር የማይስተካከል የተዋረደና የዘቀጠ ነው።

ሰዎች ሁሉ የኣደም ልጆች ናቸው። አላህም ኣደምን ከአፈር ነው የፈጠራቸው። መሰረቱ ከአፈር የሆነ ደግሞ በራሱ ሊኮራና ሊደነቅ አይገባውም። የዚህም ማረጋገጫ እንዲህ የሚለው የአላህ ንግግር ነው፦ {እናንተ ሰዎች ሆይ! እኛ ከወንድና ከሴት ፈጠርናችሁ። እንድትተዋወቁም ጎሳዎችና ነገዶች አደረግናችሁ። አላህ ዘንድ በላጫችሁ በጣም አላህን ፈሪያችሁ ነው። አላህ ግልፅን አዋቂ ውስጥንም አዋቂ ነው።} [ሑጁራት: 13

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. በዘርና በጎሳ መኩራራት መከልከሉን እንረዳለን።

(65074)

(٢١٨) - عن عائشة رضي الله عنها عن النبي صلى الله عليه وسلم قال: «إِنَّ أَبْغَضَ الرِّجَالِ إِلَى اللهِ الْأَلَدُّ الْخَصِمُ». [صحيح] - [متفق عليه]

(218) - ከእናታችን ዓኢሻህ -አላህ መልካም ስራዋን ይውደድላትና- እንደተላለፈው ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንዲህ ብለዋል: "ከሰዎች ሁሉ አላህ ዘንድ እጅግ የተጠላው ደረቅ ተከራካሪ የሆነ ሰው ነው።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

የጠራውና ከፍ ያለው አላህ ከሰዎች ውስጥ ለእውነት እጅ መስጠትን የማይቀበል፣ እውነታውን በክርክሩ ለመመለስ የሚሞክር ወይም እውነትን ይዞ ቢከራከርም ነገር ግን ከሚዛናዊነት በሚያስወጣው መልኩ ክርክርን የሚያበዛና ያለ እውቀት የሚከራከርን ደረቅ ተከራካሪንና ክርክር የሚያበዛን እንደሚጠላ ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ተናገሩ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ተበዳይ ሀቁን ሸሪዓዊ በሆነ መልኩ መክሰሱ የተወገዘ የሆነው የክርክር ይዘት ውስጥ አይገባም።
2. ክርክርና ንትርክ በሙስሊሞች መካከል ልዩነትንና ጀርባ መሰጣጠትን የሚየስከትሉ የምላስ ወለምታዎች ናቸው።
3. እውነትን ይዘና በጥሩ ዘይቤ ከሆነ ክርክር የተወደሰ ይሆናል። ውሸትን ለማፅናትና እውነትን ለመመለስ ከሆነ ወይም ያለማስረጃ ከሆነ ደግሞ የተወገዘ ክርክር ይሆናል።

(5474)

(٢١٩) - عن أبي بَكرة رضي الله عنه قال: سمعت رسول الله صلى الله عليه وسلم يقول: «إِذَا الْتَقَى الْمُسْلِمَانِ بِسَيْفَيْهِمَا فَالْقَاتِلُ وَالْمَقْتُولُ فِي النَّارِ»، فَقُلْتُ: يَا رَسُولَ اللهِ هَذَا الْقَاتِلُ، فَمَا بَالُ الْمَقْتُولِ؟ قَالَ: «إِنَّهُ كَانَ حَرِيصًا عَلَى قَتْلِ صَاحِبِهِ». [صحيح] - [متفق عليه]

(219) - ከአቢ በክረህ -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸው- እንደተላለፈው እንዲህ ብለዋል፦ የአላህን መልክተኛ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ ሲሉ ሰምቻዋለሁ፦ "ሁለት ሙስሊሞች በሰይፋቸው (ሊጋደሉ) የተገናኙ ጊዜ ገዳዩም ሆነ ተገዳዩ እሳት ውስጥ ናቸው። " እኔም "የአላህ መልክተኛ ሆይ! ይህ ገዳይ ሆኖ (እሳት መግባቱ መልካም) ተገዳዩ (እሳት የሚገባው) በምን ጥፋቱ ነው?" አልኩ። እርሳቸውም "እሱ ባልደረባውን ለመግደል ጉጉ ስለነበር ነው።" አሉ። [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ሁለት ሙስሊሞች እርስ በርሳቸው እያንዳንዳቸው የባልደረባውን ህይወት ማጥፋትን ቋምጠው በሰይፋቸው ሊጋደሉ የተገናኙ እንደሆነ ሁለቱም እሳት እንደሚገቡ ተናገሩ። ገዳዩ ባለደረባውን በመግደሉ ምክንያት እሳት ውስጥ ይገባል። ሰሐቦች የተገዳዩ እሳት መግባት ግራ አጋባቸው: እንዴት የእሳት ይሆናል? ብለው ጠየቁ። ነቢዩም የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ባልደረባውን ለመግደል በመጓጓቱ ፤ በገዳዩ ከመቀደም በስተቀር ከመግደል ምንም የከለከለው ነገር ስለሌለ እሱም ጭምር የእሳት መሆኑን ተናገሩ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ወንጀል ለመስራት በልቡ የቆረጠና መዳረሻዎቹን የፈፀመ ሰው ለቅጣት የተገባ መሆኑን፤
2. ሙስሊሞች እርስ በርስ በመጋደላቸው ዙሪያ ብርቱ ማስጠንቀቂያና የእሳት ዛቻም መምጣቱን፤

3. በሙስሊሞች መካከል የተፈጠረው መጋደል በእውነት ጉዳይ ከሆነ ዛቻ ውስጥ አይካተትም። ለምሳሌ ከመሪ ትእዛዝ የወጡ ወሰን አላፊዎችና ሀገር የሚያበላሹን መዋጋትን ይመስል።
4. ከባድ ወንጀል የሰራ ሰው በመስራቱ ብቻ ከሀዲ አይሆንም። ምክንያቱም ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ሁለቱን እርስ በርስ የሚጋደሉትን ሙስሊሞች ብለው ጠርተዋቸዋልና።
5. ሁለት ሙስሊሞች በማንኛውም ለመግደል የሚያደርስ በሆነ መሳሪያ ሊጋደሉ ተገናኝተው አንዱ አንዱን ቢገድል ገዳዩም ተገዳዩም እሳት ውስጥ ናቸው። ሐዲሡ ውስጥ ሰይፍ መጠቀሱ ለምሳሌ ያክል ብቻ ነው።

(4304)

(٢٢٠) - عن أبي موسى الأشعري رضي الله عنه عن النبي صلى الله عليه وسلم قال: «مَنْ حَمَلَ عَلَيْنَا السِّلَاحَ فَلَيْسَ مِنَّا». [صحيح] - [متفق عليه]

(220) - ከአቡ ሙሳ አልአሽዐሪይ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል: "መሳሪያውን በኛ ላይ ያነሳ ከኛ አይደለም።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

**ትንታኔ:**

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ለማስፈራራት ወይም ንብረታቸውን ለመቀማት በሙስሊሞች ላይ መሳሪያ ከማንሳት አስጠነቀቁ። ያለ አግባብ ይህንን የፈፀመም ትልቅ ሀጢአትንና ወንጀልን መፈፀሙን ለዚህ ከባድ ዛቻም መጋረጡን አሳሰቡ።

**ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:**

1. ሙስሊም ከሙስሊም ወንድሙ ጋር መጋደሉ ብርቱ ማስጠንቀቂያ የመጣበት ጉዳይ መሆኑን እንረዳለን።

2. በምድር ላይ ከሚሰሩ ትላልቅ ወንጀሎችና ብክለቶች መካከል መሳሪያን በሙስሊሞች ላይ ማንሳትና በመግደል ማበላሸት ነው።
3. የተጠቀሰው ዛቻ ወሰን አላፊዎችን፣ አጥፊዎችንና ሌሎችም የመሳሰሉትን በሀቅ (በሸሪዓ በተፈቀደ ምክንያት) መጋደልን አያካትትም።
4. ለቀልድ እንኳ ቢሆን ሙስሊሞችን በመሳሪያ ወይም በሌላ ነገር ማስፈራራት መከልከሉን እንረዳለን።

(2997)

(٢٢١) - عن عائشة رضي الله عنها قالت: قال النبي صلى الله عليه وسلم: «لَا تَسُبُّوا الْأَمْوَاتَ، فَإِنَّهُمْ قَدْ أَفْضَوْا إِلَى مَا قَدَّمُوا». [صحيح] - [رواه البخاري]

(221) - ከእናታችን ዓኢሻህ -አላህ መልካም ስራዋን ይውደድላትና- እንደተላለፈው እንዲህ አለች: ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንዲህ አሉ: "ሟቾችን አትሳደቡ! እነርሱ ወዳስቀደሙት (ስራቸው) ሂደዋልና።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ሟቾችን መሳደብና ክብራቸውን መንካት ክልክል መሆኑን አብራሩ። ከእኩይ ስነ ምግባሮችም የሚመደብ እንደሆነ ገለፁ። ምክንያቱም ይህ ስድብ በህይወት ያሉ ሰዎችን ከመጉዳት የዘለለ ለነርሱ የማይደርሳቸው ከመሆኑም በተጨማሪ እነሱ ወዳስቀደሙት መልካምም ይሁን መጥፎ ስራቸው ደርሰዋልና።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ሐዲሡ ሟቾችን መሳደብ ክልክል መሆኑን ይጠቁማል።
2. ሟቾችን ከመሳደብ መታቀብ የህያው ሰዎችን ጥቅምም የማህበረሰቡንም ሰላም ከመጣላትና ከመናቆር ይጠብቃል።

3. ሟቾችን ከመሳደብ የመከልከሉ ጥበብ ወዳስቀደሙት ስራ ስለደረሱ መስደቡ ከንቱ ስለሆነና በተጨማሪ የህያው ቅርብ ዘመዶቹን ስለሚያውክ ነው።
4. የሰው ልጅ ጥቅም የሌለውን ነገር መናገር አይገባውም።

(5364)

(٢٢٢) - عن أبي أيوب الأنصاري رضي الله عنه أن رسول الله صلى الله عليه وسلم قال: «لَا يَحِلُّ لِرَجُلٍ أَنْ يَهْجُرَ أَخَاهُ فَوْقَ ثَلَاثِ لَيَالٍ، يَلْتَقِيَانِ، فَيُعْرِضُ هَذَا وَيُعْرِضُ هَذَا، وَخَيْرُهُمَا الَّذِي يَبْدَأُ بِالسَّلَامِ». [صحيح] - [متفق عليه]

(222) - ከአቡ አዩብ አልአንሷሪይ -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው የአላህ መልክተኛ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንዲህ ብለዋል: "ሲገናኙ ይህም እየዞረ ያኛውም እየዞረ ወንድሙን ከሶስት ሌሊቶች በላይ ሊያኮርፈው አይፈቀድለትም። ከሁለቱ ምርጡ በሰላምታ የሚጀምረው ነው። " [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም አንድ ሙስሊም ሙስሊም ወንድሙን አንዱ ሌላኛውን በሚያገኘው ጊዜ ሰላምታም ሳይሰጠውና ሳያናግረው ከሶስት ሌሊቶች በላይ ማኩረፍን ከለከሉ።

ከነዚህ ሁለት ጠበኞች መካከል በላጩ ኩርፊያውን ለማስወገድ የሚሞክርና ሰላምታ የሚጀምረው ነው። እዚህ ሐዲስ ውስጥ ኩርፊያ በማለት የተፈለገው በነፍሱ ፍላጎቶች ያኮረፈ እንደሁ ነው። ወንጀለኞችን፣ የቢድዓ ባለቤቶችንና መጥፎ ጓደኞችን የመሰሉ ሰዎችን ለአላህ ሀቅ ብሎ ማኩረፍ ከሆነ ግን በወቅት ሳይሆን የሚገደበው ኩርፊያው በሚያመጣው ጥቅምና ያለባቸው ችግር በመወገዱ ላይ ነው የሚገደበው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. የሰውን ልጅ ተፈጥሮ ለመጠበቅ ሲባል ለሶስት ቀንና ከዛ በታች ማኩረፍ እንደተፈቀደ እንረዳለን። ለሶስት ቀናት ማኩረፉም ይቅር የተባለው ይህንኑ ተፈጥሯዊ ባህሪ ለማስተናገድ ሲባል ነው።
2. ሰላምታ ነፍሶች ውስጥ ያለን አለመግባባት ማስወገዱና የመዋደድ ምልክትም በመሆኑ የሰላምታን ደረጃ ያስረዳናል ፤
3. ኢስላም በወንድማማችነት ላይና በአማኞቹ አንድነት ዙሪያ መጓጓቱን እንረዳለን።

(5365)

(٢٢٣) - عن سهل بن سعد رضي الله عنه عن رسول الله صلى الله عليه وسلم قال: «مَنْ يَضْمَنْ لِي مَا بَيْنَ لَحْيَيْهِ وَمَا بَيْنَ رِجْلَيْهِ أَضْمَنْ لَهُ الْجَنَّةَ». [صحيح] - [رواه البخاري]

(223) - ከሰህል ቢን ሰዕድ -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው የአሏህ መልዕክተኛ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ ብለዋል፡ "በሁለት መንገጭላዎቹ መካከል እና በሁለት እግሮቹ መካከል ያሉትን (ሊጠብቅ) ዋስትና ለገባልኝ እኔም ጀነትን ዋስትና እገባለታለሁ።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን አንድ ሙስሊም እነርሱን በሚገባ ከጠበቀ ጀነት የሚገባባቸው የሆኑ ሁለት ጉዳዮችን ተናገሩ።

የመጀመርያው፡ የላቀው አሏህን ከሚያስቆጣ ንግግር ምላስን መቆጣብ፤

ሁለተኛው፡ ብልትን ብልግና ከመፈፀም መጠበቅ ነው።

ምክንያቱም አብዛኛውን ጊዜ ወንጀል የሚፈፀምባቸው እነዚህ ሁለቱ አካላት ስለሆኑ ነው።

## ከሐዲሡ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ምላስንና ብልትን መጠበቅ ጀነት ለመግባት ሰበብ መሆኑን እንረዳለን።
2. ምላስና ብልት ተለይተው የተጠቀሱበት ምክንያት የሰው ልጅ በዱንያውም ሆነ በአኺራው ለሚመጣበት መከራ ዋነኛ ምንጮች ሁለቱ በመሆናቸው ነው።

(3475)

(٢٢٤) - عَنْ أَبِي سَعِيدٍ الخُدْرِيِّ رَضِيَ اللهُ عَنْهُ -وَكَانَ غَزَا مَعَ النَّبِيِّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ ثِنْتَيْ عَشْرَةَ غَزْوَةً- قَالَ: سَمِعْتُ أَرْبَعًا مِنَ النَّبِيِّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ، فَأَعْجَبْنَنِي، قَالَ: «لاَ تُسَافِرِ المَرْأَةُ مَسِيرَةَ يَوْمَيْنِ إِلَّا وَمَعَهَا زَوْجُهَا أَوْ ذُو مَحْرَمٍ، وَلاَ صَوْمَ فِي يَوْمَيْنِ: الفِطْرِ وَالأَضْحَى، وَلاَ صَلاَةَ بَعْدَ الصُّبْحِ حَتَّى تَطْلُعَ الشَّمْسُ، وَلاَ بَعْدَ العَصْرِ حَتَّى تَغْرُبَ، وَلاَ تُشَدُّ الرِّحَالُ إِلَّا إِلَى ثَلاَثَةِ مَسَاجِدَ: مَسْجِدِ الحَرَامِ، وَمَسْجِدِ الأَقْصَى، وَمَسْجِدِي هَذَا». [صحيح] - [متفق عليه]

(224) - ከአቡ ሰዒድ አልኹድሪይ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና እንደተላለፈው - ከነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ጋር አስራ ሁለት ዘመቻዎችን ዘምቷል። - እንዲህ አለ: "አራት ነገሮችን ከነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ሰምቼ አስደንቀውኛል። እንዲህ ብለዋል: 'ሴት ልጅ ከርሷ ጋር ባሏ ወይም ዘመዷ ከሌሉ በቀር ሁለት ቀን የሚያስኬድ መንገድን አትጓዝ። ሁለት ቀናት ላይ መፆም የለም፤ ዒደል ፊጥርና አድሓ። ከሱብሒ በኋላ ፀሀይ እስክትወጣ ድረስ ሶላት የለም፤ ከዐስር በኋላም ፀሀይ እስክትገባ ድረስም ሶላት የለም። ወደ ሶስት መስጂዶች ካልሆነ በቀርም ጓዝን ሸክፎ አይኬድም: ወደ መስጂደል ሐራም፣ ወደ መስጂደል አቅሷና ወደዚህ መስጂዴ።'" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ከአራት ጉዳዮች ከለከሉ።

የመጀመሪያው: ሴት ልጅን ያለባሏ ወይም ያለ አንድ ዘመዷ ሁለት ቀን የሚያስኬድ መንገድ ከመጓዝ መከልከል ነው። ዘመዷ የተባሉትም እንደ ልጅ፣ አባት፣ የወንድም ልጅ፣ የእህት ልጅ፣ አጎትና የመሳሰሉት ያሉ ለዘላለም በነርሱ ላይ ለጋብቻ እርም የተደረገችባቸው ቅርብ ዘመዶቿ ናቸው።

ሁለተኛው: የዒደል ፊጥርና የዒደል አድሓ ቀንን የመፆም ክልክልነት ነው። በነዚህ ቀናቶች ላይ አንድ ሙስሊም ለስለትም ወይም ለበጎ ፍቃደኝነትም ወይም ለማካካሻ ብሎም መፆሙ ክልክል ነው።

ሶስተኛው: ከዐስር ሶላት በኋላ ፀሀይ እስክትገባ ድረስና ጎህ ከቀደደ በኋላ ፀሀይ እስክትወጣ ድረስ ሱና ሶላትን ከመስገድ መከልከሉ ነው።

አራተኛው: ከነዚህ ሶስት መስጂዶች በቀር ወደ ማንኛውም ስፍራ ወደርሱ የመጓዝን ብልጫ አስቦ፣ በመጓዝ ምክንያትም ምንዳ ይነባበራል ብሎ በማመን መጓዝ መከልከላቸው ነው። ከነዚህ ሶስት መስጂዶች በቀርም በውስጧ ለመስገድ በሚል ጓዝ ተሸክፎ አይኬድም። ከነዚህ ሶስት መስጊዶች በቀርም ምንዳ አይነባበርምና። እነሱም: መስጂደል ሐራም፣ የነቢዩ መስጂድና መስጂደል አቅሷ ናቸው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ሴት ልጅ ያለ ቅርብ ዘመዷ መጓዟ አለመፈቀዱን እንረዳለን።
2. ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) "ባሏ ወይም ቅርብ ዘመዷ" ስላሉ፤ ሴት ልጅ ለሴት ልጅ ጉዞ ላይ መሕረም አትሆንም።
3. ጉዞ ተብሎ የሚጠራን ሁሉ ሴት ልጅ ከባሏ ጋር ወይም ቅርብ ዘመዷ ጋር ካልሆነች በቀር መጓዟ ትከለከላለች። በዚህ ሐዲሥ የተጠቀሰውም ከጠያቂውና ከስፍራው መጠን አንፃር ነው።
4. የሴት ልጅ መሕረም የሚባለው ባሏ ወይም እንደ አባት፣ ልጅ፣ አጎት የመሰሉ በቅርብ ዝምድና ምክንያት ከነርሱ ጋር መጋባትን ለዘላልም እርም የተደረገባት አካላቶች፤ ወይም እንደጥቢ አባቷ፣ የጥቢ አጎቷ ይመስል በጥቢ ምክንያት ከነርሱ ጋር ለዘላለም መጋባትን እርም የተደረገባት አካላቶች፤ ወይም እንደባል አባት የመሰሉ በአማችነት ምክንያት ከነርሱ ጋር

መጋባትን እርም የተደረገባት አካላት ናቸው። "መሕረም" የተባለው ሙስሊም፣ አቅመ አዳም የደረሰ፣ ጤነኛና ታማኝ መሆን ይገባዋል። ከመሕረሙ የተፈለገው ነገር ሴትን መጠበቅ ከለላ መሆንና የሚያስፈልጋትን ማሟላት ነውና።

5. ኢስላማዊ ሸሪዓ በሴት ጉዳይ ትኩረት መስጠቱን፣ መጠበቁንና ከለላ መሆኑን እንረዳለን።
6. ልቅ የሆኑ (በጊዜ ያልተገደቡ) ሱና ሶላቶች ከፈጅርና ዐስር ሶላት በኋላ ተቀባይነት እንደሌላቸው እንረዳለን። ከዚህ ውስጥ ግን ያመለጡ ግዴታ ሶላቶችና እንደተሒየተል መስጂድ ያሉት ምክንያት ያላቸው ሶላቶች ተለይተው ይወጣሉ።
7. ፀሀይ ከወጣች በኋላ በቀጥታ ሶላት መስገድ ክልክል ነው። ይልቁንም የግድ ከአስር ደቂቃ እስከ ሩብ ሰአት ያክል ቆይቶ የጦር ርዝመት ያክል ከፍ እስክትል ድረስ መጠበቅ ይገባል።
8. የዐስር ወቅት ፀሀይ እስክትገባ ድረስ ይረዝማል።
9. ከዚህ ሐዲሥ ወደ ሶስቱ መስጊድ ጓዝ ሸክፈን መጓዝ እንደሚፈቀድ እንረዳለን።
10. የሶስቱ መስጂዶችን ትሩፋትና ከሌሎች መስጂዶች የተለዩ መሆናቸውን እንረዳለን።
11. የነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ቀብር እንኳ ቢሆን ቀብሮችን ለመዘየር መጓዝ እንደማይፈቀድ እንረዳለን። መዲና ውስጥ ላለ ወይም ለሸሪዓዊና ለተፈቀደ ዓላማ ለመጣ ሰው ግን መዘየሩ ይፈቀድለታል።

(10603)

(٢٢٥) - عن أسامة بن زيد رضي الله عنهما عن النبي صلى الله عليه وسلم قال: «مَا تَرَكْتُ بَعْدِي فِتْنَةً أَضَرَّ عَلَى الرِّجَالِ مِنَ النِّسَاءِ». [صحيح] - [متفق عليه]

(225) - ከኡሳማህ ቢን ዘይድ -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንዲህ ብለዋል: "ከኔ በኋላ ወንዶች ላይ ከሴት የበለጠ እጅግ ጎጂ ፈተና አልተውኩም።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ከሳቸው በኋላ በወንዶች ላይ ከሴቶች የበለጠ እጅግ ጎጂ ፈተናና መሞከሪያ እንዳልተዉ ተናገሩ። ከቤተሰቡ አባላት ከሆነች ሸሪዓን ከሚፃረር መንገድ ላይ እሷን የመከታተል ጣጣው ይገኝበታል። ባዳ ከሆነች ደግሞ ከሷ ጋር በመቀላቀልና ለብቻቸው በመገለል በርሱ ሳቢያ ብልሽቶችን የሚያመጡ ነገሮችን በመፈፀም ነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ሙስሊም የሆነ ሰው የሴቶችን ፈተና መጠንቀቅና በርሷ ወደ መፈተን የሚያደርሰውን መንገዶችን ሁሉ መዝጋት ይገባዋል።
2. አንድ አማኝ በአላህ መጠበቅና ከፈተና ነፃ እንዲያደርገውም ወደርሱ መከጀል ይገባዋል።

(5830)

(٢٢٦) - عَن عَبْدِ اللهِ بنِ مَسْعُودٍ رَضِيَ اللهُ عَنْهُ قَالَ: كُنَّا مَعَ النَّبِيِّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ، فَقَالَ: «مَنِ اسْتَطَاعَ البَاءَةَ فَلْيَتَزَوَّجْ، فَإِنَّهُ أَغَضُّ لِلْبَصَرِ، وَأَحْصَنُ لِلْفَرْجِ، وَمَنْ لَمْ يَسْتَطِعْ فَعَلَيْهِ بِالصَّوْمِ، فَإِنَّهُ لَهُ وِجَاءٌ». [صحيح] - [متفق عليه]

(226) - ከዐብደላህ ቢን መስዑድ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: «ከነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ጋር ሳለን እንዲህ አሉ: "የጋብቻን ጣጣ የቻለ ሰው ያግባ! ጋብቻ አይንን ሰባሪና ብልትን ጠባቂ ነውና። ጋብቻን ያልቻለ ሰው መፆም አለበት። ፆም ለርሱ ማኮላሺያ (የጾታዊ ፍላጎቱን የሚቆርጥለት) ነውና።"» [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ግንኙነትንና የጋባቻን ጣጣ የቻለን ሰው እንዲያገባ አነሳሱ። ይህም ጋብቻ አይንን ከሐራም ጠባቂና ብልቱንም እጅግ በጣም ጠብቆለት ዝሙት ላይ ከመውደቅ ስለሚከለክለው ነው። የጋብቻን ጣጣ ሳይችል ግንኙነትን የቻለ ሰውም መጾም ይገባዋል። ፆም የብልትን ስሜት እና መጥፎ የዘር ፈሳሽን ይቆርጣልና።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. እስልምና በጨዋነት ምክንያቶች ላይና ከዝሙት መፅዳት ላይ ጥረት ማድረጉን እንረዳለን።
2. የጋብቻን ጣጣ ያልቻለ ሰው በመፆም መነሳሳቱን እንረዳለን። ፆም ስሜትን ያዳክማልና።
3. ፆም ከመኮላሸት ጋር የተመሳሰለው: መኮላሸት ማለት የሁለቱን ፍሬዎች ደምስር መቀጥቀጥ ማለት ነው። ሁለቱ ፍሬዎች በመወገዳቸውም

የግንኙነት ፍላጎት ይወገዳል። ልክ እንደዚሁ ፆምም የግንኙነትን ስሜት ያደክማል።

(5863)

(٢٢٧) - عَنْ أَبِي سَعِيدٍ الْخُدْرِيِّ رضي الله عنه عَنِ النَّبِيِّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ قَالَ: «إِنَّ الدُّنْيَا حُلْوَةٌ خَضِرَةٌ، وَإِنَّ اللهَ مُسْتَخْلِفُكُمْ فِيهَا، فَيَنْظُرُ كَيْفَ تَعْمَلُونَ، فَاتَّقُوا الدُّنْيَا وَاتَّقُوا النِّسَاءَ، فَإِنَّ أَوَّلَ فِتْنَةِ بَنِي إِسْرَائِيلَ كَانَتْ فِي النِّسَاءِ». [صحيح] - [رواه مسلم]

(227) - ከአቡ ሰዒድ አልኹድሪይ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል፦ "ዱንያ ጣፋጭና አረንጓዴ (ለምለም) ናት። አላህም እንዴት እንደምትሰሩ ሊያያችሁ በውስጧ ምትኮች አድርጓችኋል። ዱንያንም ተጠንቀቁ! ሴቶችንም ተጠንቀቁ! የበኒ ኢስራኢሎች የመጀመሪያ ፈተና የተከሰተው በሴቶች ነበርና።" [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ዱንያ ስትቀመስ ጣፋጭ ስትታይ ደግሞ አረንጓዴ ለምለም ስለሆነች ሰው በርሷ እንደሚሸወድ፣ በርሷ እንደሚሰምጥና ትልቁ ጉዳዩ እንደሚያደርጋትም ገለፁ። ከፍ ያለውና ጥራት የተገባው አላህ በዚህች የዱንያ ህይወት እንዴት እንደምንሰራና ለርሱ ታዛዥ እንሆናለን? ወይስ እናምፀዋለን? የሚለውን ለመመልከት ከፊላችን ከፊሉን እንዲተካ አድርጓል። ከዚያም: "የዱንያ መጣቀሚያና ጌጧ እንዳይሸውዳችሁ፤ አላህ ያዘዛችሁን ለመተውና በከለከላችሁ ላይ ለመውደቅ እንዳያነሳሳችሁ ተጠንቀቁ! አሉ። እጅግ ትልቁ ከዱንያ ፈተናዎች መካከል መጠንቀቅ ግድ የሚሆንብንም የሴቶች ፈተና ነው። ሴት በኒ ኢስራኢሎች የወደቁበት የመጀመሪያዋ ፈተና ናት።"

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ጥንቁቅነትን አጥብቆ በመያዝ ላይና በዱንያ ውጫዊ ገፅታና ጌጧ አለመሸወድ ላይ መነሳሳቱ።
2. ሴቶችን በማየት ወይም ከባዕድ ወንዶች ጋር መቀላቀላቸውን በማቃለል ወይም ከዚህ ውጪም ባሉ መፈተኛዎች በሴቶች ፈተና ከመውደቅ መጠንቀቅ እንደሚገባ እንረዳለን።
3. የሴቶች ፈተና ከዱንያ እጅግ ትላልቅ ፈተናዎች መካከል አንዱ ነው።
4. ባለፉት ህዝቦች መገሰፅና ትምህርትን መውሰድ እንደሚገባ እንረዳለን። በኒ ኢስራኢሎች ላይ የተከሰተው ሌላውም ላይ ሊከሰት ይችላልና።
5. የሴቶች ፈተና ሲባል ሚስት ከሆነች ሰውየውን ከአቅሙ በላይ በሆነ ወጪ ታስገድደውና በዚህም ዲናዊ ጉዳዮችን ከመፈለግ ጠምዳው ሙሉ ጊዜውን ዱንያን በመፈለግ ላይ እያዋለ እንዲጠፉ ታደርገዋለች፤ ባዕድ ሴት ከሆነች ደግሞ የርሷ ፈተና ከቤቷ በምትወጣ ወቅትና ከወንዶች ጋር በምትቀላቀል ጊዜ ወንዶችን ማታለሏና ከእውነት ዞር እንዲሉ ማድረጓ ነው። በተለይ ደግሞ የተራቆቱና የተገላለጡ ከሆኑ እንደየደረጃው ዝሙት ላይ ወደ ለመውደቅ ይዳርጓቸዋል። ስለዚህም የትኛውም አማኝ በአላህ ለመጠበቅና ከነርሱ ፈተና ለመዳን ከአላህ ጋር ትስስሩን ማጠንከር ይገባዋል።

(3053)

(٢٢٨) - عَنْ عُقْبَةَ بْنِ عَامِرٍ رضي الله عنه أَنَّ رَسُولَ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ قَالَ: «إِيَّاكُمْ وَالدُّخُولَ عَلَى النِّسَاءِ» فَقَالَ رَجُلٌ مِنَ الأَنْصَارِ: يَا رَسُولَ اللهِ أَفَرَأَيْتَ الحَمْوَ؟ قَالَ: «الحَمْوُ المَوْتُ».
[صحيح] - [متفق عليه]

(228) - ከዑቅበህ ቢን ዓሚር (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: የአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና እንዲህ ብለዋል: "ሴቶች ጋር ከመግባት ተጠንቀቁ!" አንድ ከአንሷር የሆነ ሰውዬም "የአላህ መልክተኛ ሆይ! ስለባል ቅርብ ዘመዶች ንገሩኝ እስኪ?" አለ። እርሳቸውም "የባል ቅርብ ዘመድማ ሞት ነው።" አሉ። [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

**ትንታኔ:**

ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ከእንግዳ ሴቶች ጋር ከመቀላቀል እንዲህ በማለት አስጠነቀቁ "በሴቶች ላይ ከመግባትና ሴቶችም እናንተ ዘንድ እንዳይገቡ ነፍሳችሁን ጠብቁ!"

አንድ የአንሷር ሰውዬም እንዲህ አለ: እስኪ ንገሩኝ የባል ወንድም፣ የወንድሙ ልጅ፣ አጎቱ፣ የአጎቱ ልጅ፣ የእህቱ ልጅና የመሳሰሉት ባታገባ ኖሮ ልታገባቸው የሚፈቀዱላት የባል ቅርብ ዘመዶች ቢገቡስ ይፈቀዳልን?

ነቢዩም (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና "ሞትን እንደምትጠነቀቁት እርሱንም ተጠንቀቁት! ከባል ዘመዶች ጋር ገለል ብሎ ማሳለፍ ለሃይማኖት ፈተናና ጥፋት የሚመራ ነው። ከአባቱና ከልጆቹ ውጪ ያሉ የባል ቅርብ ዘመዶችን መከልከል ከሌላው ባዳ ወንድ የበለጠ የተገባ ነው። ይህም ከሌላ ባዳ ጋር ለብቻ ከምታሳልፍበት ጊዜ ይልቅ ከባል ቅርብ ዘመድ ጋር ለብቻ የማሳለፍ እድሉ የበዛ ስለሆነ ከሌላው በበለጠ ከርሱ ጋር መጥፎ ነገር መከሰቱ ስለሚገመትና ያለምንም አውጋዥ ወደ ሴቷ መድረስና ከርሷ ጋር ለብቻ ማሳለፍ ስለሚችል ፈተና የመከሰት እድሉም የሚመች ነው። በተለምዶ የባል ወንድም የወንድሙ ሚስት ብቻዋን እያለች መግባት ቸል የሚባል ጉዳይ ስለሆነ ፈተና መከሰቱ የማይቀር ጉዳይ ነው። ከባዳ ወንድ ጋር

ለብቻ ማሳለፍማ የሚጠነቀቁት ጉዳይ ነው። ከርሱ በተቃራኒ ከባል ዘመድ ጋር ለብቻ የማሳለፍ አፀያፊነትና የሚያስከትለው ችግር ግን ከሞት ጋር ይመሳሰላል።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ዝሙት ላይ የመውደቂያን መዳረሻ ለመዝጋት ወደ ባዳ ሴቶች ከመግባትና ከነርሱ ጋር ለብቻ ከማሳለፍ መከልከሉን እንረዳለን።
2. ይህ ክልከላ የሴቷ ቅርብ ዘመዶች ያልሆኑን የባል ወንድምንና ቅርብ ዘመዶቹን ጨምሮ ባዳ ወንዶችን ባጠቃላይ የሚጠቀልል ነው። (ባል በሌለበት) መግባቱ ብቻ ከርሷ ጋር መገለልን ማስፈረዱ የማይቀር ጉዳይ ነው።
3. መጥፎ ነገር ላይ መውደቅን በመፍራት ብዙሃን ስህተት ላይ የሚወድቁበትን ስፍራ መራቅ ይገባል።
4. ነወዊ እንዲህ ብለዋል: «የቋንቋ ምሁራን ባጠቃላይ እንደተስማሙት "አሕማእ" ማለት የባል ቅርብ ዘመዶች ናቸው። አባቱ፣ አጎቱ፣ ወንድሙ፣ የወንድሙ ልጅ፣ የአጎቱ ልጅና የመሳሰሉት ማለት ነው። "አኽታን" ማለት ደግሞ የሚስት ቅርብ ዘመዶች ናቸው። "አስሃር" የሚለው ቃል ደግሞ ለሁለቱም የሚውል ስም ነው።»
5. የባል ዘመድ ከሞት ጋር አመሳስለው የመግለፃቸው ምስጢር:- ኢብኑ ሐጀር እንዲህ ብለዋል: «ዐረቦች የሚጠሉትን ነገር በሞት ይመስሉታል። የመመሳሰሉም መልክ ከባል ዘመድ ጋር ወንጀል ከተፈፀመ በዲን በኩል እንደሞት ነው፤ ወንጀል ከተፈፀመም ከባል ዘመድ ጋር ተገልላ ያሳለፈችው የመወገር ግዴታ ስላለባት ትሞታለች፤ ባል ቅናቱ ለፍቺ ከገፋፋውም ከባሏ መለየቷ ለሴቷ ጥፋት ነው።»

(5888)

(٢٢٩) - عن أبي موسى رضي الله عنه أن النبي صلى الله عليه وسلم قال: «لا نِكَاحَ إلّا بِوَلِيٍّ».
[صحيح] - [رواه أبو داود والترمذي وابن ماجه وأحمد]

(229) - ከአቡ ሙሳ (ረዲየላሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ አሉ፦ "ያለ ወሊይ ፈቃድ ጋብቻ የለም።" [ሶሒሕ ነው።] - [አቡዳውድ፣ ቲርሚዚ፣ ኢብኑማጀህና አሕመድ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) አንዲት ሴት የጋብቻዋን ውል ለማሰር ሀላፊነት በሚወስድ ወሊይ ካልሆነ በስተቀር ጋብቻ መፈፀም እንደማይበቃላት ገለፁ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. የወሊይ መኖር ጋብቻው ትክክለኛ እንዲሆን መስፈርት ነው። ያለ ወሊይ ወይም ሴቲቱ ራሷን ብትድር ጋብቻው አይበቃም።
2. ወሊይ የሚሆነው ወደ ሴቷ እጅግ ቅርብ ዘመድ የሆነ ወንድ ነው። ከርሱ የቀረበ ወሊይ እያለ ሩቅ የሆነ ወሊይ እሷን ማጋባት አይችልም።
3. ወሊይ ለመሆን የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይገባዋል: - አቅመ አዳምና የአይምሮ ጤነኛ (ሙከለፍ) መሆን፣ ወንድ መሆን፣ የጋብቻን ጥቅም የሚያውቅ አስተዋይ መሆኑ (ቂላቂል አለመሆን)፣ ወሊዩና ተጋቢዋ ተመሳሳይ እምነት መከተላቸው ነው። እነዚህን ባህሪያቶች ያልተላበሰ የጋብቻን ውል በማሰር ረገድ ለወሊይነት የተገባ አይደለም።

(58066)

(٢٣٠) - عن عقبة بن عامر رضي الله عنه قال: قال رسول الله صلى الله عليه وسلم: «أَحَقُّ الشُّرُوطِ أَنْ تُوفُوا بِهِ مَا اسْتَحْلَلْتُمْ بِهِ الْفُرُوجَ». [صحيح] - [متفق عليه]

(230) - ከዑቅበህ ቢን ዓሚር -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: "የአላህ መልክተኛ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንዲህ አሉ: 'ልታሟሉት ከሚገቡ መስፈርቶች ሁሉ ልታሟሉት እጅግ የተገባው ብልትን ሐላል ያደረጋቹበትን መስፈርት ነው።'" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል። ]

## ትንታኔ:

ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም መሙላቱ እጅግ የተገባው መስፈርት በሴት መጠቀምን ሐላል ለማድረግ ሰበብ የሆነውን መስፈርት መሆኑን እየነገሩን ነው። ይህም ሚስት በጋብቻው ውል ወቅት የምታስቀምጣቸው የተፈቀዱ መስፈርቶች ናቸው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ሐላልን ሐራም ሐራምን ሐላል ከሚያደርጉ መስፈርቶች በስተቀር ከሁለቱ ጥንዶች መካከል አንዱ ለሌላው ቃል የገባውን መስፈርቶች መሙላት ግዴታ ነው።
2. የኒካሕን መስፈርቶች ማሟላት ከሌላ መስፈርቶች የበለጠ ሊሟላ የሚገባው ነው። ምክንያቱም እነዚህ መስፈርቶች ብልትን ሐላል ለማድረግ የሚገቡት ቃል ነውና።
3. ኢስላም የጋብቻ መስፈርቶችን እንዲጠበቁ አፅንኦት መስጠቱ ጋብቻ በኢስላም ውስጥ ያለው ደረጃ ከፍ ያለ መሆኑን ያስረዳል።

(6021)

(٢٣١) - عن عبد الله بن عمرو رضي الله عنهما أن رسول الله صلى الله عليه وسلم قال: «الدُّنْيَا مَتَاعٌ، وَخَيْرُ مَتَاعِ الدُّنْيَا الْمَرْأَةُ الصَّالِحَةُ». [صحيح] - [رواه مسلم]

(231) - ከዐብደላህ ቢን ዐምር -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው የአላህ መልክተኛ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንዲህ ብለዋል፦ "ዱንያ መጣቀሚያ ናት። ከዱንያ መጣቀሚያዎች ምርጡ መልካም ሚስት ናት።" [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ዱንያም ውስጧ ያሉ ነገሮችም በሙሉ ጊዜያዊ መጠቀሚያዎች ሆነው ከዚያም የሚጠፉ መሆናቸውን፤ በላጬ መጣቀሚያም ሲያያት የምታስደስተው፣ ሲያዛት የምትታዘዘው፣ ሲርቅ ነፍሷንና ንብረቱን የምትጠብቅ መልካም ሚስት መሆኗን ተናገሩ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. አላህ ለባሮቹ ፍቁድ ባደረጋቸው የዱንያ መልካም ነገሮች ላይ ያለማባከንና ያለመኩራራት መጠቀም መፈቀዱን ፤
2. ባልን በጌታው አምልኮ ላይ ስለምታግዝ መልካም ሚስት በመምረጥ ላይ መነሳሳቱን ፤
3. ከዱንያ መጣቀሚያዎች ሁሉ ምርጡ አላህን በማምለክ ላይ የሆነ ወይም አላህን በማምለክ ላይ አጋዥ የሆኑ ነገር መሆኑን እንረዳለን።

(5794)

(٢٣٢) - عَنْ جَرِيرِ بْنِ عَبْدِ اللهِ رَضِيَ اللهُ عنه قَالَ: سَأَلْتُ رَسُولَ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ عَنْ نَظَرِ الْفُجَاءَةِ فَأَمَرَنِي أَنْ أَصْرِفَ بَصَرِي. [صحيح] - [رواه مسلم]

(232) - ከጀሪር ቢን ዐብደላህ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ ብለዋል፦ «የአላህን መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ስለድንገተኛ እይታ ጠየቅኳቸው። እርሳቸውም አይኔን እንዳዞር አዘዙኝ።» [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ጀሪር ቢን ዐብደላህ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና ነቢዩን (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ወንድ ልጅ ባዳ ሴትን ሳያስበው በድንገት በማየቱ ጉዳይ ጠየቀ። ነቢዩም (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና እንዳወቀ ፊቱን ወደሌላ አቅጣጫ ማዞር ግዴታው መሆኑን አሳሰቡት። ይህን ካደረገም ወንጀል እንደማይኖርበት ተናገሩ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. አይንን በመስበር መታዘዙን እንረዳለን።
2. ዓይኑ ማየቱ ክልክል ወደ ሆነ ነገር ሳያስበው በድንገት ካረፈ አትኩሮ ከመመልከት መከልከሉን እንረዳለን።
3. እዚህ ሐዲሥ ውስጥ ሶሐቦች ዘንድ ሴቶችን የመመልከት ክልክልነት የተረጋገጠ ጉዳይ እንደነበር ያስረዳናል። የዚህም ማስረጃው ጀሪር (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና ነቢዩን (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና የጠየቀው ሳያስበው ዓይኑ ሴት ልጅ ላይ ቢያርፍ ብይኑ አስቦ እንዳየው ነውን? የሚል ነበርና ነው።

4. ይህ ሐዲሥ ሸሪዓ ሰዎችን ለሚጠቅም ነገር እንዴት ትኩረት እንደሰጠ ያስረዳናል። ሴትን ልጅ ማየት ዱንያዊና አኺራዊ ጉዳት ስለሚያስከትል ሸሪዓ ሴትን ከመመልከት ከለከለ።
5. ሶሐቦች አስቸጋሪ ጥያቄ ሲያጋጥማቸው ወደ ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ተመልሰው እንደሚጠይቁ እንረዳለን። ልክ እንደዚሁ ዛሬም ሙስሊሞች አስቸጋሪ ጉዳይ ሲያጋጥማቸው ወደ ዑለማዎች ተመልሰው መጠየቅ ይገባቸዋል።

(8902)

(٢٣٣) - عَنْ أَنَسٍ رَضِيَ اللهُ عنهُ قَالَ: ضَحَّى النَّبِيُّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ بِكَبْشَيْنِ أَمْلَحَيْنِ أَقْرَنَيْنِ، ذَبَحَهُمَا بِيَدِهِ، وَسَمَّى وَكَبَّرَ، وَوَضَعَ رِجْلَهُ عَلَى صِفَاحِهِمَا. [صحيح] - [متفق عليه]

(233) - ከአነስ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና እንደተላለፈው እንዲህ ብለዋል: «ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ለኡዱሒያ ሁለት ቡራቡሬና ቀንዳም የሆኑ ሙክቶችን በእጃቸው አረዱ። "ቢስሚላህ አላሁ አክበር" አሉና እግራቸውን አንገቱ ላይ አድርገው አረዱት።» [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

አነስ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) የዒድ አልአድሓ ቀን በእጃቸው ሁለት ቀንዳሞችና ጥቁር የተቀላቀለባቸው ነጫጭ ወንድ ሙክት በጎችን "ቢስሚላህ አላሁ አክበር" በማለት እግራቸውን አንገታቸው ላይ አድርገው እንዳረዱ ተናገረ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ኡዱሒያ የተደነገገ እንደሆነ እንረዳለን። በዚህም ጉዳይ ዑለሞች ባጠቃላይ ተስማምተዋል።

2. ኡዱሒያው ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ያረዱት አይነት መሆኑ በላጭ ነው። ይህም ሲታይ ስለሚያምርና ሞራውና ስጋውም ጣፋጭ ስለሚሆን ነው።
3. ነወዊይ እንዲህ ብለዋል: «በዚህ ሐዲሥ አንድ ሰው ኡዱሒያውን በራሱ ማረድ እንደሚገባና በቂ ምክንያት ሳይኖረው ለማረድ ሰው መወከል እንደሌለበት እንረዳለን። በቂ ምክንያት ካለው ግን ሲታረድ መገኘቱ ይወደድለታል። በርሱ ፋንታ እንዲያርድለት ሙስሊም ሰው ከተካ ያለምንም ልዩነት ይፈቀዳል።
4. ኢብኑ ሐጀር እንዲህ ብለዋል: «በዚህ ሐዲሥ ውስጥ በማረድ ወቅት ቢስሚላህ ከማለት ጋር አላሁ አክበር ማለት እንደሚወደድ፤ እግርን ደሞ በሚታረደው ቀኝ የአንገቱ ክፍል ላይ ማኖር እንደሚወደድ እንረዳለን። የሚታረደውን የምናስተኛው በግራ ጎኑ በመሆኑ ዑለሞች ተስማምተዋል። ለአራጁ ቢላን በቀኝ እጅ መያዝ፣ በግራ እጁ ደግሞ ጭንቅላቱን መያዝ እንዲቀለው እግሩን በሚታረደው እንስሳ ቀኝ አንገት ላይ ያደርጋል።
5. ኡዱሒያ ቀንዳሙን ማረድ እንደሚወደድ እንረዳለን። ቀንድ ከሌለውም ግን ይፈቀዳል።

(2971)

(٢٣٤) - عَن عَبْدِ الرَّحْمَنِ بْنِ أَبِي لَيْلَى أَنَّهُمْ كَانُوا عِنْدَ حُذَيْفَةَ، فَاسْتَسْقَى فَسَقَاهُ مَجُوسِيٌّ، فَلَمَّا وَضَعَ القَدَحَ فِي يَدِهِ رَمَاهُ بِهِ، وَقَالَ: لَوْلاَ أَنِّي نَهَيْتُهُ غَيْرَ مَرَّةٍ وَلاَ مَرَّتَيْنِ –كَأَنَّهُ يَقُولُ: لَمْ أَفْعَلْ هَذَا–، وَلَكِنِّي سَمِعْتُ النَّبِيَّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ يَقُولُ: «لاَ تَلْبَسُوا الحَرِيرَ وَلاَ الدِّيبَاجَ، وَلاَ تَشْرَبُوا فِي آنِيَةِ الذَّهَبِ وَالفِضَّةِ، وَلاَ تَأْكُلُوا فِي صِحَافِهَا، فَإِنَّهَا لَهُمْ فِي الدُّنْيَا وَلَنَا فِي الآخِرَةِ».

[صحيح] - [متفق عليه]

(234) - ከዐብዱረሕማን ቢን አቢ ለይላ እንደተላለፈው እነርሱ ሑዘይፋ ዘንድ ነበሩ። የሚጠጣ እንዲሰጡት ሲጠይቅ አንድ እሳት አምላኪ የሚጠጣ (በብር እቃ) ሰጠው። እቃውን (በሑዘይፋ) እጁ ላይ ሲያኖረውም በርሱ ወረወረበትና እንዲህ አለ: "ከአንድና ሁለት ጊዜ በላይ ባልከለክለው ኖር - ይህን አላደርግም

ነበር - ነበር። ነገር ግን ነቢዩን (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ሲሉ ሰምቻቸዋለሁ: "የቀጭን ሐርንና የወፍራም ሐርን ልብስ አትልበሱ! በወርቅና ብር እቃ አትጠጡ! በ(ወርቅና ብር) ትሪም አትብሉ! እርሷ በዚህ ዓለም ለነርሱ ናት፤ በመጪው ዓለም ደግሞ ለኛ ናት።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) የሐርን ልብስ በየትኛውም አይነቱ ከመልበስ ወንዶችን ከለከሉ። ወንዶችንም ሴቶችንም በወርቅና ብር እቃዎችና መሳሪያ ከመብላትና ከመጠጣት ከለከሉ። ይህም አማኞች በዚህች አለም አላህን ለመታዘዝ እንደራቁት ሁሉ የትንሳኤ ቀን ደግሞ ለአማኞች ብቻ እንደሆነ ተናገሩ። ከነዚህ መካከልም ለከሀዲያኖች በመጪው ዓለም ምንም የላቸውም። ምክንያቱም የአላህን ትእዛዝ በማመፅ ቸኩለው በዚህ ዓለም ህይወታቸው ምርጥ የሚሉትን ነገሮች በመያዝ ስለተጠቀሙ ነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. በወንዶች ላይ ቀጭንና ወፍራም ሐር ክልክል መሆኑንና የለበሰው ላይም ብርቱ ዛቻ እንዳለበት እንረዳለን።
2. ቀጭንና ወፍራም ሐር መልበስ ለሴቶች ይፈቀዳል።
3. በወንድም ሆነ በሴቶች ላይ በወርቅና ብር ትሪዎችና እቃዎች መብላትና መጠጣት ክልክል መሆኑን እንረዳለን።
4. የሑዘይፋ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና አወጋገዝ ጠንከር ያለ መሆኑን እንመለከታለን። የዚህንም ምክንያት ከአንድ ጊዜ በላይ የወርቅና ብር እቃዎችን እንዳይጠቀም መከልከሉና እርሱ ግን አለመቆጠቡ እንደሆነ ገልጿል።

(2985)

(٢٣٥) - عن علي رضي الله عنه عن النبي صلى الله عليه وسلم قال: «رُفِعَ الْقَلَمُ عن ثلاثة: عن النائم حتى يَسْتَيْقِظَ، وعن الصبي حتى يَحْتَلِمَ، وعن المجنون حتى يَعْقِلَ».
[صحيح] - [رواه أبو داود والترمذي والنسائي في الكبرى وابن ماجه وأحمد]

(235) - ከዐሊይ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና እንዲህ ብለዋል: "ከሶስት ዓይነት አካላት ላይ ብእር ተነስቷል። የተኛ ሰው እስኪነቃ ድረስ፤ ህፃን ልጅ አቅመ አዳም እስኪደርስ ድረስ እና እብድ ጤነኛ እስኪሆን ድረስ ነው።" [ሶሒሕ ነው።] - [አቡዳውድ፣ ቲርሚዚ፣ ነሳኢ በኩብራ፣ ኢብኑማጀህና አሕመድ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ከነዚህ ሶስት አካላት በቀር የግዴታ ነገሮች ተጠያቂነት ለአደም ልጆች ሁሉ የማይቀር እንደሆነ ተናገሩ።

ጨቅላ ህፃን ልጅ እስኪተልቅና አቅመ አዳም እስኪደርስ ድረስ፤

አይምሮውን ያጣ እብድ አይምሮው ወደርሱ እስኪመለስለት ድረስ፤

እንቅልፉን የተኛ ሰው እስኪነቃ ድረስ ናቸው።

ከነዚህ አካላት ተጠያቂነት ተነስቷል። ወንጀል ቢሰሩ በነርሱ ላይ አይፃፍም። ነገር ግን ከእብድና የተኛ ሰው ውጪ ለትንሽ ህፃን ልጅ መልካም ስራ ከሰራ ይፃፍለታል። ይህም እብድና የተኛ ሰው አይምሮዋቸው ስለተወገደ አምልኮን አስተካክለው የሚፈፅሙ አካላት ስላልሆኑ ነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. የሰው ልጅ ተጠያቂነት የሚነሳለት ወይ ግዴታውን ከመፈፀም መንቃት እንዳይችል ባደረገው እንቅልፍ ምክንያት ነው፤ ወይም ከተጠያቂነት እድሜ በማነሱና ልጅ በመሆኑ ምክንያት ነው ፤ ወይም የአይምሮው ተግባር የተምታታበት እብድ በመሆኑ ወይም ወደ እብደት የተጠጋ ስካር

ላይ በመሆኑ ምክንያት ነው። ትክክለኛ መለየትንና መረዳት ያልቻለ ሰውና በነዚህ ሶስት ምክንያቶች ሳቢያ ለተጠያቂነት ብቁ ያልሆነ ሰው አላህ ተባረከ ወተዓላ በፍትሃዊነቱ፣ በቻይነቱና ቸርነቱ በአላህ ሐቅ ላይ ከሚያጓድለው ወይም ወሰን ከሚያልፈው ነገር ተጠያቂነቱን አንስቶለታል።

2. በነርሱ ላይ ወንጀል አለመፃፉ አንዳንድ ዱንያዊ ፍርዶች ይመለከታቸዋል ከሚለው ጋር አይጣረስም። ለምሳሌ እብድ ቢገል የመገደልና ጉማ የመክፈል ግዴታ የለበትም። በወራሽ ቤተሰቦቹ (የርሱ "ዓቂላ" በሆኑት) ላይ ግን ጉማ የመክፈል ግዴታ አለባቸው።
3. ለአቅመ አዳምነት መድረስ ሶስት ምልክቶች አሉት: በህልም ወይም በሌላ ምክንያት የዘር ፈሳሽ ማፍሰስ ወይም የብልት አካባቢ ፀጉር በማብቀል ወይም አስራ አምስት አመት በመሙላት ነው። ሴት ከሆነች አራተኛ ምልክት አላት፤ እርሱም የወር አበባ ማየት ነው።
4. ሱብኪ እንዲህ ብለዋል: ጨቅላ በማለት የተፈለገው ህፃን ልጅ ማለት ነው። ሌሎች ዑለሞች ደግሞ: ልጅ እናቱ ሆድ ውስጥ እያለ ፅንስ ይባላል። ሲወለድ ጨቅላ ሲጠነክር ጀምሮ እስከ ሰባት አመቱ ደግሞ ህፃን ይባላል። ከዚያም እስከ አስር አመቱ ለምድ አዙር ይባላል። ከዚያም እስከ አስራ አምስት አመቱ ደግሞ የደረሰ ይባላል። በነዚህ ሁሉ አመታት ውስጥ ባለው እርከን ህፃን ልጅ ከመባል አይወገድም ብለዋል። ይህንም የተነተኑት ሱዩጢይ ናቸው።

(58148)

(٢٣٦) - عن ابن عمر رضي الله عنهما: أَنَّ رَسُولَ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ نَهَى عَنِ الْقَزَعِ.
[صحيح] - [متفق عليه]

(236) - ከኢብኑ ዑመር -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው: "የአላህ መልክተኛ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ፀጉርን አንዱን ተላጭቶ አንዱን ትቶ ከመቆረጥ ከልክለዋል።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም የጭንቅላት ፀጉርን አንዱን ተላጭቶ አንዱን ትቶ ከመቆረጥ ከለከሉ።
ክልከላው ልጅም አዋቂም ወንዶችን የሚያጠቃልል ነው። ሴት ግን የጭንቅላት ፀጉሯን መላጨት አይፈቀድላትም።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ኢስላማዊ ሸሪዐ ለሰው ልጅ አካላዊ መገለጫም ትኩረት መስጠቱን እንረዳለን።

(8914)

(٢٣٧) - عن ابن عمر رضي الله عنهما عن النبي صلى الله عليه وسلم قال: «أَحْفُوا الشَّوَارِبَ وأَعْفُوا اللِّحَى». [صحيح] - [متفق عليه]

(237) - ከኢብኑ ዑመር (ረዲየላሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል: "ቀድሞ ቀመስን (ከአፍንጫ ስር ያለውን ፂም) አሳጥሩ ሪዛችሁን (የመንጋጭላ ፂማችሁን) ልቀቁ!" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ቀድሞ ቀመስን መቁረጥና አለመልቀቅን አዘዙ። እንደውም በደንብ መቁረጥ እንዳለበት ገለፁ።

በተቃራኒው ሪዝን (የመንጋጭላን ፂም) መልቀቅና እንደበዛ መተውን አዘዙ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ሪዝን መላጨት መከልከሉን እንረዳለን።

(3279)

(٢٣٨) - عَن أَبِي سَعِيدٍ الْخُدْرِيِّ رضي الله عنه أَنَّ رَسُولَ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ قَالَ: «لَا يَنْظُرُ الرَّجُلُ إِلَى عَوْرَةِ الرَّجُلِ، وَلَا الْمَرْأَةُ إِلَى عَوْرَةِ الْمَرْأَةِ، وَلَا يُفْضِي الرَّجُلُ إِلَى الرَّجُلِ فِي ثَوْبٍ وَاحِدٍ، وَلَا تُفْضِي الْمَرْأَةُ إِلَى الْمَرْأَةِ فِي الثَّوْبِ الْوَاحِدِ». [صحيح] - [رواه مسلم]

(238) - ከአቡ ሰዒድ አልኹድሪይ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል: "ወንድ ልጅ ወደ ወንድ ልጅ ሀፍረተ ገላ አይመልከት! ሴት ልጅም ወደ ሴት ልጅ ሀፍረተ ገላ አትመልከት! ወንድ ልጅ ከሌላ ወንድ ጋር በአንድ ልብስ ውስጥ አይጠቅለል! ሴት ልጅም ከሌላ ሴት ጋር በአንድ ልብስ ውስጥ አትጠቅለል!" [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ ( የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ወንድ ልጅ ወደ ሌላ ወንድ ልጅ ሀፍረተ ገላ መመልከቱን ወይም ሴት ልጅ ወደ ሌላ ሴት ልጅ ሀፍረተ ገላ መመልከቷን ከለከሉ።

ሀፍረተ ገላ ማለት: ግልፅ የሆነ ጊዜ የሚያሳፍር የሆነ አካል ሁሉ ነው። የወንድ ልጅ ሀፍረተ ገላ ከእምብርት እስከ ጉልበቱ ሲሆን፤ የሴት ልጅ ደግሞ ከባዕድ ወንዶች አንፃር ሁሉም ሰውነቷ ሀፍረተ ገላ ነው። ከሴቶችና ከዘመዶቿ አንፃር ደግሞ በተለምዶ ቤት ውስጥ ስሰራ ግልፅ የሚሆነውን ያክል ግልፅ ታደርጋለች።

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ወንድ ልጅ ተራቁቶ ከሌላው ወንድ ጋር በአንድ ልብስ ውስጥ ወይም ለብቻቸው ከአንድ ብርድ ልብስ ስር መገለላቸውን ከለከሉ። ሴት ልጅም ተራቁታ ወደ ሴት ልጅ በአንድ ልብስ ውስጥ ወይም ለብቻቸው ከአንድ ብርድ ልብስ ስር መገለላቸውን ከለከሉ። ምክንያቱም ይህ አንዱ የሌላኛው ኣደኛውን ሀፍረተ ገላ ወደመንካት ያደርሰዋልና። መንካቱ ደግሞ እንደማየቱ ክልክል ነው። እንደውም ወደ ትልቅ ብክለት ስለሚያመራ መንካቱ ከማየትም በበለጠ ክልክል ነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ባልና ሚስት ካልሆኑ በቀር ሀፍረተ ገላን ከመመልከት መከልከሉን እንረዳለን።
2. ኢስላም ማህበረሰቡን በማፅዳትና ለብልሹነት የሚያደርሱ መንገዶችን በመዝጋት ላይ ያለውን ጥረት እንረዳለን።
3. እንደ ህክምና ለመሰሉ ጉዳዮች ሀፍረተ ገላን መመልከት አስፈላጊ ሆኖ የተገኘ ጊዜ መመልከት ይፈቀዳል። ነገር ግን ከስሜት ውጪ በሆነ ሁኔታ መሆን ይገባዋል።
4. ሙስሊም ሀፍረተ ገላውን በመሸፈን ላይና የሌላን ሰው ሀፍረተ ገላ ከመመልከት አይኑን ዝቅ በማድረግ ላይ መታዘዙን እንረዳለን።
5. ክልከላው ወንዶችን ከወንዶች ጋር፣ ሴቶችን ከሴቶች ጋር ብቻ በመከልከል መገደቡ ማየትና ሀፍረተ ገላን መግለጥ ብዙ ጊዜ ቀለል ተደርጎ የሚታይ ስለሆነ ነው።

(8904)

(٢٣٩) - عن عبد الله بن عمرو رضي الله عنهما قال: لَمْ يَكُنِ النَّبِيُّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ فَاحِشًا وَلَا مُتَفَحِّشًا، وَكَانَ يَقُولُ: «إِنَّ مِنْ خِيَارِكُمْ أَحْسَنَكُمْ أَخْلَاقًا». [صحيح] - [متفق عليه]

(239) - ከዐብደላህ ቢን ዐምር -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው እንዲህ ብለዋል፡- "ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ባለጌ (ጸያፍ) አልነበሩም፣ ጸያፍ ቃላትም አይናገሩም። እንዲህም ይሉ ነበር: ' ከናንተ ምርጡ ስነምግባሩ እጅግ ያማረው ነው።'" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ከነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ስነምግባር መካከል ፀያፍ መናገር ወይም ፀያፍ ድርጊት አይገኝም ነበር። ትዝም አይላቸው። እሳቸው ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም የላቀ ስነምግባር ባለቤት ነበሩ።

ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንዲህ ይሉ ነበር: "አላህ ዘንድ ከናንተ መካከል በላጬ መልካምን በመለገስ፣ ፊቱን በመፍታት፣ ሰውን ከማወክ በመቆጠብና የነሱን ክፋት በመቻል እንዲሁም ሰዎች ጋር ባማረ መልኩ በመናኗር ስነምግባሩ እጅግ ያማረው ነው።"

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. አንድ አማኝ ከፀያፍ ንግግርና ከመጥፎ ተግባር ሊርቅ እንደሚገባው፤
2. የአላህ መልክተኛ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ስነምግባር ምሉዕ መሆኑንና ከሳቸው መልካም ስራና ምርጥ ንግግር እንጂ ሌላ እንደማይመነጭ፤
3. መልካም ስነምግባር የሽቅድድም መድረክ መሆኑን እንረዳለን። የቀደመ ምርጥ አማኝና ኢማኑ የሞላ ይሆናል።

(5803)

(٢٤٠) - عن عائشة رضي الله عنها قالت: سمعت رسول الله صلى الله عليه وسلم يقول: «إِنَّ الْمُؤْمِنَ لَيُدرِكُ بِحُسْنِ خُلُقِهِ دَرَجَةَ الصَّائِمِ القَائِمِ». [صحيح بشواهده] - [رواه أبو داود وأحمد]

(240) - ከእናታችን ዓኢሻህ -አላህ መልካም ስራዋን ይውደድላትና- እንደተላለፈው እንዲህ ብላለች: "የአላህ መልክተኛን ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንዲህ ሲሉ ሰምቻለሁ:- 'አንድ ሙእሚን በመልካም ስነምግባሩ የፆመኛና (የሌሊት) ሰጋጅን ደረጃ ያገኛል።'" [በማመሳከሪያዎቹ ሶሒሕ ነው።] - [አቡዳውድና አሕመድ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

መልካም ስነምግባርን የተላበሰ ሰው ቀኑን በመፆምና ሌሊቱን በመቆም የዘወተረ ሰውን ደረጃ እንደሚደርስ ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ገለፁ። መልካም ስነምግባር ሲጠቀለል: መልካምን መለገስ፣ ንግግርን ማሳመር፣ ፊትን መፍታት፣ ሰውን ከመጉዳት መቆጠብና የነሱን ክፋት መቻል ነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ኢስላም ስነምግባርን በማጥራትና በማሟላት ላይ ትልቅ ትኩረት መቸሩን እንረዳለን።
2. አንድ ሰው በመልካም ስነምግባሩ ቀን ምንም ሳያፈጥር የሚፆምና ምንም ሳይደክም ሌሊቱን የሚቆም ሰው ደረጃ ላይ መድረሱ የመልካም ስነምግባርን ትሩፋት ያስረዳናል።
3. ቀኑን መፆምና ሌሊቱን መቆም ለነፍስ የሚከብዱ ትልልቅ ስራዎች ናቸው። መልካም ስነምግባርን የተላበሰ ሰው የነርሱን ደረጃ የደረሰውም ነፍሱን በመልካም መስተጋብር ላይ ስለታገለ ነው።

(5799)

(٢٤١) - عن أبي هريرة رضي الله عنه قال: قال رسول الله صلى الله عليه وسلم: «أَكْمَلُ الْمُؤْمِنِينَ إِيمَانًا أَحْسَنُهُمْ خُلُقًا، وَخَيْرُكُمْ خَيْرُكُمْ لِنِسَائِهِمْ». [حسن] - [رواه أبو داود والترمذي وأحمد]

(241) - ከአቡ ሁረይራ -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ ብለዋል: "የአላህ መልዕክተኛ ሰለሏሁ ዓለይሂ ወሰለም እንዲህ ብለዋል፡ 'ከአማኞች መካከል ኢማናቸው የተሟላው ስነምግባራቸው እጅግ ያማረ የሆኑት ናቸው ፤ ከአማኞች መካከል ምርጦቹ ደግሞ ለሴቶቻቸው ምርጥ የሆኑት ናቸው።'" [ሐሰን ነው።] - [አቡዳውድ፣ ቲርሚዚና አሕመድ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ከሰዎች መካከል ኢማኑ የሞላው ስነምግባሩ ያማረ ሰው እንደሆነ ተናገሩ። ይህም ለሰዎች ፊቱን ፈታ በማድረግ፣ መልካምን በመስጠት፣ ንግግርን በማሳመርና ሰዎችን ከማወክ በመቆጠብ ነው።

ከአማኞች መካከል ምርጦቹ ደግሞ ለሴቶቻቸው ለምሳሌ ለሚስቱ፣ ለሴት ልጆቹ፣ ለእህቶቹና ለቅርብ ዘመዶቹ ምርጥ የሆኑ ናቸው። ምክንያቱም ሴቶች በመልካም ስነምግባር ሊኗኗራቸው ከሰዎች ሁሉ ይበልጥ የተገቡ ስለሆኑ ነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. የመልካም ስነምግባር ትሩፋትን እንረዳለን። እሱ ከኢማን የሚመደብ ነውና።
2. ተግባር ከኢማን የሚመደብ መሆኑን፤ ኢማን ይጨምራልም ይቀንሳልም።
3. ኢስላም ሴቶችን የሚያከብር እምነት መሆኑን፤ ለነርሱ መልካም በመስራት ላይ መበረታታቱንም እንረዳለን።

(5792)

(٢٤٢) - عن أبي هريرة رضي الله عنه قال: سُئِلَ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ عَنْ أَكْثَرِ مَا يُدْخِلُ النَّاسَ الْجَنَّةَ، فَقَالَ: «تَقْوَى اللهِ وَحُسْنُ الْخُلُقِ»، وَسُئِلَ عَنْ أَكْثَرِ مَا يُدْخِلُ النَّاسَ النَّارَ فَقَالَ: «الْفَمُ وَالْفَرْجُ». [حسن صحيح] - [رواه الترمذي وابن ماجه وأحمد]

(242) - ከአቡ ሁረይራ -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: የአላህ መልክተኛ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም በአብዛኛው ሰዎችን ጀነት ስለሚያስገባው ነገር ተጠየቁ፤ እሳቸውም "አላህን መፍራት እና መልካም ስነምግባር ነው።" አሉ። በአብዛኛው ሰዎችን እሳት ስለሚያስገባቸው ነገርም ተጠየቁ። እሳቸውም "ምላስና ብልት ነው።" አሉ። [ሐሰኑን ሶሒሕ ነው።] - [ቲርሚዚ፣ ኢብኑ ማጀህና አሕመድ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ጀነት የሚያስገቡ ትልልቅ ምክንያቶች ሁለት መሆናቸውን ገለፁ። እነሱም:

አላህን መፍራትና መልካም ስነምግባር ናቸው።

አላህን መፍራት: በአንተና በአላህ ቅጣት መካከል መጠበቂያ ማድረግህ ነው። ይህም ትእዛዙን በመፈፀምና ክልከላውን በመራቅ ነው።

መልካም ስነምግባር ደሞ: ፊትን ፈታ በማድረግ ፣ መልካምን በመለገስና ከማወክ በመቆጠብ ነው።

እሳት የሚያስገቡት ትልልቅ ምክንያቶች ደግሞ ሁለት ናቸው። እነሱም:

ምላስና ብልት ናቸው።

ከምላስ ወንጀሎች መካከል:- ውሸት፣ ሀሜት፣ ወሬ ማዋሰድና ሌሎችም ናቸው።

ከብልት ወንጀሎች መካከል ደሞ:- ዝሙት፣ ግብረሰዶምና ሌሎችም ይጠቀሳሉ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ጀነት መግባት ከአላህ ትእዛዝ ጋር የተገናኙ ምክንያቶች አሉት። ከነሱም መካከል:- አላህን መፍራትን ይመስል። ከሰዎች ጋር የተገናኙ ምክንያቶችም አሉት። ከነሱም መካከል:- መልካም ስነምግባርን ይመስል።
2. ምላስ እሳት ከመግቢያ ምክንያቶች መካከል ስለሆነ በባለቤቱ ላይ አደገኛ መሆኑ፤
3. የስሜት ተገዢ መሆንና ፀያፍ ወንጀሎችን መስራት በአብዛኛው እሳት የመግቢያ ምክንያቶች መካከል አንዱ ስለሆነ በሰው ላይ አደጋ መሆኑን እንረዳለን።

(5476)

(٢٤٣) - عن أنس بن مالك رضي الله عنه قال: كَانَ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ أَحْسَنَ النَّاسِ خُلُقًا. [صحيح] - [متفق عليه]

(243) - ከአነስ ቢን ማሊክ -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው እንዲህ አለ: "የአላህ መልክተኛ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ከሰዎች ባጠቃላይ ይበልጥ ስነምግባራቸው እጅግ ያማረ ሰው ነበሩ።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ከሰዎች ሁሉ ስነምግባራቸው እጅግ የተሟላ ሰው ናቸው። ንግግርን በማሳመር፣ መልካምን በመለገስ፣ ፊታቸው በመፍታት፣ መጥፎ ከመስራት በመቆጠብ፣ ሌሎች የሚያደርሱባቸውን ጉዳት

በመቻል በሁሉም ስነምግባሮችና መልካምነት ባጠቃላይ ግንባር ቀደም ናቸው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. የነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ስነምግባር ምሉዕ መሆኑን እንረዳለን።
2. ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም በመልካም ስነምግባር የተሟሉ ተምሳሌት ናቸው።
3. በመልካም ስነምግባር ዙሪያ ነቢዩን ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም መከተል መነሳሳቱን እንረዳለን።

(6180)

(٢٤٤) - قال سعد بن هشام بن عامر –عندما دخل على عائشة رضي الله عنها-: يَا أُمَّ الْمُؤْمِنِينَ، أَنْبِئِينِي عَنْ خُلُقِ رَسُولِ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ، قَالَتْ: أَلَسْتَ تَقْرَأُ الْقُرْآنَ؟ قُلْتُ: بَلَى، قَالَتْ: فَإِنَّ خُلُقَ نَبِيِّ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ كَانَ الْقُرْآنَ. [صحيح] - [رواه مسلم في جملة حديثٍ طويل]

(244) - ሰዕድ ቢን ሂሻም ቢን ዓሚር እናታችን ዓኢሻህ ዘንድ -አላህ መልካም ስራዋን ይውደድላትና- የገባ ወቅት እንዲህ አለ: "የሙእሚኖች እናት ሆይ! ስለአላህ መልክተኛ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ስነምግባር ንገሪኝ! እሷም 'ቁርአን አትቀራምን?' አለችኝ። እኔም 'እንዴታ!' አልኩኝ። እሷም ' የነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ስነምግባር ቁርአን ነበር።' አለችኝ።" [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ረጅሙ የሐዲሦ ጥቅል ውስጥ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

የአማኞች እናት የሆነችው ዓኢሻህ -አላህ መልካም ስራዋን ይውደድላትና- ስለነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ስነምግባር ተጠየቀች። ጠያቂውን ሁሉንም ምሉዕ ባህሪያት ወደ ሰበሰበው ወደ ተከበረው ቁርአን በመመለስ ጠቅላይ በሆነ ንግግር መለሰችለት። ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ቁርአናዊውን ስነምግባር የተላበሱ ፤ ቁርአን ያዘዘውን ይፈፅሙ፣ ቁርአን የከለከለውን ደግሞ ይርቁ

እንደነበር፤ የሳቸው ስነምግባር በቁርአን መስራት ፣ ድንበሩ ላይ መቆም፣ የቁርአንን አዳብ መላበስ ፣ ምሳሌዎቹንና ታሪኮቹን ማስተንተን ነበር ብላ መለሰችላት።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ቁርአናዊ ስነምግባር በመላበሳቸው ነቢዩን ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም አርአያ ማድረግ ላይ መነሳሳቱን እንረዳለን።
2. የአላህ መልክተኛ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ስነምግባር መሞገሱ። የሳቸው ስነምግባር ከወሕይ ምንጭ የተቀዳ ነውና።
3. ቁርአን ለሁሉም የተከበሩ ስነምግባሮች ምንጭ መሆኑን እንረዳለን።
4. ስነምግባር በኢስላም ሁሉንም የሃይማኖቱን ክፍሎች ያጠቃልላል፤ ይህም ትእዛዛትን በመፈፀምና ክልከላውን በመራቅ ነው።

(8265)

(٢٤٥) - عَنْ عَائِشَةَ أُمِّ المُؤمنينَ رضي الله عنها قَالَتْ: كَانَ النَّبِيُّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ يُعْجِبُهُ التَّيَمُّنُ، فِي تَنَعُّلِهِ، وَتَرَجُّلِهِ، وَطُهُورِهِ، وَفِي شَأْنِهِ كُلِّهِ. [صحيح] - [متفق عليه]

(245) - ከአማኞች እናት ዓኢሻ (ረዲየሏሁ ዐንሃ) - አላህ መልካም ሥራዋን ይውደድላትና - እንደተላለፈው እንዲህ ብላለች፡- «ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ጫማ ሲለብሱ፣ ሲያበጥሩ፣ ሲፅዳዱና በሁሉም ጉዳያቸው ቀኝን መጠቀም ይወዱ ነበር።» [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ለማክበር የተገቡ የሆኑ ጉዳያቸውን ሲፈፅሙ በቀኝ መጀመርን ይወዱና ያስበልጡ ነበር። ከነዚህ ጉዳዮችም መካከል: ጫማ ሲያደርጉ በቀኝ እግር ይጀምራሉ፤ የጭንቅላታቸውን ፀጉርና ፂማቸውን ሲያበጥሩ፣ ሲቀቡና ሲያስውቡ በቀኝ

ይጀምሩ ነበር፣ እጃቸውና እግራቸውን ዉዱእ ሲያደርጉም ቀኛቸውን ከግራ ያስቀድሙ ነበር።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ኢማሙ ነወዊይ እንዲህ ብለዋል፦ ይህ በሸሪዓ ውስጥ ቀጣይነት ያለው መርህ ነው። እርሱም ልብስና ሱሪ መልበስ፣ ጫማ መልበስ፣ መስጂድ መግባት፣ ጥርስን መፋቅ፣ መኳል፣ ጥፍርን መቁረጥ፣ ቀድሞ ቀመስን ማሳጠር፣ ፀጉር ማበጠር፣ የብብት ፀጉርን መንጨት፣ ጭንቅላትን መላጨት፣ ከሶላት ማሰላመት፣ የንፅህና አካላትን መታጠብ፣ ከሽንት ቤት መውጣት፣ መብላት፣ መጠጣት፣ መጨባበጥ፣ ጥቁሩን ድንጋይ ሰላም ማለትና የመሳሰሉትን በዚሁ ደረጃ ላይ ያሉ ክብርና ልቅና ያለውን ነገር በቀኝ መጀመር ይወደዳል። በተቃራኒው የሆነ ነገር ደግሞ ሽንት ቤት መግባት፣ ከመስጂድ መውጣት፣ መናፈጥ፣ ኢስቲንጃእ፣ ልብስና ሱሪ ማውለቅ፣ ጫማ ማውለቅና የመሳሰሉትን በግራ መጀመር ይወደዳል። ይህ ሁሉም ቀኝ ክብርና ልቅና ስላላት ነው።
2. "ቀኝን መጠቀም ይወዱ ነበር።" የሚለው: ድርጊቶችን በቀኝ እጅ፣ በቀኝ እግር ፣ በቀኝ ጎን፣ መጀመርንና ነገሮችን በቀኝ መቀባበልን ያካትታል።
3. ነወዊይ እንዲህ ብለዋል: «ከዉዱእ አካላት መካከል ቀኝን ማስቀደም የማይወደድበት አካላቶች አሉ። እነርሱም ሁለቱ ጆሮዎች፣ ሁለቱ መዳፎችና ጉንጮች ሲሆኑ እነዚህ ሁሉ እኩል ነው የሚፀዱት። ይህንን ማድረግ የማይችል አካሉ የተቆረጠና መሰል (አንድ ላይ ማድረግ የማይችል) አይነት ከሆነ ቀኝን ያስቀድማል።»

(3018)

(٢٤٦) - عن شداد بن أوس رضي الله عنه قال: ثِنْتَانِ حَفِظْتُهُمَا عَنْ رَسُولِ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ قَالَ: «إِنَّ اللهَ كَتَبَ الْإِحْسَانَ عَلَى كُلِّ شَيْءٍ، فَإِذَا قَتَلْتُمْ فَأَحْسِنُوا الْقِتْلَةَ، وَإِذَا ذَبَحْتُمْ فَأَحْسِنُوا الذَّبْحَ، وَلْيُحِدَّ أَحَدُكُمْ شَفْرَتَهُ، فَلْيُرِحْ ذَبِيحَتَهُ». [صحيح] - [رواه مسلم]

(246) - ከሸዳድ ቢን አውስ - አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተዘገበው እንዲህ አሉ: ሁለቱን ከአላህ መልክተኛ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ንግግር ሸምድጃለሁ፡- "አላህ በሁሉም ነገሮች ላይ ኢሕሳን (እንድናሳምር) ፅፏል። የገደላችሁ ጊዜ አገዳደላችሁን አሳምሩ፤ ያረዳችሁም ጊዜ አስተራረዳችሁን አሳምሩ። አንዳችሁ ቢላውን ይሞርድ እርዱንም ይገላግለው። " [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም አላህ በኛ ላይ በሁሉም ነገሮችኢሕሳንን ግዴታ እንዳደረገ ተናገሩ። ማሳመር (ኢሕሳን) ማለት  በአምልኮውም ውስጥ፣ መልካምን ሲፈፅምም፣ ከፍጡራን ላይ ጎጂን ነገር ሲያስወግድም ዘወትር አላህ ያየኛል ማለት ሲሆን ከነዚህም ውስጥ በመግደልና በማረድ ውስጥ ማሳመርም አንዱ ነው።

በመግደል ኢሕሳን ሲባል በቂሷስ (ሸሪዐዊ የቅጣት ብይን ለምሳሌ የገደለ መገደል) ተፈፃሚነት ወቅት: ለመግደል ገሩን፣ ቀላሉንና የተገዳዩን ነፍስ በፍጥነት ሊያወጣ የሚችለውን መንገድ በመምረጥ ነው።

በእርድ ማሳመር ሲባል ደግሞ እንስሳ በምናርድበት ወቅት ነው። ይህም መሳሪያውን በደንብ በመሞረድ ፣ የሚታረደው እንስሳ እያየ ፊት ለፊቱ ባለመሞረድና ሌላ እርዱን የሚመለከት እንስሳ በታው ላይ እያለ ባለማረድ ለእንስሳ በማዘን ነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. የላቀውና የተከበረው አላህ በፍጡራኑ ላይ ያለው እዝነትና ርህራሄን፤

2. አገዳደልና አስተራረድ ላይ ኢሕሳን የሚባለው ሸሪዐውን የተከተለ (የዋጀ) በሆነ መልኩ ሲፈፀም ነው።
3. ሸሪዐ ምሉዕና ሁሉንም መልካም ነገር የጠቀለለ ሲሆን ከዚህም መካከል ለእንስሳት ማዘኑና መራራቱ አንዱ ነው፤
4. የሰውን ልጅ ከገደሉ በኋላ ሰውነቱን መቆራረጥ መከልከሉን፤
5. እንስሳትን መቅጣት ያለበት ነገር ሁሉ ክልክል መሆኑን ተረድተናል።

(4319)

(٢٤٧) - عن عبد الله بن عمرو رضي الله عنهما قال: قال رسول الله صلى الله عليه وسلم: «إِنَّ الْمُقْسِطِينَ عِنْدَ اللهِ عَلَى مَنَابِرَ مِنْ نُورٍ، عَنْ يَمِينِ الرَّحْمَنِ عَزَّ وَجَلَّ، وَكِلْتَا يَدَيْهِ يَمِينٌ، الَّذِينَ يَعْدِلُونَ فِي حُكْمِهِمْ وَأَهْلِيهِمْ وَمَا وَلُوا». [صحيح] - [رواه مسلم]

(247) - ከዐብደላህ ቢን ዐምር -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው እንዲህ አለ፡- የአላህ መልክተኛ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንዲህ ብለዋል፡- "ፍትሃዊዎች (የትንሳኤ ቀን) አላህ ዘንድ በብርሃን በተሰራ ወንበር ላይ ከአርራሕማን ቀኝ በኩል ይሆናሉ። ሁለቱም የአላህ እጆች ቀኝ ናቸው። (ፍትሃዊ የሚባሉትም) እነዚያ በፍርዳቸው፣ በቤተሰቦቻቸውና በተሾሙበት ጉዳዮች ላይ ፍትህን የሚያሰፍኑ ናቸው።" [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

እነዚያ በአመራራቸውና በፍርዳቸው ስር ያሉ ሰዎችን እና በቤተሰቦቻቸው መካከል በፍትህና በእውነት የሚፈርዱ ሰዎች የትንሳኤ ቀን ለነሱ ክብር ይሆን ዘንድ ከፍ ባሉ ከብርሃን የተፈጠሩ ወንበሮች ላይ እንደሚቀመጡ ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ተናገሩ። እነዚህም ወንበሮች በአርራሕማን ቀኝ በኩል የሚገኙ ናቸው። ጥራት የተገባው አላህ ሁለቱም እጆቹ ቀኝ ናቸው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. የፍትህ ትሩፋቱና በሱ ላይ መበረታታቱ፤

2. ፍትህ በሰዎች መካከል ያሉ ሁሉንም ፍርድና ኃላፊነትን የሚያካትት ጠቅላይ ቃል ነው። በሚስቶች፣ በልጆችና በሌሎችም መካከል ፍትህ ማስፈን ሳይቀር ፍትሃዊነት ውስጥ ይገባል።
3. የትንሳኤ ቀን የፍትሃዊዎች ደረጃ መገለፁን ፤
4. የትንሳኤ ቀን የኢማን ባለቤቶች ደረጃ የሚበላለጥ መሆኑን ፤ ሁሉም በስራው ልክ ነውና የሚመነዳው።
5. በማነሳሳት ማስተማር ዘይቤ የሚማሩትን ሰዎች ትምህርቱን እንዲቀበሉ የሚያነሳሳ ከሆኑት የማስተማር ዘይቤዎች መካከል መሆኑን እንረዳለን።

(4935)

(٢٤٨) - عن أبي سعيد الخدري رضي الله عنه أن رسول الله صلى الله عليه وسلم قال: «لَا ضَرَرَ وَلَا ضِرَارَ، مَنْ ضَارَّ ضَرَّهُ اللهُ وَمَنْ شَاقَّ شَقَّ اللهُ عَلَيْهِ». [صحيح بشواهده] - [رواه الدارقطني]

(248) - ከአቢ ሰዒድ አልኹድሪይ -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው የአላህ መልክተኛ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንዲህ አሉ: "አውቆ መጉዳትም ሆነ ሳያውቁ መጎዳዳትም የለም (አይቻልም)። ጎጂን አላህ ይጎዳዋል። ሰዎችን ያስጨነቀ አላህ ያጨናንቀዋል።" [በማመሳከሪያዎቹ ሶሒሕ ነው።] - [ዳረቁጥኒይ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ጉዳትን በማንኛውም አይነት መገለጫው ይሁን ከነፍስ ላይም ይሁን ከሌሎች ላይ መከላከል ግዴታ እንደሆነ ገለፁ። ስለሆነም አንድም ሰው ራሱንም ይሁን በተመሳሳይ መልኩ ሌላንም ቢሆን ማወክ አይፈቀድለትም።

እንዲሁም ጉዳትን በጉዳት መመለስም አይፈቀድለትም። ምክንያቱም ወሰን ባልታለፈበት የማመሳሰል (የቂሷስ ህግ) ካልሆነ በስተቀር ጉዳትን በመጉዳት አይወገድምና።

ከዚያም ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ሰዎችን ለሚጎዳ ሰው ጉዳት እንደሚያገኘው ፤ ሰዎችን ለሚያጨናንቅም መጨናነቅ እንደሚያገኘው ዛቱ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ከማመሳሰል (ከደረሰበት በደል) በበዛ መልኩ መበቀል መከልከሉን፤
2. አላህ ባሮቹን በአንዳችም የሚጎዳቸው በሆነ ነገር አላዘዛቸውም ፤
3. በንግግር ወይም በተግባር ወይም በመተውም ቢሆን አውቆም ይሁን ሳያውቁ መጉዳት መከልከሉ ፤
4. ምንዳ በስራው አይነት ነው የሚሰጠው። የጎዳ ሰው አላህ ይጎዳዋል ፤ ያስጨነቀም አላህ ያጨናንቀዋል።
5. ከሸሪዐ መርሆዎች መካከል አንዱ: - "ጉዳት መወገድ ይገባዋል።" የሚል ነው። ሸሪዓ በፍፁም ጉዳትን እንደማያፀናና መጉዳትን እንደሚያወግዝ እንረዳለን።

(4711)

(٢٤٩) - عَنْ أَبِي مُوسَى رضي الله عنه عَنِ النَّبِيِّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ قَالَ: «إِنَّمَا مَثَلُ الْجَلِيسِ الصَّالِحِ وَالْجَلِيسِ السَّوْءِ كَحَامِلِ الْمِسْكِ وَنَافِخِ الْكِيرِ، فَحَامِلُ الْمِسْكِ: إِمَّا أَنْ يُحْذِيَكَ، وَإِمَّا أَنْ تَبْتَاعَ مِنْهُ، وَإِمَّا أَنْ تَجِدَ مِنْهُ رِيحًا طَيِّبَةً، وَنَافِخُ الْكِيرِ: إِمَّا أَنْ يُحْرِقَ ثِيَابَكَ، وَإِمَّا أَنْ تَجِدَ رِيحًا خَبِيثَةً».

[صحيح] - [متفق عليه]

(249) - ከአቡ ሙሳ (ረዲየላሁ ዐንሁ) -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ አሉ: "የመልካም ጓደኛና የመጥፎ ጓደኛ ምሳሌ እንደ ሽቶ ተሸካሚና እንደወናፍ ነፊ ነው። ሽቶ ተሸካሚ ወይ ይሰጥሀል፣ ወይ ትገዛዋለህ፣ ወይ ከርሱ መልካም መአዛን ታገኛለህ። ወናፍ ነፊ ደሞ ወይ ልብስህን ያቃጥላል ወይም ከርሱ መጥፎ ሽታን ታገኛለህ።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ሁለት አይነት ሰዎችን በምሳሌ ገለፁ።

የመጀመሪያው አይነት: ወደ አላህ የሚጠቁም፣ ወደ አላህ ውዴታ የሚመራና በአምልኮ ላይ የሚያግዝ መልካም ጓደኛ ነው። የርሱም ምሳሌ ሽቶ እንደሚሸጥ ሰው ምሳሌ ነው። ወይ ይሰጥሀል፣ ወይ ትገዛዋለህ፣ ወይም ከርሱ መልካም መአዛን ታሸታለህ።

ሁለተኛው አይነት ደግሞ ከአላህ መንገድ የሚያቅብ፣ ወንጀል በመፈፀም ላይ የሚያግዝ ፣ መጥፎ ተግባራትን የምታይበት መጥፎ ጓደኛ ነው። የሱን አይነት ሰው ወዳጅና ጓደኛ አድርገህ በመያዝህም የሚያስወቅስህ ነው። የርሱም ምሳሌ ወናፍ እንደሚያናፋ ብረት ቀጥቃጭ ነው። እርሱም ወይ በሚፈነጣጠረው እሳት ልብስህን ያቃጥላል ወይም ወደርሱ በመቅረብህ መጥፎ ሽታን ታገኛለህ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. አዳማጩ ሀሳቡ እንዲገባው ምሳሌ ማድረግ እንደሚፈቀድ እንረዳለን።
2. የመልካምና የበጎ ባለቤቶችን በመቀማመጥ ላይና የብክለትና የመጥፎ ስነ ምግባር ባለቤቶችን በመራቅ ላይ መነሳሳቱና መበረታታቱን እንረዳለን።

(3127)

(٢٥٠) - عن أبي هريرة رضي الله عنه: أَنَّ رَجُلًا قَالَ لِلنَّبِيِّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ: أَوْصِنِي، قَالَ: «لَا تَغْضَبْ» فَرَدَّدَ مِرَارًا قَالَ: «لَا تَغْضَبْ». [صحيح] - [رواه البخاري]

(250) - ከአቡ ሁረይራ -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተዘገበው እንዲህ አሉ: አንድ ሰውዬ ለነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንዲህ አለ: "ምከሩኝ!" እሳቸውም "አትቆጣ!" አሉት። ጥያቄውን ደጋግሞ መላልሶ ጠየቃቸው እርሳቸውም "አትቆጣ!" አሉት። [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ከሰሓቦች አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና አንዱ ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም አንድ የሚጠቅመውን ነገር እንዲጠቁሙት ፈለገ። እርሳቸውም እንዳይቆጣ አዘዙት። ይህም ማለት ወደቁጣ የሚያነሳሱ ምክንያቶችን እንዲርቅ፣ የሚያስቆጣ ነገር በተከሰተ ጊዜም ነፍሱን እንዲቆጣጠር፣ በቁጣው ወደ መግደል፣ መማታት፣ ስድብና የመሳሰሉት ነገር እንዳይሻገር ማለት ነው።

ሰውዬውም በተደጋጋሚ ምክር እንዲጨምሩለት ፈለገ። ነቢዩም ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም "አትቆጣ!" ከምትለው ምክር የዘለለ ምንም አልጨመሩለትም።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ከቁጣና መንስኤዎቹ መጠንቀቅ እንደሚገባ፤ ቁጣ የክፋት መሰብሰቢያ ነው። ከሱ መጠበቅ የመልካም መሰብሰቢያ ነው።
2. ለአላህ ብሎ መቆጣት የአላህ ክልከላዎች ሲደፈሩ መቆጣትን ይመስል ምስጉን የሆነ ቁጣ ነው።
3. ሰሚው እስኪሸመድደውና አንገብጋቢነቱን እስኪገነዘብ ድረስ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ንግግርን መደጋገም እንደሚገባ፤
4. አዋቂ ከሆነ ሰው ምክር መፈለግ ያለውን ትሩፋት ተረድተናል።

(٢٥١) - عن أبي هريرة رضي الله عنه أن رسول الله صلى الله عليه وسلم قال: «لَيْسَ الشَّدِيدُ بِالصُّرَعَةِ، إِنَّمَا الشَّدِيدُ الَّذِي يَمْلِكُ نَفْسَهُ عِنْدَ الْغَضَبِ». [صحيح] - [متفق عليه]

(251) - ከአቡ ሁረይራ -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው የአላህ መልክተኛ ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም እንዲህ ብለዋል፡ "ብርቱ የሚባለው ታግሎ ያሸነፈ ሳይሆን በቁጣ ወቅት እራሱን የተቆጣጠረ ነው።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ትክክለኛ ሀይል አካላዊ ሀይል ወይም ጉልበተኞችን የሚጥል ሳይሆን ብርቱና ሀይለኛ የሚባለው ቁጣው በሚበረታ ወቅት ነፍሱን የታገለና ያሸነፋት መሆኑን ገለፁ። ምክንያቱም ይህ ሰው ነፍሱን የመቆጣጠርና ሰይጣንን የማሸነፍ አቅም እንዳለው ይጠቁማልና።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. የቻይነትና ነፍስን በቁጣ ወቅት የመቆጣጠር ትሩፋትን እንረዳለን። ይህ ኢስላም ያነሳሳበት ከሆኑ መልካም ስራዎች መካከል አንዱ ነውና።
2. ነፍስን በቁጣ ወቅት መታገል ጠላትን ከመታገልም የበለጠ ከባድ መሆኑን እንረዳለን።
3. ጃሂሊዮች ለሀይለኝነት የሰጡትን ትርጓሜ ኢስላም ወደ ክቡር መገለጫ ስነ ምግባር መለወጡን እንረዳለን። ከሰዎች ሁሉ እጅግ ብርቱ የነፍሱን ልጓም የተቆጣጠረ ነውና።
4. በግለሰብም ደረጃ ይሁን በማህበረሰብ ደረጃ ጉዳት ከማስከተሉ አኳያ ከቁጣ መራቅ እንደሚገባ እንረዳለን።

(5351)

(٢٥٢) - عَنْ عَبْدِ اللهِ بْنِ عَمْرٍو رضي الله عنهما قال: قال رَسولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ: «أَرْبَعٌ مَنْ كُنَّ فِيهِ كَانَ مُنَافِقًا خَالِصًا، وَمَنْ كَانَتْ فِيهِ خَلَّةٌ مِنْهُنَّ كَانَتْ فِيهِ خَلَّةٌ مِنْ نِفَاقٍ حَتَّى يَدَعَهَا: إِذَا حَدَّثَ كَذَبَ، وَإِذَا عَاهَدَ غَدَرَ، وَإِذَا وَعَدَ أَخْلَفَ، وَإِذَا خَاصَمَ فَجَرَ».
[صحيح] - [متفق عليه]

(252) - ከዐብደላህ ቢን ዐምር (ረዲየሏሁ ዐንሁ) -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው እንዲህ አሉ፦ «የአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና እንዲህ ብለዋል፦ "አራት ነገሮች ያሉበት ሰው ጥርት ያለ ሙናፊቅ ይሆናል። ከነርሱ መካከል ከፊሉ ያለበት ሰው እስኪተወው ድረስ ከፊል ንፍቅና ይኖርበታል። ሲያወራ ይዋሻል፣ ቃልኪዳን ይዞ ያፈርሳል፣ ቀጠሮ ይዞ ያፈርሳል፣ ሲሟገት (ድንበር ያልፋል) በጥመት ላይ ነው።"» [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ከአራት ነገሮች አስጠነቀቁ። እነዚህ አራት ነገሮች አንድ ሙስሊም ላይ የተሰባሰቡ ጊዜ በነዚህ ነገሮች ሰበብ ከመናፍቃን ጋር እጅግ በጣም ይመሳሰላል። ይህ ግን እነዚህ አራት ነገሮች እርሱ ላይ በብዛት የሚስተዋሉ ከሆነ ነው እንጂ አልፎ አልፎ የሚስተዋልበት ከሆነ ግን እዚህ ውስጥ አይካተትም። እነሱም:-

የመጀመሪያው: ሲያወራ ሆን ብሎ ይዋሻል፣ በንግግሩም እውነቱን አይናገርም።

ሁለተኛ: አንድ ቃል ኪዳን ከገባ ቃልኪዳኑን አይሞላም። ቃልኪዳን ለገባለት ሰውም ቃሉን ያፈርሳል።

ሶስተኛ: ቀጠሮን የቀጠረ ጊዜ የገባውን ቃል አይሞላም። ቀጠሮውን ያፈርሳል።

አራተኛ: ከአንድ ሰው ጋር የተጨቃጨቀና የተሟገተ ጊዜ ሙግቱ ሀይለኛ ይሆናል። ከእውነትም ይዘነበላል። እውነትን ላለመቀበልም በተንኮል ጥመትና ውሸትን ይናገራል።

ንፍቅና ማለት ውስጡ ካለው ተቃራኒ የሆነን ነገር ግልፅ ማውጣት ነው። የዚህ ሀሳብም በተመሳሳይ እነዚህን ነገሮች በሚተገብር ላይ ይገኛሉ። ንፍቅናውም ባዋራው፣ በቀጠረው፣ ባመነው፣ በተከራከረውና ቃልኪዳን በገባለት ሰው ሐቅ ላይ ነው እንጂ እስልምናን ግልፅ እያደረገ ክህደትን በመደበቅ በእስልምና ላይ መናፍቅ ሆኗል ማለት አይደለም። ከነዚህ ነገሮች መካከል አንድ ጉዳይ ያለበትም እስኪተወው ድረስ በርሱ ላይ የንፍቅና ባህሪ አለበት።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. አንዳንድ የሙናፊቅ ምልክቶች መገለጻቸው እርሱ ላይ ከመውደቅ ለማስፈራራትና ለማስጠንቀቅ ነው።
2. ከሐዲሡ የተፈለገው ቁምነገር እነዚህ ነገሮች የንፍቅና ጉዳዮች እንደሆኑ፣ ባለቤቱ በነዚህ ጉዳዮች ከመናፍቃን ጋር ተመሳሳይ እንደሆነ፣ የነርሱን ባህሪ የተላበሰ እንደሆነ ማሳወቅ ተፈልጎ ነው እንጂ እስልምናን ግልፅ እያደረገ ክህደትን የሚደብቅ ሙናፊቅ ሆኗል ለማለት ተፈልጎበት አይደለም። እነዚህ ነገሮች ያመዘኑበት፣ በነርሱ የተሳነፈና ያቃለላቸው አብዛኛው ሰው እምነቱም ብልሹ የሆነ ነው በሚልም ተተርጉሟል።
3. ሻዘሊ እንዲህ ብለዋል: «የሃይማኖት መሰረት በሶስት ነገሮች ላይ የታጠረ ነው:- ንግግር፣ ተግባርና ኒያ ናቸው። በውሸታምነት ንግግራቸው ብልሹ እንደሆነ፣ አደራ በመካድ ድርጊታቸው ብልሹ እንደሆነ፣ ቃልን በማፍረስ ኒያቸው ብልሹ እንደሆነ አስገነዘበ። ምክንያቱም ቃልን ማፍረስ የገባውን ቃል ተቃርኖ የመተው ቁርጠኝነት እስከሌለው ድረስ የሚያስነውር ተግባር አይባልም። ቃሉን ለማክበር ቁርጠኛ ሆኖ ከዚያም እንዳያከብር የሚያደርገው ከልካይ ነገር ወይም ቃሉን ለመለወጥ የተሻለ ሀሳብ ቢያጋጥመው ይህ የሙናፊቅ መለዮ አልተገኘበትም ነው የሚባለው።

4. ንፍቅና ሁለት አይነት ነው: እምነታዊ ንፍቅና: ይህ ሰውዬውን ከኢማን የሚያስወጣው ነው። ይህም እስልምናን ግልፅ አድርጎ ክህደትን መደበቅ ነው። ሌላው ተግባራዊ ንፍቅና: እርሱም ከመናፍቃን ጋር በባህሪያቸው መመሳሰል ነው። ይህም ሰውዬውን ከኢማን አያስወጣም። ነገር ግን ከትላልቅ ወንጀሎች መካከል አንዱ ነው።
5. ኢብኑ ሐጀር እንዲህ ብለዋል: «ዑለማዎች ባጠቃላይ በቀልቡም በምላሱም አምኖ ነገር ግን እነዚህን ነገሮች የሰራ ሰው በክህደት እንደማይፈረጅና በእሳት የሚዘወትር ሙናፊቅ እንደማይሆን ተስማምተዋል።»
6. ነወዊ እንዲህ ብለዋል: «የተወሰኑ ዑለሞች እንዲህ ብለዋል: እዚህ ሐዲሥ ውስጥ የተፈለጉት መናፍቃን በነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ዘመን የነበሩ በውሸት አምነናል ብለው የተናገሩ፣ በእምነታቸው ታምነው የካዱ፣ በሃይማኖት ጉዳይ እስልምናን ሊረዱ ቃልገብተው ቃላቸውን ያፈረሱ፣ በሙግቶቻቸው ጥመትን ይዘው የተሟገቱ ናቸው።»

(65124)

(٢٥٣) - عَنْ عَبْدِ اللهِ بْنِ مَسْعُودٍ رضي الله عنه قَالَ: قَالَ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ: «لَيْسَ الْمُؤْمِنُ بِالطَّعَّانِ وَلاَ اللَّعَّانِ وَلاَ الفَاحِشِ وَلاَ البَذِيءِ». [صحيح] - [رواه الترمذي]

(253) - ከዐብደላህ ቢን መስዑድ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: «የአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና እንዲህ ብለዋል: "ሙእሚን የሆነ ሰው እጅግ ተቺ፣ እጅግ ተራጋሚ፣ ፀያፍ ተግባር ሰሪ፣ መጥፎ ንግግር ተናጋሪ አይደለም።"» [ሶሒሕ ነው።] - [ቲርሚዚ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ምሉዕ ኢማን ያለው አማኝ ሰዎችን በዘራቸው የሚተች፣ ስድብና

እርግማን የሚያበዛ፣ ሃፍረተ ቢስነትን የተላበሰ ፀያፍ ድርጊትና ንግግርን የሚያበዛ እንዳልሆነ ተናገሩ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. በሸሪዓዊ ጥቅሶች ውስጥ ክልክል በመተግበር ወይም ግዴታን በመተው ካልሆነ በቀር ኢማን ውድቅ አይደረግም።
2. አካላትን በመጠበቅና ከመጥፎ ተግባራት በመታቀብ ላይ መነሳሳቱን እንረዳለን። በተለይ ምላስን።
3. ሲንዲይ እንዲህ ብለዋል: (እጅግ ተቺና እጅግ ተራጋሚ) በማለት ሁለቱ በተጋኖ ቃል መጠቀሳቸው ትችትና እርግማን የሚገባውን ሰው በትንሹ መተቸትና መርገም የኢማን ሰዎችን በኢማን ከመገለፅ እንደማያጎድልባቸው ያስረዳል።

(65869)

(٢٥٤) - عن عبد الله بن عمر رضي الله عنهما قال: سَمِعَ النَّبِيُّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ رَجُلًا يَعِظُ أَخَاهُ فِي الْحَيَاءِ، فَقَالَ: «الْحَيَاءُ مِنَ الْإِيمَانِ». [صحيح] - [متفق عليه]

(254) - ከዐብደላህ ቢን ዑመር -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: "ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም አንድ ሰውዬ ወንድሙን በአይነአፋርነቱ ሲወቅሰው ሰሙና 'አይነአፋርነት ከኢማን ነው።' አሉት። [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም አንድን ሰውዬ ለወንድሙ አይነአፋርነት ማብዛት እንዲተው ሲመክረው ሰሙትና አይነአፋርነት ከኢማን መሆኑን እና ከመልካም በስተቀር ይዞ እንደማይመጣ ገለፁለት።

አይነአፋርነት መልካም ድርጊት ለመስራትና እኩይ ተግባር ለመተው የሚያነሳሳ ስነምግባር ነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ከመልካም ተግባር የሚከለክል ባህሪ ተወዛጋቢነት፣ ደካማነት፣ ልፍስፍስነትና ፈሪነት እንጂ አይነአፋርነት አይባልም።
2. ከአሏህ ሓያእ ማድረግ የሚሆነው ትእዛዛትን በመፈፀምና ክልከላትን በመተው ነው።
3. ከፍጡራን ሐያእ ማድረግ የሚሆነው እነሱን በማክበር፣ በሚመጥናቸው ደረጃቸው ላይ በማስቀመጥና በተለምዶ ከሚያፀይፍ ድርጊት በመራቅ ነው።

(5478)

(٢٥٥) - عن المِقدام بن معدي كرب رضي الله عنه عن النبي صلى الله عليه وسلم قال: «إِذَا أَحَبَّ الرَّجُلُ أَخَاهُ فَلْيُخْبِرْهُ أَنَّهُ يُحِبُّهُ».

[صحيح] - [رواه أبو داود والترمذي والنسائي في السنن الكبرى وأحمد]

(255) - ከሚቅዳም ቢን መዕዲከሪብ እንደተላለፈው ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ ብለዋል: "አንድ ሰው ወንድሙን ከወደደው እንደሚወደው ይንገረው።" [ሶሒሕ ነው።] - [አቡዳውድ፣ቲርሚዚ፣ ነሳኢ በሱነኑል ኩብራ ፣ አሕመድ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም በምእመናን መካከል መስተጋብራቸውን ከሚያጠናክሩና በመካከላቸውም ውዴታን ከሚያሰፍኑ ሰበቦች መካከል አንዱን ጠቀሱ። ይኸውም አንድ ሰው ወንድሙን የሚወደው ከሆነ እንደሚወደው ይንገረው አሉ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ለዓለማዊ ጥቅም ሳይሆን ጥርት ባለ መልኩ ለአላህ ብሎ መውደድ ያለውን ደረጃ፤

2. መዋደዱና መግባባቱ እንዲጨምር ለአላህ ብለው የሚወዱትን እንደሚወዱት መንገር እንደሚበረታታ፤
3. በምእመናን መካከል መዋደድ መስፋፋቱ ኢማናዊ የሆነውን ወንድማማችነት እንደሚያጠነክርና ማህበረሰቡንም ከመለያየትና ከመበታተን እንደሚታደግ፤

(3017)

(٢٥٦) - عن جابر بن عبد الله رضي الله عنهما عن النبي صلى الله عليه وسلم قال: «كُلُّ مَعْرُوفٍ صَدَقَةٌ». [صحيح] - [رواه البخاري من حديث جابر، ورواه مسلم من حديث حذيفة]

(256) - ከጃቢር ቢን ዐብደላህ -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንዲህ ብለዋል: "መልካም ነገሮች ሁሉ ምፅዋት ናቸው።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪ ከጃቢር በተላለፈ ሐዲሥ ሙስሊም ደግሞ ከሑዘይፋ በተላለፈ ሐዲሥ አውርተውታል።]

## ትንታኔ:

በንግግርም ይሁን በተግባር ለሌሎች የምንውለው በጎነትና ጥቅም ሁሉ ምፅዋት እንደሚሆንና በሱም ምንዳና አጅር እንደምናገኝበት ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ተናገሩ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ምፅዋት የሰው ልጅ ከገንዘቡ በሚያወጣው ላይ ብቻ የተገደበ ሳይሆን የሰው ልጅ ወደ ሌሎች በሚደርስ መልኩ የሚሰራውና የሚናገረውን ሁሉ መልካም ነገሮችን ያቀፈ ነው።
2. በዚህ ሀዲስ ውስጥ ለመልካምና ለሌሎች ጥቅም ላለው ነገር ሁሉ መልፋትን ያነሳሳል።
3. ትንሽም እንኳን ብትሆን ከመልካም ነገር አንዳችም ማሳነስ እንደማይገባ እንረዳለን።

(5346)

(٢٥٧) - عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ رَضِيَ اللهُ عَنْهُ قَالَ: قَالَ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ: «كُلُّ سُلاَمَى مِنَ النَّاسِ عَلَيْهِ صَدَقَةٌ، كُلَّ يَوْمٍ تَطْلُعُ فِيهِ الشَّمْسُ يَعْدِلُ بَيْنَ الاِثْنَيْنِ صَدَقَةٌ، وَيُعِينُ الرَّجُلَ عَلَى دَابَّتِهِ فَيَحْمِلُ عَلَيْهَا أَوْ يَرْفَعُ عَلَيْهَا مَتَاعَهُ صَدَقَةٌ، وَالكَلِمَةُ الطَّيِّبَةُ صَدَقَةٌ، وَكُلُّ خُطْوَةٍ يَخْطُوهَا إِلَى الصَّلاَةِ صَدَقَةٌ، وَيُمِيطُ الأَذَى عَنِ الطَّرِيقِ صَدَقَةٌ». [صحيح] - [متفق عليه]

(257) - ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: «የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል: "ሁሉም የሰው ልጅ መገጣጠሚያ አጥንቶች ምፅዋት አለባቸው። ፀሀይ በምትወጣበት ቀናት ሁሉ፤ በሁለት ሰዎች መካከል ማስታረቅ ምፅዋት ነው። ሰውዬውን መጓጓዣው ላይ እንዲወጣ ማገዝ ፣ እርሷ ላይ ማሸከም ወይም እቃውን እርሷ ላይ መጫን ምፅዋት ነው። መልካም ንግግር ምፅዋት ነው። ወደ ሶላት የሚራመዳት ሁሉም እርምጃ ምፅዋት ነው። ከመንገድ ላይ ቆሻሻን ማስወገድ ምፅዋት ነው።"» [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ሁሉም ቀን በሁሉም ለአቅመ አዳም በደረሰ ሙስሊም ላይ ሁሉ በመገጣጠሚያ አጥንቶቹ ቁጥር ያህል ለሰጠው ጤንነት ለማመስገንና አጥንቶቹን መጨበጥና መዘርጋት በሚችል መልኩ ስለገጣጠመው ለአላህ ብሎ መመፅወት እንደሚገባው ገለፁ። ይህቺም ምፅዋት በመልካም ተግባራት ባጠቃላይ እንደሚፈፀምና ገንዘብ በመስጠት ላይ ብቻ እንዳልታጠረ ገለፁ። ከነርሱም መካከል: በተጣሉ ሁለት ሰዎች መካከል ማስታረቅና መፍረድ ምፅዋት ነው። መጓጓዣው ላይ ለመውጣት ለተሳነው ሰውዬ በማሰቀልህ ወይም እቃውን በመጫን ማገዝህ ምፅዋት ነው። ዚክር፣ ዱዓ ማድረግ፣ ሰላምታ ማቅረብና ሌሎችም መልካም

ንግግሮች ምፅዋት ናቸው። ወደ ሶላት የምትራመዳት ሁሉም እርምጃ ምፅዋት ናት። መንገድ ላይ የሚያውክን ነገር ማስወገድም ምፅዋት ነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. የሰው ልጅ አጥንቶች ተገጣጥመው መሰራታቸውና የነርሱም ደህና መሆን ከአላህ ትላልቅ ፀጋዎች መካከል እንደሆነ እንረዳለን። ለያንዳንዱ ፀጋ የሚያቀርበው ምስጋና እንዲሞላም ለሁሉም አጥንት መመፅወት አስፈላጊ ነው።
2. ይህ የአላህ ፀጋ እንዲዘወትርም ምስጋናን በየቀኑ በማደስ ላይ መነሳሳቱን እንረዳለን።
3. በየቀኑ ግዴታ ያልሆኑ ስራዎችን በመስራትና ምፅዋት በማድረግ ላይ በመዘውተር መነሳሳቱን እንረዳለን።
4. በሰዎች መካከል ማስታረቅ ያለውን ትሩፋት እንረዳለን።
5. ወንድምን በማገዝ ላይ መነሳሳቱን እንረዳለን። ይህም ወንድምን ማገዝ ምፅዋት ስለሆነ ነው።
6. የጀመዓ ሶላት በመገኘት ላይ፣ ወደርሱ በመሄድ ላይና መስጂድን በዚህ በማሳመር ላይ መነሳሳቱን እንረዳለን።
7. ሙስሊሞች የሚያውካቸውንና የሚጎዳቸውን ነገር በማራቅ የሙስሊሞችን መንገድ ማስከበር ግዴታ እንደሆነ እንረዳለን።

(4568)

(٢٥٨) - عَنْ أَبِي بَرْزَةَ الأَسْلَمِيِّ رضي الله عنه قَالَ: قَالَ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ: «لَا تَزُولُ قَدَمَا عَبْدٍ يَوْمَ القِيَامَةِ حَتَّى يُسْأَلَ عَنْ عُمُرِهِ فِيمَا أَفْنَاهُ، وَعَنْ عِلْمِهِ فِيمَ فَعَلَ، وَعَنْ مَالِهِ مِنْ أَيْنَ اكْتَسَبَهُ وَفِيمَ أَنْفَقَهُ، وَعَنْ جِسْمِهِ فِيمَ أَبْلَاهُ». [صحيح] - [رواه الترمذي]

(258) - ከአቡ በርዛህ አልአስለሚይ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ ብለዋል: "የአላህ መልዕክተኛ ሰለላሁ ዐለይሂ ወስለም እንዲህ ብለዋል፦ "የትንሳኤ ቀን የትኛውም ባሪያ እድሜውን በምን እንዳጠፋው፣ በእውቀቱ ምን እንደሰራበት፣ ገንዘቡን ከየት እንዳገኘውና ምን ላይ እንዳዋለው፣ በአካሉ ምን እንዳደረገበት ሳይጠየቅ እግሮቹ አይንቀሳቀሱም።'" [ሶሒሕ ነው።] - [ቲርሚዚ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) የትንሳኤ ቀን ከሒሳብ መተሳሰቢያ ስፍራ አንድም ሰው ስለተወሰኑ ጉዳዮች ሳይጠየቅ ወደ ጀነት ወይም ወደ እሳት እንደማያልፍ ተናገሩ።

የመጀመሪያው: ህይወቱን በምን እንዳጠፋውና እንዳሳለፈው?

ሁለተኛው: ዕውቀቱን ለአላህ ብሎ ነው የፈለገው? በእውቀቱ ሰርቶበታልን? ማወቅ ለሚገባውስ አስተላልፎታልን?

ሶስተኛው: ገንዘቡን ከየት ነው ያገኘው? ከሐላል ነው ወይስ ከሐራም? ለምንስ አዋለው? አላህን በሚያስደስት ነገር ላይ አዋለው? ወይስ በሚያስቆጣው ነገር ላይ?

አራተኛው: ስለ አካሉ፣ ሀይሉ፣ ጤንነቱ፣ ወጣትነቱ ነው። ምን ላይ ተጠቅሞ እንዳሳለፈው?

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ህይወትን ማሳለፍ ያለብን አላህን በሚያስደስት ነገር ላይ እንዲሆን መነሳሳቱን እንረዳለን።

2. አላህ በባሮቹ ላይ የዋለው ፀጋ ብዙ ናቸው። ስለነበረበት ፀጋም ይጠይቀዋል። ስለዚህ የአላህን ፀጋዎች እርሱን በሚያስደስት ነገር ላይ ማዋል ይገባዋል።

(4950)

(٢٥٩) - عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ قَالَ: قَالَ النَّبِيُّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ: «السَّاعِي عَلَى الأَرْمَلَةِ وَالمِسْكِينِ، كَالْمُجَاهِدِ فِي سَبِيلِ اللهِ أَوِ القَائِمِ اللَّيْلَ الصَّائِمِ النَّهَارَ». [صحيح] - [متفق عليه]

(259) - ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: "ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል: ‹ባሏ ለሞተባትና ለሚስኪን የሚለፋ ሰው ልክ በአላህ መንገድ እንደሚታገል ሰው አምሳያ ወይም ልክ ሌሊት እየሰገደ ቀኑን እንደሚፆም አምሳያ ነው›" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ባሏ ለሞተባትና የሚያስፈልጋትን ጉዳይ የሚያሟላላት አንድም ሰው ለሌላት ሴት እና ተረጂ ለሆነ ሚስኪን ጥቅማቸውን በሟሟላት የቆመ እንዲሁም አላህ ዘንድ ምንዳን በማሰብ ለነርሱ ወጪ የሚያደርግ ሰው በምንዳ ደረጃ ልክ በአላህ መንገድ እንደሚታገል ወይም ለተሀጁድ ሶላት ሳይደክም እየቆመ ምንም ሳያፈጥር እንደሚፆም ሰው አምሳያ መሆኑን ነቢዩ (የአሏህ ሶለዋትና ሰላም በሳቸው ላይ ይስፈንና) ተናገሩ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. በመተጋገዝ፣ ሀላፊነት በመወጣትና የደካሞችን አስፈላጊ ጉዳዮች በማሟላት ላይ መነሳሳቱን እንረዳለን።
2. አምልኮ ሲባል ሁሉንም መልካም ስራ ይሰበስባል። ከአምልኮዎች መካከልም ባሏ ለሞተባት ሴትና ለሚስኪን ጥቅም መልፋት አንዱ ነው።

3. ኢብኑ ሁበይራ እንዲህ ብሏል: "ከዚህ ሐዲሥ የተፈለገው ከፍ ያለው አላህ የታጋይ (የሙጃሂድ)ና እየፆመ ሌሊት የሚቆምን ሰው ምንዳ በአንድ ጊዜ ይሰበስብለታል ማለት ነው። ይህም ባሏ ለሞተባት ሴት የባሏን ቦታ ተክቶ ስለተወጣ ... ራሱን ችሎ መቆም ለተሳነው ሚስኪንም የተረፈውን ቀለብ ወጪ አድርጎ በአቅሙ ስለመፀወተ የሰጠው ጥቅም ፆም፣ የሌሊት ሶላትና ጂሀድን የሚመጥን ሆነ።"

(3135)

(٢٦٠) - عن أبي هريرة رضي الله عنه عن رسول الله صلى الله عليه وسلم قال: «مَنْ كَانَ يُؤْمِنُ بِاللهِ وَالْيَوْمِ الْآخِرِ فَلْيَقُلْ خَيْرًا أَوْ لِيَصْمُتْ، وَمَنْ كَانَ يُؤْمِنُ بِاللهِ وَالْيَوْمِ الْآخِرِ فَلْيُكْرِمْ جَارَهُ، وَمَنْ كَانَ يُؤْمِنُ بِاللهِ وَالْيَوْمِ الْآخِرِ فَلْيُكْرِمْ ضَيْفَهُ». [صحيح] - [متفق عليه]

(260) - ከአቡ ሁረይራ -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው የአላህ መልክተኛ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንዲህ ብለዋል: "በአላህና በመጨረሻው ቀን ያመነ መልካምን ይናገር ወይም ዝም ይበል! በአላህና በመጨረሻው ቀን ያመነ ጎረቤቱን ያክብር! በአላህና በመጨረሻው ቀን ያመነ እንግዳውን ያክብር!" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

**ትንታኔ:**

ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም በአላህ እና መመለሻውም በስራው የሚመነዳበትም በሆነው መጨረሻው ቀን ያመነ ባሪያ ኢማኑ እነዚህን ጉዳዮችን በመፈፀም ላይ እንደሚያነሳሳው ገለፁ:

የመጀመሪያው: መልካም መናገር ነው። በዚህ ውስጥ ሱብሓነላህ ማለት፣ ላኢላሃኢለላህ ማለት፣ በመልካም ማዘዝ፣ ከመጥፎ መከልከል፣ በተጣሉ ሰዎች መካከል ማስማማት የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ። ይህንን ካልፈፀመ ዝምታን ያዘውትር፣ ክፋቱን ይቆጥብ፣ ምላሱን ይጠብቅ።

ሁለተኛ: ጉረቤትን ማክበር፡ ይህም እነሱን ባለማወክና ለነርሱ በጎ በማድረግ ነው።

ሶስተኛ: ለመዘየር የመጣን እንግዳ መልካም በማናገር፣ ምግብ በማብላትና ይህን በመሳሰሉት ማክበር ነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. በአላህና በመጨረሻው ቀን ማመን ለሁሉም መልካም ነገር መሰረት ነው። መልካም ተግባራትን በመፈፀም ላይም ያነሳሳል።
2. ከምላስ ወለምታ መከልከሉን ፤
3. የኢስላም ሃይማኖት የአንድነትና የቸርነት ሃይማኖት መሆኑን ፤
4. እነዚህ ጉዳዮች ከኢማን ክፍሎችና ምስጉን ከሆኑ ስነስርአቶች መሆናቸውን ፤
5. ንግግር ማብዛት ወደሚጠላ ወይም ወደተከለከለ ነገር ይጎትታል። ሰላም የሚገኘው ከመልካም ውጪ ባለመናገር እንደሆነ እንረዳለን።

(5437)

(٢٦١) - عن أبي ذر رضي الله عنه قال: قال لي النبي صلى الله عليه وسلم: «لَا تَحْقِرَنَّ مِنَ الْمَعْرُوفِ شَيْئًا، وَلَوْ أَنْ تَلْقَى أَخَاكَ بِوَجْهٍ طَلْقٍ». [صحيح] - [رواه مسلم]

(261) - ከአቡ ዘር -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንዲህ አሉኝ: "ከመልካም ነገር አንዳችም አታሳንስ ወንድምህን ፈታ ባለ ፊት ማግኘትንም ቢሆን እንኳ (እንዳታሳንስ)።" [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ትንሽም ብትሆን እንኳ መልካምን ከመፈፀም እንዳናሳንስ አነሳሱን። ከነዚህ መካከልም ከሙስሊም ጋር በሚገናኝ ወቅት በፈገግታ ፊትን መፍታት ይጠቀሳል። አንድ ሙስሊም ይህን በመፈፀሙ ምክንያት ሙስሊም ወንድሙን ማዝናናትና በውስጡ ደስታን መጨመር ስለሚያመጣ በዚህ ላይ ሊጓጓ ይገባል።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. በአማኞች መካከል መዋደድ፣ ሲገናኙ ፈገግ ማለትና ማበሰር ያለውን ትሩፋት ፤
2. ሸሪዓ ለሙስሊሞች በሚጠቅምና ህብረታቸውን አንድ በሚያደርግ ነገር ሁሉ መምጣቱ የዚህ ሸሪዓን ምሉዕነትና ጠቅላይነት ፤
3. ትንሽም ብትሆን እንኳ መልካም በመስራት ላይ መበረታታቱን ፤
4. በሙስሊሞች መካከል አንድነትን ስለሚያረጋግጥ በሙስሊሞች ላይ ደስታን መጨመር ተወዳጅ መሆኑን እንረዳለን።

(5348)

(٢٦٢) - عَنْ عَبْدِ اللهِ بنِ مَسعُودٍ رضي الله عنه قَالَ: قَالَ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ: «عَلَيْكُمْ بِالصِّدْقِ، فَإِنَّ الصِّدْقَ يَهْدِي إِلَى الْبِرِّ، وَإِنَّ الْبِرَّ يَهْدِي إِلَى الْجَنَّةِ، وَمَا يَزَالُ الرَّجُلُ يَصْدُقُ وَيَتَحَرَّى الصِّدْقَ حَتَّى يُكْتَبَ عِنْدَ اللهِ صِدِّيقًا، وَإِيَّاكُمْ وَالْكَذِبَ، فَإِنَّ الْكَذِبَ يَهْدِي إِلَى الْفُجُورِ، وَإِنَّ الْفُجُورَ يَهْدِي إِلَى النَّارِ، وَمَا يَزَالُ الرَّجُلُ يَكْذِبُ وَيَتَحَرَّى الْكَذِبَ حَتَّى يُكْتَبَ عِنْدَ اللهِ كَذَّابًا». [صحيح] - [متفق عليه]

(262) - ከዐብደላህ ቢን መስዑድ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: «የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል: "በእውነተኝነት ላይ አደራችሁን! እውነተኝነት ወደ መልካም ይመራል። መልካም ነገር ደግሞ ወደ ጀነት ይመራልና። ሰውዬው አላህ ዘንድ እውነተኛ ተብሎ እስኪፃፍ ድረስ እውነት ከመናገርና እውነትን ከመምረጥ አይወገድም። አደራችሁን ውሸትን ተጠንቀቁ! ውሸት ወደ ጥመት ይመራል። ጥመት ደግሞ ወደ እሳት ይመራልና። ሰውዬው አላህ ዘንድ ውሸታም ተብሎ እስኪፃፍ ድረስ ከመዋሸትና ለውሸት ከመጣር አይወገድ።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እውነተኝነትን አዘዙ። እውነተኝነትን አጥብቆ መያዝ ለዘውታሪ መልካም ስራና በመልካም ስራ ላይም እንዲዘወትር የሚያደርገው በመሆኑ ሰውዬውን ወደ ጀነት እንደሚያደርሰው ተናገሩ። ሰውዬው እውነት መናገርን በድብቅም ይሁን በይፋ ከመደጋገም እስካልተወገደ እጅግ እውነተኛ የሚል ስያሜ እስኪገባው ይደርሳል። ይህም በእውነተኝነት ላይ ጫፍ የደረሰ ሰው ማለት ነው። ቀጥለውም ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ከውሸትና ከቅጥፈት ንግግር አስጠነቀቁ። ይህም ከቀጥተኛው መንገድ ወደ መጣመም፣ ለክፋትና ለወንጀል ስለሚያነሳሳ ነው። ከዚያም ወደ እሳት ያደርሰዋል። ሰውዬውም ውሸትን ከማብዛት እስካልተወገደ ድረስ አላህ ዘንድ ውሸታም ተብሎ ይፃፋል።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. እውነተኝነት በጥረትና በትግል የሚገኝ የተከበረ ባህሪ ነው። ሰውዬው እውነት የርሱ ባህሪና ተፈጥሮው እስኪሆን ድረስ እውነት ከመናገርና ለእውነትም ከመጣር አይወገድም።
2. ውሸት ሰውዬው ባህሪውና መገለጫው እስኪሆንና ቀጥሎም አላህ ዘንድ ከውሸታሞች እስኪፃፍ ድረስ በመላመድ ብዛትና በንግግሩና በተግባሩ የሚያመጣው የተወገዘ ስነምግባር ነው።
3. እውነት የሚለው ቃል በምላስ ለሚነገር እውነት ስያሜው ይሰጣል፤ ይህም የውሸት ተቃራኒ ነው። በኒያ ለሚኖር እውነትም ስያሜው ይሰጣል፤ ይህም ስራን ለአላህ ማጥራት (ኢኽላስ) ተብሎ ይጠራል። በነየተው መልካም ነገር ላይ ላለው እውነተኛ ቁርጠኝነትም ስያሜው ይሰጣል። በተግባር ለሚኖር እውነተኝነትም የሚሰጥ ሲሆን ለዚህም ቢያንስ ውስጡና ውጪው እኩል መሆን አለባቸው። ስያሜው በተለያዩ ሁኔታዎች ላይ እውነተኛነትን ለመላበስም ይሰጣል። ለምሳሌ አላህን በመፍራት፣ አላህን በመከጀልና

በሌሎችም ሁኔታዎች እውነተኛ መሆንን ሁሉ ያጠቃልላል። በዚህ መልኩ እውነትን የተላበሰ እጅግ እውነተኛ (ሲዲቅ) ይባላል። በተወሰኑት ብቻ እውነተኛ ከሆነ ግን እውነተኛ ብቻ ነው የሚባለው።

(5504)

(٢٦٣) - عن جرير بن عبد الله رضي الله عنه قال: قال رسول الله صلى الله عليه وسلم: «مَنْ لَا يَرْحَمِ النَّاسَ لَا يَرْحَمْهُ اللهُ عَزَّ وَجَلَّ». [صحيح] - [متفق عليه]

(263) - ከጀሪር ቢን ዐብደላህ -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው እንዲህ አለ: የአላህ መልክተኛ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንዲህ አሉ: "ለሰዎች የማይራራን አሸናፊና የበላይ የሆነው አላህ አይራራለትም።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

### ትንታኔ:

ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ለሰዎች የማይራራ ሰውን የላቀውና የተከበረው አላህም እንደማይራራለት ገለፁ። ሰው ለፍጡር ማዘኑ የአላህን ርህራሄ ማግኛ ከሆኑ ትላልቅ ሰበቦች መካከል ነው።

### ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ርህራሄ ለሌሎቹም ፍጡራን ያስፈልጋል። ነገር ግን ሀዲሱ ላይ ሰውን ብቻ የጠቀሰው አፅንኦት ለመስጠት ነው።
2. አላህ ለአዛኝ ባሮቹ የሚራራ አዛኝ ጌታ ነው። ምንዳ በስራ አይነት ነው።
3. ለሰው ማዘን ሲባል ለነሱ መልካም ማድረግን፣ ጉዳትን ከነርሱ ላይ መከላከልንና ባማረ መልኩ ከነርሱ ጋር መኗኗርን ይጠቀልላል።

(5439)

(٢٦٤) - عن عبد الله بن عمرو رضي الله عنهما أن النبي صلى الله عليه وسلم قال: «الرَّاحِمُونَ يَرْحَمُهُمُ الرَّحمنُ، ارحَمُوا أهلَ الأرضِ يَرْحَمْكُم مَن في السّماء».
[صحيح] - [رواه أبو داود والترمذي وأحمد]

(264) - ከዐብደላህ ቢን ዐምር (ረዲየላሁ ዐንሁማ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ አሉ: "ለአዛኞች አዛኙ ጌታ ያዝንላቸዋል። ለምድር ነዋሪዎች እዘኑላቸው በሰማይ ያለው (አላህ) ያዝንላቹሀል።" [ሶሒሕ ነው። ] - [አቡዳውድ፣ ቲርሚዚና አሕመድ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እነዚያ ለሌሎች የሚያዝኑ አዛኙ ጌታ ሁሉን ነገር በሰፋው እዝነቱ እንደሚያዝንላቸው ገለፁ። ይህም ከሰሩት ጋር የገጠመ ምንዳ ነው።

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ቀጥለው በምድር ላይ ለሚኖር ለሰውም፣ ለእንስሳም፣ ለበራሪም ሆነ ለሌላ ማንኛውም አይነት ፍጡር ባጠቃላይ ማዘንን አዘዙ። የዚህ ምንዳም ከሰማያቱ በላይ ያለው አላህ ያዝንላቹሀል።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. የእስልምና ሀይማኖት የእዝነት ሀይማኖት ነው። የኢስላም ሁለመናው አላህን በመታዘዝና ለፍጡራን መልካም በማድረግ ላይ የቆመ ነው።
2. የላቀው አላህ በእዝነት ባህሪ የሚገለፅ ነው። ጥራት የተገባው አላህ አዛኝ ሩህሩህ ነው። ወደ ባሮቹ እዝነቱን የሚያደርስ ጌታ ነው።
3. ምንዳ የሚመነዳው በስራው አይነት ነውና ለአዛኞች አላህ ያዝንላቸዋል።

(8289)

(٢٦٥) - عَنْ عَبْدِ اللهِ بْنِ عَمْرٍو رَضِيَ اللهُ عَنْهُمَا عَنِ النَّبِيِّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ قَالَ: «المُسْلِمُ مَنْ سَلِمَ المُسْلِمُونَ مِنْ لِسَانِهِ وَيَدِهِ، وَالمُهَاجِرُ مَنْ هَجَرَ مَا نَهَى اللهُ عَنْهُ». [صحيح] - [متفق عليه]

(265) - ከዐብደላህ ቢን ዐምር (ረዲየሏሁ ዐንሁማ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው ፡ ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል: "ሙስሊም ማለት ሙስሊሞች ከምላሱና እጁ (ክፋት) ሰላም የሆኑበት ነው፤ ሙሃጂር (ስደተኛ) ማለት አላህ የከለከለውን የተወ ነው።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እስልምናው የተሟላ ሙስሊም የሚባለው ሙስሊሞች ከምላሱ ሰላም የሆኑበት ሰው እንደሆነ ተናገሩ። ስለዚህም አይሰድባቸውምም፤ አይረግማቸውምም፤ አያማቸውምም፤ በሙስሊሞች መካከል በምላስ ከሚመጡ ማናቸውም የክፋት አይነት በየትኛውም ሊጎዳቸው አይሮጥም። ከእጁም ሙስሊሞች ሰላም የሆኑበት ነው። ስለዚህም በነርሱ ላይ ወሰን አያልፍም፤ ያለ አግባብ ገንዘባቸውን አይወስድምም በሌሎች መሰል ሁኔታዎችም ሙስሊሞችን አይጎዳም። ሙሃጂር ማለት: አላህ ክልክል ያደረገውን የተወ ነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. የኢስላም ምሉዕነት ሌሎች ላይ ቁሳዊም ሆነ ሞራላዊ ጉዳትን ባለማድረስ ካልሆነ በቀር አይረጋገጥም።
2. ምላስና እጅን ብቻ በማውሳት መገደቡ በነርሱ ምክንያት የሚደርስ ጉዳትና ጥፋቶች ስለሚበዙ ነው። ምክንያቱም አብዛኞቹ ክፋቶች የሚመነጩት ከሁለቱ ነውና።
3. ወንጀልን በመተው ላይና አላህ ያዘዘውን ነገር አጥብቆ በመያዝ ላይ መነሳሳቱን እንረዳለን።

4. በላጩ ሙስሊም የሚባለው የአላህን ሐቆችና የሙስሊሞችን ሐቅ የተወጣ ነው።
5. ወሰን አላፊነት በንግግር ወይም በተግባር ሊሆን ይችላል።
6. የተሟላ ሂጅራ የሚባለው አላህ ክልክል ያደረገውን በመተው ነው።

(10101)

(٢٦٦) - عن أبي هريرة رضي الله عنه قال: سمعت رسول الله صلى الله عليه وسلم يقول: «حَقُّ الْمُسْلِمِ عَلَى الْمُسْلِمِ خَمْسٌ: رَدُّ السَّلَامِ، وَعِيَادَةُ الْمَرِيضِ، وَاتِّبَاعُ الْجَنَائِزِ، وَإِجَابَةُ الدَّعْوَةِ، وَتَشْمِيتُ الْعَاطِسِ». [صحيح] - [متفق عليه]

(266) - አቢ ሁረይራ ረዲየሏሁ ዐንሁ እንዲህ ብለዋል፡ "የአሏህ መልዕክተኛ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ ሲሉ ሰምቻለሁ፡ "አንድ ሙስሊም በሌላኛው ሙስሊም ላይ አምስት መብቶች አሉት፤ ሰላምታ መመለስ፣ ህመምተኛ መጠየቅ፣ ጀናዛን መሸኘት፣ ጥሪውን መቀበልና ባስነጠሰው ጊዜ 'የርሐሙከሏህ' ማለት ናቸው።"" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን አንድ ሙስሊም በሌላኛው ሙስሊም ወንድሙ ላይ ያለውን ጥቂት መብቶች ገለፁ። ከነዚህ መብቶች መካከል የመጀመሪያው ሰላምታ ለሰጠህ ሰላምታን መመለስ ነው።

ሁለተኛው መብት፡ ህመምተኛን መጠየቅና መዘየር ነው።

ሶስተኛው መብት፡ ጀናዛን ከቤቱ ወደ ሚሰገድበት ከዚያም ወደ መቃብሩ ተወስዶ እስኪቀበር ድረስ መሸኘት ነው።

አራተኛው መብት፡ ለሰርግም ይሁን ለሌላ ግብዣ ሲጠራ ጥሪውን አክብሮ ምላሽ መስጠት ነው።

አምስተኛ መብት፡ ሲያስነጥስ "ተሽሚት" ሊያደርግ ሲሆን ይሀውም አስነጥሶ "አልሐምዱሊላህ" (ትርጉሙም፡ ምስጋና ለአላህ ይገባው) ካለ

"የርሐሙከሏህ" (ትርጉሙም፡ አሏህ ይዘንልህ) ይበለው፤ ከዚያም ያስነጠሰውም መልሶ "የህዲኩሙሏሁ ወዩስሊሕ ባለኩም" (ትርጉሙም፡ አሏህ ይምራህ ጉዳይህንም ያስተካክልልህ) ይላል።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. እስልምና በሙስሊሞች መካከል ያሉ መብቶችን በማበርታትና በመካከላቸው ያለን ወንድማማችነትና መዋደድን በማጠናከር በኩል ያለውን ልቅና ያስረዳናል።

(3706)

(٢٦٧) - عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ رضي الله عنه قَالَ: قَالَ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ: «لَا تَدْخُلُونَ الْجَنَّةَ حَتَّى تُؤْمِنُوا، وَلَا تُؤْمِنُوا حَتَّى تَحَابُّوا، أَوَلَا أَدُلُّكُمْ عَلَى شَيْءٍ إِذَا فَعَلْتُمُوهُ تَحَابَبْتُمْ؟ أَفْشُوا السَّلَامَ بَيْنَكُمْ». [صحيح] - [رواه مسلم]

(267) - ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: "የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል፦ 'እስክታምኑ ድረስ ጀነት አትገቡም። እስክትዋደዱ ድረስም አታምኑም። የፈፀማችሁት ጊዜ የምትዋደዱበትን አንዳች ነገር ልጠቁማችሁን? በመካከላችሁ ሰላምታን አሰራጩ።'" [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ከአማኞች በስተቀር ማንም ጀነት እንደማይገባ፤ ከፊሉ ከፊሉን እስኪወድ ድረስም ኢማን እንደማይሞላና የሙስሊሙ ማህበረሰብ ሁኔታም እነደማይስተካከል ገለፁ። ከዚያም ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) በርሱ አማካኝነት ውዴታ የሚዳረስበትን በላጭ ነገር ጠቆሙ። እርሱም:

በሙስሊሞች መካከል አላህ ለባሮቹ ሰላምታ መለዋወጫ ያደረገውን ሰላምታን ማሰራጨት ነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. በእምነት ካልሆነ በቀር ጀነት መግባት እንደሌለ እንረዳለን።
2. የትኛውም ሙስሊም ለነፍሱ የሚወደውን ለወንድሙ መውደዱ ከኢማን መሟላት መገለጫዎች መካከል አንዱ ነው።
3. ለሙስሊሞች ሰላምታን ማብዛትና መለዋወጥ በሰዎች መካከል ውዴታንና ደህንነትን ስለሚያሰራጭ ይወደዳል።
4. ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) "በመካከላችሁ" ስላሉ "አሰላሙ ዓለይኩም" ከሙስሊም ጋር ካልሆነ በቀር አይባልም።
5. ሰላምታን መለዋወጥ መቆራረጥን፣ መኮራረፍንና መጣላትን ያስወግዳል።
6. በሙስሊሞች መካከል የመዋደድን አንገብጋቢነት እንረዳለን። እርሱም ኢማንን ከሚሞሉ ነገሮች መካከል አንዱ ነው።
7. በሌላ ሐዲሥ የተሟላው የሰላምታ ይዘት "አስሰላሙ ዐለይኩም ወረሕመቱሏሂ ወበረካቱህ" እንደሆነ መጥቷል። "አስሰላሙ ዐለይኩም" የሚለውም በቂ ነው።

(3361)

(٢٦٨) - عَنْ عَبْدِ اللهِ بْنِ عَمْرٍو رَضِيَ اللهُ عَنْهُمَا: أَنَّ رَجُلًا سَأَلَ النَّبِيَّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ: أَيُّ الإِسْلَامِ خَيْرٌ؟ قَالَ: «تُطْعِمُ الطَّعَامَ، وَتَقْرَأُ السَّلَامَ عَلَى مَنْ عَرَفْتَ وَمَنْ لَمْ تَعْرِفْ».

[صحيح] - [متفق عليه]

(268) - ከዐብደላህ ቢን ዐምር (ረዲየሏሁ ዐንሁማ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው:- "አንድ ሰውዬ ነቢዩን (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) 'ማንኛው የኢስላም ክፍል ነው ምርጡ?' ብሎ ጠየቀ። እርሳቸውም 'ምግብ መመገብህ፣ ሰላምታን ባወቅከውም ባላወቅከውም ሰው ላይ ማቅረብህ ነው።' ብለው መለሱለት።"

[ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ማንኛው የኢስላም ክፍል ነው በላጩ? ተብለው ተጠየቁ። እርሳቸውም ሁለት ነገሮችን ጠቀሱ።

የመጀመሪያው: ድሃዎችን ማብላትን ማብዛት ነው። እዚህ ውስጥም ሶደቃ፣ ስጦታ፣ ግብዣ፣ የሰርግ ድግስ ይገባሉ። የማብላቱ በላጭነትም በረሃብና ኑሮ በተወደደበት ወቅት የጠነከረ ይሆናል።

ሁለተኛው: አወቅከውም አላወቅከውም በሁሉም ሙስሊም ላይ ሰላምታን ማቅረብ ነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ሶሐቦች በዱንያም ሆነ በመጨረሻው ዓለም የሚጠቅመምን ጉዳይ ለማወቅ ያላቸውን ጉጉት እንረዳለን።
2. ሰላምታ ማቅረብና ምግብ ማብላት ሰዎች በሁሉም ወቅት የሚፈልጉት ስለሆነና በላጭ ስራ ከመሆኑ አንፃርበ ኢስላም ውስጥ ትልቅ ደረጃ ከሚሰጣቸው ተግባራት መካከል እንደሆኑ እንረዳለን።
3. በነዚህ ሁለት ጉዳዮች ንግግራዊም ተግባራዊም በጎነት ይሰበሰባሉ። ይህም የተሟላው በጎነት ነው።

4. እነዚህ ጉዳዮች ሙስሊሞች በመካከላቸው ሊኖራቸው ከሚገባው መስተጋብር ጋር የተያያዘ ሲሆን ሌላ ቦታ ደግሞ አንድ ባሪያ ከጌታው ጋር ሊኖረው ስለሚገባ መስተጋብር የሚገልፁ ጉዳዮች አሉ።
5. በሰላምታ መጀመር በሙስሊሞች መካከል ብቻ የተገደበ ሲሆን ካፊር በሰላምታ አይጀመርም።

(5808)

(٢٦٩) - عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ رضي الله عنه أَنَّ رَسُولَ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ قَالَ: «أَلَا أَدُلُّكُمْ عَلَى مَا يَمْحُو اللهُ بِهِ الْخَطَايَا، وَيَرْفَعُ بِهِ الدَّرَجَاتِ؟» قَالُوا بَلَى يَا رَسُولَ اللهِ قَالَ: «إِسْبَاغُ الْوُضُوءِ عَلَى الْمَكَارِهِ، وَكَثْرَةُ الْخُطَا إِلَى الْمَسَاجِدِ، وَانْتِظَارُ الصَّلَاةِ بَعْدَ الصَّلَاةِ، فَذَلِكُمُ الرِّبَاطُ».
[صحيح] - [رواه مسلم]

(269) - ከአቡ ሁረይራ (ረዲየላሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል: "አላህ ወንጀሎችን የሚሰርዝበትን፣ ደረጃዎችን ከፍ የሚያደርግበትን ነገር አልጠቁማችሁምን?" ሶሐቦችም "እንዴታ የአላህ መልክተኛ" አሉ። እርሳቸውም "በአስቸጋሪ ወቅት ዉዱእን አዳርሶ ማድረግ፣ ወደ መስጂድ እርምጃ ማብዛት፣ አንድ ሰላት ካለቀ በኋላ ሌላኛው ሰላት መጠበቅ፤ ይህው ነው "ሪባጥ" (ዘብ መጠበቅ) ናቸው።" [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ለወንጀሎቻቸው መማር፣ ከጠባቂ መላዕክት መዝገብ ወንጀላቸውን ለማሰረዝ፣ በጀነት ውስጥም ደረጃዎችን ከፍ ለማድረግ ምክንያት የሚሆኑ ስራዎችን እንዲጠቁሟቸው ይፈልጉ እንደሆነ ባልደረቦቻቸውን ጠየቋቸው።

ሶሐቦችም: "አዎን እንፈልጋለን" አሉ። እሳቸውም እንዲህ አሉ:

የመጀመሪያው: እንደ ቅዝቃዜ፣ የውሃ ማነስ፣ የሰውነት ህመምና አቃጣይ ውሃን የመሰሉ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙም ዉዱእን መሙላትና ማዳረስ ነው።

ሁለተኛው: እርምጃን ከሩቅ አካባቢ ወደ መስጂድ ማብዛትና ደጋግሞ መመላለስ ነው።

ሶስተኛ: የሶላትን ወቅት መጠበቅ፣ ልብን በሶላት ማንጠልጠል፣ ለሶላት መዘጋጀት፣ ጀመዓን ለመጠበቅ መስጂድ ውስጥ ለሶላት መቀመጥ፣ ከሰገደም በኋላ ለሌላ ሶላት መስገጃው ላይ ቁጭ ብሎ መጠበቅ ነው።

ቀጥለው ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እነዚህ ጉዳዮች ትክክለኛው ዘብ መጠበቅ እንደሆኑ ገለፁ። ምክንያቱም የሰይጣንን መንገዶች በነፍስ ላይ ስለምትዘጋ፣ ስሜትን ስለምታሸንፍ፣ ነፍስ ለወስዋስ ተገዥ እንዳትሆን ስለምትከለክል ነው። ነፍስን በማሸነፍ የአላህ ጭፍራ የሰይጣንን ሰራዊት ያሸንፉበታል። ትልቁ ጂሀድም ይህ ነው። ስለዚህ ይህ ድንበር ኬላ ላይ ጠላትን በመጠበቅ ደረጃ እንደሆነ አድርገው ገለፁት።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. መስጂድ ውስጥ የህብረት ሶላትን የመጠባበቅ አንገብጋቢነቱን፤ ለሶላት ትኩረት መስጠትና ከሶላት በሌላ ነገር መጠመድ እንደሌለብንም እንረዳለን።
2. ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ስራው የሚያስገኘውን ትልቅ ምንዳ በጥያቄያዊ መንገድ አስቀድመው ባልደረቦቻቸውን በማጓጓታቸው የትምህርት አቀራረባቸውን ማማር እንረዳለን። ይህም አንዱ የማስተማሪያ መንገድ ነው።
3. አንድን ጉዳይ በጥያቄና መልስ መንገድ ማቅረብ ብይኑን መጀመሪያ በመደበቅና ቀጥሎ በማብራራት ንግግሩ ነፍስ ውስጥ እንዲቀር የማድረግ ጥቅም አለው።
4. ነወዊ አላህ ይዘንላቸውና «ይህ ነው "ሪባጥ" (ዘብ መጠበቅ)» ማለት ተፈላጊው ዘብ መጠበቅ ይህ ነው ማለት ነው። ሪባጥ የሚለው ቃል መሰረት

በአንድ ነገር ላይ መታጠር ማለት ሲሆን በነዚህ ስራዎች አላህን በመገዛት ላይ ነፍሱን ስለሚያጥር ነው። "ጂሃድ ማለት ነፍስን መታገል ነው።" እንደሚባለው በላጩ ሪባጥ ይህ ነውም ተብሏል። በሌላ አባባል ደሞ ቀላሉና የሚመቸው ሪባጥ ነው ማለት ተፈልጎበት ሊሆንም ያስመቻል። ማለትም ከሪባጥ አይነቶች አንዱ ነው እንደማለት ነው።

5. (አል) የምትለዋ ገላጭ ገብታ "አር-ሪባጥ" የምትለዋ ቃል መደጋገሟ የነዚህ ስራዎችን ትልቅነት ያስረዳናል።

(3574)

(٢٧٠) - عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ رضي الله عنه قَالَ: قَالَ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ: «الْمُؤْمِنُ الْقَوِيُّ، خَيْرٌ وَأَحَبُّ إِلَى اللهِ مِنَ الْمُؤْمِنِ الضَّعِيفِ، وَفِي كُلٍّ خَيْرٌ، احْرِصْ عَلَى مَا يَنْفَعُكَ، وَاسْتَعِنْ بِاللهِ وَلَا تَعْجَزْ، وَإِنْ أَصَابَكَ شَيْءٌ، فَلَا تَقُلْ لَوْ أَنِّي فَعَلْتُ كَانَ كَذَا وَكَذَا، وَلَـكِنْ قُلْ قَدَرُ اللهِ وَمَا شَاءَ فَعَلَ، فَإِنَّ (لَوْ) تَفْتَحُ عَمَلَ الشَّيْطَانِ». [صحيح] - [رواه مسلم]

(270) - ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: "የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል፡- "በሁሉም ውስጥ መልካም ነገር ቢኖርም፤ ጠንካራ ሙእሚን ከደካማው ሙእሚን አላህ ዘንድ የተሻለና ይበልጥ ተወዳጅ ነው። በሚጠቅምህ ነገር ላይ ጉጉት ይኑርህ! በአላህም ታገዝ! አትስነፍ! አንዳች ነገር ሲያገኝህም ‹እንዲህ አድርጌ በነበር እንዲህ እንዲህ ይሆን ነበር።› አትበል። ይልቁንም ‹ይህ የአላህ ውሳኔ ነው። የሻውንም ፈፀመ።› በል። (እንዲህ ቢሆን ኖሮ) ማለት የሰይጣን ስራ ትከፍታለችና።'" [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ሙእሚን ሁሉ ነገሩ መልካም እንደሆነ፤ ነገር ግን በኢማኑ፣ በቆራጥነቱ፣ በገንዘቡም በሌላም የኃይል ጎን ጠንካራ የሆነው ሙእሚን ከደካማው ሙእሚን የበለጠ አላህ ዘንድ

ምርጥና ተወዳጅ መሆኑን ገለፁ። ቀጥለውም ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) አማኝ ለሆነ ሰው ጥራት በተገባውና ከፍ ባለው አላህ ላይ ከመመካትና ከመታገዝ ጋር ለዱንያዊም ይሁን ለአኺራዊ ጉዳዮቹ የሚጠቅመውን ሰበቦች መያዝ እንደሚገባው መከሩ። ቀጥለው ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ለሁለቱ ዓለም የሚጠቅሙ ነገሮችን ከመተግበር መዳከም፣ መታከትንና መሰነፍን ከለከሉ። አማኝ የሆነ ሰው በአላህ በመታገዝ በአንድ ስራ ላይ ከታገለ፣ ሰበቦችን ከያዘና ከአላህ መልካሙን ከፈለገ በኋላ ሁሉን ነገሩ ወደ አላህ ማስጠጋትና የአላህ ምርጫ የተሻለ መሆኑን ማወቅ እንጂ ሌላ ጣጣ ውስጥ መግባት የለበትም። ከዚህም በኋላ አንድ ችግር ቢያገኘው እንዲህ ማለት የለበትም: "እንዲህ ባደርግ ኖሮ እንዲህ እንዲህ ይሆን ነበር።" ""እንዲህ ባደርግ ኖሮ" ማለት የአላህን ውሳኔ በመቃወም፣ ባለፈን ነገር በመቆጨት፣ የሰይጣንን ስራ ትከፍታለች። ነገር ግን በመቀበልና በመውደድ "ይህ የአላህ ውሳኔ ነው። አላህም የፈለገውን ፈፀመ።" ይበል። የተከሰተው ነገር አላህ በፈለገው መሰረት ነው። እርሱ የፈለገውን ነገር ፈፃሚ ነው፤ የርሱን ውሳኔ መላሽ የለም፤ ፍርዱንም የሚያቅብ የለም።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ሰዎች በኢማን እንደሚበላለጡ እንረዳለን።
2. በስራዎች ላይ ጠንካራ መሆን እንደሚወደድ እንረዳለን። ምክንያቱም በደካማነት የማይገኙ ጥቅሞች በጥንካሬ አማካይነት ሊገኙ ይሆናልና።
3. የሰው ልጅ በሚጠቅመው ነገር ላይ መጓጓትና የማይጠቅመው ነገርን ደግሞ መተው ይገባዋል።
4. አንድ አማኝ በሁሉም ጉዳዮቹ የአላህን እገዛ መፈለጉ ግዴታ ነው። በነፍሱ ላይ ሊመካም አይገባውም።
5. የአላህን ውሳኔና ፍርድ ማፅደቅ ሰበቦችን ከመፈፀምና መልካምን ለመፈለግ ከመልፋት ጋር አይጋጭም።

6. ችግሮች በሚያጋጥሙ ወቅት በመበሳጨት መልኩ "እንዲህ ባደርግ ኖሮ" ማለት መከልከሉንና የአላህን ፍርድና ውሳኔ መቃወም ክልክል መሆኑን እንረዳለን።

(5493)

(٢٧١) - عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ رضي الله عنه قَالَ: قَالَ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ: «قَارِبُوا وَسَدِّدُوا، وَاعْلَمُوا أَنَّهُ لَنْ يَنْجُوَ أَحَدٌ مِنْكُمْ بِعَمَلِهِ» قَالُوا: يَا رَسُولَ اللهِ وَلَا أَنْتَ؟ قَالَ: «وَلَا أَنَا، إِلَّا أَنْ يَتَغَمَّدَنِيَ اللهُ بِرَحْمَةٍ مِنْهُ وَفَضْلٍ». [صحيح] - [متفق عليه]

(271) - ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: «የአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና እንዲህ ብለዋል: "ትክክለኛውን አካሄድ ተከተሉ፤ በተቻለ መጠን ወደ እሱ ቅርብ ለመሆን ሞክሩ ከናንተ መካከል አንድም ሰው በስራው እንደማይድንም እወቁ!" ሶሐቦችም "የአላህ መልክተኛ ሆይ! እርሶም ቢሆኑ በስራዎት አይድኑምን?" አሉ። እርሳቸውም "አላህ ከርሱ በሆነ እዝነትና ችሮታ ካልሸፈነኝ በቀር እኔም ብሆን በስራዬ አልድንም።" አሉ።» [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ሶሐቦች እንዲሰሩ፤ ወሰን ሳያልፉና ሳያጓድሉ በቻሉት ልክ አላህንም እንዲፈሩ፤ ስራቸው ተቀባይነት አግኝቶ በነርሱ ላይ የአላህ እዝነት እንዲወርድ ሰበብ እንዲሆንም በስራቸው ለአላህ በማጥራትና ሱናን በመከተል በትክክል መስራትን እንዲያስቡ አነሳሱ።

ቀጥለውም ከናንተ መካከል አንድም ሰው በስራው ብቻ አይድንም። ይልቁንም የግድ የአላህ እዝነት ያስፈልገዋል ብለው ነገሯቸው።

ሰሐቦችም "የአላህ መልክተኛ ሆይ! የእርሶ ሥራ እንዲህ መጠኑ ከመግዘፉ ጋርም (መልካም ስራዎ ብቻውን) አያድኖትምን?" አሉ።

እርሳቸውም "እኔም ብሆን አላህ በችሮታውና በእዝነቱ እስካልሸፈነኝ ድረስ በስራዬ ብቻ አልድንም።" አሉ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ነወዊ እንዲህ ብለዋ፦ል "(ሰዲዱ ወቃሪቡ) ማለት ትክክለኛውን ፈልጉ፣ በትክክልም ስሩ፤ የተስተካከለ አድርጎ መስራትን ካልቻላችሁ ወደ ትክክለኛነት ቀረብ በሉ ማለት ነው። "ሰዳድ" ማለት በትክክል መስራት ማለት ነው። እርሱም ወሰን በማለፍና በማጓደል መካከል ያለ (ሚዛናዊውን) ነው። ስለዚህ ወሰን አትለፉም አታጓድሉም ማለት ነው።"
2. ኢብኑ ባዝ እንዲህ ብለዋል፡ "መጥፎ ስራዎች እሳት የመግቢያ ምክንያት እንደሆኑ ሁሉ መልካም ስራዎችም ጀነት የመግቢያ ምክንያት ናቸው። ይህ ሐዲሥ ጀነት የሚገቡት በስራቸው ብቻ እንዳልሆነ ይገልጻል። ይልቁንም የግድ የአላህ ይቅር ባይነትና እዝነት ያስፈልጋቸዋል። እነርሱ የገቡት በስራቸው ምክንያት ቢሆንም ነገር ግን ይህንንም (በስራቸው ጀነት መግባትን ራሱ) ያስፈረደላቸው የአላህ እዝነት፣ ይቅር ባይነቱና ምህረቱ ነው።"
3. አንድ ባሪያ ስራው ምንም ያህል ቢደርስ ሊደነቅበትና ሊታለልበት አይገባም። ከርሱ ስራ ይልቅ የአላህ ሐቅ ይበልጣልና። ስለዚህም የትኛውም ባሪያ የግድ ፍራቻና ተስፋን አንድ ላይ መሰብሰብ ይገባዋል።
4. አላህ በባሮቹ ላይ ያለው ችሮታና እዝነቱ ከስራቸው የበለጠ ሰፊ ነው።
5. መልካም ስራዎች ጀነት ለመግባት ምክንያት ቢሆኑም በርሷ ስኬታማ የሚኮነው ግን በአላህ ችሮታና እዝነት ነው።
6. ኪርማኒ እንዲህ ብለዋል፡ "ማንኛውም ሰው በአላህ እዝነት ካልሆነ በቀር ጀነት የማይገቡ ከሆነ የአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ተለይተው የተጠቀሱበት ምክንያት እርሳቸው ጀነት እንደሚገቡ በቁርጥ የተረጋገጠ ከመሆኑም ጋር

እርሳቸውም በአላህ እዝነት ካልሆነ በቀር ጀነት የማይገቡ ከሆነ ከርሳቸው ውጪ ያለውም ጀነት ሊገባ የሚችለው በአላህ እዝነት ሊሆን ይበልጥ የተገባ መሆኑን ለመጠቆም ነው።"

7. ነወዊ እንዲህ ብለዋል: «{ትሰሩት በነበራችሁት ስራ ጀነት ግቡ።} [አንነሕል:32] {ይህቺም ያቺ ትሰሩት በነበራችሁት ዋጋ የተሰጣችኋት ጀነት ናት።} [አዝዙኽሩፍ: 72] የሚለው የአላህ ንግግርና የመሳሰሉት ጀነት የሚገባው ሥራ በመስራት ምክንያት መሆኑን የሚጠቁሙ አንቀጾች የያዙት ሀሳብና የዚህ ሐዲስ ሃሳብ አይጣረሱም። ይልቁኑም የአንቀጾቹ ሀሳብ ጀነት የሚገባው በስራ ምክንያት መሆኑን የሚጠቁም ነው። ከዚያም ግን ለስራው መገጠም፣ በስራው ለአላህ ብቻ ብሎ ለመስራት መመራትና ስራውም ተቀባይነትን የሚያገኘው በአላህ እዝነትና ችሮታ ነው። ስለዚህም ትክክለኛው ጭብጥ በስራው ብቻ ጀነት አልገባም ነው። ሐዲሡ ሊገልፀው የፈለገው ሃሳብም ይህ ነው። በስራው ምክንያት ነው ጀነት የገባው ሊባል ይችላል። ይህም ግን ከአላህ እዝነት የመጣ ነው።»
8. ኢብኑል ጀውዚይ እንዲህ ብለዋል: "በዚህ ዙሪያ አራት መልሶች ይገኛሉ: የመጀመሪያው: ለስራ መገጠም ራሱ ከአላህ እዝነት መሆኑ ነው። ቀዳሚ የሆነው የአላህ እዝነት ባይኖር ኖሮ ኢማን የሚባል፣ የሚድንበት የሆነው መልካም ስራም አይኖርም ነበር። ሁለተኛው: ባሪያ ለአሳዳሪው የሚያደርጋቸው ጥቅሞችና ስራዎች ሁሉ ለአለቃው የተገቡ ናቸው። አለቃው ለባሪያው ምንም ያህል ክፍያ ሰጥቶ ቢያጣቅመው ከችሮታው ነው። ሶስተኛው: አንዳንድ ሐዲሦች ውስጥ ጀነት መግባት በአላህ እዝነት እንደሆነና (በጀነት ውስጥ) የደረጃዎች ክፍፍል ግን በስራ መጠን እንደሆነ የሚጠቁም ገለፃም መጥቷል። አራተኛው: የአምልኮ ስራዎች ለጥቂት ዘመን የተሰሩ ሲሆኑ ምንዳው ግን ዘልአለሙን የማያልቅ ነው። በሚያልቅ ስራ የማያልቅ ፀጋና ምንዳ ማጣቀም በችሮታ የሚገኝ እንጂ ለስራ ክፍያ አይሆንም።"
9. አርራፊዒይ እንዲህ ብለዋል: «ማንኛውም ድርጊት ፈፃሚ ድርጊቱን የፈፀመው በአላህ መግጠም ወንጀልንም የተወው በአላህ ጥበቃ ነው። ይህ

ሁሉ ደግሞ የአላህ ቸሮታና እዝነት ነው። ስነዚህም አንድ ሰሪ መዳንን ለመፈለግና ደረጃዎችን ለማግኘት በስራው ላይ ሊመካ አይገባውም።»

(3469)

(٢٧٢) - عن ابن عمر رضي الله عنهما قال: قال رسول الله صلى الله عليه وسلم: «مَا زَالَ يُوصِينِي جِبْرِيلُ بِالْجَارِ، حَتَّى ظَنَنْتُ أَنَّهُ سَيُوَرِّثُهُ». [صحيح] - [متفق عليه]

(272) - ከኢብኑ ዑመር -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: የአላህ መልክተኛ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንዲህ አሉ: "(ጎረቤቱን) ያስወርሰዋል ብዬ እስከማስብ ድረስ ጂብሪል በጎረቤት (ሐቅ ዙሪያ) እኔን ከማዘዝ አልተወገደም።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ጂብሪል ለጎረቤታቸው ትኩረት እንዲቸሩ፣ ሐቁን እንዲጠብቁ፣ እንዳያውኩት፣ ለርሱ በጎ እንዲውሉ፣ በሚያደርስባቸው ጉዳት እንዲታገሱ ከማዘዝና ከመደጋገም እንዳልተወገደ ተናገሩ። ይህም ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ከጎረቤት ሀቅ ክብደትና ጂብሪል ይህን ትእዛዝ ከመደጋገሙ የተነሳ ከሞቱ በኋላ ትተውት የሚያልፉትን ገንዘባቸውን ለጎረቤታቸው እንዲሰጡ የሚያዝ ወሕይ ሊወርድ ይሆን ብለው እስኪያስቡ ደረሱ። ጎረቤት ሲባልም ሙስሊምም ሆነ ካፊር፣ ዘመድም ሆነ ባዳ ማንኛውም ለቤት ቅርብ የሆነ ማለት ነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. የጎረቤት ሐቅ ክብደትንና ይህንን መጠባበቅ ግዴታ እንደሆነ ፤
2. የጎረቤት ሐቅ በአደራ መልክ መጠንከሩ ጎረቤትን ማክበርን፣ መውደድን፣ ለርሱ በጎ መዋልን፣ ከርሱ ጉዳትን መከላከልን፣ ሲታመም መጠየቅን፣ በደስታ ወቅት ማስደሰትን፣ በመከራ ወቅት ማፅናናትን ያስፈርዳል ፤
3. የጎረቤት ደጃፍ በቀረበ ልክ ሐቁም የጠነከረ ይሆናል።

4. ሸሪዓ ለጎረቤት በጎ መዋልና ከነሱ ላይ ጉዳትን መከላከልን የመሰለ ለማህበረሰቡ ጥቅም ያላቸው ድንጋጌዎችን ይዞ በመምጣቱ ረገድ የተሟላ መሆኑን እንረዳለን።

(4965)

(٢٧٣) - عن أبي الدرداء رضي الله عنه عن النبي صلى الله عليه وسلم قال: «مَنْ رَدَّ عَنْ عِرْضِ أَخِيهِ رَدَّ اللهُ عَنْ وَجْهِهِ النَّارَ يَوْمَ الْقِيَامَةِ». [صحيح] - [رواه الترمذي وأحمد]

(273) - ከአቡ ደርዳእ -አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ ብለዋል፦ "ከወንድሙ ክብር የተከላከለ ሰው በትንሳኤ ቀን አላህ እሳትን ከፊቱ ይከላከልለታል።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቲርሚዚና አሕመድ ዘግበውታል።]

**ትንታኔ:**

ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ሙስሊም ወንድሙ በራቀ ወቅት እንዳይወገዝ ወይም በርሱ ላይ መጥፎ እንዳይደርስበት በመከልከል ከሙስሊም ወንድሙ ክብር ለተከላከለ ሰው አላህ የትንሳኤ ቀን ቅጣትን ከሱ እንደሚከላከልለት ተናገሩ።

**ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:**

1. የሙስሊሞችን ክብር የሚነካ ንግግር መናገር መከልከሉን፤
2. ምንዳ በስራ አምሳያ (ልክ) ነው። ከወንድሙ ክብር ለተከላከለ ሰው አላህም ከሱ ላይ እሳትን ይከላከልለታል።
3. ኢስላም በተከታዮቹ መካከል ወንድማማችነትና መረዳዳትን የሚያጠናክር እምነት መሆኑን እንረዳለን።

(5514)

(٢٧٤) - عَنْ أَنَسٍ رَضِيَ اللهُ عَنْهُ عَنِ النَّبِيِّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ قالَ: «لاَ يُؤْمِنُ أَحَدُكُمْ، حَتَّى يُحِبَّ لِأَخِيهِ مَا يُحِبُّ لِنَفْسِهِ». [صحيح] - [متفق عليه]

(274) - ከአነስ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል: "አንዳችሁ ለነፍሱ የሚወደውን ነገር ለወንድሙ እስካልወደደ ድረስ አላመነም።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ለነፍሱ የሚወደውን አምልኮዎችና ሃይማኖታዊም ይሁን ዱንያዊ መልካም ነገሮችን ለወንድሙ እስከሚወድ ድረስ፤ ለነፍሱ የሚጠላውንም ለርሱም እስኪጠላ ድረስ ለአንድ ሙስሊም የተሟላ ኢማን እንደማይረጋገጥ ገለፁ። በሙስሊም ወንድሙ ላይ የዲን ጉድለት ከተመለከተም ለማስተካከል ይታገላል። በርሱ ላይ መልካምን ከተመለከተም ያበረታዋል፣ ያግዘዋል፣ የዲኑን ወይም የዱንያውን ጉዳይም ይመክረዋል።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. አንድ ሙስሊም ለነፍሱ የሚወደውን ነገር ለወንድሙ የመውደድ ግዴታ እንዳለበት እንረዳለን። ለነፍሱ የሚወደውን ነገር ለወንድሙ የማይወድ ሰው ላይ ኢማን ውድቅ መደረጉ ይህን መተግበር ግዴታ መሆኑን ይጠቁማልና።
2. ለአላህ ብሎ ወንድማማች መሆን ከዘር ወንድማማችነትም በላይ ነው። የኢስላማዊ ወንድማማችነት ግዴታውም የበለጠ ነው።
3. ይህንን ውዴታ የሚቃረን ሁሉ ማጭበርበር፣ ሀሜት፣ ምቀኝነት፣ በሙስሊም ነፍስ ላይ ወይም ገንዘቡ ላይ ወይም ክብሩ ላይ ጠላት መሆንን የመሳሰሉ ንግግርም ሆነ ተግባርም ክልክል መሆኑን እንረዳለን።

4. "ለወንድሙ" ከሚለው ቃል ለአንድ ተግባር የሚያነሳሳ የሆነን ቃል መጠቀም እንደሚገባ እንረዳለን።
5. ኪርማኒ አላህ ይዘንላቸውና እንዲህ ብለዋል: «ከዚህም በተጨማሪ ለነፍሱ የሚጠላውን መጥፎ ነገር ለወንድሙ መጥላቱም የኢማን ክፍል ነው። ሐዲሡ ላይ ያልጠቀሱት አንድን ነገር መውደድ ተቃራኒውን መጥላት የሚያስፈርድ ስለሆነ በዚህ በመብቃቃት መጥቀሱን ተዉት።

(4717)

(٢٧٥)- عن عائشة رضي الله عنها زوج النبي صلى الله عليه وسلم عن النبي صلى الله عليه وسلم قال: «إِنَّ الرِّفْقَ لَا يَكُونُ فِي شَيْءٍ إِلَّا زَانَهُ، وَلَا يُنْزَعُ مِنْ شَيْءٍ إِلَّا شَانَهُ».

[صحيح] - [رواه مسلم]

(275) - የነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ባለቤት ከሆነችው ከእናታችን ዓኢሻህ -አላህ መልካም ስራዋን ይውደድላትና- እንደተላለፈው ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንዲህ ብለዋል፦ "በአንድ ነገር ውስጥ ገራገርነት (ልስላሴ) አይኖርም ያስዋበው ቢሆን እንጂ ፤ ከአንድ ነገር ውስጥ ደግሞ አይነሳም አስቀያሚ የሚያደርገው ቢሆን እንጂ።" [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም በንግግርም ይሁን በተግባር ገራገርነት፣ ለስላሳነትና እርጋታ ነገሮች ላይ ውበት፣ ምሉዕነትና ማማር የሚጨምር እንዲሁም ይህንኑ ባህሪ የተላበሰ ሰውም ጉዳዩን ለማሳካት የተገባ እንደሆነ ገለፁ።

ገራገር (ለስላሳ) አለመሆን ደግሞ ነገሮችን ያነውራቸዋልም አስቀያሚ ያደርጋቸዋልም፤ ስለዚህም ባለቤቱ አላማውን እንዳያገኝ ይከለክለዋል። ካገኝም በችግር ነው የሚያገኘው።

## ከሐዲሡ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ለስላሳ ባህሪን በመላበስ ላይ መበረታታቱን ተረድተናል።

2. ገራገርነት (ልስላሴ) ሰውን ያስውባል። ገራገርነት በዱንያም (ልስላሴ) በአኺራም የሚገኙ ሁሉም መልካም ጉዳዮችን ለማግኘት ምክንያት ነው።

(5796)

(٢٧٦) - عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ رضي الله عنه عَنِ النَّبِيِّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ قَالَ: «إِنَّ الدِّينَ يُسْرٌ، وَلَنْ يُشَادَّ الدِّينَ أَحَدٌ إِلَّا غَلَبَهُ، فَسَدِّدُوا وَقَارِبُوا، وَأَبْشِرُوا، وَاسْتَعِينُوا بِالْغَدْوَةِ وَالرَّوْحَةِ وَشَيْءٍ مِنَ الدُّلْجَةِ».
[صحيح] - [رواه البخاري]

(276) - ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል፦ "የእስልምና ሃይማኖት ገር ነው። አንድም ሰው የእስልምናን ሃይማኖት ከመጠን በላይ አያጠብቅም (ሃይማኖቱ) የሚያሸንፈው ቢሆን እንጂ፤ ሚዛናዊ ሁኑ! አቀራርቡ! አብሽሩ! በማለዳ አምልኮ፣ በቀትር አምልኮና በተወሰነ የሌሊት አምልኮ ታገዙ!" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና የእስልምና ሃይማኖት በሁሉም ጉዳዮች በገርነትና በማቅለል ላይ የተገነባ መሆኑን ገለፁ። አለመቻልና አስገዳጅ ምክንያቶች ሲኖሩም ገርነቱ ይጨምራል። በሃይማኖታዊ ጉዳዮች ከአቅም በላይ መጥለቅና ገራገርነትን መተውም መጨረሻው አለመቻልና ሁሉንም ወይም የተወሰነውን ስራ ማቋረጥ ነው ። ቀጥለውም ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ወሰን ሳያልፉ ሚዛናዊ በመሆን ላይ አነሳሱ። አንድ ባሪያ ከታዘዘበት ነገር ማጓደል አይኖርበትም፤ የማይችለውንም ለመስራት አይጫንበትም። ሙሉ ለሙሉ መስራት ካቃተው ወደ ሙሉነት ቀረብ አድርጎ መስራት እንደሚገባ ገለፁ።

ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ስራን አሟልቶ መስራት ያቃተው ሰው ብታንስ እንኳ ዘውታሪነቷን

ለማስቀጠል የምትሠራ ሥራ ትልቅ ምንዳ እንደምታስገኝ አበሰሩ። አለመቻል በራሱ ድክመት የመጣ እስካልሆነ ድረስ የምንዳ መጉደልን አያስከትልምና።

ዱንያ እውነታዋ ወደ መጪው ዓለም የምንጓዝበት የጉዞና የመሸጋገሪያ ሀገር እንደመሆኗ መጠን ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና አምልኮን ነቃ በሚያደርጉ ሶስት ወቅቶች ላይ ዘውትረን በመፈፀም እንድንታገዝ አዘዙ።

የመጀመሪያው: የማለዳ ጉዞ ነው: ይህም በመጀመሪያው የቀን ክፍል በማምለክ ነው። ወቅቱም በፈጅር ሶላትና በፀሐይ መውጣት መካከል አምልኮን መፈፀም ማለት ነው።

ሁለተኛው: ከዝሁር በኋላ የቀትር ጉዞ ነው።

ሶስተኛው: የሌሊቱን ሁሉ ወይም የተወሰነው ክፍል ላይ የሌሊት ጉዞ ነው። የሌሊት ስራ ከቀን ስራ የሚከብድ ስለሆነ "የተወሰነ ከሌሊትም" በማለት የተወሰነውን ሰአት ብቻ እንድናመልክበት አዘዙ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. የእስልምና ሸሪዓ ገርነትና ቀላልነትን፤ በቸልተኝነትና ወሰን በማለፍ መካከል ሚዛናዊ መሆኑን እንረዳለን።
2. አንድ ባሪያ በቻለው ልክ ሳይዘናጋ ወይም ከወሰን በላይ ሳያጠብቅ የታዘዘውን መፈፀም አለበት።
3. አንድ ባሪያ አምልኮ ሲፈፅም የንቃት ወቅቱን መምረጥ እንደሚገባው እንረዳለን። በተለይ እነዚህ ሶስት ወቅቶች አንድ ባሪያ ሰውነቱ ለአምልኮ ነቃ የሚልበት ወቅቶች ናቸው።
4. ኢብኑ ሐጀር አልዐስቀላኒ እንዲህ ብለዋል: «ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ወደሆነ ቦታ መሄድ ያለመን አንድ መንገደኛን የሚያናግሩ ነው የመሰሉት። እነዚህ ሶስት ወቅቶች ለመንገደኛ ምርጥ ወቅቶች ናቸው። ስለዚህ እኛም የንቃት ወቅቶችን እንድንሰራባቸው አስገነዘቡ። ምክንያቱም አንድ ተጓዥ ሌሊቱንም ቀኑንም በሙሉ ከተጓዘ ይደክምና ጉዞውን ያቋርጣል። በነዚህ የሚያነቁ በሆኑ

ወቅቶች መጓዝ ላይ ከበረታ ግን ያለምንም ችግር በጉዞው ላይ ለመዘውተር ይመቻዋል።»

5. ኢብኑ ሐጀር እንዲህም ብለዋል: «በዚህ ሐዲሥ ውስጥ ሸሪዓዊ ማግራሪያዎችን መያዝ እንደሚገባ ተጠቁሟል። በተግራራ ቦታ ላይ ከባዱን ግዴታ ነገር መስራት ማካበድ ነው። ለምሳሌ ውሃ መጠቀም ያልቻለና ውሃን መጠቀሙ ጉዳት የሚያደርስበት በሆነ ወቅት ተየሙምን ትቶ ውሃ ቢጠቀም ማለት ነው።»
6. ኢብኑ ሙኒር እንዲህ ብለዋል: «በዚህ ሐዲሥ ውስጥ ከነቢያት ምልክቶች መካከል አንዱ ተገልጿል። ይህም እኛም ሆንን ከኛ በፊት የነበሩት በእስልምና ውስጥ ወሰን የሚያልፍ ሰው የሆነ ቦታ ላይ ሲያቋርጥ ማየታችን ነው። በዚህ ሐዲሥ የተሟላን አምልኮ ለመስራት መፈለግን መተው አይደለም የተወገዘው። ይህማ የተወደሰ ጉዳይ ነው። ይልቁንም ወደ መሰላቸት የሚያመራ ወሰን ማለፍ ወይም የተሻለን ለመተው ወይም የግዴታ ነገር ወቅቱ እንዲያልፍ የሚያደርግ በሆነ መልኩ ትርፍ ስራዎች ላይ ወሰን ማለፍ ነው የተከለከለው። ለምሳሌ ያህል ሌሊቱን ሙሉ እየሰገድ አድሮ ሱብሒን በህብረት ሳይሰግድ ወይም ፀሀይ እሰወክትወጣበትና የግዴታው ወቅት እስኪያልፍ ድረስ የሚቆይ ሰው ይጠቀሳል።»

(5795)

(٢٧٧) - عن أنس بن مالك رضي الله عنه عن النبي صلى الله عليه وسلم قال: «يَسِّرُوا وَلَا تُعَسِّرُوا، وَبَشِّرُوا وَلَا تُنَفِّرُوا». [صحيح] - [متفق عليه]

(277) - ከአነስ ቢን ማሊክ -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንዲህ ብለዋል: "አግራሩ አታክብዱ! አበስሩ አታሸሹ!" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

**ትንታኔ:**

ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም በሁሉም ዓለማዊም ይሁን ዲናዊ በሆኑ ጉዳዮች ለሰዎች ማቅለልና ማግራራትን እንዲሁም እነርሱ ላይ አለማክበድን

አዘዙ። ይህም ማግራራት አላህ በፈቀደውና በደነገገው ድንበር ውስጥ ሆኖ ነው።

ሰዎችን በመልካም ነገሮች በማበሰርና እነርሱን ከመልካም ነገሮች ባለማሸሽ ላይም አበረታቱ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. የአንድ አማኝ ግዴታ ሰዎች አላህን እንዲወዱ ማድረግና በመልካም ነገሮች ላይ ማነሳሳት ነው።
2. ወደ አላህ የሚጣራ ሰው የኢስላምን ጥሪ ወደ ሰዎች በጥበብ እንዴት እንደሚያደርስ ማስተዋል ይገባዋል።
3. ማበሰር ለዳዒውም ለሚያስተላልፈው ነገርም ደስታን ተሰሚነትንና መረጋጋትን ያስተርፋል።
4. ማካበድ በዳዒው ንግግር ውስጥ ማሸሽን ፣ ተቀባይነት ማጣትና ጥርጣሬን ይፈጥራል።
5. ለነርሱ የወደደላቸው ገር እምነትና ቀላል ድንጋጌ በመሆኑ አላህ በባሮቹ ላይ ያለው እዝነት ሰፊ መሆኑን እንረዳለን።
6. እንድናግራራ የታዘዝንባቸውን ነገሮች ማግራራት ሸሪዓ ይዞት የመጣው አንዱ ድንጋጌ ነው።

(5866)

(٢٧٨) - عن أنس رضي الله عنه قال: كُنَّا عِنْدَ عُمَرَ فَقَالَ: «نُهِينَا عَنِ التَّكَلُّفِ».
[صحيح] - [رواه البخاري]

(278) - ከአነስ -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: "ዑመር ዘንድ ነበርንና እንዲህ አሉ: 'ከአቅም በላይ ከመጣጣር ተከልክለናል።'" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ዑመር -አላህ መልካም ስራውን ይውደድለትና- የአላህ መልክተኛ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም አንድ ነገርን ንግግርም ይሁን ድርጊት የግድ መቸጋገር ሳያስፈልግ መቸገር ያለበትን ነገር ከመጠቀም እንደከለከሏቸው ተናገሩ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ከተከለከሉት ከአቅም በላይ መጣጣር ውስጥ : - ጥያቄ ማብዛት ወይም በርሱ እውቀት በሌለው ነገር ያለአቅሙ መጣጣር ወይም አላህ ያሰፋው ጉዳዩ ላይ ማካበድ ይጠቀሳሉ።
2. ሙስሊም የሆነ ሰው በንግግሩ፣ በተግባሩ፣ በአመጋገቡ፣ በአጠጣጡና በማንኛውም ሁኔታው ገራገርነትንና አለማካበድን ለነፍሱ ማለማመድ ይገባዋል።
3. ኢስላም ገር እምነት መሆኑን እንረዳለን።

(8945)

(٢٧٩) - عن ابن عمر رضي الله عنهما أن رسول الله صلى الله عليه وسلم قال: «إِذَا أَكَلَ أَحَدُكُمْ فَلْيَأْكُلْ بِيَمِينِهِ، وَإِذَا شَرِبَ فَلْيَشْرَبْ بِيَمِينِهِ، فَإِنَّ الشَّيْطَانَ يَأْكُلُ بِشِمَالِهِ، وَيَشْرَبُ بِشِمَالِهِ». [صحيح] - [رواه مسلم]

(279) - ከኢብኑ ዑመር (ረዲየሏሁ ዐንሁማ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ አሉ: "አንዳችሁ የበላ ጊዜ በቀኙ ይብላ። የጠጣም ጊዜ በቀኙ ይጠጣ። ሰይጣን የሚበላውም በግራው፤ የሚጠጣውም በግራው ነውና።" [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) አንድ ሙስሊም ሲበላም ሆነ ሲጠጣ በቀኝ እጁ እንዲሆን አዘዙ። በግራው ከመብላትና ከመጠጣትም ከለከሉ። ይህም ሰይጣን የሚበላውም ሆነ የሚጠጣው በግራው ስለሆነ ነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. በግራ በመብላት ወይም በመጠጣት ከሰይጣን ጋር ከመመሳሰል መከልከሉ።

(58122)

(٢٨٠) - عن عُمر بن أبي سلمة رضي الله عنه قال: كُنْتُ غُلَامًا فِي حَجْرِ رَسُولِ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ، وَكَانَتْ يَدِي تَطِيشُ فِي الصَّحْفَةِ، فَقَالَ لِي رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ: «يَا غُلَامُ، سَمِّ اللهَ، وَكُلْ بِيَمِينِكَ، وَكُلْ مِمَّا يَلِيكَ» فَمَا زَالَتْ تِلْكَ طِعْمَتِي بَعْدُ. [صحيح] - [متفق عليه]

(280) - ከዑመር ቢን አቢ ሰለማህ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: "በአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ጎጀ ውስጥ የምኖር ህፃን ልጅ ነበርኩ። በማዕዱ ላይም እጄ ትሽከረከር ነበር። የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ለኔ እንዲህ አሉኝ ' አንተ ልጅ ሆይ! ቢስሚላህ በል! በቀኝህ ብላ፣ ፊትህ ካለውም ብላ!' ከዚያን ጊዜ በኋላ ከዚህ የአበላል ስርአት አልተወገድኩም።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ዑመር ቢን አቢ ሰለማህ (ረዲየላሁ ዐንሁማ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና የነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ባለቤት የሆነችው የኡሙ ሰለማህ ልጅ ነው። በሳቸው እነፃና እንክብካቤ ስር ነበር። በሚበላበት ወቅት ምግብ ለማንሳት እጁን በእቃው ዙሪያ ያዘዋውር ነበር። ነቢዩም (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ሶስት የአመጋገብ ስርአቶችን አስተማሩት:

የመጀመሪያው: መብላት ሲጀመር "ቢስሚላሂ" ማለት ነው።

ሁለተኛው: በቀኝ መብላት ነው።

ሶስተኛው: ለርሱ ቅርብ በሆነ ምግብ በኩል መመገብ ነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ከመብላትና መጠጣት ስርአቶች መካከል መጀመሪያ ቢስሚላህ ማለት አንዱ ነው።

2. ህፃናትን ስርአት ማስተማር እንደሚገባ በተለይ በሰውዬው ሀላፊነት ስር ያለን ልጅ ስርአት ማስተማር እንደሚገባ እንረዳለን።
3. ህፃናትን በማስተማርና ስርአት በማስያዙ ረገድ የነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እዝነትና ልበ ሰፊነትን እንረዳለን።
4. ከፊቱ ካለው መመገብ ከአመጋገብ ስርአቶች መካከል አንዱ ነው። የምግብ አይነቶቹ ብዙ የሆኑ ጊዜ ግን ከፊቱ ውጪ ካለ መውሰድም ይቻላል።
5. ሶሐቦች ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ያስተማሯቸውን ስርአት አጥብቀው መያዛቸውን እንረዳለን። ይህንንም ነጥብ "ከዛን ጊዜ በኋላ ከዚህ የአበላል ስርአት አልተወገድኩም።" ከሚለው የዑመር ንግግር እንረዳለን።

(58120)

(٢٨١) - عن أنس بن مالك رضي الله عنه قال: قال رسول الله صلى الله عليه وسلم: «إِنَّ اللهَ لَيَرْضَى عَنِ الْعَبْدِ أَنْ يَأْكُلَ الْأَكْلَةَ فَيَحْمَدَهُ عَلَيْهَا، أَوْ يَشْرَبَ الشَّرْبَةَ فَيَحْمَدَهُ عَلَيْهَا».

[صحيح] - [رواه مسلم]

(281) - ከአነስ ቢን ማሊክ -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው እንዲህ ብሏል: "የአላህ መልክተኛ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንዲህ ብለዋል፦ 'አላህ ባሪያው ምግብን በልቶ እንዲያመሰግነው ወይም መጠጥን ጠጥቶ እንዲያመሰግነው ይወዳል።'" [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

አንድ ባሪያ ጌታውን በቸረውና ባጣቀመው ፀጋዎቹ ምክንያት ማመስገኑ የአላህ ውዴታን ከሚያገኝባቸው ምክንያቶች መካከል አንዱ ስለሆነ ምግብ በልቶም "አልሐምዱሊላህ" ማለት ፤ የሚጠጣም ጠጥቶ "አልሐምዱሊላህ" ማለት እንደሚገባው ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ገለፁ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. አላህ ሲሳይን ችሮን በምስጋናችን በመደሰቱ የርሱን ችሮታ እንረዳለን።
2. የአላህ ውዴታ ከመብላትና መጠጣት በኋላ ማመስገንን በመሰለ ትንሽ ምክንያት እንኳ እንደሚገኝ እንረዳለን።
3. ከምግብና መጠጥ ስነስርአቶች መካከል ከበሉና ከጠጡ በኋላ አላህን ማመስገን አንዱ ነው።

(5798)

(٢٨٢) - عَنْ سَلَمَةَ بْنِ الْأَكْوَعِ رضي الله عنه: أَنَّ رَجُلًا أَكَلَ عِنْدَ رَسُولِ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ بِشِمَالِهِ، فَقَالَ: «كُلْ بِيَمِينِكَ»، قَالَ: لَا أَسْتَطِيعُ، قَالَ: «لَا اسْتَطَعْتَ»، مَا مَنَعَهُ إِلَّا الْكِبْرُ، قَالَ: فَمَا رَفَعَهَا إِلَى فِيهِ. [صحيح] - [رواه مسلم]

(282) - ከሰለማ ቢን አክወዕ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው:- "አንድ ሰውዬ የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ዘንድ በግራ እጁ በላ። እርሳቸውም 'በቀኝህ ብላ።' አሉት። እርሱም 'አልችልም!' አላቸው። እርሳቸውም 'አያስችልህ!' አሉት። ኩራት እንጂ ሌላ አልከለከለውም። ሰለማ እንዲህ አለ '(ከዛ በኃላ) እጁን ወደ አፉ ማንሳት አልቻለም።' " [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

**ትንታኔ:**

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) አንድ ሰው በግራ እጁ ሲበላ ተመለከቱትና በቀኝ እጁ እንዲበላ አዘዙት። ሰውዬውም በኩራትና በውሸት በቀኝ እጁ መብላት እንደማይችል መለሰላቸው። ነቢዩም (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) በቀኝ እጁ መመገብ አሏህ እንዳያስችለው በርሱ ላይ ዱዓ አደረጉበት። ቀኝ እጁን ሽባ በማድረግ አላህ የነቢዩን ዱዓ ተቀበለ። ከዚህ በኋላም ምግብ ወይም መጠጥ ወደ አፉ ማንሳት አልቻለም።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. በቀኝ እጅ መብላት ግዴታ መሆኑንና በግራ መብላት ክልክል መሆኑን እንረዳለን።
2. የሸሪዓን ህግጋት ተግባራዊ ከማድረግ መኩራራት ባለቤቱን ለቅጣት የተገባ ያደርገዋል።
3. አላህ ለነቢዩ ሙሐመድ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ዱዓቸውን በመቀበል ማክበሩን እንረዳለን።
4. በመልካም ማዘዝና ከመጥፎ መከልከል በሁሉም ሁኔታ ላይ በመመገብ ወቅት እንኳ ሳይቀር መደንገጉን እንረዳለን።

(3372)

(٢٨٣) - عَنْ جَابِرِ بْنِ عَبْدِ اللهِ رضي الله عنهما أَنَّ النَّبِيَّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ قَالَ: «مَنْ أَكَلَ ثُومًا أَوْ بَصَلًا، فَلْيَعْتَزِلْنَا -أَوْ قَالَ: فَلْيَعْتَزِلْ- مَسْجِدَنَا، وَلْيَقْعُدْ فِي بَيْتِهِ»، وَأَنَّ النَّبِيَّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ أُتِيَ بِقِدْرٍ فِيهِ خَضِرَاتٌ مِنْ بُقُولٍ، فَوَجَدَ لَهَا رِيحًا، فَسَأَلَ فَأُخْبِرَ بِمَا فِيهَا مِنَ البُقُولِ، فَقَالَ قَرِّبُوهَا إِلَى بَعْضِ أَصْحَابِهِ كَانَ مَعَهُ، فَلَمَّا رَآهُ كَرِهَ أَكْلَهَا، قَالَ: «كُلْ فَإِنِّي أُنَاجِي مَنْ لاَ تُنَاجِي».

ولِمُسْلِمٍ عَنْ جَابِرِ بْنِ عَبْدِ اللهِ، عَنِ النَّبِيِّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ قَالَ: «مَنْ أَكَلَ مِنْ هَذِهِ الْبَقْلَةِ، الثُّومِ - وقَالَ مَرَّةً: مَنْ أَكَلَ الْبَصَلَ وَالثُّومَ وَالْكُرَّاثَ فَلَا يَقْرَبَنَّ مَسْجِدَنَا، فَإِنَّ الْمَلَائِكَةَ تَتَأَذَّى مِمَّا يَتَأَذَّى مِنْهُ بَنُو آدَمَ». [صحيح] - [متفق عليه]

(283) - ከጃቢር ቢን ዐብደላህ (ረዲየሏሁ ዐንሁማ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና እንዲህ ብለዋል: «"ነጭ ሽንኩርት ወይም ቀይ ሽንኩርት የበላ ሰው ከኛ ገለል ይበል ወይም ከመስጂዳችን ገለል ይበል። ቤቱም ይቀመጥ" አሉ። ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና አረንጓዴ አታክልት ያለበት ድስት መጣላቸው። ውስጡም የሆነ ጠረን ሸተታቸው። ሲጠይቁም ውስጡ ስላለው ቡቃያ ተነገራቸው። እርሳቸውም ከርሳቸው ጋር ወደነበረ አንድ

ባልደረባቸው "አስጠጉት" አሉ። እሳቸው መብላቱን እንደጠሉ ሰውየው መመልከቱን ባስተዋሉ ጊዜ እርሳቸውም "ብላ እኔ አንተ የማታወራው ጋር ስለማወራ ነው።" አሉት።» [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ነጭ ሽንኩርት ወይም ቀይ ሽንኩርት የበላ ሰው የጀማዓ ሶላት የሚገኙ ወንድሞቹን በጠረኑ እንዳያውክ መስጂድ ከመምጣት ከለከሉት። ይህ መስጂድ ከመምጣት የመጣው ክልከላ ግን የውግዘት ክልከላ ነው። መብላቱ የሚፈቀድ ምግብ ስለሆነ ክልከላው ከመብላት አይደለም። ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና አረንጓዴ አትክልት ያለበት ድስት መጣላቸው። ከድስቱ ውስጥም ጠረንን ባሸተቱ ጊዜና ውስጡ ያለው ነገር ምንነቱ ሲነገራቸው ከመብላት ተቆጥበው አንዱ ባልደረባቸው እንዲበላ አቀረቡለት። ሰውዬውም እርሳቸውን ተከትሎ መብላቱን ጠላ። ነቢዩም (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ሰውዬውን የተመለከቱት ጊዜ እንዲህ አሉት: "ብላ! እኔ ያልበላሁት በራእይ ከመላእክት ጋር ስለምንሾካሾክ ነው።"

ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና የሰው ልጆች በመጥፎ ሽታ እንደሚታወኩት መላእክትም ይታወካሉ በማለት ተናገሩ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ነጭ ሽንኩርት ወይም ቀይ ሽንኩርት ወይም ባሮ የበላ ሰው መስጂድ ከመምጣት መከልከሉን እንረዳለን።
2. እንደ ሲጃራ ጭስ፣ ትምባሆና የመሳሰሉት ሰጋጆች የሚታወኩበት መጥፎ ሽታ ያለው ሁሉ በፍርድ ወደነዚህ ነገሮች ይጠጋሉ።
3. የመከልከሉ ምክንያት ሽታ ነው። ስለዚህ አብዝቶ በመቀቀል ወይም በሌላ መንገድ ሽታው ቢወገድ መጠላቱም አብሮ ይወገዳል።

4. መስጂድ ውስጥ የጀመዓ ሶላት ስለሚያስመልጠው መስጂድ ውስጥ ጀመዓ ሶላት መስገድ ባለበት ሰው ላይ እነዚህ ነገሮችን መብላቱ ይጠላል። መስጂድ የመገኘት ግዴታው እንዲነሳለት ብሎ ለዘዴ መብላቱ ግን ይከለከላል።
5. ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ነጭ ሽንኩርትና የመሳሰሉትን ከመብላት የተቆጠቡት ክልክል ስለሆነ ሳይሆን ጂብሪልን (ዐለይሂ ሰላም) ስለሚያወሩ ነው።
6. ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ብይንን ከምክንያቱ ጋር አቆራኝተው መናገራቸው የርሳቸውን የማስተማር ውበት ያሳየናል። ይህም የሚያናግሩት ሰው የመከልከል ጥበቡን በማወቅ ልቡ እንዲረጋጋ ነው።
7. ቃዲ እንዲህ ብለዋል: «ዑለማዎች ይህን ሐዲሥ በመመርኮዝ ከመስጂድ ውጪ ያሉ የሶላት መሰብሰቢያዎችን እንደ ዒድና ጀናዛ ሶላት ለመስገድ የሚሰበሰቡበትን አይነቱ፣ የአምልኮ መሰብሰቢያ፣ ልክ እንደዚሁ የእውቀት፣ የዚክር፣ የሰርግ ድግስና የመሳሰሉት መሰብሰቢያዎችን መስጂድ ውስጥ ከሚሰገዱት ጋር በዚሁ ፍርድ አመሳስለዋቸዋል። ሱቅና የመሳሰሉት ግን የዚህ ሐዲሥ መልእክት ውስጥ አይገቡም።»
8. ዑለማዎች እንዲህ ብለዋል: እዚህ ሐዲሥ ውስጥ ነጭ ሽንኩርትና የመሳሰሉትን የበላ ሰው መስጂዱ ባዶ እንኳ ቢሆን መስጂድ ውስጥ ከመግባት መከልከሉን ይጠቁመናል። ይህም መላእክቶች የሚኖሩበት ስለሆነና የሐዲሡ ጥቅል ሀሳብ ይህንን ስለሚጠቁም ነው።

(4850)

(٢٨٤) - عَنْ سَهْلِ بْنِ مُعَاذِ بْنِ أَنَسٍ عَنْ أَبِيهِ قَالَ: قَالَ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ: «مَنْ أَكَلَ طَعَامًا فَقَالَ: الحَمْدُ لِلهِ الَّذِي أَطْعَمَنِي هَذَا وَرَزَقَنِيهِ مِنْ غَيْرِ حَوْلٍ مِنِّي وَلاَ قُوَّةٍ، غُفِرَ لَهُ مَا تَقَدَّمَ مِنْ ذَنْبِهِ». [حسن] - [رواه أبو داود والترمذي وابن ماجه وأحمد]

(284) - ሰህል ቢን ሙዓዝ ቢን አነስ ከአባቱ እንዳስተላለፈው እንዲህ አለ: «የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል: "ምግብ በልቶ ‹አልሐምዱ ሊላሂለዚ አጥዐመኒ ሀዛ ወረዘቀኒሂ ሚን ኻይሪ ሐውሊን ሚንኒ ወላቁውዋህ› ያለ ሰው ያሳለፈው ወንጀል ለርሱ ይማርለታል።"» ትርጉሙም "ያለኔ ኃይልና ብልሃት ይህንን ላበላኝና ለለገሰኝ አላህ ምስጋና የተገባው ነው።" ማለት ነው። [ሐሰን ነው።] - [አቡዳውድ፣ ቲርሚዚ፣ ኢብኑማጀህና አሕመድ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ምግብ የበላን ሰው አላህን እንዲያመሰግንና ምግብን በማምጣቱም በመብላቱም በአላህና በእገዛው ካልሆነ በቀር ለኔ ምንም አቅም የለኝም እንዲልም አነሳሱ። ቀጥለው ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ይህንን የተናገረ ሰው ላሳለፈው ትናንሽ ወንጀሎቹ የአላህን ምህረት ለማግኘት የተገባ እንደሆነ አበሰሩ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. የምግብ መጨረሻ ላይ አላህን ማመስገን እንደሚወደድ እንረዳለን።
2. አላህ ለባሮቹ ሲሳይን መለገሱን፣ የሲሳይን ምክንያት ለነርሱ ማግራቱንና በዚህም ወንጀላቸው መማሪያን ማድረጉን ስናይ የአላህን በባሮቹ ላይ ያለውን ትልቅ ትሩፋት መብራራቱን እንረዳለን።
3. የባሮች ጉዳይ ባጠቃላይ ከአላህ ነው እንጂ በነርሱ ኃይልና ብልሃት አይደለም። የትኛውም ባሪያ ግን ሰበቦችን በመስራት የታዘዘ ነው።

(5431)

(٢٨٥) - عن أبي هريرة رضي الله عنه قال: كان رسولُ الله صلى الله عليه وسلم إذا عَطَس وضَعَ يَدَه -أو ثوبَهُ- على فيهِ، وخَفَضَ -أو غضَّ- بها صوتَهُ. [صحيح] - [رواه أبو داود والترمذي وأحمد]

(285) - ከአቡ ሁረይራ (ረዲየላሁ ዐንሁ) -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: «የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ያስነጠሱ ጊዜ እጃቸውን ወይም ልብሳቸውን አፋቸው ላይ አድርገው ድምፃቸውን ይቀንሱበት ነበር።» [ሶሒሕ ነው።] - [አቡዳውድ፣ ቲርሚዚና አሕመድ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ያስነጠሱ ጊዜ:

መጀመሪያ: ከአፋቸው ወይም ከአፍንጫቸው አንዳች ነገር ወጥቶ አብሯቸው የተቀመጠውን ላለማወክ እጃቸውን ወይም ልብሳቸውን አፋቸው ላይ ያኖራሉ።

ሁለተኛ: ድምፃቸውን ይቀንሱ ነበር። ከፍም አያደርጉትም።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. በማስነጠስ ዙሪያ የነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) መመሪያ መገለፁና በዚህ ጉዳይ እርሳቸውን መከተል እንደሚገባ እንረዳለን፤
2. አንድ ሰው ያስነጠሰ ጊዜ ከርሱ አንዳች ነገር ወጥቶ አብሮ የተቀመጠውን እንዳያውክ ልብስን ወይም መሀረምና የመሳሰሉትን አፍና አፍንጫ ላይ ማኖር እንደሚወደድ እንረዳለን።
3. ሲያስነጥሱ ድምፅን ዝግ ማድረግ የሚፈለግ ጉዳይ ነው። ይህም ስነ-ስርዓትን ከሚያሟሉና ከመልካም ስነ-ምግባር የሚመደብ ነው።

(3317)

(٢٨٦) - عَنِ ابْنِ عَبَّاسٍ رضي الله عنهما قَالَ: قَالَ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ: «إِنَّ اللهَ يُحِبُّ أَنْ تُؤْتَى رُخَصُهُ، كَمَا يُحِبُّ أَنْ تُؤْتَى عَزَائِمُهُ». [صحيح] - [رواه ابن حبان]

(286) - ኢብኑ ዐባስ -አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንዲህ አሉ: የአላህ መልክተኛ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ አሉ፦ "አላህ ግዴታ ያደረገው ሲተገበር እንደሚወደው፤ ያግራውም ሲተገበር ይወዳል።" [ሶሒሕ ነው።] - [ኢብኑ ሒባን ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን አላህ አምልኮና ህግጋቶቹን በማቅለል የደነገጋቸው ማግራሪያዎች ሲተገበሩ እንደሚወድ ተናገሩ። እንዲሁም አቅመ አዳምና ጤነኛ የሆኑ ሰዎች በተቸገሩ ሰዓት የደነገገላቸውን ማቅለያዎች ለምሳሌ፦ ጉዞ ላይ ሰላትን ማሳጠርና ሰላትን ሰብስቦ መስገድ ይመስል ሢፈጸሙም አላህ እንደሚወድ ተናገሩ። ይህም ልክ ግዴታ ያደረጋቸው ሢሰሩ (ተግባራዊ ሲደረጉ) እንደሚወደው ነው። ምክንያቱም አላህ ባግራውም ጉዳዮች ሆነ ግዴታ ባደረገው ጉዳዮች ላይ ትእዛዙ አንድ ነውና።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ጥራት የተገባው አላህ የደነገጋቸው ማግራሪያዎች ሲሰሩ መውደዱ አላህ በባሮቹ ላይ ያለውን እዝነት እንረዳለን።
2. የዚህን ሸሪዐ ምሉእነትና በሙስሊም ላይ ችግርን ያነሳ መሆኑን እንረዳለን።

(65017)

(٢٨٧) - عن أبي هريرة رضي الله عنه قال: قال رسول الله صلى الله عليه وسلم: «مَنْ يُرِدِ اللَّهُ بِهِ خَيْرًا يُصِبْ مِنْهُ». [صحيح] - [رواه البخاري]

(287) - ከአቡ ሁረይራ -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸው - እንዳስተላለፉት እንዲህ ብለዋል፡- የአላህ መልዕክተኛ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ ብለዋል፡- "አላህ ለሱ መልካም የሻለትን ሰው ይፈትነዋል።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

አላህ በአንድ አማኝ ባሪያው ላይ መልካምን የፈለገ ጊዜ በነፍሳቸው፤ በገንዘባቸውና በቤተሰቦቻቸው እንደሚፈትናቸው ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ተናገሩ። ይህም አንድ አማኝ በሱ ምክንያት ወደ አላህ በዱዓእ መጠጋት፣ የወንጀል መማርና የደረጃ ከፍ ማለትን ስለሚያገኝለት ነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. አማኝ የሆነ ሰው ለተለያዩ የመከራ አይነቶች የተጋለጠ ነው።
2. ፈተና የአንድ አማኝ ደረጃውን ከፍ ከማድረጉ፣ ማዕረጉን ከመስቀሉና ወንጀሉን ከማስማሩ አኳያ አላህ ለባሪያው ላለው ውዴታ ምልክት ሊሆን ይችላል።
3. በመከራዎች ላይ ትእግስት በማድረግና ባለመበሳጨት ላይ መነሳሳቱን እንረዳለን።

(4204)

(٢٨٨) - عَنْ أَبِي سَعِيدٍ الْخُدْرِيِّ وَعَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ رضي الله عنهما عَنِ النَّبِيِّ صلى الله عليه وسلم قَالَ: «مَا يُصِيبُ الْمُسْلِمَ مِنْ نَصَبٍ وَلَا وَصَبٍ وَلَا هَمٍّ وَلَا حُزْنٍ وَلَا أَذًى وَلَا غَمٍّ حَتَّى الشَّوْكَةِ يُشَاكُهَا إِلَّا كَفَّرَ اللهُ بِهَا مِنْ خَطَايَاهُ». [صحيح] - [متفق عليه]

(288) - ከአቡ ሰዒድና አቡ ሁረይራህ (ረዲየሏሁ ዐንሁማ) -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል፦ "አላህ በሷ ምክንያት ከወንጀሎቹ የሚምርለት ቢሆን እንጂ አንድን ሙስሊም ድካም፣ በሽታ፣ ሀሳብ፣ ሀዘን፣ ጉዳት፣ ጭንቀት የምትወጋው አንዷት እሾክ እንኳ (በከንቱ) አታገኘውም።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ሙስሊምን ከበሽታዎች ፣ ከጭንቀቶች፣ ከሀዘኖች፣ ከችግሮች፣ ከመከራዎች፣ ከመአቶች እንዲሁም ከፍርሀትና ረሀብ ቢደርስበት አንዷት እሾህ እንኳ ብትወጋውና ብታሰምመው ለርሱ ወንጀሎቹን ማስማሪያና ኃጢአቶቹን ማስሰረያ እንደሚሆንለት የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ገለፁ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. አላህ በአማኝ ባሮቹ ላይ በሚደርስባቸው ትንሽ ጉዳት ምክንያት ወንጀሎችን መማሩ በአማኝ ባሮቹ ላይ ያለው ችሮታና እዝነቱን ይገልፃል።
2. አንድ ሙስሊም የሚደርስበት ችግር ለደረጃው ከፍታና ለወንጀሉ መማሪያ እንዲሆንለት አላህ ዘንድ የሚያገኘውን ምንዳ በማሰብ፤ በትንሹም ሆነ በትልቁ መከራ ሁሉ ሊታገስ ይገባዋል።

(3701)

(٢٨٩) - عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ رضي الله عنه قَالَ: قَالَ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ: «مَا يَزَالُ البَلَاءُ بِالمُؤْمِنِ وَالمُؤْمِنَةِ فِي نَفْسِهِ وَوَلَدِهِ وَمَالِهِ حَتَّى يَلْقَى اللهَ وَمَا عَلَيْهِ خَطِيئَةٌ».
[حسن] - [رواه الترمذي وأحمد]

(289) - ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) እንደተላለፈው እንዲህ ብለዋል፦ «የአሏህ መልዕክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል፡ "አማኝ የሆነ ወንድና ሴት በርሱ ላይ ምንም ወንጀል የሌለበት ሆኖ አላህን እስኪገናኝ ድረስ በነፍሱ፣ በልጁና በገንዘቡ ላይ መከራ ከመከሰት አይወገድም።"» [ሐሰን ነው።] - [ቲርሚዚና አሕመድ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) አማኝ የሆነ ወንድና ሴት ባሪያ ከፈፀማቸው ሁሉም ወንጀሎችና ኃጢዐቶች የፀዳ ሆኖ አላህን እስኪገናኝ ድረስና በነዚህ መከራዎች ሁሉንም ወንጀሎቹን አላህ እስኪምረው ድረስ በነፍሱ (በጤናውና በአካሉ)፣ በልጆቹ (በህመም ወይም ሞት ወይም በነርሱ በመበደል ወይም ከዚህ ውጪ ባሉ በልጆች ሳቢያ በሚደርሱ መከራዎች)፣ በገንዘቡ (በመደኽየት፣ ንግዱን በመክሰር፣ በመሰረቅ፣ በኑሮ መወደድ፣ በሲሳይ መጥበብ) የሚያጋጥመው መከራና ፈተና አይላቀቀውም።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. አላህ ለአማኝ ባሮቹ ካለው እዝነት በዱንያ መከራዎችና ፈተናዎች አማካይነት በዱንያ ላይ እያሉ ወንጀሎቻቸውን ከነርሱ መማሩ ነው።
2. መከራ ብቻውን ወንጀልን ያስምራል ለዚህም አምኖ መገኘት ቅድመ መስፈርቱ ነው። አንድ ባሪያ ከታገሰና ካልተማረረ ይመነዳል።
3. በሚወደውም፣ በሚጠላውም በሁሉም ጉዳዮች በመታገስ ላይ መነሳሳቱን እንረዳለን። የአላህን ምንዳ በመፈለግና ቅጣቱን በመፍራት አላህ ግዴታ ያደረገበትን በአግባቡ በመፈፀምና አላህ ክልክል ያደረገበትን ነገር በመራቅ ላይ መታገስ ይገባዋል።

4. ሐዲሡ ውስጥ "በአማኝ ወንድና ሴት ላይ" የሚለው ንግግር: አማኝ ሴት የሚለው መጨመሩ ለሴቶች ተጨማሪ አፅንዖት ለመስጠት ነው። ያለበለዚያ "አማኝ" ብቻ ቢሉም በዚህ ውስጥ ሴት ትጠቃለል ነበር። ጉዳዩ በወንድ ላይ ብቻ የተገደበ አይደለምና። መከራ በሴት ላይም ቢከሰት ልክ እንደወንዱ ወንጀሏና ኃጢአቷ በመማር ተመሳሳይ ምንዳ ቃል ተገብቶላታል።
5. አንድ ባሪያ በተደጋጋሚ በሚያጋጥሙት ህመሞች ላይ ከሚያቀሉለት ነገሮች አንዱ መከራውን ተከትለው የሚያገኛቸው ትሩፋቶች ናቸው።

(3159)

(٢٩٠) - عَنْ صُهَيْبٍ رضي الله عنه قَالَ: قَالَ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ: «عَجَبًا لِأَمْرِ الْمُؤْمِنِ، إِنَّ أَمْرَهُ كُلَّهُ خَيْرٌ، وَلَيْسَ ذَاكَ لِأَحَدٍ إِلَّا لِلْمُؤْمِنِ، إِنْ أَصَابَتْهُ سَرَّاءُ شَكَرَ، فَكَانَ خَيْرًا لَهُ، وَإِنْ أَصَابَتْهُ ضَرَّاءُ صَبَرَ، فَكَانَ خَيْرًا لَهُ». [صحيح] - [رواه مسلم]

(290) - ከሱሀይብ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: «የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል: "የአማኝ ነገር ይደንቃል። ሁሉ ነገሩ መልካም ነው። ይህም ለአማኝ እንጂ ለሌላ ለአንድም አካል ሊሆን አይችልም። ደስታ በሚያጋጥመው ጊዜ ያመሰግንና ለርሱ መልካም ይሆንለታል። ጉዳት በሚያጋጥመውም ጊዜ ይታገስና ለርሱ መልካም ይሆንለታል።"» [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) አድናቆታዊ በሆነ መልኩ በአማኝ ጉዳይና ሁኔታ ይገረማሉ። ይህም የአማኝ ሁኔታዎች ባጠቃላይ መልካም በመሆናቸው ነው። ይህም ለአማኝ እንጂ ለሌላ አይሆንም። አማኝ የሆነ ሰው ደስታ በሚያጋጥመው ጊዜ በርሱ ላይ አላህን ያመሰግናል። በማመስገኑም ምንዳን ያገኛል። ጉዳት ሲያጋጥመው ደግሞ ይታገሳልም አላህ

ዘንድ ምንዳ አገኝበታለሁ ብሎም ያስባል። በትእግስቱም ምንዳን ያገኛል። ስለዚህ እርሱ በሁሉም ሁኔታዎቹ በምንዳ ላይ ነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. በደስታ ወቅት ማመስገንና በጉዳት ወቅት መታገስ ያለውን ትሩፋት እንረዳለን። ይህንን የፈፀመም በሁለቱም ሀገሮች መልካምን ያገኛል። በፀጋዎች ላይ ያላመሰገነና በመከራዎች ላይ ያልታገሰ ሰው ምንዳም ያመልጠዋል ወንጀልም ይኖርበታል።
2. የኢማንን ደረጃ እንረዳለን። በየትኛውም ሁኔታ ምንዳ ማግኘት ለኢማን ባለቤቶች ካልሆነ በቀር ለማንም አይሆንም።
3. በደስታ ወቅት ማመስገንና በጉዳት ወቅት መታገስ ከአማኞች መገለጫ መካከል አንዱ እንደሆነ እንረዳለን።
4. በአላህ ውሳኔና ፍርድ ማመን አማኝን በሁሉም ሁኔታዎቹ ላይ የተሟላ ውዴታ እንዲኖረው ያደርገዋል። ይህም ከአማኝ ውጪ ካለ ሰው በተቃራኒው ነው። አማኝ ያልሆነ ሰው ጉዳት በሚያጋጥመው ወቅት ዘውታሪ ብስጭት ላይ ይሆናል። ከአላህ የሆኑ ፀጋዎች ባገኘ ወቅትም በፀጋው አላህን በሚወደው ላይ ቀርቶ ጭራሽ አሏህን ለማመፅ ይጠቀምበታል።

(3298)

(٢٩١) - عن أبي موسى الأشعري رضي الله عنه قال: قال رسول الله صلى الله عليه وسلم: «إِذَا مَرِضَ الْعَبْدُ أَوْ سَافَرَ كُتِبَ لَهُ مِثْلُ مَا كَانَ يَعْمَلُ مُقِيمًا صَحِيحًا». [صحيح] - [رواه البخاري]

(291) - አቢ ሙሳ አል-አሽዓሪይ ረዲየሏሁ ዐንሁ እንዲህ ማለታቸው ተላልፏል፡ "የአሏህ መልዕክተኛ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ ብለዋል፡ "አንድ ሰው በታመመ ወይም ጉዞ በወጣ ወቅት ሀገሩ እያለና ጤናማ ሳለ እንደሚያደርገው አጅር ይጻፍለታል።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ስለአሏህ እዝነትና ችሮታ እየነገሩን ነው። ይህም አንድ ሙስሊም በሀገሩ እና ጤነኛ ሳለ ልምድ ያደረገው መልካም ስራ ከዚያም ዑዝር ገጥሞት ታሞ ማድረግ ባይችል፣ ወይም በጉዞ ወይም ደግሞ በሌላ በየትኛውም ትክክለኛ ምክንያት ሳያደርገው ቢቀር ልክ ጤነኛና በሀገሩ ሆኖ ሲያደርግ እንደነበረው ምንዳ ሙሉ ሆኖ ይጻፍለታል።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. አሏህ በባሮቹ ላይ ያለው ችሮታ ስፋቱ፤
2. ጤነኛ በሆንን እና ትርፍ ጊዜ ባገኘንበት አጋጣሚ መልካም ተግባርና ጊዜን በአግባቡ በመጠቀም መበርታት እንደሚገባን እንረዳለን።

(3553)

(٢٩٢) - عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ رضي الله عنه أَنَّ رَسُولَ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ قَالَ: «بَادِرُوا بِالْأَعْمَالِ فِتَنًا كَقِطَعِ اللَّيْلِ الْمُظْلِمِ، يُصْبِحُ الرَّجُلُ مُؤْمِنًا وَيُمْسِي كَافِرًا، أَوْ يُمْسِي مُؤْمِنًا وَيُصْبِحُ كَافِرًا، يَبِيعُ دِينَهُ بِعَرَضٍ مِنَ الدُّنْيَا». [صحيح] - [رواه مسلم]

(292) - ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል: "ሰውዬው አማኝ ሆኖ ያነጋና ከሀዲ ሆኖ የሚያመሽበት፤ ወይም አማኝ ሆኖ ያመሽና ከሀዲ ሆኖ የሚያነጋበት፤ እምነቱንም በአለማዊ ሸቀጥ እስከመሸጥ የሚያደርሱ የድቅድቅ ጨለማ ቁራጭ የመሰሉ ፈተናዎች ከመምጣታቸው በፊት በመልካም ስራ ተቻኮሉ።" [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) መልካም ስራ ከመፈፀም የሚከለክሉና የሚያቅቡ ፈተናና ማምታቻዎች መጥተው መልካም ስራ መስራት ከባድ ከመሆኑ በፊት አማኞች ወደ መልካም ስራ እንዲቻኮሉና እንዲያበዙ አነሳሱ። ይህም ፈተና እንደ ሌሊት ቁራጭ ድቅድቅ ጨለማ በመሆኑ እውነቱ ከሀሰት ጋር ተደበላልቆ ለሰዎች እውነትን ከውሸት መለየት የሚከብድበት ፈተና ነው። ከፈተናዋ መክበድ የተነሳ ሰውዬው አማኝ ሆኖ አንግቶ ከሀዲ ሆኖ እስኪያመሽ፤ አማኝ ሆኖ አምሽቶ ከሀዲ ሆኖ እስኪያነጋና ጠፊ በሆነው አለማዊ ጥቅም ሃይማኖቱን እስኪተው ድረስ ሰዎች ይዋልላሉ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ሃይማኖቱን በአግባቡ ከመተግበር የሚከለክሉ ግርዶሾች ከመምጣታቸው በፊት ሃይማኖትን አጥብቆ መያዝና ወደ መልካም ስራ መቻኮል ግዴታ መሆኑን እንረዳለን።

2. በመጨረሻው ዘመን አጥማሚ ፈተናዎች ተከታትለው እንደሚመጡ መጠቆማቸው። ይህም አንድ ፈተና በተወገደች ቁጥር ሌላ ፈተና ይከተላታል።
3. የሰው ልጅ እምነት በደከመ ጊዜና ለገንዘብም ሆነ ለሌላ ዓለማዊ ጉዳዮች እምነቱን አሳልፎ ከሰጠ ይህ ከእምነቱ ለመጣመም፣ እምነቱን ለመተዉና ከፈተና ጋር አብሮ ለመነዳቱ ሰበብ ይሆንበታል።
4. እዚህ ሐዲሥ ውስጥ መልካም ስራዎች ከፈተና ለመዳን ምክንያት እንደሆኑ ይጠቁማል።
5. ፈተናዎች በሁለት ይከፈላሉ:- አንዱ የማምታቻ (የሹበሃ) ፈተናዎች ሲሆን መፍትሄውም ዕውቀት ነው። ሌላው ደግሞ የዝንባሌ/ ፍላጎት (የሸህዋ) ፈተናዎች ሲሆን መፍትሄውም ኢማንና ትእግስት ነው።
6. ይህ ሐዲሥ ስራው ያነሰ ሰው ፈተና ወደርሱ በፍጥነት እንደሚመጣና ስራው የበዛ ሰው ደግሞ በሰራው ስራ (ተመፃድቆ) መሸወድ እንደማይገባውና ይልቁንም ጨምሮ ማብዛት እንዳለበት ይጠቁማል።

(3138)

(٢٩٣)- عن معاوية رضي الله عنه قال: سمعت النبي صلى الله عليه وسلم يقول: «مَنْ يُرِدِ اللهُ بِهِ خَيْرًا يُفَقِّهْهُ فِي الدِّينِ، وَإِنَّمَا أَنَا قَاسِمٌ، وَاللهُ يُعْطِي، وَلَنْ تَزَالَ هَذِهِ الْأُمَّةُ قَائِمَةً عَلَى أَمْرِ اللهِ، لَا يَضُرُّهُمْ مَنْ خَالَفَهُمْ، حَتَّى يَأْتِيَ أَمْرُ اللهِ». [صحيح] - [متفق عليه]

(293) - ከሙዓዊያህ -አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንዲህ ሲሉ ሰምቻዋለሁ:- "አላህ ለእርሱ መልካምን የሻለትን ሰው ሃይማኖቱን ያስገነዝበዋል። እኔ አከፋፋይ ብቻ ነኝ አላህ ነው የሚሰጠው። ይህች ኡማህ በአላህ ትእዛዝ ላይ የቆመች ከመሆን አትወገድም! የአላህ ትእዛዝ እስክትመጣ ድረስም የተቃረናቸው ሁሉ አይጎዳቸውም።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

አላህ ለእርሱ መልካምን የሻለት ሰው ሃይማኖቱን መገንዘብ እንደሚቸረው፤ ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም አላህ ከሰጣቸው ሲሳይ፣ ዕውቀትና ሌሎችም ነገሮች የሚያከፋፍሉና የሚያሰራጩ አከፋፋይ ብቻ እንጂ ትክክለኛው ሰጪ አላህ ብቻ ነው። ከሱ ውጪ ያሉት ከሰበብነት የዘለለ ከርሱ ፈቃድ ውጪ እንደማይጠቅሙ፤ ይህ ኡማህ በአላህ ትእዛዝ ላይ ከመቆም እንደማይወገድና ትንሳኤ እስከሚቆም ድረስም የተፃረራቸው እንደማይጎዳቸው ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ተናገሩ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ሸሪዐዊ ዕውቀት እና እርሱን መማር ያለው ትሩፋት ትልቅ መሆኑንና በርሱም ላይ መነሳሳቱን ተረድተናል፤
2. በእዚህ ኡማህ ውስጥ በእውነት ላይ የሚቆም መኖሩ የማይቀር ጉዳይ መሆኑን፤ ከእውነተኛ መንገድ አንዱ ሲገለል ሌላው በእውነት ላይ ይቆማል።
3. ሃይማኖትን መገንዘብ አላህ ለባሪያው መልካም ከመሻቱ የሚመደብ መሆኑን ፤
4. ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም የሚሰጡት በአላህ ትእዛዝና ፍላጎት ብቻ መሆኑንና ያለርሱ ፈቃድ አንድም ነገር ማድረግ እንደማይችሉ ተረድተናል።

(5518)

(٢٩٤) - عَنْ جَابِرِ بْنِ عَبْدِ اللهِ رضي الله عنهما أَنَّ النَّبِيَّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ قَالَ: «لَا تَعَلَّمُوا الْعِلْمَ لِتُبَاهُوا بِهِ الْعُلَمَاءَ، وَلَا لِتُمَارُوا بِهِ السُّفَهَاءَ، وَلَا تَخَيَّرُوا بِهِ الْمَجَالِسَ، فَمَنْ فَعَلَ ذَلِكَ، فَالنَّارُ النَّارُ». [صحيح] - [رواه ابن ماجه]

(294) - ከጃቢር ቢን ዐብደላህ -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ ብለዋል፦ "ዕውቀትን ዑለሞችን ልትፎካከሩበት (በሊቃውንት ፊት ለመታየት)፣ ቂሎችን ልትሟገቱበት፣ በመድረኮች ላይ ቅድሚያ እንድትመረጡበት በማለም እንዳትቀስሙ። ይህን የፈፀመ (ለርሱ) እሳት አለው እሳት አለው።" [ሶሒሕ ነው።] - [ኢብኑ ማጀህ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ዑለሞችን ለመወዳደርና ለመፎካከር፣ እኔ እንደናንተው ዓሊም ነኝ የሚለውን ለማሳየት ወይም ቂሎችንና ደካማ ግንዛቤ ያላቸውን ልትሟገቱና ልታናግሩ ወይም በመድረኮች ግንባር ቀደም ለመሆንና ከሌላው ቅድሚያ እንዲሰጠው በማለም ዕውቀት ከመፈለግ ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን አስጠነቀቁ። ይህን የፈፀመ ሰው፤ ለአላህ ብሎ ዕውቀት በመፈለግ ላይ እሱ ለይዩልኝና ያለ ኢኽላስ በመስራቱ እሳት ይገባዋል።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ዕውቀትን ሊፎካከርበት ወይም ሊሟገትበት ወይም በመድረኮች ቅድሚያ እንዲሰጠውና ለመሳሰሉት አላማዎች የተማረ ሰው በእሳት እንደተዛተበት፤
2. ዕውቀትን ለሚማርና ለሚያስተምር ሰው ኒያን ማጥራት አንገብጋቢነት ፤
3. ኒያ የሥራ መሰረት መሆኑንና ምንዳም በኒያ ላይ የተመረኮዘ መሆኑን ተረድተናል።

(65047)

(٢٩٥) - عن عثمان رضي الله عنه عن النبي صلى الله عليه وسلم قال: «خَيْرُكُمْ مَنْ تَعَلَّمَ الْقُرْآنَ وَعَلَّمَهُ». [صحيح] - [رواه البخاري]

(295) - ከዑስማን -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንዲህ አሉ: "ከናንተ መካከል በላጬ ቁርአንን ተምሮ ያስተማረ ሰው ነው።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ከሙስሊሞች መካከል በላጬና አላህ ዘንድ ከፍተኛ ደረጃ ያለው ቁርአን ማንበብን፣ መሸምደድን፣ ማሳመርን፣ መገንዘብንና ማብራራትን የተማረና እርሱ ዘንድ ያለውን የቁርአን እውቀት ከመተግበሩም ጋር ለሌላው ያስተማረ መሆኑን ተናገሩ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. የቁርአን ልቅና መገለፁ። ቁርአን የአላህ ቃል ስለሆነ ምርጡ ቃል ነው።
2. ምርጥ ተማሪ ማለት ሌላውንም የሚያስተምር እንጂ በነፍሱ ላይ የሚገደብ አይደለም።
3. ቁርአንን መማርና ማስተማሩ ማንበቡንም፣ ትርጉሙንም ህግጋቱንም ያካትታል።

(5913)

(٢٩٦) - عَنْ أَبِي عَبْدِ الرَّحْمَنِ السُّلَمِي رحمه الله قَالَ: حَدَّثَنَا مَنْ كَانَ يُقْرِئُنَا مِنْ أَصْحَابِ النَّبِيِّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ أَنَّهُمْ كَانُوا يَقْتَرِئُونَ مِنْ رَسُولِ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ عَشْرَ آيَاتٍ، فَلَا يَأْخُذُونَ فِي الْعَشْرِ الْأُخْرَى حَتَّى يَعْلَمُوا مَا فِي هَذِهِ مِنَ الْعِلْمِ وَالْعَمَلِ، قَالُوا: فَعَلِمْنَا الْعِلْمَ وَالْعَمَلَ.
[حسن] - [رواه أحمد]

(296) - አቢ ዐብዲረሕማን አስሱለሚይ አላህ ይዘንላቸው እንዲህ አሉ፦ ከነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ሰሐቦች መካከል ቁርኣን ያስተምረን የነበረ አንድ ሰሐባ "ሶሀቦች ከአላህ መልክተኛ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን አስር የቁርኣን አንቀፆችን ተምረው በተማሩት አንቀፆች ውስጥ ያለውን ዕውቀትና ተግባር ሳይረዱ ሌላ ተጨማሪ አስር አንቀፆችን አይማሩም ነበር። በዚህም "ዕውቀትንም ተግባርንም ተማርን" አሉ።" ብሎ ነገረን። [ሐሰን ነው።] - [አሕመድ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ሰሐቦች -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- ከአላህ መልክተኛ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን አስር የቁርኣን አንቀፆችን ይቀስሙ ነበር። በቀሰሙት አስር አንቀፆች ውስጥ ያለውን ዕውቀት እስኪረዱና እሱን ሳይተገብሩ ወደ ሌላ እውቀት አይሸጋገሩም ነበር።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. የሰሐቦች -አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና- ደረጃና ቁርኣንን የመማር ጉጉታቸውን፤
2. ቁርኣንን መማር የሚባለው በመረዳትና ውስጡ ባለው በመተግበር ነው እንጂ በማንበቡና በመሸምደዱ ብቻ አይደለም።
3. ዕውቀት ከንግግርና ከተግባር በፊት እንደሆነ ተረድተናል።

(65058)

(٢٩٧) - عن عبد الله بن مسعود رضي الله عنه قال: قال رسول الله صلى الله عليه وسلم: «مَنْ قَرَأَ حَرْفًا مِنْ كِتَابِ اللهِ فَلَهُ بِهِ حَسَنَةٌ، وَالْحَسَنَةُ بِعَشْرِ أَمْثَالِهَا، لَا أَقُولُ {الم} حَرْفٌ، وَلَكِنْ {أَلِفٌ} حَرْفٌ، وَ{لَامٌ} حَرْفٌ، وَ{مِيمٌ} حَرْفٌ». [حسن] - [رواه الترمذي]

(297) - ከዐብደላህ ቢን መስዑድ -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: "የአላህ መልክተኛ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንዲህ ብለዋል: 'ከአላህ መጽሐፍ አንዲትን ፊደል የቀራ ሰው ለርሱ አንዲት ምንዳ ይሰጠዋል። አንዲት ምንዳ ደግሞ በአስር አምሳያዋ (ትባዛለች።) (ይሄንን ስል) {አሊፍ ላም ሚም} አንድ ፊደል ነው እያልኩ አይደለም። ነገር ግን {አሊፍ} አንድ ፊደል ነው። {ላም} አንድ ፊደል ነው። {ሚም} አንድ ፊደል ነው።'" [ሐሰን ነው።] - [ቲርሚዚ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ማንኛውም ከአላህ መጽሐፍ አንድ ፊደል የሚቀራ ሙስሊም ለርሱ ምንዳ እንዳለውና አንዱ ምንዳ ደግሞ ለርሱ በአምሳያው እስከ አስር ድረስ እንደሚባዛለት ተናገሩ።

ከዚያም ይህንን ({አሊፍ ላም ሚም} አንድ ፊደል ነው እያልኩ አይደለም። ነገር ግን {አሊፍ} አንድ ፊደል ነው። {ላም} አንድ ፊደል ነው። {ሚም} አንድ ፊደል ነው።) በሚለው ንግግራቸው ሶስት ፊደል እንደሚሆኑና ሰላሳ ምንዳ እንደሚሆኑ ገለፁ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ቁርአን ማንበብ በማብዛት ላይ መነሳሳቱን እንረዳለን።
2. አንድ ቁርአን አንባቢ የሚያነባቸው ሁሉም ቃላት ውስጥ የሚገኙ ፊደላት በአስር አምሳያቸው የሚባዙ የሆኑ ምንዳዎች አሉት።
3. አላህ ለባሮቹ በራሱ ቸርነት ምንዳዎችን ማባዛቱ የርሱ እዝነትና ቸርነት ሰፊ መሆኑን ያስረዳናል።

4. ቁርአን ከሌሎች ንግግሮች በላይ ያለውን ብልጫና ማንበቡም አላህን ማምለኪያ መሆኑን እንረዳለን። ይህም እርሱ የአላህ ቃል ስለሆነ ነው።

(6275)

(٢٩٨) - عن عبد الله بن عمرو رضي الله عنهما قال: قال رسول الله صلى الله عليه وسلم: «يقالُ لصاحبِ القرآن: اقرَأ وارتَقِ، ورتِّل كما كُنْتَ ترتِّل في الدُنيا، فإن منزِلَكَ عندَ آخرِ آية تقرؤها».
[حسن] - [رواه أبو داود والترمذي والنسائي في الكبرى وأحمد]

(298) - ዐብደላህ ቢን ዐምር -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንዲህ አሉ፦ የአላህ መልክተኛ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ ብለዋል፦ "ለቁርኣን ባለቤት "አንብብ! (ደረጃን) ውጣ! በዱንያ ውስጥ አሳምረህ ታነብ እንደነበርከው አሳምረህ አንብብ! (ጀነት ውስጥ) ያንተ ስፍራ የምታነበው የመጨረሻው አንቀፅ ዘንድ ነው።" ይባላል።" [ሐሰን ነው።] - [አቡዳውድ፣ ቲርሚዚ፣ ነሳኢ በኩብራ፣ አሕመድ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ቁርኣንን ለሚያነብ፣ ቁርኣን ውስጥ ባለው ለሚሰራ፣ በቃሉ መሸምደድንም ሆነ አሳምሮ ማንበብን አጥብቆ የያዘ ጀነት በሚገባ ጊዜ "ቁርኣንን አንብብ! በዚህም ሰበብ የጀነት ደረጃዎችን ውጣ! ቁርኣንን በስክነትና እርጋታ ዱንያ ላይ ታነበው እንደነበርከው አንብብ! ያንተ ስፍራ የምታነበው የመጨረሻው አንቀፅ ዘንድ ነው።" ይባላል በማለት ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ተናገሩ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. በቁጥርም ሆነ በሁኔታ ለሥራችን በሚመጥን መልኩ ነው የምንመነዳው።
2. ቁርኣንን በማንበብ፣ አሳምሮ መቅራት፣ በመሸምደዱ፣ በማስተንተኑና በቁርኣን በመስራት ላይ መበረታታቱ።
3. ጀነት በርካታ ደረጃዎችና እርከኖች ያሏት ሲሆን የቁርኣን ባለቤት የሆነ ሰው ከፍተኛ የሆነውን ደረጃ ነው የሚያገኘው።

(65054)

(٢٩٩) - عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ رضي الله عنه قَالَ: قَالَ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ: «أَيُحِبُّ أَحَدُكُمْ إِذَا رَجَعَ إِلَى أَهْلِهِ أَنْ يَجِدَ فِيهِ ثَلَاثَ خَلِفَاتٍ عِظَامٍ سِمَانٍ؟» قُلْنَا: نَعَمْ. قَالَ: «فَثَلَاثُ آيَاتٍ يَقْرَأُ بِهِنَّ أَحَدُكُمْ فِي صَلَاتِهِ خَيْرٌ لَهُ مِنْ ثَلَاثِ خَلِفَاتٍ عِظَامٍ سِمَانٍ». [صحيح] - [رواه مسلم]

(299) - አቡ ሁረይራ -አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና- እንዲህ አሉ፦ የአላህ መልክተኛ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ አሉ፦ "አንዳችሁ ወደ ቤተሰቡ የተመለሰ ጊዜ ሶስት ትላልቅ የሰቡ እርጉዝ ግመሎችን ቢያገኝ ያስደስተዋልን?" እኛም "አዎን" አልን። እሳቸውም "አንዳችሁ በሰላቱ ውስጥ የሚያነባቸው ሶስት አንቀፆች ከሶስት ትላልቅ የሰቡ እርጉዝ ግመሎች ለሱ የተሻሉ ናቸው።" አሉ። [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ሰላት ውስጥ ሶስት አንቀፆችን በማንበብ የሚገኘው ምንዳ አንድ ሰው ቤቱ ውስጥ ሶስት የሰቡ ትላልቅ እርጉዝ ግመሎችን ከሚያገኝ እንደሚበልጥ ገለፁ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ሰላት ውስጥ ቁርኣን የማንበብ ትሩፋት መገለፁ፤
2. መልካም ሥራዎች ከጠፊዋ ዱንያ መጣቀሚያ የተሻሉና ዘውታሪዎች መሆናቸውን፤
3. ይህ ትሩፋት ሦስት አንቀፆችን በማንበብ ብቻ የተገደበ አይደለም። ሰጋጁ ሰላቱ ውስጥ የሚያነባቸውን አንቀፆች በጨመረ ቁጥር የሚያገኘው ምንዳ ለሱ በሚያነባቸው ቁጥር ልክ የእርጉዝ ግመሎች ከሚሰጠው የተሻለ ነው።

(65053)

(٣٠٠) - عن أبي موسى الأشعري رضي الله عنه عن النبي صلى الله عليه وسلم قال: «تَعَاهَدُوا هَذَا الْقُرْآنَ، فَوَالَّذِي نَفْسُ مُحَمَّدٍ بِيَدِهِ لَهُوَ أَشَدُّ تَفَلُّتًا مِنَ الْإِبِلِ فِي عُقُلِهَا». [صحيح] - [متفق عليه]

(300) - ከአቡ ሙሳ አልአሽዐሪይ -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንዲህ አሉ: "ይህንን ቁርአን ተጠባበቁት! የሙሐመድ ነፍስ በእጁ በሆነችው ጌታ እምላለሁ እርሱ (ቁርአን) ግመል ከታሰረችበት (ፈታ) ከምታመልጠው የበለጠ በጣም የሚያመልጥ ነው።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም አንድ ሰው ቁርአንን በልቡ ከሸመደደው በኋላ እንዳይረሳው ቁርአንን በመጠባበቅና በማንበቡ ላይ መዘውተርን አዘዙ። ቁርአን ከልብ ውስጥ ከታሰረች ግመል የበለጠ እጅግ የሚጠፋና የሚወገድ መሆኑን ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም በመሀላቸው በማጠናከር ገለፁ። ግመል በክንዶቿ መሀል በገመድ ተጠፍራ ስታበቃ ሰውዬው ከተጠባበቃት ይይዛታል፤ ከለቀቃት ግን ትሄዳለችም ትጠፋለችም።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ቁርአንን የሸመደደ ሰውም ቁርአንን በማንበቡ ላይ በየጊዜው ከዘወተረ ልቡ ውስጥ እንደተጠበቀ ይቀራል። ያለበለዚያ ግን ይጠፋበታልም ይረሳዋልም።
2. ቁርአንን ከመጠባበቅ ጥቅሞች መካከል ምንዳና አጅርን ማግኘትና የትንሳኤ ቀን ከፍተኛ ደረጃን መጎናፀፍ ነው።

(5907)

(٣٠١) - عن أبي هريرة رضي الله عنه: أن رسول الله صلى الله عليه وسلم قال: «لَا تَجْعَلُوا بُيُوتَكُمْ مَقَابِرَ، إِنَّ الشَّيْطَانَ يَنْفِرُ مِنَ الْبَيْتِ الَّذِي تُقْرَأُ فِيهِ سُورَةُ الْبَقَرَةِ». [صحيح] - [رواه مسلم]

(301) - ከአቡ ሁረይራ -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው የአላህ መልክተኛ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንዲህ አሉ: "ቤቶቻችሁን መቃብር አታድርጉ። ሰይጣን የበቀራህ ምእራፍ የሚቀራበት ቤትን ይሸሻል።" [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ቤቶችን ከሶላት አራቁቶ እንደመቃብር የማይሰገድበት ማድረግን ከለከሉ።

በመቀጠልም ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ሰይጣን የበቀራህ ምእራፍ ከሚቀራበት ቤት እንደሚሸሽ ተናገሩ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ቤት ውስጥ ሱና ሶላቶችን የመሰሉ አምልኮዎችን ማብዛት እንደሚወደድ እንረዳለን።
2. ወደ ሺርክና በተቀባሪው ላይ ወሰን ወደ ማለፍ ከሚያዳርሱ መንገዶች አንዱ ስለሆነ ከጀናዛ ሶላት በስተቀር መቃብር ግቢ ውስጥ ሶላት መስገድ አይፈቀድም።
3. መቃብር ዘንድ መስገድ መከልከሉ ሶሐቦች ዘንድ የተረጋገጠ ጉዳይ ስለሆነ ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ቤቶችን ልክ እንደመቃብር የማይሰገድባቸው ከማደረግ ከለከሉ።

(6208)

(٣٠٢) - عَنْ أُبَيِّ بْنِ كَعْبٍ رضي الله عنه قَالَ: قَالَ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ: «يَا أَبَا الْمُنْذِرِ، أَتَدْرِي أَيُّ آيَةٍ مِنْ كِتَابِ اللهِ مَعَكَ أَعْظَمُ؟» قَالَ: قُلْتُ: اللهُ وَرَسُولُهُ أَعْلَمُ. قَالَ: «يَا أَبَا الْمُنْذِرِ، أَتَدْرِي أَيُّ آيَةٍ مِنْ كِتَابِ اللهِ مَعَكَ أَعْظَمُ؟» قَالَ: قُلْتُ: {اللهُ لا إِلَهَ إِلا هُوَ الْحَيُّ الْقَيُّومُ} [البقرة: 255]. قَالَ: فَضَرَبَ فِي صَدْرِي، وَقَالَ: «وَاللهِ لِيَهْنِكَ الْعِلْمُ، أَبَا الْمُنْذِرِ».

[صحيح] - [رواه مسلم]

(302) - ኡበይ ቢን ከዕብ -አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸው- እንዲህ ብለዋል፦ የአላህ መልክተኛ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ ብለዋል፦ "አቡ ሙንዚር ሆይ! ከአላህ መጽሐፍ ከሸመደድከው ውስጥ ማንኛው አንቀፅ ታላቅ እንደሆነ ታውቃለህን?" "አላህና መልክተኛው ያውቃሉ።" አልኳቸው። " እርሳቸውም በድጋሚ "አቡ ሙንዚር ሆይ! ከአላህ መጽሐፍ ከሸመደድከው ማንኛው አንቀፅ ታላቅ እንደሆነ ታውቃለህን?" አሉኝ። "{አላህ ከእርሱ በቀር በእውነት የሚመለክ አምላክ የለም። ህያው ራሱን ቻይ ነው።} [አልበቀራህ: 255]" (አያተል ኩርሲይ) አልኩኝ። እሳቸውም ደረቴን በመምታት "በአላህ እምላለሁ! እውቀት ያስደስትህ አቡ ሙንዚር!" አሉኝ።

[ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ኡበይ ቢን ከዕብን የአላህ መጽሐፍ ውስጥ ትልቁ አንቀፅ ማን ናት? በማለት ጠየቁት። መልስ ለመስጠት ካመነታ በኋላ አየቱል ኩርሲይ ናት {አላህ ከእርሱ በቀር በእውነት የሚመለክ አምላክ የለም። ህያው ራሱን ቻይ ነው።} በማለት መለሰ። ነቢዩም የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን በዕውቀትና ጥበብ የተሞላ መሆኑን ለመጠቆም ደረቱን በመምታት በዚህ ዕውቀት እንዲደሰትና እንዲገራለት ዱዐ በማድረግ ትክክለኛ መልስ እንደመለሰ በመጥቀስ አበረታቱት።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. የኡበይ ቢን ከዕብ -አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸው- ትልቅ ደረጃ፤
2. አየቱል ኩርሲይ በአላህ መጽሐፍ ውስጥ ትልቋ አንቀፅ በመሆኗ መሸምደዱ፣ ትርጉሙን ማስተንተኑና እርሱን መተግበር ተገቢ ነው።

(65059)

(٣٠٣) - عن أبي مسعود رضي الله عنه قال: قال النبي صلى الله عليه وسلم: «مَنْ قَرَأَ بِالْآيَتَيْنِ مِنْ آخِرِ سُورَةِ الْبَقَرَةِ فِي لَيْلَةٍ كَفَتَاهُ». [صحيح] - [متفق عليه]

(303) - ከአቢ መስዑድ -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው እንዲህ ብለዋል: "ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንዲህ ብለዋል: "በምሽት ውስጥ የመጨረሻዎቹን የበቀራህ ምእራፍ ሁለት አንቀፆች የቀራ ሰው ይበቁታል።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም በምሽት ውስጥ የበቀራህ ምእራፍ የመጨረሻዎቹን ሁለት አንቀፆች የቀራ ሰው አላህ መጥፎና ጎጂ ከሆኑ ነገሮች እንደሚበቃው ተናገሩ። ለሌሊት ሶላት ከመቆም ይበቁታል ማለት ነውም ተብሏል። ሌሎች ውዳሴዎችን ከማለት ይበቁታል ማለት ነውም ተብሏል። ለሌሊት ሶላት የሚቀራ ዝቅተኛው በቂ የቁርአን አንቀፆች ናቸውም ተብሏል። ከዚህም ውጪ ተብሏል። ምንአልባት ሁሉም ከላይ የተጠቀሱትን ትርጓሜዎችን ቃሉ ስለሚሰበስባቸው ሁሉም ትክክለኛ ትርጓሜ ሊሆኑ ይችላሉ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. የሱረቱል በቀራህ የመጨረሻ አንቀፆች ትሩፋት መገለፁ። እሱም { አመነ አርረሱሉ ...} ከሚለው የአላህ ንግግር እስከምእራፉ መጨረሻ ያለውን ነው።
2. የበቀራህ ምእራፍ መጨረሻዎች ምሽት ላይ ለሚቀራቸው ሰው ከጉዳት፣ ከመጥፎና ከሰይጣን ይከላከላሉ።
3. ምሽት ፀሃይ በመግባት ጀምሮ ጎህ በመውጣቱ ይጠናቀቃል።

(6274)

(٣٠٤) - عن النعمان بن بَشِير رضي الله عنه قال: سمعت النبيَّ صلى الله عليه وسلم يقول: «الدُّعَاءُ هُوَ الْعِبَادَةُ»، ثُمَّ قَرَأَ: «{وَقَالَ رَبُّكُمُ ادْعُونِي أَسْتَجِبْ لَكُمْ إِنَّ الَّذِينَ يَسْتَكْبِرُونَ عَنْ عِبَادَتِي سَيَدْخُلُونَ جَهَنَّمَ دَاخِرِينَ} [غافر: 60]». [صحيح] - [رواه أبو داود والترمذي وابن ماجه وأحمد]

(304) - ከኑዕማን ቢን በሺር -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: "ነቢዩን ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንዲህ ሲሉ ሰምቻለሁ: 'ዱዓእ እሱ አምልኮ ነው።' ከዚያም {ጌታችሁም አለ "ለምኑኝ እቀበላችኋለሁና። እነዚያ እኔን ከመግገዛት የሚኮሩት ተዋራጆች ሆነው ገሀነምን በእርግጥ ይገባሉ።"} [ጋፊር: 60] የሚለውን አነበቡ።" [ሶሒሕ ነው።] - [አቡዳውድ፣ ቲርሚዚ፣ ኢብኑማጀህና አሕመድ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ዱዓእ አምልኮ እንደሆነ ተናገሩ። በዱንያና በአኺራዊ ጉዳዮች የሚጠቅመውን ነገር እንዲሰጠውና የሚጎዳውን ነገር እንዲከላከልለት አላህ የሚጠየቅበት ልመናዊ ዱዓም ይሁን፤ ማንኛውም ውጫዊና ውስጣዊ ንግግርም ተግባርም አላህ የሚወዳቸውና የሚያስደስተው ልባዊ፣ አካላዊና ገንዘባዊ አምልኮዎችን የሚያደርጉበት አምልኳዊ ዱዓእም ያው ነው። እነዚህ የዱዓእ አይነቶችም ለአላህ ብቻ ጥርት ተደርገው መፈፀማቸው ግዴታ ነው።

ከዚያም ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ለዚህ ንግግራቸው የአላህን ንግግር ማስረጃ አደረጉ። አላህ እንዲህ ብሏል፡- {ጌታችሁም አለ "ለምኑኝ እቀበላችኋለሁና። እነዚያ እኔን ከመግገዛት የሚኮሩት ተዋራጆች ሆነው ገሀነምን በእርግጥ ይገባሉ።"}

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ዱዓእ የአምልኮ መሰረት በመሆኑ ከአላህ ውጪ ለሆነ መስጠት አይፈቀድም።
2. ዱዓእ እውነተኛ ባርነትን፣ የጌታን መብቃቃትና ችሎታ እውቅና መስጠትን እና የባሪያን ወደ አላህ ፈላጊነቱን ያካተተ ነው።
3. ከአላህ አምልኮ በመኩራትና ዱዓእን በመተው ምንዳ ዙሪያ ብርቱ ዛቻ መምጣቱን እንረዳለን። አላህን ከመለመን የሚኮሩ ሰዎች ጀሀነም የተናነሱና የተዋረዱ ሆነው ይገባሉ።

(5496)

(٣٠٥) - عن عائشة رضي الله عنها قالت: كَانَ النَّبِيُّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ يَذْكُرُ اللهَ عَلَى كُلِّ أَحْيَانِهِ.

[صحيح] - [رواه مسلم]

(305) - ከእናታችን ዓኢሻህ -አላህ መልካም ስራዋን ይውደድላትና- እንደተላለፈው እንዲህ አለች: "ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም በሁሉም ሁኔታቸው አላህን ያወሱ ነበር።" [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

የአማኞች እናት ዓኢሻህ -አላህ መልካም ስራዋን ይውደድላትና- ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም አላህን በማውሳት ላይ እጅግ ጉጉ እንደነበሩና በሁሉም ወቅት፣ ስፍራና ሁኔታ ላይ ሆነውም አላህን ያወሱ እንደነበር ተናገረች።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. አላህን ለማውሳት ከትንሹም ሆነ ከትልቁ ሐደሥ መፅዳት መስፈርት አይደለም።
2. ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም አላህን በማውሳት ላይ ዘውታሪ እንደነበሩ እንረዳለን።
3. መፀዳዳትን በመሰለ አላህን ማውሳት በሚከለከልባቸው ሁኔታዎች ካልሆነ በስተቀር ነቢዩን ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ከመከተል አኳያ በሁሉም ሁኔታ ላይ አላህን ማውሳት በማብዛት ላይ መነሳሳቱን እንረዳለን።

(8402)

(٣٠٦) - عن أبي هريرة رضي الله عنه عن النبي صلى الله عليه وسلم قال: «لَيْسَ شَيْءٌ أَكْرَمَ عَلَى اللهِ تَعَالَى مِنَ الدُّعَاءِ». [حسن] - [رواه الترمذي وابن ماجه وأحمد]

(306) - ከአቡ ሁረይራ -አላህ መልካምስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ ብለዋል: "ከዱዓእ የበለጠ አላህ ዘንድ የተከበረ አንዳችም ነገር የለም።" [ሐሰን ነው።] - [ቲርሚዚ፣ ኢብኑ ማጀህና አሕመድ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ከአምልኮዎች መካከል ከዱዓእ የበለጠ አላህ ዘንድ እጅግ በላጭ የሆነ አምልኮ አንድም እንደሌለ ገለፁ። ምክንያቱም ዱዓእ የአላህን መብቃቃት፣ የባሪያን ደካማነትና ፈላጊነት እውቅና መስጠትን ውስጡ ይዟልና ነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. የዱዓእን ትሩፋት እንረዳለን። አላህን የለመነ ሰው አላህን እያላቀ፣ የሌለው አይከጀልምና ጥራት የተገባው አምላክ እጅግ የተብቃቃ መሆኑን፣ ደንቆሮ አይለመንምና እጅግ ሰሚ መሆኑን፣ ስስታም አይለመንምና ቸር መሆኑን፣ ልበደረቅ አይለመንምና አዛኝ መሆኑን፣ ደካማ አይለመንምና ቻይ

መሆኑን፣ ሩቅ ያለ አይሰማምና ቅርብ መሆኑን እና ሌሎችም የልቅናና የምሉዕነት መገለጫዎችን ለአሏህ እያረጋገጠ ነው።

(5509)

(٣٠٧) - عَنْ أَنَسٍ رضي الله عنه قَالَ: كَانَ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ يُكْثِرُ أَنْ يَقُولَ: «يَا مُقَلِّبَ القُلُوبِ ثَبِّتْ قَلْبِي عَلَى دِينِكَ»، فَقُلْتُ: يَا رَسُولَ اللهِ، آمَنَّا بِكَ وَبِمَا جِئْتَ بِهِ فَهَلْ تَخَافُ عَلَيْنَا؟ قَالَ: «نَعَمْ، إِنَّ القُلُوبَ بَيْنَ أُصْبُعَيْنِ مِنْ أَصَابِعِ اللهِ يُقَلِّبُهَا كَيْفَ يَشَاءُ».

[صحيح] - [رواه الترمذي وأحمد]

(307) - ከአነስ (ረዲየላሁ ዐንሁ) -አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው እንዲህ ብለዋል፦ «የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) "ያ ሙቀሊበል ቁሉብ ሠቢት ቀልቢ ዐላ ዲኒክ" (አንተ ልቦናን ገለባባጭ የሆንክ ጌታ ሆይ! ልቤን በሃይማኖትህ ላይ አፅናት) ማለትን ያበዙ ነበር። እኔም "የአላህ መልክተኛ ሆይ! በርሶና ይዘውት በመጡት ሃይማኖት አምነናል። በኛ ላይ የሚፈሩልን ጉዳይ አለ ማለት ነው?" አልኳቸው። እርሳቸውም "አዎን ልቦች በአላህ ሁለት ጣቶች መካከል ናቸው። እንደፈለገው ይገለባብጣታል።" አሉኝ።» [ሶሒሕ ነው።] - [ቲርሚዚና አሕመድ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

አብዛኛው የነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ዱዓ በኢስላምና በአምልኮ ላይ መፅናትንና ከጥመት መራቅን አላህን የሚጠይቁበት ነበር። አነስ ቢን ማሊክም (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ይህን ዱዓ በማብዛታቸው ተደነቀ። ነቢዩም (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ልቦች ከአላህ ጣቶች መካከል በሁለቱ ጣቶች መሀል እንደሆኑና እንደፈለገም እንደሚያገለባብጣቸው ነገሩት። ቀልብ የኢማንና ክህደት መኖሪያ ናት። ቀልብ ቀልብ ተብሎ የተሰየመው በብዛት ስለሚገለባበጥ ነው። ቀልብ ድስት በሚንተከተክ ጊዜ ከሚገለባበጠው በላይ ይገለባበጣል። አላህ ለሻለት

ሰው ቀልቡን በቀናው መንገድ ላይና በኢስላም ላይ ያፀናለታል። አላህ ጥመት የሻለትን ሰው ደግሞ ቀልቡን ከቀናው መንገድ ወደ ጥመት ያዞርበታል።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ለጌታቸው ያላቸው መዋደቅና መተናነስን እንዲሁም ኡመታቸውም ይህንን ጥያቄ እንዲጠይቁ መጠቆማቸውን እንረዳለን።
2. በኢስላም ላይ የመፅናትና ቀጥ የማለት አንገብጋቢነቱን እንረዳለን። ዋናው በታ የሚሰጠውም ፍፃሜያችን ነው።
3. አንድ ባሪያ በኢስላም ላይ መፅናትን ከአላህ ከመፈለግ ለአይን ጨረፍታ ያህል እንኳ አይብቃቃም።
4. ነቢዩን (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ተከትለን ይህንን ዱዓ በማብዛት ላይ መነሳሳቱን እንረዳለን።
5. በእስልምና ላይ መፅናት አንድ ባሪያ ሊለፋለት የሚገባና በርሱም ጌታውን ሊያመሰግንበት የሚገባ ትልቁ ፀጋ ነው።

(3142)

(٣٠٨) - عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ رضي الله عنه قَالَ: كَانَ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ يَقُولُ: «اللهُمَّ أَصْلِحْ لِي دِينِي الَّذِي هُوَ عِصْمَةُ أَمْرِي، وَأَصْلِحْ لِي دُنْيَايَ الَّتِي فِيهَا مَعَاشِي، وَأَصْلِحْ لِي آخِرَتِي الَّتِي فِيهَا مَعَادِي، وَاجْعَلِ الْحَيَاةَ زِيَادَةً لِي فِي كُلِّ خَيْرٍ، وَاجْعَلِ الْمَوْتَ رَاحَةً لِي مِنْ كُلِّ شَرٍّ».

[صحيح] - [رواه مسلم]

(308) - ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: «የአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና እንዲህ ይሉ ነበር: "አልላሁመ አስሊሕ ሊ ዲኒለዚ ሁወ ዒስመቱ አምሪ ወአስሊሕ ሊ ዱንያየለቲ ፊሃ መዓሺ፣ ወአስሊሕ ሊ አኺረቲለቲ ፊሃ መዓዲ፣ ወጅዐሊል ሐያተ ዚያደተን ሊ ፊ ኩሊ ኸይር፣ ወጅዐሊል መውተ ራሐተን ሊ ሚን ኩሊ ሸር"»

ትርጉሙም "አላህ ሆይ! የነገሮቼ መጠበቂያ የሆነውን ሃይማኖቴን አስተካክልልኝ። በውስጧ ኑሮዬ የሆነውን ዱንያዬንም አስተካክልልኝ። መመለሻዬ የሆነውን የመጨረሻውን አለምም አስተካክልልኝ። ህይወቴን ሁሉንም መልካም ነገር የምጨምርበት አድርገው። ሞቴንም ከሁሉም መጥፎ ነገር የማርፍበት አድርገው።" ማለት ነው። [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ለመሙላት የተላኩለት የሆነውን የመልካም ስነምግባር መሰረቶችን የሰበሰበች ዱዓ አደረጉ። እነርሱም: የሃይማኖት፣ የዱንያና የመጨረሻው አለም መስተካከል ናቸው። በነዚህ አጠር ባሉ ቃላቶች የነዚህን ሶስቱንም ያጠቃለለ ጥቅምን አከታትለው ለመኑ። በቅድሚያ በሃይማኖት መስተካከል ጀመሩ። የሁለቱም ሀገሮች ሁኔታ የሚስተካከሉት በርሱ ነውና። እንዲህ አሉ:

(አላህ ሆይ! ሃይማኖቴን አስተካክለው።) በተሟላ መልኩ ስነስርዓቱን ጠብቄ እንድቆም ወፍቀኝ (አሳካልኝ)።

(የነገሮቼ መጠበቂያ የሆነውን) የጉዳዮቼ ባጠቃላይ ጠባቂ የሆነውን ሃይማኖቴ ከተበላሸ ጉዳዮቼ ባጠቃላይ ይበላሻል፤ ባዶዬን እቀራለሁ፣ እከስራለሁ። እንዲስተካከል የተፈለገው የሃይማኖት ጉዳይም ዱንያ ስትስተካከል ካልሆነ በቀር ስለማይስተካከል እንዲህ አሉ:

(ዱንያዬን ለኔ አስተካክልልኝ) የሰውነት ጤና፣ ደህንነት፣ ሲሳይ፣ መልካም ሚስት፣ ጥሩ ዘር፣ ሐላል የሆነና አንተን ለማምለክ የሚያግዘኝን የሚያሰፈልገኝን በመስጠት (ዱንያዬን ለኔ አስተካክልልኝ) ቀጥለው ዱንያቸው እንዲስተካከል የጠየቁበትን ምክንያት እንዲህ በማለት ጠየቁ:

(በውስጧ ኑሮዬ የሆነውን) የኑሮዬና የህይወት ዘመኔ ስፍራ የሆነውን።

(መመለሻዬ የሆነውን የመጨረሻውን አለም አስተካክልልኝ።) አንተን ለመገናኘት የምመለስበት የሆነውን ማለት ነው። መጨረሻ የሚያምረውም

ስራን በማስተካከልና አላህ ባሪያውን ለአምልኮ፣ ለኢኽላስና ለመልካም ፍፃሜ በመግጠሙ ነው።

ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና መጪው አለምን ከዱንያ በኋላ ያስከተሉት የመጀመሪያው አለም ለሁለተኛው አለም መስተካከል መዳረሻ ስለሆነ ነው። ዱኒያው አላህ በፈለገው መልኩ የተስተካከለለት ሰው መጪው አለምም ለርሱ ይስተካከልለታል በርሷም ውስጥ ይደሰታል።

(ህይወቴን አድርግ) የእድሜዬ መርዘምን (በሁሉም በኩል መልካም ነገር የምጨምርበት) መልካም ስራን የማበዛበት (ሞቴን አድርገው) መፍጠኑን (ከሁሉም መጥፎ ነገር የማርፍበት) ሞትን ከፈተናዎች፣ ከመከራ፣ የወንጀልና የዝንጉነት ፈተና ላይ ከመውደቅ፣ ከዱንያ ችግርና ጭንቀት የምገላገልበትና እረፍትን የማገኝበት አድርገው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ዲን ወሳኝ ነገር ነው። ስለዚህም ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ዱዓቸውን ከርሱ ጀመሩ።
2. ዲን ለሰው ልጅ ሁሉንም መጥፎ ነገር የሚከላከልለት መጠበቂያው ነው።
3. በዱኒያዊ ጉዳዮች ዱዓ የሚደረገው ዲንና መጪው አለም እንዲስተካከል ነው።
4. የዲን ፈተና በመፍራት ሞትን መመኘት ወይም አላህ ሸሂድ አድርጎ እንዲገድለው መጠየቅ አይጠላም።

(5482)

(٣٠٩) - عَنِ ابنِ عُمَرَ رضي الله عنهما قَالَ: لَمْ يَكُنْ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ يَدَعُ هَؤُلَاءِ الدَّعَوَاتِ، حِينَ يُمْسِي وَحِينَ يُصْبِحُ: «اللَّهُمَّ إِنِّي أَسْأَلُكَ الْعَافِيَةَ فِي الدُّنْيَا وَالْآخِرَةِ، اللَّهُمَّ إِنِّي أَسْأَلُكَ الْعَفْوَ وَالْعَافِيَةَ فِي دِينِي وَدُنْيَايَ وَأَهْلِي وَمَالِي، اللَّهُمَّ اسْتُرْ عَوْرَتِي -أَو: عَوْرَاتِي- وَآمِنْ رَوْعَاتِي، اللَّهُمَّ احْفَظْنِي مِنْ بَيْنِ يَدَيَّ، وَمِنْ خَلْفِي، وَعَنْ يَمِينِي، وَعَنْ شِمَالِي، وَمِنْ فَوْقِي، وَأَعُوذُ بِعَظَمَتِكَ أَنْ أُغْتَالَ مِنْ تَحْتِي». [صحيح] - [رواه أبو داود والنسائي وابن ماجه وأحمد]

(309) - ከኢብኑ ዑመር (ረዲየሏሁ ዐንሁማ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: «የአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና በሚያመሹና በሚያነጉ ጊዜ እነዚህን ዱዓዎች ከማድረግ አይቦዝኑም ነበር። "አላሁም ኢኒ አስአሉከልዓፊያተ ፊድ-ዱንያ ወልአኺረቲ፣ አላሁም ኢኒ አስአሉከል ዐፍወ ወልዓፊየተ ፊ ዲኒ ወዱንያየ ወአህሊ ወማሊ፣ አላሁም ስቱር ዐውረቲ -አው ዓውራቲ- ወአሚን ረውዓቲ፣ አሏሁም ሕፈዝኒ ሚን በይኒ የደየ፣ ወሚን ኸልፊ፣ ወዓን የሚኒ፣ ወዓን ሺማሊ፣ ወሚን ፈውቂ፣ ወአዑዙ ቢአዞመቲክ 'አን ኡግታለ ሚን ተሕቲ"» ትርጉሙም (አላህ ሆይ! በዱንያም ሆነ በመጪው አለም ደህንነትን እጠይቅሃለሁ፤ አላህ ሆይ በዱንያዬ፣ በመጪው አለሜ፣ በቤተሰቤና ገንዘቤ ይቅርታህንና ደህንነትን እጠይቅሃለሁ፤ አላህ ሆይ ነውሬን ወይም ነውሮቼን ሸሽግልኝ፣ ከፍርሃቴም ደህንነትን ስጠኝ፤ አላህ ሆይ! ከፊት ለፊቴም፣ ከኋላዬም፣ ከቀኜም፣ ከግራዬም፣ ከበላዬም ጠብቀኝ! ከበታቼ ድንገታዊ ጥቃት ከሚደርስብኝም በልቅናህ እጠበቃለሁ።) ማለት ነው። [ሶሒሕ ነው።] - [አቡዳውድ፣ ነሳኢ፣ ኢብኑማጀህና አሕመድ ዘግበውታል።]

### ትንታኔ:

ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ሲመሽና ሲነጋ እነዚህን ዱዓዎች ከማድረግ አይቦዝኑም ነበር።

(አላሁመ ኢኒ አስአሉከል ዓፊየተ) አላህ ሆይ! ከአለማዊ በሽታዎች፣ መከራዎችና ችግሮች፣ ከዲናዊ ፈተናዎችና ዝንባሌዎች ሰላም መሆንን (ፊድዱንያ ወልአኺረተ) በቅርቡም ሆነ በመጪው አለም እጠይቅሃለሁ።

(አልላሁመ ኢኒ አስአሉከል ዐፍው) አላህ ሆይ! ወንጀሎቼን ማበስ፣ ይቅር ማለትህን (ወልዓፊየተ) ከነውር መፅዳትን (ፊዲኒ) በሃይማኖቴ ከሽርክ፣ ከቢድዓና ከወንጀሎች፤ (ወዱንያየ) በዓለማዊ ህይወቴ ደሞ ከመከራዎች፣ ከሚያውክና ከክፋቶች (ወአህሊ) በቤተሰቤ ላይ በባለቤቴ፣ በልጆቼና ቅርብ ዘመዶቼ (ወማሊ) በገንዘቤና በስራዬ ላይ ደህና መሆንን እጠይቅሃለሁ።

(አልላሁመስቱር ዐውራቲ) አላህ ሆይ! እኔ ላይ ያሉትን ነውሮች፣ ጉድለቶች፣ እንከኖችን ሸሽገኝ፤ ወንጀሌንም አብስ። (ወአሚን ረውዓቲ) ድንጋጤዬንና ፍርሃቴን ደህንነት ስጠው።

(አልላሁመሕፈዝኒ) አላህ ሆይ! የሚያውኩኝንና መከራዎችን ከኔ አስወግድልኝ። (ሚን በይኒ የደየ፣ ወሚን ኸልፊ፣ ወዓን የሚኒ፣ ወዓን ሺማሊ፣ ወሚን ፈውቂ) (ከፊት ለፊቴም፣ ከኋላዬም፣ ከቀኜም፣ ከግራዬም፣ ከበላዬም) በዚህም አላህ ከሁሉም አቅጣጫዎች እንዲጠብቃቸው ጠየቁ። መከራዎችና መአቶች ወደ ሰው የሚመጡትና የሚዘሩት ከነዚህ አቅጣጫዎች መካከል በአንዱ ነውና።

(ወአዑዙ ቢዐዞመቲከ አንኡግታል) በድንገት ከመያዝና ተዘናግቼ ከምጠፋ በልቅናህ እጠበቃለሁ። (ሚንተሕቲ) በመሬት መደርመስ ከመጥፋትም ባንተ እጠበቃለሁ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. መልክተኛውን (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና በመከተል እነዚህን ቃላቶች መጠባበቅ እንደሚገባ እንረዳለን።
2. የሰው ልጅ የሃይማኖቱን ደህንነት አላህን እንዲጠይቅ እንደታዘዘው ሁሉ ለዓለማዊ ጉዳዩም እንዲጠይቅ ታዟል።

3. ጢቢ እንዲህ ብለዋል: «ስድስቱን አቅጣጫዎች ማጠቃለላቸው የመከራዎች መምጣት በነርሱ በኩል ስለሆነ ነው። የታች አቅጣጫን አበክረው የጠቀሱት ከታች የሚመጣ መከራ አዋራጅ ስለሆነ ነው።»
4. ንጋት ላይ አዝካሮችን ለመቅራት በላጩ ወቅት: ጎህ ከወጣ ጀምሮ የቀኑ መጀመሪያ ላይ ፀሃይ እስክትወጣ ድረስና ከዐስር በኋላ ፀሃይ እስክትገባ ድረስ ነው። ከዚህ በኋላም ቢል ማለትም ረፋዱ ከፍ ካለ በኋላም ቢል ይበቃለታል። ከዙህር በኋላም ቢል ይበቃለታል። ከመግሪብ በኋላም ቢል ይበቃለታል። ይህም የዚክር ወቅት ነውና።
5. ዚክሩ መባል ያለበት በተለየ ወቅት እንደሆነ ማስረጃ ከጠቆመ የሱረቱል በቀራ መጨረሻ ሁለት አንቀጾችን ምሽት ላይ መቅራትን ይመስል ፀሃይ ከገባ በኋላ ምሽት ላይ ነው የሚፈፀመው።

(5485)

(٣١٠) - عَنْ عَائِشَةَ أُمِّ المُؤْمِنِينَ رضي الله عنها أَنَّ رَسُولَ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ عَلَّمَهَا هَذَا الدُّعَاءَ: «اللَّهُمَّ إِنِّي أَسْأَلُكَ مِنَ الْخَيْرِ كُلِّهِ، عَاجِلِهِ وَآجِلِهِ، مَا عَلِمْتُ مِنْهُ وَمَا لَمْ أَعْلَمْ، وَأَعُوذُ بِكَ مِنَ الشَّرِّ كُلِّهِ، عَاجِلِهِ وَآجِلِهِ، مَا عَلِمْتُ مِنْهُ وَمَا لَمْ أَعْلَمْ، اللَّهُمَّ إِنِّي أَسْأَلُكَ مِنْ خَيْرِ مَا سَأَلَكَ عَبْدُكَ وَنَبِيُّكَ، وَأَعُوذُ بِكَ مِنْ شَرِّ مَا عَاذَ بِهِ عَبْدُكَ وَنَبِيُّكَ، اللَّهُمَّ إِنِّي أَسْأَلُكَ الْجَنَّةَ، وَمَا قَرَّبَ إِلَيْهَا مِنْ قَوْلٍ أَوْ عَمَلٍ، وَأَعُوذُ بِكَ مِنَ النَّارِ، وَمَا قَرَّبَ إِلَيْهَا مِنْ قَوْلٍ أَوْ عَمَلٍ، وَأَسْأَلُكَ أَنْ تَجْعَلَ كُلَّ قَضَاءٍ قَضَيْتَهُ لِي خَيْرًا». [صحيح] - [رواه ابن ماجه وأحمد]

(310) - የአማኞች እናት ከሆነችው ከዓኢሻ (ረዲየሏሁ ዐንሃ) - አላህ መልካም ሥራዋን ይውደድላትና - እንደተላለፈው የአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ይህን ዱዓ አስተማሯት: "አልላሁመ ኢኒ አስአሉከ ሚነል ኸይሪ ኩሊህ፣ ዓጂሊሂ ወአጂሊህ፣ ማ ዓሊምቱ ሚንሁ ወማለም አዕለም፣ ወአዑዙ ቢከ ሚነ ሸሪ ኩሊህ፣ ዓጂሊሂ ወአጂሊህ ማዓሊምቱ ሚንሁ ወማለም አዕለም። አላሁመ ኢኒ አስአሉከ ሚን ኸይሪ ማሰአለከ ዐብዱከ ወነቢዩከ፣ ወአዑዙ ቢከ ሚን ሸሪ ማዓዘ ቢሂ ዐብዱከ ወነቢዩክ፣ አላሁመ ኢኒ አስአሉከል ጀነተ ወማ ቀረበ ኢለይሃ ሚን ቀውሊን አው ዓመሊን፣ ወአስአሉከ አንተጅዐለ ኩለ ቀዷኢን ቀደይተሁ ሊ ኸይራ" ትርጉሙም "አላህ ሆይ! እኔ ከመልካም ነገር ቅርቡንም የዘገየውንም፣ ከርሱ ያወቅኩትንም ያላወቅኩትንም ሁሉንም እጠይቅሃለሁ፤ ከመጥፎ ነገርም ቅርቡንም የዘገየውንም፣ ከርሱ ያወቅኩትንም ያላወቅኩትንም ከሁሉም መጥፎ ነገር ባንተ እጠበቃለሁ። አላህ ሆይ! ባሪያህና ነቢይህ የጠየቀህን መልካም ነገር እጠይቅሃለሁ፣ ባሪያህና ነቢይህ ከተጠበቁት መጥፎ ነገርም ባንተ እጠበቃለሁ። አላህ ሆይ! ጀነትንና ወደርሷ የሚያቃርብን ንግግር ወይም ተግባር እጠይቅሃለሁ። ከእሳትና ወደርሷ ከሚያቀርቡ ንግግሮችና ተግባሮች ባንተ እጠበቃለሁ። ለኔ የወሰንከውን ሁሉንም ውሳኔዎች መልካም እንድታደርግልኝም እጠይቅሃለሁ።" ማለት ነው። [ሶሒሕ ነው።]

**ትንታኔ:**

ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ዓኢሻን (ረዲየሏሁ ዐንሃ) - አላህ መልካም ሥራዋን ይውደድላትና ጠቅላይ ዱዓዎችን አስተማሯት። እነርሱም እነዚህ አራት ዱዓዎች ናቸው:

የመጀመሪያው: ሁሉንም መልካም ነገር የጠቀለለ ዱዓ ነው (አላህ ሆይ! እኔ ከመልካም ነገር ሁሉንም እጠይቅሃለሁ) አጠቃላዩን (ቅርቡንም) ወቅቱ የቀረበውን (የዘገየውንም) መምጫ ወቅቱ የራቀውንም (ከርሱ ያወቅኩትንም) ካሳወቅከኝም (ያላወቅኩትንም) ከአንተ እውቀት ብቻ ከሆነውም እጠይቅሃለሁ። በዚህም ነገሮችን አዋቂና ውስጠ አዋቂ ወደሆነው አላህ ብቻ ማስጠጋት አለበት። ይህንን ዱዓ ላደረገ ሙስሊም አሏህ በላጩንና የተሻለውን ይመርጥለታል። (ከመጥፎ ነገርም ቅርቡንም የዘገየውንም፣ ከርሱ ያወቅኩትንም ያላወቅኩትንም ከሁሉም ነገር)

(መጠበቂያዬ) መጠጊያዬ አንተው ነህ።

ሁለተኛው ዱዓ: አንድ ሙስሊም በዱዓው ወሰን ከማለፍ ጥበቃን የሚጠይቅበት ነው። (ባሪያህና ነቢይህ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና የጠየቀህን መልካም ነገር) (አላህ ሆይ እኔ እጠይቅሃለሁ) ከአንተ እፈልጋለሁ። (ባሪያህና ነቢይህ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ከተጠበቁት መጥፎ ነገርም) (ባንተ እጠበቃለሁ) እጠጋለሁ። በዚህ ዱዓ ጠያቂው ነቢዩ ሙሐመድ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና የለመኑትን የዱዓ አይነቶች ሳይቆጥር እርሳቸው (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና አላህን ከለመኑትና ከርሱ ከፈለጉት የተሻለውን እንዲሰጠው እየጠየቀ ነው።

ሶስተኛው ዱዓ: ጀነት መግባትና ከእሳት መራቅን መፈለግ ነው። ይህም የሁሉም ሙስሊም ፍላጎትና የስራው ግብ ነው። (አላህ ሆይ! ጀነትን) በርሷ መጎናፀፍን (ወደርሷ የሚያቃርብን ንግግር ወይም ተግባርን እጠይቅሃለሁ።) የሚያስደስትህን መልካም ስራ እጠይቅሃለሁ። (ከእሳትም በአንተ እጠበቃለሁ።

) በአንተ እዝነት ካልሆነ በቀር ከፀያፍ ተግባር መጠበቂያ የለምና። (ወደርሷ ከሚያቃርብን ንግግር ወይም ተግባርም በአንተ እጠበቃለሁ።) ከሚያስቆጣህ ወንጀል በአንተ እጠበቃለሁ ማለት ነው።

አራተኛው ዱዓ: በአላህ ውሳኔ የመውደድ ዱዓ ነው። (ለኔ የወሰንከውን ሁሉንም ውሳኔዎች መልካም እንድታደርግልኝ እጠይቅሃለሁ።) አላህ ለኔ የወሰነውን ነገር ሁሉ ለኔ መልካም እንዲያደርግልኝ እጠይቃለሁ። ይህም በአላህ ፍርድ የመውደድ ዱዓ ነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ነቢዩ (ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ዓኢሻን እንዳስተማሯት አንድ ሰው ለቤተሰቦቹ ጠቃሚ የሆኑን የዲንና የዱንያ ጉዳዮችን ማስተማር እንደሚገባው እንረዳለን።
2. ለአንድ ሙስሊም በላጬ ከነቢዩ (ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና የመጡ ዱዓዎችን መሸምደድ ነው። ይህም ጠቅላይ ከሆኑ ዱዓዎች መካከል አንዱ ስለሆነ ነው።
3. ዑለማዎች ስለዚህ ሐዲሥ እንዲህ ብለዋል: ይህ ሐዲሥ መልካምን በመጠየቅና ከመጥፎ በመጠበቅ ረገድ ጠቅላይ ሐዲሥ ነው። ይህ ሐዲሥ ነቢዩ (ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ከተሰጣቸው ጠቅላይ ንግግር መካከልም ነው።
4. ከአላህ እዝነት ቀጥሎ ጀነት ከሚያስገቡ ምክንያቶች መካከል መልካም ተግባራትና ንግግሮች ይጠቀሳሉ።

(5487)

(٣١١) - عَنْ عَبْدِ اللهِ بْنِ عَمْرِو بْنِ الْعَاصِ رضي الله عنهما قَالَ: قَالَ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ: «إِنَّ الْإِيمَانَ لَيَخْلَقُ فِي جَوْفِ أَحَدِكُمْ كَمَا يَخْلَقُ الثَّوْبُ الْخَلِقُ، فَاسْأَلُوا اللهَ أَنْ يُجَدِّدَ الْإِيمَانَ فِي قُلُوبِكُمْ». [صحيح] - [رواه الحاكم والطبراني]

(311) - ዐብደላህ ቢን ዐምር ቢን አልዓስ -አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና- እንዲህ አሉ፦ የአላህ መልክተኛ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ አሉ፦ "ልክ ያረጀ ልብስ እንደሚደክመው ሁሉ ኢማንም በአንዳችሁ ልብ ውስጥ ይደክማል። አላህ ኢማንን በልባችሁ ውስጥ እንዲያድስ ለምኑት።" [ሶሒሕ ነው።] - [ሓኪምና ጦበራኒይ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን አዲስ ልብስን ለረጅም ጊዜ በመገልገላችን ምክንያት እንደሚደክም ሁሉ ኢማንም በሙስሊም ቀልብ ውስጥ እንደሚደክምና እንደሚያረጅ ተናገሩ። ይህም አምልኮ መፈፀምን በማቋረጥ ወይም ወንጀልን በመፈፀምና በስሜት ውስጥ በመዘፈቅ ምክንያት ነው። ስለዚህ ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ግዴታ ነገሮችን በመፈፀም፣ ውዳሴና ምህረት መለመንን በማብዛት አላህ ኢማናችንን እንዲያድስልን እንድንለምነው ጠቆሙን።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ፅናት እንዲሰጠንና በቀልባችን ውስጥ ኢማንን እንዲያድስልን አላህን በመጠየቅ ላይ መነሳሳቱ ፤
2. ኢማን ንግግርም ተግባርም እምነትም ሲሆን በአምልኮ (የአላህን ትዕዛዛት በመፈፀም) ሲጨምር በወንጀል ደግሞ ይቀንሳል።

(65020)

(٣١٢) - عَنِ الْعَبَّاسِ بْنِ عَبْدِ الْمُطَّلِبِ رضي الله عنه أَنَّهُ سَمِعَ رَسُولَ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ، يَقُولُ: «ذَاقَ طَعْمَ الْإِيمَانِ مَنْ رَضِيَ بِاللهِ رَبًّا، وَبِالْإِسْلَامِ دِينًا، وَبِمُحَمَّدٍ رَسُولًا».
[صحيح] - [رواه مسلم]

(312) - ከዓባስ ቢን ዐብዱል ሙጦሊብ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና እንደተላለፈው: የአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና እንዲህ ሲሉ ሰማቻው: "በአሏህ ጌትነት፣ በእስልምና ሃይማኖት እና የነብዩ ሙሐመድ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ነቢይነት የወደደ ሰው የኢማንን ጥፍጥና አጣጥሟል።" [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና በኢማኑ ላይ እውነተኛ አማኝ የሆነና ልቡ በኢማን የተረጋጋ ሰው እነዚህን ሶስት ነገሮች ከወደደ ልቡ ውስጥ መስፋት፣ መደሰት፣ ማጣጣም እንደሚሰማውና ወደ አላህ የመቅረብን እርካታ እንደሚያገኝ ተናገሩ።

የመጀመሪያው: በአላህ ጌትነት መውደድ ነው። ይህም በርሱ ላይ የአላህን ጌትነቱን የሚያስፈርዱ ሲሳይ ማከፋፈልና ሁኔታዎችን መወሰን ሲከሰትበት ልቡ ውስጥ አንዳችም ተቃውሞ አያገኝምም፤ ከአላህ ውጪ ጌታንም አይፈልግም።

ሁለተኛ: በእስልምና ሃይማኖት መውደድ ነው። ይህም እስልምና ላካተታቸው ሀላፊነቶችና ግዴታዎች ልቡን መክፈቱና ከእስልምና መንገድ ውጪ ላለ ሃይማኖት ልቡን አለመክፈቱ ነው።

ሶስተኛ: በነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና መልክተኝነት መውደድ ነው። ይህም እርሳቸው ይዘውት ላመጡት ነገር ባጠቃላይ ምንም ሳይጠራጠርና ሳያወላውል ልቡን መክፈትና መደሰት፤ የነቢዩን (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና መመሪያ የገጠመውን ካልሆነ በቀር ላያደርግ ነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. የምግብና የመጠጥ ጣዕም ጥፍጥና በአፍ እንደሚቀመሰው ኢማንም በቀልብ የሚቀመስ የሆነ ጥፍጥናና ጣዕም እንዳለው እንረዳለን።
2. ሰውነት የምግብና የመጠጥ ጣዕም ጥፍጥና የሚሰማው ጤነኛ ሲሆን ነው። ልክ እንደዚሁ ቀልብ ከአጥማሚ ዝንባሌና ክልክል ስሜቶች በሽታ ሲነፃ የኢማንን ጥፍጥና ያገኛል። ቀልብ ከታመመና ከተጎዳ ግን የኢማንን ጥፍጥና ሳይሆን የሚያገኘው መጥፊያው የሆነ ወንጀልና ዝንባሌ ነው የሚጣፍጠው።
3. የሰው ልጅ አንድን ነገር ከወደደና መልካም ካደረገው ነገሮች ይገሩለታል። አንድም ነገሩ አይከብደውም። ከርሱ በሚመጣ ነገር ባጠቃላይም ይደሰታል። የሚያስደስተው ነገር ነፀብራቅ ቀልቡን ይቀላቀለዋል። ልክ እንደዚሁ አንድ አማኝ ኢማን ቀልቡ ውስጥ የገባ ጊዜ ጌታውን መታዘዝ ይገራለታል፣ ነፍሱም በዚህ ትደሰታለች፣ እርሷን ማከምም አይከብደውም።
4. ኢብኑል ቀዪም እንዲህ ብለዋል: «ይህ ሐዲሥ በአላህ ጌትነትና ተመላኪነት መውደድን፣ በመልክተኛውና ለርሳቸው በመታዘዝ መውደድን፣ በሃይማኖቱና ለርሱ እጅ መስጠቱን መውደድን አካቷል።»

(65116)

(٣١٣) - عَنْ مُعَاذِ بْنِ جَبَلٍ رضي الله عنه: أَنَّ رَسُولَ صَلَّى عَلَيْهِ وَسَلَّمَ أَخَذَ بِيَدِهِ، وَقَالَ: «يَا مُعَاذُ، وَاللهِ إِنِّي لَأُحِبُّكَ»، فَقَالَ: «أُوصِيكَ يَا مُعَاذُ لَا تَدَعَنَّ فِي دُبُرِ كُلِّ صَلَاةٍ تَقُولُ: اللَّهُمَّ أَعِنِّي عَلَى ذِكْرِكَ وَشُكْرِكَ وَحُسْنِ عِبَادَتِكَ». [صحيح] - [رواه أبو داود والنسائي وأحمد]

(313) - ከሙዓዝ ቢን ጀበል (ረዲየሏሁ ዐንሁ) -አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው እንዲህ አሉ : «የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እጄን ያዙኝና እንዲህ አሉኝ: "ሙዓዝ ሆይ! ወላሂ እኔ እወድሃለሁ።" እንዲህም አሉ "ሙዓዝ ሆይ! ከየሁሉም ሰላት መጠናቀቂያ ላይ 'አልላሁመ አዒንኒ ዓላ ዚክሪከ፣ ወሹክሪከ፣ ወሑስኒ ዒባደቲክ' ማለትን እንዳትተው አደራ እልሃለሁ።" አሉኝ።» ትርጉሙም (አላህ ሆይ! አንተን በማውሳት፣ በማመስገንና አምልኮህን በማሳመር ላይ አግዘኝ።) [ሶሒሕ ነው።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) የሙዓዝን (ረዲየሏሁ ዐንሁ) አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና እጅ ያዙና ለርሱ እንዲህ አሉት: በአላህ እምልልሃለሁ እኔ እወድሃለሁ። ሙዓዝ ሆይ! በየሁሉም ሰላት መጨረሻ ላይ ይህን ማለት እንዳትተው አደራ እልሃለሁ። "አሏሁመ አዒኒ ዐላ ዚክሪከ" (አላህ ሆይ! አንተን በማውሳት አግዘኝ) ወደ አምልኮ የሚያቃርበኝ በሆነ ንግግርና ተግባር ሁሉ አግዘኝ። "ወሹክሪከ" ፀጋን በማግኘትና መከራን በማስወገድም (አንተን ለማመስገን) አግዘኝ። ለአላህ ስራን በማጥራትና ነቢዩን (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) በመከተል (አምልኮህን በማሳመርም) አግዘኝ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ሰውን ለአላህ ብለን እንደምንወደው መንገር የተደነገገ መሆኑን እንረዳለን።
2. በየሁሉም ግዴታና ሱንና ሰላቶች መጨረሻ ላይ ይህን ዱዓ ማድረግ መወደዱን እንረዳለን።
3. በነዚህ ጥቂት የዱዓ ቃላት ውስጥ ዱንያዊም አኺራዊም ፍላጎቶች አሉ።

4. ለአላህ ብሎ ከመውደድ ጥቅሞች መካከል በእውነት ላይ አደራ መባባል፣ መመካከር፣ በበጎና አላህን በመፍራት ላይ መተጋገዝ ይገኛሉ።
5. ጢቢይ እንዲህ ብለዋል: "አላህን ማውሳት የልብ መስፋት መግቢያ ነው። አላህን ማመስገን ደግሞ ተቀባይነት ላለው ፀጋ የሚያዳርስ ነው። አምልኮን ከማሳመር ተፈላጊው ጉዳይ ከአላህ ከሚያዘናጉ ነገሮች መለያየቱ ነው።"

(3518)

(٣١٤) - عن أبي هريرة رضي الله عنه أن رسول الله صلى الله عليه وسلم قال: «أَقْرَبُ مَا يَكُونُ الْعَبْدُ مِنْ رَبِّهِ وَهُوَ سَاجِدٌ، فَأَكْثِرُوا الدُّعَاءَ». [صحيح] - [رواه مسلم]

(314) - ከአቡ ሁረይራ -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው የአላህ መልክተኛ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንዲህ ብለዋል: "አንድ ባሪያ ወደ ጌታው እጅግ ቅርብ የሚሆነው ሱጁድ ላይ ሳለ ነው። (ስለዚህም) ዱዓእን አብዙ!" [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም አንድ ባሪያ ወደ ጌታው እጅግ ቅርብ የሚሆነው ሱጁድ ላይ ሳለ መሆኑን ገለፁ። ይህም ሰጋጅ ከሰውነቱ የላቀና የተከበረው አካሉን ለአላህ በሱጁድ ለመዋደቅ፣ ለመዋረድና ለመተናነስ ሲል መሬት ላይ የሚደፋ በመሆኑ ነው።

ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም በሱጁድ ውስጥ ዱዓእ እንድናበዛም አዘዙን። በዚህም ንግግራዊም ድርጊታዊም መተናነስ ይሰባሰባሉ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. አምልኮ ባሪያውን ወደ አላህ መቃረብን ትጨምርለታለች።
2. ሱጁድ ዱዓእ ተቀባይነት ከሚያገኝበት ስፍራዎች መካከል አንዱ ስለሆነ ሱጁድ ውስጥ ዱዓእ ማብዛት እንደሚወደድ ተረድተናል።

(5382)

(٣١٥) - عَنْ أَنَسٍ رضي الله عنه قَالَ: كَانَ أَكْثَرُ دُعَاءِ النَّبِيِّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ: «اللَّهُمَّ رَبَّنَا آتِنَا فِي الدُّنْيَا حَسَنَةً، وَفِي الآخِرَةِ حَسَنَةً، وَقِنَا عَذَابَ النَّارِ». [صحيح] - [متفق عليه]

(315) - ከአነስ (ረዲየላሁ ዐንሁ) -አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው እንዲህ ብለዋል፡- "ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እጅግ አብዝተው ያደርጉት የነበረው ዱዓ 'አልላሁመ ረበና አቲና ፊ ዱንያ ሐሰነተን ወፊል አኺረቲ ሐሰነተን ወቂና ዓዛበን-ናር' የሚለውን ነበር።" (ትርጉሙም: ጌታችን አላህ ሆይ! በዱንያ መልካሙን ስጠን፤ በመጨረሻው ዓለምም መልካሙን ስጠን። ከእሳት ቅጣትም ጠብቀን። ) [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ጠቅላይ የሆኑ ዱዓዎችን ማድረግ ያበዙ ነበር። ከነርሱም መካከል: "አልላሁመ ረበና አቲና ፊ ዱንያ ሐሰነተን ወፊል አኺረቲ ሐሰነተን ወቂና ዓዛበን-ናር" የሚለው ነበር።" (ትርጉሙም: ጌታችን አላህ ሆይ! በዱንያ መልካሙን ስጠን፤ በመጨረሻው አለምም መልካሙን ስጠን። ከእሳት ቅጣትም ጠብቀን።) ይህ ዱዓ ጣፋጬ፣ ሰፊና ሐላል የሆነ ሲሳይን፣ መልካም ሚስትን፣ የአይን ማረፊያ የሆነ ልጅን፣ እረፍትን፣ ጠቃሚ ዕውቀትን፣ መልካም ስራንና የመሳሰሉትን ተወዳጅና ፍቁድ የሆኑ ተፈላጊዎችን ባጠቃላይ የዱንያ መልካም ነገሮችን እንዲሁም በቀብር ውስጥ፣ በሒሳብ መቆሚያ ስፍራና በእሳት ውስጥ ከሚያጋጥም ቅጣቶች ሰላም መሆንን፣ የአላህን ውዴታ ማግኘት፣ ዘውታሪ ፀጋ መጎናፀፍን፣ አዛኝ ወደሆነው ጌታ መቅረብን የመሰሉ የመጨረሻው አለም መልካም ነገሮችንም የሚያጠቃልል ዱዓ ነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ነቢዩን (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) በመከተል ጠቅላይ የሆኑ ዱዓዎችን ማድረግ እንደሚወደድ እንረዳለን።

2. የተሟላ ዱዓ የሚባለው ሰውዬው በዱዓው ውስጥ ዱንያዊም አኺራዊም መልካም ጉዳዮችን የሰበሰበ እንደሆነ ነው።

(5502)

(٣١٦) - عَنْ أَبِي الدَّرْدَاءِ رضي الله عنه قَالَ: قَالَ النَّبِيُّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ: «أَلاَ أُنَبِّئُكُمْ بِخَيْرِ أَعْمَالِكُمْ، وَأَزْكَاهَا عِنْدَ مَلِيكِكُمْ، وَأَرْفَعِهَا فِي دَرَجَاتِكُمْ وَخَيْرٌ لَكُمْ مِنْ إِنْفَاقِ الذَّهَبِ وَالوَرِقِ، وَخَيْرٌ لَكُمْ مِنْ أَنْ تَلْقَوْا عَدُوَّكُمْ فَتَضْرِبُوا أَعْنَاقَهُمْ وَيَضْرِبُوا أَعْنَاقَكُمْ؟» قَالُوا: بَلَى. قَالَ: «ذِكْرُ اللهِ تَعَالَى». [صحيح] - [رواه الترمذي وأحمد وابن ماجه]

(316) - ከአቡ ደርዳእ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: «ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል: "በላጩን ሥራችሁ፣ ንጉሳችሁ ዘንድ የጠራችውን ሥራችሁ፣ ደረጃችሁንም ከፍ የምታደርገውን ስራችሁን፣ ለናንተ ወርቅና ብር ከመመፅወት የሚበልጥላችሁን ስራ፣ ጠላቶቻችሁን ተገናኝታችሁ አንገታቸውን ከምትመቱበት አንገታችሁን ከሚመቱበት ስራችሁም በላጩ የሆነውን ስራ አልነግራችሁምን?" ሶሐቦችም "እንዴታ!" አሉ። እርሳቸውም "አላህን ማውሳት ነው።" አሉ።» [ሶሒሕ ነው።] - [ቲርሚዚ፣ ኢብኑ ማጀህና አሕመድ ዘግበውታል።]

**ትንታኔ:**

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ባልደረቦቻቸውን እንዲህ በማለት ጠየቁ :

ልዕለ ኃያሉ ንጉሱ አላህ ዘንድ በላጩን፣ የላቀውን፣ የፋፋውን፣ የፀዳውንና የጠራውን ስራችሁን እንድነግራችሁ ትፈልጋላችሁን? ?

ጀነት ውስጥም ያለውን ደረጃችሁንም ከፍ የሚያደርግላችሁን ስራ?

ወርቅና ብር ከመመፅወትም ለናንተ የሚበልጥላችሁን?

ከከሀዲያን ጋር ለውጊያ ተገናኝታችሁ አንገቶቻቸውን ከምትቀሉና አንገቶቻችሁንም ከሚቀሉ የሚበልጠውን?

ሶሐቦችም: አዎ ይህንን እንፈልጋለን አሉ።

ነቢዩም (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) በሁሉም ወቅትና በአጠቃላይ ሁኔታዎች ላይ አላህን ማውሳት ነው አሏቸው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. በይፋም ይሁን በድብቅ አላህን ማውሳት ማዘውተር ከትላልቅ መቃረቢያዎችና አላህ ዘንድ እጅግ ጠቃሚ ከሆኑት ነው።
2. ሁሉም ስራዎች የተደነገጉት አላህን ማውሳትን ለማቋቋም (ተፈፃሚ ለማድረግ) ነው። አላህ እንዲህ ብሏል: {ሶላትንም (በእርሷ) እኔን ለማውሳት ስገድ።} ነቢዩም (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል "በአላህ ቤት ዙሪያ ጦዋፍ ማድረግ፣ በሶፋና መርዋ መካከል መሮጥ፣ ጠጠር መወርወር ሁሉ የተደረገው አላህን ማውሳት ለማቋቋም ነው።" አቡዳውድና ቲርሚዚ ዘግበውታል።
3. ዒዝ ቢን ዐብዱሰላም (ቀዋዒድ) በሚባለው መጽሐፋቸው ውስጥ እንዲህ ብለዋል "ይህ ሐዲሥ ምንዳ ሁሉም አምልኮዎች ላይ በልፋት ልክ እንደማይመጣ ከሚጠቁሙ ሐዲሦች አንዱ ነው። አንዳንዴ አላህ በትንሽ ስራ በትልቁ ስራ ከሚመነዳው በላይ ይመነዳል። ምንዳ የስራ ደረጃዎች በልቅና በሚበላለጡት ልክ ይበላለጣል።"
4. መናዊ "ፈይዱል ቀዲር" በሚባለው መጽሐፋቸው ውስጥ እንዲህ አሉ: ይህ ሐዲሥ የሚተረጎመው ንግግሩ ከቀረበላቸው ሰዎች አንፃር ነው ዚክር በላጭ የሚሆነው በሚል ነው። ነቢዩ ያናገሩት ሰው በውጊያ ብቃቱ እስልምና የሚጠቀምበትን አንበሳ ጀግና ሰው ቢሆን ኖሮ ለርሱ በላጩ ስራ ጂሀድ ይሉት ነበር። ወይም በገንዘቡ ድሀዎች የሚጠቀሙበትን ሀብታም ቢሆን ኖሮ ያናገሩት ለርሱ በላጩ ስራ ሶደቃ ይሉት ነበር። ሐጅ የሚችልን ሰው ያናገሩ ቢሆን ኖሮ ሐጅ ይሉት ነበር። ወይም ወላጆች ያሉትን ቢያናግሩ ኖሮ እነሱን መንከባከብ ይሉት ነበር። ሐዲሦቹ የሚስማሙት በዚህ መንገድ ነው።

5. የተሟላው ዚክር ልቦና እያስተነተነው ምላስ የተናገረው ዚክር ነው። ቀጥሎም በልብ ብቻ የተፈፀመ ዚክር ነው ተፈኩርን ይመስል። ቀጥሎ በምላስ ብቻ የተፈፀመ ነው። በሁሉም ግን ኢንሻ አሏህ ምንዳ ይገኝባቸዋል።
6. አንድ ሙስሊም ከሁኔታዎች ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ዚክሮች እንደ ንጋትና ምሽት ዚክሮች፣ ወደ መስጂድ፣ ቤት፣ ሽንት ቤት ሲገባና ሲወጣ የሚባሉትን ዚክሮችና ሌሎችንም አዘውትሮ መፈፀሙ አላህን በብዙ ከሚያመወሱት መካከል ያደርገዋል።

(3575)

(٣١٧) - عَنْ مُعَاذِ بْنِ جَبَلٍ رضي الله عنه قَالَ: كُنْتُ مَعَ النَّبِيِّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ فِي سَفَرٍ، فَأَصْبَحْتُ يَوْمًا قَرِيبًا مِنْهُ وَنَحْنُ نَسِيرُ، فَقُلْتُ: يَا رَسُولَ اللهِ أَخْبِرْنِي بِعَمَلٍ يُدْخِلُنِي الجَنَّةَ وَيُبَاعِدُنِي عَنِ النَّارِ، قَالَ: «لَقَدْ سَأَلْتَنِي عَنْ عَظِيمٍ، وَإِنَّهُ لَيَسِيرٌ عَلَى مَنْ يَسَّرَهُ اللهُ عَلَيْهِ، تَعْبُدُ اللهَ وَلاَ تُشْرِكْ بِهِ شَيْئًا، وَتُقِيمُ الصَّلاَةَ، وَتُؤْتِي الزَّكَاةَ، وَتَصُومُ رَمَضَانَ، وَتَحُجُّ البَيْتَ» ثُمَّ قَالَ: «أَلاَ أَدُلُّكَ عَلَى أَبْوَابِ الخَيْرِ: الصَّوْمُ جُنَّةٌ، وَالصَّدَقَةُ تُطْفِئُ الخَطِيئَةَ كَمَا يُطْفِئُ الْمَاءُ النَّارَ، وَصَلاَةُ الرَّجُلِ مِنْ جَوْفِ اللَّيْلِ» قَالَ: ثُمَّ تَلاَ: «{تَتَجَافَى جُنُوبُهُمْ عَنِ الْمَضَاجِعِ}، حَتَّى بَلَغَ {يَعْمَلُونَ}» ثُمَّ قَالَ: «أَلاَ أُخْبِرُكَ بِرَأْسِ الأَمْرِ كُلِّهِ وَعَمُودِهِ، وَذِرْوَةِ سَنَامِهِ؟» قُلْتُ: بَلَى يَا رَسُولَ اللهِ، قَالَ: «رَأْسُ الأَمْرِ الإِسْلاَمُ، وَعَمُودُهُ الصَّلاَةُ، وَذِرْوَةُ سَنَامِهِ الجِهَادُ» ثُمَّ قَالَ: «أَلاَ أُخْبِرُكَ بِمَلاَكِ ذَلِكَ كُلِّهِ؟» قُلْتُ: بَلَى يَا نَبِيَّ اللهِ، فَأَخَذَ بِلِسَانِهِ قَالَ: «كُفَّ عَلَيْكَ هَذَا» فَقُلْتُ: يَا نَبِيَّ اللهِ، وَإِنَّا لَمُؤَاخَذُونَ بِمَا نَتَكَلَّمُ بِهِ؟ فَقَالَ: «ثَكِلَتْكَ أُمُّكَ يَا مُعَاذُ، وَهَلْ يَكُبُّ النَّاسَ فِي النَّارِ عَلَى وُجُوهِهِمْ أَوْ عَلَى مَنَاخِرِهِمْ إِلاَّ حَصَائِدُ أَلْسِنَتِهِمْ».

[صحيح بمجموع طرقه] - [رواه الترمذي وابن ماجه وأحمد]

(317) - ከሙዓዝ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) -አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው እንዲህ አሉ : «ከነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ጋር ጉዞ ላይ ነበርኩ። አንድ እለት እየተጓዝን ሳለ ወደርሳቸው ቀረብኩኝና እንዲህ አልኳቸው: "የአላህ መልክተኛ ሆይ! ጀነት የሚያስገባኝና ከእሳትም የሚያርቀኝን ስራ ንገሩኝ?"

እርሳቸውም " በርግጥም ስለ ትልቅ ጉዳይ ነው የጠየቅከኝ፤ ጉዳዩ አላህ በርሱ ላይ ላቀለለለት ሰው ቀላል ነው። አላህን ልትገዛና በርሱ ላይ ምንንም ላታጋራ፤ ሶላትን ቀጥ ልታደርግ (በአግባቡ ልትሰግድ)፤ ዘካን ልትሰጥ፤ ረመዳንን ልትጾም፤ የአላህንም ቤት ሐጅ ልታደርግ ነው።" አሉና ቀጥለውም እንዲህ አሉ: "የመልካም ነገሮችን በር አልጠቁምህምን? ጾም ጋሻ ነው፤ ውሃ እሳትን እንደሚያጠፋው ሁሉ ምፅዋትም ወንጀልን ታጠፋለች፤ የሰውዬው በሌሊቱ አጋማሽ የሚሰግደው ሶላት" አሉና ቀጥለው {ጎኖቻቸው ከመጋደሚያ ስፍራዎች ይራራቃሉ} ከሚለው {ይሰሩትም በነበሩት} እስከሚለው ድረስ [ሱረቱ ሰጅዳ: 16-17] አነበቡ። ቀጥለውም "የነገሩ ሁሉ ራስ፣ ምሰሶውንና ሻኛውን ልንገርህን?" አሉ። እኔም "እንዴታ የአላህ መልክተኛ ሆይ!" አልኳቸው። እርሳቸውም "የነገሮች ሁሉ ራስ (ዋና) እስልምና ነው፤ ምሰሶው ሶላት ነው፤ ሻኛው ጂሃድ ነው።" አሉ። ቀጥለውም "ይህን ሁሉ የሚቆጣጠረውን ነገር ልንገርህን?" አሉ። እኔም "እንዴታ የአላህ ነቢይ ሆይ!" አልኳቸው። ምላሳቸውን ያዙና "በራስህ ላይ ይህቺን ቆጥባት!" አሉ። እኔም "የአላህ ነቢይ ሆይ! እኛ በምንናገረው እንያዛለንን?" አልኳቸው። እርሳቸውም "እናትህ ትጣህና ሙዓዝ ሆይ! ምላሳቸው ያጨደችው ካልሆነ በቀር ሰዎችን በፊታቸው ወይም በአፍጢማቸው እሳት ውስጥ የሚደፋቸው (ሌላ ነገር) አለ እንዴ?" አሉኝ።» [ከሁሉም ሰነዶቹ አንፃር ሶሒሕ ነው።] - [ቲርሚዚ፣ ኢብኑ ማጀህና አሕመድ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ሙዓዝ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንዲህ አሉ: ከነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ጋር ጉዞ ላይ ነበርኩ። አንድ እለት እየተጓዝን ሳለ ወደርሳቸው ቀረብ አልኩኝና እንዲህ አልኳቸው: የአላህ መልክተኛ ሆይ! ጀነት የሚያስገባኝና ከእሳትም የሚያርቀኝን ስራ ይንገሩኝ። እርሳቸውም እንዲህ አሉ: በነፍስ ላይ መስራቱ ከባድ ስለሆነ ስራ ነው የጠየቅከኝ። አላህ በርሱ ላይ ላቀለለለት ግን ገርና ቀላል ነው። የእስልምናን ግዴታዎች ፈፅም:

የመጀመሪያው: አላህን በብቸኝነት መገዛትና በርሱም አንዳችን አታጋራ፤

ሁለተኛው: በቀንና ምሽት አምስቱን ግዴታ ሶላቶች: ፈጅር፣ ዙህር፣ ዐስር፣ መሻሪብና ዒሻን መስፈርታቸውን፣ ማዕዘናቸውንና ግዴታዎቻቸውን አሟልተህ ቀጥ አድርገህ መስገድ ነው፤

ሶስተኛው: ግዴታ የሆነብህን ዘካ ማውጣት ነው: ይህም ገንዘብ በሸሪዓ የተገደበን መጠን በደረሰ ጊዜ ለሚገባው አካል የሚሰጥ በሁሉም ገንዘብ ላይ ግዴታ የሆነ ገንዘባዊ አምልኮ ነው፤

አራተኛው: ረመዳንን ትጾማለህ: እርሱም አምልኮን በመነየት ጎህ ከወጣችበት ወቅት ጀምሮ ፀሐይ እስክትገባ ድረስ ከመብላት፣ ከመጠጣትና ከሌሎችም የሚያስፈጥሩ ነገሮችም መቆጠብ ነው።

አምስተኛው: የሐጅ አምልኮን ለመተግበር አላህን ለማምለክ መካን በማሰብ የአላህን ቤት ሐጅ ማድረግ ነው።

ቀጥለውም ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ አሉ: ወደ መልካም በሮች የሚያደርስ መንገድ አላሳውቅህምን? ይህም እነዚህን ግዴታዎችና ሱና ተግባራትን በመከተል ነው:

የመጀመሪያው: ሱና ጾም መጾም ነው። ይህም ስሜትን በመስበርና ሀይልን በማድከም ወንጀል ላይ ከመውደቅ የሚከላከል ነው።

ሁለተኛው: ሰደቃ (ግዴታ ያልሆነ ምፅዋት) መስጠት ነው። ይህም ወንጀል ከተሰራ በኋላ ወንጀልን ታጠፋለች፣ ታስወግዳታለች፣ ፋናዋንም ታብሳታለች።

ሶስተኛው: በሌሊቱ የመጨረሻ ሲሶ የተሀጁድ ሶላት መስገድ ነው። ቀጥለው ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) {ጎኖቻቸው ከመጋደሚያ ስፍራዎች ይራራቃሉ} በሶላት፣ በዚክር፣ በመቅራትና በዱዓ {ጌታቸውን ይጠሩታል።} {ለመፍራትና ለመከጀል ከሰጠናቸውም (ጸጋ) ይለግሳሉ። ከዓይኖች መርጊያ ለእነርሱ የተደበቀላቸውን (ጸጋ) ማንኛይቱም ነፍስ አታውቅም።} ማለትም የትንሳኤ ቀን በጀነት ውስጥ በሚያገኙት ፀጋ አይኖቻቸው በርሱ የምትረጋበትን ነፍሳቸው አታውቅም። {ይሰሩትም በነበሩት ለመመንዳት።}

ቀጥለው ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና እንዲህ አሉ: የሃይማኖቱ መሰረት የሆነውን አልነግርህምን? መሰረቱ በርሱ ላይ የሚደገፍበት ምሰሶውንስ አልነግርህምን? ሻኛውንስ አልነግርህምን?

ሙዓዝም (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - "እንዴታ የአላህ መልክተኛ ሆይ!" አለ።

ነቢዩም (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና: የነገሮች ራስ (ዋና) እስልምና ነው። እርሱም ሁለቱ የምስክር ቃላቶች ናቸው። የሃይማኖቱ መሰረት ከሰውዬው ጋር የሚቆይለት በሁለቱ ቃላት ነው። ምሰሶው: ሶላት ነው። ቤት ያለምሰሶ እንደማይኖር ሁሉ ያለ ሶላትም እስልምና የለም። የሰገደ ሰው ሃይማኖቱ ይጠነክራልም ከፍ ይላልም። ሻኛውና ከፍታው ደሞ በጂሃድና የአላህን ቃል ከፍ ለማድረግ የእስልምና ጠላቶችን ለመዋጋት አቅምን በመለገስ ነው።

ቀጥለው ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና እንዲህ አሉ: ቀደም ብዬ የነገርኩህን ነገር የሚያስረውና የሚጠብቀውን ልንገርህን? ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ምላሳቸውን ያዙና "ይህንን ቆጥብ። የማይመለከትህን አትናገር።" አሉት። ሙዓዝም: "ጌታችን በምንናገረው ሁሉ ይቀጣናል? ይተሳሰበናል? ይይዘናልን"?

ቀጥለውም ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና "እናትህ ትጣህ" አሉት። በዚህም እርሱን መርገም ፈልገው ሳይሆን ነገር ግን ዐረቦች ሊታወቅና ሊገነዘቡት የሚገባን ነገር ለማስገንዘብ የሚናገሩት ንግግር ነው። ቀጥለው እንዲህ አሉ "እንደ ክህደት፣ ዘለፋ፣ ስድብ፣ ሀሜት፣ ነገር ማሳበቅ፣ ቅጥፈትና በመሳሰሉት ምላሳቸው ባጨደችው ክፋት ካልሆነ በቀር ሰዎችን እሳት ውስጥ በፊታቸው የሚጥላቸውና የሚደፋቸው (ሌላ ነገር) አለ እንዴ"?

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ሶሐቦች (ረዲየሏሁ ዐንሁም) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - በእውቀት ላይ ያላቸውን ጥረት እንረዳለን። ለዛም ነቢዩን (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና በእውቀት ጉዳይ አብዝተው ይጠይቁ ነበር።
2. ስራዎች ጀነት ለመግባት ምክንያት መሆኑን ማወቃቸው የሶሐቦች (ረዲየሏሁ ዐንሁም) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - ግንዛቤን ያስረዳናል።
3. ከሙዐዝ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - የመጣው ጥያቄ በርግጥም ትልቅ ጥያቄ ነው። በእውነቱ ይህ ጥያቄ የህይወትና የመኖር ምስጢር ነውና። በዚህ አለም የሚገኙ የአደም ልጅና የጂን ፍጡር ሁሉ ፍፃሜው ወይ ጀነት ወይ እሳት ስለሆነ ይህ ጥያቄ እጅግ ትልቅ ጥያቄ ነው።
4. ጀነት መግባት አምስቱን የእስልምና ማዕዘናት መፈፀምን ተከትሎ መሆኑን እንረዳለን። እነርሱም: ሁለቱ የምስክር ቃሎች፣ ሶላት፣ ዘካ፣ ፆምና ሐጅ ናቸው።
5. የእስልምና መሰረት፣ ውዱ አላማና ትልቁ ግዴታ አላህን በአምልኮ ብቸኛ አድርጎ መነጠልና በርሱ ላይ አለማጋራት ነው።
6. አላህ ለባሮቹ የምንዳና ወንጀል ማስማሪያ ሰበቦችን እንዲሰነቁ የመልካም በሮችን ለነርሱ መክፈቱ የርሱን እዝነት ያስረዳናል።
7. ግዴታን ከተወጡ በኋላ በትርፍ ስራዎች ወደ አላህ የመቃረብን ትሩፋት እንረዳለን።
8. ሶላት በእስልምና ያለው ደረጃ ድንኳን የሚቆምበት ምሰሶ ለድንኳኑ እንዳለው ደረጃ ያህል ነው። ምሰሶው ሲወድቅ ድንኳኑም እንደሚወድቀው ሁሉ ሶላት ስትወገድም እስልምናው አብሮ ይወገዳል።
9. የሰው ልጅ ሃይማኖቱን ከሚጎዳው ነገር ምላሱን የመጠበቅ ግዴታ እንዳለበት እንረዳለን።

## 10. ምላስን መቆጠብ፣ መጠበቅና መገደብ የመልካም ነገር ሁሉ መሰረት ነው።

(4303)

(٣١٨) - عَنْ عَائِشَةَ رضي الله عنها: أَنَّ النَّبِيَّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ كَانَ إِذَا أَوَى إِلَى فِرَاشِهِ كُلَّ لَيْلَةٍ جَمَعَ كَفَّيْهِ، ثُمَّ نَفَثَ فِيهِمَا فَقَرَأَ فِيهِمَا: {قُلْ هُوَ اللهُ أَحَدٌ}، وَ{قُلْ أَعُوذُ بِرَبِّ الْفَلَقِ}، وَ{قُلْ أَعُوذُ بِرَبِّ النَّاسِ}، ثُمَّ يَمْسَحُ بِهِمَا مَا اسْتَطَاعَ مِنْ جَسَدِهِ، يَبْدَأُ بِهِمَا عَلَى رَأْسِهِ وَوَجْهِهِ وَمَا أَقْبَلَ مِنْ جَسَدِهِ، يَفْعَلُ ذَلِكَ ثَلَاثَ مَرَّاتٍ. [صحيح] - [رواه البخاري]

(318) - ከምእመናን እናት ዓኢሻህ -አላህ መልካም ሥራዋን ይውደድላትና- እንደተላለፈው፡- "ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ሁል ጊዜም በምሽት ወቅት ወደ ፍራሻቸው የተጠጉ ጊዜ መዳፋቸውን ይሰበስቡና ከዚያም ትንፋሻቸውን እየነፉበት {ቁል ሁወ አላሁ አሐድ}ን፣ {ቁል አዑዙ ቢረቢል ፈለቅ}ን፣ {ቁል አዑዙ ቢረቢ ናስ}ን ይቀሩበት ነበር። ከዚያም ከሰውነታቸው የቻሉትን በመዳፋቸው ያብሳሉ። (ሲያብሱም) ጭንቅላታቸውን፣ ፊታቸውንና ከሰውነታቸው የፊትለፊቱን በቅድሚያ ያብሳሉ። ይህንንም ሶስት ጊዜ ይፈፅሙታል።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪ ዘግበውታል።]

**ትንታኔ:**

ከነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን መመሪያ መካከል ለመተኛት ወደ ፍራሻቸው የተጠጉ ጊዜ ልክ ዱዐ እንደሚያረግ ሰው መዳፋቸውን ሰብስበው ከፍ ያደርጉት ነበር። በሱም ላይ ከትንሽ ምራቅ ጋር በመቀላቀል ቀለል ያለ መንፋት በአፋቸው እየነፉበት ሶስት ምእራፎች ያነቡበታል። {ሱረቱል ኢኽላስ}ን፣ {ሰረቱል ፈለቅ}ን፣ {ሱረቱ አንናስ}ን ከዚያም የቻሉትን ያህል የሰውነታቸውን ክፍል ከጭንቅላታቸው፣ ከፊታቸውና ከሰውነታቸው የፊትለፊት ክፍል በመጀመር በመዳፋቸው ያብሱታል። ይህንንም ድርጊት ሦስት ጊዜ ይደጋግሙታል።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ከመተኛት በፊት የኢኽላስን ምእራፍና ሙዐወዘተይንን መቅራትና ምራቅ የቀላቀለን ትንፋሽ በመንፋት የተቻለውን ያህል የሰውነትን ክፍል ማበስ እንደሚወደድ እንረዳለን።

(65060)

(٣١٩) - عَنْ شَدَّادِ بْنِ أَوْسٍ رَضِيَ اللهُ عَنْهُ عَنِ النَّبِيِّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ: «سَيِّدُ الاِسْتِغْفَارِ أَنْ تَقُولَ: اللَّهُمَّ أَنْتَ رَبِّي لاَ إِلَهَ إِلَّا أَنْتَ، خَلَقْتَنِي وَأَنَا عَبْدُكَ، وَأَنَا عَلَى عَهْدِكَ وَوَعْدِكَ مَا اسْتَطَعْتُ، أَعُوذُ بِكَ مِنْ شَرِّ مَا صَنَعْتُ، أَبُوءُ لَكَ بِنِعْمَتِكَ عَلَيَّ، وَأَبُوءُ لَكَ بِذَنْبِي فَاغْفِرْ لِي، فَإِنَّهُ لاَ يَغْفِرُ الذُّنُوبَ إِلَّا أَنْتَ» قَالَ: «وَمَنْ قَالَهَا مِنَ النَّهَارِ مُوقِنًا بِهَا، فَمَاتَ مِنْ يَوْمِهِ قَبْلَ أَنْ يُمْسِيَ، فَهُوَ مِنْ أَهْلِ الجَنَّةِ، وَمَنْ قَالَهَا مِنَ اللَّيْلِ وَهُوَ مُوقِنٌ بِهَا، فَمَاتَ قَبْلَ أَنْ يُصْبِحَ، فَهُوَ مِنْ أَهْلِ الجَنَّةِ».

[صحيح] - [رواه البخاري]

(319) - ከሸዳድ ቢን አውስ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ አሉ: "የምህረት አጠያየቅ (የኢስቲሻፋር) አለቃ 'አልላሁመ አንተ ረቢ ላ ኢላሃ ኢላ አንተ፣ ኸለቅተኒ ወአነ ዐብዱክ፣ ወአነ ዓላ ዐህዲከ ወወዕዲከ ማስተጦዕቱ፣ አዑዙ ቢከ ሚን ሸሪ ማ ሶነዕቱ፣ አቡኡ ለከ ቢኒዕመቲከ ዐለየ፣ ወአቡኡ ለከ ቢዘንቢ ፈሻፊር ሊ፣ ፈኢነሁ ላየሻፊሩዝ-ዙኑበ ኢላ አንተ።' ማለትህ ነው።'" እንዲህም ብለዋል "በርሷ አምኖ ቀን ላይ ያላትና በዛው ቀን ከማምሸቱ በፊት የሞተ ሰው እርሱ ከጀነት ባለቤቶች ነው። በርሷ አምኖ ምሽት ላይ ያላትና ከማንጋቱ በፊት የሞተ ሰውም እርሱ ከጀነት ባለቤቶች ነው።" (ትርጉሙም: አላህ ሆይ! አንተ ጌታዬ ነህ፤ ከአንተ በቀር በእውነት የሚመለክ የለም፤ ፈጥረሀኛል እኔም ባሪያህ ነኝ፣ እኔ በቻልኩት መጠን በቃል ኪዳንህ ላይ እገኛለሁ፤ ከሰራሁት ክፉት በአንተ እጠበቃለሁ፣ በኔ ላይ የዋልከውን ፀጋ አረጋግጣለሁ፣ ወንጀሌንም ላንተ አረጋግጣለሁና ማረኝ! እነሆ ካንተ በቀር ወንጀሎችን የሚምር የለምና።) [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪ ዘግበውታል።]

**ትንታኔ:**

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ምህረት የሚጠየቅበት የተለያዩ ቃላቶች እንዳሉና በላጩና ትልቁ አንድ ባሪያ እንዲህ ብሎ መጠየቁ እንደሆነ ተናገሩ: "አልላሁመ አንተ ረቢ ላ ኢላሃ ኢላ አንተ፣ ኸለቅተኒ ወአነ ዐብዱክ፣ ወአነ ዓላ ዐህዲከ ወወዕዲከ ማስተጦዕቱ፣ አዑዙ ቢከ ሚን ሸሪ ማ ሶነዕቱ፣ አቡኡ ለከ ቢኒዕመቲከ ዐለየ፣ ወአቡኡ ለከ ቢዘንቢ ፈግፊር ሊ፣ ፈኢነሁ ላየግፊሩዝ-ዙኑበ ኢላ አንተ።" (ትርጉሙም: አላህ ሆይ! አንተ ጌታዬ ነህ፤ ከአንተ በቀር በእውነት የሚመለክ የለም፤ ፈጥረህኛል እኔም ባሪያህ ነኝ፣ እኔ በቻልኩት መጠን በቃል ኪዳንህ ላይ እገኛለሁ፤ ከሰራሁት ክፋት በአንተ እጠበቃለሁ፣ በኔ ላይ የዋልከውን ፀጋ አረጋግጣለሁ፣ ወንጀሌንም ላንተ አረጋግጣለሁና ማረኝ! እነሆ ካንተ በቀር ወንጀሎችን የሚምር የለምና።) በቅድሚያ ባሪያው የአላህን ብቸኝነት ያረጋግጣል። አላህ ፈጣሪው፣ ምንም አጋር ሳይኖረው የሚያመልከው መሆኑን፤ ጥራት ለተገባው አላህ የገባውን በርሱ የማመንና ለርሱ ታዛዥ የመሆንን ቃልኪዳን በአቅሙ ልክ እንደሚወጣ ያረጋግጣል። በአቅሙ ልክ ቃሉን እንደሚወጣ የሚያረጋግጠውም አንድ ባሪያ ምንም ያክል በአምልኮ ላይ ቢቆም አላህ ያዘዘውን ሁሉ መፈፀም ስለማይችል ነው። ለተዋለለት ፀጋ የሚገባውን ምስጋናም ማቅረብ አይችልም። ወደ አላህም ይጠጋል፣ በርሱም ይጠበቃል፣ ባሪያ ከሰራው ክፋት መጠበቂያው አላህ ነውና። አላህ ለርሱ የዋለለትን ፀጋም በታዛዥነት ለርሱ ያረጋግጣል፤ እውቅናንም ይሰጣል። ወደ ነፍሱ በመመለስም ወንጀሉና ኃጢአቱን ያረጋግጣል፤ ያምናልም። በዚህ መልኩ ወደ አላህ ከተቃረበ በኋላ ጌታው እንዲምረው፣ ወንጀሎቹን እንዲሸሽግለት፣ በይቅር ባይነቱ፣ በችሮታውና እዝነቱ ከወንጀሎቹ እንዲጠብቀውም ዱዓ ያደርጋል። ምክንያቱም ከአላህ በቀርም ወንጀሎችን የሚምር የለምና። ቀጥለውም ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ይህቺ ዱዓ ከንጋትና ምሽት ውዳሴዎች መካከል መሆኗንና በቀኑ መጀመሪያ ፀሀይ ከወጣችበት ጊዜ አንስቶ ወደ መግቢያዋ ዘንበል እስክትል ድረስ ባለው ወቅት ላይ በእርግጠኝነት፣ መልዕክቷን በማሰብ አምኖባት ካለ

በኋላ የሞተ ሰው ጀነት የሚገባ መሆኑን ተናገሩ። በምሽትም ወቅት እርሱም ፀሀይ ከገባችበት አንስቶ ጎህ እስኪወጣ ድረስ ያለ ሰውና ከመንጋቱም በፊት የሞተ ጀነት ይገባል።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ምህረትን የመጠየቂያ ቃላቶች የተለያዩ ሲሆኑ ከፊሉም ከከፊሉ ይበላለጣል።
2. አንድ ባሪያ በዚህ ዱዓ አላህን ለመለመን መጓጓት ይገባዋል። ምክንያቱም የምህረት አጠያየቅ (የኢስቲግፋር) አለቃ ነውና።

(5503)

(٣٢٠) - عَنْ أَبِي هُرَيْرَةَ رضي الله عنه عَنِ النَّبِيِّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ: أَنَّهُ كَانَ يَقُولُ إِذَا أَصْبَحَ: «اللهُمَّ بِكَ أَصْبَحْنَا، وَبِكَ أَمْسَيْنَا، وَبِكَ نَحْيَا، وَبِكَ نَمُوتُ، وَإِلَيْكَ النُّشُورُ» وَإِذَا أَمْسَى قَالَ: «بِكَ أَمْسَيْنَا، وَبِكَ أَصْبَحْنَا، وَبِكَ نَحْيَا، وَبِكَ نَمُوتُ، وَإِلَيْكَ النُّشُورُ» قَالَ: وَمَرَّةً أُخْرَى: «وَإِلَيْكَ الْمَصِيرُ».
[حسن] - [رواه أبو داود والترمذي والنسائي في الكبرى وابن ماجه]

(320) - ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና: እርሳቸው ያነጉ ጊዜ እንዲህ ይሉ ነበር "አልላሁመ ቢከ አስበሕና ወቢከ አምሰይና ወቢከ ነሕያ ወቢከ ነሙቱ ወኢለይከ ኑሹር" ትርጉሙም "አላህ ሆይ በአንተ አነጋን፣ በአንተም አመሸን፣ በአንተም ህያው እንሆናለን፣ በአንተም እንሞታለን፣ መቀስቀስም ወደ አንተ ነው።" ያመሹ ጊዜ ደግሞ እንዲህ ይሉ ነበር "አልላሁመ ቢከ አምሰይና ወቢከ አስበሕና ወቢከ ነሕያ ወቢከ ነሙቱ ወኢለይከ ኑሹር" ትርጉሙም "አላህ ሆይ! በአንተ አመሸሁ፣ በአንተም አነጋሁ፣ በአንተም ህያው እንሆናለን፣ በአንተም እንሞታለን፣ መቀስቀስም ወደ አንተ ነው።" በሌላ ጊዜም እንዲህ ብለዋል "... ወኢለይከል መሲር" ትርጉሙም "... መመለሻም ወደ አንተ ነው።" [ሐሰን ነው።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና በርሳቸው ላይ ንጋት የገባ ጊዜ (ይህም ጎህ ከመውጣቱ ጋር የቀኑ መጀመሪያ የሆነው ጊዜ ነው።) እንዲህ ይሉ ነበር:

(አላህ ሆይ! በአንተ አነጋን) በጥበቃህ ተከልለን፣ በፀጋህ ተሸፍነን፣ አንተን በማውሳት ተጠምደን፣ በስምህ ታግዘን፣ በመግጠምህ ተከበን፣ በብልሃትህና በሀይልህ ተንቀሳቃሽ ሆነን አነጋን ማለት ነው። (በአንተ አመሸን፣ በአንተ ህያው እንሆናለን፣ በአንተም እንሞታለን።) ይህ ማለት ምሽት ላይ ከማድረግ ጋር ቀደም ተብሎ እንደተብራራው እንዲህ ይላል: አላህ ሆይ ባንተ አምሸተናል፣ ህያው አድራጊ በሆነው ስምህ ህያው እንሆናለን። ህይወትን የሚነጥቅ በሚለው ስምህ እንሞታለን። (መቀስቀስም ወዳንተ ነው።) መቀስቀስ ከሞት በኋላ ነው፤ መለያየት ከመሰብሰብ በኋላ ነው። በሁሉም ወቅቶች ሁኔታችን በዚህ ሁኔታ ይቀጥላል። በተቀሩትም ሁኔታዎቼ ከአላህ አልላቀቅምም አልተወውምም።

ከዐስር በኋላ ምሽት የገባ ጊዜም (አላህ ሆይ! በአንተ አመሸሁ፣ በአንተም አነጋሁ፣ በአንተም ህያው እንሆናለን፣ በአንተም እንሞታለን፣ መመለስም ወደ አንተ ነው።) ይሉ ነበር። በዱንያም መመለሻዬ፣ በመጨረሻም መመለሻዬ ወደ አንተ ነው። ህያው የምታደርገኝም አንተው ነህ፤ የምትገድለኝም አንተው ነህ። ማለት ነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. በንጋትና ምሽት ወቅት ነቢዩን (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና በመከተል አኳያ ይህን ዱዓ ማድረግ እንደሚወደድ እንረዳለን።
2. አንድ ባሪያ በሁሉም ሁኔታዎቹና ወቅቶቹ ወደ ጌታው ፈላጊ መሆኑን እንረዳለን።

3. ንጋት ላይ አዝካሮችን ለመቅራት በላጬ ወቅት የንጋቱን ጎህ ከወጣችበት ጀምሮ የቀኑ መጀመሪያ ላይ ፀሃይ እስክትወጣ ድረስ፤ የምሽቱን ከዓስር በኋላ ጀምሮ ፀሃይ ከመግባቷ በፊት ድረስ ያለው ወቅት ነው። ከዚህ በኋላ ቢለው ማለትም የንጋቱን ረፋዱ ከፍ ካለ በኋላ ቢለው ይበቃለታል። ከዙህር በኋላ ቢለውም ይበቃለታል። የምሽቱንም ከመግሪብ በኋላም ቢለው ይህ የዚክር ወቅት ስለሆነ ይበቃለታል።
4. "መቀስቀስም ወደ አንተ ነው።" የሚለው ንግግር ከንጋት ጋር የሚያገናኘው ይህ ቃል ሰዎች ከሞቱ በኋላና የትንሳኤ ቀን በሚቀሰቀሱ ጊዜ ያለውን ህያው መደረግና ትልቁን መቀስቀስ ስለሚያስታውሰው ነው። ከእንቅልፉ የሚነቃበት ይህ ቀንም ነፍሶች የሚመለሱበትና ሰዎች የሚበተኑበት፣ አላህ የፈጠረው አዲስ ንጋት የሚተነፍስበት አዲስ መቀስቀስና አዲስ ቀን ነው። ይህም አዲስ ንጋት በአደም ልጅ ላይ ምስክር እንዲሆን፣ ወቅቶቹና ሰአቶቹም የስራዎቻችን ድልብ የሚሆኑበት [ሌላ እድል] ነው።
5. "መመለስም ወደ አንተ ነው።" የሚለው ቃል የምሽት ዚክር ላይ ተስማሚ የሆነው፤ ሰዎች ከስራዎቻቸው፣ ለጥቅማቸውና ለኑሯቸው ከተበታተኑ በኋላ ወደ ቤታቸው በሚመለሱ ጊዜ ወደ የማደሪያቸው መጥተው ማረፍን ያዘወትራሉ። ይህም ወደ አላህ ተባረከ ወተዓላ መመለስን ያስታውሳል።

(5490)

(٣٢١) - عَنْ أَبَانَ بْنِ عُثْمَانَ قَالَ: سَمِعْتُ عُثْمَانَ ابْنِ عَفَّانَ رضي الله عنه يَقُولُ: سَمِعْتُ رَسُولَ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ يَقُولُ: «مَنْ قَالَ بِسْمِ اللهِ الَّذِي لَا يَضُرُّ مَعَ اسْمِهِ شَيْءٌ، فِي الْأَرْضِ، وَلَا فِي السَّمَاءِ، وَهُوَ السَّمِيعُ الْعَلِيمُ، ثَلَاثَ مَرَّاتٍ، لَمْ تُصِبْهُ فَجْأَةُ بَلَاءٍ، حَتَّى يُصْبِحَ، وَمَنْ قَالَهَا حِينَ يُصْبِحُ ثَلَاثُ مَرَّاتٍ، لَمْ تُصِبْهُ فَجْأَةُ بَلَاءٍ حَتَّى يُمْسِيَ»، قَالَ: فَأَصَابَ أَبَانَ بْنَ عُثْمَانَ الْفَالِجُ، فَجَعَلَ الرَّجُلُ الَّذِي سَمِعَ مِنْهُ الْحَدِيثَ يَنْظُرُ إِلَيْهِ، فَقَالَ لَهُ: مَا لَكَ تَنْظُرُ إِلَيَّ؟ فَوَاللهِ مَا كَذَبْتُ عَلَى عُثْمَانَ، وَلَا كَذَبَ عُثْمَانُ عَلَى النَّبِيِّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ، وَلَكِنَّ الْيَوْمَ الَّذِي أَصَابَنِي فِيهِ مَا أَصَابَنِي غَضِبْتُ فَنَسِيتُ أَنْ أَقُولَهَا. [صحيح] - [رواه أبو داود والترمذي وابن ماجه والنسائي في الكبرى وأحمد]

(321) - ከአባን ቢን ዑሥማን እንደተላለፈው እንዲህ አለ: «ዑሥማን ቢን ዐፋን (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና እንዲህ ሲሉ ሰማሁዋቸው: "የአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና እንዲህ ሲሉ ሰማሁዋቸው: ‹ሶስት ጊዜ 'ቢስሚላሂለዚ ላየዱሩ መዐስሚሂ ሸይኡን ፊልአርዲ ወላፊስሰማእ ወሁወስ'ሰሚዑል ዐሊም' (ትርጉሙም: በዚያ ከስሙ ጋር በምድርም ይሁን በሰማይ ምንም ነገር የማይጎዳ በሆነው እንዲሁም ሰሚና አዋቂ በሆነው አላህ ስም።) ያለ ሰው እስኪነጋ ድረስ ድንገተኛ መከራ አያገኘውም። በሚያነጋ ጊዜም ሶስት ጊዜ ያላት ሰው እስኪያመሽ ድረስ ድንገተኛ መከራ አያገኘውም።› አባን ቢን ዑሥማንን የግማሽ አካል ሽባነት አገኘውና ከርሱ ይሄን ሐዲሥ የሰማው ሰውዬም አተኩሮ ተመለከተው። አባንም ለርሱ እንዲህ አለው: እንደዚ አተኩረህ የምታየኝ ምን ሆነው ነህ? በአላህ እምላለሁ! በዑሥማን ላይ ምንም አልዋሸሁም! ዑሥማንም በነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ላይ ምንም አልዋሸም። ነገር ግን ዛሬ የደረሰብኝ ነገር የደረሰው ተቆጥቼ ስለነበር ይህን ዚክር ማለት ረስቼ ስለነበር ነው።"» [ሶሒሕ ነው።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ሁሉ ቀን ጎህ ከቀደደ በኋላ ንጋት ላይና ፀሀይ ከመግባቷ በፊት ደግሞ ሁሌ ምሽት ላይ ሶስት ጊዜ ይህንን ዚክር ያለ ሰው:(ቢስሚላሂ) በአላህ ስም ከሁሉም ጎጂ ነገር እጠበቃለሁም እታገዛለሁም። (ያ ስሙን ከማውሳት ጋር) ምንም ያህል ቢተልቅ (አንዳችም የማይጎዳው) (በምድርም ውስጥ) ከምድር የሚወጡ በሆኑ መከራዎችም (በሰማይ ውስጥም) ከሰማይ የሚወርዱ በሆኑ መከራዎችም (እርሱ ንግግራችንን ሰሚ) ሁኔታችንንም (አዋቂ ነው።) የምንጎዳ አይደለንም።

:በሚያመሽ ወቅት የተናገራት እስኪያነጋ ድረስ ድንገተኛ መከራ አያገኘውም። በሚያነጋ ወቅት የተናገራት ደግሞ እስኪያመሽ ድረስ ድንገተኛ መከራ አያገኘውም።

ሐዲሡን ያወራው አባን ቢን ዑስማንን በወቅቱ የሰውነቱ ግማሽ ሽባ የመሆን በሽታ አጋጥሞት ስለነበር ከርሱ ይሄን ሐዲሥ የሰማው ሰውዬም በግርምት አይን ተመለከተው። አባንም ለሰውዬው እንዲህ አለው "እንደዚህ የምትመለከተኝ ምን ሆነህ ነው? በአለህ እምላለሁ! በዑሥማንም ላይ አልዋሸሁም። ዑሥማንም በነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ላይ አልዋሸም። ነገር ግን ይህ በሽታ ባጋጠመኝ እለት አላህ እንድረሳው አልወሰነልኝም ነበር። የሚያስቆጣ ነገር አጋጠመኝና እነዚህን የተጠቀሱ ቃላቶች ማለትን ዘነጋሁኝ።"

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ሰውዬው በአላህ ፍቃድ ከድንገተኛ መከራ ወይም ከመከረኛ ጦስ ወይም ከመሳሰሉት የተጠበቀ እንዲሆን ንጋት ላይና ምሽት ላይ እነዚህን ዚክሮች ማለት እንደሚወደድ እንረዳለን።
2. የመጀመሪያዎቹ ቀደምቶች በአላህ ላይ ያላቸው እርግጠኝነትና የአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና በተናገሩት ላይ ያላቸው እምነት ጠንካራ መሆኑን እንረዳለን።

3. ዚክር በንጋትና በምሽት ላይ የመገደቡ ካሉት ጥቅሞች መካከል ከሙስሊም ላይ ዝንጉነትን መቁረጥና ዘውትር እርሱ የአላህ ባሪያ መሆኑን እንዲያስታውስ ማድረግ ይገኝበታል።
4. አላህን የሚያወሳው ሰው ካለው ኢኽላስና የቂን (እርግጠኝነት) ጋር ባለው ኢማን፣ መተናነስና ልቡን እንደማቅረቡ ልክ የዚክሩ ተፅዕኖም የተረጋገጠ ይሆናል።

(6093)

(٣٢٢) - عَن عبدِ اللهِ بن خُبَيب رضي الله عنه أنه قال: خَرَجْنَا فِي لَيْلَةِ مَطِيرَةٍ وَظُلْمَةٍ شَدِيدَةٍ، نَطْلُبُ رَسُولَ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ؛ يُصَلِّي لَنَا، قَالَ: فَأَدْرَكْتُهُ، فَقَالَ: «قُلْ»، فَلَمْ أَقُلْ شَيْئًا، ثُمَّ قَالَ: «قُلْ»، فَلَمْ أَقُلْ شَيْئًا، قَالَ: «قُلْ»، فَقُلْتُ: مَا أَقُولُ؟ قَالَ: «{قُلْ هُوَ اللهُ أَحَدٌ} وَالْمُعَوِّذَتَيْنِ حِينَ تُمْسِي وَتُصْبِحُ ثَلَاثَ مَرَّاتٍ، تَكْفِيكَ مِنْ كُلِّ شَيْءٍ». [صحيح] - [رواه أبو داود والترمذي والنسائي]

(322) - ከዐብደላህ ቢን ኹበይብ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: "በዝናባማና በድቅድቅ ጨለማ ምሽት የአላህ መልክተኛን (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እኛን እንዲያሰግዱን ፈልገን ወጣን። አገኘኋቸውና 'በል!' አሉኝ። ምንም አላልኩኝም። ቀጥለውም 'በል!' አሉኝ። ምንም አላልኩኝም። አሁንም 'በል!' አሉኝ። እኔም ምን ልበል? አልኳቸው። እርሳቸውም 'ሱረቱል ኢኽላስ እና ሁለቱን መጠበቂያዎች (ሱረቱል ፈለቅና ሱረቱን-ናስን) ስታመሽና ስታነጋ ሶስት ጊዜ ካልክ ለሁሉም ነገር ይበቁሃል።' አሉኝ።" [ሶሒሕ ነው።] - [አቡዳውድ፣ ቲርሚዚና ነሳኢ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ታላቁ ሶሐባ ዐብደላህ ቢን ኹበይብ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና በርካታ ዝናብ በሚዘንብበትና ድቅድቅ ጨለማ በነበረበት ምሽት የአላህን መልክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲያሰግዷቸው ፈልገው እንደወጡና እንዳገኟቸው ተናገረ።

ነቢዩም (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ለርሱ "በል!" ማለትም አንብብ! አሉት። እርሱም ምንም አላነበበም። ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ንግግራቸውን ሲደጋግሙለት ዐብደላህም "የአላህ መልክተኛ ሆይ! ምን ልቅራ?" አላቸው። ነቢዩም (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) "ሱረቱል ኢኽላስን እና ሁለቱን መጠበቂያዎች ሱረቱል ፈለቅ እና ሱረቱ አን-ናስን በምሽት ወቅትና በንጋት ወቅት ሶስት ጊዜ ቅራ! ከሁሉም ክፉትና ጉዳት ይጠብቅሃል።" አሉት።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ከሁሉም ክፉት መጠበቂያ ስለሆኑ ንጋትና ምሽት ላይ ሱረቱል ኢኽላስንና ሁለቱን መጠበቂያዎች መቅራት ይወደዳል።
2. የሱረቱል ኢኽላስንና ሁለቱ መጠበቂያዎችን መቅራት ትሩፋት እንረዳለን።

(6082)

(٣٢٣) - عَنْ عَائِشَةَ رضي الله عنها قَالَتْ: فَقَدْتُ رَسُولَ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ لَيْلَةً مِنَ الْفِرَاشِ فَالْتَمَسْتُهُ فَوَقَعَتْ يَدِي عَلَى بَطْنِ قَدَمَيْهِ وَهُوَ فِي الْمَسْجِدِ وَهُمَا مَنْصُوبَتَانِ، وَهُوَ يَقُولُ: «اللهُمَّ أَعُوذُ بِرِضَاكَ مِنْ سَخَطِكَ، وَبِمُعَافَاتِكَ مِنْ عُقُوبَتِكَ، وَأَعُوذُ بِكَ مِنْكَ لَا أُحْصِي ثَنَاءً عَلَيْكَ أَنْتَ كَمَا أَثْنَيْتَ عَلَى نَفْسِكَ». [صحيح] - [رواه مسلم]

(323) - ከእናታችን ዓኢሻ (ረዲየሏሁ ዐንሃ) -አላህ መልካም ሥራዋን ይውደድላትና- እንደተላለፈው እንዲህ ብላለች፦ «በአንድ ምሽት የአላህን መልክተኛ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ከፍራሼ ላይ አጣኋቸው። በዳሰሳ ስፈልጋቸውም እጄ መስገጃቸው ላይ የተተከለችው የእግራቸው ውስጥ ላይ አረፈች። እርሳቸውም እንዲህ እያሉ ነበር " አላሁመ አዑዙ ቢሪዷከ ሚን ሰኸጢክ፣ ወቢሙዓፋቲከ ሚን ዑቁበቲክ፣ ወአዑዙ ቢከ ሚንክ፣ ላኡሕሲ ሠናአን ዐለይክ አንተ ከማ አሠነይተ ዐላ ነፍሲክ"» ትርጉሙም "አላህ ሆይ! ከቁጣህ በውዴታህ፣ ከቅጣትህ በይቅር ባይነትህ እጠበቃለሁ፤ ከአንተ በአንተ እጠበቃለሁ፤ አንተ እራስህን

ያወደስከውን ያህል ላወድስህ አልችልም።" ማለት ነው። [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ዓኢሻ (ረዲየሏሁ ዐንሃ) -አላህ መልካም ሥራዋን ይውደድላትና- እንዲህ አለች "ከነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ጎን ተኝቼ ነበር። ሌሊት ላይ አጣኋቸሁ። ቤት ውስጥ ይሰግዱበት የነበረውን ስፍራ በእጄ ዳሰስኩ። በዛን ጊዜም ሱጁድ ላይ ተደፍተው እግራቸውን ተተክለው አገኘሁ። እርሳቸውም እንዲህ እያሉ ነበር:

(በውዴታህ) በኔ ላይም ይሁን በኡመቴ ላይ ከምትቆጣው (ቁጣህ) (እጠበቃለሁ) እቃረባለሁ። (ከቅጣትህ) ይቅር ባይነትህ ብዙ ነውና (በይቅር ባይነትህ) (እጠበቃለሁ)። (በአንተ ከአንተ እጠበቃለሁ።) ውብ በሆኑት ባህሪያትህ የልቅና መገለጫ ከሆኑት ባህሪያትህ እጠበቃለሁ። ከአንተ በቀር ከአንተ ለሚመጣው ቅጣት የሚጠብቅ የለምና። ወደ አላህ በመጠጋት ካልሆነ በቀርም ከአላህ መዳኛም መጠጊያም የለም። (በአንተ ላይ አወድሼ አልዘልቅም።) ፀጋህንና በጎ ውለታህን ቆጥሬ መዝለቅ ስለማልችል አንተ የሚገባህንም ውዳሴ በቁጥርም በገደብም ማወደሱን ብጥር እንኳ አልችልም። ለራስህ የሚገባውን በቂ ውዳሴ በራስህ ላይ ያወደስከው አንተ ብቻ ነህና (አንተ ነፍስህን ባወደስክበት ልክ ማወደስ አልችልም።) አንተን የማወደስ ሐቁን በአግባቡ መወጣት የሚችልስ ሌላ አካል ማን አለና!?

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ሱጁድ ላይ ይሄን ዱዓ ማለት ተወዳጅ እንደሆነ እንረዳለን።
2. ሚረክ እንዲህ ብለዋል: «በአንድ የነሳኢ ዘገባ ደሞ ይህን ዱዓ ሶላታቸውን አጠናቀው ወደ መኝታቸው ሲወጡ እንደሚሉት ተዘግቧል።»
3. አላህን በቁርአንና ሐዲሥ በመጡ ባህርያቱ ማወደስና በስሞቹ ዱዓ ማድረግ እንደሚወደድ እንረዳለን።
4. ይህ ሐዲሥ ፈጣሪን ሩኩዕና ሱጁድ ውስጥ ማላቅ እንደሚገባ ያስረዳናል።

5. በአላህ ሱብሓነሁ ወተዓላ ዛት መጠበቅ እንደሚፈቀደው በአላህ ባህሪም መጠበቅ እንደሚፈቀድ እንረዳለን።
6. ኸጧቢይ እንዲህ ብለዋል: "ይህ ንግግር ውስጥ ረቂቅ ሀሳብ ይገኛል። እርሱም: እርሳቸው ከአላህ ቁጣ በውዴታው፣ ከቅጣቱ ደሞ በይቅርታው ተጠበቁ። ውዴታና ቁጣ ሁለት ተቃራኒ ነገሮች ናቸው። እንዲሁም ይቅር ባይነትና በወንጀል መቅጣትም ተቃራኒ ናቸው። ለርሱ ተነፃፃሪ የሌለውን አላህን ሱብሓነሁ ወተዓላ ሲጠቅሱ ግን ከርሱ በሌላ ሳይሆን በራሱ ተጠበቁ። የዚህም ሀሳብ: ይቅር ባይነቱ የተጠየቀው አላህ ሊመለክና ሊወደስበት ከሚገባው መብቱ ስለማጓደላችን ነው። (በአንተ ላይ አወድሼ አልዘልቅም።) ሲሉ አንተን በሚገባህ ልክ ማወደስ የምችልበት አቅሙ የለኝም ማለታቸው ነው።"

(3566)

(٣٢٤) - عن سَمُرَةَ بن جندبٍ رضي الله عنه قال: قال رسول الله صلى الله عليه وسلم: «أَحَبُّ الْكَلَامِ إِلَى اللهِ أَرْبَعٌ: سُبْحَانَ اللهِ، وَالْحَمْدُ لِلهِ، وَلَا إِلَهَ إِلَّا اللهُ، وَاللهُ أَكْبَرُ، لَا يَضُرُّكَ بِأَيِّهِنَّ بَدَأْتَ».
[صحيح] - [رواه مسلم]

(324) - ከሰሙረህ ቢን ጁንዱብ -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: የአላህ መልክተኛ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንዲህ አሉ: "አላህ ዘንድ ተወዳጅ የሆኑ ንግግሮች አራት ናቸው። 'ሱብሓነላህ' (አላህ ሆይ! ጥራት ተገባህ) 'አልሐምዱ ሊላህ' (ምስጋና ለአላህ የተገባ ነው።) 'ላኢላሃ ኢለላህ' (ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ አምላክ የለም) 'አሏሁ አክበር' (አላህ ታላቅ ነው።) በማንኛቸውም ብትጀምር አይጎዳህም።" [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም አላህ ዘንድ ተወዳጅ ንግግሮች አራት መሆናቸውን ተናገሩ:

"ሱብሓነላህ": ማለትም አላህን ከሁሉም ጉድለት ማጥራት ነው።

"አልሐምዱ ሊላህ": አላህን ከመውደድና ከማላቅ ጋር በምሉዕነት ባህሪ መግለፅ ነው።

"ላኢላሃ ኢለላህ": ማለትም ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ አምላክ የለም።

"አላሁ አክበር": ማለትም አላህ ከሁሉም ነገር የበለጠ ታላቅና ሀያል ነው።

ትሩፋቷንና ምንዳዋን ለማግኘት የቃላቱን ቅደም ተከተል መጠበቅ ግዴታ አይደለም።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. በማንኛውም ቃል መጀመር ምንም ችግር አለማሳደሩ ሸሪዓ ገር መሆኑን ያስረዳናል።

(5475)

(٣٢٥) - عن أبي أيوب رضي الله عنه عن النبي صلى الله عليه وسلم قال: «مَنْ قَالَ: لَا إِلَهَ إِلَّا اللهُ وَحْدَهُ لَا شَرِيكَ لَهُ، لَهُ الْمُلْكُ وَلَهُ الْحَمْدُ وَهُوَ عَلَى كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ، عَشْرَ مِرَارٍ كَانَ كَمَنْ أَعْتَقَ أَرْبَعَةَ أَنْفُسٍ مِنْ وَلَدِ إِسْمَاعِيلَ». [صحيح] - [متفق عليه]

(325) - ከአቡ አዩብ -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንዲህ ብለዋል፦ "አስር ጊዜ 'ላ ኢላሃ ኢለሏህ ወሕደሁ ላ ሸሪከ ለህ ፤ ለሁል ሙልኩ ወለሁል ሐምዱ ወሁወ ዓላ ኩሊ ሸይኢን ቀዲር' ያለ ሰው ከኢስማዒል ዘሮች የሆኑ አራት ነፍሶችን ነፃ እንዳወጣ ይቆጠርለታል።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

በዚህ ሐዲሥ ነቢዩ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንደሚነግሩን ይህንን ውዳሴ ያለ፦ "ላ ኢላሃ ኢለሏህ ወሕደሁ ላ ሸሪከ ለህ ፤ ለሁል ሙልኩ ወለሁል ሐምዱ ወሁወ ዓላ ኩሊ ሸይኢን ቀዲር" ትርጉሙም: ከአላህ ውጪ በእውነት የሚመለክ አምላክ የለም፤ ብቸኛና ለሱ አጋር የለውም፤ ጥራት የተገባው አላህ

በምሉዕ ንግስና የተለየ ነው፤ ከሱ ውጪ ያሉት የማይገባቸውን ውዳሴና ሙገሳ ከውዴታና ልቅና ጋር በብቸኝነት የተገባው ነው ፤ እርሱም አንዳችም የማያቅተው ቻይ ነው። ይህንን ታላቅ ውዳሴም በቀን አስር ጊዜ የደጋገመም ሰው በነርሱ ላይ የአላህ ሶላትና ሰላም ይስፈንና የኢብራሂም ልጅ ከሆኑት ከኢስማዒል ዘሮች አራት ባሮችን ከባርነት ነፃ እንዳወጣ ሰው ምንዳ አምሳያ ለርሱ ይኖረዋል። የኢስማዒል ዐለይሂ ሰላም ዘሮች የተለዩትም እነርሱ ከሌሎች የላቁ ስለሆኑ ነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. የዚህ ውዳሴ ትሩፋት አላህን በተመላኪነት፣ በንግስና፣ በምስጋናና በተሟላ ችሎታ መነጠልን ያካተተ ነው።
2. ይህንን ውዳሴ አከታትሎም ሆነ በተለያየ ቆይታ ያለ ሰው የዚህን ውዳሴ ምንዳ እንደሚያገኝ እንረዳለን።

(5517)

(٣٢٦) - عن أبي هريرة رضي الله عنه عن النبي صلى الله عليه وسلم قال: «كَلِمَتَانِ خَفِيفَتَانِ عَلَى اللِّسَانِ، ثَقِيلَتَانِ فِي الْمِيزَانِ، حَبِيبَتَانِ إِلَى الرَّحْمَنِ: سُبْحَانَ اللهِ الْعَظِيمِ، سُبْحَانَ اللهِ وَبِحَمْدِهِ».

[صحيح] - [متفق عليه]

(326) - ከአቡ ሁረይራ -አላህ መልካም ስራውን ይውደድለትና- እንደተላለፈው የአላህ መልክተኛ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንዲህ ብለዋል: "ለምላስ ቀላል የሆኑ፣ ሚዛን ላይ የሚከብዱ፣ አርራህማን ዘንድ ተወዳጅ የሆኑ ሁለት ቃላቶች አሉ: ''ሱብሓነላሂ አልዐዚም ሱብሓነላሂ ወቢሐምዲሂ።'" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም የሰው ልጅ ያለምንም መጨናነቅና በማንኛውም ሁኔታ ላይ ሆኖ ስለሚናገራቸው ሁለት ቃላቶች ነገሩን። እነሱም ምንዳቸው ሚዛን ላይ የገዘፈ፣ ጌታችን አር-ራሕማንም የሚወዳቸው ናቸው።

"ሱብሓነላሂ አልዐዚም ሱብሐነላሂ ወቢሐምዲሂ" የሚሉት ናቸው። ደረጃቸው የላቀበትም ምክንያት የአላህን የልቅናና የምሉዕነት ባህሪያት የያዙ ፤ የላቀውንና የጠራውን አላህንም ከጉድለቶች ስለሚያጠሩ ነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. በላጬ ውዳሴ አላህን ማጥራትና ማወደስን የሰበሰበ ውዳሴ ነው።
2. አላህ በጥቂት ስራ ብዙ ምንዳ መመንዳቱ በባሮቹ ላይ ያለው እዝነት ሰፊ መሆኑን ይገልፅልናል።

(5507)

(٣٢٧) - عن أبي هريرة رضي الله عنه أن رسول الله صلى الله عليه وسلم قال: «مَنْ قَالَ: سُبْحَانَ اللهِ وَبِحَمْدِهِ، فِي يَوْمٍ مِائَةَ مَرَّةٍ، حُطَّتْ خَطَايَاهُ وَإِنْ كَانَتْ مِثْلَ زَبَدِ الْبَحْرِ». [صحيح] - [متفق عليه]

(327) - ከአቡ ሁረይራ -አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው የአላህ መልክተኛ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንዲህ ብለዋል፦ "በቀን ውስጥ መቶ ጊዜ ሱብሓነላሂ ወቢሐምዲሂ "ጥራት ምስጋና ለአላህ ይገባው።" ያለ ሰው (የወንጀሉ ብዛት) የባህር ዓረፋ አምሳያ ቢሆን እንኳ ወንጀሉ ይታበስለታል።" [ሶሒሕ ነው።] - [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

በቀን ውስጥ መቶ ጊዜ "ሱብሓነሏሂ ወቢሐምዲሂ" (ጥራት ምስጋና ለአላህ ይገባው።) ያለ ሰው ባህር በሚናወጥ ወቅት ከላዩ እንደሚንጣለለው ነጭ አረፋ አምሳያ ወንጀሉ የበዛ ቢሆን እንኳ ወንጀሉ ይማራል ይታበሳል ብለው ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እየተናገሩ ነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ይህን ምንዳ የሚያገኘው በቀን ውስጥ አከታትሎም ይሁን በተለያየ ጊዜ እነዚህን ቃላት ያለ ሰው ነው።

2. ተስቢሕ ማለት: - አላህን ከጉድለት ማጥራት ሲሆን ፤ ሐምድ ማለት ደግሞ አላህን ከመውደድና ከማላቅ ጋር በምሉዕነት መግለፅ ነው።
3. በሐዲሡ ወንጀልን ማስማር ከሚለው የተፈለገበት ትናንሽ ወንጀሎችን ብቻ ነው። ትላልቅ ወንጀሎች ግን የግድ ተውበት ያስፈልጋቸዋል።

(5516)

(٣٢٨) - عن أبي مالكٍ الأشعريِّ رضي الله عنه قال: قال رسول الله صلى الله عليه وسلم: «الطُّهُورُ شَطْرُ الْإِيمَانِ، وَالْحَمْدُ لِلهِ تَمْلَأُ الْمِيزَانَ، وَسُبْحَانَ اللهِ وَالْحَمْدُ لِلهِ تَمْلَآنِ -أَوْ تَمْلَأُ- مَا بَيْنَ السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضِ، وَالصَّلَاةُ نُورٌ، وَالصَّدَقَةُ بُرْهَانٌ، وَالصَّبْرُ ضِيَاءٌ، وَالْقُرْآنُ حُجَّةٌ لَكَ أَوْ عَلَيْكَ، كُلُّ النَّاسِ يَغْدُو، فَبَايِعٌ نَفْسَهُ فَمُعْتِقُهَا أَوْ مُوبِقُهَا». [صحيح] - [رواه مسلم]

(328) - አቢ ማሊክ አልአሽዐሪይ - አላህ መልካም ሥራቸው ይውደድላቸውና - እንዲህ ብለዋል፦ የአላህ መልክተኛ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ አሉ: "ንፅህና የኢማን ግማሽ ነው 'አልሐምዱ ሊላህ' (ምስጋና ለአላህ የተገባ ነው) የሚለው ሚዛን ይሞላል፤ 'ሱብሐነላህ ወል'ሐምዱ ሊላህ' (አላህ ጥራት የተገባው ነው፤ ምስጋናም ሁሉ ለአላህ ነው) የሚለው በሰማያትና በምድር መካከል ያለውን ይሞላሉ ወይም ይሞላል ፤ ሰላት ብርሃን ነው፣ ምጽዋት ማስረጃ ነው፣ ትዕግስት ወገግታ (አንፀባራቂ ብርሃን) ነው፣ ቁርኣን ላንተ ወይም በአንተ ላይ ማስረጃ ነው። ሁሉም ሰው በማለዳ ወጥቶ ነፍሱን ይሸጣል። ወይ ከጥፋት ነፃ ያወጣታል ወይም ወደ ጥፋት ይጥላታል። " [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ውጫዊ ንፅህና በውዱ እና በገላ ትጥበት የሚተገበር እንደሆነና የሰላት ቅድመ መስፈርት እንደሆነም ይነግሩናል ። "አልሐምዱሊላህ ሚዛንን ትሞላለች " የሚለው ነቢያዊ ንግግር :- ጥራት ይገባውና አላህን ማወደስ እንዲሁም ምሉዕ በሆኑ ባህሪያቶች እሱን መግለፅ፥ የትንሳኤ ቀን ስትመዘን የስራዎችን ሚዛን ትሞላለች ማለት ነው።

"ሱብሐነላሀ ወልሐምዱሊላህ " የሚለውን መናገር አላህን ከሁሉም ጉድለት ማጥራትና እሱን ከመውደድና ማላቅ ጋር ለግርማው የሚመጥን በሆነ የተሟላ ምሉዕነት መግለፅ ሲሆን በሰማያትና ምድር መሀል ያለውንም ይሞላል። "ሰላት ብርሃን ነው። " ለአንድ ሰው ለቀልቡም፣ ለፊቱም ፣ በቀብሩም ውስጥ ፣ በትንሳኤ ቀንም ብርሃን ይሆንለታል። "ምፅዋት ማስረጃ ነው።" ምፅዋት የአንድ አማኝ ኢማን እውነተኝነትንና ለምፅዋት የተገባውን ቃልኪዳን ባለማመኑ ምፅዋት ከመስጠት ከሚታቀበው ሙናፊቅ ተቃራኒ መሆኑንም የሚጠቁም ማስረጃ ነው። "ትእግስት (አንፀባራቂ ብርሃን) ወገግታ ነው።" ትእግስት ማለት ነፍስን ከትእግስት ማጣትና መበሳጨት መቆጣጠር ሲሆን ትእግስት እንደ ፀሀይ ብርሀን ሀሩርና ማቃጠል አብሮት የሚኖር ብርሃን ነው። ምክንያቱም መታገስ ነፍስን መታገልና ከዝንባሌዋ ማቀብ የሚፈልግ ስለሆነ አስቸጋሪ ነው። ታጋሽ ሰው ብርሃናማ፣ የተመራና በትክክለኛነት ላይ ዘውታሪ ከመሆን አይወገድም። ትእግስት ሲባል አላህን በመታዘዝ ላይ ፣ አላህን ከመወንጀል በመራቅ ላይ መታገስ እና ከመከራና አለማዊ የችግር ዓይነቶች ላይ መታገስ ነው። ቁርኣንን ማንበብና ተግባራዊ በማድረግ ምክንያት "ቁርኣን ላንተ ማስረጃ

ነው።" ወይም በሱ ሳይሰሩና ሳያነቡ ቁርኣንን በመተዉ ምክንያት "በአንተ ላይ ማስረጃ ይሆናል።" ቀጥሎ ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ሰዎች ሁሉ እንደሚለፉ፣ ለተለያዩ ተግባራትም እንደሚበታተኑ፣ ከእንቅልፋቸው በመንቃት ለተለያዩ ተግባራት ከቤቶቻቸው እንደሚወጡ ተናገሩ። ከነሱም መካከል በአላህ ትእዛዝ ላይ በመፅናት ነፍሱን ከእሳት ነፃ የሚያወጣ ሲኖር ፤ ከነሱም ውስጥ ከዚህ የአላህ ትእዛዝ በመዘንበል ወንጀል ውስጥ የሚወድቅና ነፍሱ እሳት ውስጥ በመግባቷ ለጥፋት የሚዳርጋት አለ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ንፅህና ሁለት አይነት ነው። ውጫዊ ንፅህና በዉዱእ እና በገላ ትጥበት ሲሆን፤ ውስጣዊ ንፅህና ደግሞ በተውሒድ፣ በኢማንና መልካም ስራ የሚመጣ ነው።

2. ሰላት ለአንድ ባሪያ በዱንያም ሆነ በትንሳኤ ቀን ብርሃን ስለሆነ ሰላትን በጥንቃቄ መስገድ አንገብጋቢ ጉዳይ መሆኑን እንረዳለን።
3. ምፅዋት የእውነተኛ ኢማን ማስረጃ ነው።
4. ቁርኣን በአንተ ላይ ሳይሆን ለአንተ ማስረጃ እንዲሆን ቁርኣንን መተግበር እና ማመን አንገብጋቢ ጉዳይ መሆኑን እንረዳለን።
5. ነፍስ በአምልኮ ካልጠመድካት በወንጀል ታጠምድሀለች።
6. ሁሉም ሰው መስራቱ የማይቀር ጉዳይ ነው። ወይ ነፍሱን በአምልኮ ነፃ ያወጣታል ወይም በወንጀል ለጥፋት ይዳርጋታል።
7. ትዕግስት እጅግ አስቸጋሪ በመሆኑ ቻይነትንና ምንዳን ከአላህ ማሰብ ይፈልጋል።

(65004)

(٣٢٩) - عن أبي هريرة رضي الله عنه قال: قال رسول الله صلى الله عليه وسلم: «لَأَنْ أَقُولَ: سُبْحَانَ اللهِ، وَالْحَمْدُ لِلهِ، وَلَا إِلَهَ إِلَّا اللهُ، وَاللهُ أَكْبَرُ، أَحَبُّ إِلَيَّ مِمَّا طَلَعَتْ عَلَيْهِ الشَّمْسُ».

[صحيح] - [رواه مسلم]

(329) - ከአቡ ሁረይራ -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ ብሏል: "የአላህ መልዕክተኛ ሶለሏሁ ዓለይሂ ወስለም እንዲህ ብለዋል፡ "ሱብሓነሏህ ወልሐምዱሊላህ ወላኢላሃ ኢለሏህ ወሏሁ አክበር' ማለቴ ፀሀይ የወጣችበት ክልል ሁሉ (ከሚሰጠኝ) የበለጠ ወደእኔ እጅግ ተወዳጅ ነው።'" [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም በነዚህ ትላልቅ ቃላቶች አላህን ማወደስ ከዱንያና በውስጧ ካለው ሁሉ የተሻለ መሆኑን ተናገሩ። እነሱም:

"ሱብሓነሏህ" ይህም አላህን ከጉድለት ማጥራት ነው።

"አልሐምዱሊላህ" ይህም አላህን ከመውደድና ከማላቅ ጋር በምሉዕ ባህሪያቶቹ ማወደስ ነው።

"ላኢላሃ ኢለሏህ" ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ አምላክ የለም።

"አሏሁ አክበር" አላህ ከሁሉም ነገር የበለጠ ታላቅ ነው ማለት ነው።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. አላህን በማውሳት ላይ መነሳሳቱ። አላህን ማውሳት ፀሀይ የወጣችበት ክልል ሁሉ ከሚሰጠን የበለጠ ተወዳጅ ነውና።
2. ውዳሴ ማብዛት ደረጃና ምንዳ ስላለው በርሱ ላይ መነሳሳቱን እንረዳለን።
3. የዱንያ መጠቀሚያ ትንሽ ነው። ስሜትን የሚያስደስቱ ነገሮቿ ጠፊ ናቸው።

(6211)

(٣٣٠) - عن جابر رضي الله عنه قال: سمعت رسول الله صلى الله عليه وسلم يقول: «أَفْضَلُ الذِّكْرِ: لَا إِلَهَ إِلَّا اللهُ، وَأَفْضَلُ الدُّعَاءِ: الْحَمْدُ لِلهِ».

[حسن] - [رواه الترمذي والنسائي في الكبرى وابن ماجه]

(330) - ጃቢር ረዲየሏሁ ዐንሁ እንዲህ ማለቱ ተላልፏል: "የአሏህ መልዕክተኛ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን እንዲህ ሲሉ ሰምቻለሁ: "በላጩ ዚክር 'ላ ኢላሃ ኢለሏህ' ማለት ሲሆን  በላጩ ዱዓእ ደግሞ 'አልሐምዱሊላህ' ማለት ነው።'" [ሐሰን ነው።] - [ቲርሚዚ፣ ነሳኢ በኩብራ ውስጥ፣ ኢብኑ ማጀህ ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን በላጩ ዚክር "ላ ኢላሃ ኢለሏህ" - ትርጉሙም: ከአሏህ በቀር በእውነት አምልኮ የሚገባው የለም - መሆኑን፤ ከዱዓእ በላጩ ደግሞ "አልሐምዱሊላህ" - ትርጉሙም: ፀጋንም የሚውለው ለተሟላ ውብ መገለጫም የተገባው እርሱ አላህ ብቻ መሆኑን ማመን - እንደሆነ ተናገሩ።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. አሏህን በተውሒድ ቃል ማስታወስና በምስጋና ቃል መማፀን ማብዛት መበረታታቱን እንረዳለን።

(3567)

(٣٣١) - عن خَوْلَةَ بِنْتَ حَكِيمٍ السُّلَمِيَّةَ قالت: سَمِعْتُ رَسُولَ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ يَقُولُ: «مَنْ نَزَلَ مَنْزِلًا ثُمَّ قَالَ: أَعُوذُ بِكَلِمَاتِ اللهِ التَّامَّاتِ مِنْ شَرِّ مَا خَلَقَ، لَمْ يَضُرَّهُ شَيْءٌ حَتَّى يَرْتَحِلَ مِنْ مَنْزِلِهِ ذَلِكَ». [صحيح] - [رواه مسلم]

(331) - ከኸውለህ ቢንት ሐኪም አስሱለሚየህ እንደተላለፈው እንዲህ አለች: "የአላህ መልክተኛ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንዲህ ሲሉ ሰምቻለሁ: "በአንድ ስፍራ ላይ አርፎ ከዚያም ‹አዑዙ ቢከሊማቲላሂ አትታማቲ ሚን ሸሪ ማ ኸለቀ (ምሉዕ በሆኑ የአላህ ቃላት ከፈጠራቸው ጎጂ ነገሮች እጠበቃለሁ)› ያለ ሰው ከዛ ስፍራ እስኪንቀሳቀስ ድረስ አንዳችም አይጎዳውም።" [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም የሰው ልጅ አንድ ስፍራ ላይ በሚያርፍበት ጊዜ የሚፈራቸውን ሁሉ አስፈሪ ነገሮች የሚከላከልበትን ጠቃሚ መጠበቂያና መጠጊያ ለኡመታቸው እየጠቆሙ ነው። ይህም ጉዞም ላይ ይሁን ሊዝናናም ይሁን ወይም ከዛ ውጪ ባረፈበት ስፍራ ላይ ከሚገኝ ፍጡራን ሁሉ ክፋት በትሩፋቱ፣ በበረከቱና በጥቅሙ የተሟላ በሆነውና ከሁሉም ነውርና ጉድለት የፀዳ በሆነው የአላህ ቃል ከተጠበቀና ከተጠጋ በዛ ስፍራ እስካለ ድረስ ከሁሉም ጎጂ ነገሮች ደህንነቱ ይጠበቃል።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. በአላህ መጠበቅ አምልኮ ነው። የተፈቀደ የሚሆነውም በአላህ ወይም በስሞቹና በባህሪያቶቹ ሲጠበቅ ነው።
2. ከአላህ ባህሪያቶች መካከል አንዱ በሆነው የአላህ ቃል መጠበቅ እንደሚፈቀድ እንረዳለን። ይህም በማንኛውም ፍጡር ከመጠበቅ ተቃራኒ ሲሆን ከአላህ ውጪ ካለ አካል ጥበቃን መሻት ሺርክ ነው።
3. የዚህ ዱዓእ ትሩፋትና በረከትን እንረዳለን።

4. በዚክሮች መመሸግ (መከላከል) ሰው ከክፋቶች እንዲጠበቅ አንዱ ሰበብ ነው።
5. በጋኔን ፣ በጠንቋይ፣ በአታላዮችና በሌሎችም ከአላህ ውጪ ባሉ አካላት ጥበቃ መፈለግ ውድቅ መደረጉ፤
6. ይህ ዱዓእ በሀገሩም ይሁን በጉዞ አንድ ስፍራ ላይ ላረፈ ሰው መደንገጉን እንረዳለን።

(5932)

(٣٣٢) - عَنْ أَبِي حُمَيْدٍ أَوْ عَنْ أَبِي أُسَيْدٍ قَالَ: قَالَ رَسُولُ اللهِ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ: «إِذَا دَخَلَ أَحَدُكُمُ الْمَسْجِدَ فَلْيَقُلِ: اللَّهُمَّ افْتَحْ لِي أَبْوَابَ رَحْمَتِكَ، وَإِذَا خَرَجَ فَلْيَقُلِ: اللَّهُمَّ إِنِّي أَسْأَلُكَ مِنْ فَضْلِكَ». [صحيح] - [رواه مسلم]

(332) - ከአቡ ሑመይድ ወይም አቡ ኡሰይድ እንደተዘገበው እንዲህ አለ: "የአላህ መልዕክተኛ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ብለዋል: ‹አንዳችሁ መስጂድ የገባ ጊዜ: 'አልላሁምመፍተሕ ሊ አብዋበ ረሕመቲከ' (ትርጉሙም: አላህ ሆይ! ለኔ የእዝነትህን በሮች ክፈትልኝ) ይበል። የወጣ ጊዜም 'አልላሁምመ ኢኒ አስአሉከ ሚን ፈድሊክ' (ትርጉሙም: አላህ ሆይ! እኔ ከትሩፋትህ እጠይቅሀለሁ።) ይበል።›" [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) መስጂድ በሚገባ ወቅት የሚባለውን ዱዓ ለኡመታቸው ጠቆሙ። (አልላሁምመ ኢፍተሕ ሊ አብዋበ ረሕመቲክ) (አላህ ሆይ! ለኔ የእዝነትህን በሮች ክፈትልኝ) የእዝነትን ምክንያቶች ለርሱ እንዲያመቻችለት አላህን ይጠይቃል። ከመስጂድ ለመውጣት የፈለገ ጊዜም (አልላሁምመ ኢኒ አስአሉከ ሚን ፈድሊክ) (አላህ ሆይ! እኔ ከትሩፋትህ እጠይቅሀለሁ።) ይበል። አላህን ከችሮታውና ከሐላል ሲሳዩ ተጨማሪ ፀጋዎቹን ይጠይቃል።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ወደ መስጂድ በሚገባ ወቅትና ከመስጂድ በሚወጣ ወቅት ይህን ዱዓ ማድረግ እንደሚወደድ እንረዳለን።
2. ሲገባ እዝነትን በመጠየቅ ላይ ሲወጣ ደሞ ችሮታን በመጠየቅ ላይ የተገደበው: መስጂድ የሚገባ ሰው ወደ አላህና ወደ ጀነት በሚያቃርበው ነገሮች ላይ ነው የሚጠመደው ስለዚህ ከቦታው ጋር የሚስማማው እዝነትን መጠየቅ ነው። የወጣ ጊዜ ደሞ ከሲሳይ የአላህን ችሮታ ለመፈለግ በምድር ላይ ስለሚሯሯጥ ከቦታው ጋር የሚስማማው ችሮታ መወሳቱ ነው።
3. እነዚህ ዚክሮች የሚባሉት መስጂድ መግባትና መውጣት ሲፈለግ እንደሆነ እንረዳለን።

(65092)

(٣٣٣) - عَنْ جَابِرِ بْنِ عَبْدِ اللهِ رضي الله عنهما أَنَّهُ سَمِعَ النَّبِيَّ صَلَّى اللهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ يَقُولُ: «إِذَا دَخَلَ الرَّجُلُ بَيْتَهُ، فَذَكَرَ اللهَ عِنْدَ دُخُولِهِ وَعِنْدَ طَعَامِهِ، قَالَ الشَّيْطَانُ: لَا مَبِيتَ لَكُمْ، وَلَا عَشَاءَ، وَإِذَا دَخَلَ، فَلَمْ يَذْكُرِ اللهَ عِنْدَ دُخُولِهِ، قَالَ الشَّيْطَانُ: أَدْرَكْتُمُ الْمَبِيتَ، وَإِذَا لَمْ يَذْكُرِ اللهَ عِنْدَ طَعَامِهِ، قَالَ: أَدْرَكْتُمُ الْمَبِيتَ وَالْعَشَاءَ». [صحيح] - [رواه مسلم]

(333) - ከጃቢር ቢን ዐብደላህ (ረዲየሏሁ ዐንሁማ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እርሱ ነቢዩን (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) እንዲህ ሲሉ ሰማ: "አንድ ሰው ወደ ቤቱ ሲገባ በሚገባበት ወቅትም በሚበላበት ወቅትም አላህን ካወሳ ሰይጣን (ለባልደረቦቹ) 'ማደሪያም እራትም የላችሁም።' ይላል። በሚገባ ወቅት አላህን ሳያወሳ የገባ እንደሁ ሰይጣን 'ማደሪያ አግኝታችኋል' ይላል። በሚበላበት ወቅትም አላህን ካላወሳ ደግሞ 'ማደሪያም እራትም አግኝታችኋል።' ይላል።" [ሶሒሕ ነው።] - [ሙስሊም ዘግበውታል።]

## ትንታኔ:

ነቢዩ ( የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ቤት በሚገባ ወቅትና ምግብ ከመመገባችን በፊት አላህን ማውሳት አዘዙ። እርሱ ቤት በሚገባ ወቅትና ምግቡን በሚጀምር ወቅት አላህን (ቢስሚላህ) በማለት ያወሳ ጊዜ ሰይጣን ለግብረ አበሮቹ "እዚህ ባለቤቱ አላህን በማውሳት ከናንተ የተጠበቀበት በሆነው ቤት ውስጥ ምንም ማደሪያም እራትም የላችሁም።" ይላቸዋል። ሰውዬው ቤቱ በሚገባ ወቅትና ምግብ በሚመገብበት ወቅት አላህን ካላወሳ ግን ሰይጣን ለግብረአበሮቹ እዚህ ቤት ውስጥ ማደሪያም እራትም እንዳገኙ ይናግራቸዋል።

## ከሐዲሱ የምንጠቀማቸው ቁምነገሮች:

1. ቤት በሚገቡበትና ምግብ በሚመገቡበት ወቅት አላህን ማውሳት እንደሚወደድ እንረዳለን። የቤቱ ባለቤቶች አላህን ካላወሱ ሰይጣን ቤቶች ውስጥም ያድራል፤ ከባለቤቶቹ ምግብም ይመገባል።
2. ሰይጣን የሰውን ልጅ በስራው፣ በእንቅስቃሴውና በሁሉም ጉዳዩ ይጠባበቀዋል። ሰው ከዚክር (ከውዳሴ) በተዘናጋ ጊዜ ሸይጧንም ከርሱ የሚፈልገው ፍላጎቱን ያገኛል።
3. ዚክር (ውዳሴ) ሰይጣንን እንደሚያባርር እንረዳለን።
4. ሁሉም ሰይጣን በንግግሩ የሚደሰቱና ትእዛዙን የሚከተሉት ተከታይና ወዳጆች እንዳሉት እንረዳለን።

(3037)

መቅድም ........ 1

ስራዎች የሚለኩት በኒያዎች) በሀሳብ (ብቻ ነው። ሁሉም ሰው የሚያገኘው ያሰበውን ነው።........ 2

›በዚህ በመመሪያችን ውስጥ ከርሱ) ከትእዛዛችን (የሌለን አዲስ ነገር የፈጠረ ሰው እርሱ) የፈጠረው አዲስ ነገር (ተመላሽ ነው። ........ 3

ኢስላም ማለት ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ አምላክ እንደሌለና ሙሐመድም የአላህ መልክተኛ መሆናቸውን ልትመሰክር፣ ሰላት ደንብና ስርዓቱን ጠብቀህ ልትሰግድ፣ ዘካን ልትሰጥ ፣ ረመዷንን ልትፆምና ወደርሱ መንገድን ከቻልክም የአላህን ቤት ልትጎበኝ ሐጅ ልታደርግ ነው።........ 5

እስልምና በአምስት መሰረቶች ተገነባ ........ 9

አላህ በባሮቹ ላይ ያለው ሐቅ ሊገዙትና በሱ ላይም አንዳችንም ላያጋሩ ሲሆን፤ ባሮች በአላህ ዘንድ ያላቸው ሐቅ ደግሞ በሱ ላይ አንዳችንም ያላጋራን ላይቀጣ ነው።........11

አላህ በእርሱ ላይ እሳትን እርም ቢያደርግ እንጂ አንድም በእውነተኛ ልቡ ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ አምላክ እንደሌለ ሙሐመድም የአላህ መልክተኛ መሆናቸውን የሚመሰክር የለም። ........13

ላኢላሃ ኢለሏህ ብሎ ከአላህ ውጪ በሚመለኩ ነገሮች የካደ ሰው ገንዘቡም ደሙም እርም ይሆናል። ሂሳቡ ያለው አላህ ላይ ነው።' ........ 15

በአላህ ላይ አንዳችንም ሳያጋራ የሞተ ሰው ጀነት ገባ፤ በአላህ ላይ አንዳችን እያጋራ የሞተ ሰው እሳት ገባ። "አሉ።16

ከአላህ ውጪ ሌላን ቢጤን) ባላንጣን (እየተጣራ የሞተ ሰው እሳት ገባ። ........ 17

አንተ የመጽሐፍ ባለቤት ወደሆኑ ህዝቦች ትሄዳለህ። ስለዚህም እነርሱ ዘንድ ስትደርስ ከአሏህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ አምላክ እንደሌለና ሙሐመድም የአሏህ መልዕክተኛ መሆናቸውን ........18

የቂያማ ቀን በኔ አማላጅነት ከሰዎች ሁሉ ይበልጥ እድለኛ የሚሆኑት ጥርት ባለ መልኩ ከልባቸው ወይም ከነፍሳቸው' ላ ኢላሃ ኢለሏህ 'ያሉት ናቸው።' ........20

ኢማን ሰባ ምናምን ወይም ስልሳ ምናምን ክፍሎች አሉት። በላጬ ክፍልም' ላኢላሃ ኢለሏህ 'ማለት ሲሆን ዝቅተኛው ክፍል መጥፎን ነገር ከመንገድ ላይ ማስወገድ ነው። ........ 22

ነቢዩን) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና' (አላህ ዘንድ እጅግ ትልቁ ወንጀል ምንድነው '?ብዬ ጠየቅኩ። እርሳቸውም' አላህ ፈጥሮህ ሳለ ለርሱ ቢጤን ማድረግክ ነው።........23

እኔ በሽርክና ከማጋራት ከተብቃቁ ሁሉ እጅግ የተብቃቃሁ ነኝ። ከኔ ጋር ሌላን አጋርቶ ስራን የሰራ እሱንም ማጋራቱንም እተወዋለሁ።' ........ 25

ሁሉም ህዝቦቼ ጀነት ይገባሉ እምቢ ያለ ሲቀር ........ 26

ክርስቲያኖች የመርየም ልጅን ሲያሞግሱ ወሰን እንዳለፉት እኔን ስታሞግሱ ወሰን አትለፉ። እኔ የአሏህ ባሪያ ብቻ ነኝ። ስለዚህም የአላህ ባሪያና መልክተኛው በሉኝ።' ........ 27

አንዳችሁ ከወላጆቹ ፣ ከልጁና ከሰዎች ባጠቃላይ እርሱ ዘንድ እጅግ ተወዳጁ እኔ እስክሆን ድረስ አላመነም።'.. 28

በተውኳችሁ ላይ ተዉኝ። ከናንተ በፊት የነበሩት ህዝቦች የጠፉት በመጠየቃቸውና ነቢያቶቻቸውን በመቃረናቸው ነው። ........ 29

አንዲትም አንቀጽ ቢሆን ከኔ አስተላልፉ። ከቤተ እስራኤላውያንም አውሩ ችግር የለውም። ሆን ብሎ በኔ ላይ የዋሸ መቀመጫውን ከእሳት ያመቻች። ........32

አዋጅ !ከእኔ የሆነ ሐዲሥ ወደ አንዱ በአልጋው ላይ እንደተደገፈ ይደርሰውና፡" በእኛና በእናንተ መካከል) የሚዳኘን (የአላህ መጽሐፍ ነው........33

በአይሁድ እና ክርስቲያኖች ላይ የአላህ እርግማን ይውረድ ! የነቢያቶቻቸውን መቃብር መስገጃ አድርገው ያዙ።35

አሏህ ሆይ !ቀብሬን ጣኦት........36

ቤቶቻችሁን መቃብር አታድርጉ !ቀብሬንም የሚጎበኝ የበአል ስፍራ አታድርጉት !ይልቅ በኔ ላይ ሶለዋት አውርዱ !የትም ብትሆኑ ሶለዋታችሁ ትደርሰኛለችና። ........37

እነዚህ ከመካከላቸው መልካም) ጻድቅ (ባርያ ወይም መልካም ሰው ሲሞት በመቃብሩ ላይ መስገጃን የሚገነቡ39

እኔ ከናንተ መካከል ፍፁም ወዳጅ ከመያዝ ወደ አላህ እጥራራለሁ። ምክንያቱም የላቀው አሏህ ኢብራሂምን ፍፁም ወዳጅ ........ 41

የአላህ መልክተኛ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም በላኩኝ ነገር ላይ ልላክህን ?ማንኛውም ምስልን) ስታገኝ (ያስወገድከው ቢሆን እንጂ ላትተወው ነው፤ ማንኛውም ከፍ ያለ ቀብርንም ያስተካከልከው ቢሆን እንጂ ላትተወው ነው።' ............ 43
የገድ እምነት ሺርክ ነው። የገድ እምነት ሺርክ ነው። የገድ እምነት ሺርክ ነው።) አሉ ሶስት ጊዜ '(ከኛ መካከል በልቡ የገድ እምነት የሚመጣበት እንጂ አንድም የለም። ነገር ግን አላህ በርሱ ላይ በመመካታችን ምክንያት ያስወግደዋል። ......... 44
የገድ ተግባርን የፈፀመ ወይም ለሱ የተፈፀመለት፣ ወይም የጠነቆለ ወይም ያስጠነቆለ፣ ወይም የደገመ ወይም ያስደገመ፣ ............ 45
በራሱ የሚተላለፍ ተላላፊ በሽታ የለም፣ ገድም የለም ተስፈኝነት) በጎ ምኞት (ግን ያስደስተኛል።" "አልፈእል) በጎ ምኞት ( ምንድነው "?ተባሉ። እርሳቸውም" መልካም ንግግር ነው። "አሉ። ............ 47
ጌታችሁ ምን እንዳለ ታውቃላችሁን "?ሰሓቦችም" አላህና መልክተኛው ያውቃሉ "አሉ። እርሳቸውም አላህ እንዲህ አለ፦ "ከባሮቼ በኔ ያመነም የካደም ሆኖ ያነጋ አለ ............ 48
ሒርዝ ያንጠለጠለ ሰው በርግጥም አጋርቷል '!አሉ። ............ 50
ማነብነብ) ሩቃ (፣ ሂርዝ ማንጠልጠልና መስተፋቅር ሽርክ ናቸው። ............ 51
ሩቅ አዋቂ ነኝ ባይ ጋር የሄደና ስለአንዳች ነገር የጠየቀው የአርባ ሌሊት ሶላቱ ተቀባይነት አይኖራትም። ............ 53
ከአሏህ ውጭ ባለ አካል የማለ ከፍሯል ወይም አጋርቷል።' ............ 54
እኔ ወላሂ አላህ ከሻ በአንድ ጉዳይ ከማልኩ በኋላ ተቃራኒው የተሻለ ሆኖ ከታየኝ የተሻለውን ፈፅሜ ለመሀላዬ ማካካሻ አደርጋለሁ እንጂ ከዚህ ውጪ ሌላ አላደርግም። "አሉን። ............ 55
አላህ ከሻ) ከፈለገ (እና እከሌ ከሻ) ከፈለገ '(አትበሉ። ይልቁንም' አላህ ከሻ) ከፈለገ (ከዚያም እከሌ ከሻ) ከፈለገ '(በሉ። ............ 57
በናንተ ላይ ከምፈራው ነገር እጅግ አስፈሪው ትንሹ ሺርክ ነው። "ሶሐቦችም" የአላህ መልክተኛ ሆይ !ትንሹ ሺርክ ምንድነው "? ብለው ጠየቁ። እሳቸውም" ይዩልኝ ነው። ............ 59
በሰዎች ውስጥ ሁለት ነገሮች አሉ፤ ክህደት ናቸው። በዘር መተቻትና በሞተ ላይ ሙሾ ማውረድ ናቸው። ............ 60
መቃብሮች ላይ አትቀመጡ !ወደርሷም አትስገዱ'! ............ 61
መላዕክቶች ውሻና ስዕል ወዳለበት ቤት አይገቡም። ............ 62
መላእክት ውሻ እና ቃጭል ካላቸው መንገደኞች ጋር አብረው) አይጎዳኙም (አይሄዱም። ............ 63
ሰይጣን አንዳችሁ ዘንድ በመምጣት" ይህን የፈጠረው ማነው ?ይህንንስ የፈጠረው "?እያለ ይጠይቃችኋል" ጌታህንስ የፈጠረው ማነው "?ብሎ እስኪጠይቃችሁ ድረስ ይደርሳል፤ ይህ ጥያቄ የደረሰው ጊዜ በአላህ ይጠበቅም ይከልከልም። ............ 65
›የኔን ወዳጅ) ወሊይ (ጠላት አድርጎ የያዘን ሰው በርግጥም ጦርነት እንዳወጀኩበት አሳውቄዋለሁ። ባሪያዬ ግዴታ ካደረግኩበት በበለጠ ወደ እኔ ተወዳጅ በሆነ በአንዳችም ነገር አይቃረብም። ............ 66
አላህን በመፍራት፤ የሐበሻ ባሪያ እንኳ ቢሆን) መሪያችሁ (እንድትሰሙና እንድትታዘዙ አደራ እላችኋለሁ። ከኔ በኋላ ከባድ ልዩነትን ታያላችሁ፤ ስለሆነም በኔ ሱናና የተመሩ ቅን በሆኑት ምትኮቼ ሱና አደራችሁን! ............ 69
ከመሪ ትእዛዝ አምፆ በመውጣት የሙስሊሙን ህብረት ተለይቶ የሞተ የድንቁርና አሟሟት ሙቷል። ............ 71
አላህ አንድ ሀላፊነት ላይ ሹሞት የተሰጠውን ሀላፊነት የሚያታልል ሆኖ የሚሞት ባሪያ የለም አላህ በርሱ ላይ ጀነትን እርም የሚያደርግ ቢሆን እንጂ። ............ 73
እነሆ በናንተ ላይ መሪዎች ይሾማሉ። የምታውቁትንም የምታወግዙትንም ስራ ይሰራሉ።) የሚሰሩትን ውግዝ ስራ (የጠላ ሰው) ከወንጀል (ጠራ። ያወገዘም ሰው ሰላም ሆነ። ነገር ግን) የነሱን ውግዝ ተግባር (የወደደና የተከተለ) ወንጀል ውስጥ ወደቀ( ............ 74
ለወደፊት የምታወግዟቸው ጉዳዮችና አድልዎ ይከሰታል '!ሰሐቦችም' የአላህ መልክተኛ ሆይ !ምን ያዙናል '?አሉ። እርሳቸውም 'በናንተ ላይ ያለባችሁን ግዴታ ትወጣላችሁ። ለናንተ ያላችሁን ሐቅ ደግሞ ከአላህ ትጠይቃላችሁ። 'አሉ። ...... 76
ሁላችሁም እረኞች) ሀላፊ (ናችሁ። ስለምትጠብቁት ነገርም ትጠየቃላችሁ። ............ 78
አላህ ሆይ !ከኡመቴ ጉዳይ በአንዳች ነገር የተሾመና እነርሱን ለችግር የዳረገ እርሱንም የሚቸገር አድርገው ። ከኡመቴ ጉዳይ በአንዳች ነገር የተሾመና ለነሱ የራራን ለርሱም ራራለት። ............ 79
ሃይማኖት) ኢስላም (መቆርቆር) ታማኝነት (ነው። ............ 80

እነዚያ ከቁርኣን የተመሳሰለውን የሚከተሉትን ከተመለከትሽ አላህ ተጠንቀቁዋቸው ብሎ የጠቀሳቸው እነሱ ናቸው። ..... 83
ከእናንተ መካከል መጥፎ ሢሠራ የተመለከተ፥በእጁ ይለውጠው) ያስተካክለው(፤ ይህንን ካልቻለ በምላሱ ይከላከል፤ ይህንንም ካልቻለ በቀልቡ) ልቡ (ይጥላ ይህ ግን ደካማው የኢማን ክፍል ነው። ..... 86
በአላህ ድንበር ላይ በአግባቡ የቆሙና የርሱን ድንበር የሚተላለፉ ሰዎች ምሳሌ በመርከብ ላይ) ቦታ ለመምረጥ (እጣ እንደተጣጣሉ ሰዎች ምሳሌ ነው።) በእጣው መሰረት (ከፊሉን የመርከቡ የላይኛው ክፍል ሲደርሰው ከፊሉን ደግሞ የታችኛው ክፍል ደረሰው። ..... 88
ወደ ቅናቻ የተጣራ ሰው የተከተሉትን ሰዎች አምሳያ ምንዳ ያገኛል። ይህም) ለርሱ የሚሰጠው ምንዳ (ከምንዳቸው አንዳች ሳይቀነስ ነው። ..... 90
ወደ መልካም የጠቆመ ሰው የሰሪውን ምንዳ አምሳያ ይመነዳል። ..... 91
በአላህ እምላለሁ !ለአንተ ቀይ ግመል ከሚኖርህ በአንተ ሰበብ አላህ አንድ ሰው ቢመራልህ የተሻለ ነው። ..... 92
ከህዝቦች ጋር የተመሳሰለ እርሱ ከነርሱው ይመደባል። ..... 95
ሰውዬው በጓደኛው ሃይማኖት ላይ ነው። አንዳችሁ የሚጎዳኘውን ሰው ይመልከት። ..... 96
የዚህ ሃይማኖት ጉዳይ ቀንና ምሽት የደረሰበት ስፍራ ሁሉ ይደርሳል። አላህ፤ በሀያሉ ሀይልም ይሁን በውርደታሞች ውርደት ይህንን ሃይማኖት እያንዳንዱ የግንብ) የከተማ (ቤት ውስጥም ይሁን የሳር ቤት) የገጠር ቤት (ውስጥ ሳያስገባው አይቀርም። ..... 97
ያ የሙሐመድ ነፍስ በእጁ በሆነችው ጌታ እምላለሁ !ከዚህ ኡመት ውስጥ አንድም አይሁድ ይሁን ክርስቲያን ስለኔ ሰምቶ ከዚያም በዛ በተላኩበት ሳያምን የሚሞት የለም። ከእሳት ጓዶች መካከል ቢሆን እንጂ ..... 99
እናንተ ሰዎች ሆይ !በሃይማኖት ላይ ወሰን ከማለፍ ተጠንቀቁ !ከናንተ በፊት የነበሩትን ህዝቦች ያጠፋቸው በሃይማኖት ላይ ወሰን ማለፍ ነው። 'አሉ። ..... 101
ፅንፈኞች) ወሰን አላፊዎች( ..... 102
አይሁዶች ቁጣ የሰፈነባቸው ሲሆኑ ክርስቲያኖች ደግሞ የተሳሳቱ ናቸው። ..... 103
አላህ ሰማያትንና ምድርን ከመፍጠሩ ከሀምሳ ሺህ ዓመት በፊት የፍጡራንን ውሳኔ ፅፏል ..... 104
እውነተኛና) ይዘውት በመጡትም ሁሉ (እውነተኛ የተባሉት የአላህ መልክተኛ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) ይህንን (ነገሩን፦ "የአንዳችሁ ፍጥረት በእናቱ ሆድ ውስጥ ለአርባ ቀንና ምሽት ይሰበሰባል ..... 105
ጀነት ወደ እያንዳንዳችሁ ከጫማው ማሰሪያ የበለጠ ቅርብ ናት። እሳትም እንደዚሁ። ..... 107
ጀሀነም ነፍስያ በምትወዳቸው ስሜታዊ ነገሮች ተጋረደች፤ ጀነት ደግሞ ነፍስ በምትጠላቸው ነገሮች ተጋረደች። ..... 108
አላህ ጀነትና እሳትን እንደፈጠረ ጂብሪልን ዐለይሂ ሰላም ..... 109
የምድራችሁ እሳት ከጀሀነም እሳት ሰባ ክፍል አንዷ ክፍል ናት። ..... 111
አላህ ምድርን በጭብጡ ያደርጋል፤ ሰማያትንም በቀኝ እጁ ይጠቀልልና ከዚያም ‹እኔ ነኝ ንጉሱ !የምድር ነገስታት የት አሉ!?› ይላል።' ..... 112
የትንሳኤ ቀን አላህ ዘንድ ከሰዎች ሁሉ እጅግ ብርቱ ቅጣት የሚቀጡት እነዚያ በአላህ ፍጥረት የሚፎካከሩት ናቸው። ..... 113
ነፍሴ በእጁ በሆነው ጌታ እምላለሁ። በናንተ ውስጥ የመርየም ልጅ ፍትሃዊ ዳኛ በቅርቡ ሆኖ ይወርዳል። መስቀልን ይሰባብራል፣ አሳማን ይገድላል፣ ግብርን ያነሳል፣ አንድም ሰው እስከማይቀበለው ድረስም ገንዘብ) ሀብት (ይበዛ። ..... 115
ላ ኢላሀ ኢለላህ በል የትንሳኤ ቀን ላንተ በርሱ እመሰክርልሀለሁ ..... 116
የሐውዴ ) ኩሬ ስፋቱ (አንድ ወር ያስኬዳል ፤ ውኃው ከወተት የነጣ፣ ሽታው ከሚስክ እጅግ የሚያውድ ..... 118
ሞት በቡራቡሬ ሙክት ተመስሎ ተይዞ ይመጣል ..... 119
በአላህ ላይ ትክክለኛውን መመካት ብትመኩ ኖሮ ወፍን እንደሚለግሰው ለናንተም ሲሳይን ይለግሳቹህ ነበር።) ወፍ (ተርባ ማልዳ ትወጣለች። ሆዷ) በጥጋብ (ሞልቶ ትመለሳለች። ..... 121
የሚጋልብ ሰው በእግረኛ ላይ ሰላምታን ያቅርብ፤ እግረኛ በተቀማጭ ላይ ሰላምታን ያቅርብ፤ ጥቂት ሰዎች በብዙ ሰዎች ላይ ሰላምታን ያቅርቡ።' ..... 122

ባሮቼ ሆይ !እኔ በደልን በነፍሴ ላይ እርም አድርጌያለሁ !በመካከላችሁም እርም አድርጌዋለሁ !ስለሆነም አትበዳደሉ! ........................................ 123
በደልን ተጠንቀቁ !በደል የትንሳኤ ቀን ድርብርብ ጨለማዎች ነውና። ስስትንም ተጠንቀቁ !ስስት ከናንተ በፊት የነበሩትን ህዝቦች አጥፍቷልና። ........................................ 126
አላህ በዳይን ያዘገየዋል። የያዘው ጊዜ ግን አይለቀውም! ........................................ 127
አላህ መልካሞችና ኃጢዐቶችን ፅፏል ከዚያም ይህንን አብራርቷል። አንድን መልካም ስራ) ለመስራት (ያሰበና ያልሰራት አላህ እሱ ዘንድ ለሱ ሙሉ ምንዳን ይጻፍለታል ። እሱ) ለመስራት (አስቧት ከሰራት ደግሞ አላህ እሱ ዘንድ ለሱ ከአስር እስከ ሰባት መቶ እጥፍ) ከዛም አልፎ (እስከ ብዙ እጥፍ ድርብ የሚደርስ ምንዳዎች ይጻፍለታል። አንድን ኃጢዐት) ለመስራት (ያሰበና ያልሰራት አላህ እሱ ዘንድ ለሱ ሙሉ ምን ........................................ 129
የአላህ መልክተኛ ሆይ !በጃሂሊያ) ከእርሶ መላክ በፊት ባለው የድንቁርና ዘመን (በሠራነው ሥራ እንቀጣለን "?ነቢዩም) የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን (እንዲህ አሉት፡" –በኢስላም ሥራውን ያሳመረ፥ በጃሂሊያ በሠራው ሥራ ተጠያቂ አይሆንም። እስልምናን ተቀብሎም መጥፎ የሠራ ግን በቀድሞውም በኋለኛውም ስራው ይጠየቅበታል። ...... 131
የምትናገረውና የምትጣራበት ጉዳይ መልካም ነው። ለሰራነው ፀያፍ ተግባር ማስማሪያ እንዳለው እንደው ብትነግረን? ........................................ 132
ካሳለፍከው መልካም ተግባር ጋር ነው የሰለምከው። ........................................ 134
አላህ አማኝን አንድም መልካም ሥራውን አይበድለውም በዱንያ በሷ ምክንያት) መልካም ነገር (ሲሰጠው በአኺራም በሷ ምክንያት ይመነዳዋል ........................................ 135
›የአደም ልጅ ሆይ አንተ እስከለመንከኝና እስከከጀልከኝ ድረስ አንተ ላይ ካለብህ ወንጀልህ ጋርም እምርሃለሁ።) በመማሬም ( ምንም አይመስለኝም፤ ........................................ 136
አንድ ባሪያ አንድን ወንጀል ሰራና እንዲህ አለ" አላህ ሆይ !ወንጀሌን ማረኝ! ........................................ 138
ኃጢዓትን የሠራ ከዚያም ተነስቶ ዉዱእ አድርጎ የሚሰግድ ከዚያም ለኃጢዓቱ ከአሏህ ምህረት የሚጠይቅ አንድም ሰው የለም፤ አላህ ለርሱ የሚምረው ቢሆን እንጂ። ........................................ 140
አላህ ዐዘ ወጀል በቀን ኃጢዓት የፈፀሙ እንዲፀፀቱ) ተውበት እንዲያደርጉ (በምሽት እጁን ይዘረጋል። በምሽት ኃጢዓት የፈፀሙ እንዲፀፀቱ) ተውበት እንዲያደርጉ (ደግሞ በቀን እጁን ይዘረጋል። ይህም ፀሀይ በመግቢያዋ በኩል እስክትወጣ ድረስ ቀጣይ ነው። ........................................ 141
የላቀውና ከፍ ያለው ጌታችን በሁሉም ሌሊት የመጨረሻ ሲሶ ወደ ቅርቢቱ ሰማይ ይወርዳል። ........................................ 143
ሐላል) የተፈቀደ (ነግር ሁሉ ግልፅ ነው። ሐራሙም) እርም የተደረገ (ነግር ሁሉ ግልፅ ነው። ........................................ 144
ባልደረቦቼን አትሳደቡ፤ ከናንተ መካከል አንዱ የኡሑድን ተራራ አምሳያ የሚያህል ቢመፅውት የአንዳቸውንም እፍኝ ሆነ የእፍኙን ግማሽ የመፀወቱት ጋር አይደርስም። ........................................ 146
አንተ ልጅ ሆይ !እኔ ቃላቶችን አስተምርሃለሁኝ !አላህን ጠብቅ ይጠብቅሀል፤ አላህን ጠብቅ ፊት ለፊትህ ታገኘዋለህ፤ የጠየቅክ ጊዜ አላህን ጠይቅ !፤ እገዛን የፈለግክ ጊዜም በአላህ ታገዝ! ........................................ 147
በኢስላም ውስጥ ከርሶ ውጪ ስለርሱ አንድንም ሰው የማልጠይቀው የሆነን አንድን ንግግር ንገሩኝ አልኳቸው። እርሳቸውም 'በአላህ አምኛለሁ በል ከዚያም ቀጥ በል። 'አሉኝ ........................................ 149
የአማኞች እርስ በርስ የመዋደዳቸው፣ የመተዛዘናቸውና የመራራታቸው ምሳሌ እንደ አንድ የሰውነት ክፍል ነው። ከርሱ አንድ አካል የታመመ ጊዜ የተቀረው ሰውነት በእንቅልፍ እጦትና ትኩሳት ይሰቃያል። ........................................ 150
ውዱእን አሳምሮ ያደረገ ወንጀሎቹ ከጥፍሮቹ ስር ሳይቀር ከሰውነቱ ባጠቃላይ ይወጣሉ።' ........................................ 151
እርሱ ውሃው አፅጂ ነው፤ ውስጡ የሞተም ሐላል ነው። ........................................ 152
ውሃው ሁለት' ቁለተይን 'ከደረሰ ነጃሳን አይሸከምም። ........................................ 154
መፀዳጃ በታ የመጣችሁ ጊዜ ወደ ቂብላ አትዙሩም ጀርባ አትስጡም !ነገር ግን ወደ ምስራቅ ወይም ምዕራብ ዙሩ ........................................ 155
አንዳችሁ እየሸና ሳለ ብልቱን በቀኝ እጁ አይያዘው፤ ሲፀዳዳም በቀኝ እጁ አይጥረግ፤ በእቃ ውስጥም አይተንፍስ!156
አንዳችሁ ከእንቅልፉ የነቃ ጊዜ ሶስት ጊዜ አፍንጫው ውስጥ ውሃ እየከተተ ያውጣ፤ ሸይጧን በአፍንጫው ውስጥ ያድራልና። ........................................ 157

ነቢዩ) ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ገላቸውን ከአንድ ቁና ውሃ እስከ አምስት እፍኝ ድረስ ባለ ውሃ ያጥቡ ወይም ይታጠቡ ነበር። በአንድ እፍኝ ደግሞ ዉዱእ ያደርጉ ነበር። ........ 158

አንዳችሁ ዉዱእ በሌለው ጊዜ ዉዱእ እስኪያደርግ ድረስ አላህ ሶላቱን አይቀበለውም። ........ 160

አንድ ሰውዬ ውዱእ አደረገና እግሩ ላይ ጥፍር የምታክል ስፍራ ተወ። ነቢዩ) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ( ተመለከቱትና እንዲህ አሉት :‹ተመለስና ዉዱእህን አሳምር!› ተመልሶ) አስተካከለና (ከዚያም ሰገደ።' ........ 161

ተረከዞቻችሁን ከእሳት አድኑ !ዉዱእን አዳርሳችሁ አድርጉ! ........ 162

ነቢዩ) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና (በሁሉም ሶላት ወቅት ዉዱእ ያደርጉ ነበር። ........ 164

ነቢዩ) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና (አንድ አንድ ጊዜ ዉዱእ አደርገዋል። ........ 165

ነቢዩ) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና (ሁለት ሁለት ጊዜ ዉዱእ አድርገዋል። ........ 166

እኔ እንዳደረጉት አይነት ዉዱእ አድርጎ ከዚያም ነፍሱን ምንም በሃሳብ ሳያደፈርስ ሁለት ረከዐ የሰገደ ሰው ያሳለፈው ወንጀሉ ተምሮለታል። 'አሉ።' ........ 167

አንዳችሁ ዉዱእ ባደረገ ጊዜ አፍንጫው ውስጥ ውሀ አድርጎ ከዚያም ያውጣው፣ በድንጋይ ያደራረቀ ሰውም) የድንጋዩን ቁጥር (ጎዶሎ ያድርገው። ........ 169

እነርሱ እየተቀጡ ነው።) በናንተ እይታ (ትልቅ በሆነ ወንጀልም አይደለም የሚቀጡት። አንደኛቸው ከሽንት አይጥራራም ነበር። ሌላኛው ደግሞ ነገር በማመላለስ የሚዞር ነበር። ........ 171

ነቢዩ) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና (መፀዳጃ ቤት የገቡ ጊዜ' አልላሁመ ኢንኒ አዑዙ ቢከ ሚነል ኹብሢ ወልኸባኢሥ 'ይሉ ነበር። "ትርጉሙም" አላህ ሆይ !እኔ ከወንድ ሰይጣንና ከሴት ሰይጣናት በአንተ እጠበቃለሁ። "ማለት ነው። ........ 172

ነቢዩ) ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ከመፀዳጃ ቤት የወጡ ጊዜ" ጉፍራነክ "ይሉ ነበር።») ትርጉሙም" ምህረትህን እለምንሃለሁ "ማለት ነው።( ........ 173

ሲዋክ አፍን የሚያጠራ) የሚያፀዳ(፤ የአሏህንም ውዴታ የሚያስገኝ ነው።' ........ 174

ነቢዩ) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና (ሌሊት የተነሱ ጊዜ አፋቸውን በመፋቂያ ይፍቁ ነበር። . 175

በአማኞች ላይ ወይም በኡመቴ ላይ እንዳይከብዳቸው ብዬ ነው እንጂ በሁሉም ሶላቶች ወቅት መፋቂያ እንዲጠቀሙ አዛቸው ነበር። ........ 176

እያንዳንዱ ሙስሊም በየሰባት ቀኑ አንድ ጊዜ ገላውን መታጠብ አለበት። ሲታጠብም ጭንቅላቱንም ገላውንም መታጠብ አለበት። ........ 177

አምስቱ ከተፈጥሯዊ) ኢስላማዊ ሱናዎች (ናቸው፡- መገረዝ፣ የብልትን ፀጉር መላጨት፣ ቀድሞ ቀመስን) ከአፍንጫ ስር ያለን ፂም (ማሳጠር፣ ጥፍሮችን መቁረጥና የብብትን ፀጉር መንጨት ። ........ 179

መዚይ) ስሜት በሚቀሰቀስ ወቅት የሚወጣ ፈሳሽ ነው። (የሚበዛብኝ ሰው ነበርኩ። ልጃቸው እኔ ዘንድ በመሆኗ ነቢዩን )የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) (ስለብይኑ (መጠየቅ አፈርኩና ሚቅዳድ ቢን አስወድን እንዲጠይቃቸው አዘዝኩት፤ ጠየቃቸው። እርሳቸውም' ብልቱን ይታጠብና ዉዱእ ያድርግ። ........ 180

የአላህ መልክተኛ) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና (ከጀናባ በሚታጠቡ ጊዜ ሁለት እጃቸውን ይታጠቡና ለሶላት የሚያደርጉትን አምሳያ ዉዱእ ያደርጋሉ። ከዚያም) ሙሉ ገላቸውን (ይታጠቡ ነበር። ........ 182

በእጅህ እንዲህ ብታደርግ በቂህ ነበር። 'አሉና ከዚያም በሁለት እጃቸው መሬቱን አንድ ጊዜ መቱ። ከዚያም በግራ እጃቸው ቀኝ እጃቸውን አበሱ። የላይኛውን የመዳፋቸው ክፍልንና ፊታቸውን አበሱ። ........ 183

እኔ ንፁህ እንደሆነ ነው ያደረግኳቸውና ተዋቸው። ........ 185

ይህ የደም ስር መቆረጥ ነው። ባይሆን የወር አበባ ስታይበት በነበርሽው የቀናት ልክ ሶላትን ተይ !ከዚያም ታጠቢና ስገጂ። ' አሏት። ........ 187

አንዳችሁ ከሆዱ ውስጥ አንዳችን ነገር ያገኘ ጊዜ ከሆዱ አንዳች ነገር ወጥቷል ወይስ አልወጣም የሚለውን መለየት ካስቸገረው ድምፅ እስኪሰማ ወይም ሽታ እስኪያገኝ ድረስ) ሶላቱን አቋርጦ (ከመስጂድ አይውጣ።' ........ 188

ውሻ ከአንዳችሁ እቃ የጠጣ ጊዜ) እቃውን (ሰባት ጊዜ ይጠበው። ........ 189

አዛን ባዩ' :አላሁ አክበሩ አላሁ አክበር) 'አላህ ታላቅ ነው። (ያለ ጊዜ አንዳችሁ ከልቡ' አላሁ አክበሩ አላሁ አክበር 'ካለ፤ ........ 191

ሙአዚኑን የሰማችሁ ጊዜ የሚለውን አምሳያ በሉ። ከዚያም በኔ ላይ ሶለዋት አውርዱ።.......193

አዛን ሲባል የሰማ ጊዜ' :አሽሃዱ አን ላኢላሃ ኢለሏሁ ወሕደሁ ላሸሪከ ለህ ወአነ ሙሐመደን ዐብዱሁ ወረሱሉህ ረዲቱ ቢላሂ ረበን ወቢሙሐመደን ረሱለን ወቢል ኢስላሚ ዲና 'ያለ ሰው ወንጀሉ ይማራል።) "ትርጉሙም :ከአላህ በቀር በእውነት የሚመለክ የለም። ብቸኛና አጋር የሌለው ነው። ሙሐመድም የአላህ ባሪያውና መልክተኛው ናቸው ብዬ እመሰክራለሁ፤ በአላህ ጌትነት፣ በሙሐመድ መልክተኝነት፣ በኢስላም ሃይማኖትነ.......195

በአዛንና ኢቃም መካከል የሚባል ዱዓ አይመለስም) ተቀባይነቱ ጥርጥር የለውም(።.......196

የሶላትን ጥሪ ትሰማለህን '?አሉት። እርሱም' አዎን 'አላቸው። እሳቸውም' እንግዲያውስ ለጥሪው መልስ ስጥ '!አሉት።
.......197

ንገሩኝ እስኪ !አንዳችሁ በር ላይ በየቀኑ አምስት ጊዜ የሚታጠብበት ወንዝ ቢኖር ይህ ከእድፉ ያስቀራል ትላላችሁን?
.......198

በአላህ መንገድ መታገል ነው። 'አሉ።.......199

ትልቅ ወንጀል እስካልፈፀመ ድረስ ግዴታ ሶላት አጋጥሞት ዉዱኡን፣ ተመስጦውንና ሩኩዑን አሳምሮ የሚሰግድ አንድም ሙስሊም የለም፤ ከሶላቷ በፊት የነበረበትን ወንጀል ማስማሪያ ቢሆነው እንጂ፤ ይህም እድሜልኩን ነው።'.. 200

ከባባዶቹን ወንጀሎች ከተጠነቀቁ አምስቱ ሶላቶች፣ ከጁሙዐ እስከ ጁሙዐ፣ ከረመዳን እስከ ረመዳን በመካከላቸው የተሰሩትን ወንጀሎች ያስሰርዛሉ።.......202

ልጆቻችሁን ሰባት አመት ሲሆኑ በሶላት እዘዟቸው፤ አስር አመት ሲሞላቸው ሶላት ላለመስገዳቸው ምቷቸው፤ በመካከላቸውም የመኝታ ስፍራቸውን ለዩ!.......203

ከፍ ያለው አላህ እንዲህ አለ' :ሶላትን በኔና በባሪያዬ መካከል ለሁለት ከፈልኩት። ለባሪያዬም የጠየቀው አለው።204

በኛና በነርሱ) በከሀዲዎች (መካከል ያለው) መለያ (ቃል ኪዳን ሶላት ነው። ሶላትን የተወ ሰው በርግጥም ክዷል።'207

በሰውየውና በሺርክ፣ በክህደት መካከል ያለው) ግርዶ (ሶላትን መተው ነው።'.......208

›ቢላል ሆይ !ሶላትን ኢቃም ብለህ በሶላት እረፍት ስጠን።›'.......209

አልላሁምመ ባዒድ በይኒ ወበይነ ኸጧያየ ከማ ባዐድተ በይነል መሽሪቂ ወልመኻሪብ.......210

የአላህ መልክተኛ) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና (ሶላት በሚከፍቱበት ወቅትና.......212

የመጽሐፉን መክፈቻ) ፋቲሓን (ያላነበበ ሰው ሶላት የለውም።.......214

ነፍሴ በእጁ በሆነው እምላለሁ እኔ ከአላህ መልዕክተኛ) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና (ሶላት ጋር ለመመሳሰል እጅግ የቀረበውን ሶላት የምሰግድ ነኝ። ዱንያን እስኪለያዩ ድረስ ይህቺው ነበረች አሰጋገዳቸው።215

በሰባት አጥንቶቼ ሱጁድ እንዳደርግ ታዝዣለሁ።.......217

ጌታ ወደ ባሪያ እጅግ ቅርብ የሚሆነው በመጨረሻው የሌሊቱ አጋማሽ ነው።.......218

ይህን ጨረቃ እንደምትመለከቱት ጌታችሁንም በርግጥ ታያላችሁ። እርሱን ለማየትም ምንም አትቸገሩም።220

ሁለቱን ቀዝቃዛ ወቅቶች ሶላት የሰገደ ሰው ጀነት ገባ።.......221

የሱብሒን ሶላት የሰገደ ሰው በአላህ ከለላ ስር ነው።.......222

የዐስርን ሶላት የተወ ሰው በርግጥም ስራው ተበላሸ።'.......223

ሶላትን የረሳ ሰው ባስታወሰው ጊዜ ይስገድ። ከዚህ በቀር ማካካሻ የለውም።.......224

በመናፍቃን ላይ እጅግ ከባዱ ሶላት የዒሻእ ሶላትና የፈጅር ሶላት ናቸው። በውስጧ ያለውን ምንዳ ቢያውቁ ኖሮ እየዳሁም ቢሆን ይመጡ ነበር.......225

የአላህ መልዕክተኛ) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና (ከሩኩዕ ወገባቸውን ቀና ያደረጉ ጊዜ" ሰሚዐሏሁ ሊመን ሐሚደህ.......226

ነቢዩ) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና (በሁለቱ ሱጁዶች መካከል' ረቢግፊርሊ ረቢግፊርሊ' 'ጌታዬ ሆይ !ማረኝ ! ጌታዬ ሆይ !ማረኝ '!ይሉ ነበር።.......227

ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም በሁለቱ ሱጁዶች መካከል" አላሁመግፊር ሊ ወርሐምኒ ወዓፊኒ ወህዲኒ ወርዙቅኒ) "አላህ ሆይ ! ማረኝ፣ እዘንልኝም፣ ጤናን ለግሰኝም፣ ምራኝም፣ ሲሳይን ለግሰኝም (ይሉ ነበር።.......228

›ሶላትን መስገድ የፈለጋችሁ ጊዜ ሰልፋችሁን አስተካክሉ። ከዚያም አንድ ሰው ይምራችሁ። ኢማሙ ተክቢራ ያደረገ ጊዜ እናንተም ተክቢራ አድርጉ!.......229

የአላህ መልክተኛ) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና (እጄ በእጃቸው መካከል ሆኖ አንድን የቁርአን ምእራፍ እንደሚያስተምሩኝ ተሸሁድን አስተማሩኝ። ........ 234
አላህ ሆይ !እኔ ከቀብር ቅጣት፣ ከእሳት ቅጣት፣ ከህይወትና ሞት ፈተና እና ከመሲሕ ደጃል ፈተና ባንተው እጠበቃለሁ። 'እያሉ ዱዓእ ያደርጉ ነበር። ........ 236
›ለአላህ ሱጁድ እንድታበዛ አደራ እልሀለሁ። ለአላህ አንድ ሱጁድ አትወርድም አላህ በርሷ ደረጃህን ከፍ ቢያደርግና ወንጀልህንም የሚሰርዝ ቢሆን እንጂ› ........ 238
ምግብ ቀርቦ አልያም ሁለቱ ቆሻሻዎች እያጨናነቁት ሶላት የለም። ........ 239
ይሄ ሰይጣን ነው። ኺንዘብ ይባላል። ይህ ስሜት የተሰማህ ጊዜ ከርሱ በአላህ ተጠበቅ !ወደ ግራህም ሶስት ጊዜ ትፋ! ........ 240
›ከሚሰርቁ ሰዎች ሁሉ እጅግ መጥፎው ሶላቱን የሚሰርቅ ነው።› እርሱም ‹እንዴት ሶላቱን ይሰርቃታል?› አላቸው። እርሳቸውም ‹ሩኩዑንም ሆነ ሱጁዱን ባለማሟላት።› ብለው መለሱለት። ........ 241
አንዳችሁ ከኢማም በፊት ጭንቅላቱን ቀና ያደረገ ጊዜ አላህ ጭንቅላቱን የአህያ ጭንቅላት እንዳያደርገው ወይም አላህ የሰውነት ቅርፁን የአህያ የሰውነት ቅርፅ እንዳያደርግበት አይፈራምን!? ........ 243
አንዳችሁ ሶላቱ ውስጥ የተጠራጠረ ጊዜ ሶስት ይሁን አራት ስንት እንደሰገደ ካላወቀ ጥርጣሬውን ይጣልና እርግጠኛ በሆነበት ላይ ይገንባ። ከዛም ከማሰላመቱ በፊት ሁለት ሱጁዶችን ይውረድ። ........ 244
ነቢዩ) ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ዘንድ እስኪነጋ ድረስ ምሽቱን የተኛ ሰውዬ ተወሳ። እርሳቸውም" ይህ ሸይጧን ጆሮዎቹ ውስጥ ወይም ጆሮው ውስጥ የሸናበት ሰው ነው። "አሉ። ........ 245
ፀሀይ ከወጣችባቸው ቀናቶች ሁሉ በላጩ ቀን የጁመዓ ቀን ነው። ........ 247
የጁመዓ ቀን ልክ እንደ ጀናባ ትጥበት ከታጠበ በኃላ ማልዶ የሄደ ሰው ልክ የግመል ቁርባን እንዳቀረበ ነው።. 248
አላሁመ አንተ አስሰላም ወሚንከ አስሰላም ተባረክተ ዘል ጀላሊ ወልኢክራም ........ 250
የአላህ መልክተኛ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ከሁሉም ሶላቶች በኋላ እነዚህን ውዳሴዎች ይሉ ነበር።' ........ 252
ነቢዩ) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና (ከሁሉም ግዴታ ሶላቶች በኋላ እንዲህ ይሉ ነበር ........ 254
ከሁሉም) ግዴታ (ሶላት በኋላ ሰላሳ ሶስት ጊዜ አላህን ያጠራ) ሱብሓነሏህ (ያለ፤ ሰላሳ ሶስት ጊዜ አላህን ያመሰገነ) አልሐምዱ ሊላህ (ያለ፣ ሰላሳ ሶስት ጊዜ ተክቢራ) አላሁ አክበር (ያለ፤ ይህም በድምሩ ዘጠና ዘጠኝ ሲሆን መቶ መሙያውንም" ላኢላሃ ኢለላሁ ወሕደሁ ላሸሪከ ለሁ፣ ለሁል ሙልኩ ወለሁል ሐምዱ ወሁወ ዓላ ኩሊ ሸይኢን ቀዲር "ያለ ሰው ወንጀሉ የባህር አረፋ አምሳያ ቢደርስ እንኳ ይማራል። ........ 256
ከሁሉም ግዴታ ሶላት በኋላ አየተል ኩርሲይን የቀራ ሰው ጀነት ለመግባት ከሞት በቀር ምንም አይከለክለውም።257
ከነቢዩ) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና (አስር ረከዓዎችን ሸምድጃለሁ። ........ 258
በየሁሉም ሁለት አዛኖች መካከል ሶላት አለ። በየሁሉም ሁለት አዛኖች መካከል ሶላት አለ። "ቀጥለው በሶስተኛው" ለፈለገ ሰው "አሉ። ........ 260
አንዳችሁ መስጂድ የገባ ጊዜ ከመቀመጡ በፊት ሁለት ረከዓ ይስገድ። ........ 261
የጁሙዐ ቀን ኢማሙ ኹጥባ እያደረገ ሳለ ለባልደረባህ' ዝም በል '!ካልከው በርግጥም ውድቅ ንግግርን ተናግረሀል። ........ 262
ቁመህ !ካልቻልክ ተቀምጠህ ካልቻልክ በጎንህ ተጋድመህ ስገድ።' ........ 263
በዚህ መስጂዴ የሚሰገድ ሶላት ከርሱ ውጪ ከሚሰገዱ አንድ ሺህ ሶላቶች የተሻለ ነው። የተከበረው መስጊድ) መስጂደል ሐራም (ሲቀር። ........ 264
ለአላህ ብሎ መስጂድን የገነባ አላህም ለርሱ አምሳያውን ጀነት ውስጥ ይገነባለታል።› 'አለ። ........ 265
የወርቅና የብር ባለቤት ሆኖ ሐቃቸውን የማይወጣ ሰው የትንሳኤ ቀን ለርሱ የእሳት ዝርግ ተዘርግቶለት በርሷ በጀሃነም እሳት ውስጥ ሳይቃጠል የሚቀር የለም። ጎኑም፣ ግንባሩና ጀርባውም የሚተኮስ መሆኑ አይቀርም። ........ 266
ምፅዋት) ከሰጪው (ገንዘብ ላይ አታጎድልም፤ አላህ ለአንድ ባሪያ ይቅር በማለቱ) ምክንያት (ከልቅና በስተቀር አይጨምርለትም፤ አንድም ሰው ለአላህ ብሎ አይተናነስም አላህ ከፍ ያደረገው ቢሆን እንጂ። ........ 270
አላህ እንዲህ ብሏል' የአደም ልጅ ሆይ !ስጥ ላንተም ይሰጥሃል'! ........ 271
ሰውዬው) ምንዳ እንደሚያገኝበት (እያሰበ ለቤተሰቡ ወጪ ያወጣ ጊዜ ለርሱ ምፅዋት ትሆንለታለች። ........ 272

የሰው ልጅ ሲሞት ከሶስት ስራዎቹ ውጪ ስራዎቹ ከርሱ ይቋረጣሉ። ሰደቀቱል ጃሪያህ) ተሻጋሪ ምፅዋቶቹ (ወይም ጠቃሚ ዕውቀት ያስተላለፈ ወይም ለርሱ ዱዓ የሚያደርግለት መልካም ልጅ ያለው ሲቀር ሌሎቹ ስራዎቹ ይቋረጣሉ።273
›ብር በወርቅ እጅ በእጅ ካልሆነ በቀር አራጣ ነው፤ ስንዴ በስንዴ መለዋወጥ እጅ በእጅ ካልሆነ በቀር አራጣ ነው፤ ገብስ በገብስ መለዋወጥ እጅ በእጅ ካልሆነ በቀር አራጣ ነው፤ ተምር በተምር መለዋወጥ እጅ በእጅ ካልሆነ በቀር አራጣ ነው።›275
እናንተ ሰዎች ሆይ !ሰላምታን አስፋፉ፣ ምግብንም አብሉ፣ ዝምድናን ቀጥሉ፣ ሰዎች በተኙበት በሌሊት ስገዱ ጀነት ትገባላችሁ በሰላም። ........ 278
እናንተ ሰዎች ሆይ !አላህ መልካም ነው። ከመልካም በቀርም አይቀበልም። አላህ መልክተኞችን ባዘዘው ነገር አማኞችንም አዟል። ........ 279
ለተቸገረ) ባለዕዳ (ጊዜ የሰጠ ወይም ይቅር ያለ  አላህ ከጥላው በስተቀር ጥላ በሌለበት የትንሳኤ ቀን ከዐርሹ ጥላ ስር ያስጠልለዋል። ........ 282
ሲሸጥም፣ ሲገዛም ይሁን ያበደረውን ሲያስመልስ ገር የሆነን ሰው አሏህ ይዘንለት። ........ 283
ሰዎች ጋር የሚበዳደር አንድ ሰውዬ ነበር። ለሰራተኛውም እንዲህ ይለው ነበር፡' ምናልባት አላህ እኛንም ይቅር ቢለን ........ 284
በአላህ ገንዘብ ያለአግባብ የሚገለገሉ ሰዎች ለነርሱ የትንሳኤ ቀን እሳት ተዘጋጅቶላቸዋል። ........ 285
አላህ እንዲህ ብሏል ፡‹ሁሉም የአደም ልጅ ስራ ለርሱ ነው ፆም ሲቀር፤ ፆም ለኔ ነው። በርሱ የምመነዳውም እኔው ነኝ። ........ 287
)ግዴታነቱን (አምኖ እና ምንዳውን ከአላህ አስቦ የረመዳንን ወር የፆመ ሰው ያለፈ ወንጀሉ ይማርለታል። ........ 290
የአላህ መልክተኛ) ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና በሌላ ጊዜያት ለአምልኮ ከሚጥሩት የተለየ በመጨረሻዎቹ አስሩ የረመዷን ቀናት ይጥሩ ነበር። ........ 291
ፍፁም ወዳጄ የሆኑት ነቢዩ) ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ሶስት ነገሮች ላይ አደራ ብለውኛል። ከሁሉም ወር ሶስት ቀናት በመጾምን፣ የዱሓን ሁለት ረከዓ በመስገድንና ከመተኛቴ በፊት ዊትር መስገድን አደራ ብለውኛል። ........ 292
መወሰኛይቱን ሌሊት) ለይለቱል ቀድርን (በአላህ አምኖና ምንዳውን አስቦ የቆመ  ሰው ያለፈው ኃጢዓቱ ይማርለታል። ........ 294
ሚስቱን ሳይገናኝ እንዲሁም ሳያምፅ ለአሏህ ሐጅ አድርጎ የተመለሰ ልክ እናቱ እንደወለደችበት ቀን) ከወንጀል ንፁህ (ሆኖ ይመለሳል። ........ 295
ከነዚህ ቀናቶች የበለጠ መልካም ስራዎች ወደ አላህ ተወዳጅ የሚሆኑበት ምንንም ቀን የለም። 'ማለትም አስሩ የዙልሂጃ ቀናቶች ናቸው። ........ 296
›የሚያጠራጥርህን ነገር ተውና ወደ ማያጠራጥርህ ሂድ !እውነት እርጋታን የተላበሰ ነው። ውሸት ደሞ ጥርጣሬን የተላበሰ ነው።› ........ 297
አላህ ከኡመቴ በውስጣቸው የሚናገሩትን ነገር እስካልሰሩት ወይም እስካልተናገሩት ድረስ ይቅር ብሏቸዋል።298
አላህ ወደ ቅርፃችሁና ገንዘቦቻችሁ አይመለከትም ነገር ግን ወደ ልቦቻችሁና ስራዎቻችሁ ይመለከታል። ........ 299
›አላህ ይቀናል። የአላህ መቅናት ሰውዬው አላህ በሱ ላይ ክልክል ያደረገበትን ሲዳፈር ነው።› ........ 300
ሰባት አጥፊዎችን ተጠንቀቁ! ........ 301
ከትልልቅ ወንጀሎች ትልቁን አልነግራችሁምን? ........ 303
ትላልቅ ወንጀሎች፡- በአላህ ማጋራት፣ የወላጆችን ሐቅ ማጓደል፣ ነፍስ ማጥፋትና የውሸት መሀላ ናቸው። ........ 305
የትንሳኤ ቀን በሰዎች መካከል መጀመሪያ የሚፈረደው ጉዳይ የደም ጉዳይ ነው። ........ 306
በቃል ኪዳን ስር ያለን) ሙዓሀድን (የገደለ ሰው የጀነትን ሽታ አያሸትም። የጀነት ሽታዋ የሚገኘው አርባ አመት ከሚያስኬድ ርቀት በኃላ ነው። ........ 307
ዝምድናን ቆራጭ ጀነት አይገባም። ........ 308
ሲሳዩ እንዲሰፋለትና እድሜው እንዲረዝምለት የወደደ ሰው ዝምድናውን ይቀጥል። ........ 309

ዝምድና ቀጣይ የሚባለው ላደረጉለት መልካም ነገር ምላሹን የሚሰጥ የሆነው አይደለም፤ ይልቁንም ዝምድና ቀጣይ የሚባለው ዝምድናው በተቆረጠ ጊዜ የሚቀጥል የሆነው ነው። ...... 310
ሀሜት ምን እንደሆነ ታውቃላችሁን "?ሶሐቦችም" አላህና መልክተኛው ያውቃሉ። "አሉ። እሳቸውም" ወንድምህን በሚጠላው ነገር ማውሳትህ ነው። ...... 311
አስካሪ ሁሉ ኸምር ነው። አስካሪ ሁሉ ክልክል ነው። በዚህ ዓለም አስካሪ መጠጥ አዘውትሮ ጠጥቶ ንስሀ ሳይገባ የሞተ ሰው በመጪው ዓለም አይጠጣም። ...... 312
የአላህ መልዕክተኛ) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና (በፍርድ አሰጣጥ ዙሪያ ጉቦ ሰጪንም ተቀባይንም ረገሙ። ...... 313
አደራችሁን ጥርጣሬን ተጠንቀቁ !ጥርጣሬ እጅግ ውሸት የሆነ ወሬ ነውና። ...... 314
ነገር አዋሳጅ ጀነት አይገባም። ...... 316
ወንጀላቸውን ይፋ ከሚያደርጉ በስተቀር ሁሉም ህዝቦቼ ይማርላቸዋል። ...... 317
እናንተ ሰዎች ሆይ !አላህ ከናንተ ላይ የድንቁርና ዘመንን ኩራትና በአባቶች መኩፈስን አስወግዷል። ...... 318
ከሰዎች ሁሉ አላህ ዘንድ እጅግ የተጠላው ደረቅ ተከራካሪ የሆነ ሰው ነው። ...... 320
ሁለት ሙስሊሞች በሰይፋቸው) ሊጋደሉ (የተገናኙ ጊዜ ገዳዩም ሆነ ተገዳዩ እሳት ውስጥ ናቸው። ...... 321
መሳሪያውን በኛ ላይ ያነሳ ከኛ አይደለም። ...... 322
ሚቾችን አትሳደቡ !እነርሱ ወዳስቀደሙት) ስራቸው (ሂደዋልና። ...... 323
ሲገናኙ ይህም እየዞረ ያኛውም እየዞረ ወንድሙን ከሶስት ሌሊቶች በላይ ሊያኮርፈው አይፈቀድለትም። ከሁለቱ ምርጡ በሰላምታ የሚጀምረው ነው። ...... 324
በሁለት መንገጭላዎቹ መካከል እና በሁለት እግሮቹ መካከል ያሉትን) ሊጠብቅ (ዋስትና ለገባልኝ እኔም ጀነትን ዋስትና እገባለታለሁ። ...... 325
ሴት ልጅ ከርሷ ጋር ባሏ ወይም ዘመዷ ከሌሉ በቀር ሁለት ቀን የሚያስኬድ መንገድን አትጓዝ። ...... 326
ከኔ በኋላ ወንዶች ላይ ከሴት የበለጠ እጅግ ጎጂ ፈተና አልተውኩም። ...... 329
የጋብቻን ጣጣ የቻለ ሰው ያግባ !ጋብቻ አይንን ሰባሪና ብልትን ጠባቂ ነውና። ጋብቻን ያልቻለ ሰው መፆም አለበት። ፆም ለርሱ ማኮላሺያ) የጾታዊ ፍላጎቱን የሚቆርጥለት (ነውና። ...... 330
ዱንያ ጣፋጭና አረንጓዴ) ለምለም (ናት። አላህም እንዴት እንደምትሰሩ ሊያያችሁ በውስጧ ምትኮች አድርጓችኋል። ዱንያንም ተጠንቀቁ !ሴቶችንም ተጠንቀቁ! ...... 331
ሴቶች ጋር ከመግባት ተጠንቀቁ "!አንድ ከአንሷር የሆነ ሰውዬም" የአላህ መልክተኛ ሆይ !ስለባል ቅርብ ዘመዶች ንገሩኝ እስኪ "? አለ። እርሳቸውም" የባል ቅርብ ዘመድማ ሞት ነው። "አሉ። ...... 333
ያለ ወሊይ ፈቃድ ጋብቻ የለም። ...... 335
ልታሟሉት ከሚገቡ መስፈርቶች ሁሉ ልታሟሉት እጅግ የተገባው ብልትን ሐላል ያደረጋቹበትን መስፈርት ነው።' ...... 336
ዱንያ መጣቀሚያ ናት። ከዱንያ መጣቀሚያዎች ምርጡ መልካም ሚስት ናት። ...... 337
የአላህን መልክተኛ) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና (ስለድንገተኛ እይታ ጠየቅኳቸው። እርሳቸውም አይኔን እንዳዞር አዘዙኝ። ...... 338
ነቢዩ) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና (ለኡዱሒያ ሁለት ቡራቡሬና ቀንዳም የሆኑ ሙክቶችን በእጃቸው አረዱ።" ቢስሚላህ አላሁ አክበር "አሉና እግራቸውን አንገቱ ላይ አድርገው አረዱት። ...... 339
የቀጭን ሐርንና የወፍራም ሐርን ልብስ አትልበሱ !በወርቅና ብር እቃ አትጠጡ !በ)ወርቅና ብር (ትሪም አትብሉ !እርሷ በዚህ ዓለም ለነርሱ ናት፤ በመጪው ዓለም ደግሞ ለኛ ናት። ...... 340
ከሶስት ዓይነት አካላት ላይ ብእር ተነስቷል። የተኛ ሰው እስኪነቃ ድረስ፤ ህፃን ልጅ አቅመ አዳም እስኪደርስ ድረስ እና እብድ ጤነኛ እስኪሆን ድረስ ነው። ...... 342
የአላህ መልክተኛ ሶላላሁ ዐለይሂ ወሰለም ፀጉርን አንዱን ተላጭቶ አንዱን ትቶ ከመቆረጥ ከልክለዋል። ...... 344
ቀድሞ ቀመስን) ከአፍንጫ ስር ያለውን ፂም (አሳጥሩ ሪዛችሁን) የመንጋጭላ ፂማችሁን (ልቀቁ! ...... 345
ወንድ ልጅ ወደ ወንድ ልጅ ሀፍረተ ገላ አይመልከት !ሴት ልጅም ወደ ሴት ልጅ ሀፍረተ ገላ አትመልከት! ...... 346

ከናንተ ምርጡ ስነምግባሩ እጅግ ያማረው ነው።' ..... 347
አንድ ሙእሚን በመልካም ስነምግባሩ የፆመኛና) የሌሊት (ሰጋጅን ደረጃ ያገኛል።' ..... 348
ከአማኞች መካከል ኢማናቸው የተሟላው ስነምግባራቸው እጅግ ያማረ የሆኑት ናቸው ፤ ከአማኞች መካከል ምርጦቹ ደግሞ ለሴቶቻቸው ምርጥ የሆኑት ናቸው።' ..... 349
የአላህ መልክተኛ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም በአብዛኛው ሰዎችን ጀነት ስለሚያስገባው ነገር ተጠየቁ፤ እሳቸውም" አላህን መፍራት እና መልካም ስነምግባር ነው። "አሉ። ..... 350
የአላህ መልክተኛ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ከሰዎች ባጠቃላይ ይበልጥ ስነምግባራቸው እጅግ ያማረ ሰው ነበሩ። 351
የነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ስነምግባር ቁርአን ነበር። 'አለችኝ። ..... 352
ነቢዩ) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና (ጫማ ሲለብሱ፣ ሲያበጥሩ፣ ሲፅዳዱና በሁሉም ጉዳያቸው ቀኝን መጠቀም ይወዱ ነበር። ..... 353
አላህ በሁሉም ነገሮች ላይ ኢሕሳን) እንድናሳምር (ፅፏል። ..... 355
ፍትሃዊዎች) የትንሳኤ ቀን (አላህ ዘንድ በብርሃን በተሰራ ወንበር ላይ ከአርራሕማን ቀኝ በኩል ይሆናሉ። ሁለቱም የአላህ እጆች ቀኝ ናቸው። ..... 356
አውቆ መጉዳትም ሆነ ሳያውቁ መጎዳዳትም የለም) አይቻልም(። ጎጂን አላህ ይጎዳዋል። ሰዎችን ያስጨነቀ አላህ ያጨናንቀዋል። ..... 357
የመልካም ጓደኛና የመጥፎ ጓደኛ ምሳሌ እንደ ሽቶ ተሸካሚና እንደወናፍ ነፊ ነው። ..... 358
አትቆጣ! ..... 360
ብርቱ የሚባለው ታግሎ ያሸነፈ ሳይሆን በቁጣ ወቅት እራሱን የተቆጣጠረ ነው። ..... 361
አራት ነገሮች ያሉበት ሰው ጥርት ያለ ሙናፊቅ ይሆናል። ከነርሱ መካከል ከፊሉ ያለበት ሰው እስኪተወው ድረስ ከፊል ንፍቅና ይኖርበታል። ሲያወራ ይዋሻል፣ ቃልኪዳን ይዞ ያፈርሳል፣ ቀጠሮ ይዞ ያፈርሳል፣ ሲሟገት) ድንበር ያልፋል (በጥመት ላይ ነው። ..... 362
ሙእሚን የሆነ ሰው እጅግ ተቺ፣ እጅግ ተራጋሚ፣ ፀያፍ ተግባር ሰሪ፣ መጥፎ ንግግር ተናጋሪ አይደለም። ..... 364
አይነአፋርነት ከኢማን ነው። ..... 365
አንድ ሰው ወንድሙን ከወደደው እንደሚወደው ይንገረው። ..... 366
መልካም ነገሮች ሁሉ ምፅዋት ናቸው። ..... 367
ሁሉም የሰው ልጅ መገጣጠሚያ አጥንቶች ምፅዋት አለባቸው። ..... 368
የትንሳኤ ቀን የትኛውም ባሪያ እድሜውን በምን እንዳጠፋው፣ በእውቀቱ ምን እንደሰራበት፣ ገንዘቡን ከየት እንዳገኘውና ምን ላይ እንዳዋለው፣ በአካሉ ምን እንዳደረገበት ሳይጠየቅ እግሮቹ አይንቀሳቀሱም።' ..... 370
›ባሏ ለሞተባትና ለሚስኪን የሚለፋ ሰው ልክ በአላህ መንገድ እንደሚታገል ሰው አምሳያ ወይም ልክ ሌሊት እየሰገደ ቀኑን እንደሚፆም አምሳያ ነው› ..... 371
በአላህና በመጨረሻው ቀን ያመነ መልካምን ይናገር ወይም ዝም ይበል! ..... 372
ከመልካም ነገር አንዳችም አታሳንስ ወንድምህን ፈታ ባለ ፊት ማግኘትንም ቢሆን እንኳ) እንዳታሳንስ(። ..... 373
በእውነተኝነት ላይ አደራችሁን !እውነተኝነት ወደ መልካም ይመራል። መልካም ነገር ደግሞ ወደ ጀነት ይመራልና። ..... 374
ለሰዎች የማይራራን አሸናፊና የበላይ የሆነው አላህ አይራራለትም። ..... 376
ለአዛኞች አዛኙ ጌታ ያዝንላቸዋል። ለምድር ነዋሪዎች እዘኑላቸው በሰማይ ያለው) አላህ (ያዝንላቹሀል። ..... 377
ሙስሊም ማለት ሙስሊሞች ከምላሱና እጁ) ክፋት (ሰላም የሆኑበት ነው፤ ሙሃጂር) ስደተኛ (ማለት አላህ የከለከለውን የተወ ነው። ..... 378
አንድ ሙስሊም በሌላኛው ሙስሊም ላይ አምስት መብቶች አሉት፤ ሰላምታ መመለስ፣ ህመምተኛ መጠየቅ፣ ጀናዛን መሸኘት፣ ጥሪውን መቀበልና ባስነጠሰው ጊዜ' የርሐሙከሏህ 'ማለት ናቸው።' ..... 379
እስክታምኑ ድረስ ጀነት አትገቡም። እስክትዋደዱ ድረስም አታምኑም። የፈፀማችሁት ጊዜ የምትዋደዱበትን አንዳች ነገር ልጠቁማችሁን ?በመካከላችሁ ሰላምታን አሰራጩ።' ..... 380

አንድ ሰውዬ ነቢዩን) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና' (ማንኛው የኢስላም ክፍል ነው ምርጡ '?ብሎ ጠየቀ። እርሳቸውም' ምግብ መመገብህ፣ ሰላምታን ባወቅከውም ባላወቅከውም ሰው ላይ ማቅረብህ ነው። 'ብለው መለሱለት። ........ 382

አላህ ወንጀሎችን የሚሰርዝበትን፣ ደረጃዎችን ከፍ የሚያደርግበትን ነገር አልጠቁማችሁምን?........ 383

በሁሉም ውስጥ መልካም ነገር ቢኖርም፤ ጠንካራ ሙእሚን ከደካማው ሙእሚን አላህ ዘንድ የተሻለና ይበልጥ ተወዳጅ ነው። ........ 385

ትክክለኛውን አካሄድ ተከተሉ፤ በተቻለ መጠን ወደ እሱ ቅርብ ለመሆን ሞክሩ ከናንተ መካከል አንድም ሰው በስራው እንደማይድንም እወቁ "!ሶሐቦችም" የአላህ መልክተኛ ሆይ !እርሶም ቢሆኑ በስራዎት አይድኑምን "?አሉ። እርሳቸውም" አላህ ከርሱ በሆነ እዝነትና ቸሮታ ካልሸፈነኝ በቀር እኔም ብሆን በስራዬ አልድንም። "አሉ። ........ 387

)ጎረቤቴን (ያስወርሰዋል ብዬ እስከማስብ ድረስ ጂብሪል በጎረቤት) ሐቅ ዙሪያ (እኔን ከማዘዝ አልተወገደም።. 390

ከወንድሙ ክብር የተከላከለ ሰው በትንሳኤ ቀን አላህ እሳትን ከፊቱ ይከላከልለታል።........ 391

አንዳችሁ ለነፍሱ የሚወደውን ነገር ለወንድሙ እስካልወደደ ድረስ አላመነም። ........ 392

በአንድ ነገር ውስጥ ገራገርነት) ልስላሴ (አይኖርም ያስዋበው ቢሆን እንጂ ፤ ከአንድ ነገር ውስጥ ደግሞ አይነሳም አስቀያሚ የሚያደርገው ቢሆን እንጂ። ........ 393

የእስልምና ሃይማኖት ገር ነው። አንድም ሰው የእስልምናን ሃይማኖት ከመጠን በላይ አያጠብቅም) ሃይማኖቱ ( የሚያሸንፈው ቢሆን እንጂ፤ ሚዛናዊ ሁኑ !አቀራርቡ!........ 394

አግራሩ አታክብዱ !አበስሩ አታሸሹ!........ 396

ዑመር ዘንድ ነበርንና እንዲህ አሉ' :ከአቅም በላይ ከመጣጣር ተከልክለናል።'........ 398

አንዳችሁ የበላ ጊዜ በቀኙ ይብላ። የጠጣም ጊዜ በቀኙ ይጠጣ። ሰይጣን የሚበላውም በግራው፤ የሚጠጣውም በግራው ነውና። ........ 399

አንተ ልጅ ሆይ !ቢስሚላህ በል !በቀኝህ ብላ፣ ፊትህ ካለውም ብላ!........ 400

አላህ ባሪያው ምግብን በልቶ እንዲያመሰግነው ወይም መጠጥን ጠጥቶ እንዲያመሰግነው ይወዳል።'........ 401

አንድ ሰውዬ የአላህ መልክተኛ) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና (ዘንድ በግራ እጁ በላ። እርሳቸውም' በቀኝህ ብላ። 'አሉት። እርሱም' አልችልም '!አላቸው። እርሳቸውም' አያስችልህ '!አሉት።........ 402

ነጭ ሽንኩርት ወይም ቀይ ሽንኩርት የበላ ሰው ከኛ ገለል ይበል ወይም ከመስጂዳችን ገለል ይበል። ቤቱም ይቀመጥ "አሉ። ........ 403

ምግብ በልቶ ‹አልሐምዱ ሊላሂለዚ አጥዐመኒ ሀዛ ወረዘቀኒሂ ሚን ጎይሪ ሐውሊን ሚንኒ ወላቁውዋህ› ያለ ሰው ያሳለፈው ወንጀል ለርሱ ይማርለታል።")› ትርጉሙም" ያለኔ ኃይልና ብልሃት ይህንን ላበላኝና ለለገሰኝ አላህ ምስጋና የተገባው ነው። " ማለት ነው።........ 406

የአላህ መልክተኛ) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና (ያስነጠሱ ጊዜ እጃቸውን ወይም ልብሳቸውን አፋቸው ላይ አድርገው ድምፃቸውን ይቀንሱበት ነበር። ........ 407

አላህ ግዴታ ያደረገው ሲተገበር እንደሚወደው፤ ያግራውም ሲተገበር ይወዳል።........ 408

አላህ ለሱ መልካም የሻለትን ሰው ይፈትነዋል። ........ 409

አላህ በሷ ምክንያት ከወንጀሎቹ የሚምርለት ቢሆን እንጂ አንድን ሙስሊም ድካም፣ በሽታ፣ ሀሳብ፣ ሀዘን፣ ጉዳት፣ ጭንቀት የምትወጋው አንዲት እሾክ እንኳ) በከንቱ (አታገኘውም።........ 410

አማኝ የሆነ ወንድና ሴት በርሱ ላይ ምንም ወንጀል የሌለበት ሆኖ አላህን እስኪገናኝ ድረስ በነፍሱ፣ በልጁና በገንዘቡ ላይ መከራ ከመከሰት አይወገድም። ........ 411

የአማኝ ነገር ይደንቃል። ሁሉ ነገሩ መልካም ነው። ይህም ለአማኝ እንጂ ለሌላ ለአንድም አካል ሊሆን አይችልም።412

አንድ ሰው በታመመ ወይም ጉዞ በወጣ ወቅት ሀገሩ እያለና ጤናማ ሳለ እንደሚያደርገው አጅር ይጻፍለታል።414

ሰውዬው አማኝ ሆኖ ያነጋና ከሀዲ ሆኖ የሚያመሽበት፤ ወይም አማኝ ሆኖ ያመሽና ከሀዲ ሆኖ የሚያነጋበት፤ እምነቱንም በአለማዊ ሸቀጥ እስከመሸጥ የሚያደርሱ የድቅድቅ ጨለማ ቁራጭ የመሰሉ ፈተናዎች ከመምጣታቸው በፊት በመልካም ስራ ተቻኮሉ። ........ 415

አላህ ለእርሱ መልካምን የሻለትን ሰው ሃይማኖቱን ያስገነዝበዋል። ........ 416

ዕውቀትን ዑለሞችን ልትፎካከሩበት) በሊቃውንት ፊት ለመታየት(፣ ቂሎችን ልትሚገቱበት ............................................ 418
ከናንተ መካከል በላጩ ቁርአንን ተምሮ ያስተማረ ሰው ነው። ...................................................................... 419
ሶሀቦች ከአላህ መልክተኛ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን አስር የቁርኣን አንቀፆችን ተምረው በተማሩት አንቀፆች ውስጥ ያለውን ዕውቀትና ተግባር ሳይረዱ ሌላ ተጨማሪ አስር አንቀፆችን አይማሩም ነበር ............ 420
ከአላህ መጽሐፍ አንዲትን ፊደል የቀራ ሰው ለርሱ አንዲት ምንዳ ይሰጠዋል። አንዲት ምንዳ ደግሞ በአስር አምሳያዋ )ትባዛለች።(................................................................................................................................. 421
ለቁርኣን ባለቤት" አንብብ) !ደረጃን (ውጣ !በዱንያ ውስጥ አሳምረህ ታነብ እንደነበርከው አሳምረህ አንብብ) !ጀነት ውስጥ ( ያንተ ስፍራ የምታነበው የመጨረሻው አንቀፅ ዘንድ ነው። "ይባላል።.................................................................. 422
አንዳችሁ ወደ ቤተሰቡ የተመለሰ ጊዜ ሶስት ትላልቅ የሰቡ እርጉዝ ግመሎችን ቢያገኝ ያስደስተዋልን? ........... 423
ይህንን ቁርአን ተጠባበቁት !የሙሐመድ ነፍስ በእጁ በሆነችው ጌታ እምላለሁ እርሱ) ቁርአን (ግመል ከታሰረችበት) ፈታ ( ከምታመልጠው የበለጠ በጣም የሚያመልጥ ነው።........................................................................................ 424
ቤቶቻችሁን መቃብር አታድርጉ። ሰይጣን የበቀራህ ምእራፍ የሚቀራበት ቤትን ይሸሻል። ................................ 425
አቡ ሙንዚር ሆይ !ከአላህ መጽሐፍ ከሸመደድከው ማንኛው አንቀፅ ታላቅ እንደሆነ ታውቃለህን "?አሉኝ።}" አላህ ከእርሱ በቀር በእውነት የሚመለክ አምላክ የለም። ህያው ራሱን ቻይ ነው።] {አልበቀራህ :255) "ኣያተል ኩርሲይ (አልኩኝ። እሳቸውም ደረቴን በመምታት" በአላህ እምላለሁ !እውቀት ያስደስትህ አቡ ሙንዚር "!አሉኝ። ........................ 426
በምሽት ውስጥ የመጨረሻዎቹን የበቀራህ ምእራፍ ሁለት አንቀፆች የቀራ ሰው ይበቁታል። ........................... 427
ዱዓእ እሱ አምልኮ ነው።.................................................................................................................... 428
ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም በሁሉም ሁኔታቸው አላህን ያወሱ ነበር።...................................................... 429
ከዱዓእ የበለጠ አላህ ዘንድ የተከበረ አንዳችም ነገር የለም። ................................................................... 430
የአላህ መልክተኛ) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና" (ያ ሙቀሊበል ቁሉብ ሠቢት ቀልቢ ዐላ ዲኒክ) "አንተ ልቦናን ገለባባጭ የሆንክ ጌታ ሆይ !ልቤን በሃይማኖትህ ላይ አፅናት (ማለትን ያበዙ ነበር።...................................431
አልላሁመ አስሊሕ ሊ ዲኒለዚ ሁወ ዒስመቱ አምሪ ........................................................................... 432
አላህ ሆይ !በዱንያም ሆነ በመጪው አለም ደህንነትን እጠይቅሃለሁ፤ ............................................................ 435
አልላሁመ ኢኒ አስአሉከ ሚነል ኸይሪ ኩሊህ፣ ዓጂሊሂ ወአጂሊህ፣ ማ ዓሊምቱ ሚንሁ ወማለም አዕለም፣ ወአዑዙ ቢከ ሚነ ሸሪ ኩሊህ፣ ዓጂሊሂ ወአጂሊህ ማዓሊምቱ ሚንሁ ወማለም አዕለም።............................................................438
ልክ ያረጀ ልብስ እንደሚደክመው ሁሉ ኢማንም በአንዳችሁ ልብ ውስጥ ይደክማል። አላህ ኢማንን በልባችሁ ውስጥ እንዲያድስ ለምኑት። ......................................................................................................................... 441
በአኗህ ጌትነት፣ በእስልምና ሃይማኖት እና የነብዩ ሙሐመድ) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና (ነቢይነት የወደደ ሰው የኢማንን ጥፍጥና አጣጥሟል። .......................................................................................442
ከየሁሉም ሶላት መጠናቀቂያ ላይ' አልላሁመ አዒንኒ ዓላ ዚክሪከ፣ ወሹክሪከ፣ ወሑስኒ ዒባደቲክ 'ማለትን እንዳትተው አደራ እልሃለሁ። "አሉኝ።» ትርጉሙም) አላህ ሆይ !አንተን በማውሳት፣ በማመስገንና አምልኮህን በማሳመር ላይ አግዘኝ።( ..........................................................................................................................................444
አንድ ባሪያ ወደ ጌታው እጅግ ቅርብ የሚሆነው ሱጁድ ላይ ሳለ ነው።) ስለዚህም (ዱዓእን አብዙ! ...................445
ነቢዩ) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና (እጅግ አብዝተው ያደርጉት የነበረው ዱዓ' አልላሁመ ረበና አቲና ፊ ዱንያ ሐሰነተን ወፊል አኺረቲ ሐሰነተን ወቂና ዓዘበን-ናር 'የሚለውን ነበር።) "ትርጉሙም :ጌታችን አላህ ሆይ !በዱንያ መልካሙን ስጠን፤ በመጨረሻው ዓለምም መልካሙን ስጠን። ከእሳት ቅጣትም ጠብቀን።( .........................446
በላጩን ሥራችሁ፣ ንጉሳችሁ ዘንድ የጠራችውን ሥራችሁ፣ ደረጃችሁንም ከፍ የምታደርገውን ስራችሁን፣.447
በርግጥም ስለ ትልቅ ጉዳይ ነው የጠየቅከኝ፤ ጉዳዩ አላህ በርሱ ላይ ላቀለለለት ሰው ቀላል ነው። ......................449
ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን ሁል ጊዜም በምሽት ወቅት ወደ ፍራሻቸው የተጠጉ ጊዜ መዳፋቸውን ይሰበስቡና ከዚያም ትንፋሻቸውን እየነፉበት} ቁል ሁወ አላሁ አሐድ{ን፣} ቁል አዑዙ ቢረቢል ፈለቅ{ን፣} ቁል አዑዙ ቢረቢ ናስ{ን .....................................................................................................................................454
የምህረት አጠያየቅ) የኢስቲግፋር (አለቃ ..........................................................................................455
አልላሁመ ቢከ አስበሕና ወቢከ አምሰይና ወቢከ ነሕያ ወቢከ ነሙቱ ወኢለይከ ኑሹር.........................................457

›ሶስት ጊዜ' ቢስሚላሂለዚ ላየዱሩ መዐስሚሂ ሸይኡን ፊልአርዲ ወላፊስሰማእ ወሁወስ'ሰሚዑል ዐሊም) 'ትርጉሙም :በዚያ ከስሙ ጋር በምድርም ይሁን በሰማይ ምንም ነገር የማይጎዳ በሆነው እንዲሁም ሰሚና አዋቂ በሆነው አላህ ስም። (ያለ ሰው እስኪነጋ ድረስ ድንገተኛ መከራ አያገኘውም። ........ 460
ሱረቱል ኢኽላስ እና ሁለቱን መጠበቂያዎች) ሱረቱል ፈለቅና ሱረቱን–ናስን (ስታመሽና ስታነጋ ሶስት ጊዜ ካልክ ለሁሉም ነገር ይበቁሃል። 'አሉኝ። ........ 462
አላሁመ አዑዙ ቢሪዷከ ሚን ሰኸጢክ፣ ወቢሙዓፋቲከ ሚን ዑቁበቲክ፣ ወአዑዙ ቢከ ሚንክ፣ ላኡሕሲ ሠናአን ዐለይክ አንተ ከማ አሥነይተ ዐላ ነፍሲክ"» ትርጉሙም" አላህ ሆይ !ከቁጣህ በውዴታህ፣ ከቅጣትህ በይቅር ባይነትህ እጠበቃለሁ፤ ከአንተ በአንተ እጠበቃለሁ፤ አንተ እራስህን ያወደስከውን ያህል ላወድስህ አልቻልም። "ማለት ነው። ........ 463
አላህ ዘንድ ተወዳጅ የሆኑ ንግግሮች አራት ናቸው።' ሱብሓነላህ) 'አላህ ሆይ !ጥራት ተገባህ' (አልሐምዱ ሊላህ) 'ምስጋና ለአላህ የተገባ ነው።' (ላኢላሃ ኢለላህ) 'ከአላህ በስተቀር በእውነት የሚመለክ አምላክ የለም' (አሏሁ አክበር) 'አላህ ታላቅ ነው። ( በማንኛቸውም ብትጀምር አይጎዳህም። ........ 465
አስር ጊዜ' ላ ኢላሃ ኢለሏህ ወሕደሁ ላ ሸሪከ ለህ ፤ ለሁል ሙልኩ ወለሁል ሐምዱ ወሁወ ዓላ ኩሊ ሸይኢን ቀዲር 'ያለ ሰው ........ 466
ለምላስ ቀላል የሆኑ፣ ሚዛን ላይ የሚከብዱ፣ አርራህማን ዘንድ ተወዳጅ የሆኑ ሁለት ቃላቶች አሉ ........ 467
በቀን ውስጥ መቶ ጊዜ ሱብሓነላሂ ወቢሐምዲሂ" ጥራት ምስጋና ለአላህ ይገባው። "ያለ ሰው) የወንጀሉ ብዛት (የባህር ዓረፋ አምሳያ ቢሆን እንኳ ወንጀሉ ይታበስለታል። ........ 468
ንፅህና የኢማን ግማሽ ነው' አልሐምዱ ሊላህ) 'ምስጋና ለአላህ የተገባ ነው (የሚለው ሚዛን ይሞላል፤' ሱብሐነላህ ወል'ሐምዱ ሊላህ) 'አላህ ጥራት የተገባው ነው፤ ምስጋናም ሁሉ ለአላህ ነው (የሚለው በሰማያትና በምድር መካከል ያለውን ይሞላሉ ወይም ይሞላል ........ 469
'ሱብሓነሏህ ወልሐምዱሊላህ ወላኢላሃ ኢለሏህ ወሏሁ አክበር 'ማለቴ ፀሀይ የወጣችበት ክልል ሁሉ) ከሚሰጠኝ (የበለጠ ወደእኔ እጅግ ተወዳጅ ነው።' ........ 471
በላጬ ዚክር' ላ ኢላሃ ኢለሏህ 'ማለት ሲሆን በላጬ ዱዓእ ደግሞ' አልሐምዱሊላህ 'ማለት ነው።' ........ 472
በአንድ ስፍራ ላይ አርፎ ከዚያም ‹አዑዙ ቢከሊማቲላሂ አትታማቲ ሚን ሸሪ ማ ኸለቀ) ምሉዕ በሆኑ የአላህ ቃላት ከፈጠራቸው ጎጂ ነገሮች እጠበቃለሁ(› ያለ ሰው ከዛ ስፍራ እስኪንቀሳቀስ ድረስ አንዳችም አይጎዳውም። ..... 473
›አንዳችሁ መስጂድ የገባ ጊዜ' :አልላሁምመፍተሕ ሊ አብዋበ ረሕመቲከ) 'ትርጉሙም :አላህ ሆይ !ለኔ የእዝነትህን በሮች ክፈትልኝ (ይበል። የወጣ ጊዜም ‹አልላሁምመ ኢኒ አስአሉከ ሚን ፈድሊክ) 'ትርጉሙም :አላህ ሆይ !እኔ ከትሩፋትህ እጠይቅሀለሁ። (ይበል።› ........ 474
አንድ ሰው ወደ ቤቱ ሲገባ በሚገባበት ወቅትም በሚበላበት ወቅትም አላህን ካወሳ ሰይጣን) ለባልደረቦቹ' (ማደሪያም እራትም የላችሁም። 'ይላል። ........ 475

## አጠር ያለ ገለፃ

ነቢያዊ ሓዲሦች ከኢስላማዊ የድንጋጌ ምንጮች (ከቁርአን ቀጥሎ) ሁለተኛው ምንጭ ነው። የላቀው አሏህ እንዲህ ብሏል: {ከልብ ወለድም አይናገርም፡፡} (3) {እርሱ (ንግግሩ) የሚወርረድ ራእይ እንጅ ሌላ አይደለም፡፡} (4) [አን□ነጅም: 3 □ 4]

ይህ የነቢያዊ የሓዲሦች ኢንሳይክሎፒዲያ ጥንቅር ጥቅል መልዕክት ያላቸው ለሙስሊሙ በዲኑም በዱኒያውም ጉዳይ የሚያስፈልገውን የሓዲሦች ክምችት አጠር ካለ ማብራርያ፣ ሀሳብና እንዲሁም በውስጡ የያዛቸውን ፍሬ ሀሳቦች ከመግለፅ ጋር የተዘጋጀ ነው። መላው አለም በትምህርቱ ተጠቃሚ ይሆን ዘንድ እና የረሱላቸው ሶለሏሁ ዓለይሂ ወሰለም ሱና በየቋንቋቸው ሊደርሳቸው ዘንድ ስራው በዓለም ታላላቅ ቋንቋች በመተርጎም ላይ ያለ የሓዲሦች ጥንቅር ነው።

Am380

978-603-8474-33-4